
# የኢትዮጵያ ታሪክ

## ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ
## ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ






ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ

Niguss
Digital Library

ያለደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊያሳትም ፡ አይችልም ።

All Rights Reserved

የመዠመሪያው ፡ እትም ፡ 109100፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ።

ተሻሽሎ ፡ የታተመ ፡ (4ኛ ፡ እትም) ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ጥንታዊውንና ፡ አዲሱን ፡ ጠላት ፡ አባረው ፡ በድል ፡ አድራጊነት
ግርማ ፡ ከዋናው ፡ መናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ለገቡበት ፡ የተሰጠ ፡
መታሰቢያ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ቀ ፡ ኃ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

## ማውጫ

**መቅድም** 9
***የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።*** ***15***
**ምዕራፍ ፡ 1 ።** **16**
**ምዕራፍ ፡ 2 ።** **18**
ጠላትን ፡ በመናቅ ፡ የሚመጣ ፡ የመሸነፍ ፡ ፍዳ ። 18
**ምዕራፍ ፡ 3 ።** **20**
ደጃች ፡ ካሳ ፡ ደጃች ፡ ጕሹን ፡ ጕር ፡ አምባ ፡ ላይ ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ አይሻል ፡ ላይ ፡ ድል ፡ እንዳደረጓቸውና ፡ ብሩ ፡ ጕሹን ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ገደሉት ። 20
**ምዕራፍ ፡ 4።** **23**
ስለ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ -ደጃች ፡ ካሳ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ለማድረግ እንዳሰቡ ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ እንደ ፡ ደፉ ። 23
**ምዕራፍ 5** **26**
ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከወሎና ፡ ከሸዋ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ። 26
**ምዕራፍ ፡ 6።** **29**
ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የቤተ ፡ መንግሥትንና ፡ የቤተ ፡ ክህነትን ፡ ሕግ ፡ እንዳቆሙ ፡ ሸዋ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ እንደሸፈተባቸው ፡ -- የእቴጌ ፡ ተዋበች ዕረፍት። 29
**ምዕራፍ ፡ 7 ።** **33**
የልጅ ፡ ጋረድ ፡ የብሩ ፡ ጎይሉና ፡ የደጃች ፡ ተድላ ፡ ጓሉ ፡ ዕረፍት ፡ - ያቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣት ። 33
**ምዕራፍ ፡ 8።** **35**
የካፒቴን ፡ ፕሎውዴን ፡ ሞት ፡ -- የካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ መምጣት ፡ -- ደጃዝማች ፡ ንጉሤና ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ---ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወይዘሮ ጥሩ ፡ ወርቅን ፡ እንዳገቡ ። 35
**ምዕራፍ ፡ 9።** **37**
የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ የማስፋፋት ፡ አሳባቸው ፡ --ወደ ፡ ንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ የላኩት ፡ ደብዳቤ ። 37
**ምዕራፍ ፡ 10።** **40**
የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ብስጭት ፡ --የካፒቴን ፡ እስራትና ፡ ራሳም ፡ ተልኮ ፡ እንደ ፡ መጣ ። 40
**ምዕራፍ ፡ 11** **44**
ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ በግፍ ፡ እንዳፈሰሱ ። 44
**ምዕራፍ ፡ 12።** **45**
ዐፄ ፡ ቴዎድርስ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ እንደ ፡ ተጓዙ ፡ --እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ አባታቸውን ፡ እንደ ፡ ተረዱ። 45
**ምዕራፍ ፡ 13።** **46**
የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መምጣት ። 46
**ምዕራፍ ፡ 14።** **52**

የእሮጌ ፡ ጦርነት ፡ --የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዕረፍት ፡፡ 52
ዐፄ ፡ ዎድሮስ ፡ የተቀበሩበት ፡ መቅደላ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን 60
**ምዕራፍ ፡ 15 61**
የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መመለስ ፡፡ 61
***የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡፡ 70***
**ምዕራፍ ፡ 16 ፡፡ 71**
ስለ ፡ ጣሰው ፡ ጐበዜ ፡ ሞት ፡ -ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጐበዜ ፡ እንደ ፡ ነገሡ ፡ - ስለ ራስ ፡ አዳልና ፡ ስለ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡፡ 71
**ምዕራፍ ፡ 17 ፡፡ 73**
ባፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስና ፡ በደጃች ፡ ካሣ ፡ ጦርነት ፡ ዋዜማ ፡ ሁለቱ ፡ ለፈረንሳዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለናፖሊዎን ፡ 3ኛ ፡ የጻፉዋቸው ፡ ደብዳቤዎች ፡፡ 73
**ምዕራፍ ፡ 18 ፡፡ 78**
ያፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስና ፡ የደጃዝማች ፡ ካሣ ፡ ጦርነት ፡ 78
***የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት፡፡ 82***
**ምዕራፍ ፡ 19 ፡፡ 83**
ደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ ዮሐንስ ፡ ተብለው ፡ እንደ ፡ ነገሡ ፡ -- ስለ ፡ ራስ ፡ አዳልና ፡ ስለ ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡፡ 83
**ምዕራፍ ፡ 20 ፡፡ 85**
የግብጽ ፡ መንግሥት ፡ አገር ፡ ለመያዝ ፡ እንዳሰበ ፡ --የወርነር ፡ ሙንዚንገር ፡ ሞት ፡ -- መዠመሪያ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከግብጾች ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ፡፡ 85
**ምዕራፍ ፡ 21 ፡፡ 88**
ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በግብጾች ፡ ላይ ፡ ሁለተኛ ፡ ያገኙት ፡ ድል ፡፡ 88
**ምዕራፍ ፡ 22 ፡፡ 90**
የንጉሥ ፡ ምኒልክና ፡ የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጦርነት ፡ - ንጉሥ ፡ ምኒልክና ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በሩ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተገናኙ ፡---የራስ ፡ አርኣያና ፡ የወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ጋብቻ ፡፡ 90
**ምዕራፍ ፡ 23 ፡፡ 92**
ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ግዛታቸውን ፡ እንዳሰፉ ፡፡ 92
**ምዕራፍ ፡ 24 ፡፡ 96**
የአውሮፓ ፡ መንግሥታትና ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዐሰብ ፡ በር፡፡ 96
**ምዕራፍ 25 ፡፡ 99**
የዓፄ ፡ ዮሐንስና ፡ የኢጣልያኖች ፡ ግንኙነት --- የኢጣልያ ፡ ጦር ፡ ምጥዋ ፡ እንደገባ - የሰሐጢና ፡ የዶጋዓሊ ፡ ጦርነት ፡-- የሐረርጌ ፡ መያዝ ፡፡ 99
**ምዕራፍ ፡ 26 ፡፡ 106**
ስለ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡፡ 106
**ምዕራፍ ፡ 27 ፡፡ 108**

ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ እንዳሰቡና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሚሲዮናውያንን ፡ እንዳስወጡ ። 108

**ምዕራፍ ፡ 28 ። 110**

የግብፆች ፡ ውድቀት ፡ -- የደርቡሽ ፡ ወረራ ፡-- የሔዊት ፡ ውል ፡-- የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ የድርቡሾች ፡ ጦርነት ፡ 110

**ምዕራፍ ፡ 29 ። 114**

የመተማ ፡ ጦርነትና ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዕረፍት ። 114

***የዳግማዊ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ። 121***

**ምዕራፍ ፡ 30 ። 122**

ስለ ፡ አቶ ፡ በዛብህ ፡ --ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክና ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ጋራ ፡ ስላላቸው ፡ ግንኙነት ። 122

**ምዕራፍ ፡ 31 ። 130**

ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ ተጉዘው ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ እንዳደረጉ ፡ -ቡሩ ፡ ሜዳ ፡ ውጫሌ ፡ ላይ ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተዋዋሉ ፡ ከቦሩ ፡ ሜዳ ፡ ተመልሰው ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ እንደ ፡ ደፉ። 130

**ምዕራፍ ፡ 32 ። 139**

የኰዓቲት ፡ የአምባ ፡ አላጌ ፡ የመቀሌ ፡ ጦርነት ። 139

**ምዕራፍ ፡ 33 ። 150**

የዐድዋ ፡ ጦርነት ። 150

**ምዕራፍ ፡ 34 162**

ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ መረብን ፡ አልፈው ፡ አሥመራን ፡ ያሊያዙበት ፡ ምክንያት ፡ የሮማው ፡ ጳጳስ ፡ ስለ ፡ ኢጣሊያ ፡ ምርኮኞች ፡ የጻፉት ፡ ደብዳቤ ፡ ስለ ፡ ዕርቅና ፡ ስለ ፡ ወሰን ፡ ክለላ ፡ የተደረገ ፡ ውል ። ስለ ፡ ምርኮኞች ፡ መለቀቅ ። 162

**ምዕራፍ ፡ 35 ። 167**

የዓድዋ ፡ ድልና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ 167

**ምዕራፍ ፡ 36 ። 169**

ሱማልያና ፡ ሱማሌዎች ። 169

**ምዕራፍ ፡ 37 ። 173**

የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ኃይል ፡ መሰብሰብና ፡ ግዛት ፡ ማስፋት ። 173

**ምዕራፍ ፡ 38 ። 174**

ስለ ፡ ወይዘሮ ፡ ባፈና ፥ ስለ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፥ ስለ ፡ ራስ ፡ ዳርጌ ፥ ስለ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፥ ስለ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፥ ስለ ፡ ራስ ፡ በዛብኽ ፥ ስለ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፥ - ስለ ፡ ራስ ፡ ወሌ ። 174

ስለ ፡ ወይዘሮ ፡ ባፈና ። 174

ስለ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ። 174

ስለ ፡ ራስ ፡ ዳርጌ ። 178

ስለ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ዮሐንስ ። 180

ስለ ፡ ራስ ፡ መኰንን ። 182

ስለ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ። 186

ስለ ፡ ራስ ፡ በዛብኸ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ። 186

ስለ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ። 186

ስለ ፡ ራስ ፡ ወሌ ። 188

**ምዕራፍ ፡ 39 ። 190**

የጅቡቲ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሐዲድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥልጣኔ ፡ ምልክት ። 190

**ምዕራፍ ፡ 40 192**

የሦስቱ ፡ መንግሥታት ፡ ስምምነት ። 192

**ምዕራፍ ፡ 41 ። 194**

የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታመም ፡ - የእቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ሥልጣን ፡ -የደጃች ፡ አብርሀ ፡ አርአያ ፡ መሸፈት ። 194

**ምዕራፍ ፡ 42 ። 196**

የአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ኣልጋ ፡ ወራሽነት ፡ የራስ ፡ ተሰማ ፡ ዕረፍት ፡ በመኳንንቱ ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ ክርክር ፡ የራስ ፡ አባተ ፡ መያዝ ፡ የአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ወደ ፡ ጊሚራ ፡ መሄድና ፡ መመለስ ፡ የፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ግጭት ፡ - የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዕረፍት ፡ የራስ ፡ ሚካኤል ፡ ንጉሥ ፡ መባል ፡ የራስ ፡ ስብሐትና ፡ የደጃች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ መዋጋት ። 196

***የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ። 206***

**ምዕራፍ ፡ 43 ። 207**

የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ መንግሥትና ፡ ኣካሄዳቸው ፡ -የጀርመን ፡ ፖለቲካ ። 207

***የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት 211***

**ምዕራፍ ፡ 44 ። 212**

የወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ መሆን ፡ - ደጃዝማች ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ራስ ፡ ተብለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ። 212

**ምዕራፍ ፡ 45 ። 214**

የልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ መኰንን ፡ አጭር ፡ ታሪክ ። 214

**ምዕራፍ ፡ 46 ። 216**

የቶራ ፡ መስክና ፡ የሰገሌ ፡ ጦርነት ፡ የንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ መማረክ ፡ የንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ የራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ንጉሥ ፡ መባል ። 216

**ምዕራፍ ፡ 47 ። 218**

አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ በወሎ ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ ሰብስበው ፡ ስለ ፡ መዋጋታቸውና ፡ ድል ፡ ሆነው ስለ ፡ መሸሻቸው ፥ በኋላም ፡ ግብጽያ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መያዛቸው ። 218

**ምዕራፍ ፡ 48 ። 219**

የኢትዮጵያ ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ መግባት ። 219

**ምዕራፍ ፡ 49 ። 221**

የልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ የኤውሮፓን ፡ መንግሥታት ፡ ከተሞች ፡ መጐብኘት 221

**ምዕራፍ ፡ 50 ። 223**

ስለ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘውድ ፡ መመለስ ። 223

**ምዕራፍ ፡ 51 ። 227**

ልዑል ፡ ኣልጋ ፡ ወራሽ ፡ አገራቸውን ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ስለ ፡ መምራታቸውና ፡ ስለ ፡ ገጠማቸው ፡ ዕንቅፋት ። ____ 227

**ምዕራፍ ፡ 52 ።** ____ **235**

የራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወሌ ፡ መሸፈትና ፡ በጦርነት ፡ መሞት ። ____ 235

***የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ።*** ____ ***239***

**ምዕራፍ ፡ 53 ።** ____ **240**

የንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዕረፍት--- የግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ተፈሪ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ መድፋት ። ____ 240

**ምዕራፍ ፡ 54 ።** ____ **248**

ስለ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መቆም ፥ በምክር ፡ ቤቱ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተናገሩት ፡ ዲስኩር ። 248

**ምዕራፍ ፡ 55 ።** ____ **252**

አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ከፍቼ ፡ ኣምልጠው ፡ እንደ ፡ ተያዙ ፡ - የራስ ፡ ኀይሉ ፡ መታሰር ። ____ 252

**ምዕራፍ ፡ 56 ።** ____ **256**

ኢትዮጵያና ፡ 3ቱ ፡ የኤውሮፓ ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ። ____ 256

**ምዕራፍ ፡ 57 ።** ____ **259**

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ኣጭር ፡ ታሪክና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ጠላትነት ። ____ 259

**ምዕራፍ ፡ 58 ።** ____ **262**

የጐንደር ፡ ቆንስል ፡በዘበኞች ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ ጠብ ። ____ 262

**ምዕራፍ ፡ 59 ።** ____ **266**

የወልወል ፡ ግጭት — ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወደ ፡ ዤኔብ ፡ ያስተላለፉት ፡ ቃል ። ____ 266

**ምዕራፍ ፡ 60 ።** ____ **269**

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የተናገሩት ፡ ዲስኩር ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ያቀረበው ፡ የዕርቅ ፡ አሳብ ። ____ 269

**ምዕራፍ ፡ 61 ።** ____ **274**

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ ቤኒቶ ፡ ሙሶሊኒ ፡ ጦርነቱን ፡ እንዳስታወቀ ፡ ጳጳሱም ፡ ካሳቡ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተባበሩለትና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ጋዜጣ ፡ ጸሓፊዎች ፡ እንደ ፡ ተወቀሱ ። ____ 274

**ምዕራፍ ፡ 62 ።** ____ **279**

የመዠመሪያው ፡ ጦርነት ፡ የዐድዋ ፡ መያዝ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ስለ ፡ መከላከል ፡ የተናገሩት ፡ ዲስኩር ። ____ 279

**ምዕራፍ ፡ 63 ።** ____ **287**

የጦር ፡ ወታደር ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ እንደ ፡ ተሰበሰበ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ለመኳንንቱና ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ የሰጡት ፡ ምክር ። ____ 287

**ምዕራፍ ፡ 64 ።** ____ **297**

**ምዕራፍ ፡ 65 ።** ____ **301**

የደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ክዳት ። ____ 301

**ምዕራፍ ፡ 66 ።** ____ **306**

የውጋዴን ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ የቆራሔ ፡ ጦርነት ፡ የደጃዝማች ፡ አፈወርቅ ፡ ሞት ። ____ 306

**ምዕራፍ ፡ 67 ። 310**
ስለ ፡ መቀሌ ፡ መያዝ ፥ ስለ ፡ ጄኔራል ፡ ደቦኖ ፡ መለወጥ ። 310
**ምዕራፍ ፡ 68 ። 311**
የማሬሻል ፡ ባዶሊዮ ፡ መምጣትና ፡ የደምበጉና ፡ ጦርነት ። 311
**ምዕራፍ ፡ 69 ። 313**
የመዠመሪያው ፡ የተንቤን ፡ ጦርነትና ፡ የአምባ ፡ አራዳም ፡ ጦርነት ። 313
**ምዕራፍ ፡ 70 ። 316**
2ኛው ፡ የተንቤን ፡ ጦርነትና ፡ የሺሬ ፡ ጦርነት ። 316
**ምዕራፍ ፡ 71 ። 319**
ከቡር ፡ ራስ ፡ ደስታና ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ መርድ ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ያደረጉት ፡ ጦርነት ። 319
**ምዕራፍ ፡ 72 ። 325**
የውጋዴን ፡ ጦርነት ። 325
**ምዕራፍ ፡ 73 ። 327**
የማይጨው ፡ ጦርነት ። 327
**ምዕራፍ ፡ 74 ። 336**
የኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መፈታት ። 336
**ምዕራፍ ፡ 75 ። 339**
የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ መሄድ ፡ በዤኔብ ፡ ጉባኤ ፡ የተናገሩት ፡ ዲስኩር ። 339
**ምዕራፍ ፡ 76 ። 348**
የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ያ5 ፡ ዓመት ፡ አገዛዝ ፡ የግራዚያኒ ፡ አደጋ ፡ ደናኔና ፡ ጀናሌ ። 348
**ምዕራፍ ፡ 77 ። 355**
የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የኀይል ፡ ፖለቲኩን ፡ ለመለወጥ ፡ እንደ ፡ ተገደደ ። 355
**ምዕራፍ ፡ 78 ። 366**
የአክሲስ ፡ መንግሥቶች ፥ የኢጣሊያ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ መግባት ። 366
**ምዕራፍ ፡ 79 ። 372**
የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ መመለስና ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ መግባት ። 372
**ምዕራፍ ፡ 80 ። 379**
የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መግባት ። 379
**ስለደራሲው በጥቂቱ 389**

# መቅድም

ታሪክ ፡ በመላው ፡ ዓለምና ፡ ባ1 ፡ መንግሥት ፡ እንደዚሁም ፡ ባ1 ፡ ሰው ፡ ሕይወት ፡ ውስጥ ፡ የሆነውን ፡ ጠቅላላ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሰንሰለት ፡ አያይዞ ፡ መጪውን ፡ እስካላየንበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ እንድናውቅ ፡ ከማድረጉ ፡ በላይ ፡ ታሪክ ፡ ማንበቡ ፡ ብቻ ፡ አእምሯችንንና ፡ አስተያየታችንን ፡ ያሰፋልናል ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ባልነበረበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያኽል ፡ ሆኖ ፡ ከኋላው ፡ ከረዥም ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘመኑ ፡ ድረስ ፡ በተደረገው ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ በንባብ ፡ ሲመላለስ ፡ አእምሮው ፡ ይበስልና ፡ ለያንዳንዱ ፡ ላነበበው ፡ ወገን ፡ ባለቤት ፡ ይሆናል ። በታሪክ ፡ ካነበበው ፡ ውስጥ ፡ አሳቡ ፡ የተነካበትን ፡ ላልሰሙ ፡ በተረከ ፡ ጊዜ ፡ ባዳማጮቹ ፡ ዘንድ ፡ ግምት ፡ ያገኛል።

ገዥም ፡ ተገዥም ፡ ወጊም ፡ ተከላካይም ፡ ማናቸውም ፡ ባለተግባር ፡ በየግል ንብረቱ ፡ ከታሪክ ፡ ይጠቀማል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ተጠቅልሎ ፡ ባይጻፍ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ በዕድሜው ፡ ያላየው ፡ ነገር ፡ አይገኝምና ፡ ከተጻፈው ፡ ላይ ፡ ሁሉም ፡ የየራሱን ፡ ጒዳይና ፡ ስሜት ፡ በሚነካው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ ባነበበ ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቱ ፡ በደስታ ፡ ይረካል ።

የታላላቅ ፡ ጦርነቶች ፡ የታናናሽ ፡ ግጭቶች ፡ መነሻቸውና ፡ ፍጻሜያቸው ፡ ያንዱ ፡ ሰው ፡ አነሣሥና ፡ አወዳደቁ ፡ በመካከሉ ፡ ከተደረገው ፡ ትግል ፡ ጋራ ፡ ከታሪክ ፡ ይገኛል ። ስለዚህ ፡ ያለፈን ፡ ታሪክ ፡ አጥርቶ ፡ ማወቅ ፡ በመጪው ፡ ጊዜ ፡ ለመጠንቀቅና ፡ ለማመዛዘን ፡ ይጠቅማል ። ብልህ ፡ ሰው ፡ ብዙውን ፡ ነገር ፡ በዕድሜው ፡ ከሚገጥመው ፡ ላይ ፡ ይማራል ። ከዚህም ፡ አልፎ ፡ ከታሪክ ላይ ፡ ያለፈውን ፡ ከተገነዘበ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚገጥመው ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ እንግዳና ፡ አሳሳች ሊሆንበት ፡ አይችልም ።

የጦርነትን ፡ ታሪክ ፡ የሚያነብ ፡ ሰው ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ እንዳረጀ ፡ የጦር ፡ ሰው ፡ የጦርነትን ፡ ባህል ፡ ባሳቡ ፡ ያውቃል ። ባሳቡ ፡ ያወቀውንም ፡ በሥራበት ፡ ጊዜ ፡ እጦርነት ፡ ላይ ፡ ባልዋለ ፡ ወይም ፡ የጦርነትን ፡ ዜና ፡ ባላነበበ ፡ ላይ ፡ ሲሊጫወት ፡ ይችላል።

ከዚህ ፡ በቀር ፡ ካለፉት ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራ ፡ ከሠሩት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ በታሪክ ፡ አማካይነት ፡ እየተዋወቅን ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ዛሬ ፡ አብረውን ፡ እንዳሉ ፡ ያኽል ፡ የምንወዳቸውም ፡ የምንጠላቸውም ፡ አሉ። የምንወዳቸውንም ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ዝናቸውን ፡ በታሪክ ፡ ባነበብን ፡ ጊዜ ፡ መንፈሳችን ፡ ይቀሰቀሳል ፡ እንደ ፡ እነርሱም ፡ እንሆን ፡ ይሆናል ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ ስናደርግ ፡ ዛሬ ፡ ባለንበት ፡ ዝቅተኛ ፡ ሥፍራ ፡ አናፍርም ።

ደግሞ ፡ የባዕድን ፡ ታሪክ ፡ ከመመርመርና ፡ ከመጻፍ ፡ የራስንና ፡ የወገንን ፡ ታሪክ ፡ ማወቅና ፡ መጻፍ ፡ የተገባና ፡ የቀረበ ፡ ነው። እኛም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ልናውቅ ፡ ከምንፈልጋቸው ፡ ታሪኮች ፡ ውስጥ ቅድሚያ ፡ መስጠት ፡ የሚገባን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ነው።

ቢሆንም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ከመሠረቱ ፡ ምሮ ፡ ለመመርመርና ፡ ለማወቅ ፡ ለመጻፍም ፡ የሚያስብ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተዘረዘሩትን ፡ በግድ ፡ ሊፈጽም ፡ ይገባዋል።

***ሀ)*** ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ከኢትዮጵያና ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ደራሲዎች ፡ የተጻፉትን ፡ መጻሕፍት ፡ በሙሉ ፡ በቤቱ ፡ ማኖርና ፡ ቋንቋቸውንም ፡ ማወቅ።

***ለ)*** በግእዝና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፉትን ፡ እያለተያዩ ፡ ልዩነታቸውንና ፡ የሚሩለሱበትን ፡ ማወቅ።

***ሐ)*** ያነበበውን ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝር ፡ ወይም ፡ አርእስት ፡ አርእስቱን ፡ ባሳብ ፡ መያዝ።

***መ)*** ታሪክ የተደረገበትን ፡ ሥፍራ ፡ እየዞሩ ፡ ባይን ፡ ማየት ።

***ሠ)*** ለጽሕፈት ፡ አእምሮን ፡ የተደራጀ ፡ አድርጎ ፡ መገኘት።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተዘረዘሩት ፡ መሠረት ፡ ጸ ፡ ሰው ፡ ጽሑፍን ፡ ብቻ ፡ ተከትሎ ፡ ታሪክ ፡ ያዘጋጀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነገሩ ፡ ከራሱ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ (የራሱ ፡ አርት) ፡ ያኸል ፡ ይቈጠራል ። የጨለመውን ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ለማምጣት ፡ የሚጣሉትን ፡ ለማስታረቅ ፡ በማይስማሙትም ፡ ታሪኮች ፡ ላይ ፡ ለመፍረድ ፡ ይችላል ። አጸጻፉም ፡ የራሱን ፡ ጠባይ ፡ ስለሚይዝ ፡ ሰጠያቂውም ፡ ማስረጃ ፡ መስጠት ፡ አያቅተውም።

በዚህም ፡ ላይ ፡ ጸሓፊው ፡ የከበረ ፡ ሀብታም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ታሪኩን ፡ ሰመሰብሰብ ፡ ድካሙ ፡ ይቀልለታል ። ይኸውም ፡ ለታሪኩ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መጻሕፍትና ፡ መሣሪያ ፡ እንደ ‹ ልብ ፡ በማግኘት ፡ ዐዋቂዎችን ፡ እቤቱ ፡ ድረስ ፡ እየጠራ ፡ በመጠየቅ ፡ ጽፎም ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ለታሪኩ ፡ የሚስማማ ፡ ነገር ፡ ትዝ ፡ ባለው ፡ ቊጥር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እየደጋገመ ፡ በማስገልበጥ ፡ ይልቊንም ፡ በማሳተም ፡ ጊዜ ፡ ባለው ፡ ሁናቴ ፡ ችግር ፡ አያገኘውም ። በዚህም ፡ ጠገን ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ ሲሆን ፡ የጽሕፈት ፡ አሳቡ ፡ አይቀጭጭም።

እኔም ፡ መንግሥታችን ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ ታሪክ ፡ ለመጻና፡ ፡ ይረዳኛል ፡ ብዬ ፡ ሳላስብ ፡ ለማንበብና ፡ ለማወቅ ፡ ብቻ ፡ እንዲጠቅመኝ ፡ ስል ፡ በወር ፡ ከማገኘው ፡ ቀለቤ ፡ ላይ ፡ እያነሣሁ ፡ በተለይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክና ፡ ጒዳይ የሚነኩ ፡ ኢያሌ ፡ መጻሕፍት ፡ እየገዛሁ ፡ ለራሴ ፡ በቤቲ ፡ ውስጥ ትንሽ ፡ በብልዮቴክ ፡ አቆምሁ ። ከነዚህም ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ይበልጦቹን ፡ በየተራ ፡ አንብቤ ፡ ጨረስሁ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያንባቢነት ፡ አሳበ. ፡ ወደ ፡ ጸሓፊነት ፡ ተለወጠና ፡ ለድርሰቱ ፡ የሚረዱኝን ፡ አርእስቶች ፡ ባንድ ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ አስቀድሜ ፡ አዘጋጀሁ ። ዳሩ ግን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ለመጻፍ ፡ አስፈላጊዎች ፡ አድርጌ ፡ ከ(ሀ) ፡ እስከ ፡ (ሠ) ፡ የዘረዘርኋቸውን ፡ በሙሉ ፡ ስላልፈጸምሁ ፡ ካነበብሁት ፡ ጊዜ ፡ ያለውን ፡ መጻፍ ፡ ትቼ ፡ ከለዘበልኝና ፡ አሳቤ ፡ ከደረሰበት ፡ ጊዜ ያለውን ፡ በመጻፍ ፡ ተወሰንሁ።

ይኸውም ፡ « ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ከሺ 845እስከ ፡ ሺ933 ፡ ዓ.ም » ያለውን ፡ ነው። እኔም ፡ ይህን ፡ ለመጻፍ ፡ የደፈርሁት ፡ በራሴ ፡ ችሎታና ፡ ዐቅም ፡ ሳይሆን ፡

**ሀ)** በሀገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የታሪክ ፡ ጽሑፍ ፡ ያነሰ ፡ በመሆኑ ፡

**ለ)** ለኢትዮጵያ ፡ ባዕድ ፡ የሆኑት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በየራሳቸው ፡ ቋንቋ ፡ እንዳሳባቸው ፡ የጻፉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክና ፡ ጉዳይ ፡ በብዙ ፡ የሚቆጠር ፡ ስለ ፡ ሆነና ፡ ርሱንም ፡ አብዛኛው ፡ የሀገራችን ፡ ሕዝብ ፡ ሊያነበው ፡ ባልመቻሉ ፡ ነው። ፡

ጽሕፈቱንም ፡ ከመዠመሬ ፡ በፊት ፡ በማውቃቸው ፡ ቋንቋዎች ፡ በፈረንሳዊና ፡ በኢጣሊያ ፡ ቋንቋ ፡ ባማርኛ ፡ የተጻፉትን ፡ መጻሕፍት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጋዜጣዎችም ፡ በመመልከት ፡ በማመሳከር ፡ ከሽማግሌዎች ፡ በመጠየቅ ፡ ቈየሁ።

ለታሪኩም ፡ ተስማሚ ፡ የሚሆኑትን ፡ የጥንት ፡ ፎቶግራፎች ፡ በመሰብሰብና ፡ በየጊዜው ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፡ የተገጠመውን ፡ ግጥም ፡ በማጠራቀም ፡ ቈየሁ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጽሕፈቱን ፡ ጅምሬ ፡ ከደንበኛው ፡ ሥራዩ ፡ ውጭ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ እየሠራሁ ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ጨረስሁና ፡ ሊታተም ፡ ወደ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ተላለፈ ፡

ሊታተም ፡ ከመተላለፉ ፡ በፊት ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ተመልክተው ፡ አንዳንድ ፡ ምክር ፡ ለሰጡኝ ፡ ለፕሮፌሰር ፡ ተኣምራት ፡ ዐማኑኤል ፡ ለብላታ ፡ መርስዓ ፡ ኀዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ ላቶ ፡ አርአያ ፡ ሥላሴ ፡ ወረታ ፡ የሚጠቅም ፡ መጽሐፍ ፡ ላዋሱኝና ፡ አንዳንድ ፡ ግጥም ፡ ለነገሩኝ ፡ ለቄስ ፡ ባድማ ፡ ያለው ፡ ላቶ ፡ ሠረቀ ፡ ብርሃን ፡ ገብረ ፡ እግዚእና ፡ ለአባ ፡ ጅሮም ፡ ገብረ ፡ ሙሴ ፡ ጥልቅ ፡ ምስጋናዬን ፡ አቀርባለሁ።

መጽሐፉን ፡ በማደራጅበት ፡ ጊዜ ፡ የጽሕፈት ፡ ልማድ ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ ስላንድ ፡ ነገር ፡ የተጻፈ ፡ የ3 ፡ የ4 ፡ ሰው ፡ ድርሰት ፡ እየመረመርሁ ፡ ሳመሳክር ፡ ከቀኑና ፡ ካመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ልዩነት ፡ በቀር ፡ አንዳንድ ፡ በፍጹም ፡ የተሳሳተ ፡ ነገር ፡ ስላጋጠመኝ ፡ እንደዚሁ ፡ ከኔም ፡ ድርሰት ፡ አንዳንድ ፡ ስሕተት ፡ ወይም ፡ ላንባቢው ፡ አሳብ ፡ ደስ ፡ የማይለው ፡ ይገኝ ፡ ይሆናል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ገሚሱ ፡ በዝንጋታ ፡ የቀረውም ፡ ባስተያየት ፡ ልዩነት ፡ ይሆናል ። በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ የድርሰትን ፡ እርምጃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ለመያዝ ፡ በሚያደርስ ፡ ወቀሣ ፡ እንዳልወቀሥ ፡ ላንባቢዎች ፡ ልመናዬን ፡ ማስቀደም ፡ ታሰበኝ።

መዠመጮሪያ ፡ ከተደረሰ ፡ መጽሐፍ ፡ በመጨረሻ ፡ የተደረሰ ፡ የተሻለ ፡ እንደሚሆን ፡ ርግጥ ፡ ነው። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ስላንድ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ስላንድ ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ ፡ ኢያሌ ፡ መጻሕፍት ፡ በየፈራረቃ ፡ ይጻፋሉ ። አንባቢዎችም ፡ ከቀኑት ፡ መጻሕፍት ፡ ይልቅ ፡ የመጨረሻውን ፡ ድርሰት ፡ ማንበብ ፡ ይመርጣሉ።

ወንጌላዊው ፡ ዮሐንስም ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የጌታችንን ፡ ታሪክ ፡ ከጸፉት ፡ ከ3ቱ ፡ ወንጌላውያን ፡ (ከማቴዎስ ፡ ከማርቆስ ፡ ከሉቃስ) በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ እነሱ ፡ አስቀድመው ፡ ሲጽፉ ፡ የዘነጉትን ፡ እየጨመረ ፡ 4ኛ ፡ ወንጌል ፡ ጻፈ ። እንዲሁም ፡ ከዚህ ፡ ካሁኑ ፡ መጽሐፍ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ መጽሐፍ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ እንደሚጽፉ የታወቀ ፡ መሆኑን ፡ የተወደዱ ፡ አንባቢዎች ፡ እንዲገነዘቡልኝ ፡ እለምናለሁ።

በሺ888 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተደረገው ፡ በዐድዋ ፡ ጦርነትና ፡ ይልቁኑም ፡ በጊዜያችን በሺ928 ‹ዓ.ም ፡ በማይጨው ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ በውጊያና ፡ ባሳብ ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ዘግይቶ ፡ የሚመጣውን ፡ ክብራቸውን ፡ በቅርብ ፡ በነበረ ፡ ጥቅም ፡ ሳይለውጡ ፡ በውጭ ፡ አርበኝነት ፡ በውስጥ ፡ አርበኝነት ፡ በስደት ፡ በመላላክ ፡ ሀገራቸውን ፡ አገልግለው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ የተለዩ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ብዞዎች ፡ መኖራቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው። ለነሱም ፡ በታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ከመወሳት ፡ በላይ ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ አልነበራቸውም ።

ነገር ፡ ግን ፡ በዝርዝር ፡ ሰጪና ፡ በነጋሪ ፡ እጦት ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ስማቸው ፡ ሳይወሳ ፡ የቀሩትን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በየበኩሉ ፡ የሚጻፈው ፡ ታሪክ ፡ እንደማይዘነጋቸው ፡ ዐውቀው ፡ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ በዚሁ ፡ እንዲጽናኑ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

# ማመልከቻ

አርእስቱ ፡ እንደሚገልጸው ፡ ታሪኩ ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሆኖ ፡ በሰፊው ፡ ወይም ፡ ባጭሩ ፡ ሳይሆን ፡ ካንድ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተደረገውን ፡ የዘመን ፡ ታሪክ ፡ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ በየጊዜው ፡ የነበረውን ፡ የፖለቲካና ፡ የጦርነት ፡ ግድያ ፡ መጠነኛና ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ -ይገልጻል።

ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ እየገቡ ፡ የተጻፉ ፡ ውሎችና ፡ ደብዳቤዎች ፡ ይገኛሉ ፡ እነዚህም ፡ ዋናዎቹን ፡ ያማርኛዎቹን ፡ ማግኘት ፡ ችግር ፡ እየሆነ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ በትክክል ፡ ተተርጕሟል።

የቀኑና ፡ የዓመተ ፡ ምሕረቱም ፡ አቈጣጠር ፡ «እ ፡ ኤ ፡ ቈጥር ፡ » ከሚለው ፡ በቀር ፡ የቀረው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያችን ፡ አቈጣጠር ፡ ነው።

በኢኮኖሚና ፡ በእጅ ፡ ጥበብ ፡ በጠቅላላውም ፡ በሰላማዊ ፡ አስተዳደር ፡ ረገድ ፡ በየጊዜው ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ያሠሩትና ፡ ሕዝቡም ፡ የሠራው ፡ ልዩ ፡ ልዩ የኑሮ ፡ ተግባር ፡ መኖሩ ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ በጽሐጥ ፡ የሆነ ፡ ዝርዝር ለማግኘት ፡ ዐቅም ፡ ስላነሰኝ ፡ አልተጻፈም ።

ተክለ ፡ ጻድቅ ፡ መኩሪያ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ የካቲት ፡ 30 ፡ ቀን ፡ 1936 ፡ ዓ.ም ፡

# የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

# ምዕራፍ ፡ 1 ።

የልጅ ካሳ ልደትና እድገት ፡-- ከወይዘሮ ተዋበች ጋራ እንደ ተጋቡ ፡ --ደጃች ፡ ወንድ ይራድንና እቴጌ መነንን ድል አድርገው እንደ ማረኳቸው ።

በኢትዮጵያ ፡ የነገሥታት ፡ ኀይል ፡ ደግሞ ፡ በስማቸው ፡ ብቻ ፡ ለመግዛት ፡ መሳፍንት ፡ በገነኑበት ፡ ዘመን ፡ ይልቍንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምዕራብና ፡ ሰሜን ፡ የቱርክና ፡ የግብፅ ፡ መንግሥት ፡ ተስፋፍቶ ፡ ራሷንም ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሚያሠጋበት ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምዕራብ ፡ በቋራ ፡ በተለይ ፡ ሻርጌ ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የነጋሢነት ፡ ዘር ፡ ባይኖረው ፡ ስሙ ፡ ከመግነን ፡ ጋራ ፡ ያሸናፊነት ፡ ዕድል ፡ ያለውን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አሥነሥቶ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የታፈረች ፡ ሆና ፡ እንድትኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ፈለገ ፡ ኃይሉ ፡ የሚባሉ ፡ የቋራ ፡ ተወላጅ ፡ ከደንቢያ ፡ ባላባት ፡ ከሚወለዱት ፡ ከእመት ፡ አትጠገብ ፡ ልጅ ፡ ካሳን ፡ (በኋላ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የተባሉትን) ፡ ባ1811 ፡ ዓ.ም ፡ ወለዱ ። ሌሎች ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊዎች ፡ አባታቸው ፡ እንጂ ፡ እናቲቱ ፡ ባላባትነት ፡ የላቸውም ፡ እንዲያውም ፡ በድኽነት ፡ ምክንያት ፡ ኮሶ ፡ ይሸጡ ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በሁለቱም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ባላባትነት ፡ ካላቸው ፡ ውስጥ ፡ መወለዳቸው ፡ ርግጥ ፡ ሆኖ ፡ እናትዮዋም ፡ በድኽነት ፡ ምክንያት ፡ ኮሶ ፡ እየሸጡ ፡ ልጅ ፡ ካሳን ፡ ማሳደጋቸው ፡ የታመነ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ እንደ ፡ ተወለዱ ፡ አባታቸው ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ከናታቸው ፡ ጋራ ፡ ተቀመጡ። በኋላ ፡ ግን ፡ ዕድሜያቸው ፡ ለትምህርት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የደንቢያና ፡ የቋራ ፡ ባላባት ፡ አጎታቸው ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ በትምህርት ፡ እንዲያድጉ ፡ ልጅ ፡ ካሳን ፡ ማኅበረ ፡ ሥላሴ ፡ ወደሚባለው ፡ ገዳም ፡ ወስደው ፡ ለመነኩሳቱ ፡ ሰጧቸው።

በዚህ ፡ ገዳም ፡ ዳዊት ፡ ጨርሰው ፡ ሌላውን ፡ ትምህርት ፡ በሚቀጥሉበት ፡ ጊዜ ፡ ዳጃች ፡ ማሩ ፡ የሚባል ፡ የመንገሥ ፡ ፍላጎት ፡ የነበረው ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የነበሩ ፡ መሳፍንት ፡ ባባቱ ፡ ያደረጉትን ፡ ቂም ፡ እገዳሙ ፡ በሚማሩት ፡ ልጆች ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ ሲል ፡ ከገዳሙ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ብዙ ፡ ሕፃናት ፡ ፈጀ። ልጅ ፡ ካሳ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ አምልጠው ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ አገር ፡ ሸሽተው ፡ ተቀመጡ። በሌላ ፡ ታሪክ ፡ ደግሞ ፡ ደጃች ፡ ማሩ ፡ አጎታቸው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እገዳሙ ፡ ውስጥ ፡ አግኝቶ ፡ እንሽፍት ፡ ብሎ ፡ ይዟቸው ፡ ሄደ ፡ የሚል ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ። ስለዚህ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በቋራ ፡ ከነበሩት ፡ ሽፍቶች ፡ ጋሪ ፡ ተደባልቀው ፡ የዘመቻ ፡ ዐቅድና ፡ የጦር ፡ መላ ፡ ተማሩ ። በብዙ ፡ ሽፍቶችም ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ አለቃ ፡ ሆነው ፡ ይታዩ ፡ ዠመር ። በኋላም ፡ ሽፍትነቱን ፡ ትተው ፡ ከደጃች ፡ ጐሹና ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ቤት ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ አስተዳደግና ፡ የወታደርነት ፡ ሥራ ፡ ሲለምዱ ፡ ኖሩ። ስናር (በሰዳን ፡ ውስጥ) ፡ በሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ከግብጾች ፡ ጦርነት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ጀብዱ ፡ ሠርተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ዝናቸው ፡ በያለበት ፡ ተሰማ።

ስለዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ዠግና ፡ በጋብቻ ፡ ገመድ ፡ አስረው ፡ ከሥልጣናቸው ፡ በታች ፡ ለማድረግ ፡ ሲሉ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ለስሙ ፡ ዘውድ ፡ ጭኖ ፡ በጐንደር ፡ ይቀመጥ ፡ የነበረው ፡ የሦስተኛ ፡ ዮሐንስ ባለቤት ፡ (- የራስ ፡ ዐሊ ፡ እናት) ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ የልጅ ፡ ልጃቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበችን ፡ ባ1840 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በሚስትነት ለልጅ ፡ ካሳ ፡ ዳሩላቸው። ጋብቻውም ፡ ለዚያ ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ድኻና ፡ ባንዲት ፡ እመቤት ፡ መካከል ፡ ለሰላም ፡ ፍለጋ ፡ የተደረገ ፡ የጋብቻ ፡ ፖለቲካ ፡ መሰለ ፡ እንጂ ፡ አቻ ፡ ለአቻ ፡ የማተያዩ ፡ ሆነው ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ አልተገመቱም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ዋናው ፡ አሳባቸው ፡ መላዋን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጠቅልለው ፡ ከሥልጣናቸው ፡ በታች ፡ ለማግባት ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ ለእቴጌዩቱና ፡ ለልጃቸው ፡ ለራስ ፡ ዐሊ ፡ ተገዥ ፡ ሆነው ፡ ለመኖር ፡ አልፈቀዱም።

ስለዚህ ፡ ለዦን ፡ የሚባል ፡ የፈረንሳዊ ፡ ቆንስል ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከግብጾች ፡ ጋራ ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ቈስለው ፡ ሳለ ፡ የማገገሚያ ፡ አንድ ፡ መሲና ፡ በመላክ ፡ ፈንታ ፡ አንድ ፡ ወርች ፡ ሥጋ ፡ ስለ ፡ ላኩላቸው ፡ ይኸውም ፡ ክብራቸውን ፡ የሚያዋርድባቸው ፡ በመሆኑ ፡ ላይ ፡ ባለቤታቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበችን ፡ ክድኻ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ከወገናችን ፡ የማይስማማውን ፡ አገባሽ ፡ እያለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሁሉ ፡ ይወቅሣቸው ፡ ነበርና ፡ ከባለቤታቸው ጋራ ፡ ተስማምተው ፡ ባንድነት ፡ ሸፈቱ። ሌሎችም ፡ ባለታሪኮች ፡ መድኀኒት ፡ በቀመሱበት ፡ ቀን ፡ ወርች ፡ ሥጋ ፡ ስለ ፡ ላኩላቸው ፡ ነው ፡ የሸፈቱት ፡ ይላሉ።

መሸፈታቸውንም ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ሰሙ ፡ ከጦር ፡ አለቆቻቸው ፡ አንዱን ፡ ደጃች ፡ ወንድይራድን ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ አሲዘው ፡ ላኳቸው ። ደጃች ፡ ወንድይራድም ፡ ያንን ፡ የኮሶ ፡ ሻጭ ፡ ልጅ ፡ ይዤ ፡ ከነሕይወቱ ፡ አመጣለሁ ፡ ብለው ፡ ሊፈጽሙት ፡ ያልቻሉትን ፡ ተስፋ ፡ ለእቴጌ ፡ መነን ፡ ሰጥተው ፡ ልጅ ፡ ካሳን ፡ ለመውጋት ፡ ሄዱ ። ልጅ ፡ ካሳም ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ የማይበልጡትን ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ጫጮ ፡ እሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ የሚመጣባቸውን ፡ ሲጠባበቁ ፡ ወዲያው ፡ የሁለቱ ፡ ወገን ፡ ጭፍራ ፡ ተገናኝቶ ፡ ሲዋጉ ፡ ደጃች ፡ ወንድይራድ ፡ በጦር ፡ ተወግተው ፡ በልጅ ፡ ካሳ ፡ እጅ ፡ ተማረኩ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለእቴጌይቱ ፡ በትምክሕት ፡ ተናግረውት ፡ የነበው ፡ ንግግር ፡ ትዝ ፡ ብሏቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እግብር ፡ ላይ ፡ ሌላው ፡ ጠጅና ፡ ጠላ ፡ በሚጋበዝበት ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ወንድይራድን ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ኮሶ ፡ እየደጋገሙ ፡ አጠጥተው ፡ ተበቀሏቸው።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የስሜኑ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ጐንደርን ፡ በጦርነት ፡ ይዘው ፡ ለመንገሥ ፡ ያስባሉ ፡ እየተባለ ፡ ይፈራ ፡ ነበርና ፡ ልጃቸውን ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ከብዙ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጋራ ፡ ወገራ ፡ ትተው ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ቍጥሩ ፡ እስከ ፡ 20 ፡ ሺሕ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጦራቸው ፡ አዝማች ፡ ሆነው ፡ ልጅ ፡ ካሳን ፡ ለመውጋት ፡ ጒዞ ፡ አደረጉ ። በጒዞ ፡ ጊዜ ፡ «ይህ ፡ ቆለኛ ፡ (ካሣ) ፡ ወዴት ፡ አባቱን ፡ ሊገባ ፡ ይሆን» ፡ ብለው ፡ ነበር ፡ ወደ ፡ ጦርነቱም ፡ ቦታ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ «አያፍርም ፡ እኮ ፡ ይህ ፡ ቆለኛ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ሊዋጋ ፡ ቆሟል» አሉ ፡ ይባላል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ጦርነቱ ፡

ደንቢያ ፡ ላይ ፡ ሲደረግ ፡ ከጦር ፡ ሠራዊት ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ እቴጌይቱ ፡ ድል ፡ ሊያደርጉ ፡ ጥቂት ፡ ሲቀራቸው ፡ በጦር ፡ ጭናቸውን ፡ ተወግተው ፡ ስለ ፡ ወደቁ ፡ ድሉ ፡ የልጅ ፡ ካሳ ፡ ሆነ። እቴጌይቱንም ፡ የልጅ ፡ ካሳ ፡ አሽከሮች ፡ አንሥተው ፡ ለጌታቸው ፡ አቀረቧቸው ። ልጅ ፡ ካሳም ፡ ይህ ፡ ቆለኛ ፡ እያሉ ፡ በተሳደቡበት ፡ ባቄላ ፡ አስፈጩአቸው ፡ ይባላል ። ራስ ፡ ዐሊ ፡ ይኸንኑ ፡ ሰምተው ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ይዘው ፡ ለመዋጋት ፡ አስበው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ ዕርቅ ፡ ማድረግ ፡ የተሻለ ፡ መንገድ ፡ መሆኑን ፡ አመዛዝነው ፡ እናታቸውን ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ደንቢያንና ፡ ቋራን ፡ ለልጅ ፡ ካሳ ፡ ለመልቀቅ ፡ የዕርቅ ፡ ድርድር ፡ አቀረቡ ። ልጅ ፡ ካሳም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚያደርጉትን ፡ ባሳባቸው ፡ እያዘጋጁ ፡ የዕርቀኑን ፡ አሳብ ፡ ለጊዜው ፡ ተቀብለው ፡ እቴጌዪቱን ፡ ለራስ ፡ ዐሊ ፡ መልሰው ፡ ላኩላቸው። ልጅ ፡ ካሳም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዝናቸው ፡ በያለበት ፡ ተሰማ ፡ ሰውም ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ይላቸው ፡ ዠመር ።

# ምዕራፍ ፡ 2 ።

## ጠላትን ፡ በመናቅ ፡ የሚመጣ ፡ የመሸነፍ ፡ ፍዳ ።

ደጃች ፡ ካሳ ፡ በመጀመሪያ ፡ አነሣሳቸው ፡ ላይ ፡ ደጃች ፡ ወንድይራድን ፡ ይልቁንም ፡ አቴጌ ፡ መነንን ፡ በውጊያ ፡ ያሸንፋሉ ፡ ወደፊትም ፡ ደጃች ፡ ጐሹን ፡ ቀጥለው ፡ ዋናውን ፡ እንደራሴ ፡ ያሸንፋሉ ፡ ከርሳቸውም ፡ ቀጥሎ ፡ ሊነግሥ ፡ የሚዘጋጁትን ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ይነግሣሉ ፡ ብሎ ፡ የጠረጠረ ፡ ያለ ፡ አይመስልም ።

እቴጌይቱንም ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ከማረኩ ፡ ወዲህ ፡ ይኸው ፡ ንቀት ፡ እንዳላቋረጠ ፡ በደጃች ፡ ጐሹ ፡ ደብዳቤና ፡ በተገጠመው ፡ ግጥም ፡ ላይ ፡ ይታያል። ደጃች ፡ ጐሹ ፡ የጐጃም ፡ መስፍን ፡ የደጃች ፡ ብሩ አባት ፡ ናቸው።

እርሳቸውም ፡ የጐጃም ፡ ገዥ ፡ በነበሩበት ፡ ሰዓት ፡ አንቷንና ፡ አርኖ ፡ ዳባዲ ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ የፈረንሳዊ ፡ ወንድማማች ፡ ነበሩ ። አንቷን ፡ ዳባዲ ፡ የቀለም ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ከጐንደር ፡ ሊቃውንትና ፡ ከነደብተራ ፡ አሰጋኸኝ ፡ ጋር ፡ ስለመጻሕፍት ፡ ስለታሪክ ፡ ስለቋንቋ ፡ በመነጋገር ፡ ጊዜውን ፡ ያሳልፍ ፡ ነበር ። ሰውም ፡ አንቷን ፡ የሚባለውን ፡ ስሙን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አጠራር ፡ እንጦንዮስ ፡ እያለ ፡ ይጠራው ፡ ነበር።

ወንድሙ ፡ ደግሞ ፡ ሚሸል ፡ አርኖ ፡ ዳባዲ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለደጃች ፡ ውቤ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለደጃች ፡ ጐሹ ፡ እንደዚሁም ፡ ለራስ ፡ አሊ ፡ ሎሌነት ፡ እያደረ ፡ የጦር ፡ መሣርያ ፡ ጠመንጃና ፡ ጥይት ፡ እያቀበለ ፡ ከብዙ ፡ መኳንንት ፡ ጋር ፡ ተዋውቆ ፡ ወዳጅና ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ ፡ ነበር ፡ የበለጠ ፡ ግን ፡ የቆየው ፡ ከደጃዝማች ፡ ጐሹ ፡ ጋር ፡ ነበር። ሙሉ ስሙ ፡ በፈረንሳዊ ፡ ሚሸል ፡

አርኖ ፡ ዳባዲ ፡ የሚባለውን ፡ መኳንንቱ ፡ ሚሚካኤል ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ይሉት ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ከደጃዝማች ፡ ካሳ ፡ ለውጊያ ፡ ከተሰለፉበት ፡ ጊዜ ፡ ትንሽ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ለዚሁ ፡ ለሚካኤል ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡ ጽፈውለታል ፡ "ዛቲ ፡ ጦማር ፡ ዘተፈነወት ፡ እምኀበ ፡ ደጃዝማች ፡ ጉሹ ፡ ትብጻሕ ፡ ኀበ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ እጅጉን ፡ እጅጉን ፡ እንዴት ፡ አለህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመገናኘት ፡ እስቲያበቃን ። ፈረሱን ፡ መልካም ፡ ፈረስ ፡ ይዤልሃለሁ ፡ አሁን ፡ መንገዱ ፡ ቢቸግር ፡ ነው ፡ የቀረ ። አሁንም ፡ የላክህብኝ ፡ የዕቃው ፡ ነገር ፡ የምወደውን ፡ ዕቃ ፡ አንተ ፡ ታውቀዋለህ ። ኩላሊት ፡ ኪዳነ ፡ ማርያም ፡ ተቀብሎ ፡ ተኔ ፡ ያድርስልኝ ። ተካሳ ፡ ጋር ፡ የተዋጋን ፡ እንደሆነ ፡ ጐንደር ፡ እገባለሁ ፡ እንገናኛለን ። ወደቆላ ፡ የሸሸ ፡ እንደሆነ ፡ ሰው ፡ ባገኝ ፡ ፈልጌ ፡ እሰድልሃለሁ ፡ ፈረሱን ። በቅሎም ፡ ቸግሮህ ፡ እንደሆነ ፡ ጨምሬ ፡ እሰድልነሃለሁ ፡ ቢሆን ፡ ቢሆን ፡ አንተም ፡ እንድትመጣ። መልካም ፡ ነገር ፡ የምትቀመጥበት ፡ አቆይሃለሁ ። እጅግ ናፍቄሃለሁ ።"

ደብዳቤው ፡ የተገኘው ፡ በፓሪስ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ በአንቷን ፡ ዳባዲ ፡ ፋይል ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የለውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ወደፊት ፡ እንደምናነበው ፡ ከደጃች ፡ ጉሹ ፡ የተዋጉት ፡ ከራስ ፡ አሊ ፡ በ1845 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከመዋጋታቸው ፡ በፊት ፡ ስለሆነ ፡ ምናልባት ፡ በደብዳቤያቸው ፡ ውስጥ ፡ "የዕቃው ፡ ነገር ፡ የምወደውን ፡ ዕቃ ፡ ታውቀዋለህ" ፡ የሚሉት ፡ ጠበንጃና ፡ ጥይት ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ይኸም ፡ ከደጃች ፡ ካሣ ፡ ጋር ፡ ለመዋጊያ ፡ እንዲያገለግል ፡ ነው ። ፈረንሳዩ ፡ ደጃች ፡ ጉሹንም ፡ ደጃች ፡ ውቤንም ፡ ራስ ፡ አሊንም ፡ ጌቶቼ ፡ እያለ ፡ ግብር ፡ እየበላ ፡ ጭፍራውን ፡ አበጅቶ ፡ እነዚህኑ ፡ በፈራረቃ ፡ እያጀበ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መኰንን ፡ ተስማምቶ ፡ ተመሳስሎ ፡ የሚኖር ፡ ነበር ። በተረፈ ፡ ከካሳ ፡ ጋር ፡ የተዋጋን ፡ እንደሆነ ፡ ጐንደር ፡ እገባለሁና ፡ እንገናኛለን ፡ ወደቆላ ፡ የሸሸ ፡ እንደሆነ ፡ ሰው ፡ ባገኝ ፡ ፈልጌ ፡ እልክልሃለሁ" ፡ ሲሉ ፡ በእርግጥ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ፈርተው ፡ የሚሸሹ ፡ አለዚያም ፡ ቢዋጉ ፡ የሚሸነፉ ፡ መሆኑን ፡ አምነውበት ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። የሁሉም ፡ መሳፍንት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በደጃች ፡ ካሳ ፡ ላይ ያላቸው ፡ የንቀት ፡ ግምት ፡ እንደዚሁ ፡ ተመሳሳይ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ነገር ግን ፡ የናቁት ፡ ሁሉ ፡ እየተሸነፉ ፡ ተዋረዱ ። ጠላትን ፡ መናቅ ፡ ሞኝነት ፡ መሆኑ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ በደንብ ፡ ይታያል። እቴጌ ፡ መነን ፡ የራስ ፡ ዐሊ እናት ፡ ካሣን ፡ ሊወጉ ፡ ሲጓዙ ፡ «ይህ ፡ ቆለኛ ፡ ወዴት ፡ ሲገባ ፡ ይሆን» ፡ ያሉትን ፡ የንቀት ፡ አነጋገርና ፡ በኋላ ፡ መሸነፋቸውን ፡ ስናነበው ፡ ጠላትን ፡ መናቅ ፡ ራስን ፡ አዋርዶ ፡ ጠላትን ፡ ማክበር ፡ መሆኑን ፡ በደንብ ፡ እንመለከታለን ።

# ምዕራፍ ፡ 3 ።

## ደጃች ፡ ካሳ ፡ ደጃች ፡ ጕሹን ፡ ጕር ፡ አምባ ፡ ላይ ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ አይሻል ፡ ላይ ፡ ድል ፡ እንዳደረጓቸውና ፡ ብሩ ፡ ጕሹን ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ገደሉት ።

በራስ ፡ ዐሊና ፡ በደጃች ፡ ካሳ ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ዕርቅ ፡ ቢደረግ ፡ ነገሩ ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ለመፈለግ ፡ እንጂ ፡ ከልብ ፡ ሁኖ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚቈይ ፡ ሰላም ፡ ለማድረግ ፡ አልነበረም ። ስለዚህ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ እናታቸውን ፡ ካገኙ ፡ በኋላ ፡ ከጐጃሙ ፡ ገዥ ፡ ከደጃች ፡ ጕሹ ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ደንቢያ ፡ መጡ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ አንዳንዱን ፡ በየተራ ፡ እንጂ ፡ እነዚህን ፡ ኀይል ፡ የሚሰማቸውን ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ ገዥዎች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመግጠም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የነበራቸው ፡ ኃይል ፡ ስለማይፈቅድላቸው ፡ ደንቢያን ፡ ለቀው ፡ መውጫ ፡ መግቢያውን ፡ ወደሚያውቁትና ፡ ተወልደው ፡ ወዳደጉበት ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ሄዱ ። ራስ ፡ ዐሊም ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ በጭራሽ ፡ የሸሸመስሏቸው ፡ የደንቢያን ፡ ግዛት ፡ ለደጃች ፡ ጕሹ ፡ ሰጥተው ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ተመለሱ ። ደጃች ፡ ጕሹም ፡ በጐጃም ፡ ግዛታቸው ፡ ላይ ፡ ደንቢያ ፡ ስለ ፡ ተጨመረላቸው ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ከልጃቸው ፡ ከብሩ ፡ ጕሹ ፡ ጋራ ፡ ጦራቸውን ፡ እያደራጁ ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ የራስ ፡ ዐሊን ፡ መራቅና ፡ የደጃች ፡ ጕሽን ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከቋራ ፡ ተነሥተው ፡ ደጃች ፡ ጕሹን ፡ ለመውጋት ፡ በፍጥነት ፡ ወደ ፡ ጕር ፡ አምባ ፡ ጥግ ፡ ገሠገሡ ። ደጃች ፡ ጕሹ ፡ ዝግንነት ፡ ከኀይል ፡ ጋራ ፡ ከሚሰማቸው ፡ በቀር ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸው ፡ አያሌ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከግጥሚያው ፡ በፊት ፡ አዝማሪያቸው ፡ በሠራዊቱ ፡ መካከል ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ይዘምር ፡ ነበር ።

> አያችሁት ፡ ብያ ፡ የኛን ፡ እብድ ፡
> 5 ፡ ጋሞች ፡ ይዞ ፡ ቸር ፡ አምባ ፡ ሲወርድ ።
> ያንዻብባል ፡ እንጂ ፡ መች ፡ ይዋጋል ፡ ካሳ ፡
> ወርደኸ ፡ ጥመድበት ፡ በሸንብራው ፡ ማሳ ።
> ወዶ ፡ ወዶ ፡ በሴቶቹ ፡ በነጕንጭት ፡ ለምዶ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጦርነቱ ፡ እዚሁ ፡ ጕር ፡ አምባ ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሲዋጉ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ጕሹ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ የደጃች ፡ ካሳ ፡ ጦርም ፡ ተፈቶ ፡ መሸሽም ፡ ዠምሮ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ከጥቂቶች ፡ ደፋሮች ፡ ወታደሮቻቸው ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ በጥብቅ ፡ ሲዋጉ ፡ ደጃች ፡ ጕሹ ፡ በፈረስ ፡ ፊት ፡ ቀድመው ፡ በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡

በጥይት ፡ ተመተው ፡ ወደቁ ። ሠራዊታቸውም ፡ ገሚሱ ፡ ተበተነ ፡ ገሚሱም ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ዞረ።

ደጃች ፡ ጉሹ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በጦርነት ፡ ተጋጥመው ፡ ቢሞቱ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በደጃች ፡ ጉሹ ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ስለ ፡ ደጃች ፡ ጉሹ ፡ ሞት ፡ ደስ ፡ ሳይላቸው ፡ ሥርዐተ ፡ መቃብራቸውን ፡ በክብር ፡ አስፈጸሙላቸው ። አስቀድሞም ፡ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ እባክዎ ፡ እኔና ፡ እርስዎ ፡ ኣባትና ፡ ልጅ ፡ ነንና ፡ መዋጋት ፡ አይገባንም ፡ ደንቢያን ፡ ለቀው ፡ ይሂዱልኝ ፡ ብለው ፡ ለምነዋቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኣልቃሽ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ገጠመች ።

ጉሹ ፡ እንደ ፡ ኦርዮ ፡ ዐሊ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡

ከጥንት ፡ አይዶለሞይ ፡ ተልኮ ፡ መሞት ።

ዳግም ፡ "ያ ፡ ያንጓብባል ፡ እንጂ ፡ መች ፡ ይዋጋል ፡ ካሳ" ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ የደጃች ፡ ጉሹ ፡ ኣዝማሪ ፡ በጠቋሚ ፡ ተይዞ ፡ እደጃች ፡ ካሳ ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ቀረበ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ብለህ ፡ ሰደብኸኝ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ ከጭንቀት ፡ የተነሣ ፡ ምሕረት ፡ ያገኘሁ ፡ መስሎት ፡

ኣወይ ፡ ያምላክ ፡ ቊጣ አወይ ፡ የግዜር ፡ ቀጣ ፡

ኣፍ ፡ ወዳጁን ፡ ያማል ፡ ሥራ ፡ ሲያጣ ፡

ሽመል ፡ ይገባዋል ፡ ያዝማሪ ፡ ቀልባጣ ፡

ብሎ ፡ በራሱ ፡ ስለ ፡ ፈረደ ፡ በሽመል ፡ ተደብድቦ ፡ ሞት ፡ ይላሉ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ የደጃች ፡ ጉሹን ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ መሞት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ያዘውን ፤ ደጃች ፡ በለውን ፤ ደጃች ፡ አቤን ፡ የላስታውን ፡ ብሩ ፡ ዐሊን ፡ አድርገው ፡ ከደጃች ፡ ውቤም ፡ ወታደር ፡ ጨምረው ፡ ላኳቸው ። እነዚህም ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ ደጃች ፡ ጉሹ ፡ ድል ፡ ሆኑ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ሰውም ፡ ብረትም ፡ እየሰበሰቡ ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ለመውጋት ፡ ይዘጋጁ ፡ ዠመር ። ራስ ፡ ዐሊም ፡ በበኩላቸው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አዘጋጅተው ፡ ጦርነት ፡ ከማድረጋቸው ፡ በፊት ፡ የደጃች ፡ ጉሹ ፡ ልጅ ፡ ብሩ ፡ ጉሹ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ደጃች ፡ ካሳን ፡ እንዲወጋ ፡ ሲያባብሉት ፡ እንዲሁም ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ብሩ ፡ ጉሹን ፡ ካባትኸኸም ፡ ያጣላን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ አሁንም ፡ ያባትኸን ፡ ግዛት ፡ እመልስልኻለሁ ፡ በማለት ፡ ተስፋ ፡ ሰጥተው ፡ በጐናቸው ፡ እንዲሠለፍ ፡ ይጥሩ ፡ ነበር። ብሩ ፡ ጉሹ ፡ ግን ፡ ከማንኛውም ፡ ወገን ፡ ሳይሆን ፡ እንዲሁ ፡ ተራውን ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ቊጥሩ ፡ 100 ፡ ሺሕ ፡ የሚደርሰውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ እጣና ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ ጉርጉራ ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ድረስ ፡ ወርደው ፡

ተጋጥመው ፡ ጦርነቱም ፡ ተፋፍሞ ፡ ሲዋጉ ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ ሰው ፡ ሸሽት ፡ ዠምሮ ፡ የደጃት ፡ ካሳ ፡ ሰው ፡ ያባርር ፡ ዠመር። ራስ ፡ ዐሊም ፡ ያንን ፡ ሥፍራ ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ የተረፈውን ፡ ጦራቸውን ፡ ሰብስበው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከፊተኛው ፡ ውጊያ ፡ በ3ኛው ፡ ወር ፡ ተጋጠሙ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የደጃች ፡ ካሳ ፡ ጦር ፡ አሸናፊነት ፡ ሲሰማው ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ ሰው ፡ የካሳን ፡ ጦር ፡ በፍጹም ፡ የማይበገር ፡ መሆኑን ፡ በፍርሀት ፡ ዐቅል ፡ እያመዛዘነ ፡ ለሽሽት ፡ ያወላውል ፡ ዠመር። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ በመጨረሻ ፡ ባላቸው ፡ ዐቅም ፡ በርትተው ፡ ከተከላከሉ ፡ ወዲህ ፡ አሁንም ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ድል ፡ ስላደረጓቸው ፡ ነገሩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መሆኑን ፡ ተረድተውት ፡ «ይህ ፡ በትር ፡ የአግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የካሳ ፡ አይደለም» ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ከቈረጡ ፡ በኋላ ፡ ባ1845 ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ደውለው ፡ ደምበጫ ፡ ገቡ። ከዚያም ፡ ሌሊቱን ፡ ሲገሠግሥ ፡ አድረው ፡ ማኅደረ ፡ ማርያም ፡ ገቡ። በዚያም ፡ ካህናቱ ፡ ቀርበው ፡ ድል ፡ አድራጊው ፡ እርስዎን ፡ ሲል ፡ መጥቶ ፡ ደብራችንን ፡ ይበረብርብናል ፡ ብለው ፡ መፍራታቸውን ፡ ስለ ፡ ገለጹላቸው ፡ ወደ ፡ ደራ ፡ ሸሹ ። በዚያም ፡ የደራው ፡ ባላባት ፡ ዋቀኍ ፡ ዲቦ ፡ ይዞ ፡ አሰራቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሸዋ ፡ ንጉሥ ፡ ኀይለ ፡ መለኮት ፡ ሰምተው ፡ ወደ ፡ ዶራ ፡ ዘምተው ፡ ዋቄ ፡ ዲቦን ፡ ወግተው ካሰሩ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ፈተው ፡ ወደ ፡ አንኮበር ፡ አመጡና ፡ በከበሬታ ፡ አስቀመጧቸው። በኋላ ፡ ግን ፡ ወዳገሬ ፡ መመለስ ፡ እፈልጋለሁ ፡ ቢሏቸው ፡ ሸኚ ፡ ጨምረው ፡ ላኳቸው ። ርሳቸውም ፡ በየጁ ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ ራያ ፡ ወሰን ፡ ገብተው ፡ ተቀምጠው ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፡ ሞቱ።

ደጃች ፡ ካሳ ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ድል ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ በጠቅላላው ፡ ያማራን ፡ ግዛት ፡ ስለ ፡ ያዙና ፡ ይልቁኑም ፡ የጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በእጃቸው ፡ ሆኖ ፡ ገዥዎች ፡ በነበሩበት ፡ በነራስ ፡ ዐሊ ፡ እግር ፡ ስለ ፡ ተተኩ ፡ የደንቡን ፡ ግብርና ፡ ጳጳሱን ፡ አቡነ ፡ ሰላማን ፡ ይልኩላቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ መልክተኛ ፡ ላኩ ፡ ደጃች ፡ ውቤም ፡ አባ ፡ ሰላማን ፡ አጠገባቸው ፡ ያስቀመጡበት ፡ ምክንያት ፡ በተመቸ ፡ ቀን ፡ ጐንደርን ፡ ይዘው ፡ በጳጳሱ ፡ እጅ ፡ ተቀብተው ፡ የመንገሥ ፡ አሳብ ፡ ስላላቸው ፡ ነበርና ፡ ጳጳሱን ፡ ለመላክ ፡ አለመቻላቸውን ፡ አስታውቀኍ ። ደጃች ፡ ካሳም ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ለመግጠም ፡ ከመሄድ ፡ በፊት ፡ ባጠገባቸው ፡ ያለውን ፡ የጐጃሙን ፡ ብሩ ፡ ጐሹን ፡ ወግተው ፡ በዚህ ፡ ወገን ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ መደዳውን ፡ በድል ፡ ለማስተካከል ፡ አስበው ፡ ጦራቸውን ፡ ወደ ፡ ብሩ ፡ ጐሹ ፡ አዞረው ፡ በመዠመሪያ ፡ ሚስቱን ፡ ከማረኩ ፡ በኋላ ፡ ብሩ ፡ ጐሹንም ፡ በጥቂት ፡ ጦርነት ፡ ድል ፡ አደረጉት።

# ምዕራፍ ፡ 4።

## <u>ስለ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ -ደጃች ፡ካሳ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ለማድረግ እንዳሰቡ ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ እንደ ፡ ደፉ ።</u>

በሸዋ ፡ የአቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘር ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ባማራና ፡ በበጌምድር ትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ በስሜንና ፡ በትግሬ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ በሚገዙበት ፡ ጊዜ ፡ የጉንደሩ ፡ ሊቅ ፡ የሸዋው ፡ ተወላጅ ፡ አለቃ ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ተልከው ፡ ወደ ፡ እስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ኣጳጳስ ፡ ወደ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጳጳስ ፡ ለማምጣት ፡ ሄዱ ፡ በእስክንድርያም ፡ ስለ ፡ ጳጳሱ ፡ ምርጫ ፡ ስብሰባ ፡ ተደርጎ ፡ እንድርያስ ፡ ይባሉ ፡ የነበሩት ፡ የ25 ፡ ዓመት ፡ ወጣት ፡ ተመረጡ። ወዲያው ፡ እንደ ፡ መዠመሪያው ፡ ጳጳስ ፡ እንደ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ (ፍሬም ናጦስ) ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ተብለው ፡ ከአለቃ ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ጋራ ፡ ባ1834 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኅዳር ፡ 3 ፡ ቀን ፡ መጥተው ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ጋራ ፡ ቍይተው ፡ ሳለ ፡ ደጃች ፡ ውቤና ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ በሥልጣን ፡ ተዋግተው ፡ ( ሁለቱም ፡ ድል ፡ የሆኑ መስሏቸው ፡ ሸሹ ፡ ተብሎ ፡ በተሣቀባቸው ፡ ጊዜ) ፡ በመጨረሻ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ድል አድርገው ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ማረኳቸው።

በኋላግን ፡ በሁለቱ ፡ ጠበኞች ፡ መካከል ፡ ዕርቅ ፡ ተደርጎ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ያነግሡኛል ፡ ብለው ፡ ያስመጧቸውን ፡ አቡነ ፡ ሰላማን ፡ ለራስ ፡ ዐሊ ፡ ሰጥተው ፡ ወደ ፡ ግዛታቸው ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ተመለሱ ። አቡነ ፡ ሰላማም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ የሚሉትን ፡ የጸጋ ፡ ልጆችንና ፡ ካቶሊኮችን ፡ ገዝተው ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ እያሉ ፡ ሲያስተምሩ ፡ በዚህ ፡ የተነሣ ፡ ክርክርና ፡ ጭቅጭቅ ፡ ተነሥቶ ፡ ከሸዋም ፡ ብዙ ፡ የጸጋ ፡ ሃይማኖትን ፡ የያዙ ፡ ሊቃውንት ፡ ሄደው ፡ አባ ፡ ሰላማን ፡ ከጐንደር ፡ ወጥተው ፡ እንዲሄዱ ፡ ኣስገደዷቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከጐንደርና ፡ ከሸዋ ፡ ሊቃውንት ፡ ጋራ ፡ ገዥዎቹም ፡ እነራስ ፡ ዐሊ ፡ ባንድነት ፡ ለማስወጣት ፡ ስላደሙባቸው ፡ ጐንደርን ፡ ትተው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ስሜን ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ሄዱ። ደጃች ፡ ውቤም ፡ ኣባ ፡ ሰላማን ፡ በመልካም ፡ ኣቀባበል ፡ ተቀብለው ፡ በከበሬታ ፡ ይዘዋቸው ፡ ሲኖሩ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ በየጊዜው ፡ ያደረጉትን ፡ ድል ፡ ይሰሙ ፡ ዠመር ። ይልቍንም ፡ ከደጃች ፡ ጉሹና ፡ ከእቴጌ ፡ መነንም ፡ ስመ ፡ ጥሩውን ፡ ያማራውን ፡ ገዥ ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ድል ፡ ስላደረጉ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚያደርጉትን ፡ የድል ፡ እርምጃ ፡ እንኳን ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ሌላም ፡ ከእርሳቸው ፡ የበለጠ ፡ ቢሆን ፡ ለማገድ ፡ አለመቻሉን ፡ እዚያው ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ጋራ ፡ በፍቅር ፡ አብረው ፡ በሚበሉበትና ፡ በሚጠጡበት ፡ ጊዜ ፡ ያመዛዝኑ ፡ ዠመር ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ከደጃች ፡ ካሳ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ በሚማረኩበት ፡ ቀን ፡ አብሬ ፡ ከመማረክ ፡ አስቀድሜ ፡ ብሄድ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ቀብቼ ፡ አነግሥኻለሁ ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተስፋ ፡ የሰጧቸውን ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ትተው ፡ በማስታረቅ ፡ ስም ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ መጡ ። ደጃች ፡ ካሳም ፡ ያቡነ ፡ ሰላማን ፡ መምጣት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ካሉበት ፡ ሰፍራ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ሄደው ፡ በሰላምታ ፡ ከተገናኘ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚያደርጉትን ፡ ነገር ፡ ይማከሩ ፡ ዠመር ።

ኢትዮጵያንም ፡ ባንድነት ፡ ለመግዛት ፡ አስቀድሞ ፡ የሕዝቡ ፡ ሃይማኖት ፡ ኣንድ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ፡ ሲሉ ፡ ውስጧ ፡ በቀል ፡ ያለበትን ፡ ምክራቸውን ፡ ለደጃች ፡ ካሳ ፡ አቀረቡላቸው ። ምክሩም ፡ በደጃች ፡ ካሳ ፡ ፊት ፡ ደስ ፡ ስላሰኘ ፡ ኣባ ፡ ሰላማ ፡ ካቶሊኮችንና ፡ የጸጋ ፡ ልጆችን ፡ የሚቃወመውን ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ ነው ፡ ቀቢና ፡ ተቀቢም ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተቀብቶ ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ አልሆነም ፡ የሚለውን ፡ ሃይማኖት ፡ በጽሕፈት ፡ ኣዘጋጅተው ፡ ሐምሌ ፡ 8 ፡ ቀን ፡ 1846 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ባዋጅ ፡ እንዲነገር ፡ አደረጉ ።

ደጃች ፡ ካሳም ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡ የሚሉትን ፡ ሃይማኖት ፡ ያልተቀበለ ከላይ ፡ አንገቱ ፡ ከታች ፡ ባቱ ፡ ይቈረጣል ፡ ሲሉ ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ። አቡኑና ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ጉን ፡ ለጉን ፡ ሆነው ይህን ፡ ዐዋጅ ፡ ሲያስነግሩ ፡ ተርታው ፡ ክርስቲያንና ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ በደስታ ፡ ተቀብሎ ፡ ከዚህ ፡ ሃይማኖት ፡ አንወጣም ፡ ቃልዎ ፡ ይድረሰን ፡ እያለ ፡ በጭብጨባ ፡ ተቀበለ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ የጸጋ ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚወዱ ፡ የጐንደርና ፡ የሸዋ ፡ ሊቃውንት ፡ ካቶሊኮችም ፡ ገሚሶቹ ፡ ከፍርሀት ፡ የተነሣ ፡ ሲቀበሉ ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ኣንቀበልም ፡ ብለው ፡ በተከራከሩ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በሰላም ፡ ፈንታ ፡ ሁከት ተነሥቶ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከውስጣቸው ፡ የታሰረና ፡ የተገረፈ ፡ የተገደለም ፡ አለ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በአከለ ፡ ጉዛይና ፡ ምጥዋ ፡ የካቶሊክን ፡ ሚሲዮን ፡ የሚመራው ፡ ነጮች ፡ ቤስኮቦ ፡ ጃውስቲኖ ፡ ዴ ፡ ጃኮቢስ ፡ የሚሉት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ግን ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ የሚሉት ፡ የኢጣሊያ ፡ ተወላጅ ፡ ሚሲዮናዊ ፡ ነበር ። ከእሱም ፡ ጋራ ፡ በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ የተሳሰሩት ፡ እናባ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ ነበሩ ። ደጃች ፡ ካሳም ፡ አባ ፡ ያዕቆብን ፡ ሃይማኖቴን ፡ ይዞሽ ፡ ተቀመጥ ፡ አለዚያም ፡ ከነሰውኽ ፡ ውጣ ፡ ካሉት ፡ በኋላ ፡ በዚያው ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ ታሰረ ። ከኢትዮጵያውያንም ፡ ውስጥ ፡ ዐይነተኛው ፡ ካቶሊክ ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ እንዲሞቱ ፡ ፈርደውባቸው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ጥሎ ፡ ውዴን ፡ የሚባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ቆንሲል ፡ በመካከሉ ፡ ገብቶ ፡ ስላማለደ ፡ የሞቱ ፡ ፍርድ ፡ በግርፋትና ፡ በስራት ፡ ተለውጦ ፡ ወህኒ ፡ ገብተው ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፡ ሞተ ፡ ።

አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ግን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ በመሆኑ ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ ተላከ ። አቡነ ፡ ሰላማ ፡ ይህን ፡ ያደረጉት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የጐንደርና ፡ የሸዋ ፡ ሊቃውንት ፡ ባለፈው ፡

ያደረጉባቸውን ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ ቢሆን ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ስትሆን ፡ እንደዚሁ ፡ ሕዝቡ ፡ በማንኛውም ፡ አንድነት ፡ ሆኖ ፡ በቱርኮችና ፡ በግብጾች ፡ ላይ ፡ ለሚያደርጉት ፡ ፖለቲካ ፡ እንዲመቻቸው ፡ ነበር ። ደጃች ፡ ካሳ ፡ ይህን ፡ በስብከት ፡ እንጂ ፡ በቅጣትና ፡ ባዋጅ ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ሊታነጽ ፡ የማይቻለውን ፡ የሃይማኖት ፡ የመዠመሪያ ፡ ድንጋይ ፡ ከአባ ፡ ሰላማ ፡ ጋራ ፡ ከበገሩ ፡ ( ከጣሉ) ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ለመውጋት ፡ ተዘጋጁ ። ነገር ፡ ግን ፡ በመካከሉ ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ልጅ ፡ ዳንጉልና ፡ ብላታ ፡ ኮከቤ ፡ ለደጃች ፡ ካሳ ፡ የሚሰጥ ፡ ገንዘብ ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ ዕርቅ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ። ይህም ፡ ዕርቅ ፡ ሁለቱ ፡ ጠበኞች ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ እንዲዘጋጁ ፡ ጊዜ ፡ ከመስጠት ፡ በቀር ፡ ያተረፈው ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ ወዲያው ፡ ደጃች ፡ ካሳና ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ለጦርነት ፡ ተሰልፈው ፡ ደረስጌ ፡ ላይ ፡ ተጋጠሙ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በዠግንነት ፡ ሲዋጉ ፡ ውለው ፡ የጦርነቱ ፡ ዕድል ፡ ወደ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሚያወላውልበት ፡ ጊዜ ፡ ጦርነቱን ፡ ደኅና ፡ ኣድርጎ ፡ መክቶ ፡ ይህ ፡ የነበረው ፡ እሸቴ ፡ የሚባለው ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ልጅ ፡ ተመቶ ፡ ከፈረሱ ፡ ወደቀ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሠራዊቱ ፡ መካከል ፡ ፍርሀትና ፡ ድንጋጤ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ያስታራቂ ፡ መላከተኛ ሆኖ ፡ ከደጃች ፡ ውበት ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ተልኮ ፡ የነበረው ፡ ብላታ ፡ ኮከቤ ፡ አስቀድሞ ፡ ንግግር ፡ እንዳለው ፡ ሳይታወቅ ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ከድቶ ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ዞረ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያረጀው ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ የዠግንነት ፡ ሥራ ፡ ገና ፡ ግለትና ፡ ደፋርነት ፡ በሚሰኩው ፡ በደጃች ፡ ካሳ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ ኣልነበረውምና ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ትንሽ ፡ ቈይተው ፡ እጃቸውን ፡ ሰጡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ በሠራዊታቸው ፡ ታጅበው ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ግርማ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ አሠርተውት ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡ ደረስጌ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲደርሱ ፡ ሴቱም ፡ ወንዱም ፡ በእልልታና ፡ በጭብጨባ ፡ ተቀበላቸው ። ወዲያው ፡ ከድሉ ፡ በ3ኛው ፡ ቀን ፡ 1847 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የካቲት ፡ 5 ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ በጳጳሱ ፡ ባቡነ ፡ ሰላማ ፡ እጅ ፡ ተቀብተው ፡ « ዳግማዊ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ » ፡ ተብለው ፡ ነገሡ ። ከሌላውም ፡ ስም ፡ ቴዎድሮስ ፡ መባልን ፡ የመረጡበት ፡ ምክንያት ፡ ቴዎድሮስ ፡ የሚባል ፡ ንጉሥ ይነግሥና ፡ ኀይለኛና ፡ ፍርድ ፡ አስተካካይ ፡ ይሆናል ፡ የኢትዮጵያንም ፡ ግዛት ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ያደርሳል ፡ የተባለው ፡ አንተ ፡ ነኽ ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አስቀድመው ፡ ይተነቡላቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከዳተኛው ፡ ብላታ ፡ ኮከቤ ፡ ለርስዎ ፡ ስል ፡ ጌታዬን ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ከድቼ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ሠራሁ ፡ ሹመትና ፡ ሽልማት ፡ ይገባኛል ። ሲል ፡ ለኔ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ኣመለከተ ። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ግን ፡ ከከዳተኛ ፡ ይልቅ ፡ ደፋርና ፡ ሐቀኛ ፡ ጕበዝ ፡ ስለሚወዱ ፡ ወይም ፡ በኔም ፡ ቀን ፡ ይኸው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ እኔ ፡ ጌታውን ፡ ከሚከዳ ፡ ኣሽከር ፡ ጋራ ፡ ኣንድነት ፡ የለኝም ፡ ሲሉ ፡ በመሾምና ፡ በመሸለም ፡ ፈንታ ፡ ኣሰሩት ።

ደጃች ፡ ውቤ ፡ ተማርከው ፡ ልጃቸውም ፡ እሸቴ ፡ ከጦርነቱ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ሳለ ፡ አንደኛው ፡ ጓንጉል ፡ የሚባለው ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ልጅ ፡ መጥቶ ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጋራ ፡ ተዋግቶ ፡ ሲሸነፍ ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ሀብት ፡ ተቀምጦበት ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ከፍታው ፡ ከባሕር ፡ በላይ ፡ 3ሺ580 ፡ ሜትር ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ተራራ ፡ ገብቶ ፡ ተቀመጠ ። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ደም ፡ ከመፋሰስ ፡ በፊት ፡ ነገርን ፡ በፈሊጥ ፡ የማከናወን ፡ ስጦታ ፡ ነበራቸውና ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ በሰንሰለት ፡ እንደ ፡ ታሰሩ ፡ እፊት ፡ አስቀድመው ፡ ያባትኸን ፡ ሕይወት ፡ ለማዳን ፡ የፈለግኸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መሣሪያ ፡ አስረክበኝ ፡ አንተም ፡ እጅኸን ፡ ስጥ ፡ ቢሉት ፡ ከያዘው ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ ያባቱን ፡ ሕይወት ፡ ስለ ፡ መረጠ ፡ ገንዘቡንና ፡ ዕቃውን ፡ መሣሪያውንም ፡ በያይነቱ ፡ አስረከቦ ፡ እሱም ፡ ወዲያው ፡ እጁን ፡ ሰጠ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በትግሬ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ጦርነት ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፡ እንደራሴ ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስን ፡ አጎት ፡ ትልቁን ፡ ደጃች ፡ አርኣያን ፡ ሾመው ፡ ባለኽ ፡ ርጋ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ተመለሱ። ደጃች ፡ ውቤም ፡ ከነቤተ ፡ ሰባቸው ፡ ጐንደር ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ተራራ ፡ ታስረው ፡ ሳለ ፡ ከብስጭት ፡ የተነሣ ፡ ለምን ፡ ከነዘመዶቹ ፡ አሰረው ፡ ያጕላሉኛል ፡ ከኔስ ፡ ለመለያየት ፡ አንድ ፡ የጠመንጃ ፡ ጥይትና ፡ ጣት ፡ አይበቃምን ፡ ብለው ፡ ለዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ላኩባቸው ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሥ ፡ ሊራሩላቸው ፡ ስላልፈለጉ ፡ እንደ ፡ ታሰሩ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ቈይተው ፡ ባ1860 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሞቱ።

# ምዕራፍ 5

## ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከወሎና ፡ ከሸዋ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ።

በድል ፡ ለያዙት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ክልብ ፡ የሚያምኑዋቸውን ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ ሾመው ፡ ቀጥለው ፡ ወሎንና ፡ ሸዋን ፡ ለመያዝ ፡ ስላሰቡ ፡ ባለፈው ፡ ጦርነት ፡ የደከመው ፡ ሠራዊታቸው ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ የጋላውን ፡ አገር ፡ ወሎንና ፡ ይልቁንም ፡ ትልቁን ፡ የሸዋን ፡ አገር ፡ ይዘን ፡ ኢትዮጵያን ፡ አንድ ፡ ካደረግን ፡ በኋላ ፡ አንደኛውን ፡ ዕረፍት ፡ እናደርጋለን ፡ ብለው ፡ ሠራዊታቸውን ፡ በንግግር ፡ ካጽናኑ ፡ በኋላ ፡ ከአምባጫራ ፡ ተነሥተው ፡ ጉዟቸውን ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ አመሩ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሸዋው ፡ ንጉሥ ፡ ኀይለ ፡ መለኮት ፡ ግዛታቸውን ፡ እስከ ፡ አሩሲ ፡ ድረስ ፡ ለማቅናት ፡ ሄደው ፡ ሲመለሱ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ሰሙት ፡ በቋራ ፡ 1 ፡ ሰው ፡ ተነሥቶ ፡ ጐጃምንና ፡ መላውን ፡ ያማራን ፡ አገር ፡ ትግሬንም ፡ ጭምር ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ተብሎ ፡ ነገሠ ፡ አሁንም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መምጣቱ ፡ አይቀርም ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው።

ንጉሥ ፡ ኀይለ ፡ መለኮትም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ወሎን ፡ ትገዛ ፡ ከነበረችው ፡ ከወ ፡ ይዘሮ ፡ ወርቂት ፡ ተላልከው ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ታቹን ፡ በጐጃም ፡ አቋርጠው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ሲመጡ ፡ እኔ ፡ ከግንባራቸው ፡ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ሠራዊትሽን ፡ ሰብስበሽ ፡ በጐናቸው ፡ ስትገጥሚ ፡ ድል ፡ እናደርጋቸዋለን ፡ ብለው ፡ በዚህ ፡ አሳብ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ተስማሙ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይኸንኑ ፡ ሲማከሩ ፡ ሰምቶ ፡ የነበረ ፡ ተደብቆ ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሄዶ ፡ ገለጸላቸው። ሰላዩንም ፡ የላኩት ፡ የኤፍራታው ፡ ገዥ ፡ አቶ ፡ በድሉ ፡ ናቸው ፡ ይባላል። እሳቸውም ፡ ብዙውን ፡ ጠላት ፡ በየተራ ፡ መግጠም ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ ባለፈው ፡ ጦርነት ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ በጐጃም ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ በመምጣት ፡ ፈንታ ፡ ገሥግሠው ፡ የእግዜር ፡ ድልድይ ፡ በሚባለው ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ ሲገቡ ፡ የወሎ ፡ ሕዝብ ፡ ገሚሱ ፡ ግብር ፡ እየያዘላቸው ፡ መጣ።

እርሳቸውም ፡ ግብሩን ፡ ተቀብለው ፡ በሰላም ፡ አሰናብተው ፡ ጉዟቸውን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለመቀጠል ፡ ሲያስቡ ፡ የወሎ ፡ ሹማምት ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ ሰብስቦ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እነደጃች ፡ ጉበዜ ፡ (በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የተባሉት) ፡ እነራስ ፡ ዐሊ ፡ ሌሎችም ፡ ቢመጡብን ፡ በኸግንነት ፡ እየተዋጋን ፡ መለስናቸው። አሁን ፡ ግን ፡ አስቀድመን ፡ ሳንዋጋ ፡ እንደ ፡ ሴት ፡ አገራችንን ፡ እንዴት ፡ እንለቃለን ፡ ብለው ፡ ሠራዊቱን ፡ በስብከት ፡ ስላነቃቁት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ፈረሱን ፡ ጭኖ ፡ ለጦርነት ፡ ተነሣ ።

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከጊምቢያ ፡ ሠፈራቸው ፡ ተነሥተው ፡ በመካከሉ ፡ ሜዳ ፡ ሲጓዙ ፡ ግራ ፡ ቀኙ ፡ ተራራ ፡ ነውና ፡ እንደ ፡ ወትሮ ፡ ልማድ ፡ በፈረስ ፡ ሲመጣ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፈረሰኛ ፡ በክፍል ፡ በክፍሉ ፡ አድርገው ፡ በየግንባሩ ፡ ቢለቁበት ፡ የወሎ ፡ ጦር ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ሸሽት ፡ ጀመረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮቻቸው ፡ ያመጡላቸውን ፡ የወሎ ፡ ምርኮኛ ፡ ከገበረ ፡ በኋላ ፡ ከወጋኝ ፡ ምሕረት ፡ ኣይገባውም ፡ ብለው ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ እጁን ፡ ቈርጠው ፡ በያንገቱ ፡ እያሰሩ ፡ ለወሎ ፡ ሕዝብ ፡ መቀጣጫ ፡ እንዲሆን ፡ ላኩለት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የወሎ ፡ ሕዝብ ፡ አላህ ፡ ምን ፡ አመጣብን ፡ ከዚህስ ፡ ጋራ ፡ ማን ፡ ተዋግቶ ፡ ይተርፋል ፡ ሲል ፡ ሁሉም ፡ አሜን ፡ ብሎ ፡ ገበረ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከወሎ ፡ አየር ፡ አለመስማማት ፡ የተነሣ ፡ ይልቁንም ፡ ቤቱን ፡ ከተወ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የቈየው ፡ ወታደር ፡ በወሎ ፡ ያገኘውን ፡ ጨርቋውን ፡ እሸት ፡ በየርሻው ፡ እየተሠማራ ፡ ሲበላ ፡ ሆዱን ፡ እየታመመ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አለቀ።

ወሎን ፡ ካስገበሩ ፡ በኋላ ፡ ጳጳሱን ፡ አቡነ ፡ ሰላማን ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ለመሄድ ፡ ግሼ ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ ይኸንኑ ፡ አገር ፡ ይገዛ ፡ የነበረው ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ የሚባለው ፡ ቢዋጋቸው ፡ ድል ፡ አደረጉት።

ከዚያ ፡ አልፈው ፡ ባ1848 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥቅምት ፡ ወር መንዝ ፡ ደረሱ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡን ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ጳጳሱን ፡ አቡነ ፡ ሰላማን ፡ ጐንለጐን ፡ ሆነው ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተክህነት ፡ መስማማቱን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በዙሪያው ፡ ያለ ፡ የግድምና ፡ የኤፍራታ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ እየመጣ ፡ ገበረላቸው። ንጉሡም ፡ አገርና ፡ አባት ፡ ያለኽ ፡ በያገርኽ ፡ በያባትኽ ፡ ግባ። አገርና ፡ አባት ፡ የሌለኽ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ አባት ፡ እሆንኻለሁና ፡ ደጅ ፡ ጥናኝ ፡ በሚል ፡ ቃል ፡ የሸዋን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አስደሰቱት ። ከዚያም ፡ አልፈው ፡ በጥቅምት ፡ 14 ፡ ቀን ፡ ኽርብ ፡ ዋሻ ፡ ሲደርሱ ፡ የጠራው ፡ አቶ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ በኽርግንነት ፡ ካፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሲዋጉ ፡ ሞቱ ። በጥቅምት ፡ 12 ፡ ቀን ፡ አንኮበርን ፡ የሚጠብቁ ፡ የንጉሥ ፡ ኀይለ ፡ መለኮት ፡ አሽከሮች ፡ በጌታችን ፡ ቤት ፡ ጠላት ፡ አይግባበት ፡ ብለው ፡ ያንኮበርን ፡ ከተማ ፡ የንጉሥን ፡ አዳራሽና ፡ ቅጥሩን ፡ አቃጠሉት።

ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ መለኮት ፡ ግን ፡ መኳንንቶቻቸው ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ አጠገብ ፡ አታክልት ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ቀጥለው ፡ ለመዋጋት ፡ ሲያስቡ ፡ በጽኑ ፡ ደዌ ፡ ድንገት ፡ ታመው ፡ ወዲያው ፡ ዐርፈው ፡ በደብረ ፡ በግዕ ፡ አባ ፡ ሕፃን ፡ ሞዓ ፡ ደብር ፡ ባ1848 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኅዳር ፡ 1 ፡ ቀን ፡ ተቀበሩ ። ከሞታቸው ፡ በፊት ፡ የሸዋን ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ ሰብስበው ፡ አልጋ ፡ ወራሼ ፡ ምኒልክ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አስታውቀው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ መኳንንቱ ፡ ልጅ ፡ ምኒልክን ፡ ይዘው ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቱም ፡ የንጉሥ ፡ ኀይለ ፡ መለኮትን ፡ ዕረፍት ፡ ዐውጀው ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ለመውጋት ፡ ከየረር ፡ ተነሥተው ፡ በምንጃር ፡ ቈላ ፡ አለፉ ። ከዚያ ፡ ከሰምን ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ በረከት ፡ ሲደርሱ ፡ ወሬያቸው ፡ ተሰማ ። ስለዚህ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ራስ ፡ እንግዳን ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፡ አድርገው ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ልከው ፡ የሁለቱ ፡ ወገን ፡ ሠራዊቶች ፡ ጦርነት ፡ ገጥመው ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ የሸዋ ፡ ጦር ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ለመመለስ ፡ ባለመቻሉ ፡ መኳንንቱና ፡ ይልቁንም ፡ አቶ ፡ አብቱ ፡ በከንቱ ፡ ከምናልቅ ፡ እጃችንን ፡ ብንሰጥ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ባንድነት ፡ መክረው ፡ አቤቶ ፡ ምኒልክ ፡ ገና ፡ ያሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ሳሉ ፡ ለዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አሳልፈው ፡ ሰጧቸው።

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ግን ፡ ምኒልክን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በጠላት ፡ ፀይን ፡ ሳያዩ ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ በፍቅር ፡ ዐይን ፡ ተመልክተው ፡ በደስታ ፡ ተቀብለው ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ይዘዋቸው ፡ ሄዱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ አንኮበር ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ በሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ጊዜ ፡ አምሮ ፡ የተሠራውና ፡ ከቃጠሎ ፡ የተረፈው ፡ የከተማው ፡ ዐቅድ ፡ ደስ ፡ ስላሰኛቸው ፡ እንዳይዘረፍ ፡ ከለከሉ ። ቢሆንም ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በማጆር ፡ ሐሪስ ፡ በኩል ፡ ለንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ሰጥቷቸው ፡ የነበረውን ፡ መድፍና ፡ ጠመንዣ ፡ እንዲወሰድ ፡ አደረጉ።

ንጉሥ ፡ ኀይለ ፡ መለኮትም ፡ የርሳቸውንና ፡ ያባታቸውን ፡ የሣህለ ፡ ሥላሴን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ሌላውም ፡ ሀብት ፡ የሚገኝበትን ፡ ስፍራ ፡ ጽፈው ፡ እንደ ፡ ክታብ ፡ በልጃቸው ፡ በምኒልክ ፡ አንገት ፡ አስረውላቸው ፡ ነበርና ፡ ንጉሡ አባትኽ ፡ ሲሞት ፡ ምን ፡ አውርሶኽ ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቋቸው ፡ ምኒልክ ፡ ክታባቸውን ፡ አሳዩ ። ወዲያው ፡ ካንገታቸው ፡ አውልተው ፡ በሰንጢ

፡ በጥሰው ፡ ካነበቡት ፡ በኋላ ፡ በጽሕፈቱ ፡ እየተመሩ ፡ አሽናፊዎቹ ፡ ወታደሮች ፡ ወርቁንና ፡ ብሩን ፡ ለራሳቸው ፡ ተካፈሉት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ለሸዋ ፡ አልጋ ፡ የሣህለ ፡ ሥላሴን ፡ ልጅ ፡ የንጉሥ ፡ ኀይለ ፡ መለኮትን ፡ ወንድም ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ኀይለ ፡ ሚካኤልን ፡ ሾመው ፡ አበጋዝ ፡ አቶ ፡ አንዳርጋቸውን ፡ አድርገው ፡ በያገሩ ፡ እያረፉና ፡ እየሰነበቱ ፡ ከብዙ ፡ ድካም ፡ በኋላ ፡ ተመልሰው ፡ ጐንደር ፡ ገቡ።

# ምዕራፍ ፡ 6።

## ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የቤተ ፡ መንግሥትንና ፡ የቤተ ፡ ክህነትን ፡ ሕግ ፡ እንዳቆሙ ፡ ሸዋ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ እንደሸፈተባቸው ፡ -- የእቴጌ ፡ ተዋበች ዕረፍት።

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጐጃምን ፥ ጐንደርን ፥ ትግሬን ፥ ወሎንና ፥ ሸዋን ፡ በመላው ፡ በኀይልና ፡ በሙሣሪያ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደ ፡ ጥንቷ አንድ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገር ፡ ካደረጓት ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ የሚተዳደርበትን ፡ የቤተ ፡ ክህነትንና ፡ የቤተ ፡ መንግሥትን ፡ ደንብና ፡ ሕግ ፡ ለማቆም ፡ አሰቡ ። በቤተ ፡ ክህነት ፡ በኩል ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከአባ ፡ ሰላማ ፡ ጋራ ፡ የተስማሙበትን ፡ የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ እንዲቀበል ፡ ክርስቲያንም ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ካንድ ፡ ሚስት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እንዳያገባ ፡ ሲሉ ፡ ለዚሁ ፡ የመዠመሪያ ፡ ለሕዝብ ፡ አብነት ፡ ለመሆን ፡ ራሳቸው ፡ እቴጌ ፡ ተዋበችን ፡ ኣስቀርተው ፡ የነበሯቸውን ፡ ቍባቶች ፡ ሁሉ ፡ አሰናበቱ ። በቄስና ፡ በደብተራ ፡ መካከል ፡ ያለውንም ፡ የመሬት ፡ ግብር ፡ ወሰኑ።

በቤተ ፡ መንግሥትም ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በዕለት ፡ ተግባሩና ፡ በደመወዙ ፡ እንዲያድር ፡ እንጂ ፡ ባሪያ ፡ መሸጥ ፡ ወይም ፡ መሸፈት ፡ እንዳይኖር ፡ በጠቅላላው ፡ ገበሬም ፡ ወደ ፡ ርሻው ፡ ነጋዴም ፡ ወደ ፡ ንግዱ ፡ የቀረውም ፡ ሰው ፡ በየሥራው ፡ እንዲመለስ ፡ ባዋጅ ፡ አስታወቁ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የቱዝባ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ቀርበው ፡ ጃንሆይ ፡ ሰዉን ፡ ሁሉ ፡ በየሥራኹ ፡ ግባ ፡ ካሉት ፡ እኛም ፡ ክሌብነትና ፡ ከሽፍትነት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ የለንምና ፡ ይኸንኑ ፡ ሥራችንን ፡ ይፍቀዱልን ፡ ሲሉ ፡ ጥቂት ሆነው ፡ አመለከቷቸው ። ርሳቸውም ፡ በኋላ ፡ በነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሚፈርዱትን ፡ በልባቸው ፡ ይዘው ፡ እኔም ፡ ለራሴ ፡ ታማኝ ፡ ዘበኛ ፡ ለመቅጠር ፡ የምፈልገው ፡ እንደናንተ ፡ የዚህ ፡ ልማድ ፡ ያለውን ፡ ጠንካራ ፡ ሰው ፡ ነው። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ያላችሁት ፡ ጥቂቶች ፡ ናችሁና ፡ ሌላ ፡ ባዕድ ፡ ሳትጨምሩ ፡ የዚህ ፡ ልማድ ፡ ያላቸውን ፡ ብቻ ፡ አጣርታችሁ ፡ ይዛችሁልኝ ፡ ኑ ፡ ብለው ፡ አሰናበቷቸው።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መኳንንቱ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ሌቦች ፡ መግረፍ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ማሰናበት ፡ እንዴት ፡ ይገባል ፡ እያሉ ፡ ሲያስቡ ፡ በተባለው ፡ ቀን ፡ ሌቦቹ ፡ ተሰብስበው ፡ በፊታቸው ፡ ቆሙ ። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ እነሱ ፡ ብቻ ፡ መሆናቸውን ፡ ጠይቀው ፡ አዎን ፡ ጃንሆይ ፡ ብለው ፡ ከመለሱላቸው ፡ በኋላ ፡ በዙሪያቸው ፡ የቆሙትን ፡ ወታደሮች ፡ አዘው ፡ በጥይት ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ፡ አስደበደቧቸው ። ከዚያ ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ የሣቅና ፡ የቀልድ ፡ ንግግር ፡ በፍጹም ፡ ቀረ ፡ ይባላል ። በእንደዚህም ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እያለ ፡ ኖረ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የነበሩትም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እስከ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ለአደንም ፡ ለሌላም ፡ ጉዳይ ፡ እስከ ፡ ምሽት ፡ ድረስ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሲሉ ፡ ማንም ፡ ይነካቸው ፡ እንዳልነበረ ፡ ራሱ። ፡ ለዣን ፡ የሚባለው ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ታሪክ ፡ የጻፈው ፡ ፈረንሳዊ ፡ ገልጾታል።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በድል ፡ የያዙት ፡ አገር ፡ ጊዜ ፡ እየፈለገና ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ መራቅ ፡ ምክንያት ፡ እያደረገ ፡ ይሸፍትባቸው ፡ ዦመር ። ከነዚሁም ፡ በሸዋ ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልጅ ፡ የኀይለ ፡ መለኮት ፡ ወንድም ፡ አቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ ባማራ ፡ አገር ፡ የደጃች ፡ ክንፉ ፡ ልጅ ፡ ጋረድና ፡ ግንባሮ ፡ ካሳ ፡ በጐጃም ፡ ተድላ ፡ ጓሉና ፡ እነብሩ ፡ ኀይሉ ፡ በትግሬ ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ዘመድ ፡ ደጃች ፡ ንጉሤ ፡ ናቸው።

መርድ ፡ አዝማች ፡ ኀይሌ ፡ ካቶ ፡ ሰይፉ ፡ ጋራ ፡ ባላንጣነት ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ አስረዋቸው ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ከሚስታቸው ፡ በስውር ፡ ከሙብል ፡ ጋራ ፡ በተላከላቸው ፡ ሞረድ ፡ እግር ፡ ብረታቸውን ፡ ሰብረው ፡ አመለጡ ። 'መርድ ፡ አዝማች ፡ ኀይሌም ፡ ሊሸፍቱ ፡ ነው ፡ ተብለው ፡ ባፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ተጠረጠሩ ፡ በኰላሽ ፡ አምባ ፡ ታሰሩ። ለሸዋም ፡ ከሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ምንም ፡ ዘር ፡ የሌላቸው ፡ አቶ ፡ በዛብኽ ፡ ስለ ፡ ተሾሙ ፡ አቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ በዚሁ ፡ ተናደው ፡ አንኮበር ፡ መጥተው ፡ በዛብኽን ፡ አባረው ፡ በሸዋ ፡ አልጋ ፡ ተቀመጡ።

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ይኸንኑ ፡ ስለ ፡ ሰሙ ፡ በመዠመሪያ ፡ የድል ፡ እርምጃቸው ፡ ጊዜ ፡ የድል ፡ መጨረሻ ፡ ወዳደረጉት ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ባ1852 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጓዙ ። ደርሰውም ፡ ከአቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ ጋራ ፡ ተጋጥመው ፡ ኣቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ በኀይልና ፡ በዥግንነት ፡ ሲዋጓቸው ፡ ዋሉ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የሸዋን ፡ ወታደር ፡ ዠግንነት ፡ በማድነቅ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ወታደሮች ፡ ኑረው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በፊተኛው ፡ ጕዞዬ ፡ ጊዜ ፡ በፍጹም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ልገባ ፡ ባልቻልሁም ፡ ነበር ፡ አሉ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከመርድ ፡ አዝማች ፡ ኃይሌ ፡ ወዲህ ፡ ለሸዋ ፡ ግዛት ፡ ተሹመው ፡ የነበሩት ፡ አቶ ፡ በዛብህ ፡ የሸዋን ፡ ሕዝብ ፡ እያሳደሙ ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ ይዋጓቸው ፡ ነበርና ፡ አቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ በኀይል ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቤን ፡ አላስጨርስም ፡ ብለው ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ መራቤቴ ቈላ ፡ ወርደው ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡ የገዛ ፡ አሽከራቸው ፡ ገደላቸው። አልቃሽም ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ አለቀሰችላቸው።

የሸዋ ፡ መኳንንት ፡ እንግዴህ ፡ ኦትልፉ ፡

ተመዞ ፡ የነበር ፡ ተከተተ ፡ ሰይፉ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በፊተኛው ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንዳይዘረፍ ፡ የከለከሉትን ፡ አንኮበርን ፡ አዘረፉት ። የተማረከውም ፡ ምርኮኛ ፡ ተሰብስቦ ፡ ከፊታቸው ፡ ቆሞ ፡ ሳለ ፡ አቶ ፡ በዛብኽ ፡ ይህ ፡ ታማኝ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ የከዳነው ፡ እያሉ ፡ ካስተናበሩ ፡ በኋላ ፡ የከዳውን ፡ አገር ፡ አስጠፉት ። ከጦርነቱ ፡ የተማረከውንም ፡ እጅና ፡ እግሩን ፡ በጭካኔ ፡ አስቈረጡት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንዲት ፡ አልቃሽ ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ገጠመች።

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እጅግ ፡ ተዋረዱ ፡
የሸዋን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ ነሥተውት ፡ ሄዱ።
ባለድባብ ፡ ንጉሥ ፡ ባለጥና ፡ አቡን ፡
እየዞሩ ፡ ፈቷት ኢትዮጵያን ።

ሸዋን ፡ ሁለተኛ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ሹመቱን ፡ በኋላ ፡ ለከዷቸው ፡ ላቶ ፡ በዛብኽ ፡ መርቀው ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ የሚወዷቸው ፡ ባለቤታቸው ፡ ክፉውንና ፡ ደጉን ፡ መከራውንና ፡ ደስታውን ፡ ሲካፈሏቸው ፡ የኖሩት ፡ ይልቁንም ፡ በተናደዱና ፡ በተበሳጩ ፡ ጊዜ ፡ መክረው ፡ የሚያበርዷቸውና ፡ የሚያጽናኗቸው ፡ እቴጌ ፡ ተዋበች ፡ በጽኑ ፡ ሕመም ፡ ታመው ፡ ወደቁ። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ያየር ፡ መለወጥ ፡ የሚያሽል ፡ መስሏቸው ፡ ወደ ፡ ወረህ ፡ ይመኑ ፡ አመጧቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ተወስኖ ፡ የተሰጠው ፡ ዕድሜ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ያየር ፡ መለወጥ ፡ የሐኪም ፡ ዕውቀት ፡ የዘመድም ፡ ብዛት ፡ የዘርም ፡ ታላቅነት ፡ ሊያድን ፡ አይችልምና ፡ ሞቱ ። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ሬሳቸውን ፡ በሣጥን ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ግሼን ፡ ለመቅበር ፡ ሲያጉዙ ፡ እቴጌ ፡ ተዋበች ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ በሚስትነት ፡ ከሚያገለግሏቸው ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ናት ፡ እየመከሩ ፡ በችግርም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ገረድ ፡ እየሆኑ ፡ ሲያገለግሏቸው ፡ የኖሩት ፡ ትዝ ፡ አላቸውና ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ የልቅሶ ፡ ግጥም ፡ ገጠሙ

እስቲ ፡ ጠይቀኚልኝ ፡ ርቃ ፡ ሳትሄድ ፡

እቴጌ ፡ ተዋበች ፡ ሚስት ፡ ናት ፡ ገረድ።

ደግሞ ፡ በትልቅ ፡ ሰው ፡ ልጅነታቸውና ፡ የንጉሥ ፡ ሚስት ፡ በመሆናቸው ፡ ላይ ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ በኩል ፡ ባለሙያ ፡ ስለ ነበሩ §

አጅግ ፡ ሥራ ፡ ዐዋቂ ፡ ትናንትና ፡ ሞተች ፡

መድኅኒቱን ፡ ምሳ ፡ ታበላኝ ፡ ነበረች ፡

ብለው ፡ ገጠሙ።

እቴጌ ፡ ተዋበች ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ገና ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ሲባሉ ፡ ካገቧቸው ፡ አንሥቶ ፡ ሞት ፡ እስኪለያያቸው ፡ ድረስ ፡ ካጠገባቸው ፡ አልተለዩም ። ዕድላቸውም ፡ ከባላቸው ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ በመሆኑ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ካያታቸው ፡ ከእቴጌ ፡ መነን ፡ ወይም ፡ ካባታቸው ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ በተዋጉ ፡ ጊዜ ፡ ላባታቸውና ፡ ላያታቸው ፡ አድልተው ፡ ካፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አልተለዩም ። በነገሥት ፡ መጽሐፍ ፡ እንደምናነበው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ዳዊት ፡ ለመንግሥቱ ፡ ሲል ፡ ከጉልበቱ ፡ ከወጣው ፡ ልጁ ፡ ከአቤሴሎም ፡ ጋራ ፡ ተዋግቷል ። ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ ለመንገሥ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ወግተው ፡ ከማረኩ ፡ በኋላ ፡ ያለርኅራሄ ፡ አስረው ፡ ለሞት ፡ ሲያደርሷቸው ፡ የእኅታቸው ፡ ባል ፡ መሆናቸውን ፡ እግምት ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ ሊያመዛዝኑት ፡ እንዳልቻሉ ፡ እንደዚሁም ፡ እቴጌ ፡ ተዋበች ፡ የባላቸው ፡ ክብር ፡ የራሳቸው ፡ በመሆኑ ፡ ካባት ፡ ከናታቸው ፡ ክብር ፡ አብልጠው ፡ ለባላቸው ፡ ያደሉ ፡ ነበር።

ነገር ፡ ግን ፡ እቴጌ ፡ ተዋበች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ካባታቸው ፡ ባላቸውን ፡ መርጠው ፡ ቢቀመጡ ፡ አስፈቅደውም ፡ ቢሆን ፡ በስውርም ፡ ቢሆን ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ሁሉ ፡ እየጠየቁ ፡ አሉበት ፡ ድረስ ፡ ይልኩላቸው ፡ ነበርና ፡ አባታቸው ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ የልጃቸውን ፡ ሞት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ መሪር ፡ ኀዘን ፡ አዝነው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ የልቅሶ ፡ ግጥም ፡ ገጠሙ።

ጠጅ ፡ አማረኝ ፡ ስላት ፡ ማሩን ፡ ታስጭናለች።
ራበኝም ፡ ስላት ፡ እኽሉን ፡ ታስጭናለች።
በረደኝም ፡ ስላት ፡ ሸማ ፡ ትሰዳለች።
ሌባዬ ፡ ተይዛ ፡ ባሏጋ ፡ ትሄዳለች።
የት ፡ አባቷን ፡ ዐውቃ ፡ ታሳዝነኛለች ።
የጣቴን ፡ ቀለበት ፡ አንተ ፡ አድርገው ፡ ካሳ።
በኔማ ፡ ጣት ፡ ገብቶ ፡ አስጨነቀኝሳ።

እቴጌ ፡ ተዋበችንም ፡ ሐይቅ ፡ ደሴት ፡ ባማረ ፡ ፍታት ፡ አስፈትተው ፡ ከደጃ ፡ ሰላሙ ፡ አስቀበሯቸው ።

# ምዕራፍ ፡ 7 ።

## የልጅ ፡ ጋረድ ፡ የብሩ ፡ ጎይሉና ፡ የደጃች ፡ ተድላ ፡ ጓሉ ፡ ዕረፍት ፡ - ያቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣት ።

ልጅ ፡ ጋረድ ፡ የጎይለኛውና ፡ የስመ ፡ ጥሩው ፡ የደጃዝማች ፡ ከንፉ ፡ ልጅ ፡ በመሆኑ ፡ ያማራ ፡ ገዥ ፡ ለመሆን ፡ ያስብ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የባለቤታቸውን ፡ ኀዘን ፡ ሳይጨርሱ ፡ ተነሣባቸው ፡ ርሳቸውም ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ ሄደው ፡ ደባርቅ ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ተገናኝተው ፡ ይዋጉ ፡ ዠመር። ካፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጋራ ፡ ቤል ፡ የሚባል ፡ የስኮትላንድ ፡ ሰው ፡ ቀድሞ ፡ ካገሩ ፡ መጥቶ ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ሲያገለግል ፡ ኖሮ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዞሮ ፡ ያማራ ፡ ሴት ፡ አግብቶ ፡ ሃይማኖቱንም ፡ ተዋሕዶ ፡ ስላደረገ ፡ በዚሁ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ የሊቀ ፡ መኳስነት ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥተው ፡ ስሙንም ፡ ዮሐንስ ፡ ብለውት ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከልጅ ፡ ጋረድ ፡ በሚዋጉበት ጊዜ ፡ ባጠገባቸው ፡ ሆኖ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር። የጦርነቱ ፡ ድል ፡ ወደ ፡ ማን ፡ መሆኑ ፡ ገና ሳይታወቅ ፡ እሳቸውን ፡ አስቀድሜ ፡ ከጣልሁ ፡ ሕዝቡ ፡ ዐውቆ ፡ ወደኔ ፡ ይዞራል ፡ በማለት ፡ ልጅ ፡ ጋረድ ፡ ሠራዊቱን ፡ እየጣሰ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ለመግደል ፡ መጣ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ዮሐንስ ፡ (ቤል) ፡ በሽጒጥ ፡ መቶ ፡ ጣለው ፡ የጋረድም ፡ ወንድም ፡ ተኩሶ ፡ ሊቀ ፡ መኳሱን ፡ በገደለው ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁም ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የጋረድን ፡ ወንድም ፡ ወዲያው ፡ ስለ ፡ ገደሉት ፡ በቀል ፡ ለበቀል ፡ ተደጋገፈ። ቀጥሎም ፡ የጌታቸውን ፡ መሞት ፡ ሲያዩ ፡ የልጅ ፡ ጋረድ ፡ ሰዎች ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ሸሸት ፡ ሲዠምሩ ፡ ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ 500 ፡ የሚሆኑ ፡ ተማርከው ፡ ተገደሉ። ከድሉም ፡ በኋላ ፡ ግብር ፡ ተዘርግቶ ፡ ሳለ ፡ ከተቀማመጩ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ላዝማሪው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ነግሮ ፡ አስዘመረ።

ጋረድ ፡ ሞተ ፡ እንኳን ፡ ተቀበረ ።

ያንት ፡ ወንድም ፡ ነውና ፡ እንፈራው ፡ ነበረ።

የጋረድንም ፡ ሽፍትነት ፡ በድል ፡ ከደመሰሰ ፡ ወዲህ ፡ ብሩ ፡ ጎይሉ ፡ የሚባለው ፡ ሽፍታ ፡ ባማራ ፡ አገር ፡ ያሉት ፡ ሹሞች ፡ ሲያባርሩት ፡ መጥቶ ፡ ጣና ፡ ባሕር ፡ ገብቶ ፡ በደሴቱ ፡ ተቀመጠ ፡ ወዲያው ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ተከታትለው ፡ ባሕሩን ፡ በታንኳ ፡ ገብተው ፡ እጦሩ ፡ ጅንፎ ፡ ላይ ፡ ረዥምም ፡ ገመድ ፡ እያሰሩ ፡ የጠላትን ፡ ታንኳ ፡ ከሩቅ ፡ ወግተው ፡ ገመዱን ፡ ከታንኳው ፡ እየሳቡ ፡ አምጥተው ፡ ብሩ ፡ ጎይሉን ፡ ከነሰዉ ፡ ገደሉት ። ይህነንም ፡ የመሰለ ፡ የባሕር ፡ ጦርነት ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ አልተደረገም ፡ ይባላል ። ቀጥሎም ፡ ደጃዝማች ፡ ተድላ ፡ ጓሉ ፡ የሚባሉ ፡ ራሳቸው ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አምነው ፡ የጐጃም ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ አድርገዋቸው ፡ የነበሩት ፡ በያለበት ፡ ሽፍታ ፡ መነሣቱን ፡ ካዩ ፡ ቦኋላ ፡ ወገኖቻቸውም ፡ የራስኸን ፡ ነፃነት ፡ ለማግኘት ፡

ጊዜኸ ፡ አሁን ፡ ነው ፡ ስላሏቸው ፡ በዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ላይ ፡ ሸፈቱባቸውና ፡ ሳይዋጉ ፡ ቈይተው ፡ ባ1860 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በበሽታ ፡ ሞቱ።

ደጃዝማች ፡ ተድላ ፡ ጓሉ ፡ ቸርነት ፡ የመላቸው ፡ የጐጃም ፡ መስፍን ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ድኻውን ፡ ሁሉ ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ እየሰበሰቡ ፡ ያበሉ ፡ ነበር ። በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ መሞታቸው ፡ ለጊዜው ፡ ሳይነገር ፡ ተደብቆ ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተገጠመላቸው ፡ ይባላል።

አልሞተም ፡ ይሉናል ፡ ደጃዝማች ፡ ተድላን ፡
አሁን ፡ እሑድ ፡ ሲቀር ፡ የምናውቀውን።
የውሸ ፡ ወስደው ፡ ጣሉት ፡ ደጃዝማች ፡ ተድላን ፡
ይነሣ ፡ ነበረ ፡ አብማ ፡ ቢሆን።

ውኃ ፡ ዋና ፡ እንኳ ፡ አላውቅ ፡ ዋ ፡ ምን ፡ ይበጀኝ ፡
ጌታ ፡ የውሸ ፡ ገቡ ፡ የዳ ፡ ጥለውኝ።

በሸዋም ፡ ተላከ ፡ ጥናው ፡ ሊመጣ ፡ ነው ፡
በትግሬም ፡ ተላከ ፡ ጥናው ፡ ሊመጣ ፡ ነው ፡
ተድላ ፡ ጓሉ ፡ ሞቶ ፡ ጐጃም ፡ ሊፈታ ፡ ነው።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ቀድሞ ፡ ክርስቲያን ፡ ካልሆናችሁ ፡ ተብለው ፡ የተጉላሉትም ፡ እስላሞች ፡ አሕመድ ፡ ሽሪፍ ፡ የሚባለውን ፡ መሪ ፡ አድርገው ፡ በሽፍትነት ፡ ተነሡ ። ከነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የሚያስፈራው ፡ ተከታይም ፡ የበረከተለት ፡ ሽፍታ ፡ ግን ፡ የትግሬው ፡ ደጃዝማች ፡ ንጉሤ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ የወሎ ፡ ሰዎች ፡ እንደዚሁ ፡ በሽፍትነት ፡ ተነሥተው ፡ ብዙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አቃጥለው ፡ ነበርና ፡ እነዚህን ፡ ለማባረር ፡ በሄዱ ፡ ሰዓት ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ (የቀድሞ ፡ ስማቸው ፡ ዳውድ) ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጡ። የመጡበትም ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ይባላል ። 1ኛ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ የሚሄዱት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አገራችንን ፡ እባክዎ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይዩልን ፡ እያሉ ፡ ይለምኗቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አገር ፡ ለመጐብኘት ። 2ኛ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከቱርኮች ፡ ጋራ ፡ ተጣልተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ለማስታረቅ ። 3ኛ ፡ ካይሮ ፡ ያለውን ፡ የቅዱስ ፡ ማርቆስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማሳደስ ፡ አስበው ፡ ነበርና ፡ የገንዘብ ፡ ርዳታ ፡ ለማግኘት ፡ ነው ፡ ይላሉ። የመጡትም ፡ ባ1852 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥቅምት ፡ ወር ፡ ነው።

አቡነ ፡ ቄርሎስም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲደርሱ ፡ ወታደሩ ፡ የበዓል ፡ ልብሱን ፡ ካህናቱ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኗቸውን ፡ እየለበሱ ፡ በክብር ፡ ተቀበሏቸው ። ንጉሡም ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በፍቅር ፡ ተቀብለው ፡ ሲያስተናግዷቸው ፡ ሳለ ፡ በኋላ ፡ አቡኑ ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ንግግር ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ ሥጋዊና ፡ ወደ ፖለቲካ ፡ ንግግር ፡ ስላዘነበሉ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የክርስቲያን ፡ አባት ፡

ሆናችሁ ፡ የኔ ፡ የክርስቲያኑ ፡ ረዳት ፡ በመሆን ፡ ፈንታ ፡ የእስላም ፡ ንጉሥ ፡ ረዳት ፡ ናችሁን? ብለው ፡ በጥርጣሬ ፡ ሊቀ ፡ ጳልጳሱን ፡ ከጳጳሱ ፡ ካቡነ ፡ ሰላማ ፡ ጋራ ፡ አሰሯቸው። በኋላ ፡ ግን ፡ ዕርቅ ፡ ተደርጎ ፡ ብዙ ፡ ወርቅና ፡ የዝሆን ፡ ጥርስ ፡ ንጉሡ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ሰጥተው ፡ በፍቅር ፡ ከተለያዩ ፡ በኋላ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ወዳገራቸው ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ተመለሱ ።

# ምዕራፍ ፡ 8።

## የካፒቴን ፡ ፕሎውዴን ፡ ሞት ፡ -- የካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ መምጣት ፡ -- ደጃዝማች ፡ ንጉሤና ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ---ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወይዘሮ ጥሩ ፡ ወርቅን ፡ እንዳገቡ ።

የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በራስ ፡ ዐሊ ፡ ጊዜ ፡ ኬከል ፡ ፕሎውዴን ፡ የሚባለውን ፡ በምጥዋ ፡ ቆንሲል ፡ አስቀምጦ ፡ ነበር ። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከነገሡ ፡ ወዲህ ፡ ጐንደር ፡ ሄዶ ፡ ካፄ ፡ ቴዎድሮድስ ፡ ጋራ ፡ በንግድም ፡ በሌላም ፡ አኳኋን ፡ ግንኙነት ፡ እንዲያደርግ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ከግርማዊት ፡ ቢክቶርያ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ተላለፈለት ፡ ከምጥዋ ፡ ተነሥቶ ፡ ንጉሡ ፡ ሠፍረው ፡ ወደ ፡ ነበሩበት ፡ ሥፍራ ፡ ሄደ ፡ ንጉሡም ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ መልከተኛ ፡ የሚገባውን ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ አድርገው ፡ እጉናቸው ፡ አስቀመጡት ። ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ፕሎውዴን ፡ ለንጉሥ ፡ ወዳጅ ፡ ሆኖ ፡ ለሕዝቡም ፡ አማላጅነት ፡ እየተላከ ፡ በምክርና ፡ በሌላም ፡ ነገር ፡ እየረዳ ፡ ኖረ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ ጋረድ ፡ በሸፈተበት ፡ ወራት ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ለመመለስ ፡ ካፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ተሰናብቶ ፡ ጉዞ ፡ እንደ ፡ ዠመረ ፡ የልጅ ፡ ጋረድ ፡ ሽፍቶች ፡ በደፈጣ ፡ አግኝተው ፡ ክፉኛ ፡ ካቈሰሉት ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ሰንብቶ ፡ ባ1853 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ሞተ።

ዐፄ፡ ቴዎድሮስ ፡ ይኸንኑ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ወዳጃቸው ፡ ነበርና ፡ በጣም ፡ ስለ ፡ ተናደዱ ፡ ሽፍቶቹን ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ አባረው ፡ ከያዙ ፡ በኋላ ፡ እጅና ፡ እግራቸውን ፡ እየቈረጡ ፡ ተበቀሏቸው። የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የፕሎውዴንን ፡ መሞት ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ለተደረገለት ፡ በቀል ፡ ምስጋናውን ፡ አቅርቦ ፡ በሱ ፡ ምትክ ፡ ካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ የሚባለውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የእንግሊዝ ፡ ቆንስል ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ላከው ፡ በጥቅምም ፡ በፖለቲካም ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ጒዳይ ፡ በሱ ፡ በኩል ፡ ያከናውን ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ካፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ የጠበቀ ፡ መሆኑን ፡ ከተገነዘበ ፡ በኋላ ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ደግሞ ፡ በበኩሉ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከወንጌል ፡ ስብከት ፡ በቀር ፡ በፍጹም ፡ ወደ ፡ ፖለቲካ ፡ አልገባም ፡ የሚሄደውም ፡ ለጽድቅ ፡ ሲል ፡ በእግሩ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ነጮችም ፡

ኢትዮጵያውያንም ፡ በሚያደንቁት ፡ በአባ ፡ ያዕቆብ ፡ አማካይነት ፡ ባፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ላይ ፡ ከተነሡት ፡ ውስጥ ፡ በከፍተኛነት ፡ ይገመት ፡ ከነበረው ፡ ከደጃች ፡ ንጉሤ ፡ ጋራ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ በኩል ፡ ግዛቱን ፡ ለማስፋት ፡ ይላላክ ፡ ዠመር ። ደጃች ፡ ንጉሤም ፡ የፈረንሳዊን ፡ መንግሥት ፡ ድጋፍ ፡ ስላገኘ ፡ መሣሪያም ፡ ልካችሁ ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ ካፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በምዋጋበት ፡ ጊዜ ፡ ርዱኝ ፡ እንጂ ፡ የመሬት ፡ ነገር ፡ ግድ ፡ የለም ፡ በማለት ፡ ወዲያው ፡ ካንድ ፡ ለፔር ፡ ከሚባል ፡ ፈረንሳዊ ፡ ጋራ ፡ ደብዳቤ ፡ አሲዞ ፡ ወገኖቹ ፡ የሆኑትን ፡ መልክተኞች ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ናፖሊዮን ፡ ሦስተኛና ፡ ዘጠነኛው ፡ ፒዮስ ፡ ወደሚባለው ፡ የሮማ ፡ ጳጳስ ፡ የብር ፡ የበቅሎ ፡ ዕቃ ፡ የአንበሳ ፡ ቈዳና ፡ ሌላም ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ጨምሮ ፡ ላከላቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ደጃች ፡ ንጉሤን ፡ ከቴዎድሮስ ፡ ይልቅ ፡ የመላዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ መሆኑን ፡ ብታውቊለትና ፡ በማንኛውም ፡ ብትረዱት ፡ ለፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ጥቅም ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ጽፎ ፡ ለናፖሊዎን ፡ ሦስተኛ ፡ ልኮ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የደጃች ፡ ንጉሤ ፡ መልክተኞች ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ከምጥዋ ፡ ተነሥተው ፡ «ሜሳጄር ፡ እምፔሪያል» ፡ በሚባለው ፡ መርከብ ፡ በፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ሒሳብ ፡ ተጕዘው ፡ ባ1852 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ሮማ ፡ ደርሰው ፡ ለጳጳሱ ፡ የተላከውን ፡ ደብዳቤ ፡ ካስረከቡ ፡ በኋላ ፡ ሮማን ፡ ትተው ፡ በማርሴይ ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ደረሱ ። የፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ ናፖሊዮን ፡ መልክተኞቹን ፡ በመልካም ፡ አቀባበል ፡ ተቀብሎ ፡ ባስተርጓሚ ፡ ያስነበበው ፡ የደብዳቤውም ፡ ቃል ፡ እንደሀ ፡ የሜል ፡ ነው ፡ «የተላከ ፡ ከደጃች ፡ ንጉሤ ፡ ይድረስ ፡ ከግርማዊ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ ከናፖሊዎን ፡ ሦስተኛ ፡ ሰላም ፡ ለርስዎ ፡ ይሁን ። ኢትዮጵያ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዠምራ ፡ ወድቃ ፡ አሁን ፡ ለመነሣት ፡ የራሷ ፡ ኀይል ፡ ስለማይበቃት ፡ የፈረንሳዊን ፡ መንግሥት ፡ ርዳታ ፡ ትፈልጋለች ፡ ባገሬም ፡ ውስጥ ፡ ባለኝ ፡ ዐቅሜ ፡ የፈረንሳዊን ፡ ጥቅም ፡ ለመጠበቅ ፡ የተዘጋጀሁ ፡ መሆኔን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ልከው ፡ ቢያስመረምሩ ፡ ይረዱታል ። አሁንም ፡ በፊቱ ፡ ያለውን ፡ የካቶሊኮች ፡ ጠላት ፡ የሆነውን ፡ ቴዎድሮስን ፡ የምወጋበት ፡ መሣሪያና ፡ የሚረዳኝም ፡ ወታደር ፡ እንዲልኩልኝ ፡ እለምናለሁ ፡ ደግሞ ፡ ለማናቸውም ፡ አባ ፡ ያዕቆብን ፡ ይጠየቊ።»

የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመግባት ፡ ደጃች ፡ ንጉሤን ፡ ምክንያት ፡ ማግኘቱን ፡ በደብዳቤ ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ መሣሪያና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ካሥር ፡ መርከቦች ፡ ጋራ ፡ ለነዚሁ ፡ ዋና ፡ ኮንቴ ፡ ሩሴልን ፡ አድርጎ ፡ ለደጃች ፡ ንጉሤ ፡ በቶሎ ፡ እንዲደርሱለት ፡ አደረገ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ይኸንን ፡ ሁሉ ፡ አስቀድመው ፡ ወሬውን ፡ ከደኀና ፡ ምንጭ ፡ ሰምተው ፡ ነበርና ፡ እነዚህ ፡ ወታይሮች ፡ ከነመሣሪያቸው ፡ ለደጃች ፡ ንጉሤ ፡ ከመድረሳቸው ፡ በፊት ፡ እመንገድ ፡ አስደፍጠው ፡ ሊይዟቸው ፡ አስከብበዋቸው ፡ ነበር። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህኑ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ወታደሮች ፡ ካገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ልማድ ፡ ያለው ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ መንገድ ፡ ይመራቸው ፡ ነበርና ፡ ካቶሊካውያን ፡ ከሆኑት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ አድርጎ ፡ በሌሊት ፡ አምልጠው ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ እንዲሸሹ ፡ አደረገ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ደጃች ፡ ንጉሤን ፡ ለያዘልኝ ፡ ሰው ፡ ማንም ፡ ያልተሸለመውን ፡ ሽልማት ፡

እሸልመዋለሁ ፡ ብለው ፡ ራሳቸውም ፡ እያባረሩ ፡ እስከ ፡ ወልቃዩት ፡ ድረስ ፡ ገሠገሡ። ደጃች ፡ ንጉሤም ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፡ ከነወንድሙ ፡ ባ1852 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተማረከ ። ወዲያውም ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የንጉሤን ፡ ጭፍራ ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ እየቈረጡ ፡ ከቀጡት ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ንጉሤን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ በደስታ ፡ ሲመለሱ ፡ የመልካቸው ፡ ቊንዥና ፡ በደም ፡ ግባት ፡ የተዋበውን ፡ የደጃች ፡ ውቤን ፡ ልጅ ፡ ወይዘሮ ፡- ጥሩ ፡ ወርቅን ፡ በሥርዐት ፡ አገቡ ። ከርሳቸውም ፡ ዓለማየሁ ፡ የሚባል ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለዱ ። በዚሁም ፡ ዓለማየሁ ፡ በተወለደበት ቀን ፡ ስለ ፡ ደስታ ፡ በጥፋት ፡ የታሰሩ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ እሥረኞች ፡ ተለቀቀ ፡ ይባላል።

# ምዕራፍ ፡ 9።

## <u>የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ የማስፋፋት ፡ አሳባቸው ፡ --ወደ ፡ ንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ የላኩት ፡ ደብዳቤ ።</u>

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታላላቅ ፡ መሳፍንት ፡ መዠመሪያ ፡ ከመንገሣቸው ፡ በፊት ፡ በየተራ ፡ እየጣሉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ አንድነት ፡ መሠረቱ ። ቀጥሎም ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ በያለበት ፡ ቢሸፍትባቸው ፡ እንደዚሁ ፡ እየተከታተሉ ፡ ካጠፉ ፡ በኋላ ፡ አሳባቸውን ፡ ምጥዋን ፡ ወደ ፡ ያዙት ፡ ወደ ፡ ቱርኮችና ፡ ወደ ፡ ግብጾች ፡ አቀኑ ፡ እነዚህንም ፡ ለመውጋት ፡ የራሳቸው ፡ ኀይል ፡ በቂ ፡ አለመሆኑን ፡ ወይም ፡ ሕዝባቸው ፡ ሊያብርላቸው ፡ አለመቻሉን ፡ ገምተው ፡ ሌላ ፡ የውጭ ፡ ክርስቲያን ፡ የሆነ ፡ መንግሥት ፡ ረዳት ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ከፈረንሳዊና ፡ ይልቊንም ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግ ፡ ከቆንስሉ ፡ ከካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ ተነጋግረው ፡ ለእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ደብዳቤ ፡ ለመላክ ፡ አሰቡ ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ ባንድነት ፡ በሦስትነት ፡ እግዚአብሔር ፡ መርጦ ፡ ያነገሠው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ቢክቶሪያ ። እንዴት ፡ አሉ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደኅና ፡ ነኝ ። እስተ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አባቶቼ ፡ ነገሥታቱ ፡ ፈጣሪአችነን ፡ ቢበድሉት ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለጋላና ፡ ለቱርክ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶባቸው ፡ ነበረ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ከተወለድሁ ፡ ፈጣሪየ ፡ ካመድ ፡ አንሥቶ ፡ ኃይል ፡ ሰጥቶ ፡ ባባቶቼ ፡ መንግሥት ፡ አቆመኝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ጋሎችን ፡ (ራስ ፡ አሊን ?) ፡ አስለቀቅኋቸው ፡ ቱርኮች ፡ ግን ፡ ያባቶቼን ፡ መሬት ፡ ልቀቁ ፡ ብላቸው ፡ እምቢ ፡ ብለውኝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ይኸው ፡ ልታገል ፡ ነኝ። እነአቶ ፡ ቡላዲን ፡ (ጥለውዲን) ፡ እነሊቀ ፡ መኳስ ፡ ዮሐንስ ፡ (ዮሐንስ ፡ ቤል) ፡ የክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡ ታላቅ ፡ ሰው ፡ ክርስቲያን ፡ የሚወዱ ፡ አሉ እናስተዋውቅህ ፡ አለን ፡ እያሉኝ ፡ እጅግ ፡ እወዳቸው ፡ ነበረ ፡ የርስዎን ፡ ወዳጅነት ፡ ያገኘሁ ፡ እየመሰለኝ ። ሞት ፡ አይቀርምና ፡ የጠሉኝ ፡ ሰዎች ፡ እኔን ፡ ይከፋው ፡ ሲሉ ፡ ገደሉአቸው ፡ እኔም ፡ በእግዚኦጦሔር ፡ ኃይል ፡ ደመኞቹን ፡ ፩ ፡ ሳልተው ፡ ፈጀኋቸው ፡ የገዛ ፡ ዘመዶቼን ። በአግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ የርስዎን ፡ ዝምድና ፡ ስፈልግ ። ቱርኮች ፡ ከባሕር ፡ ላይ ፡ ሁነው ፡ መልከተኛየን ፡ አናሳልፍ ፡ ብለው ፡ ቸግሮኝ ፡ ሳለ ፡ ቆንስል ፡ ኬምሮን ፡ (ካሜሮን) መጣልኝ ፡ ወረቀትና ፡ የፍቅር ፡ በረከት ፡ ይዞ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ ደህንነትዎንና ፡ ፍቅርዎን ፡ ብሰማ ። የሰደዱልኝንም ፡ የፍቅር ፡ በረከት ፡ (ስጦታ) ፡ ተቀበልሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ። አሁንም ፡ መልክተኛየን ፡ ከቆንስል ፡ ኬምሮን ፡ ጋር ፡ የፍቅር ፡ በረከት ፡ ይዞ ፡ እንዳልሰደው ፡ ቱርኮች ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የማያስተላልፉልኝ ፡ ሆነ ፡ አሁንም ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ ስፍራ ፡ እከሌ ፡ ይቀበለው ፡ ብለው ፡ ይላኩብኝ ። ምላሹን ፡ ቆንስል ፡ ካሜሮን ፡ ይዞልኝ ፡ ይምጣ ። እናንተም ፡ ተገፉልኝ ፡ ክርስቲያኑን ፡ እስላም ፡ አጠቃህ ፡ ሲለኝ ፡ (እስላሙ ፡ ሲያጠቃኝ ፡ ግፌን ፡ ተመልከቱልኝ) ፡ ተጻፈ ፡ በሰባት ፡ ሺ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ አምስት ፡ ዘመን ፡ በሉቃስ ፡ በወርኃ ፡ ጥቅምት ፡ በ፳ ፡ ቀን ፡ ጐጃም ፡ በይባባ ፡ ከተማ።



NIGUSS DIGITAL LIBRARY

ለፈረንሳዊ ፡ ንጉሥም ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ ባርዲል ፡ በሚባል ፡ በፈረንሳዊ ፡ በኩል ፡ ልከው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ አሳቡ ፡ ከሚቼ ፡ ከንጉሤ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ባለው ፡ አስተያየት ፡ አልተመለከተውም ። ለንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ የላኩትን ፡ ደብዳቤ ፡ ግን ፡ ካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ሄጄ ፡ ሰጥቼ ፡ የተካከለ ፡ መልስ ፡ አመጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ከተቀበላቸው ፡ በኋላ ፡ ወረቀቱን ፡ አዘግይቶ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ሎንዶን ፡ በመላክ ፡ ፈንታ ፡ ወደ ፡ አደን ፡ ስለ ፡ ላከው ፡ ከብዙ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሎንዶን ፡ ደረሰ ። ራሱም ፡ ካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ ከጐንደር ፡ ወደ ፡ ሎንዶን ፡ ለመሄድ ፡ ተነሥቶ ፡ ሲጓዝ ፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ከረን ፡ ከከረን ፡ ወደ ፡ ከሰላ ፡ ከዚያም ፡ ታመምሁ ፡ ብሎ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ነበሩበት ፡ ወደ ፡ ደንቢያ ፡ ተመለሰ። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ግን ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ እንረዳኻለን ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ሄዶ ፡ ያመጣ ፡ መስሏቸው ፡ ቢጠይቁት ፡ እንኳን ፡ ርዳታና ፡ ለደብዳቤያቸውም ፡ መልስ ፡ ሳይሰጣቸው ፡ በመቅረቱ ፡ የእንግሊዝና ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ የተስማሙባቸው ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፡ በጣም ፡ አዘኑ ። ይኸውም ፡ የእንግሊዝና ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የጠብ ፡ ምንጭ ፡ መሆኑን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ የጻፉ ፡ አረጋግጠዋል ። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ አንድነት ፡ ከመሠረቱ ፡ በኋላ ፡ ግዛታቸውን ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ለማድረስና ፡ ከዚያም ፡ አልፈው ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ለመግዛት ፡ የየቀኑ ፡ አሳባቸው ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ ሕዝቡም ፡ በየድግሱና ፡ በየበዓሉ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ እየዘፈነ ፡ ያደፋፍራቸው ፡ ነበር።

ታጠቅ ፡ ብሎ ፡ ፈረስ ፡ ካሳ ፡ ብሎ ፡ ስም ፡
ዐርብ ፡ ዐርብ ፡ ይሸበራል ፡ ኢየሩሳሌም ።

አንተም ፡ ጌታ ፡ አይደለህ ፡ እኔም ፡ ሎሌ ፡
የየሩሳሌም ፡ ሰው ፡ ካልጫኜ ፡ በርሞሌ።
አባ ፡ ታጠቅ ፡ ካሳ ፡ ነገር ሲያሰላስል ፡
ባሕሩን ፡ ያስባል ፡ መረብ ፡ ጣይ ፡ ይመስል።

የታጠቅ ፡ ፈረሶች ፡ እንዴት ፡ ያሽካካሉ ፡
ባሕር ማዶ ፡ ጨፌ ፡ መልቀም ፡ ያስባሉ።

በሱ ፡ አልተዠመረ ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ መሄድ ፡
ሴቷ ፡ እንኳ ፡ ማከዳ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ስትወርድ ።

አበሻ ፡ በመላው ፡ ምን ፡ ያጉመተምታል ፡
በመርከብ ፡ ተሻግሮ ፡ ገና ፡ ባሕር ፡ ይዘምታል።

የታጠቅ ፡ ጐራዴ ፡ ብረት ፡ የነበረ ፡
እየቀላ ፡ ሄደ ፡ ደም ፡ እየመስለ ፡ (ቱርክ ፡ እየመሰለ) ።

ፈረሱ ፡ አባ ፡ ታጠቅ ፡ ስሙ ፡ ቴዎድሮስ ፡

ጠላት ፡ የሚበትን ፡ እንዳውሎ ፡ ነፋስ ።

ታጠቅን ፡ ባል ፡ ብሎ ፡ ማን ፡ አምኖ ፡ ይቈርባል ፡
ሴሰኛውን ፡ ኊበዝ ፡ ያራቱን ፡ ማዕዘን ፡ ባል ።

የሸዋ ፡ የጐጃም ፡ የወሎ ፡ የትግሬ ፡ ተበትኖ ፡ ከብቱ ፡
ገዛው ፡ አባ ፡ ታጠቅ ፡ ሰብስቦ ፡ በሀብቱ።

ራሳቸውም ፡ ደስ ፡ ባላቸው ፡ ቀን ፡ «መይሳው ፡ ካሳ ፡ ባጭር ፡ ታጣቂ ፡ ዘመድ ፡ ከዘመድ ፡ አደባላቂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባል ፡ የኢየሩሳሌም ፡ እጮኛ» ፡ እያሉ ፡ ይፎክሩ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ በዚህ ። አሳባቸው ፡ ላይ ፡ ተስፋ ፡ ያደረጉት ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ሳይተባበርላቸው ፡ ቀረ። እሱ ፡ እንኳ ፡ ቀርቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አውራጃ ፡ በጐጃም ፡ በጐንደር ፡ በትግሬ ፡ በሸዋ ፡ ያለው ፡ ባላባት ፡ ከነሕዝቡ ፡ ቢያብርላቸው ፡ ኖሮ ፡ ወዲያው ፡ ጦርነት ፡ አንሥተው ፡ አሰቡበት ፡ ዳካ ፡ ለመድረስ ፡ ሳይጠጉ ፡ አይቀሩም ፡ ነበር።

# ምዕራፍ ፡ 10።

## የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ብስጭት ፡ --የካፒቴን ፡ እስራትና ፡ ራሳም ፡ ተልኮ ፡ እንደ ፡ መጣ ።

በትግሬ ፡ ደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ (ዐፄ ፡ ዮሐንስ) ፡ በላስታ ፡ ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጐበዜ ፡ (ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ) ፡ በሸዋ ፡ ከመቅደላ ፡ ያመለጡት ፡ ምኒልክ ፡ (ዐፄ) ፡ ሌሎቹም ፡ ባላባቶችና ፡ ሹማምቶች ፡ በዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ላይ ፡ ተነሡባቸው ። ለዚሁም ፡ የሚወዷቸው ፡ ባለቤታቸው ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ሞተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የሚጽናኑበት ጠፋ።

ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ (ካ1856) ፡ ከብስጭት ፡ የተነሣ ፡ ራሳቸው ፡ እንደ ፡ ዞረ ፡ ያኸል ፡ ሆኑ። አንዳንድ ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ታሪክ ፡ የጻፉ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ያለፍርድ ፡ እየገደሉ ፡ ከሕግ ፡ የወጡት ፡ ሰው ፡ መድኃኒት ፡ አቅምሷቸው ፡ ነው ፡ ይላሉ። መድኀኒት ፡ ያቀመሳቸው ፡ ግን ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይታወቅም ። ይኸውም ፡ እንዳይባል ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ በሚያፈሱበትና ፡ ከእንግሊዝም ፡ ጋራ ፡ በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ ይናገሩት ፡ የነበረው ፡ ንግግር ፡ መድኀኒት ፡ ከቀመሰ ፡ ይልቅ ፡ አእምሮ ፡ ትክክል ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ የተሻለ ፡ ነበር ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በመድኀኒትም ፡ ቢሆን ፡ ያለመድኀኒትም ፡ ቢሆን ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ አንሥተው ፡ ከጳጳሱም ፡ ከካህሀናቱም ፡

ከመኳንንቱም ፡ ከተራው ፡ ሕዝብም ፡ ከነጭም ፡ ጠበኛ ፡ ሆኑ ፡ በፊታቸውም ፡ በታማቾኝነት ፡ የሚገምመት ፡ ጠፉ።

ካህፍቱን ፡

ይህ ፡ አርግራጊ ፡

አቴና ፡ ወጊ ፡

ራሱን ፡ ታጣቂ ፡

ወገቡን ፡ ሰባቂ ፡

እያሉ ፡ ይዘልፉት ፡ ዠመር።

ካንዱ ፡ አገር ፡ ወዳንዱ ፡ አገር ፡ ሲዘዋወሩ ፡ በከበሮ ፡ በጽናጽል ፡ ሊቀበላቸው ፡ የሚመጣውን ፡ ካህን ፡ በወታደር ፡ እያለከበቡ ፡ በጥይት ፡ ያስደበድቡት ፡ ዠመር ። ጳጳሱንም ፡ ተጣልተው ፡ በግዞት ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ሰደዷቸው ፡ ባጠገባቸው ፡ የነበሩትንም ፡ ነጮች ፡ ይልቁንም ፡ ካሜሮንን ፡ አንተ ፡ ነኽ ፡ የከዳኸኝ ፡ ብላው ፡ ሁሉንም ፡ አሰሯቸው ። ስለዚህ ፡ የካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ መታሰር ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ በአደን ፡ ምክትል ፡ የፖለቲካ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የነበረው ፡ ሆርሙዝድ ፡ ራሳም ፡ የሚባለው ፡ የሜስፖውታሚያ ፡ ተወላጅ ፡ የአፍሪቃ ፡ ምሥራቅን ፡ አገር ፡ ጠባይና ፡ ባህል ፡ ያውቃል ፡ በማለት ፡ ተመርጦ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሄይዶ ፡ በዕርቅ ፡ እስረኞቹን ፡ አስፈትቶ ፡ እንዲመለስ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ አሲዞ ፡ ላከው። ራሳምም ፡ አገርዎን ፡ ለመጐብኘት ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ተልኬ ፡ እመጣጸለሁና ፡ እንዲፈቀድልኝ ፡ ብሎ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ለንጉሡ ፡ ላከባቸው። ንጉሡም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ የላኩት ፡ ደብዳቤ ፡ መልስ ፡ ሳያገኝ ፡ የቀረውን ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ ሲሉ ፡ በፍጹም ፡ መልስ ፡ ሳይሰጡት ፡ ቈይተው ፡ ባመቱ ፡ 3ኛ ፡ በላከባቸው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ፈቃዳቸው ፡ መሆኑን ፡ ካስታወቀኑት ፡ በኋላ ፡ ራሳምና ፡ ተከታዮቹ ፡ በትግሬ ፡ የሸፈቱት ፡ አደጋ ፡ እንዳያደርጉባቸው ፡ ክአደን ፡ በካይሮ ፡ ዞረው ፡ በሱዳን ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ መተማ ፡ ደረሱ።

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ መተማ ፡ መድረሳቸውን ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ሰሙ ፡ ተቀባይ ፡ ላኩ ። መልክተኞቹ ፡ ንጉሡ ፡ እነበሩበት ፡ እዳሞት ፡ ድረስ ፡ ይዘዋቸው ፡ መጥተው ፡ ተገናኙ ። ወዲያውም ፡ ካሜሮንን ፡ ያሰሩበት ፡ ምክንያት ፡ የሚገባቸውን ፡ ክብር ፡ በማጉደል ፡ መሆኑን ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ የንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ ደብዳቤ ፡ ከመጣልኝ ፡ እለቃለሁ ፡ ብለው ፡ እስረኞቹን ፡ ፈተው ፡ አስረከቡት ። እሱም ፡ እነሱን ፡ ይዞ ፡ ወዳግሬ ፡ እሄዳለሁና ያሰናብቱኝ ፡ ብሎ ፡ አሰናብተውት ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የተላላከው ፡ ከቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ተስማምቶ ፡ ለእስረኞች ፡ ነፃነት ፡ ሲል ፡ ኖሯልን ፡ በማለት ፡ ተጠራጥረው ፡ አሰናብተዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ ነጮች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መልሰው ፡ ሁሉንም ፡

አሰሯቸው ። የታሠሩትም ፡ ራሱ ፡ ቆንሲሉ ፡ ካሜሮን ፡ አዲስ ፡ መልክተኛ ፡ ራሳም ፥ ፍላድ ፥ ፐሪዶ ፥ ብላንክ ፥ ኮራንስ ፥ ፒየትሮስቲርን ፥ ባርዴል ፥ ኤስሌር ፥ ሮዚንታል ፡ ከሚስቱና ፡ ክልጁ ፡ ጋር ፡ ክነዚህም ፡ በቀር ፡ በድምሩ ፡ 40 ፡ የሚሆኑ ፡ አሉ። ቀጥሎም ፡ ባገሬ ፡ ውስጥ ፡ መድፍና ፡ ጠመንዣ ፡ የሚሠራበት ፡ ቤት ፡ ለማቆም ፡ በጋፋት ፡ ዥምሪያለሁና ፡ የዚህን ፡ ሥራ ፡ የሚያውቁ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች፡ ከነመሣሪያቸው ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ካላከልኝ ፡ እነዚህን ፡ እስረኞች ፡ ለመልቀቅ ፡ አልችልም ፡ ብለው ፡ ስላስታወቁ ፡ ይኸንኑ ፡ ራሳም ፡ በደብዳቤ ፡ አድርጎ ፡ ፍላድ ፡ የሚባለውን ፡ የጀርመኑን ፡ ተወላጅ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ላከው ። የነዚህም ፡ መልክተኞች ፡ እስራት ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሁለተኛ ፡ ሲሰማ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በዓለም ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ ታላቅ ፡ የተከበረ ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሥራ ፡ ክብሩን ፡ የሚያዋርድበት ፡ በመሆኑ ፡ ይፈቱ ፡ እንደሆን ፡ ይፍቱ ፡ አለዚያ ፡ ወገኖቻችንን ፡ በጦር ፡ ኀይል ፡ እንፈታቸዋለን ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ አሲዞ ፡ ፍላንድን ፡ መልሶ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ላከ ። ፍላንድም ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ መልክቱን ፡ ነግሮ ፡ የእንግሊዝን ፡ መንግሥት ፡ ታላቅነት ፡ እየገለጸ ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ እንዳይዋጉ ፡ በወዳጅነት ፡ ለዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሲያስረዳቸው ፡ ንጉሡ ፡ ግን ፡ የጦርነት ፡ ድል ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በታላቅነት ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ መልስ ፡ ሰጥተው ፡ ለጦርነት ፡ ይዘጋጁ ፡ ዠመር።

የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የታሰሩትን ፡ እስረኞች ፡ በጦርነት ፡ እንጂ ፡ በመላክትና ፡ በገጸ ፡ በረከት ፡ ማባባል ፡ ለማስፈታት ፡ አለመቻሉን ፡ ስለ ፡ ተረዳው ፡ ግድ ፡ ጦርነት ፡ ማስፈለጉን ፡ ሎንዶን ፡ ያለው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ቊረጠ። ስለዚህ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ መዠመሪያ ፡ በፐሎውዴን ፡ ቀጥሎ ፡ በካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ በኮንት ፡ ሩሴል ፡



እስረኞቹ

ኮራንስ ፥ ራሳም ፥ ስቲርንና ፕሪዶ ፥ ሙሴ ሮዜንታል ፡ ከሚስቱና ከልጁ ጋር ብላንክ ፥ ጴጥሮስ ፥ ካሜሮን

በኩል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ ክብርና ፡ ጥቅም ፡ በማበላለጥ የፖለቲካ ፡ ግድያ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ የሁለቱም ፡ መንግሥት ፡ የፖለቲካ ፡ እርምጃ ፡ በደጃች ፡ ንጉሤ ፡ መሞትና ፡ በካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ እስራት ፡ ተደናቀፈ ።

# ምዕራፍ ፡ 11

## ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ በግፍ ፡ እንዳፈሰሱ ።

የጐጃም ፡ ገዥ ፡ ደጃች ፡ ተድላ ፡ ጓሉ ፡ የሚባሉት ፡ ከመሞታተቸው ፡ በፊት ፡ ሸፍተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከርሳቸው ፡ ጦር ፡ የተማረከውንና ፡ ርሳቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ አስተናግዷል ፡ የተባለውን ፡ አገር ፡ ሕዝቡን ፡ ሰብስበው ፡ እጅና ፡ እግሩን ፡ እየቈረጡ ፡ ፈጁት ። ከመቅደላ ፡ የምኒልክን ፡ ማምለጥ ፡ እንደ ፡ ሰሙ ፡ የታሰሩትን ፡ የወሎ ፡ መኳንንቶችና ፡ የወይዘሮ ፡ ወርቂትን ፡ ልጅ ፡ አምጡልኝ ፡ ብለው ፡ እጅና ፡ እግራቸውን ፡ እየቈረጡ ፡ ገደል ፡ ያስጥሏቸው ፡ ዠመር ። ወደ ፡ ዘጌም ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ የባላገሩን ፡ ቤት ፡ እየበረበሩ ፡ ከቤቱ ፡ ዕቃው ፡ ተዘርፎ ፡ ሲያልቅ ፡ በጓሮው ፡ ያለውን ፡ አታክልት ፡ እየጨፈጨፉ ፡ እንዳይበቅል ፡ ከሥሩ ፡ አስነቀሉት ። ቊሙንም ፡ ከብት ፡ ከበጌምድር ፡ ባላገር ፡ ዘርፈው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ አምጥተው ፡ ለወታደሮቻቸው ፡ አከፋፈሉት ። ደግሞ ፡ የሜጫና ፡ የአገው ፡ መኳንንት ፡ የከዳት ፡ ነገር ፡ ተገኝቶባቸው ፡ 400 ፡ የሚሆኑ ፡ ተይዘው ፡ እኽልና ፡ ውሃ ፡ እንዳያገኙ ፡ ተከልክለው ፡ ነበርና ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ወሰን ፡ ቢሰውር ፡ የሚባል ፡ ባለባት ፡ እባክዎ ፡ ጃንሆይ ፡ 500 ፡ ብር ፡ ከፍዬ ፡ አንድ ፡ ዋንጫ ፡ ውሃ ፡ ልጠጣ ፡ ብሎ ፡ ለምኖ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሊያገኝ ፡ አልቻለምና ፡ በውሃ ፡ ጥም ፡ ሞተ ። ሚስቱም ፡ እንደዚህ ፡ ብላ ፡ አለቀሰችለት ፡ ይባላል። ፡

ጌታ ፡ የጌታው ፡ ልጅ ፡ ወሰን ፡ ቢሰውር ፡
ውሃ ፡ ልግዛ ፡ ይላል ፡ ባምስት ፡ መቶ ፡ ብር።

ቀጥሎም ፡ በጥፋትም ፡ ያለጥፋትም ፡ የሚያዘውን ፡ ሰው ፡ ወንዱንም ፡ ሴቱንም ፡ ሕፃኑንም ፡ ባንድነት ፡ እየሰበሰቡ ፡ ሰቀላ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እያገቡ ፡ ቤቱን ፡ ከውጭ እየዘጉ ፡ አዲስ ፡ ቅጣት ፡ ፈጥረው ፡ ያቃጥሉት ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ በመንገድ ፡ የሚሄደው ፡ ሲያርስም ፡ የተገኘው ፡ እየተሰበሰበ ፡ ያለጥፋት ፡ ተደበደበ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አልቃሽ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ገጠመች ።

ሞጣ ፡ ቀራንዮ ፡ ምነው ፡ አይታረስ ፡
በሬሳ ፡ ላይ ፡ መጣሁ ፡ ከዚያ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ።

በሰንሰለት ፡ ታስሮ ፡ ዓመት ፡ ካራት ፡ ወር ፡ -

ማንን ፡ ዋስ ፡ አገኝቶ ፡ ተፈታ ፡ ጐንደር ።

አንጥረኛው ፡ ብዙ ፡ ከንጉሡ ፡ ቤት ፡
ባላልቦ ፡ አደረጉት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሴት።

ወንድሟና ፡ አባቷ ፡ በግፍ ፡ የተሰቀሉባት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ከንዴት ፡ የተነሣ ፡ ቢገድሉኝም ፡ ይግደሉኝ ፡ ስትል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ገጠመች

ጠጅም ፡ እንዳያምረኝ ፡ ድሮ ፡ ጠጥቻለሁ ፡
ሥጋም ፡ እንዳያምረኝ ፡ ቋንጣ ፡ ሰቅያለሁ ፡
ቢሻኝ ፡ ከወንድሜ ፡ ካባቴ ፡ እበላለሁ።
አንድ ፡ እግር ፡ በርበሬ ፡ መንቀል ፡ አቅቷችሁ ፡
አንድዶ ፡ ለብልቦ ፡ አቃጥሎ ፡ ይፍጃችሁ።

ሺ ፡ ፈረስ ፡ ከኋላው ፡ ሺ. ፡ ፈረስ ፡ ከፊቱ ፡
ሺ. ፡ ብረት ፡ ከኋላው ፡ ሺ ፡ ብረት ፡ ከፊቱ ፡
ይህን ፡ ሳታይ ፡ ሞተች ፡ ኮሶ ፡ ሻጭ ፡ እናቱ።

ይህንን ፡ ሲሰማ ፡ ያጕራል ፡ ላመሉ ፡
ማናትም ፡ ቢላችሁ ፡ ምንትዋብ ፡ ናት ፡ በሉ።

ይህችም ፡ ሴት ፡ ተይዛ ፡ እንጉሡ ፡ ፊት ፡ ከቀረበች ፡ በኋላ ፡ በኔ ፡ እጅ ፡ ሞተሽ ፡ ሰማዕትነት ፡ ለመቀበል ፡ አስበሻልና ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ አልገድልሽም ፡ ብለው ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ አሰናበቷት ፡ ይባላል።

# ምዕራፍ ፡ 12።

## ዐፄ ፡ ቴዎድርስ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ እንደ ፡ ተጓዙ ፡ --እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ አባታቸውን ፡ እንደ ፡ ተረዱ።

ንጉሡ ፡ በበጌምድር ፡ ሳሉ ፡ ወታደሮቻቸው ፡ የዘረፉትን ፡ እኽልና ፡ ከብት ፡ ጦርነት ፡ በሚያደርጉበት ፡ ጊዜ ፡ ሥንቅ ፡ እንዲሆናቸው ፡ ከብቱን ፡ እያለነዱ ፡ እኽሉንም ፡ ወታደር ፡ ጭኖ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ተጓዙ። ደብረ ፡ ታቦርም ፡ ደርሰው ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ጋራ ፡ በሚዋጉበት ፡ ቀን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ማረፊያና ፡ መዋጊያ ፡ ስፍራ ፡ እንዲሆናቸው ፡ መቅደላን ፡ ገና ፡ አስቀድመው ፡ ባሳባቸው ፡ መድበውት ፡ ነበርና ፡ አራት ፡ ሺሕ

፡ ብረት ፡ በያዘ ፡ የጦር ፡ ሠራዊትና ፡ ስልሳ ፡ ሺሕ ፡ በሚሆን ፡ ተከታይ ፡ ሕዝብ ፡ ታጅበው ፡ በጋፋት ፡ ያሠሩትን ፡ መድፍ ፡ በከብትና ፡ በሰው ፡ ትከሻ ፡ እያለጉተቱ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ሲጓዙ ፡ የባለቤታቸው ፡ የእቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ አባት ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ሞቱ። መርዶውም ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ በማለዳ ፡ ለእቴጌይቱ ፡ ከተነገረ ፡ በኋላ ፡ ይለቀስ ፡ ዠመር ። በዚህ ፡ ለጦርነት ፡ በሚዘጋጁበት ፡ ጊዜ ፡ በጦርነትም ፡ በዘረፋም ፡ በጉዞም ፡ ዘመዴ ፡ ሞተ ፡ ብሎ ፡ ማንም ፡ እንዳያለቅስ ፡ ተከልክሎ ፡ ነበርና ፡ በደጃች ፡ ውቤ ፡ መርዶ ፡ ምክንያት ፡ ሲለቀስ ፡ ሁሉም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ የሞተውን ፡ ዘመዱን ፡ እያለታወሰ ፡ ስላለቀሰ ፡ አንዲት ፡ የበጌምድር ፡ አልቃሽ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ አለቀሰች።

የኔታ ፡ ደጃዝማች ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ደግነት ፡
ዛሬ ፡ እንኳ ፡ ለድኻው ፡ እንባ ፡ አተረፉለት።

የኅዘኑም ፡ ቀን ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የሚያስቸግረውን ፡ መንገድ ፡ በብርታትና ፡ በግሥጋሤ ፡ አልፈው ፡ መቅደላ ፡ ደረሱ ። በጉዞውም ፡ ጊዜ ፡ ያንዱን ፡ ባላገር ፡ ከብትና ፡ የሚወዳትን ፡ ሚስቱን ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ ቀምቶ ፡ ስለ ፡ ወሰደበት ፡ ላቤቱታ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሄዶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንጋጦ ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ ሲል ፡ ንጉሡ ፡ ሰምተው ፡ ለምን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታሳጣኛለኽ? እኔ ፡ ብሞት ፡ ትወዳለኽን ? ቢሉት ፡ «ጃንሆይ ፡ እባክዎ ፡ አያስጕምጁኝ ፡ » ብሎ ፡ መለሰላቸው ፡ ይባላል ። እሳቸውም ፡ ይህን ፡ ንግግር ፡ ከብስጭትና ፡ ከንዴት ፡ የተነሣ ፡ መሆኑን ፡ አመዛዝነው ፡ ሊቀጡት ፡ አልፈለጉም።

ወዲያውም ፡ መቅደላ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ እስረኛውን ፡ እፊታቸው ፡ እያቀረቡ ፡ ኀጢአቱ ፡ የቀለለውን ፡ በነፃ ፡ ሲለቁ ፡ ኀጢአቱ ፡ የከበደውንና ፡ የከዳቸውን ፡ እመቅደላ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ እያወጡ ፡ ገደል ፡ ያስጥሉት ፡ ጀመር ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በመንገድ ፡ የሚያልፍ ፡ አንድ ፡ መነኩሴ ፡ መንገዱን ፡ ትቶ ፡ ይህን ፡ ጉድ ፡ አያለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲጠጋ ፡ እሱንም ፡ አሲዘው ፡ ገደል ፡ ሰደዱት።

# ምዕራፍ ፡ 13።

## የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መምጣት ።

የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ለሚልከው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፡ ጄኔራል ፡ ሮቤርት ፡ ከርኔሌስ ፡ ናፒየር ፡ የሚባለውን ፡ ሾመ። ጄኔራል ፡ ናፒየርም ፡ ከልጅነቱ ፡ ዠምሮ ፡ በህንድ ፡ አገር ሲኖር የወታደርነትና ፡ የመሐንዲስነት ፡ ትምህርት ፡ የተማረ ፡ ነው ። ህንዶች ፡ በሸፈቱም ፡ ጊዜ ፡ ደኅና ፡ ሙያ ፡ ሠርቶ ፡ ነበርና ፡ ስሙና ፡ ዝናው



Sir Robert Napier, British commander

፡ በእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ነበር። ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ወታደር ፡ ለማምጣት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የስዌዝ ፡ በር ፡ አልተከፈተም ፡ ነበርና ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ የእንግሊዝ ፡

ስምንት ፡ ሺህ ፡ የህንድ ፡ ወታደሮች ፡ ይዞ ፡ ከህንድ ፡ ወደ ፡ ዙላ ፡ (ዙላ ፡ በምጥዋ ፡ አጠገብ ፡ ያለ ፡ የጥንት ፡ የወደብ ፡ ከተማ ፡ ነው) ፡ መጥቶ ፡ ሰፈረ ።



## የዙላ ወደብ

ከነዚህ ፡ ወታደሮች ፡ በቀር ፡ መንገድና ፡ ድልድይ ፡ የሥሩ ፡ ሚሥንቅና ፡ መሣሪያ ፡ የሚያግዙ ፡ ኻያ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ። ዙላም ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ የሚያደርሰውን ፡ መንገድ ፡ ሲመርጡ ፡ ወዲያው ፡ ከዙላ ፡ ወደ ፡ ሰናዓፌ ፡ የሚወስድ ፡ የጥንት ፡ ስልት ፡ መንገድ ፡ አገኙ ። ከዙላ ፡ እስከ ፡ ሰናዓፌ ፡ ርቀቱ ፡ መቶ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ነው።



## የዙላ ዲፖት

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በንጉሡ ፡ በዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ላይ ፡ ከሸፈቱት ፡ ከትግሬ ፡ ሹማምቶች ፡ ከነደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ ከላስታው ፡ ከነዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጐበዜ ፡ መላላክ ፡ ዠምረው ፡ የትግሬና ፡ የላስታ ፡ ሕዝብም ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደር ፡ መምጣት ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ መንገድ ፡ እየመራ ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ ይረዳቸው ፡ ዠመር ። እንግሊዞችም ፡ በሺሕ ፡ 880 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ በሙሉ ፡ ተጓዘው ፡ ከዙላ ፡ ተነሥተው ፡ እስከ ፡ ሰናዓፌ ፡ ሲደርሱ ፡ ምንም ፡ መንገዳቸውን ፡ የሚያሰናክል ፡ ነገር ፡ አልገጠማቸውም ። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እንኳን ፡ ጦር ፡ በላያቸው ፡ ሲመጣና ፡ በላያቸው ፡ ጦር ፡ ለማድረግ ፡ የሚዘጋጀውን ፡ አለበት ፡ ድረስ ፡ እየገሠገሠ ፡ ሄደው ፡ ድል ፡ ሲያደርጉ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወታደር ፡ ከድቷቸው ፡ እግዚአብሔርና ፡ ሕዝብም ፡ እንደ ፡ ጠላቸው ፡ ተረድተው ፡ የሚመጣብኝን ፡ እዚሁ ፡ እመክታለሁ ፡ ብለው ፡ እዚያው ፡

እመቅደላ ፡ ምሽግ ፡ ተቀመጡ ፡ እንጂ ፡ ሄደው ፡ ለመግጠም ፡ ወይም ፡ የደፈጣ ፡ አደጋ ፡ አድርገው ፡ የጠላታቸውን ፡ እርምጃ ፡ ለማሰናከል ፡ አልቻሉም ። ጄኔራል ፡ ናፒየር ፡ ሰናዓፌ ፡ ሆኖ ፡ ከትግሬና ፡ ከላስታ ፡ ሹማምት ፡ ጋራ ፡ ስምምነቱን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በነሱ ፡ እየተረዳ ፡ ከሰናዓፌ ፡ በአጋሜና ፡ በአሸንጌ ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ በዋድላ ፡ አጠገብ ፡ ካለው ፡ ሣንሣራ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ደረሰ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ውድቀት ፡ የሚመኘው ፡ መኳንንትና ፡ ሹማምት ፡ ከነወታደሩ ፡ እየተሰበሰበ ፡ በእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጕን ፡ ይሰለፍ ፡ ነበር።



<u>የእንግሊዝ የጦር ካምፕ</u>




<u>የእንግሊዝ ጦር</u>

# ምዕራፍ ፡ 14።

## የአሮጌ ፡ ጦርነት ፡ --የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዕረፍት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጄኔራል ፡ ናፒየር ፡ ዋድላ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ የታሰሩትን ፡ እስረኞች ፡ ፈተው ፡ ይላኩልኝ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ለዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ልኮባቸው ፡ መልስ ፡ ሳይሰጡት ፡ ስለ ፡ ቀሩ ፡ ከነጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ዋድላን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ደላንታ ፡ መጣ። በዚህም ፡ በደላንታና ፡ ዐፄ ፡ ዐቴዎድሮስ ፡



የአሮጌ ፡ ጦርነት

ባሉበት ፡ ምሽግ ፡ መካከል ፡ በሽሎ ፡ የሚባለው ፡ ወንዝ ፡ ነበር ። ከወንዙ ፡ በደቡብ ፡ ወገን ፡ በእሮጌ ፡ ትይዩ ፡ ያለውን ፡ ፉህላ ፡ ሥላሴ ፡ የሚባለውን ፡ ንጉሡ ፡ አስመሽገው ፡ ራሳቸው ፡ እስላምጌ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የክብር ፡ ልብሳቸውን ፡ ለብሰው ፡ ባጠገባቸው ፡ ላለው ፡ ወታደር ፡ ድፍረትና ፡ ግለት ፡ የሚሰጥ ፡ ንግግር ፡ አድርገው ፡ ሲጨርሱ ፡ የእንግሊዝ ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ የበሽሉን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሮ ፡ ወደ ፡ እሮጌ ፡ ሲመጣ ፡ ቀድሞ ፡ በወዳጅነት ፡ ጊዜ ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በተላከላቸው ፡ በሩቅ ፡ በሚያሳይ ፡ መነጽር ፡ ተመለከቱ። ወዲያውም ፡ የተጠመደው ፡ መድፍ ፡ እንዲተኩስ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጡ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በራሳቸው ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡ «ቴዎድሮስ» ፡ የሚባለው ፡ መድፋቸው ፡ ስለ ፡ ፈነዳ ፡ እግዚአብሔር ፡ የመንግሥታቸውን ፡ ፍጻሜ ፡ እንዳቀረበው ፡ ተረዱት። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከልብ ፡ የሚያምኗቸውን ፡ የጦር ፡ አዛዦቸውን ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብርዬን ፡ ልከው ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብርዬም ፡ ከነወታደራቸው ፡ እጦር ፡ ማኸል ፡ ገብተው ፡ ሲዋጉ ፡ እነዚያ ፡ ደኅና ፡ ስፍራ ፡ ይዘው ፡ ይጠባበቋቸው ፡ ኖሮ ፡ ወዲያው ፡ መትረየሳቸውን ፡ ደግነው ፡ ፈጇዋቸው ። ፊታውራሪ ፡ ገብርዬም ፡ በዠግንነት ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ስለ ፡ ጌታቸው ፡ ክብር ፡ ሕይወታቸውን ፡ በጦርነቱ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አሳለፉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ከሞት ፡ የተረፈው ፡ ሸሽቶ ፡ ሲመጣና ፡ ይልቁንም ፡ የታማኛቸውን ፡ የፊታውራሪ ፡ ገብርዬን ፡ መሞት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ፊታቸው ፡ ተለወጠ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ አሰፋለሁ ፡ የማለት ፡ ተስፋቸውም ፡ ተቈርጦ ፡ የሕይወታቸው ፡ ፍጻሜ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ተረዱት ።


ቢሆንም ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ተቻለው ፡ ድረስ ፡ መውጫውን ፡ ማሰቡ ፡ አይቀርምና ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ወደ ወሎ ፡ ለመሸሽ ፡ አስበው ፡ ነበር።ዳሩ ፡ ግን ፡ መንገዱ ፡ ሁሉ ፡ ጠላታቸው ‹ ፡ - በምትሆን ፡ በወይዘሮ ፡ ወርቂት ፡ ወታደሮች ፡ ስለ ፡ ተያዘ ፡ በዚያው ፡ ባሉበት ፡ ምሽግ ፡ ሆነው ፡ አማቻቸውን ፡ ደሾች ፡ ዓለሜንና ፡ ከነጮችም ፡ ጨምረው ፡ የዕርት ፡ ነገር ፡ ለመፈተን ፡ ወደ ፡ ጄኔራል ፡ ናፒየር ፡ ላኩ ። ጄኔራሉም ፡ መላክተኞቹን ፡ ተገናኝቶ ፡ ንጉሡ ፡ ያሰሯቸውን ፡ የእንግሊዝ ፡ እስረኞች ፡ ለቀው ፡ እሳቸውም ፡ እጃቸውን ፡ ካልሰጡ ፡ ዕርቅ ፡ ማድረግ ፡ አይቻልም ፡ በማለት ፡ የዚህን ፡ መልስ ፡ በ24 ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ለማወቅ ፡ እፈልጋለሁ ፡ ሲል ፡ (ኡልቲማቱም) ፡ ላከባቸው ። ንጉሡም ፡ ይኸንኑ ፡ ከደጃች ፡ ዓለሜ ፡ አፍ ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ መልክተኞቹን ፡ አሰናብተው ፡ ወደ ፡ ፈጣሪያቸው ፡ ጸልየው ፡ ሲጨርሱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናገሩ። «ኀይለኞችን ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ በክንዱ ፡ ይዞ ፡ የኖረ ፡ እንደኔ ፡ ያለ ፡ ወታደር ፡ ዛሬ ፡ በሰው ፡ ክንድ ፡ መያዝን ፡ ሊታገሥ ፡ አይችልም»። ይኸንንም ፡ ተናግረው ፡ ሲጨርሱ ፡ ሽጉጣቸውን ፡ አውጥተው ፡ ሊጠጡ ፡ ሲሉ ፡ ወዲያው ፡ ባጠገባቸው ፡ ያሉት ፡ ወዳጆቻቸው ፡ ቀምተው ፡ አስጣሏቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚወዷቸውን ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ባለቤታቸውን ፡ እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅን ፡ አስጠርተው ፡ ሲያነጋግሯቸው ፡ እቴጌዩቱም ፡ ዕንባቸውን ፡ እያፈሰሱ ፡ ጨካኙን ፡ የንጉሡን ፡

መንፈስ ፡ ሲያለሰልሱ ፡ በዚያ ፡ ከቆሙት ፡ አንዱ ፡ ጃንሆይ ፡ እንግዴህ ፡ መሞታችን ፡ ካልቀረ ፡ የዚህ ፡ ጦርነት ፡ ምክንያት ፡ የሆኑትን ፡ እነዚህን ፡ የታሰሩትን ፡ እንግሊዞች ፡ መዠመሪያ ፡ ገድለን ፡ እኛም ፡ ሄደን ፡ እንሙት ፡ ብሎ ፡ አማከራቸው ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ «ያገሬን ፡ ሕዝብ ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ እኔ ፡ ያጉላላሁት ፡ አንሶ ፡ ደግሞ ፡ እነዚህን ፡ ገድዬ ፡ ሕዝቤን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ እንዲጠቃ ፡ አላደርግም» ፡ ብለው ፡ መለሱለት ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሲያስመሰግናቸው ፡ ይኖራል ። ንጉሡ ፡ በማግስቱ ፡ የፋሲካ ፡ በዓል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ እንዲሆነው ፡ ብዙ ፡ ሠንጋና ፡ በግ ፡ ከደብዳቤ ፡ ጋራ ፡ ለጄኔራል ፡ ናፒየር ፡ ላኩለት። የደብዳቤውም ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው።

«በሰማይ ፡ እንጂ ፡ በመሬት ፡ የማንገናኝ ፡ መሆናችንን ፡ አስቤ ፡ እጅዎን ፡ ይስጡ ፡ ብለኸ ፡ በላክኸብኝ ፡ ጊዜ ፡ መልስ ፡ ሳልክብኸ ፡ ቀረሁ ። የፊታውራሪ ፡ ገብርዬንም ፡ ሬሳ ፡ አብረን ፡ እንቀበራለን ፡ በማለት ፡ እስካሁን ፡ ሳላስነሣ ፡ ቆየሁ። አሁን ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ መኖሬ ፡ ካልቀረ ፡ እንድቀብረው ፡ ፍቀዱልኝ ፡ እናንተም ፡ የምትፈልጉትን ፡ እስረኞቻችሁን ፡ ለማግኘት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እኔም ፡ ሁሉንም ፡ እልክላችኋለሁ» ። ለጄኔራሉ ፡ የላኳቸውን ፡ ከብቶች ፡ በደስታ ፡ ተቀብሏል ፡ ማለትን ፡ ከሐሰተኛ ፡ ሰው ፡ ሰምተው ፡ ነበር። ከብቶቹን ፡ ግን ፡ ከድኻ ፡ የተወሰዱ ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ከሰፈሩ ፡ ውጭ ፡ አድርጎ ፡ ያስጠብቃቸው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በፍጹም ፡ አልነካቸውም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለመልእክቱ ፡ መልስ ፡ ሳያገኙ ፡ ንጉሥ ፡ ከፉህላ ፡ ተነሥተው ፡ የተረፏቸውን ፡ ጥቂት ፡ ወታደሮች ፡ አስከትለው ፡ እመቅደላ ፡ ምሽግ ፡ ገብተው ፡ በመድፍና ፡ በጥይት ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ገጠሙ ። በዚሁ ፡ ጦርነት ፡ ከእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሰፈር ፡ የተተኰሰ ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ የነበሩበትን ፡ መዝጊያ ፡ ሰብሮ ፡ ጣለው ። እንግሊዞችም ፡ ይዘውት ፡ የነበረው ፡ መድፍና ፡ መትረየስ ፡ አዲስ ፡ የወጣ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የመድፉ ፡ ጥይት ፡ ተተኩሶ ፡ እመሬት ፡ ካረፈ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እየፈነዳ ፡ የመጣውን ፡ ያኸል ፡ ደግሞ ፡ እየሄደ ፡ ጠላትን ፡ የሚጉዳ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ንጉሡም ፡ በመጨረሻ ፡ ባላቸው ፡ ኀይል ፡ ከጠላታቸው ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ ስሰ ፡ ሆኑ ፡ ባጠገባቸው ፡ የቆሙትን ፡ የሚወዷቸውን ፡ ወታደሮች ፡ ስመው ፡ እንዲሸሹ ፡ ካሰናበቷቸው ፡ በኋላ ፡ እንግሊዞች ፡ ለመማረክ ፡ ታችኛውን ፡ በር ፡ ሰብረው ፡ እየተጋፉ ፡ ሲገቡ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ በር ፡ አልፈው ፡ በጨበጡት ፡ በገዛ ፡ ሽጉጣቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ገድለው ፡ ወድቀው ፡ ተገኙ።



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY



<u>የአፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሽጉጥ</u>



NIGUSS DIGITAL LIBRARY

እንግሊዞችም ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ ሬሳቸው ፡ ሄደው ፡ የርሳቸው ፡ ሬሳ ፡ ለመሆኑ ፡ ሲያመነቱ ፡ ታስረው ፡ ከነበሩት ፡ እንግሊዞች ፡ ውስጥ ፡ እነካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ በጣም ፡ ያውቋቸው ፡ ነበርና ፡ የርሳቸው ፡ ሬሳ ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጡ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መዠመሪያ ፡ ፎቶግራፍ ፡ አነሥዋቸው ። ወዲያው ፡ በወርቅ ፡ ግምጃ ፡ ተገንዘው ፡ በተወለዱ ፡ በ50ኛ ፡ በነገሡ ፡ በ14ኛው ፡ ዓመት ፡ በ1860 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ሚያዝያ ፡ 6 ፡ ቀን ፡ ዐርፈው ፡ በመቅደላ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀበሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አልቃሾች ፡ ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ ግጥም ፡ አለቀሱላቸው ።

አባ ፡ ታጠቅ ፡ ካሣ ፡ ተባቱ ፡ ተባቱ ፡
አንድ ፡ ሰባራ ፡ ብረት ፡ ሳይሰጠው ፡ አባቱ ፡
አልማሚት ፡ ሠራዊት ፡ ያስጉዛል ፡ በፊቱ ፡
እርሱ ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ 1 ነው ፡ ለናቱ።

ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ይዞ ፡ የገዛው ፡ ንጉሥ ፡
እንዲህነ ፡ ሥሡ ፡ ነው ፡ ጠመንዣ ፡ እሜጙርሥ ፡
ጠላቶቹን ፡ ሁሉ ፡ ዐጭዶ ፡ እንደ ፡ ገብስ ፡
መቅደላ ፡ ተጣለው ፡ ራሱን ፡ በራስ።

በመቅደላ ፡ በኩል ፡ ጩኸኸት ፡ በረከተ ፡
የሴቱን ፡ አናውቅም ፡ ወንድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሞተ።

አያችሁት ፡ ብያ ፡ ያንበሳውን ፡ ሞት ፡
በሰው ፡ እጅ ፡ መሞትን ፡ ነውር ፡ አድርጎነት።

የትግሬንም ፡ ንጉሥ ፡ ሲንቀኍ ፡ ሲንቀኍ ፡
የሸዋንም ፡ ንጉሥ ፡ ሲንቀኍ ፡ ሲንቀኍ ፡
ወንድ ፡ አለራስዎ ፡ ገድለውም ፡ አያውቀኍ።

አባትና ፡ እናቱ ፡ አላንድ ፡ አልወለዱ ፡
አባ ፡ ታጠቅ ፡ ካሳ ፡ ያው ፡ አንዱ ፡ ያው ፡ አንዱ ፡

መላው ፡ የጐጃም ፡ ሰው ፡ መላው የትግሬ ፡ ሰው ፡
ተይዞ ፡ በምጥ።
የእንግሊዝ ፡ ሐኪሞች ፡ መጥተው ፡ ቢይዙት ፡
ተገላገለ ፡ አሉ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ፍጥረት።

ገደልን ፡ እንዳይሉ ፡ ሙተው ፡ አገኗቸው ፡
ማረክን ፡ እንዳይሉ ፡ ሰው ፡ የለ ፡ በጃቸው ፡

ምን ፡ አሉ ፡ እንግሊዞች ፡ ሲገቡ ፡ አገራቸው ፡ |
ለወሬ ፡ አይመቹም ፡ ተንኰለኛ ፡ ናቸው ።

አምላክን ፡ መስሎ ፡ ቴዎድሮስ ፡
ንዑና ፡ ሑሩ ፡ ሲል ፡ ዋለ ፡ ኀሙስ።

ሰኞ ፡ መቅደላ ፡ ተጨነቀ ፡
ሰው ፡ መሆኑ ፡ ታወቀ።

ቀኑን ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ ሲወጣ ፡ ፈረስ ፡
የሌሊቱን ፡ ነገር ፡ ያውቃል ፡ ክርስቶስ ፡
ጠላቶቹን ፡ ሁሉ ፡ አጭዶ ፡ እንደ ፡ ገብስ ፡
መቅደላ ፡ ተጣላው ፡ ራሱን ፡ በራስ።



ዐፄ ፡ ዎድሮስ ፡ የተቀበሩበት ፡ መቅደላ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን

# ምዕራፍ ፡ 15

## የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መመለስ ።

በየግዛታቸው ፡ ነፃ ፡ ገዥ ፡ መሆንን ፡ የሚፈልጉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሳፍንት ፡ በጋራ ፡ ጠላትነት ፡ የሚመለከቷቸውን ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ድል ፡ ካደረገላቸው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚያደርገውን ፡ አጥብቀው ፡ በመመልከት ፡ ይከታተሉት ፡ ነበር ። በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የነበሩት ፡ መሳፍንት ፡ በላስታ ፡ ዋግ ፡ ሥዩም ፡ (ዋግ ፡ ሹም) ፡ ጕበዜ ፥ በትግሬ ፡ ደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፥ በወልቃይት ፡ ጣሰው ፡ (ጥርሶ) ፡ ጕበዜ ፥ በሸዋ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፥ በጐጃም ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ናቸው ። ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጕበዜም ፡ አጎታቸውን ፡ ደጃች ፡ መሸሻ ፡ የሚባሉትን ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ በማንኛውም እንዲረዷቸውና ፡ ወዲያውም ፡ ሥራቸውንና ፡ አሳባቸውን ፡ እንዲሰልሉ ፡ አዘዋቸው ፡ ነበር ። የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከምኒልክና ፡ ከራስ ደስታ ፡ በቀር ፡ እላይ ፡ በተባሉት ፡ ባማራና ፡ በትግሬ ፡ ገዥዎች ፡ እየተረዱና ፡ እየተመሩ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ድል ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ከመቅደላ ፡ ያገኙትን ፡ የወርቅ ፡ አክሊልና ፡ የወርቅ ፡ ጽዋ ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ መስቀል ፡ ጋሻና ፡ በያይነቱ ፡ የጥንት ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ ለመሂድ ፡ ሰበሰቡ ። ከዚሁም ፡ የወርቅ ፡ ጽዋ ፡ ውስጥ ፡ 1ኛው ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ጽሕፈት ፡ ነበረበት።

«ዝንቱ ፡ ጽዋዕ ፡ ዘወሀብዋ ፡ ዳግማዊ ፡ ኢያሱ ፡ ወብእሲቱ ፡ ወለተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ለቅድስት ፡ ቍስቋም ፡ ከመ ፡ ትኩኖሙ ፡ መድኀኒተ ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ»። ከዘውዱም ፡ 1ኛው ፡ የወርቅ ፡ ዘውድ ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ለዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሰጥተዋቸው ፡ የነበረውና ፡ በኋላ ፡ እንግሊዞች ፡ ባ1917 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የመለሱት ፡ ነው። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከጐጃምና ፡ ከጐንደር ፡ ገዳማትና ፡ አድባራት ፡ የሰበሰቡትን ፡ ስንክሳርና ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ሌሎችንም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ ይዘው ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ለረዷቸው ፡ ለደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሰጥተው ፡ ታስረው ፡ የነበሩትን ፡ እስረኞችና ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ልጅ ፡ ዓለማየሁን ፡ እቴጌ ፡ ጥሩወርቅን ፡ ይዘው ፡ ወዳገራቸው ፡ ጉዞ ፡ ዠመሩ። በኋላ ፡ ግን ፡ እቴጌዩቱ ፡ በመንገድ ፡ ዓለማየሁ ፡ በሎንዶን ፡ ላይ ፡ ሞቱ።



<u>የናፒየር ሰራዊት ከመቅደላ የዘረፈውን ቅርስ ይዞ ወደ ምጽዋ ሲንቀሳቀስ</u>




ቀዳሚሁ፡ ለወንጌሉ፡ ለኢየሱስ፡ ክር
ስቶስ፡ ወልደ፡ እግዚአብሔር፡ በከመ
ጽሑፍ፡ ውስተ፡ መጽሐፈ፡ ኢሳይያስ፡ ና
ሁ፡ አነ፡ እፌኑ፡ መልአክየ፡ ቅድመ፡ ገጽከ
ዘይጼሕሕ፡ ፍኖተከ፡ ቃለ፡ ዐዋዲ፡ ዘ
ሰብክ፡ በገዳም፡ ወይብል፡ ጺሑ፡ ፍኖ
ቶ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወሀርዩ፡ ምጽሐ
ቶ፡ ወሀሎ፡ አሐዱ፡ ብእሲ፡ ዘስሙ፡ ዮሐን
ስ፡ የጠምቅ፡ በገዳም፡ ወይሰብክ፡ ጥም
ቀቶ፡ ከመ፡ ይኔስሑ፡ ወይትሐደግ፡ ሎሙ፡
ኃጢአቶሙ፡ ወየሐውሩ፡ ኀቤሁ፡ ኵሎ
ሙ፡ ሰብአ፡ ይሁዳ፡ ወኢየሩሳሌም፡ ወ
የጠምቆሙ፡ ለኵሎሙ፡ በፈለገ፡ ዮርዳ
ኖስ፡ ወይትአመኑ፡ ወይኔስሑ፡ በእን
ተ፡ ኃጢአቶሙ፡ ወለብሱ፡ ለዮሐንስ፡
ጸጕረ፡ ገመል፡ ወቅናት፡ ዘአዲም፡ ው
ስተ፡ ሐቌሁ፡ ወሲሳዩ፡ አንበጣ፡ ወመ
ዐረ፡ ገዳም፡ ጸደና፡ ወሰበከ፡ ወይቤ፡ ይ
መጽእ፡ ዘይጸንዐኒ፡ እምድኅሬየ፡ ዘኢ
ይደልወኒ፡ እድንን፡ ወእፍታሕ፡ ቶታነ፡
አሣእኒሁ፡ እምእገሪሁ፡ ወአንሰ፡ አጠ
መቅኩክሙ፡ በማይ፡ ወውእቱሰ፡ ያጠም
ቅክሙ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ወይእተ፡ አ
ሚረ፡ መጽአ፡ ኢየሱስ፡ እምገሊላ፡ እም
ሀገረ፡ ናዝሬት፡ ወአጥመቆ፡ ዮሐንስ፡ በ
ፈለገ፡ ዮርዳኖስ፡ ወወፂኦ፡ እማይ፡ ር
እየ፡ ተከሥተ፡ ሰማይ፡ ወወረደ፡ መንፈስ፡ ቅ
ዱስ፡ ከመ፡ እንተ፡ ርግብ፡ ወነበረ፡ ዲቤሁ፡
ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወመጽአ፡ ቃል፡ እ
ም ሰማይ፡ ዘይብል፡ አንተ፡ ውእቱ፡ ወልድ
የ፡ ዘአፈቅር፡ ወኪያሁ፡ ሠመርኩ፡
ወአውጽኦ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ሰቢሆ፡ ገዳ
ም፡ ወነበረ፡ ሐቅለ፡ አርብዓ፡ መዋልተ፡


ወአርብዓ፡ ለሊተ፡ ወተመከረ፡ ሰይ
ጣን፡ ወነበረ፡ ምስለ፡ አራዊት፡ ወመ
ላእክት፡ ይትለአክዎ፡ ወእምድኅረ፡
ሶሐዝዎ፡ ለዮሐንስ፡ መጽአ፡ እግዚእ፡ ኢ
የሱስ፡ እምገሊላ፡ ወሰበከ፡ ወንጌለ፡ መን
ግሥተ፡ እግዚአብሔር፡ ወይቤ፡ በጽሐ፡
ገዚሁ፡ ወቀርበት፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡
ሥሑ፡ ወእመኑ፡ በወንጌሉ፡ ወእንዘ፡ የሐል
ፍ፡ መንገለ፡ ባሕረ፡ ገሊላ፡ ረከቦሙ፡ ለስም
ዖን፡ ወለእንድርያስ፡ እኁሁ፡ ይሥግሩ፡ ውስተ
ባሕር፡ እስመ፡ መሠግራን፡ እሙንቱ፡፡
ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ንዑ፡ ትልዉ
ኒ፡ ወእሬስየክሙ፡ መሠግራነ፡ ሰብእ፡
ወኅደጉ፡ መሣግሪሆሙ፡ ወተለውዎ፡ ሰ
ኁ፡ ወኀሊፎ፡ እምህየ፡ ሕቀ፡ ረከቦሙ፡ ለ
ያዕቆብ፡ ወለዮሐንስ፡ እኁሁ፡ ደቂቀ፡ ዘብ
ዴዎስ፡ ወሀለዉ፡ ምስሌሆሙ፡ ውስተ፡
ሐመር፡ ያጸንዑ፡ መሣግሪሆሙ፡ ወጸው
ዖሙ፡ ወኅደጉ፡ ዘብዴዎስሃ፡ አቡሆሙ፡
ምስለ፡ ዐሣብ፡ ውስተ፡ ሐመር፡ ወሖሩ፡
ወተለውዎ፡ ወሖሩ፡ ቅፍርናሆም፡ ወ
ቦአ፡ በሰንበት፡ ምኵራበ፡ ወአኀዘ፡ ይም
ህሮሙ፡ ወአንከሩ፡ ምህሮቶ፡ እስመ፡
ከመ፡ መኰንን፡ ይምህሮሙ፡ ወአኮ፡ ከመ
ጸሐፍቶሙ፡ ወሀሎ፡ ብእሲ፡ ዘጋኔን፡ እ
ኩይ፡ ውስተ፡ ምኵራብ፡ ወአውየወ፡ ወይ
ቤ፡ ምንት፡ ብነ፡ ምስሌከ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ ናዝራዊ፡ መጻእከኑ፡ ታጥፍአነ፡ አእመ
ርናከ፡ መኑ፡ አንተ፡ ቅዱሱ፡ ለእግዚአብሔ
ር፡ አንተ፡ ወገሠጾ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤ
ሎ፡ ተፈጸም፡ ወፃእ፡ እምኔሁ፡ መንፈስ፡ ር
ኩስ፡ ወአንፈራገጾ፡ ውእቱ፡ ጋኔን፡ እኩይ፡ ወ
አውየወ፡ በዐቢይ፡ ቃል፡ ወወፅአ፡ እምኔሁ፡

ወደንገፁ፡ኵሎሙ፡ወይቤሉ፡በበይ
ናቲሆሙ፡ምንትኑ፡ዝንቱ፡ትምህር
ት፡ሐዲስ፡ዘበትእዛዝ፡ይኤዝዞሙ፡
ለአጋንንት፡እኩያን፡ወይወፅኡ፡ወ
ተሰምዐ፡ነገሩ፡በኵሉ፡በሐውርት፡
፳፱ ገሊላ፡ወወፂኦ፡እምኵራብ፡ቦአ፡ቤ
ተ፡ስምዖን፡ወምስለሁ፡እንድርያስ
ወያዕቆብ፡ወዮሐንስ፡ወሐማቱ፡ለ
ስምዖን፡ትፈጽን፡ወነገርዎ፡በእን
ቲአሃ፡ወቀርበ፡ኀቤሃ፡ወአኀዘ፡እ
ዴሃ፡ወአንሥኣ፡ወኀደጋ፡ፈጽንቱ፡ሶ
በሂ፡ወተንሥአት፡ወተልእከቶሙ፡
ወመሲዮ፡ጊዜ፡ሶበ፡ሀሎ፡የዐርብ፡አምጽ
ኡ፡ኀቤሁ፡ኵሎ፡ድውያነ፡ወእለሂ፡
አጋንንት፡ወተጋብኡ፡ኵሉ፡ሀገር፡ኀ
በ፡አንቀጽ፡ወፈወሶሙ፡ለብዙኃን፡
፴፬ ድውያን፡ወሐመማት፡
ወአውጽኦሙ፡ለብዙኃን፡አጋንንት፡
ወኢየብሖሙ፡ይንብቡ፡እስመ፡የአ
፴፭ ምርዎ፡ከመ፡ውእቱ፡ክርስቶስ፡
ወበጽባሕ፡ተንሥአ፡ወሖረ፡በሌሊት፡
ወወፅአ፡ወሖረ፡ሐቅለ፡ወጸለየ፡በህ
ወዴገንዎ፡ስምዖን፡ወእለ፡ምስሌ
ሁ፡ወረከብዎ፡ወይቤልዎ፡እንጋ፡ኵ
ሉ፡የኀሥሡከ፡ወይቤሎሙ፡መልአ፡
እንከ፡ካልእተ፡አህጉረ፡ከመ፡በህ
የኒ፡ንስብክ፡እስመ፡እንበይነ፡ዝንቱ፡
ወጻእኩ፡ወተፈነውኩ፡ወሖረ፡ወ
ሰበኩ፡ምኵራባቲሆሙ፡ወበኵሉ፡ይሁዳ፡
ወገሊላ፡ወያወፅእ፡አጋንንተ፡
፵ ወመጽአ፡ዘለምጽ፡ኀቤሁ፡ወአስተብ
ረከ፡ወአስተብቍዖ፡ወይቤሎ፡እግ
ዚኦ፡እመሰ፡ፈቀድከ፡ትክል፡አንጽ
ሖትየ፡ወምሕሮ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡
ወሰፍሐ፡እዴሁ፡ወገሰሶ፡ወይቤሎ፡
እፈቅድ፡አንጽሕ፡ወበጊሜሃ፡ከመዝ፡


ሐየወ፡ስምዐ፡ሀሉ፡ወንጽሐ፡ለምጹ፡
ፈነዎ፡ወይቤሎ፡ዑቅ፡ወአትንግ
ወኢለመኑሂ፡ወሑር፡ወአርእ
ርእስከ፡ለካህን፡ወአብእ፡
ባእከ፡ዘአዘዘ፡ሙሴ፡ከመ፡ይኩን፡ስምዐ
፵፭ ሆሙ፡ወወፂኦ፡አኀዘ፡ይስብክ፡ወ
ይንግር፡ብዙኀ፡እስከ፡ኢይክል፡ገ
ሀገረ፡ክሡተ፡አላ፡አፍአ፡ይ
ይነብር፡ወይመጽኡ፡ኀቤሁ፡እም
ኵሉ፡ወቦአ፡ካዕበ፡ሀገረ፡ቅፍርናሆም፡ምንዳቤ፡ወሰምዑ፡ከመ፡ሀ
ሎ፡ውስተ፡ቤት፡ወተጋብኡ፡ብዙ
ኃን፡እስከ፡ኢያገምሮሙ፡ወአ፡ኀበ
ት፡ወይነግሮሙ፡ቃሎ፡ለአሉ፡መጽአ
ኀቤሁ፡ወአምጽኡ፡ኀቤሁ፡ድው
የ፡መፃጕዐ፡ወይጸውርዎ፡ዘጸሩ
አርባዕቱ፡ወሶበ፡ኢክህሉ፡አብ
አቶ፡ኀበ፡ህላዌ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡
ወነሥቱ፡ጠፈረ፡ወአውረድዎ፡ም
ስለ፡ሀራቱ፡ዘዲቤሁ፡ይሰከብ፡ው
እቱ፡መጻጕዕ፡ወርእየ፡እግዚእ፡
ኢየሱስ፡ሃይማኖቶሙ፡ይቤሎ፡እ
ግዚእ፡ኢየሱስ፡ለውእቱ፡መጻጕዕ
ወልድየ፡ተኀደገ፡ለከ፡ኀጢአትከ፡
ወሀለዉ፡ጸሐፍት፡ይነብሩ፡ወሐ
ለዩ፡በልቦሙ፡ወይቤሉ፡ለምንት
ኑ፡ከመዝ፡ዘይነብብ፡ጸርፈተ፡መ
ኑ፡ይክል፡ኀዲገ፡ኀጢአት፡ዘእንበ
ለ፡እግዚአብሔር፡ወአእመሮሙ፡
እግዚእ፡ኢየሱስ፡በመንፈሱ፡ከመ፡
ከመዝ፡ይኄልዩ፡ወይቤሎሙ፡ለም
ንትኑ፡ትኄልዩ፡በልብክሙ፡ምንተ፡ይ
ቀልል፡እምብሂሎቱ፡ለዝ፡መጻጕዕ
ተኀድገ፡ለከ፡ኀጢአትከ፡
ወእምብሂሎቱ፡ለድውይ፡ተንሥ

ሥዕለ፡ ቅዱስ፡ ቴዎድሮስ፡ ሥዕለ፡ ቅዱስ፡ ጊዮርጊስ፡






<u>ከበሮ</u>



በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጄኔራል ፡ ናፒየር ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ድል ፡ ማድረጉንና ፡ አስረኞቹን ፡ ከነሕይወታቸው ፡ መረከቡን ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ አስተላልፎ ፡ ነበርና ፡ ወዲያው ፡ ሠራዊቱ ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ ይመለስ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ለመነጋገር ፡ ወደዚህ ፡ እንድትመጣ ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ስለ ፡ መጣበት ፡ ሠራዊቱን ፡ በያገሩ ፡ ልኮ ፡ ራሱ ፡ ግን ፡ በግብጽ በኩል ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ሎንዶን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ለድል ፡ አድራጊ የሚገባ ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ ተደረገለት ፡ ይልቁንም ፡ ከመቅደላ ፡ ይዞት ፡ የሄደው ፡ የጥንት ፡ መሣሪያና ፡ በብራና ፡ የተጻፉት ፡ መጻሕፍት ፡ ለሎንዶን ፡ ቢብልዮቴክና ፡ ለጥንታዊ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ የሚጠቅሙ ፡ በመሆናቸው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ተሰኙበት ። ስለዚህም ፡ ጄኔራል ፡ ናፒየርን ፡ «ባሮን ፡ አፍ ፡ መቅደላ» ፡ ብለው ፡ ሠየሙት።



ዓፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ራሳቸውን ፡ በሽጉጥ ፡ ገድለው ፡ እንደወደቁ ።

# ዓፄ ፡ ቴዎድሮስ



# የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ 16 ።

## ስለ ፡ ጣሰው ፡ ጕበዜ ፡ ሞት ፡ -ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጕበዜ ፡ እንደ ፡ ነገሡ ፡ - ስለ ራስ ፡ አዳልና ፡ ስለ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ።

ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የቀድሞ ፡ ስማቸው ፡ ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጕበዜ ፡ ነው ፡ አገራቸው ፡ ላስታ ፡ ዘራቸውም ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘር ፡ ሲወርድ ፡ የመጣውን ፡ የነገሥታትን ፡ ዘር ፡ አሸንፈው ፡ በኀይል ፡ የነገሡት ፡ የነዛጔ ፡ ዘር ፡ ነው ፡ ይባላል ። አባታቸውም ፡ ዋግ ፡ ሹም ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ ይባላሉ።

ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጕበዜ ፡ በዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የሕይወት ፡ መጨረሻ ፡ ከነበሩት ፡ መሳፍንት ፡ የበለጡና ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውም ፡ እስከ ፡ 60 ፡ ሺሕ ፡ ይደርስ ፡ ነበር። ይኸንኑም ፡ እንግሊዞች ፡ ያውቊ ፡ ነበርና ፡ ወዳገራቸው ፡ በሚመለሱበት ፡ ቀን ፡ የመቅደላን ፡ ምሽግና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይምጡና ፡ እናስረክብዎ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ። ርሳቸውም ፡ መኳንንቶቻቸውን ፡ ሰብስበው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ ብለው ፡ ቢያማክሯቸው ፡ አስሮ ፡ ይዞዎት ፡ ይሄዳልና ፡ አይሂዱ ፡ ብለው ፡ መጥፎ ፡ ምክር ፡ አቀረቡላቸው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ርሳቸው ፡ አልመጣም ፡ ስላሉ ፡ ላኀታቸው ፡ ለደጃች ፡ መሸሻ ፡ ምሽጉን ፡ ብቻ ፡ አስረከቧቸው። ወዲያውም ፡ በመቅደላ ፡ ታስረው ፡ የነበሩት ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ እንግዴህ ፡ ገዢያችን ፡ እርስዎ ፡ ነዎት ፡ እያሉ ፡ ለዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጕበዜ ፡ አመኑላቸው ።

ከዚህም ፡ በፊት ፡ በደንቢያና ፡ በወልቃይት ፡ ጣሰው ፡ (ጥርሶ) ፡ ጕበዜ ፡ የሚባለው ፡ እንዲሁ ፡ ለመንገሥ ፡ ያስብ ፡ ነበርና ፡ ባ1860 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በ መጋቢት ፡ 22 ፡ ቀን ፡ ከበጌምድር ፡ በስተሰሜን ፡ በለሳ ፡ እሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ አድርገውት ፡ ጣሰው ፡ (ጥርስ) ፡ ጕበዜም ፡ እጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞተ።

ቀጥሎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለመንገሥ ፡ በጐጃምና ፡ በትግሬ ፡ በሸዋም ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ማስገበር ፡ የግድ ፡ ማስፈለጉን ፡ ተመልክተው ፡ መዠመሪያ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ።

ጐጃምንም ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ ደጃች ፡ ተድላ ፡ ጓሉ ፡ ሲገዙት ፡ ኑረው ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ልጃቸው ፡ ደጃች ፡ ንጉሤ ፡ ተድላ ፡ የጐጃምን ፡ ግዛት ፡ 15 ፡ ቀን ፡ ያኸል ፡ እንደ ፡ ገዙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊስሙ ፡ በሄዱበት ፡ ቀን ፡ ታናሽ ፡ ወንድማቸው ፡ ደጃች ፡ ደስታ ፡ ተድላ ፡ በግቢው ፡ የቀረውን ፡ ዘበኛ ፡ አሳድመው ፡ ደጃች ፡ ንጉሤ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲመለሱ ፡ ግቢያቸው ፡ በደጃች ፡ ደስታና ፡ በዐድመኞቻቸው ፡ ተይዞ ፡ ስላገኙት ፡ ሸሽተው ፡ በረሓ ፡ ገቡ።.የጐጃምንም ፡ ግዛት ፡ ደጃች ፡ ደስታ ፡ አባ ፡ ቀማው ፡ ይገዙ ፡ ዠመር።

ስለዚህ ፡ ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጒበዜ ፡ ገብርልኝ ፡ ብለው ፡ ለደጃች ፡ ደስታ ፡ ቢልኩባቸው ፡ አልገብርም ፡ በማለት ፡ ተዋግተው ፡ ከተሸነፉ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ በረሓ ፡ ገቡ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጒበዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ደስታን ፡ ባንድ ፡ ቊራጭ ፡ አገርና ፡ በባላምባራስነት ፡ ስለ ፡ ወሰዷቸው ፡ በዚሁ ፡ ተቀይመው ፡ በበረሓ ፡ ይኖሩ ፡ ለነበሩት ፡ ለባላምባራስ ፡ አዳል ፡ ተሰማ ፡ እኅታቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ላቀች ፡ ገብረ ፡ መድኅንን ፡ ድረው ፡ የራስነት ፡ ማዕርግ ፡ ጨምረው ፡ የጐጃምን ፡ ግዛት ፡ ሰጧቸው።

እንደዚሁም ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ተላልከው ፡ ካስገበሩ ፡ በኋላ ፡ «ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ» ፡ ተብለው ፡ ጳጳስ ፡ ስለሌለ ፡ በዕጨጌው ፡ እጅ ፡ ተቀብተው ፡ ባ1861 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነገሡ።

ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ለሰው ፡ በመራራትና ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ በግፍ ፡ ከማፍሰስ ፡ የሚጠነቀቊ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በፊት ፡ ለፊት ፡ ጦርነት ፡ የገጠማቸውን ፡ ድል ፡ በመምታት ፡ ዠግንነታቸው ፡ የታወቀ ፡ በመሆኑ ፡ በጊዜያቸው ፡ እንዲህ ፡ እየተባለ ፡ ይዘፈን ፡ ነበር ። ከጐንደር ፡ ተነሥቶ ፡ እሞጣ ፡ (አሚጣ) ፡ ድረስ ፡ ጀሀድ ፡ ብሎ ፡ ገዳይ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ።

ቀጥሎ ፡ በበጌምድር ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ የሚባሉ ፡ መዠመሪያ ፡ እገብራለሁ ፡ ብለው ፡ ተገዢነታቸውን ፡ ካመኑ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሸፍተው ፡ የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ሹማምንቶች ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ አባረሯቸው ። በኋላ ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሠራዊታቸውን ፡ አስከትለው ፡ ቢሄዱባቸው ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ለመቋቋም ፡ ስላልቻሉ ፡ ባንገታቸው ፡ ድንጋይ ፡ አሥረው ፡ ይማሩኝ ፡ ብለው ፡ መጡ። ንጉሡም ፡ ከጠባያቸው ፡ ደግነትና ፡ ርኅራኄ ፡ የመላባቸው ፡ ነበሩና ፡ ምሬኻለሁ ፡ ብለው ፡ ወዲያው ፡ ውለው ፡ ሳያድሩ ፡ የበጌምድርን ፡ ግዛት ፡ መለሱላቸው።

ራስ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ሸፍተው ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ እንደዚሁ ፡ በየጁ ፡ ዐሊ ፡ ፋሪስ ፡ የሚባለው ፡ ሸፈተባቸው ። ንጉሡም ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ማርያምን ፡ መዠመሪያ ፡ በኀይል ፡ አስፈራርተው ፡ መልሰው ፡ ሾመው ፡ የበጌምድርን ፡ አገር ፡ ካደላደሉ ፡ ወዲህ ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ ዐሊ ፡ ፋሪስን ፡ ለመግጠም ፡ ሄዱ። ዐሊ ፡ ፋሪስም ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ጋላ ፡ አገር ፡ ሄደ።

# ምዕራፍ ፡ 17 ።

## ባፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስና ፡ በደጃች ፡ ካሣ ፡ ጦርነት ፡ ዋዜማ ፡ ሁለቱ ፡ ለፈረንሳዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለናፖሊዎን ፡ 3ኛ ፡ የጻፉዋቸው ፡ ደብዳቤዎች ።

ቀድሞ ፡ በዘመነ ፡ መሳፍንት ፡ በነገሥተ ፡ ነገሥታቱ ፡ ደካማነት ፡ በእንደራሴዎቻቸው ፡ ማየል ፡ የተፈጠረው ፡ የውስጥ ፡ አንድነት ፡ ባፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ባፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ አልጸና ፡ እያንዳንዱ ፡ የየአውራጃ ፡ መስፍን ፡ የመንገሥ ፡ ፍላጎት ፡ በየልቡ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚጉላላ ፡ ሊነግሥም ፡ የሚችለው ፡ በቂ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በማግኘት ፡ መሆኑን ፡ የጦር ፡ መሣሪያም ፡ የሚገኘው ፡ በቅድሚያ ፡ የውጭ ፡ አገርን ፡ የመንግሥታት ፡ መሪዎችን ፡ በመወዳጀት ፡ መሆኑን ፡ ስለሚገነዘብ ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የተቀመጡት ፡ ዓፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ለዚህ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ምኞት ፡ ያላቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ገና ፡ ያልደረሱት ፡ ደጃዝማች ፡ ካሣ ፡ የትግሬው ፥ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ የሸዋው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ መሪዎች ፡ ጋር ፡ ለመዛመድ ፡ በያለበት ፡ ደብዳቤ ፡ ይጻጻፋሉ ።

በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ደጃዝማች ፡ ካሣ ፡ ርዕሰ ፡ መኳንንት ፡ እየተባሉ ፡ ትግሬን ፡ የሚገዙት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ (1862 ፡ ዓ ፡ ም) ምንም ፡ እንኳን ፡ ለእኅታቸው ፡ ባል ፡ ላፄ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እየገበሩ ፡ የተቀመጡ ፡ ቢሆን ፡ በልባቸው ፡ ግን ፡ ለመንገሥ ፡ ፍላጎት ፡ ስለአላቸው ፡ ከውጭ ፡ መንግሥታት ፡ መሪዎች ፡ ጋር ፡ ዝምድናን ፡ በሚፈልጉበት ፡ ሰዓት ፡ በቅድሚያ ፡ ምጥዋ ፡ ከሚቀመጠው ፡ ሙንዚንገር ፡ ከሚባለው ፡ ቀድሞ ፡ የግብፅ ፡ አሁን ፡ የፈረንሳዊ ፡ ቆንስል ፡ ከሆነው ፡ ጋር ፡ ተዋውቀው ፡ ወዳጅነት ፡ ከወጠኑ ፡ በኋላ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ በግዛታቸው ፡ እየገቡ ፡ ሕዝቡን ፡ በመስበክ ፡ ያስቸገሩዋቸውን ፡ ካቶሊኮቹን ፡ እንዲያስጥላቸው ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ በዚሁ ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ወዳጅነት ፡ ለመመሥረት ፡ ሲሉ ፡ እ.ኤ.አ. ቊጥር ፡ ከ1852 ፡ እስከ ፡ 1870 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለገዛው ፡ ለፈረንሳዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለናፖሊዎን ፡ 3ኛ ፡ ደብዳቤ ፡ ሲጻጻፉ ፡ ቆይተዋል ፡ አሁንም ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፉ።

በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀዳማዊ ፡ ወደኃራዊ ፡ ዘይሤለስ ፡ በአካላት ፡
ወይትዋሐድ ፡ በመለኮት ፡ ሎቱ ፡ ይደሉ ፡ ስብሐት ፡ አሜን።

የተላከ ፡ ከደጃዝማች ፡ ካሣ ፡ ርእሰ ፡ መኳንንት ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘብሔረ ፡ አክሱም ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ አግአዚት ፡ ወደ ፡ ክቡር ፡ ናጶልዎን (፩) :የፈረንሲስ ፡ (ፈረንሳዊ) ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ።

ሰላም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምሉዓ ፡ ምሕረት ።
የሰደዱት ፡ ወረቀት ፡ ደርሶኝ ፡ በደስታ ፡ ተቀበልሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ፡ እለምንዎታለሁ (፪) ። የካቶሊክ ፡ ካህናቶች ፡ እኔ ፡ አስተምሩ ፡ ሳልላቸው ፡ ቤተ ክርስቲያኑ ፡ የኛ ፡ ነው ፡ ካህናቱም ፡ የኛ ፡ ናቸው ፡ እያሉ ፡ አስቸገሩኝ ። በዚህ ፡ ነገር ፡ የመጣ ፡ አይሆንልኝም ፡ ጥንት ፡ በሴትና ፡ በካህን ፡ ነው ፡ ጠብ ፡ የሚመጣ ፡ አሁንም ፡ ከርስዎ ፡ ጋር ፡ እንዳያጣሉኝ ። የካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ከፉ ፡ ነው ብዬ ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ዕጣዬ ፡ የማርቆስ ፡ የእስከንድርያ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ። ካባ ፡ አትናቴዎስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አባ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ድረስ ፡ ሌላ ፡ አስተማሪ ፡ መጥቶብን ፡ አያውቅም ፡ ከማርቆስ ፡ በቀር። አሁንም ፡ እነዚህን ፡ ካህናት ፡ ቢከለክሉልኝ ፡ ስለብዙ ፡ ገንዘብ ፡ እቁጥረዋለሁ። ነጋዴ ፡ ቢመጣ ፡ እጠብቃለሁ ፡ አገር ፡ የሚያይ ፡ ቢመጣ ፡ እቀበላለሁ። የክርስቲያን ፡ አገር ፡ ነው ፡ አልከለክልም ። በሚቻለኝ ፡ የርስዎን ፡ ወዳጅነት ፡ የርስዎን ፡ ልፈጽም ፡ እወድአለሁ። ከርስዎ ፡ ጋር ፡ ፍቅር ፡ አጥብቄ ፡ እፈልጋለሁ ። የፍቅር ፡ ወረቀትዎ ፡ በቆንስልዎ ፡ እጅ ፡ ምጥዋ ፡ ባይለየኝ ፡ እወድአለሁ ። እኔም ፡ የፍቅር ፡ ወረቀቴን ፡ በቆንስልዎ ፡ እጅ ፡ ምጥዋ ፡ አለይም ፡ እሰዳለሁ ።”

(( ደጃዝማች ፡ ካሣ ))
ርዕሰ ፡ መኳንንት ፡ ዘኢትዮጵያ፡

ተጽሕፈት ፡ በ፪ ፡ ቀን ፡ በመጋቢት ፡ በ፲፰፰፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ አዲ ፡ መጐንቲ ፡ ላይ።





<u>ዳግማዊ ዓጼ ተክለ ጊዮርጊስ (ዋግሹም ጎበዜ ገብረ መድኅን)</u>

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አማቻቸውና ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ ዓፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ አልታዘዝም ፡ አልገብርም ፡ ብለው ፡ ሁለተኛም ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ከውጭ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ጋር ፡ ወዳጅነት ፡ ወጥነው ፡ ስለአስቸገሩዋቸው ፡ እርሳቸውም

(1)ናፖሊዎን ፡

(2) በዛሬ ፡ አነጋገር፡- ነገር ግን አንድ የምለምንዎት ፡ ነገር ፡ አለኝ።

፡ በበኩላቸው ፡ የናፖሊዎንን ፡ ወዳጅነት ፡ ለመፈለግና ፡ ደግሞም ፡ ደጃዝማች ፡ ካሣን ፡ ለመውጋትና ፡ ለማሳመን ፡ ስለፈለጉ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ወዳጄን ፡ ለምን ፡ ወጋህ ፡ ብሎ ፡ እንዳይቀየማቸው ፡ በመሥጋት ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈውለታል ።

"በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ዓፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ። ይድረስ ፡ እግዜር ፡ ከሰው ፡ መርጦ ፡ ካነገሡዎ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ናፖሊዮን ። እንዴተ ፡ አሉ ፡ ደህና ፡ አሉን ፡ ኢጅጉን።

እኔ ፡ የርስዎን ፡ ወዳጅነት ፡ ኢጅግ ፡ እፈልጋለሁ። በረከትም ፡ ልሰድልዎ ፡ ወድጄ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ መንገዱ ፡ አልተመቸኝም ፡ የፍቅር ፡ ወረቀት ፡ ብቻ ፡ መስደዴ ፡ የመላላክ ፡ መመሪያ ፡ እንዲሆን ፡ የርስዎንም ፡ ፍቅር ፡ መፈለጌ ፡ ምልክት ፡ ይሆነዎ ፡ ብዬ ነው ። ዓፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ያከፉትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከምክረዎና ፡ ከፍቅረዎ ፡ ጋር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ አቀናዋለሁ ፡ ብዬ ፡ አስባለሁ ። እኔ ፡ ባገሬ ፡ ቆንስልዎ ፡ እንዲገባ ፡ ያገረዎም ፡ ነጋዴ ፡ ገብቶ ፡ እንዲገበይ ፡ እኔም ፡ የምፈልገው ፡ በርስዎ ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሆንልኝ ፡ እወዳለሁ። ደጃች ፡ ካሣ ፡ ኢያቱ ፡ ላያቴ ፡ አባቱ ፡ ለባቱ ፡ ተገዝቶ ፡ ይኖር ፡ ነበረ። እርሱንም ፡ እኔ ፡ ሾሜ ፡ አገር ፡ ጠብቅ ፡ ብዬ ፡ ብተወው ፡ አምጦ ፡ (ሸፍቶ) ፡ አልታዘዝም ፡ አለ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ የምጠይቀው ፡ (የምወጋው) ፡ ነኝና ፡ አይፍረዱብኝ ። ይህን ፡ መልክት ፡ በሌላ ፡ ኢጅ ፡ መስደዴ ፡ ሰውን ፡ ባላምን ፡ ነው።

ከጌታችን ፡ ልዶት ፡ በሺሕ ፡ ከስምንት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በዘመነ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ ፡ በሐምሌ ፡ መዠመሪያ ፡ ቀን ፡



ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

ዓፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ በሐምሌ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1862 ዓ ፡ ም ፡ የጻፉት ፡ በቅድሚያ ፡ ደጃች ፡ ካሣ ፡ (ዓፄ ፡ ዮሐንስ ) በመጋቢት ፡ 2 ፡ ቀን ፡ 1862 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከጻፉ ፡ ወዲህ ፡ መሆኑን ፡ ደብዳቤዎቹ ፡ ያረጋግጣሉ። ደብዳቤዎቹ ፡ እንዳፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ደብዳቤ ፡ የዘመኑን ፡ አማርኛና ፡ ያጻጻፍ ፡ ቅርጽ ፡ ያመለከታሉ። ዓፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በደብዳቤያቸው ፡ ላይ ፡ ደጃች ፡ ካሣ ፡ አያቱ ፡ ላያቴ ፡ አባቱ ፡ ላባቴ ፡ ይገብር ፡ ይገዛ ፡ የነበረውን ፡ እርሱን ፡ እኔው ፡ ብሾመው ፡ አምጦ ፡ ሸፈተብኝ ፡ ያሉትን ፡ ከላይ ፡ የአያቶቻቸውን ፡ ሁኔታ ፡ አላረጋግጥም ። "ያፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አባት ፡ ዋግ ፡ ሹም ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ ከላስታ ፡ ገዥነት ፡ አልፈው ፡ የደጃች ፡ ካሣን ፡ አባት ፡ ሹም ፡ ተምቤን ፡ ምርጫን ፡ በበላይ ፡ መግዛታቸው ፡ ማስረጃ ፡ የለም ፡ " እንደ ፡ አውነቱ ፡ ሁለቱም ፡ የላስታና ፡ የተምቤን ፡ ባላባቶችና ፡ ገዥዎች ፡ በየአውራጃ ፡ ግዛታቸው ፡ ነፃ ፡ ሆነው ፡ ሁለቱም ፡ ለስሙ ፡ ለነገሠው ፡ ለጕንደሩ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ለእንደራሴዎቹ ፡ ለነራስ ፡ ጉግሣ ፡ ለነራስ ፡ አሊ ፡ (ትንሹ) ፡ እየገበሩ ፡ ሳይቀመጡ ፡ አይቀሩም ።

በደጃች ፡ ካሣ ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ የበለጠ እንደሚታየው ፡ ደጃዝማች ፡ ካሣ ፡ ከመንገሣቸው ፡ በፊትና ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ ከማርቆስ ፡ ወንበር ፡ መንጭታ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስለተመሠረተችው ፡ ስለተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ከልብ ፡ ከማሰባቸው ፡ የተነሣ ፡ ወዳገሪቱ ፡ እየመጡ ፡ በመስበክ ፡ ከተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ወደ ፡ ካቶሊክ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ፕሮቲስታንት ፡ የሚስቡትን ፡ አጥብቀው ፡ ይቃወሙ ፡ ነበር ። የደብዳቤው ፡ ዓላማ ፡ እነርሱን ፡ እዚህ ፡ ሲቃወሙ ፡ የነርሱ ፡ የበላይ ፡ ጠባቂ ፡ የፈረንሳዊው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንዳይቀየምና ፡ ወዳጅነታቸው ፡ እንዳይቋረጥ ፡ በማሰብ ፡ ነው ።

አሁን ፡ እኔሁ ፡ ደጃች ፡ ካሣ ፡ ካፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጋር ፡ ተዋግተው ፡ ካሸነፉ ፡ በኋላ ፡ ስማቸውን ፡ ዮሐንስ ፡ አሰኝተው ፡ እንደምን ፡ እንደነገሡ ፡ በሚቀጥለው ፡ ምዕራፍ ፡ እንመለከታለን ።

# ምዕራፍ ፡ 18 ።

## ያፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስና ፡ የደጃዝማች ፡ ካሣ ፡ ጦርነት ፡

ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ ደጃዝማች ፡ ካሣ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተቃቅረው ፡ ተለያይተው ፡ ሁለቱም ፡ በየበኩላቸው ፡ እየተዘጋጁ ፡ የ1862ን ፡ መጨረሻና ፡ የ1863 ፡ ዓ ፡

ምሕረትን ፡ የመዠመሪያውን ፡ ወራቶች ፡ ካሳለፉ በኋላ ፡ አሁን ፡ በሐምሌ 5 ፡ ቀን ፡ መዋጋታቸውንና ፡ በውጊያው ፡ ደጃች ፡ ካሣ ፡ ማሸነፋቸውን ፡ እንመለከታለን ።

ደጃዝማች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ አባታቸው ፡ የተንቤን ፡ የነራስ ፡ ሚካኤል ፡ ሥሑል ዘር ፡ ናቸው። ስማቸውም ፡ መረጨ ፡ ካሳ ፡ ሥዩም ፡ ሹም ፡ ተንቤን ፡ ምርጫ ፡ ይባላሉ ።

ርሳቸውም ፡ የእንደርታውን ፡ የራስ ፡ አርአያን ፡ እኅት ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ በዝብዝ ፡ ካሳን ፡ ወለዱ ፡ ደጃዝማች ፡ ካሳም ፡ በትግሬ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ካደጉ ፡ በኋላ ፡ መዠመሪያ ፡ ለዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አድረው ፡ የባላምባራስነት ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥተዋቸው ፡ ሳለ ፡ ርሳቸውም ፡ ይህንን ፡ ስም ፡ ንቀው ፡ በረሓ ፡ ገቡ። በኋላ ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ካረፉ ፡ በኋላ ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አሽከሮች ፡ ከራስ ፡ ባሪያው ፥ ከደጃዝማች ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፥ ከደጃች ፡ ሣህሉ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ ስላደረጉ ፡ ከእንግዴህ ፡ ወዲያ ፡ ደጃዝማች ፡ ካሳ ፡ እያላችሁ ፡ ጥሩኝ ፡ ብለው ፡ በፈቃዳቸው ፡ ደጃዝማች ፡ ተብለው ፡ በተንቤንና ፡ በእንደርታ ፡ ገዥ ፡ ሆኑ። ማኅተማቸውም ፡ «ደጃዝማች ፡ ካሳ ፡ ርእሰ ፡ መኳንንት ፡ ዘኢትዮጵያ» ፡ የሚል ፡ ነበር ። እንግሊዞች ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ለመውጋት ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ላገሩ ፡ እንግዳ ፡ በመሆናቸው ፡ በጣም ፡ ተቸግረው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ የትግሬ ፡ ሕዝብ ፡ በደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ ትእዛዝ ፡ መውጫ ፡ መግቢያውን ፡ እያሳየ ፡ በራሱ ፡ አገር ፡ አሳልፎ ፡ በውጊያው ፡ ጊዜ ፡ በጦርነት ፡ ስለ ፡ ረዳ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አዛዥ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ነበርና ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ በሚመለስበት ፡ ጊዜ ፡ ለዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መንግሥቱንና ፡ መሣሪያውን ፡ ይምጡና ፡ ይረከቡ ፡ ቢላቸው ፡ እንቢ ፡ ካሉት ፡ በኋላ ፡ በድምሩ ፡ የሁለት ፡ ሬጂማንት ፡ ወታደር ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ መድፍ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ጠመንዣ ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ በመጋዘን ፡ አስቀምጦት ፡ የነበረውን ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ጥይትና ፡ ሥንቅ ፡ ለደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ አስረከባቸው ። ደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳም ፡ ይህን ፡ መሣሪያ ፡ ቀድሞ ፡ በነበራቸው ፡ ላይ ፡ አግኝተው ፡ ወታደራቸውን ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ አዘጋጅተው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ለእኅታቸው ፡ ለወይዘሮ ፡ ድንቅነሽ ፡ ባለቤት ፡ ለዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክዎ ፡ ድረስ ፡ እገዛልዎታልሁ ፡ ብለው ፡ የነበረውን ፡ ቃል ፡ ለውጠው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለርስዎ ፡ አልታዘዝም ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወሎን ፡ ለማስገበር ፡ እስከ ፡ ዘቢጥ ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ ነበርና ፡ የትግሬን ፡ መሸፈት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉንም ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ አቀኑ ። ወዲያውም ፡ በዛቻ ፡ ነገሩ ፡ የሚከናወን ፡ መስሏቸው ፡ የወታደራቸውን ፡ ብዛት ፡ ለማስረዳት ፡ አንድ ፡ ስልቻ ፡ ጤፍ አድርገው ወታደሬ ፡ በዚህ ፡ ልክ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ላኩላቸው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ባለቤት ፡ የደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ እኅት ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ በትግሪኛ ፡ ገጥመው ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

እናንት ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ዐድዋ ፡ አትሂዱ ፡
በእሳተ ፡ ገሞራ ፡ እንዳትነዱ ፡
ያባ ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ ቈራጥ ፡ ናት ፡ ሆዱ።

ደጃች ፡ ካሳም ፡ የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አባት ፡ አንካሳ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡
ከቱርክ ፡ ይዋጋል ፡ እንኳን ፡ ካንካሳ ፡
ያባ ፡ ፈንቅል ፡ ልጅ ፡ ወሬሳው ፡ ካሳ ፡

ብለው ፡ ፎከረው ፡ ወዲያውም ፡ ወታደርህ ፡ እንደዚህ ፡ ቢበዛ ፡ በጥይት ፡ ቈልቼ ፡ ነው ፡ የምሰደው ፡ ሲሉ ፡ ጤፉን ፡ ቈልተው ፡ መልሰው ፡ ላኩላቸው ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ስልሳ ፡ ሺሕ ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ አስከትለው ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺሕ ፡ የሚሆን ፡ ወታደር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያና ፡ ምቹ ፡ ስፍራ ፡ ይዘው ፡ የሚጠባበቋቸውን ፡ ደጃች ፡ ካሳን ፡ ለመግጠም ሄዱ። ጦርነቱም ፡ ሐምሌ 5 ፡ ቀን ፡ 1883 ፡ ዓ.ም ፡ ዐድዋ ፡ ካለው ፡ ሜዳና ፡ አሰም ፡ ከሚባለው ፡ ወንዝ ፡ ዳርቻ ፡ ላይ ፡ ተዠመረ ። ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በፈረስ ፡ ተቀምጠው ፡ እስከ ፡ ምሽጉ ፡ ድረስ ፡ ግባበት ፡ እያሉ በሠራዊታቸው ፡ ራስጌ ፡ ሆነው ፡ ሲዋጉ ፡ እነዚያ ፡ ግን ፡ ከጠባዩ ፡ ምሽግነት ፡ ያለውን ፡ ስፍራ ፡ ይዘው ፡ በርጋታ ፡ እያነጣጠሩ ፡ ሲተኩሱ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የተቀመጡበት ፡ ፈረስ ፡ ተመቶ ወደቀ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡም ፡ ክፉኛ ፡ አወዳደቅ ፡ ወደቁ። ወታደሮቻቸውም ፡ ንጉሣቸው ፡ የሞቱ ፡ መስሏቸው ፡ በድንጋጤ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሲባረሩ ፡ ስላዩዋቸው ፡ ደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ ያሉበትን ፡ ስፍራ ፡ ከነወታደሮቻቸው ፡ ትተው ፡ ሠራዊታቸውን ፡ አባረው ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ማረኳቸው ። ወዲያው ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ በሚባለው ፡ ተራራ ፡ አስረዋቸው ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ኖሩ ፡ ሞቱ። እቴጌ ፡ ድንቅነሽም ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ገጠሙ።

ተናግሬ ፡ ነበር ፡ እኔስ ፡ አስቀድሜ ፡
አሁን ፡ ምን ፡ ልናገር ፡ ከኀዘን ፡ ላይ ፡ ቆሜ ፡
የተሻረው ፡ ባሌ ፡ ተሿሚው ፡ ወንድሜ ፡
ከእንግዴህስ ፡ ወዲህ ፡ አለምንም ፡ ዕድሜ።

# ሌሎች ፡ የገጠሙት ።

ላባ ፡ በዝብዝ ፡ ግብር ፡ በቶሎ ፡ እንዲደርስ ፡
ጥሬውን ፡ ጤፍ ፡ ቢልክ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ስልቻው ፡ ተፈቶ ፡ ትግሬ ላይ ፡ ቢፈስ ፡

አባ ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ ቈላው ፡ እንደ ፡ ገብስ ።
የወንዱ ፡ አባ ፡ ታጠቅ ፡ ተቀባይ ፡ ሁነኽ
ምነው ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ደከመ ፡ ኀይልኽ።
ባባ ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ ታጥፎ ፡ ግንባርኽ ፡
ተሸክመኽ ፡ ወርደኽ ፡ አልጋኽን ፡ ሰጠኽ።
በሙሉ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ የተሠራው ፡ አልጋ ፡
ከሰቈጣ ፡ ወርዶ ፡ ትግሬ ፡ ተዘረጋ።
ለምን ፡ ትለኛለህ ፡ ሰቈጣ ፡ ሰቈጣ ፡
ጥንቱን ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ ለአኩስም ፡ የመጣ ፡
ዛሬ ፡ ጊዜ ፡ አግኝቶ ፡ ከላስታ ፡ ቢወጣ።

## ዳግማዊ ዓጼ ተክለ ጊዮርጊስ (ዋግሹም ጎበዜ ገብረ መድኅን)



# የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY


# ምዕራፍ ፡ 19 ።

## ደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ ዮሐንስ ፡ ተብለው ፡ እንደ ፡ ነገሡ ፡ -- ስለ ፡ ራስ ፡ አዳልና ፡ ስለ ፡ ራስ ፡ ደስታ ።

ደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሳ ፡ ሐምሌ ፡ 5 ፡ ቀን ፡ 1863 ፡ ዓ ፡ ም ፡ አፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ወግተው ፡ ድል ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ደስታቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርበው ፡ ወዲያው ፡ በ2ኛው ፡ ቀን ፡ ሐምሌ ፡ 7 ፡ ቀን ፡ የዐድዋ ፡ ሥላሴን ፡ በዓል ፡ አከበሩ ። ቤተ ፡ ክርስቲያኑንም ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ አሳንጸውት ፡ ነበርና ፡ ቅዳሴ ፡ ቤቱ ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ተደረገ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለበዓለ ፡ ንግሥ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሲያደራጁ ፡ ቈይተው ፡ ባ1864 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጥር 13 ፡ ቀን ፡ አኩስም ፡ ጽዮን ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ሥርዐተ ፡ ንግሥ ፡ ተደርጎ ፡ «ዮሐንስ ፡ 2ኛ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ» ፡ ተብለው ፡ በአቡነ ፡ አትናቴዎስ ፡ እጅ ፡ ተቀብተው ፡ በመላዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነገሡ ።

በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ በሸዋና ፡ በላስታ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የራያና ፡ ያዘቦ ፡ ጋላ ፡ ባጠገቡ ፡ ከሚገኘው ፡ ከክርስቲያን ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ያንድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ ቢሆኑ ፡ የሃይማኖትና ፡ የነገድ ፡ ልዩነት ፡ እያደረጉ ፡ ስለሚዛረፉ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ሁከት ፡ ሆኖ ፡ ነበረ ። ይህንኑ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ሰምተው ፡ ወደ ፡ ራያና ፡ አዘቦ ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ አጥፊዎቹን ፡ ቀጥተው ፡ አገሩን ፡ ካረጋጉ ፡ በኋላ ፡ ወዳገራቸው ፡ ተመለሱ ።

ቀጥሎ ፡ የጐጃሙ ፡ ራስ ፡ አዳል ፡ ተሰማ ፡ የሚቷቸን ፡ የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስን ፡ እኅት ፡ ወይዘሮ ፡ ላቀችን ፡ አግብተው ፡ አማች ፡ ከመሆናቸው ፡ በቀር ፡ ከዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጋራ ፡ ልዩ ፡ ፍቅር ፡ ነበራቸውና ፡ አማቴን ፡ አሳውረው ፡ ከሞት ፡ ላደረሷቸው ፡ ለዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ አልገዛም ፡ ብለው ፡ ለመሸፈት ፡ አስበው ፡ ነበር። ግን ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ከግርማቸውና ፡ ከጦር ፡ ሠራዊታቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ራስ ፡ አዳል ፡ ወታደራቸውን ፡ ይዘው ፡ ለመግጠም ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ በረሓ ፡ ገቡ።



አፄ ፡ ዮሐንስ

ንጉሡም ፡ የጐጃምን ፡ ግዛት ፡ ለቀድሞው ፡ ገዢ ፡ ለደጃች ፡ ደስታ ፡ ራስ ፡ ብለው ፡ ሰጥተው ፡ ወደ ፡ መቀሌ ፡ ተመለሱ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ አዳል ፡ የንጉሡ ፡ መራቅ ፡ ተመችቷቸው ፡ ሰው ፡ አሳብረው ፡ ራስ ፡ ደስታን ፡ በጦርነት ፡ ገጥመው ፡ ገደሏቸው። ራስ ፡ አዳልም ፡ ይህን ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ጐጃም ፡ ጥንትም ፡ ያባቴ ፡ ግዛት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ምሕረት ፡ አድርገው ፡ ይመልሱልኝና ፡ እኔም ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ እየገበርሁ ፡ ልገዛልዎ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ደብዳቤና ፡ መላክተኛ ፡ ላኩ ። ንጉሥ ፡ ግን ፡ የሾምሁትን ፡ ከገደልህ ፡ ደሙን ፡ ሳልበቀልለት ፡ ብትገብርልኝም ፡ ለመታረቅ ፡ አልችልም ፡ ብለው ፡ ሊወጓቸው ፡ አስበው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ግብጾች ፡ አሥመራንና ፡ የትግሬን ፡ ግዛት ፡ ለመያዝ ፡ የሚያስፈራሩበት ፡ ጊዜ ፡ በመሆኑና ፡ መኳንንቶቻቸውም ፡ እገብራለሁ ፡ ካለ ቢምሩት ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ምክር ፡ ስላቀረቡላቸው ፡ ከልብም ፡ ቢሆን ፡ ከአፍ ፡ እገብራለሁ ፡ ብለው ፡ ዕርቅ ፡ ለጠየቋቸው ፡ ለራስ ፡ አዳል ፡ የጐጃምን ፡ ግዛት ፡ መልሰው ፡ ሰጧቸው።

# ምዕራፍ ፡ 20 ።

## የግብጽ ፡ መንግሥት ፡ አገር ፡ ለመያዝ ፡ እንዳሰበ ፡ --የወርነር ፡ ሙንዚንገር ፡ ሞት ፡ -- መዠመሪያ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከግብጾች ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ።

የግብጽ ፡ መንግሥት ፡ የጥንቱን ፡ ገናናነት ፡ መልሶ ፡ ለማቋቋም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ለመግባት ፡ ሲያስብ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የኀይለኝነትና ፡ የጀግንነት ፡ ስም ፡ አግዶ ፡ ይዞት ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዠግንነት ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ያነሰ ባይሆን ፡ የግብጽ ፡ መንግሥት ፡ የግድ ፡ ግዛቱን ፡ የሚያሰፋበት ፡ ጊዜ ፡ በመድረሱ ፡ ይልቁንም ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ የነገሠው ፡ ኢስማኤል ፡ የሚባለው ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ በሜዲቴራንያ ፡ አጠገብ ፡ ከሚገኘው ፡ ከራሱ ፡ ግዛት ፡ ከግብጽ ፡ አንሥቶ ፡ ከሱዳን ፡ ጋራ ፡ ኢትዮጵያንም ፡ ጨምሮ ፡ ግዛቱን ፡ እስከ ፡ ህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ለማድረስ ፡ ያስብ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ በቱርክ ፡ መንግሥት ፡ እየተገዛ ፡ አስቀድሞ ፡ ወታደር ፡ እየላከ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ የሚገኘውን ፡ ከረንን ፡ በምሥራቅ ፡ ያለውን ፡ በርበራንና ፡ ዘይላን ፡ ሐረርንም ፡ ጭምር ፡ ይዞ ፡ ሲኖር ፡ ቀጥሎም ፡ 1ዱ ፡ ከታጁራ ፡ (ከጅቡቲ) ፡ 2ኛው ፡ ከምጥዋ ፡ ተነሥቶ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሰሜን ፡ ግዛት ፡ የሚይዝ ፡ ከሁለት ፡ የተከፈለ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አዘጋጀ።



ወርነር ፡ ሙንዚንገር

ከታጁራ ፡ ለሚመጣው ፡ የጦር ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፡ ወርነር ፡ ሙንዚንገር ፡ ፓሻ ፡ የሚባለው ፡ የስዊስ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ ተሾመ ። እሱም ፡ በካይሮና ፡ በእስክንድርያ ፡ የግብጾችን ፡ ልማድ ፡ ይዞ ፡ ካደገ ፡ ወዲህ ፡ ወዲያው ፡ ለግብጽ ፡ መንግሥት ፡ አገልግሎት ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ መጥቶ ፡ ከምጥዋ ፡ ወደ ፡ ከረን ፡ ከከረን ፡ ወደ ፡ በርበራ ፡ እየተመላለሰ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰሜን ፡ ደጎና ፡ አድርጎ ፡ በመመርመሩ ፡ የትግሬንም ፡ ቋንቋ ፡ ለማወቅ ፡ ቻለ ፡ በሱዳንም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላይ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ነበር።

የእንግሊዝም ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በጄኔራል ፡ ናፒየር ፡ አዝማችነት ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ለመውጋት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ መንገድ ፡ በመምራትና ፡ በማስተርጐም ፡ ደጎና ፡ አድርጎ ፡ ረድቶ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ ሙንዚንገር ፡ የግብጽን ፡ ወታደር ፡ ይዞ ፡ ከታጁራ ፡ ተነሥቶ ፡ የአውሳን ፡ በረሓ ፡ ሲጓዝ ፡ ውሎ ፡ እመሐመድ ፡ አንፋሪ ፡ ግዛት ፡ በተለይ ፡ አሰል ፡ እሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ ስለ ፡ መሸበት ፡ በዚያው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሌሊቱን ፡ ደንከሊዎች ፡ አግኝተው ፡ ከበቧቸው ። ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የከዱት ፡ አለቃ ፡ ብሩና ፥ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሤ ፡ የሚባሉ ፡ አብረው ፡ ነበሩ። ወታደሮቹም ፡ በበረሓ ፡ መንገድ ፡ ሲሄዱ ፡ ውለው ፡ ስለ ፡ ደከሙ ፡ የከበደ ፡ እንቅልፍ ፡ ተጭኗቸው ፡ ነበርና ፡ ምንም ፡ ሳይሰሙ ፡ ሙንዚንገር ፡ ፓሻ ፡ ከነሚስቱ ፡ ወደተኛበት ፡ ስፍራ ፡ ደንከሊዎቹ ፡ (ጥልጣሎቹ) ፡ ደረሱ።

ሙንዚንገርም ፡ ከእንቅልፉ ፡ ነቅቶ ፡ ሦስቱን ፡ ደንከሊዎች ፡ በጠመንዣ ፡ ከመካከላቸው ፡ እንደ ፡ ገደለ ፡ ወዲያው ፡ እነሱም ፡ በጦርና ፡ በጩቤ ፡ ወግተው ፡ ገደሉት ። ወታደሮቹም ፡ ከእንቅልፋቸው ፡ ነቅተው ፡ እየተደናበሩ ፡ ሲሸሹ ፡ ደንከሊዎቹ ፡ እየተከታተሉ ፡ ፈጁዋቸው።

እንደዚሁም ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ትግሬን ፡ ለመያዝ ፡ አራኬል ፡ ቤይ ፡ በሚባለው ፡ አርመናዊና ፡ ኮሎኔል ፡ አሬን ፡ ድሩፕ ፡ በሚባለው ፡ በተቀጠረ ፡ በዳንማርክ ፡ ተወላጅ ፡ አዝማችነት ፡ ሁለት ፡ ሺሕ ፡ ሁለት መቶ ፡ የሚሆን ፡ መድፍና ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ መሣሪያ ፡ የያዘ ፡ የግብጽ ፡ ሠራዊት ፡ ባሥመራ ፡ በኩል ፡ መጣ። ቀጥሎ ፡ ኩዶ ፡ ፈላሲን ፡ አልፎ ፡ ዐዲ ፡ ቀይሕ ፡ ደረሰ ። በዐዲ ፡ ቀይሕም ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ትቶ ፡ ሙንዚንገር ፡ በደንከሊዎች ፡ በተገደለበት ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ጉንደት ፡ ተጠጋ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ አስከትለው ፡ ወደመረብ ፡ ሄዱ። ቀጥለው ፡ ስመ ፡ ጥሩውን ፡ የጦር ፡ አዝማቻቸውን ፡ ራስ ፡ አሉላን ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ልከው ፡ እሳቸው ፡ ጕንዳጕንዲ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ሆነው ፡ ራስ ፡ አሉላ ፡ ከምዕራብ ፡ ንጉሡ ፡ ከምሥራቅ ፡ በኩል ፡ የግብጽን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከበቡት ። ወዲያው ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ ባ1866 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ውጊያው ፡ ተዠምሮ ፡ ከጧቱ ፡ ከሦስት ፡ ሰዓት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ስለ ፡ ቈየ ፡ ግብጾች ፡ መሸሻ ፡ ስፍራ ፡ አልነበራቸውና ፡ እጃችንን ፡ ሰጥተን ፡ ከምንማረክ ፡ መሞት ፡ ይሻለናል ፡ እያሉ ፡ በጥብቅ ፡ ይዋጉ ፡ ዠመር። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከነሱ ፡ በበለጠ ፡ ዥግንነት ፡ ስለ ፡ ወጓቸው ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ድል ፡ አደረጓቸው ። የግብጽም ፡

ጦር ፡ ገሚሱ ፡ እጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞቶ ፡ ገሚሱም ፡ ተማረከ ። የቀረውም ፡ እየሸሸ ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ ገባ።

# ምዕራፍ ፡ 21 ።

## ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በግብጾች ፡ ላይ ፡ ሁለተኛ ፡ ያገኙት ፡ ድል ።

በመዠምመሪያ ፡ የተላከው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ድል ፡ መሆን ፡ በግብጽ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ ሆኖ ፡ ባራቱ ፡ የአፍሪካ ፡ ማዕዘን ፡ የሚነገረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዝግንነት ፡ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ የተረጋገጠ ፡ ሆነ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የምስር ፡ ኸደዊ ፡ (ከዲብ) ፡ ኢስማኤል ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ሌላ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ልኬ ፡ ብድሬን ፡ ሳልመልስ ፡ እንደዚሁ ፡ ልተው ፡ አልችልም ፡ ብሎ ፡ እንግዴህ ፡ ቢበቃን ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ለመከሩት ፡ አረጋገጠላቸው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከቀድሞው ፡ የበለጠ ፡ ብዙ ፡ መድፍና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያ ፡ አሲዞ ፡ የኻያ ፡ አምስት ፡ ባታዮ ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲዘምት ፡ አደረገ።

ለዚህም ፡ ጦር ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፡ ከጀርመን ፡ የወታደር ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ በማጆርነት ፡ የወጣውን ፡ ሙለይ ፡ ሐሰን ፡ ፓሻ ፡ የሚባለውን ፡ የገዛ ፡ ልጁን ፡ ሾመው ። ከርሱም ፡ በቀር ፡ የግብጽ ፡ የጦር ፡ ሹማምቶች ፡ እየተመረጡ ፡ አብረውት ፡ ነበሩ። ከነዚሁም ፡ ሹማምቶች ፡ ውስጥ ፡ ስሙ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ራቲብ ፡ ፓሻ ፡ የሚባለው ፡ ነው። ባ1868 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር የግብጽ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከያለበት ፡ መጥቶ ፡ ምጥዋ ፡ ላይ ፡ ሰፈረ ። ከዚያም ፡ አልፎ ፡ ሰገነይቲ ፡ አጠገብ ፡ በተለይ ፡ ጉራዕ ፡ እሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ደረሰ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ ይኸንኑ ፡ ሰምተው ፡ ከትግሬ ፡ ወታደር ፡ በቀር ፡ ከሸዋም ፡ ከጐጃምም ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ጨምረው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ ለመደምሰስና ፡ ሕዝባችንን ፡ ባሪያ ፡ አድርጎ ፡ ሴቶቻችንንም ፡ ለማርከስ ፡ የሚፈልግ ፡ የእስላም ፡ ጦር ፡ መጥቶብናልና ፡ ወታደር ፡ ብረትኸን ፡ እየያዝኽ ፡ ተነሣ ፡ ቄስና ፡ ደብተራም ፡ በየቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ጸሎት ፡ አድርስ ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ ነግረው ፡ ስልሳ ፡ ሺሕ ፡ ደኅና ፡ ደኅና ፡ ብረት ፡ የያዙትን ፡ የጦር ፡ ወታደሮች ፡ ይዘው ፡ ግብጾች ፡ ወደ ፡ መሸጉበት ፡ ስፍራ ፡ በግፍ ፡ የመጡባቸውን ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ለመግጠም ፡ ሄዱ።

የዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ መምጣት ፡ በግብጾች ፡ ሰፈር ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፍርሃትና ፡ ድንጋጤ ፡ አደረባቸው። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ኣንድ ፡ ጊዜ ፡ ቈርጠው ፡ ከግብጽ ፡ ድረስ ፡ የመጡበት ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከመዋጋት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሚያደርጉት ፡ ነገር ፡ አልነበረም። ጦርነቱም ፡ ከመዠመሩ ፡

በፊት ፡ ምክር ፡ ሲደረግ ፡ ራቲብ ፡ ፓሻ ፡ እዚሁ ፡ እመሸግንበት ፡ ሆነን ፡ ስንከላከል ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በረኃብ ፡ ምክንያት ፡ ተመልሰው ፡ ይሄዳሉ ፡ ብሎ ፡ መከረ ። የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ማጆር ፡ ሐሰን ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያውንን ፡ ኀይል ፡ በመናቅና ፡ ቀድሞ ፡ በወገናቹ ፡ ላይ ፡ የደረሰባቸውን ፡ ድል ፡ በዕጥፍ ፡ ለመበቀል ፡ አይሆንም ፡ ብሎ ፡ ብዙውን ፡ ሠራዊት ፡ ከምሽጉ ፡ ውጭ ፡ አሰልፎ ፡ ወዲያው ፡ እንዲዋጉ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጉራዕ ፡ እሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ የሁለቱ ፡ ወገን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጦርነት ፡ ገጥሞ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በዠግንነት ፡ ሲዋጉ ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ወታደር ፡ ሞቶ ፡ ሬሳ ፡ በሬሳ ፡ ተከመረ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሐሰን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ ስለ ፡ ተረዳውና ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ሽማግሌው ፡ ራቲብ ፡ አስቀድሞ ፡ የመከረው ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ ወታደሩ ፡ በየምሽጉ ፡ ተመልሶ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዲዋጋ ፡ ትእዛዝ ፡ አደረገ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እግብጾች ፡ ሰልፍ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ በጨበጣ ፡ ይወጓቸው ፡ ነበርና ፡ አልተቻለም ። በምሽግም ፡ ቀርተው ፡ የነበሩት ፡ ግብጾች ፡ ወገናችንን ፡ ደርበን ፡ እንመታለን ፡ በማለት ፡ አንድም ፡ ጥይት ፡ ለመተኩስ ፡ አልቻሉም ። በኋላዎ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እየፎከሩ ፡ እስከ ፡ ምሽጉ ፡ ገብተው ፡ ይዋጉ ፡ ዠመር።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግብጾች ፡ በፍጹም ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ መሣሪያቸውን ፡ እየተው ሸሸት ፡ ዠመሩ። አዝማቻቸውም ፡ ሐሰን ፡ ጥቂት ፡ የተረፉትን ፡ ወታደሮቹን ፡ ይዞ ፡ በፈረስ ፡ ከዚያ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ሄደ። ያንንም ፡ ስፍራ ፡ ሌሊቱን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ኢትዮጵያውን ፡ ከበው ፡ ስለ ፡ ወጉት ፡ ወዲያው ፡ ከሹማምቶቹ ፡ ጋራ ፡ እጁን ፡ ሰጥቶ ፡ ተማረከ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለብሰው ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ምርኮኞቹ ፡ በፊታቸው ፡ እየተሰለፉ ፡ ሲያልፉ ፡ ሐሰን ፡ ፓሻን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ወደዚህ ፡ አቅርበው ፡ ብለው ፡ በሁለት ፡ ክንዱ ፡ ላይ ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ አስነቀሱበት ይባላል። በኋላ ፡ ግን ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ኢስማኤል ፡ ፓሻ ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ መላከተኛና ፡ ገንዘብ ፡ ልኮ ፡ ከታረቊ ፡ በኋላ ፡ እስረኞቹና ፡ ሐሰን ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ሄዱ ። ርግጠኛ ፡ ባልሆነ ፡ ባንዳንድ ፡ ታሪክ ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል።

«ሐሰን ፡ ድል ፡ መሆኑን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ጦርነቱን ፡ አቊሞ ፡ የቦጐስንና ፡ የሜንሳን ፡ አገር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ እለቃለሁና ፡ እንታረቅ ፡ ብሎ ፡ ወደ ንጉሥ ፡ ላከ። ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ግን ፡ ያለድርድር ፡ እጅኸን ፡ ካልሰጠኸ ፡ ድል ፡ መሆንኸን ፡ ከተረዳኸ ፡ በኋላ ፡ የለመንከውን ፡ ዕርቅ ፡ አታገኝም ፡ ብለው ፡ መልስ ፡ ላኩበት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሚሄድበትን ፡ በር ፡ ይጠብቊ ፡ ለነበሩት ፡ ለራስ ፡ ባሪያው ፡ የያዘውን ፡ ወርቊንና ፡ ገንዘቡን ፡ በሙሉ ፡ አስረክቦ ፡ ለማምለጥ ፡ ብቻ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በር ፡ ይክፈቱልኝ ፡ ብሎ ፡ ተስማምቶ ራስ ፡ ባሪያውም ፡ ከክብር ፡ ይልቅ ፡ ገንዘብ ፡ ወዳድ ፡ ኖረው ፡ ወርቊንና ፡ ገንዘቡን ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ በሩን ፡ ለቀቊለት። እሱም ፡ በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ ከዚያ ፡ የፈረጠጠ ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ሲጋልብ ፡ አድሮ ፡ በስንት ፡ ድካም ፡

ባ1868 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመጋቢት ፡ ምጥዋ ፡ ገባ ። ራስ ፡ ባሪያውም ፡ በዚሁ ፡ የተነሣ ፡ ተከሰው ፡ ስለ ፡ ተፈረደባቸው ፡ ታሰሩ» ፡ ይላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከማምለጡ ፡ ይልቅ ፡ በመማረኩ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍትና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ተስማምተውበታል።

ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ የግብጽን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ በዝግንነት ፡ እየተዋጉ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ስለ ፡ መለሱትና ፡ የዝግንነታቸው ፡ ዝና ፡ በውጭ ፡ አገርም ፡ በኢትዮጵያም ፡ ስለ ፡ ተሰማ ፡ ከጉራዕ ፡ ወደ ፡ ከተማቸው ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱና ፡ ሕዝቡ ፡ ተሰልፎ ፡ በእልልታና ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተቀበላቸው። ወዲያውም ፡ እንዲህ ፡ እየተባለ ፡ ይዘፈንላቸው ፡ ነበር ።

ከላይ ፡ የወረደው ፡ ከጽዮን ፡ መቅደስ ፡
ባባቱ ፡ ሚካኤል ፡ በናቱ ፡ ሥላስ ፡
ዐጨደው ፡ ከመረው ፡ ያን ፡ ያሕዛብ ፡ ገብስ ፡
ወቃው ፡ ደበደበው ፡ ሰጠው ፡ ለነፋስ ፡
ዐሊሙ ፡ ነፍጠኛ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ።

# ምዕራፍ ፡ 22 ።

## የንጉሥ ፡ ምኒልክና ፡ የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጦርነት ፡ - ንጉሥ ፡ ምኒልክና ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ቦሩ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተገናኙ ፡-----የራስ ፡ አርኣያና ፡ የወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ጋብቻ ።

በትግሬና ፡ በሐማሴን ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፥ ደጃች ፡ ደበበ ፥ ደጃች ፡ ባሕታ ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስና ፡ ከራስ ፡ አሉላ ፡ እየተቀያየሙ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ ወገን ፡ እየሆኑ ፡ (ወደ ፡ ፊት ፡ ተጽፎ ፡ እንደሚገኘው) ፡ አንገዛም ፡ እያሉ ፡ ያውኳቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንደዚሁም ፡ በሽዋና ፡ በጐጃም ፡ ያሉት ፡ መሳፍንት ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ እንዳይነሡባቸው ፡ የሁለቱ ፡ ኀይል ፡ ተመዛዝኖ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከዚህ ፡ የኀይል ፡ መመዛዘን ፡ ውስጥ ፡ የበላይነታቸው ፡ ክብር ፡ እንዲገኝ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የምኒልክን ፡ ንጉሥነት ፡ ባ1870 ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጋቢት ፡ 18 ፡ ቀን ፡ አውቀውላቸው ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ ወዲያው ፡ ራስ ፡ አዳልንም ፡ እበጌምድር ፡ ድረስ ፡ አስጠርተው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የጐጃም ፡ ባላባት ፡ ንጉሥ ፡ ተብሎ ፡ የማያውቀውን ፡ ስማቸውን ፡ ተክለ ፡

ሃይማኖት ፡ አሰኝተው ፡ ባ1873 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ባሉበት ፡ የንጉሥነት ፡ ማዕረግ ፡ ሰጧቸው።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ የሸዋ ፡ ግዛታቸውን ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲያሰፉ ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከጐጃም ፡ ግዛታቸው ፡ አሸከራቸውን ፡ ራስ ፡ ደረሶን ፡ ከሸዋ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ቀድመው ፡ አገር ፡ እንዲይዙ ፡ ላኳቸው። ከንጉሥ ፡ ምኒልክም ፡ የተላኩ ፡ ራስ ፡ ጐበና ፡ ነበሩና ፡ ከራስ ፡ ደረሶ ፡ ጋራ ፡ ካባይ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ጐድሩ ፡ ላይ ፡ ተገናኝተው ፡ ግጭት ፡ ዠመሩ። ስለዚህ ፡ ለራስ ፡ ደረሶ ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለራስ ፡ ጐበና ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ደርሰውላቸው ፡ የሁለቱ ፡ ወገን ፡ ጭፍራ ፡ ባ1874 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሚያዝያ ፡ 30 ፡ ቀን ፡ እምባቦ ፡ ላይ ፡ ተጋጥሞ ፡ ሲዋጋ ፡ ወዲያው ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቈስለው ፡ ተማረኩ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ በሩ ፡ ሜዳ ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ ምርኮኛውን ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ይዘኸ ፡ እንድትመጣ ፡ ብለው ፡ ለንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ደብዳቤ ፡ ላኩባቸው ።ንጉሥ ፡ ምኒልክም ፡ እንደ ፡ ደብዳቤው ፡ ቃል ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ‹ይዘው ፡ ቦሩ ፡ ሜዳ ፡ ሄደው ፡ በነሐሴ ፡ 6 ፡ ቀን ፡ ባ1874 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተገናኙ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ ያለርሳቸው ፡ ፈቃድ ፡ አገር ፡ በመያዝ ፡ የተነሣ ፡ ጦርነት ፡ በማድረጋቸው ፡ ከወቀሥዋቸው ፡ በኋላ ፡ የወሎን ፡ ግዛት ፡ ከንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ወስደው ፡ እሁለት ፡ ከፍለው ፡ 1ኛውን ፡ ለልጃቸው ፡ ለራስ ፡ አርኣያ ፡ 2ኛውን ፡ በፊት ፡ መሐመድ ፡ ዐሊ ፡ ሲባሉ ፡ ቈይተው ፡ በኋላ ፡ ሚካኤል ፡ አሰኝተው ፡ ክርስትና ፡ ላስነሡዋቸው ፡ ለራስ ፡ ሚካኤል ፡ ሰጧቸው።

እንደዚሁም ፡ አገው ፡ ምድርን ፡ ከንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወስደው ፡ ለራስ ፡ አሉላ ፡ ሰጧቸው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሁለቱ ፡ ንጉሦች ፡ ኀይል ፡ ተመዛዝኖ ፡ እኩል ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ሲያስቡ ፡ የንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ የኀይል ፡ ሚዛን ፡ እየደፋ ፡ ይሄድ ፡ ዠመር። ስለዚህ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ የወሎ ፡ ግዛት ፡ በመሄዱ ፡ ቅር ፡ ብሏቸው ፡ ሳለ ፡ ወዲያው ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዕርቅና ፡ ሰላም ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ እንዲመሠረት ፡ ልጃቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱን ፡ ለልጃቸው ፡ ለራስ ፡ አርኣያ ፡ ሥላሴ ፡ ይድሩላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለመኗቸው።

የዚህም ፡ የጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ ምኒልክ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የገነኑ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ኦልነበራቸውምና ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ቀጥለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ ሲጭኑ ፡ የልጃቸውን ፡ የወይዘሮ ፡ ዘውዲቱን ፡ ባል ፡ ራስ ፡ አርኣያ ፡ ሥላሴን ፡ ከርሳቸው ፡ ቀጥለው ፡ እንዲያነግሡላቸው ፡ ያሰቡ ፡ ይመስላል።

የራስ ፡ አርኣያና ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ሠርግ ፡ ባ1875 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥቅምት ፡ 13 ፡ ቀን ፡ ተሠርጎ ፡ በዚህ ፡ ጋብቻ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ በንጉሡ ፡ መካከል ፡ እምነት ፡ ከተመሠረተ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ደቡብና ፡ ምዕራብ ፡ አገር ፡ ግዛታቸውን ፡ ያሰፉ ፡ ዘንድ ፡ ለንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ፈቀዱላቸው።

# ምዕራፍ ፡ 23 ።

## ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ግዛታቸውን ፡ እንዳሰፉ ።

ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ከቦሩ ፡ ሜዳ ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ ከአባ ፡ ጅፋር ፡ ጋራ ፡ ተላልከው ፡ አባ ፡ ጅፋርም ፡ እገብራለሁ ፡ ብሎ ፡ የንጉሥ ፡ ምኒልክን ፡ ገዢነት ፡ ዐወቀ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ በሻሽ ፡ አቦዬ ፡ በጅማ ፡ አልፈው ፡ የጉማን ፥ የጌራን ፡ አገር ፡ አቀኑ። ቀጥለውም ፡ የከፋን ፡ አገር ፡ ሲገዙ ፡ ባላባቱ ፡ ጊጀብ ፡ ሆኖ ፡ ጥቂት ፡ ከተከላከለ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ገበረ ። ከዚያ ፡ በግቤና ፡ በአዋሽ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ያዙ።

ደጃች ፡ ባሻሽ ፡ አቦዬ ፡ ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ሲያቀኑ ፡ እንደዚሁ ፡ ራስ ፡ ጐበና ፡ ጨቦና ፡ ወሊሶን ፡ አመያንና ፡ ኖኖን ፡ ሌቃንና ፡ ለቀምትን ፡ ሰዮንና ፡ የወለጋን ፡ አገር ፡ አቀኑ።


ደግሞ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሊሙን ፡ ጃንጀሮን ፡ አስገበሩ ። በመጨረሻም ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ራሳቸው ፡ ሄደው ፡ የወላሞን ፡ አገር ፡ ካስገበሩ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የከፋ ፡ ባላባት ፡ ሸፍቶ ፡ ነበረና ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስንና ፡ ራስ ፡ ደምሰውን ፡ ልከው ፡ በጦርነት ፡ እንዲገብር ፡ አስገደዱት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ከራስ ፡ ደምሰው ፡ ጋራ ፡ የጅማው ፡ አባ ፡ ጅፋር ፡ አብሮ ፡ እየሄደ ፡ የከፋን ፡ አገር ፡ በማቅናት ፡ በጣም ፡ ረድቷል ። ንጉሥ ፡ ምኒልክም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ ከማስፋት ፡ ጋራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ 1 ፡ እንዲሆን ፡ የሸዋን ፡ ሕዝብ ፡ በድል ፡ ወደ ፡ ተያዘው ፡ አገር ፡ እየላኩ ፡ በድል ፡ በተያዘው ፡ አገር ፡ ያሉትን ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ አምጥተው ፡ በክብር ፡ እያሳደጉ ፡ በነገድ ፡ ተለያይቶ ፡ የነበረውን ፡ አዛመዱት። በጋብቻም ፡ አብሮ ፡ በመብላትም ፡ በሃይማኖትም ፡ አንድነት ፡ ተዋሕዶ ፡ በፍቅርና ፡ በወንድማማችነት ፡ እየተሳሰበ ፡ ስለ ፡ ሀገሩም ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ሕይወቱን ፡ እንዲሠዋ ፡ አደረጉት።

(ሙሶሊኒ ፡ ባ1927 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የሸዋ ፡ ሕዝብ ፡ ይህንን ፡ ኣገር ፡ በግድ ፡ አስገብሮ ፡ ሕዝቡን ፡ በግፍ ፡ ይገዛዋል ፡ የእኩልነት ፡ መብት ፡ የላቸውም) ፡ ብሎ ፡ ሐሰት ፡ የመላበትን ፡ ክስ ፡ ለዓለም ፡ ማኅበር ፡ አቀረበ ። ይህንንም ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ -የሚያስረዳ ፡ ምርኮኞች ፡ ተብለው ፡ ከሚጠሩት ፡ ውስጥ ፡ ልጆች ፡ ሆነው ፡ ደጃች ፡ ባልቻንና ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ አምጥተው ፡ ካሳደጓቸው ፡ በኋላ ፡ ለታላቅ ፡ ማዕርግ ፡ አበቋቸው።


በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሁለቱ መኳንንት ፡ ጉዞ ፡ እየተጓዙ ፡ እተማረኩበት ፡ ስፍራ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ባልቻ ፡ ይኸውልዎ ፡ የተማረክንበት ፡ ብለው ፡ ለፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አስታወሷቸው። ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስም ፡ ይህ ፡

ስፍራ ፡ የተባረክንበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የተማረክንበት ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ እውነተኛውን ፡ መልስ ፡ ሰጧቸው ፡ ይባላል።





ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዲነግዴ



ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ ሳፎ

# ምዕራፍ ፡ 24 ።

## የአውሮፓ ፡ መንግሥታትና ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዐሰብ ፡ በር።

ላለፉት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ጒዳይ ፡ የነበራቸው ፡ የፖርቱጋል ፥ የአስፓንያ ፥ የቱርክና ፡ የግሪክ ፡ መንግሥታት ፡ ነበሩ ። ካንደኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ አንሥቶ ፡ አሁን ፡ እስካለንበት ፡ ድረስ ፡ ግን ፡ ከኢጣሊያ ፡ በቀር ፡ ከጠላትነት ፡ ይልቅ ፡ - በወዳጅነት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ መንግሥታት ፡ እንግሊዝ ፥ ፈረንሳዊ ፥ መስኮብ ፥ ጀርመን ፡ ናቸው ። እንግሊዝ ፡ በሰሜን ፡ አፍሪካ ፡ በግብጽ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የበላይነቱን ፡ ክብር ፡ በመደገፍና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ድል ፡ በማድረጉ ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ በመዠመሪያ ፡ ከትግሬው ፡ ገዥ ፡ ከደጃች ፡ ንጉሤ ፡ ጋራ ፡ በመላላኩና ፡ በኋላም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የጅቡቲ ፡ ቊራጭ ፡ መሬት ፡ በእጁ ፡ በመሆኑ ፡ የመስኮብ ፡ መንግሥት ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖት ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ በመሆኑ ፡ እነዚህ ፡ እላይ ፡ የተባሉት ፡ መንግሥታት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አኳኋን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለመግባት ፡ አበክረው ፡ ይደክሙ ፡ ነበር። ነገር ፡ ግን ፡ ከመስኮብና ፡ ከጀርመን ፡ በስተቀር ፡ ሁለቱ ፡ እላይ ፡ የተባሉት ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ ከእስያ ፡ ውስጥ ፡ ካላቸው ፡ ግዛት ፡ በስተቀር ፡ በሰሜንና ፡ በደቡብ ፡ በምዕራብ ፡ ያለውን ፡ የአፍሪካን ፡ ግዛት ፡ ገሚሱን ፡ በቅኝነት ፡ ገሚሱን ፡ በጠባቂነት ፡ ስም ፡ ተከፋፍለው ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ ይዘው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ አጋጥሟት ፡ በሰላምና ፡ በወዳጅነት ፡ ለመግባት ፡ ከማሰብ ፡ በስተቀር ፡ እንደ ፡ ኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በነገሩ ፡ በጣም ፡ አልተጨነቊበትም ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ የሚፈልጋቸውን ፡ እስረኞች ፡ ካገኘ ፡ ወዲህ ፡ በመጣበት ፡ መንገድ ፡ ወዳገሩ ፡ ተመለሰ ፡ እንጂ ፡ ለመግዛት ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዋጋለን ፡ እያሉ ፡ ከሚያስቡት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከነበሩት ፡ መሳፍንት ፡ ጋራ ፡ በፍጹም ፡ ጠብ ፡ ሊያበቅል ፡ አልፈለገም።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ በአውሮፓ ፡ ያለውን ፡ የራሱን ፡ ግዛት ፡ ከሰሜን ፡ በኩል ፡ የነምሳ ፡ (የኦትሪሽ) ፡ መንግሥት ፡ እያጠቃ ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ ወሰደበት ። መንግሥቱም ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ አንድ ፡ ሳይሆን ፡ የተከፋፈለ ፡ ነበርና ፡ ይኸንኑ ፡ የተከፋፈለውን ፡ አንድ ፡ ለማድረግና ፡ የነምሳ ፡ መንግሥት ፡ የወሰደውን ፡ ለመመለስ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ሲፋሰስ ፡ ቈይቶ ፡ ነበርና ፡ ከአፍሪካ ፡ ሰፊ ፡ ግዛት ፡ ሳያገኝ ፡ በመቅረቱ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ጸጸት ፡ ነበረበት ። ስለዚህ ፡ በካቡር ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትርነት ፡ የመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ በመላው ፡ የኢጣሊያ ፡ አሳብና ፡ ጥረት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመያዝ ፡ ሆነ ። ስለዚህ ፡ እንደ ፡ ተለመደ ፡ ወታደር ፡ ከመላኩ ፡ በፊት ፡ አባ ፡

ማስያስንና ፡ ጁሴፔ ፡ ሳፔቶን ፡ ሌሎችንም ፡ በወንጌል ፡ ስብከት ፡ ስም ፡ ወዲያውም ፡ ያገሩን ፡ አኳኋን ፡ የሚመረምሩ ፡ ሚሲዮናውያን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላከ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመግባት ፡ መዠመሪያ ፡ እግሩን ፡ የሚያስቀምጥበት ፡ ስፍራ ፡ ማግኘት ፡ ያስፈልገው ፡ ነበርና ፡ ጁሴፔ ፡ ሳፔቶ ፡ የሚባለው ፡ የላዛሪስት ፡ ሚሲዮናዊ ፡ የዐሰብን ፡ የወደብ ፡ በር ፡ ለመግዛት ፡ ኢብራሂምና ፡ ሐሰን ፡ መሐመድ ፡ ከሚባሉት ፡ ከዐሰብና ፡ ከራሂታ ፡ ሥልጣኖች ፡ ጋራ ፡ ተነጋገረ። እነዚህም ፡ ሡልጣኖች ፡ በዚች ፡ በሚሸጡለት ፡ ራጭ ፡ ቦታ ፡ ገብቶ ፡ ወደፊት ፡ የነሱንና ፡ የብዙ ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ደም ፡ ማፍሰሱን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሊቀበሉት ፡ የቀረበላቸው ፡ ገንዘብ ፡ አእምሯቸውን ፡ ጋርዷቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ለመሸጥ ፡ ፈቃዳቸው ፡ መሆኑን ፡ ገለጹለት ። ስለዚህ ፡ ሚሲዮናዊው ፡ ከዐሰብ ፡ ተነሥቶ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡ ፍሬንሴ ፡ በፍጥነት ፡ ሄዶ ፡ ከውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትሩና ፡ በመርከብ ፡ ሸቀጥ ፡ እያመላለሰ ፡ ከሚነግደው ፡ ሩባቲኖ ፡ ከሚባለው ፡ ማኅበር ፡ ፕሬዚዳን ፡ ጋራ ፡ ተነጋገረ ። ነገሩም ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥትንና ፡ ማኅበሩን ፡ ደስ ፡ ስላሰኘ ፡ 20 ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አስታቅፈው ፡ ወደ ፡ ዐሰብ ፡ መልሰው ፡ ያንኑ ፡ ሚሲዮናዊ ፡ ላኩት። እሱም ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ እላይ ፡ ከተባሉት ፡



ሡልጣን ፡ ኢብራሂም ፡ ዐሰብን ፡ የሸጠ

ሡልጣኖች ፡ ጋራ ፡ ተገናኝቶ ፡ የግዢውን ፡ ጉዳይ ፡ ተነጋግሮ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ 7 ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ የሚሆነውን ፡ እባሕር ፡ ዳር ፡ ያለውን ፡ መሬት ፡ በስምንት ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ መግዛቱን ፡ «ሩባቲኖ» ፡ በሚባለው ፡ በመርከብ ፡ ዕቃ ፡ እያመላለሰ ፡ በሚነግደው ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ ተፈራረመ።

ወዲያው ፡ ሡልጣኖቹ ፡ ገንዘቡን ፡ ተቀብለው ፡ በማግስቱ ፡ ስለ ፡ ደስታው ፡ ኻያ ፡ አንድ ፡ ጊዜ መድፍ ፡ ተተኩሶ ፡ የኢጣሊያ ፡ ባንዲራ ፡ ተተከለ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያኸል ፡ በማኅበሩ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ቈየ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ለማኅበሩ ፡ 416 ፡ ሺሕ ፡ ሊሬ ፡ ከፍሎ ፡ በጭራሽ ፡ ከማኅበሩ ፡ ወስዶ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ከኢጣሊያ ፡ አገር ፡ እያመጣ ፡ በዙሪያው ፡ ያለውንና ፡ ዕቀይ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ደሴቶች ፡ ጭምር ፡ በውልም ፡ በውጊያም ፡ እያለፋፉ ፡ ያዘ ።

የኤርትራ ፡ መያዝ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ አግዞት ፡ እንደ ነበረ ፡ የዐሰብ ፡ መያዝ ፡ ደግሞ ፡ ኤርትራን ፡ ለመያዝ ፡ በጣም ፡ አግዞት ፡ ነበረ።

ጁሴፔ ፡ ሳፔቶ ፡ ከሡልጣኖቹ ፡ ተነጋግሮ ፡ የዐሰብን ፡ በር ፡ በመዠመሪያ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ ገዝቶ ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ትልቅ ፡ ውለታ ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ፎቶግራፉን ፡ በያለበት ፡ እየለጠፉ ፡ መጽሐፍም ፡ እየጻፉ ፡ ያመሰግኑታል ።

# ምዕራፍ 25 ።

## <u>የዓፄ ፡ ዮሐንስና ፡ የኢጣልያኖች ፡ ግንኙነት --- የኢጣልያ ፡ ጦር ፡ ምጥዋ ፡ እንደገባ - የሰሐጢና ፡ የዶጋዓሊ ፡ ጦርነት ፡--- የሐረርጌ ፡ መያዝ ።</u>

የኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ በዘመኑ ፡ በነበረው ፡ ደካማነት ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ እንግሊዝና ፡ እንደ ፡ ፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ ኃይል ፡ አግኝቶ ፡ በእስያና ፡ በአፍሪቃ ፡ ለመስፋፋት ፡ አልቻለም ። በአውሮፓም ፡ የሚያደርገው ፡ ፖለቲካ ፡ በነምሳ ፡ መንግሥት ፡ ተጫኝነት ፡ የተነካ ፡ የደከመ ፡ ነበር።

ነገር ፡ ግን ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ በግዛትም ፡ በኃይልም ፡ በሀብትም ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ይፎካከር ፡ ነበርና ፡ ግብፆችና ፡ ቱርኮች ፡ ለቀውት ፡ የሚሔዱትን ፡ ምጥዋንና ፡ በዙሪያው ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ይልቅ ፡ ኢጣልያ ፡ ብትይዘውና ፡ ኃይሉዋ ፡ ትንሽ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ደረጃ ፡ ቢጠጋ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ይወድ ፡ ነበር።

ስለዚህ ፡ የኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ አሥመራንና ፡ ምጥዋን ፡ ሱማሌንም ፡ ለመያዝ ፡ ችሎታ ፡ ያገኘው ፡ በእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ደጋፊነት ፡ ነው። የኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ እነዚህን ፡ አገሮች ፡ ከመያዙ ፡ በፊት ፡ በንግድና ፡ በወዳጅነት ፡ ምክንያት ፡ መላክተኞች ፡ እየላከ ፡ ከዓፄ ፡ ዮሐንስና ፡ ከንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግ ፡ ወደ ፡ ዓፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ካቫሊዬር ፡ ብራንኪ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ማርኬዝ ፡ አንቲኖሪ ፡ ተልከው ፡ ነበር ። ብራንኪም ፡ ከነተከታዮቹ ፡ ዓፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ቆንሲል ፡ ሆኖ የመንግሥቱን ፡ ፖለቲካ ፡ እየጠበቀ ፡ የኢጣልያንን ፡ ንጉሥ ፡ መልእክትና ፡ ወዳጅነት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይነግራቸው ፡ ነበርና ፡ እርሳቸውም ፡ የልብ ፡ ወዳጅ ፡ መስሎአቸው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ መልእክት ፡ ሁለት ፡ የአንበሳ ፡ ግልገሎች ፡ ጨምረው ፡ ለኢጣልያ ፡ ንጉሥ ፡ ላኩ።

«እኔ ፡ ዓፄ ዮሐንስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ነገሥት ፡ በእናታችን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቸርነት ፡ ይህቺን ፡ ደብዳቤ ፡ እልካለሁ ።

## ግርማዊ ፡ የኢጣልያ ፡ ንጉሥ ፡ ኡምቤርቶ ፡

የወዳጅነት ፡ ሰላምታዬን ፡ ይቀበሉኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እኔ ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እስላሞች ፡ መንገዱን ፡ ስለዘጉብኝ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ጽፌ ፡ አላውቅም ። አሁን ፡ ግን ፡ ይህችን ፡ መንገድ ፡ ክፍቼ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ መጻፍ ፡ ስለቻልኩ ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ተልከው ፡ እዚህ ፡ ያሉት ፡ ኢጣልያኖች ፡ ይህቺን ፡ ደብዳቤ ፡ እንድጽፍልዎ ፡ መልካም ፡ ምክንያት ፡ ሰጡኝ። ከግርማዊነትዎ ፡ ጋር ፡ ወዳጅነትዎን ፡ እንደ ፡ አገኘሁ ፡ ብዙ ፡ የምዋዋለው። ፡ ጉዳይ ፡ አለኝ ። ከእኔ ፡ ወገን ፡ ወዳጅነት ፡ ለመጀመሬ ፡ ምልክት ፡ እንዲሆንዎ ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ ይዞ ፡ የሚመጣው ፡ መላክተኞዬ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ አንበሶች ፡ እንዲያበረክትልዎ ፡ አዝዣለሁ።

ጐንደር ፡ ከተማ ፡ ሰኔ ፡ 11 ፡ ቀን ፡ 1871 ፡ ዓ ፡ ም

የኢጣልያ ፡ መንግሥት ከአንድ ፡ ወገን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ከሌላው ፡ ወገን ፡ የእንግሊዝን ፡ መንግሥት ፡ ወዳጅነት ፡ በማግኘቱ ፡ ግብጾች ፡ የሚለቁትን ፡ ምጥዋን ፡ ለመያዝ ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ንግግር ፡ ያደርግ ፡ ነበር ። የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በሒዊት ፡ አማካይነት ፡ የምጥዋ ፡ በር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሊሰጥ ፡ የግብፅንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ከአዋዋለ ፡ በኋላ ፡ ተፎካካሪው ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ከታጁራ ፡ ተነሥቶ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ አገሮች ፡ የያዘ ፡ እንደሆነ ፡ ኃይል ፡ አግኝቶ ፡ ሱዳንን ፡ እንዳይነጥቀው ፡ በመሥጋት ፡ ምጥዋን ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲይዝ ፡ ለኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ መከረው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ እንደ ፡ ውሉ ፡ ቃል ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምጥዋን ፡ በር ፡ እንዳታገኝ ፡ ከዳች ፡ ማለት ፡ ነው።

ስለዚህ ፡ የኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ ኮሎኔል ፡ ሳሊታን ፡ 800 ፡ ወታደር ፡ አሲዞ ፡ ምጥዋን ፡ እንዲይዝ ፡ ከናፖሊ ፡ ላከው ፡ ወታደሩም ፡ በ1878 ፡ ዓመት ፡ በጥር ‹ ወር ፡ መጨረሻ ፡ ምጥዋ ፡ ላይ ፡ ተራገፈና ፡ የቶሉዱን ፡ የአቲምሎን ፡ የምንኩሎን ፡ የራስ ፡ ማዱርን ፡ ምሽጐችና ፡ የጉራር ፡ ደሴቶችን ፡ ጭምር ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ያዘ ። የግብፅም ፡ ወታደር ፡ የመልቀቂያው ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ያውቃልና ፡ በፍጹም ፡ አልተቃወመም ። በየምሽጉም ፡ ላይ ፡ የግብፅና ፡ የኢጣልያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማዎች ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ተሰቅለው ፡ ሲውለበለቡ ፡ የሁለቱም ፡ ወገን ፡ ወታደሮች ፡ በሰላም ፡ አንድነት ፡ ሰነበቱ። የዚህንም ፡ ወሬ ፡ ሰምተው ፡ ዓፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በጣም ፡ ተናደው ፡ ስለነበረ ፡ ግርማዊነታቸውን ፡ ለማባበልና ፡ የኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ በመንግሥታቸው ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ጉዳት ፡ አያደርግም ፡ ለማለት ፡ የንጉሥን ፡ ደብዳቤና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ይዞ ፡ ካፒቱን ፡ ፌራሪ ፡ ከኢጣልያ ፡ አሥር ፡ ወደ ፡ ዓፄ ዮሐንስ ፡ መጣ። ዓፄ ዮሐንስም ፡ ምጥዋ ፡ በታሪክም ፡ በአገር ፡ አቀማመጥም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በተደረገው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ለመያዝ ፡ የሚያስቡትን ፡ አገር ፡ አስቀድሞ ፡ በጦር ፡ እየያዘ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ወዳጅ ነኝና ፡ ምንም ፡ ልበድልዎ ፡ አልችልም ፡ ቢል ፡ ነገሩ ፡ ሊያሳስታቸው ፡ አይችልምና ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ቀልድ ፡ ያለበትን ፡ ወዳጅነት ፡ አልተቀበሉትም ። ስለዚህ ፡ መላክተኛው ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ መሔድ ፡ ግድ ሆነበት ።

ምጥዋን ፡ የኢጣልያ ፡ ወታደር ፡ በመያዙ ፡ እንዲሁ ፡ የሐማሴን ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ስመ ፡ ጥሩው ራስ ፡ አሉላ ፡ በጣም ፡ ተናደው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በኢትዮጵያና ፡ በግብፅ ፡ መንግሥት ፡ መኻከል ፡ ስለምጥዋ ፡ ውል ፡ መደረጉን ፡ ያውቃሉና ፡ ነገሩ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለመረዳት ፡ ሲሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ደብዳቤ ፡ ለግብፆች ፡ አዛዥ ፡ ላኩ።

# የተላከ ፡ ከራስ ፡ አሉላ ፡ ዝውእቱ ፡ ቱርክ ፡ ባሻ ፡ ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ማርኮፖሎ ፡ ቢይ ፡

ኢጣልያኖች ፡ መጥተው ፡ ምጥዋን ፡ሲይዙት ፡ ለምን ፡ አታባርሩዋቸ. ውም። እኔስ ፡ ለግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ለከዲቭ ፡ ከበሬታ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በምጥዋ ፡ መኻከል ፡ ያለውን ፡ በር ፡ እዘጋው ፡ ነበር ፡ እናንተስ ፡ ቢሆን ፡ እንደምን ፡ ፈቃድ ፡ ሰጣችኋቸው ፡ አሁንም ፡ አባርሩዋቸው ። ይህቺም ፡ ሥፍራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ መሆንዋንና ፡ ኢጣልያኖችም ፡ እንዲቀመጡ ፡ አለመፍቀዱን ፡ በስመ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዮሕንስ ፡ አስታውቃችኋለሁና ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ይመለሱ ፡ ሐምሌ ፡ 3 ፡ ቀን ፡ 1878 ፡ ዓ ፡ ም ፡

ኢጣልያ ፡ ምጥዋን ፡ የያዘው ፡ በጠባቂያቸውና ፡ በወዳጃቸው ፡ በእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ፈቃድና ፡ ውስጠ ፡ ስምምነት ፡ መሆኑን ፡ ግብፆች ፡ ያውቃሉና ፡ ኢጣልያኖችን ፡ መቃወም ፡ ቀርቶ ፡ ለደብዳቤያቸው ፡ እንኳን ፡ መልስ ፡ አልሰጡዋቸውም ፡ የኢጣልያ ፡ መንግሥትም ፡ ወደ

፡ ምጥዋ ፡ እያከታተለ ፡ አዲስ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ይልክ ፡ ዠመር ። በመጨረሻም ፡ የመጣው ፡ በጀኔራል ፡ ካርሎ ፡ ዠኔ ፡ የሚታዘዘው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከምሽግ ፡ እየወጣ ፡ እስከ ፡ ሰሐጢና ፡ እስከ ፡ ዊአ ፡ ድረስ ፡ እየመጣ ፡ አገር ፡ ይይዝ ፡ ጀመር። ራስ ፡ አሉላም ፡ እንደገና ፡ ለራሱ ፡ ለኢጣልያኑ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ለጀኔራል ፡ ካርሎ ፡ ዠኔ ፡ አላገባብ ፡ የያዘውን ፡ አገር ፡ ለቆ ፡ እንዲሔድ ፡ ላኩበት ።

እሱም ፡ አለቅም ፡ ሲል ፡ የመጨረሻ ፡ አሳቡን ፡ ከገለጸላቸው ፡ በኋላ ፡ ወታደራቸውን ፡ ይዘው ፡ ሄደው ፡ መሽጎ ፡ ይጠባበቅ ፡ ከነበረው ፡ ከማጆር ፡ ቦረቲ ፡ ጋራ ፡ ውጊያ ፡ ገጥመው ፡ ድል ፡ አደረጉት ፡፡፡ ቀጥሎ ፡ ሌተና ፡ ኮሎኔል ፡ ቶማስ ፡ ዲ ፡ ክሪስቶፎሮስ ፡ የሚባል ፡ ሦስት ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ይዞ ፡ ዶገዓሊ ፡ (ተደዓሊ) ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ መጥቶ ፡ ባ1879 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ 17 ፡ ቀን ፡ ከራስ ፡ አሉላ ፡ ጋራ ፡ ሁለተኛ ፡ ጦርነት ፡ ተጋጠሙ።

ራስ ፡ አሉላም ፡ ኮሎኔሉ ፡ በትምህርት ፡ ካገኘው ፡ የጦር ፡ መላ ፡ ይልቅ ፡ ርሳቸው ፡ ከጠባያቸው ፡ ያገኙት ፡ የጦር ፡ ዕቅድ ፡ ይበልጥ ፡ ነበርና ፡ ወዲያው ፡ የመጣውን ፡ ጦር ፡ ከበው ፡ ሁሉንም ፡ ፈጁት ። ስለዚህ ፡ የራስ ፡ አሉላ ፡ ዠግንነት ፡ በተወላጆቻቸው ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ቀርቶ ፡ የባዕዱ ፡ የኢጣሊያ ፡ ታሪክ ፡ እንኳን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ሲያስታውሳቸው ፡ ይኖራል ።

## ስለራስ ፡ አሉላ ፡ የተገጠመ ፡

መብቱን ፡ ዮሐንስ ፡ ላሉላ ፡ ቢሰጠው ፡
እንደ ፡ ቀትር ፡ እሳት ፡ ቱርክን ፡ ገላመጠው ፡
ጣልያንም ፡ ወደቀ ፡ እያንቀጠቀጠው ፡
አጭዶና ፡ ከምሮ ፡ እንደ ፡ ገብስ ፡ አሰጣው ።

አባ ፡ ነጋ ፡ አሉላ ፡ ካሥመራ ፡ ቢነሣ ፡
እንዳንበሳ ፡ ሆኖ ፡ እሳት ፡ እያገሣ ፡

የችግር ፡ ምስጋና ፡ ባይወሳ ፡
ቢቸግረው ፡ ጣልያን ፡ አለ ፡ ፎርሳ ፡ ፎርሳ ።

ጣልያን ፡ ባገርህ ፡ አልሰማህም ፡ ወሬ ፡
የበዝብዝ ፡ አሽከሮች ፡ እነሞት ፡ አይፈሬ ፡
ዘለው ፡ ጉብ ፡ ይላሉ ፡ እንደ ፡ ጒፈር ፡ አውሬ።

አባ ፡ ነጋ ፡ አሉላ ፡ የደጋ ፡ ላይ ፡ ኮሶ ፡
በጥላው ፡ ያደክማል ፡ እንኳንስ ፡ ተቀምሶ።

ጣልያን ፡ ሰሐጢ ፡ ላይ ፡ እግሩን ፡ ቢዘረጋ ፡
በብረት ፡ ምጣዱ ፡ በሰሐጢ ፡ ኣደጋ ፡
አንገርግቦ ፡ ቆላው ፡ አሉላ ፡ አባ ፡ ነጋ።

ተው ፡ ተመከር ፡ ጣልያን ፡ ይሻላል ፡ ምክር ፡
ሰሐጢ ፡ ላይ ፡ ሆነህ ፡ መሬት ፡ ብትቆፍር ፡
ኋላ ፡ ይሆንሃል ፡ ላንተው ፡ መቃብር ፡
ይቺ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የበዝበዝ ፡ አገር ፡
ምንም ፡ አትቃጣ ፡ እንዳራስ ፡ ነበር ።

የዶጋዓሊም ፡ የጦርነት ፡ ፍጻሜ ፡ ወሬው ፡ በያለበት ፡ ሲነዛ ፡ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ በኢጣልያ ፡ አገር ፡ ሲሰማ ፡ ታላቅ ፡ ኀዘን ፡ ሆኖ ፡ ወዲያውም ፡ 20 ፡ ሺሕ ፡ የሚሆኑ ፡ ወታደሮች ፡ ከኢጣልያ ፡ መጥተው ፡ ምጥዋ ላይ ፡ እንዲሰበሰቡና ፡ ያለፈውን ፡ ብድር ፡ እንዲመልሱ ፡ ታሰበ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ጦራቸውን ፡ አስከትተው ፡ ወዲያው ፡ የኢጣሊያንን ፡ በግፍ ፡ መምጣት ፡ ለእንግሊ" ፡ መንግሥት ፡ በደብዳቤ ፡ አስታውቀው ፡ ነበርና ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት፡ ፡ ሁለቱን ፡ ጠበኞች ፡ ለመገላገል ፡ ያቀረበው ፡ አሳብ ፡ ሳይፈጸም ፡ ቀርቶ ፡ ለጦርነት ፡ ተሰላለፉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የነበሩበት ፡ ስፍራ ፡ በረሓና ፡ ውሃ ፡ የሌለበት ፡ በመሆኑ ፡ ግጭት ፡ እንጂ ፡ የገሃድ ጦርነት ፡ ሳያደርጉ ፡ ሁለቱም ፡ በየስፍራቸው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሱ ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ዐሰብን ፡ በግዥ ፡ ምጥዋን ፡ በጦርነት ፡ ካገኘ ፡ ወዲህ ፡ እንዲሁ ፡ ሐረርም ፡ ከግብጽ ፡ ተገዥነት ፡ ሲወጣ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ እንዳይቀየምበት ፡ አስፈቅዶ ፡ ሐረርጌን ፡ ለመያዝ ፡ አሰበ ። ስለዚህ ፡ ወታደር ፡ ከመላኩ ፡ በፊት ፡ አገሩን ፡ የሚሰልሉ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ላከ ። እነሱንም ፡ የሐረሩ ፡ ባላባት ፡ አግኝቶ ፡ ከገደላቸው ፡ ወዲህ ፡ ወገኖቻችን ፡ የሞቱበት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ልኮ ፡ ለመያዝ ፡ ሲያስብ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ከእንጦጦ ፡ ከተማቸው ፡ ይኸንኑ ፡ ሐረርጌን ፡ ለመያዝ ፡ ኅዳር ፡ 4 ቀን ፡ 1879 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ተነሡ።


ጉዚቸውን ፡ ባሩሲ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ በጨርጨር ፡ አልፈው ፡ ጨለንቆ ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሐረርን ፡ ይገዛ ፡ የነበረው ፡ አሚር ፡ ዐብዱላሂ ፡ ሳይቀድሙኝ ፡ ልቅደማቸው ፡ በማለት ፡ ከሐረር ፡ ተነሥቶ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩበት ፡ ደረስና ፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በታኅሣሥ ፡ 29 ቀን ፡ ጦርነቱን ፡ ገጠመ። ነገር ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፡ የሸዋ ፡ ጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ ስለ ፡ ጨረሰበት ፡ በፈረስ ፡ አምልጦ ፡ ሐረር ፡ ገባ። ከዚያም ቤተሰቡን ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ሌሊት ፡ ከተማውን ፡ ጥሎ ፡ ጠፋ።



ጁሴፔ ፡ ሳፔቶ

ንጉሥ ፡ ምኒልክም ፡ ካሉበት ፡ ስፍራ ፡ ተጉዘው ፡ በታላቅና ፡ በሚያስፈራ ፡ ግርማ ፡ ሐረር ፡ ገብተው ፡ ባለኸ ፡ ርጋ ፡ ብለው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ አቆሙ። አገሩንም ፡ እንዲያስተዳድሩ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ባላምባራስ ፡ የነበሩትን ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ ብለው ፡ ሾሚቸውና ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ በየካቲት ፡ 28 ፡ ቀን ፡ እንጦጦ ፡ ከተማቸው ፡ ተመልሰው ፡ ገቡ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በዚህ ፡ በሐረር ፡ መያዝ ፡ የተነሣ ፡ ከንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ መጣላት ፡ ሲያምረው ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ተጣልቶ ፡ ነበርና ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ጠላት ፡ እንዳያፈራ ፡ «የሐረር ፡ ባላባት ፡ የገደላቸውን ፡ የኢጣሊያኖችን ፡ ደም ፡ ተበቅለው ፡ አገሩን ፡ እንኳን ፡ ያዙት» ፡ ሲል ፡ ውስጠ ፡ ንዴት ያለበትን ፡ የደስታ ፡ ቃል ፡ ላከባቸው።



ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል

# ምዕራፍ ፡ 26 ።

## ስለ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ።

ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ከሐማሴን ፡ ባላባት ፡ ወገን ፡ ይወለዳሉ። አባታቸው ፡ አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ ኢያታቸው ፡ ከንቲባ ፡ ዘርዓይ ፡ ይባላሉ ። አገራቸውም ፡ ሐዘጋ ፡ ነው ፡ በዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ሸፍተው ፡ ሲኖሩ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ደጃች ፡ ኀይሉን ፡ አስረው ፡ የሐማሴንን ፡ ግዛት ፡ ራስ ፡ አሉላን ፡ ቈራጭ ፡ አድርገው ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ሰጧቸው። በዚሁ ፡ በራስአሉላ ፡ ቈራጭነት ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ተቀይመው ፡ ቢሸፍቱ ፡ ደጃች ፡ ኀይሉን ፡ ፈተው ፡ ወደ ፡ ሐማሴን ፡ ላኳቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከደጃች ፡ ኀይሉ ፡ ጋራ ፡ ማዕበላ ፡ ላይ ፡ ተዋግተው ፡ ደጃች ፡ ኀይሉን ፡ ከገደሏቸው ፡ በኋላ ፡ ተመልሰው ፡ በረሓ ፡ ገቡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ራስ ፡ ባሪያውን ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ አሲዘው ፡ ላኳቸው።

ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ይኸንኑ ፡ ስለ ፡ ሰሙ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ምጥዋንና ፡ የአሥመራን ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ይገዙ ፡ ከነበሩት ፡ ግብጾች ፡ 300 ፡ የሰናድር ፡ ጠመንዣ ፡ ተቀብለው ፡ በራስ ፡ ባሪያው ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ ይገሠግሡ ፡ ዠመር ። ራስ ፡ ባሪያው ፡ ግን ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤልን ፡ በጣም ፡ ይንቁ ፡ ነበርና ፡ ይኸውና ፡ ደረሰ ፡ ቢሏቸው ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አጠገቤ ፡ ሳይደርስ ፡ ለሱ ፡ ጦር ፡ ተሰልፌ ፡ አልቈይም ፡ ብለው ፡ አሥመራ ፡ በድንኳናቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር።

በኋላም ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ በግሥጋሤ ፡ ድንገት ፡ ደርሰው ፡ ወታደሮቹ ፡ ሲገጥሙ ፡ ራስ ፡ ባሪያውን ፡ ከድንኳናቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ ገብተው ፡ ገደሏቸው ፡ ይላሉ ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ በሰልፍ ፡ ተጋጥመው ፡ በኀይል ፡ ሲዋጉ ፡ ነው ፡ ራስ ፡ ባሪያው ፡ የሞቱት ፡ ይላሉ ፡ ይኸውም ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ቀድሞ ፡ ባላቸው ፡ ላይ ፡ የራስ ፡ ባሪያውን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡ ኀይላቸው ፡ እየበረታ ፡ ሄደ።

ርሳቸውም ፡ በግብጾችና ፡ በቱርኮች ፡ ሥር ፡ ሆነው ፡ ሐማሴንና ፡ ቦጐስን ፡ ሐባብን ፡ ይገዙ ፡ ነበር ። ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤልን ፡ ለመያዝ ፡ ቢፈትኑ ፡ ወደ ፡ ሐባብ ፡ በረሓ ፡ እየገቡ ፡ አልገዛም ፡ ብለው ፡ አስቸግረው ፡ ነበርና ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከባላገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ «እንቢ ፡ አለ ፡ ወልዱ» እያለ ፡ ይዘፍንላቸው ፡ የነበረው ፡ ዛሬም ፡ በዲስክ ፡ ገብቶ ፡ ይዘፈንበታል ።

በኋላ ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤልን ፡ አባብለኸም ፡ ቢሆን ፡ ወግተኸም ፡ ቢሆን ፡ አስገብርልኝ ፡ ብለው ፡ ራስ ፡ አሉላን ፡ አዘዟቸው ፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ ራስ ፡ አሉላ ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ሄደው ፡ ዛሬ ፡ ጠላት ፡ በያለበት ፡ (ደርቡሽና ፡ ግብጽ) ፡ ተነሥቶ ፡ አንድ ፡ ሆነን ፡ በመመከት ፡ ፈንታ ፡ እንዴት ፡ ርስ ፡ በርሳችን ፡ እንዋጋለን ፡ ርስዎንስ ፡ ያኸል

፡ የባላባት ፡ ልጅ ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ተለይቶ ፡ ብቻውን ፡ በበረሓ ፡ እንዴት ፡ ይኖራል ፡ አሁንም ፡ ንጉሡ ፡ ከልብ ፡ ታርቀው ፡ ዋና ፡ ሊያደርጉዎ ፡ ይፈልጋሉ ፡ ብለው ፡ ማሉላቸው ፡ ይባላል ። ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤልም ፡ እውነት ፡ መስሏቸው ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ከራስ ፡ አሉላ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ለመምጣት ፡ ጉዞ ፡ ዠምረው ፡ ዐድዋ ፡ አጠገብ ፡ እሚመች ፡ ስፍራ ፡ ሲደርሱ ፡ የሐሰተኛ ፡ ከሳሽ ፡ አስነሥተው ፡ አስረትተው ፡ ራስ ፡ አሉላ ፡ በራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ሰንሰለት ፡ አገቡባቸው ። ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ የራስ ፡ አሉላን ፡ ክዳት ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ እንኳን ፡ በጦርነት ፡ ድል ፡ አድርገኸ ፡ አሊያዘኸኝ ፡ እንጂ ፡ በማታለል ፡ ተይዤ ፡ ብታሰር ፡ ግድ ፡ የለኝም ፡ ብለው ፡ ታሰሩ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ራስ ፡ አሉላ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤልን ፡ በክዳት ፡ የበደሏቸው ፡ ይመስላል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ደግሞ ፡ የወገናቸውን ፡ ንጉሥ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስን ፡ ከድተው ፡ ወደ ፡ ግብጾች ፡ ተጠግተው ፡ ለውጭ ፡ መንግሥት ፡ መሣሪያ ፡ በመሆናቸው ፡ አገራቸውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ መክዳት ፡ ነውና ፡ በደሉ ፡ የርሳቸው ፡ ያመዝናል ።

## <u>ስለ ፡ ደጃች ፡ ደበበ ፡ አርኣያ ።</u>

ደጃች ፡ ደበበ ፡ (ደብብ) ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ አጎት ፡ የትልቁ ፡ ራስ ፡ አርኣያ ፡ ልጅ ፡ የደጃች ፡ ተድላ ፡ አባ ፡ ጉመድ ፡ (ጉበን) ፡ ወንድም ፡ ናቸው ። ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ በደፉ ፡ ጊዜ ፡ በጠብ ፡ 1 ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ገደሉ ፡ ከርሳቸው ፡ ከድተው ፡ በሐማሴን ፡ በረሓና ፡ በአከለ ፡ ጉዛይ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ አሽከሮች ፡ ከወዲህ ፡ ይፈላለጓቸው ፡ ነበርና ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ምጥዋ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ወደዚያ ፡ ተጠግተው ፡ ብዙ ፡ መሣሪያ ፡ አግኝተው ፡ የባንዳ ፡ አለቃ ፡ ሁነው ፡ ነበር።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይኸውም ፡ ቢሆን ፡ ለስሙ ፡ ወይም ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በፍጹም ፡ የኢጣሊያኖችም ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ ተገዥ ፡ ሳይሆኑ ፡ ከወዲህም ፡ በዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከወዲያም ፡ በኢጣሊያኖች ፡ የሚገዙትን ፡ ነገዶች ፡ እያለገበሩ ፡ በአከለ ፡ ጉዛይና ፡ በአጋመዳ ፡ በረሓ ፡ ይቀመጡ ነበር።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ግብጾች ፡ ሲለቁ ፡ በእነርሱ ፡ እግር ፡ ተተክቶ ፡ ምጥዋን ፡ የያዘው ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ አገሩን ፡ የለመደ ፡ ባለመሆኑ ፡ መሪና ፡ መሣሪያ ፡ የሚሆነው ፡ ቀንደኛና ፡ ትንሽ ፡ ባላባትነት ፡ ያለውን ፡ በጣም ፡ ይፈልግ ፡ ነበርና ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ተነጋገሩና ፡ እንደ ፡ ተላመዱ ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፍቶ ፡ የአሥመራን ፡ ደጋ ፡ ደጋውን ፡ አገር ፡ ሲይዝ ፡ ደጃች ፡ ደበበ ፡ ከነሰዋቸው ፡ ሄደው ፡ በኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ጥሪ ፡ ተደረገላቸው ። እርሳቸውም ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የከዱት ፡ ያላዛዥ ፡ የሚቀመጡ ፡ መስሏቸው ፡ ነበርና ፡ አልመጣም ፡ ብለው ፡ መልሰው ፡ ላኩ ፡ ስለዚህ ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡

አዛዥ ፡ ጄኔራል ፡ ባልዲሴራ ፡ ባ4 ፡ የጦር ፡ ሹማምቶች ፡ የሚታዘዙ ፡ 400 ፡ ባንዶች ፡ አዘጋጅቶ ፡ ከነዚህም ፡ በስተቀር ፡ አዳም ፡ አጋ ፡ በሚባል ፡ ያገር ፡ ተወላጅ ፡ የሚታዘዙ ፡ (እወታደር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ በደንብ ፡ ያልተጻፉ) ፡ 200 ፡ ወታደሮች. ፡ ጨምሮ ፡ ለሁሉም ፡ የበላይ ፡ አዛዥ ፡ ካፒቴን ፡ ኮርናኪያ ፡ የሚባለውን ፡ አድርጎ ፡ ደጃች ፡ ደበበን ፡ እንዲወጉ ፡ ላካቸው። እነርሱም ፡ በደጃች ፡ ደበበ ፡ ላይ ፡ ድንገት ፡ ደርሰው'' አደጋ ፡ ለመጣል ፡ ባ1880 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በነሐሴ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሰገነይቲ ፡ ሲገሠግሡ ፡ ይኸንኑ ፡ ያየ ፡ ባላገር ፡ በቶሎ ሄዶ ፡ ለደጃች ፡ ደበበ ፡ ገለጸላቸው ።

እርሳቸውም ፡ በየመንገዱ ፡ ዳርና ፡ ዳር ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ አስደፍጠው ፡ ሲጠባበቁ ፡ ወዲያው ፡ ካፒቴን ፡ ኮርናኩያ ፡ ከነጭፍራው ፡ ደርሶ ፡ እምን ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ሳያውቅ ፡ ወደ ፡ መካከል ፡ ገባ ፡ ሲል ፡ ውጊያ ፡ ዠመሩት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ጣሊያኖቹና ፡ ባንዶቹም ፡ መልሰው ፡ ይዋጉ ፡ ዠመር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ደጃች ፡ ደበበ ፡ ከነሰዋቸው ፡ ከበው ፡ ከያለበት ፡ ስለ ፡ ወጓቸው ፡ አዝማቹ ፡ ኮርናኪያና ፡ 4ቱ ፡ የኢጣሊያ ፡ ሹማምቶች ፡ ከ250 ፡ ባንዶች ፡ ጋራ ፡ እዚያው ፡ እጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞቱ ፡ የተረፉት ፡ ሸሽተው ፡ ምጥዋ ፡ ገቡ ።

በኋላ ፡ ግን ፡ ባላምባራስ ፡ ክፍሌ ፡ የሚባለው ፡ ከኢጣሊያናች ፡ ከድቶ ፡ በሸፈተ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ደበበ ፡ ባ1882 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ታርቀው ፡ ገቡ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ከራስ ፡ አሉላ ፡ ጋራ ፡ ለጦርነት ፡ በተሰለፉ ፡ ጊዜ ፡ ይከዳናል ፡ በማለት ፡ ተጠራጥረው ፡ አሰሯቸው።

# ምዕራፍ ፡ 27 ።

## ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ እንዳሰቡና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሚሲዮናውያንን ፡ እንዳስወጡ ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በዘመናቸው ፡ የነበሩ ፡ የጐንደር ፥ የበጌምድር ፥ የጐጃም ፥ የሸዋ ፡ መሳፍንት ፡ ከተገዙላቸው ፡ ወዲህ ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፈትነው ፡ ያልሆነላቸውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ አደርጋለሁ ፡ ብለው ፡ ተነሡ። ወዲያው ፡ ከእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ ተላልከው ፡ 1 ፡ ጳጳስ ፡ መጥቶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመስበክ ፡ አይበቃም ፡ ብለው ፡ አራት ፡ ጳጳሳት ፡ አስመጥተው ፡ አንዱን ፡ ጳጳስ ፡ ለሸዋ ፡ አንደኛውን ፡ ለጐጃም ፡ ሰጥተው ፡ የቀሩትን ፡ ሁለቱን ፡ በትግሬ ፡ ወረዳ ፡ አስቀምጠው ፡ ወንጌል ፡ ያሰብኩ ፡ ዠመር።

ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ 2 ፡ ልደት ፡ ሃይማኖትን ፡ በጣም ፡ ይወዱ ፡ ነበርና ፡ ከሸዋ ፡ ተመልሰው ፡ ቦሩ ፡ ሜዳ ፡ ሲደርሱ ፡ 3 ፡ ልደት ፡ ከሚሉት ፡ ከሸዋ ፡ ሊቃውንት ፡ ጋራ ፡ አከራክረው ፡ ወዲያው ፡ 3 ፡ ልደት ፡ የሚሉትን ፡ ተቈጥተው ፡ የጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ምላስ ፡ እስከ ፡ መቍረጥ ፡ ደርሰዋል ፡ ይባላል ።

ከዚያም ፡ ዐድዋ ፡ ተመልሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትዕግሥትና ፡ ርኅራኄ ፡ ባልተመለከቱ ፡ መምህራን ፡ እየተመሩ ፡ ሱረት ፡ ባፍንጫው ፡ የሚጠጣውን ፡ ትምባኾ ፡ ባፉ ፡ የሚጐርሠውን ፡ በጭካኔ ፡ ይቀጡት ፡ ዠመር። ይህንንም ፡ በሚያደርጉበት ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለገሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ግፍ ፡ የሠሩ ፡ መስሎ ፡ አልታያቸውም ፡ ነበር ። ቀጥሎም ፡ የፕሮቴስታንትንና ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ ይሰብኩ ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝቤ ፡ በሃይማኖት ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ሲለያይ ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ የተለያየ ፡ ይሆናል ፡ ሲሉ ፡ ሚሲዮናውያኑን ፡ ሁሉ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ እንዲወጡ ፡ ከሸዋም ፡ አባ ፡ ማስያስን ፡ አስመጥተው ፡ አንድነት ፡ ሰበሰቧቸው ። ወዲያውም ፡ የቆሙትን ፡ ሚሲዮናውያን ፡ «ምን ፡ ልታደርጉ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጣችሁ» ፡ ብለው ፡ ጠየቋቸው ፡ እነሱም ፡ «ወንጌል ፡ ልንሰብክ ፡ ነው» ፡ ብለው ፡ መለሱ።

ንጉሡም ፡ «ወንጌል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እግዚአብሔርም ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እኔም ፡ ሕዝቤን ፡ ለመስበክ ፡ የሚበቁ ፡ ጳጳሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ አሉኝ ፡ ለማን ፡ ለመስበክ ፡ ትፈልጋላችሁ» ፡ አሏቸው ። እነርሱም ፡ «በዚህ ፡ አገር ፡ ላሉት ፡ ይሁዲዎች ፡ እስላሞች » ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው። ንጉሡም ፡ «ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስትመጡ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የአይሁድን ፡ አገር ፡ ግብጽንና ፡ ሊብያን ፡ የእስላሙን ፡ አገር ፡ እንደምን ፡ ዘላችሁ ፡ ወዲህ ፡ መጣችሁ ። አሁንም ፡ እኔ ፡ የሀገሬን ፡ ሕዝብ ፡ የእጅ ፡ ሥራና ፡ ጥበብ ፡ የሚያስተምሩ ፡ ስጋጃ ፡ ሠሪዎች ፡ አናጢዎችና ፡ ነጋዴዎች ፡ ብረት ፡ ሠሪዎች ፡ የሆኑትን ፡ እቀበላለሁ | ፡ እንጂ ፡ እናንተን ፡ አልፈልግምና ፡ አገሬን ፡ ልቀቁልኝ» ፡ ብለው ፡ ገሚሶቹን ፡ በመተማ ፡ ገሚሶቹን ፡ በምጥዋ ፡ ሰደዷቸው ።

እንደዚሁም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የነበሩትን ፡ ፈላሾችንና ፡ አረማውያንን ፡ ይልቁንም ፡ እስላሞችን ፡ በግድ ፡ እያቈረቡ ፡ ክርስቲያን ፡ አደረጓቸው ። ክርስቲያን ፡ አንሆንም ፡ ያሉትን ፡ እስላሞች ፡ በጭካኔ ፡ እየቀጡ ፡ ስላጕላሏቸው ፡ እየተሰደዱ ፡ ወደ ፡ ሱዳንና ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ እየገቡ ፡ በዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚነሣ ፡ ባላጋራ ፡ ይፈልጉ ፡ ዠመር።

# ምዕራፍ ፡ 28 ።

## የግብፆች ፡ ውድቀት ፡ -- የደርቡሽ ፡ ወረራ ፡-- የሔዊት ፡ ውል ፡-- የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ የድርቡሾች ፡ ጦርነት ፡

ከሺ 300 ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ጀምሮ ፡ በኦትማን ፡ (በኡስማን) ፡ መሥራችነት ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ተስፋፍቶ ፡ ከኤውሮፓም ፡ ከእስያም ፡ ከአፍሪካም ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ ይገዛ ፡ ነበር ፡ እንደዚሁ ፡ ምጥዋንና ፡ በአካባቢው ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ሱዳንን ፡ ሐረርን ፡ ይገዛ ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሐረርንና ፡ ምጥዋን ፡ ሱዳንን ፡ የበላይነቱ ፡ ሳይቀር ፡ ለግብፅ ፡ መንግሥት ፡ አስተላልፎለት ፡ ግብፁ ፡ እነዚህን ፡ አገሮች ፡ በቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ጥገኝነት ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ሲገዛ ፡ በመጨረሻ ፡ በሺ870 ፡ ዓ ፡ ምሕረት ፡ ከደርቡሾች ፡ መካከል ፡ መሐመድ ፡ አሕመድ ፡ የተባለው ፡ ከሱዳን ፡ ውስጥ ፡ የግብፁንና ፡ የቱርክን ፡ ገዥነት ፡ ለማስወገድ ፡ ተነሣ ፡ አስቀድሞም ፡ ማህዲ ፡ የሚባል ፡ ተነሥቶ ፡ የውጭን ፡ ገዥ ፡ ተዋግቶ ፡ የሚያጠፋና ፡ ሱዳንን ፡ ከፍ ፡ የሚያደርግ ፡ ይመጣል ፡ እየተባለ ፡ ትንቢት ፡ በእስላሞች ፡ ዘንድ ፡ ይነገርለት ፡ ነበርና ፡ ማህዲ ፡ የተባለውና ፡ የተጠበቀው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተከተለው። አኳኋኑንም ፡ የተመለከቱ ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ በእውነት ፡ የአላህ ፡ መላክተኛ ፡ ነቢይ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ያደንቁት ፡ ጀመር ፡ የሱም ፡ ትውልዱ ፡ በኑብያ ፡ ውስጥ ፡ ደንጎላ ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ አባቱም ፡ ጀልባ ሠሪ ፡ ነው ፡ ይባላል።

የሱም ፡ ዝና ፡ በያለበት ፡ ይወራ ፡ ጀመር ፡ ካርቱም ፡ ያሉትም ፡ የግብፅም ፡ ሹማምንቶች ፡ ወሬውን ፡ ሰምተው ፡ በሰላምም ፡ ለማሳመን ፡ ቢፈልጉ ፡ አልተቻላቸውም ፡ የእርሱ ፡ ተከታይ ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እየበረከተ ፡ ስለሄደ ፡ በጦርነቱም ፡ የማይበገር ፡ ሆነ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በካርቱም ፡ በገዳሪፍ ፡ በአምዱርማን ፡ ያሉ ፡ ግብፆችና ፡ ቱርኮች ፡ ተቸገሩ ፡ ከኢትዮጵያም ፡ ርዳታ ፡ እንዳያገኙ ፡ በሁለት ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ የተፋሰሱት ፡ ደም ፡ ነበርና ፡ በተጥታ ፡ ምንም ፡ ለማድረግ ፡ አልተቻለም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከቱርኮች ፡ በኋላ ፡ የሱዳን ፡ ባለቤት ፡ ለመሆን ፡ ፍላጎት ፡ የነበረው ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ለጥቅሙ ፡ ሲል ፡ ግብፆችን ፡ ለመርዳት ፡ ተነሣ ፡ ጥቅሙን ፡ ለማግኘትና ፡ እነሱንም ፡ ለመርዳት ፡ የግብፅንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ የቀድሞ ፡ ጠባቸውን ፡ አስወግዶ ፡ በውል ፡ ማስታረቅ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ **"የሔዊት ፡ ውል"** ፡ የተባለውን ፡ ውል ፡ እንዲያዋውል ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ሰር ፡ ዊሊያም ፡ ሔዊት ፡ የሚባለውን ፡ ወደ ፡ ዓፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ላከው ። ዓፄ ፡ ዮሐንስም ፡ መላክተኛውን ፡ በክብር ፡ ተቀብለው ፡ ከተገናኙት ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ያለውን ፡ ውል ፡ ተዋዋሉ።

«ግርማዊት ፡ የተዋሐደው ፡ መንግሥት ፡ የታላቋ ፡ ብርታንያና ፡ የአየርላንድ ፡ ንግሥት ፡ የሕንድ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ግርማዊ ፡ ዓፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ንጉሠ ፡ ጽዮን ፡ የኢትዮጵያና ፡ የተገዦችዎ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥትና ፡ ልዑል ፡ መሐመድ ፡ ቴውፊክ ፡ የግብፅ ፡ ከዲቭ ፡ (ኸደዊ) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዓፄ ፡ ዮሐንስና ፡ በግብፅ ፡ ከዲቭ ፡ (ኸደዊ) ፡ መሐመድ ፡ ቴውፊክ ፡ መካከል ፡ በሚገኘው ፡ ክርክር ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግና ፡ በመካከላቸው ፡ ንዋሪ ፡ ሰላም ፡ ለመመሥረት ፡ ስለፈቀዱ ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ እነርሱን ፡ ወራሾቻቸውንና ፡ ተከታዮቻቸውን ፡ የሚያስተሳስር ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ተስማምተዋል ። ግርማዊት ፡ የተዋሐደው ፡ መንግሥት ፡ የታላቋ ፡ ብርታንያና ፡ የአየርላንድ ፡ ንግሥት ፡ የሕንድ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታትም ፡ በሕንድ ፡ አገር ፡ ምሥራቅ ፡ የሚገኙትን ፡ የግርማዊነትዎን ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፡ አድሚራል ፡ ሰር ፡ ዊልያም ፡ ሔዊትን ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚ ፡ በማድረግ ፡ ግርማዊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዓፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ራሳቸው ፡ የጉዳያቸው ፡ ፈጻሚ ፡ ሆነው ፡ ልዑል ፡ የግብፅ ፡ ከዲቭ ፡ የምጥዋን ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ክቡር ፡ መሰን ፡ ቤይን ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚ ፡ በማድረግ ፡ ተስማምተው ፡ በሚከተሉት ፡ አንቀጾች ፡ ውል ፡ ገብተዋል ።

1ኛ. ፡ አንቀጽ ። ይህ ፡ ውል ፡ ከተፈረመበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በእንግሊዝ ፡ ተጠባባቂነት ፡ የሚገኘው ፡ ማናቸውም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚገባና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የሚወጣ ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ ጥይት ፡ ጭምር ፡ በነፃ ፡ በምጥዋ ፡ ማለፍ ፡ አለበት ።

2ኛ. ፡ አንቀጽ ። በሰፕተምበር ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1884 ፡ ማለት ፡ በመስከረም ፡ 8 ፡ ቀን ፡ 1887 ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ቦጐስ ፡ የተባለው ፡ አገር ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መመለስ ፡ አለበት። በከሰላ ፡ በአምድብና ፡ በሰንሂት ፡ የሚገኙት ፡ የልዑል ፡ ከዲቭ ፡ ወታደሮች ፡ ሠፈሩን ፡ በለቀቁ ፡ ጊዜ ፡ አሁን ፡ የልዑል ፡ ከዲቭ ፡ ገንዘብ ፡ የሆኑት ፡ በቦጉስ ፡ አገር ፡ የሚገኙት ፡ ሕንፃዎች ፡ ዕቃ ፡ ቤቶችና ፡ በነዚህ ፡ ሕንፃዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚቀሩት ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተረክበው ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ገንዘብ ፡ ይሆናሉ ።

3ኛ. ፡ አንቀጽ ። በከሰላ ፡ በአምድብና ፡ በሰንሂት ፡ የሚገኙት ፡ የልዑል ፡ ከዲቭ ፡ ወታደሮች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ ለማለፍ ፡ ሊረድዋቸው ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ውል ፡ ገብተዋል ።

4ኛ. ፡ አንቀጽ ። ለኢትዮጵያ ፡ አቡን ፡ ለመሾም ፡ ምናልባት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሚጠይቁትን ፡ ርዳታ ፡ ሁሉ ለመስጠት ልዑል ፡ ከዲቭ ፡ ውል ፡ ገብተዋል ።

5ኛ. ፡ አንቀጽ ። ከቅጣት ፡ ለመዳን ፡ ካንዱ ፡ ግዛት ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ግዛት ፡ የሸሹትን ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ ወንጀለኞች ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥትና ፡ ልዑል ፡ ከዲቭ ፡ ውል ፡ ገብተዋል ።

6ኛ. ፡ አንቀጽ ። ይህ ፡ ውል ፡ ከተፈረመ ፡ በኋላ ፡ ምናልባት ፡ ከልዑል ፡ ከዲቭ ፡ ክርክር ፡ ቢነሣ ፡ ነገሩን ፡ ለብርታንያ ፡ ግርማዊት ፡ ለማመልከት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተስማምተውበታል ።

7ኛ. ፡ አንቀጽ። ይህ ፡ ውልም ፡ በግርማዊት ፡ የታላቋ ፡ ብርታንያና ፡ የአየርላንድ ፡ ንግሥት ፡ የሕንድ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታትና ፡ በልዑል ፡ የግብፅ ፡ ከዲቭ ፡ መፈረም ፡ አለበት ፡ ፊርማውም ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ ወደ ፡ ዓድዋ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

የዚህ ፡ ምስክሮችም ፡ ስለግርማዊት ፡ የታላቋ ፡ ብሪታንያና ፡ የአየርላንድ ፡ ንግሥት ፡ የሕንድ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ሪር ፡ አድሚራል ፡ ሰር ፡ ወ ፡ ሔዊት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ራሳቸውና ፡ ስለ ፡ ልዑል ፡ የግብፅ ፡ ከዲቭ ፡ ከቡር ፡ መሰን ፡ ቤይ ፡ ሁነው ፡ ውሉን ፡ ፈርመው ፡ ማኅተማቸውን ፡ አትመውበታል። ተጻፈ ፡ ዓድዋ ፡ ላይ ፡ ዡን ፡ 3 ፡ ቀን ፡ 1884 ፡ ማለት ፡ ግንቦት 27 ፡ ቀን ፡ 1876።

(ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም)

**ወ ፡ ሔዊት ፡ መሰን ፡**

የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ይህን ፡ ካዋዋለ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ የተከበቡትን ፡ ግብፆች ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ የሚያወጧቸውና ፡ አገሩንም ፡ የሚያስተዳድሩ ፡ ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ በቫርል ፡ ጕርይን ፡ ጆርጅ ፡ አዝማችነት ፡ ልኮ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ከእነዚሁ ፡ ከተላኩት ፡ ከእንግሊዞች ፡ ወታደሮች ፡ ውስጥ ፡ ብዙዎቹን ፡ ደርቡሾች ፡ ከበው ፡ ፈጁዋቸው ።

ጎርዶን ፡ ፓሻም ፡ የተረፉትን ፡ ወታደሮች ፡ ይዞ ፡ የካርቱምን ፡ ከተማ ፡ አስመሽጎ ፡ በዠግንነት ፡ እየተከላከለ ፡ ርዳታ ፡ እንዲደርስለት ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገርና ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ልኮ ፡ ነበር። ነገር ፡ ግን ፡ ረዳቶቹ ፡ በጣም ስለ ፡ ዘገዩ ፡ ካርቱም ፡ ሳይደርሱ ፡ በመካከሉ ፡ የማህዲ ፡ ሰዎች ፡ (ደርቡሾች) ፡ ካርቱምን ፡ ከበው ፡ አስጨነቁት ። ጎርዶን ፡ ፓሻም ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከተከላከለ ፡ በኋላ ፡ ተሸንፎ ፡ በ1877 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ተማረከ ። ደርቡሾችም ፡ ራሱን ፡ ቈርጠው ፡ እንደ ፡ ነቢይና ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ለሚያዩት ፡ ለማህዲ ፡ ወስደው ፡ አሳዩት።

ለጎርዶንም ፡ ዛሬ ፡ በእንግሊዝና ፡ በግብጽ ፡ መንግሥት ፡ ፈቃድ ፡ በካርቱም ፡ ከተማ ፡ ግመል ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ ሐውልት ፡ ተሠርቶለት ፡ ይታያል።

ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በሰሜን ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጠረፋቸውን ፡ ገፍቶ ፡ እንዳይገባ ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበረ ። ከግብጽ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ።በውል ፡ ከታረቁ ፡ በኋላ ፡ ሹም ፡ ዳኅና ፡ ፈንታ ፡ የሚባሉትን ፡ ደርቡሾችን ፡ ተዋግተው ፡ መተማ ፡ ላይ ፡ የተቸገሩትን ፡ ግብጾችንና ፡ ቱርኮችን ፡ ይዘው ፡ ወዳገራቸው ፡ እንዲሸኙ ፡ ሰደዷቸው ። ሹም ፡ ዳኅና ፡ ፈንታም ፡ ሄደው ፡ በ1880 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከደርቡሾች ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ ግብጾችንና ፡ ቱርኮችን ፡ ከነቤተ ፡ ሰባቸው ፡ ከመተማ ፡ ይዘው ፡ ተመልሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ አልፈው ፡ በያገራቸው ፡ እንዲገቡ ፡ አይረጉ።

ይኸውም ፡ ቀድሞ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ክርስቲያን ፡ ካልሆናችሁ ፡ ብለው ፡ አባረዋቸው ፡ በሱዳን ፡ ከሚቀመጡት ፡ እስላሞች ፡ ጠብ ፡ በቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ለግብጽ ፡ ረዳት ፡ መሆን ፡ ለብዙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቃጠሎ ፡ ለብዙም ፡ ነፍስና ፡ ይልቁንም ፡ ለከበረው ፡ ለዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ሕይወት ፡ መጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ሆነ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደርቡሾች ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በተሰደዱት ፡ እስላሞች ፡ እየተመሩ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጠረፍ ፡ እያለፉ ፡ እስከ ፡ ጐንደር ፡ ገብተው ፡ ባ1880 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ 10 ፡ ቀን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ አቃጥለው ፡ ቀሳውስቱንና ፡ መነኩሳቱን ፡ ሁሉ ፡ አረዷቸው ። ገሚሱንም ፡ በምርኮ ፡ ስም ፡ እየያዙት ፡ ሲሄዱ ፡ ከምርኮኛው ፡ አንዱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ገጠመ።

> ተከተልኸኝ ፡ ብዬ ፡ ዞሬ ፡ ዞሬ ፡ ሳይ ፡
> ወይ ፡ ጥጋብ ፡ ወይ ፡ ኩራት ፡ ጐንደር ፡ ቀረኽ ፡ ወይ ፡
> ወገራ ፡ አሳላፊ ፡ ደንቢያ ፡ እንጀራ ፡ ጣይ ፡
> ተበላኽ ፡ ጐንደሬ ፡ አትነሣም ፡ ወይ።

ይኸንኑ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ አሥመራ ፡ ሆነው ፡ ቢሰሙ ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሄደኽ ፡ ከደርቡሾች ፡ ጋራ ፡ ተዋግተኽ ፡ የተቃጠለውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የፈሰሰውን ፡ የቀሳውስትን ፡ የመነኩሳትን ፡ ደም ፡ ተበቀል ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ። ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ እንደ ፡ ታዘዙ ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ የሚሆነውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ መተማ ፡ ሄደው ፡ ከደርቡሾች ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ መተማን ፡ አቃጥለው ፡ ምርኮኛቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ተመለቡ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ማህዲ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የሱዳን ፡ ገዥ ፡ የሆነው ፡ ከሊፋ ፡ ዐብዱላሂ ፡ አቡ ፡ አንጋ ፡ የሚባለውን ፡ ዋና ፡ አዝማች ፡ አድርጎ ፡ ከቀድሞ ፡ የበለጠ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከመተማ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግዛት ላከ ፡ ቍጥራቸውም ፡ ከሰማንያ ፡ ሺሕ ፡ ይበልጣል ።ንጉሥ

፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ሣር ፡ ውሃ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ሲጠባበቁ ፡ ወዲያው ፡ ጦርነት ፡ ተዠመረ። ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ የመዠመሪያውን ፡ ደጀን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲገፉ ፡ ሌላው ፡ ተጠባባቂ ፡ የደርቡሽ ፡ ወታደር ፡ ከቦ ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ብዙ ፡ ሜሪያና ፡ ዕቃ ፡ ብዙም ፡ መኳንንትና ፡ ወታደሮች ፡ ይልቁንም ፡ በጦርነትም ፡ ቢሆን ፡ ካባቱ ፡ አልለይም ፡ ብለው ፡ የተከተሏቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ምንትዋብ ፡ የሚባሉት ፡ ሴት ፡ ልጃቸው ፡ አንድነት ፡ ተማረኩ።

እሳቸው ፡ ግን ፡ ከጥቂት ፡ ወታደሮችና ፡ ከልጃቸው ፡ ከራስ ፡ በዛብኽ ፡ ጋራ ፡ በፈረስ ፡ ሸሽተው ፡ አመለጡ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ልጃቸው ፡ መማረክና ፡ ስለ ፡ ራሳቸውም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተገጠመ።

ሣር ፡ ውሃ ፡ ከሜዳው ፡ የተዘራ ፡ አዝመራ ፡
ዐጫጁ ፡ ደርቡሽ ፡ ነው ፡ ሰብሳቢው ፡ አሞራ ፡
አትከልክልሞይ ፡ ይዘኽ ፡ አለንጋኽን ፡
አሞራ ፡ ሲበላው ፡ የገዛ ፡ ገላኽን።


ቀጥሎ ፡ ተማራኪዋ ፡ ወይዘሮ ፡ ምንትዋብ ፡ የሚከተለውን ፡ የኀዘን ፡ ግጥም ፡ ገጠሙ።
የምትሄዱ ፡ ሰዎች ፡ የምትሻገሩ ፡
ድመት ፡ በልታ ፡ ሞተች ፡ ብላችሁ ፡ ንገሩ።

# ምዕራፍ ፡ 29 ።

## የመተማ ፡ ጦርነትና ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዕረፍት ።

ንጉሥ ፡ ተክል ፡ ሃይማኖት ፡ ከደረሰባቸው ፡ አደጋ ፡ የተነሣ ፡ ተበሳጭተው ፡ ከንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ ተነጋግረው ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ ለዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ አንገዛም ፡ ብለው ፡ ስምምነታቸውን ፡ በመሐላ ፡ ፈጸሙ ። ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ወደጐጃም ፡ የሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እጐንዎ ፡ ልቀመጥ ፡ አይገባኝም ፡ ብለው ፡ እግራቸው ፡ ሥር ፡ ተቀምጠው ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክን ፡ በበላይ ፡ ዐይን ፡ ይመለከቷቸው ፡ ዠመር ። ሕዝቡም ፡ እንግዴህ ፡ የንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ደረሰ ፡ እያለ ፡ በዘፈንና ፡ በወግም ፡ ያነሣሣ ፡ ዠመር ፡ ይባላል ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ አሥመራ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ድል ፡ መሆንና ፡ የደርቡሾቹን ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ በሰሙበት ፡ ሰዓት ፡ እንደዚሁ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክና ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በርሳቸው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተስማሙባቸው ፡ ሰሙ። የዚህንም ፡ እውነተኛነት ፡ በኋላ ፡ በደብዳቤ ፡ ተላልከው ፡ እውነቱን ፡ ከንጉሥ ፡ ምኒልክየና ፡ ከንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አግኝተውታል ። ስለዚህ ፡ ካሥመራ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ መተማ ፡ በመሄድ ፡ ፈንታ ፡ በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ሰዓት ፡ የከዳኝን ፡ የጐጃምንና ፡ የሸዋን ፡ ሕዝብ ፡ እወጋለሁ ፡ ብለው ፡ መንገድ ፡ ዠምረው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ መኳንንቱና ፡ ቀሳውስቱ ፡ እኋላችን ፡ አረመኔውን ፡ ደርቡሽን ፡ ትተን ፡ ሸዋን ፡ የክርስቲያኑን ፡ አገር ፡ ወግተን ፡ ብናጠፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ አይለውም ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ መከሯቸው ፡ ጐጃምን ፡ ጥቂት ፡ እንዳጠፉት ፡ ከንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዕርቅ ፡ አርገው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ፊታቸውን ፡ አዞረው ፡ ወደ ፡ ደንቢያ ፡ ተጓዙ።



ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት (ዋግሹም ጎበዜ ገብረ መድኅን)

ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ አስከትለው ፡ የፈሰሰውን ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ ወደ ፡ መተማ ፡ ሲጓዙ ፡ በፊት ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ደርቡሾች ፡ ወደ ፡ ተዋጉበት ፡ ስፍራ ፡ ሄደው ፡ በጦርነቱ ፡ ውስጥ ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎች ፡ ዐፅም ፡ አይተው ፡ ከብዛቱ ፡ የተነሣ ፡ አዘኑ ። ወዲያውም ፡ ጒዟቸውን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየቀጠሉ ፡ ወደ ፡ መተማ ፡ ደረሱ ። ከዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ ጋራ ፡ የዘመቱ ፡ መኳንንት ፡ አጎታቸው ፡ ትልቁ ፡ ራስ ፡ ኣርኣያ ፡ የወሎው ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ራስ ፡ ኀይለ ፡ ማርያምና ፡ ራስ ፡ አሉላ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ራስ ፡ ሐጐስ ፡ ነበሩ ። ደጃዝማቹና ፡ ፊታውራሪው ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነው። የዘመተው ፡ ሠራዊት ፡ ቊጥር ፡ ተከታዩም ፡ እግረኛውም ፡ ፈረሰኛውም ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ 150 ፡ ሺሕ ፡ ይደርሳል ። የዚህም ፡ ወሬ ፡ በመተማ ፡ ሲሰማ ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤና ፡ ሽብር ፡ ሆነ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከአቡ ፡ አንጋ ፡ ቀጥሎ ፡ የተሾመው ፡ ዜኪ ፡ ቱማል ፡ የሚባለው ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ያለው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከፍርሃት ፡ የተነሣ ፡ የማይበቃኝ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ወታደር ፡ ያልሆኑትን ፡ ነጋዴና ፡ ገበሬዎች ፡ ሁሉ ፡ በግዴታ ፡ እየሰበሰበ ፡ ብረት ፡ እያሲያዘህ ፡ አሰለፋቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባ1881 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በመጋቢት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ ቅዳሜ ፡ ጦርነት ፡ ገጠሙ።

በዚህም ፡ ቀን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ደርቡሾች ፡ እስከ ፡ መሸጉበት ፡ ድረስ ፡ በፉከራ ፡ ገብተው ፡ ቀኑን ፡ ሁሉ ፡ ሲዋጉ ፡ ደርቡሾች ፡ ተስፋ ፡ ቈርጠው ፡ ሽሽት ፡ ሊዠምሩ ፡ ጥቂት ፡ ሲቀራቸው ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከበቅሏቸው ፡ ወርደው ፡ በወታደሮቻቸው ፡ መካከልና ፡ ፊት ፡ እየሄዱ ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ እያበረታቱ ፡ በዠግንነት ፡ ሲዋጉና ፡ ሲያዋጉ ፡ እድል ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ በጥይት ፡ ቈሰሉ ። ምናልባት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ መኳንንቱና ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስን ፡ እንዳንድ ፡ ሰው ፡ ቈጥረው ፡ እንደ ፡ መሩት ፡ ጠንክረው ፡ ተዋግተው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በፍጹም ፡ ድል ፡ ያደርጉ ፡ የነበረውን ፡ የንጉሡ ፡ መቊሰል ፡ በሰልፉ ፡ መካከል ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ ሆኖ ፡ ገሚሶቹ ፡ ሲታኩሱ ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ጌታችን ፡ ቈሰለብን ፡ እያሉ ፡ ከበብ ፡ ከበብ ፡ እያደረጉ ፡ የቀረውም ፡ መኳንንትና ፡ ወታደርም ፡ በኀይል ፡ ሰብሮ ፡ ገብቶበት ፡ ከነበረው ፡ ቅጥር ፡ ውስጥ ፡ የንጉሥን ፡ መቊሰል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እየተመለሰ ፡ ይወጣ ፡ ዠመር።

ንጉሡ ፡ ነገሥቱም ፡ ወዲያው ፡ የወንድማቸውን ፡ የደጃች ፡ ጉግሣን ፡ ልጅ ፡ ራስ ፡ መንገሻን ፡ አስጠርተው ፡ ወራሼ ፡ ልጄ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ነውና ፡ ለኔ ፡ ያደረጋችሁልኝን ፡ አገልግሎት ፡ ለርሱም ፡ እንዳትነፍጉት ፡ ብለው ፡ ለነራስ ፡ አሉላ ፡ አደራ ፡ ብለው ፡ በነገሡ ፡ ባ17 ፡ ዓመት ፡ ከ2 ፡ ወር ፡ በሺሕ ፡ 881 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መጋቢት ፡ 2 ፡ ቀን ፡ ዐረፉ።

ከሞት ፡ የተረፉት ፡ መኳንንቶች ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዕጨጌ ፡ ቴዎፍሎስም ፡ የጌታቸውን ፡ ሬሳ ፡ በሣጥን ፡ አግብተው ፡ በሰም ፡ መርገው ፡ ወደ ፡ አትባራ ፡ ወንዝ ፡ ፊታቸውን ፡ መልሰው ፡ ይሸሹ ፡ ዠመር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደርቡሾች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ይወጉናል ፡ እያሉ ፡ ሲሡጉ ፡ ዛሬ ፡ ዓለምንና ፡ መንግሥታትን ፡ የሚያገለግለው ፡ የስለላ ፡ ሥራ ፡

ያን ፡ ጊዜም ፡ እንደዚሁ ፡ ያገለግል ፡ ነበርና ፡ አንድ ፡ ሰላይ ፡ ልከው ፡ ቢያሰልሉ ፡ ሰላዩ ፡ ተመልሶ ፡ «ኢትዮጵያውያን ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ አትባራ ፡ አዙረው ፡ ይሸሻሉ ፡ እንጂ አንድም ፡ ወደኛ ፡ ፊቱን ፡ አዙሮ ፡ የሚዋጋ ፡ አላየሁም» ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ አበጋዙ ፡ ዜኪ ፡ ደንግጦ ፡ የነበረውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ አደፋፍሮ ፡ በግመልና ፡ በፈረስ ፡ እየሆነ ፡ ዱካቸውን ፡ እየተከታተለ ፡ በመጋቢት ፡ የ3 ፡ ቀን ፡ ሬሳውን ፡ ይዘው ፡ የሚጓዙትን ፡ በአትባራ ፡ ወንዝ ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ ሰፈሩ ፡ ደርሶባቸው ፡ ውጊያ ፡ ዠመሩ። የዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ አሽከሮችና ፡ መኳንንቶች ፡ ሬሳው ፡ ባለበት ፡ ድንኳን ፡ ዙሪያ ፡ ተሰልፈው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተፏከሩ ፡ ጠንክረው ፡ ተዋጉ ። የጌታችንንም ፡ ሬሳ ፡ ሕይወታችን ፡ ሳያልፍ ፡ አናስማርክም ፡ በማለት ፡ እድንኳኑ ፡ በር ፡ ላይ ፡ ትልቁ ፡ ራስ ፡ አርኣያ ፡ ቢትወደድ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ደጃች ፡ ተድላ ፡ ሌሎችም ፡ መኳንንቶችና ፡ ቀሳውስቶች ፡ እነሱም ፡ ሰይፈው ፡ ራሳቸውም ፡ እየተሰየፉ ፡ ይኸንን ፡ ወረታ ፡ ተመልክቶ ፡ ሊያመሰግን ፡ በማይችለው ፡ በዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ሬሳ ፡ ፊት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በማይባል ፡ ቈራጥነት ፡ እየተጨፋጨፉ ፡ ተነባብረው ፡ ወደቁ።

ነገር ፡ ግን ፡ ያለፈም ፡ ያሁንም ፡ የወደፊትም ፡ ታሪክ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉትን ላገራቸውና ፡ ለንጉሣቸው ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ የታመኑትን ፡ ቈራጥ ፡ ወታደሮች ፡ ለዘለዓለም ፡ እያለታወሰ ፡ ሲያመሰግናቸው ፡ ይኖራል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደርቡሾች ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሣጥን ፡ ከፍተው ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ሬሳ ፡ ይሆንን ፡ እያሉ ፡ ሲያመነቱ ፡ ከዚያ ፡ ከቆሙት ፡ ምርኮኞች ፡ አንዱ ፡ አዎን ፡ ብሎ ፡ ካረጋገጠላቸው ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ስመ ፡ ሞግሼያቸው ፡ እንደ ፡ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ራሳቸውን ፡ ቈርጠው ፡ ሬሳው ፡ አጠገብ ፡ ካገኙት ፡ የወርቅ ፡ ሰዓትና ፡ በወርቅ ፡ የተለበደ ፡ ወንጌል ፡ ከንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ ከመጣላቸው ፡ የሰላምታ ፡ ደብዳቤና ፡ መነጽር ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ወደ ፡ ዐብዱርማን ፡ ለከሊፋ ፡ ዐብዱላሂ ፡ ላኩለት ። ከሊፋም ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ አድርጎ ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስንም ፡ ራስ ፡ ሰክቶ ፡ በግመል ፡ ላይ ፡ ገበያ ፡ ለገበያ ፡ እያዞረ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ሲያሳየው ፡ ዋለ ፡ ይባላል ።

ለዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ የልቅሶ ፡ ግጥም ፡ ተገጠመላቸው ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ሞኝ ፡ ናቸው ፡
እኛም ፡ ሁላችን ፡ ናቅናቸው።

ንጉሥ ፡ ቢሏቸው ፡ በመኻሉ ፡
ወሰን ፡ ጠባቂ ፡ ልሁን ፡ አሉ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ይዋሻሉ ፡
መጠጥ ፡ አልጠጣም ፡ እያሉ ፡

ሲጠጡ ፡ አይተናል ፡ በርግጥ ፡
ራስ ፡ የሚያዞር ፡ መጠጥ።

በጐንደር ፡ መተኰስ ፡
በደንቢያ ፡ መታረድ ፡ አዝኖ ፡ ዮሐንስ ፡
ደሙን ፡ አፈሰሰ ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ።

እንዳያምረው ፡ ብሎ ፡ ድኻ ፡ ወዳጇን ፡
መተማ ፡ አፈሰሰው ፡ ዮሐንስ ፡ ጠጇን።

የጐንደር ፡ ሃይማኖት ፡ ቆማ ፡ ስታለቅስ ፡
አንገቱን ፡ ሰጠላት ፡ ዳግማይ ፡ ዮሐንስ ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በሞቱበት ፡ ዘመን ፡ በነሐሴ ፡ ደርቡሾች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጐንደር ፡ መጥተው ፡ ያገኙትን ፡ ትንሹንም ፡ ትልቁንም ፡ ወንዱንም ፡ ሴቱንም ፡ ቀሳውስቱንም ፡ አረዱ ። ክታረዱትም ፡ ውስጥ ፡ መምህር ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ የሚባሉ ፡ የሐዲስ ፡ መምህር ፡ (በመምህራቸው ፡ ስም ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩት) ፡ ጉባኤ ፡ አድርገው ፡ ወንጌል ፡ ሲያስተምሩ ፡ ደርቡሽ ፡ መጥቷልና ፡ ይሽሹ ፡ ብሎ ፡ ሰው ፡ ነገራቸው። ርሳቸውም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶቻቸውን ፡ የፈራችሁ ፡ ሽሹ ፡ የምትደፍሩ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ቈዩ ፡ አሏቸው ፡ ወዲያው ፡ ደርቡሽ ፡ ሰይፉን ፡ መዞ ፡ አላህ ፡ ኢሊላህ ፡ መሐመድ ፡ ረሱል ፡ አላህ ፡ እያለ ፡ በጉባኤው ፡ መካከል ፡ ገባ።

መምህሩም ፡ ከሰባት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ነአምን ፡ በክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ብለው ፡ በሰማዕትነት ፡ በነሐሴ ፡ 23 ፡ ቀን ፡ ባ1883 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተሰይፈው ፡ ዐረፉ ። ደግሞ ፡ አንድ ፡ ድምጠ ፡ መልካም ፡ አእምሮ ፡ የተባለ ፡ የጐንደር ፡ ደብተራ ፡ ጐንደር ፡ ሲጠፋ ፡ ሸሽቶ ፡ ካመለጠ ፡ በኋላ ፡ ሚስትኽ ፡ ተማረከች ፡ ብለው ፡ ቢነግሩት ፡ በጣም ፡ ይወዳት ፡ ነበርና ፡ እንደገና ፡ ለሚስቱ ፡ ሲል ፡ ተመልሶ ፡ በደርቡሾች ፡ እጅ ፡ ተማርኮ ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ መተማ ፡ ወረደ ።

ወዲያውም ፡ እስላሞች ፡ በክርስቲያኖች ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ድል ፡ ያገኙት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የእስላሞች ፡ ሃይማኖት ፡ ደስ ፡ ቢያሰኘው ፡ ይሆናል ፡ ሲል ፡ ማተቡን ፡ በጥሶ ፡ እስላም ፡ ሆነ ፡ ይባላል።

# ዐፄ ፡ ዮሐንስ



# የዳግማዊ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ 30 ።

## ስለ ፡ አቶ ፡ በዛብህ ፡ --ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክና ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ጋራ ፡ ስላላቸው ፡ ግንኙነት ።

ዐፄ ምኒልክ ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ ከአቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ትውልድ ፡ሲያያዝ ፡ የመጣው ፡ የስመ ፡ ጥሩው ፡ ንጉሥ ፡ የሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ የልጅ ፡ ልጅ የንጉሥ ፡ ኀይለ ፡ መለኮት ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። ትውልዱም ፡ ከአቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ዠምሮ ፡ ቢቈጠር ፡ ዐፄ ፡ ምኒልኩ ፡ 13ኛ ፡ ይሆናሉ ። እናታቸው ፡ ወይዘሮ እጅግ ፡ አየሁ ፡ ይባላሉ።

የተወለዱትም በ1836 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነሐሴ ፡ 12 ፡ ቀን ፡ ነው። በተወለዱ ፡ ባ11 ፡ ዓመት ፡ ከ3 ፡ ወር ፡ በሺሕ 838 ፡ ዓ.ም ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ በመጡ ጊዜ ፡ ይዘዋቸው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ሄዱ።

በዚያም ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ብልኀነታቸውንና ፡ አስተዋይነታቸውን ፡ ተመልክተው ፡ አብረው ፡ በማዕርግ ፡ ይዘዋቸው ፡ ሲኖሩ ፡ በመጨረሻም ፡ ሴት ፡ ልጃቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ አልጣሽ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ዳሩላቸው።

በዓመት ፡ በዓል ፡ የፈረስ ፡ ጉግስ ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ከምኒልክ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አይታይም ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ኢትዮጵያን ፡ አንድ ፡ አደርጋለሁ ፡ በማለት ፡ ያቀዱትን ፡ ዕቅድ ፡ በያለበት ፡ መኳንንቱና ፡ ሕዝቡ ፡ እየሸፈቱ ፡ ስላበላሹባቸው ፡ ከብስጭት ፡ የተነሣ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ያለሕግ ፡ በገደሉና ፡ ባሰሩ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚሁ ፡ አቤቶ ፡ (ምኒልክንም ፡ አስረው ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ላኳቸው።

በዚያም ፡ ከታመኑ ፡ አሽከሮቻቸውና ፡ ከናታቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ እጅግ ፡ አየሁ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ከሸዋ ፡ ባላባቶች ፡ ጋራ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ እየተላላኩ ፡ ምቹ ፡ የማምለጫ ፡ ጊዜ ፡ ሲፈልጉ ፡ ወዲያው ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የትግሬና ፡ የጐንደር ፡ የበጌምድር ፡ ሕዝብ ፡ ሸፍቶባቸው ፡ ወደ ፡ ላይና ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ሲሮጡ ፡ አቤቶ ፡ ምኒልክ ፡ ከወሎዎች ፡ ጋራ ፡ ውስጡን ፡ ተስማምተው ፡ ከመቅደላ ፡ ባ1857 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሰኔ ፡ 24 ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡ አምልጠው ፡ ወሎ ፡ ገብተው አደሩ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አቶ ፡ በዛብኽ ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነው ፡ ሸዋን ፡ ሲገዙ ፡ ይህንኑ ፡ ሰምተው ፡ ነበርና ፡ እስሪልኝ ፡ ብለው ፡ ለወሎ ፡ ገዥ ፡ ለወይዘሮ ፡ ወርቂት ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ጨምረው ፡ ላኩ።

ወይዘሮ ፡ ወርቂትም ፡ ስለ ፡ አቶ ፡ በዛብኽ ፡ ሳይሆን ፡ መቅደላ ፡ ለታሰረ ፡ ልጃቸው ፡ ለውጥ ፡ አድርገው ፡ ለዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ለመመለስ ፡ ምኒልክን ፡ የቀኑም ፡ እሥር ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ መላክተኛ ፡ ላኩ ። መላክተኞቹም ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በምኒልክ ፡ ማምለጥ ፡ ተበሳጭተው ፡ እስረኛውን ፡ ሁሉ ፡ እጅና ፡ እግሩን ፡ እየቈረጡ ፡ ገደል ፡ ሲጥሉ ፡ የወይዘሮ ፡ ወርቂትም ፡ ልጅ ፡ አብሮ ፡ መጣሉን ፡ ሰሙ ። ስለዚህ ፡ መላክተኞቹ ፡ ተመልሰው ፡ ይህንኑ ፡ ለወይዘሮ ፡ ወርቂት ፡ ነገሩ ። ወይዘሮ ፡ ወርቂትም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ተደንቀው ፡ ለምኒልክ ፡ ሸኚና ፡ አጃቢ ፡ ጨምረው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ላኳቸው። ምኒልክም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተጕዘው ፡ ጋዲሎ ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ አቶ ፡ በዛብኽ ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ ጦርነት ገጠሟቸው ። በኋላ ፡ ግን ፡ አቶ ፡ በዛብኽ ፡ ስለ ፡ ተሸነፉ ፡ ከዚያ ፡ ሸሽተው ፡ አፍቀራ ፡ ገቡ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቤቶ ፡ ምኒልክ ፡ ከሸዋ ፡ በወጡ ፡ ባ10 ፡ ዓመት ፡ ተመልሰው ፡ ሸዋ ፡ ገብተው ፡ ንጉሥ ፡ ተብለው ፡ ሲገዙ ፡ አቶ ፡ በዛብኽ ፡ አፍቀራ ፡ ሆነው ታርቀው ፡ ለመግባት ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አማላጅ ፡ ላኩ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ሊታረቋቸው ፡ ሲያስቡ ፡ ያቶ ፡ በዛብኽን ፡ አሳብ ፡ ዐውቃለሁ ፡ ባይ ፡ ገብቶ ፡ በዛብኽ ፡ አሁን ፡ ታርቄ ፡ ልግባ ፡ የሚለው ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ መኳንንቶችዎን ፡ እየሰበከ ፡ ለማስከዳት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእውነት ፡ ዕርቅ ፡ ፈልጎ ፡ አይደለም ፡ በእውነትስ ፡ ዕርቅ ፡ ፈልጎ ፡ ከሆነ ፡ የአዓፍቀራን ፡ ምሽግ ፡ አስረክበኝ ፡ ይበሉትና ፡ እስቲ ፡ ያስረክብዎ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ።



ዐፄ ፡ ምኒልክ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቶ ፡ በዛብኽ ፡ ገብተው ፡ ለንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ምሽጉን ፡ እንዲያስረክቡ ፡ ቢያዚቸው ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ አታስረክቡ ፡ ብለው ፡ ኖሮ ፡ አሽከሮቹ ፡ እንቢ ፡ አሉኝ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ፈቅጄ ፡ ነበር ፡ ስላሉ ፡ ይኸውም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ስላልተቀበሏቸው ፡ ወዲያው ፡ ተያዙና ፡ ፍርድ ፡ ተዠመረ። በፍርዱም ፡ ውስጥ ፡ መዠመሪያ ፡ ጋዲሎ ፡ ላይ ፡ አላስገባም ፡ ብለው ፡ መዋጋታቸውና ፡ ሁለተኛም ፡ የአፍቀራን ፡ ምሽግ ፡ አላስረክርብም ፡ ማለታቸው ፡ እየተጠቀሰ ፡ ይሙት ፡ በቃ ፡ ተብሎ ፡ ተፈርዶባቸው ፡ በጥይት ፡ ተደበደቡ ። በጥይትም ፡ ሲሞቱ ፡ ባሩዱ ፡ ከልብሳቸው ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ ገላቸው ፡ ስለ ፡ ነደደ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ገጠመች።

አንተም ፡ ጨካኝ ፡ ነበርኽ ፡ ጨካኝ ፡ አዘዘብኽ ፡
እንደ ፡ ገና ፡ ዳቦ ፡ እሳት ፡ ነደደብኽ።

ዐፄ ፡ ምኒልክም ፡ ባባታቸው ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጠው ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ እየተባሉ ፡ ይገዙ ፡ ዠመር ። እንዲህም ፡ አድርገው ፡ እስከ ፡ 1870 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ 12 ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ የበላይ ፡ ሳይኖርባቸው ፡ ሽዋን ፡ ሲገዙ ፡ ኖሩ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ ከጫኑ ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ከነበሩት ፡ መሳፍንት ፡ የበለጠ ፡ ኀይል ፡ ነበራቸውና ፡ አልገዛም ፡ ብለው ፡ ይዋጋሉ ፡ እየተባለ ፡ ይፈራ ፡ ነበር። ስለዚህ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በነገሡ ፡ በ7ኛው ፡ ዓመት ፡ ባ1870 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሽዋን ፡ ለማስገበር ፡ ክተት ፡ ሠራዊት ፡ ምታ ፡ ነጋሪት ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ሽዋ ፡ መጥተው ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ደረሱ።

ከዚያም ፡ አልፈው ፡ በሰላሌ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሄዱ። ንጉሥ ፡ ምኒልክም ፡ እንደ ፡ ተፈራው ፡ ሳይዋጉ ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ እገብራለሁ ፡ ሲሉ ፡ ደብዳቤ ፡ አሲዘው ፡ መላክተኛ ፡ ላኩ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ ተነጋግረን ፡ በመሐላ ፡ ዕርቃችንን ፡ እንፈጽም ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ላኩባቸው ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሄደው ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ ተገናኙ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ በክብር ፡ ከተቀበሏቸው ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክም ፡ እገብራለሁ ፡ ስላሉ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ የፍቅር ፡ ምልክት ፡ ዘውድ ፡ ሰጥተው ፡ የምኒልክን ፡ የሽዋ ፡ ንጉሥነት ፡ አጽድቀውላቸው ፡ ሁለቱም ፡ በሰላም ፡ ተሰነባበቱ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በነበራቸው ፡ የጦር ፡ ኀይልና ፡ ስፊ ፡ ግዛት ፡ በኀያላን ፡ የጦር ፡ አለቆቻቸው ፡ በነራስ ፡ ጐበና ፡ ዠግንነት ፡ የተነሣ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አሳባቸውን ፡ በልባቸው ፡ ይዘው ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ሲጠሯቸውም ፡ እየሄዱ ፡ ግብርም ፡ እገብራለሁ ፡ ብለው ፡ ለጊዜው ፡ ታዛዥ ፡ ቢመስሉ ፡ ዘራቸው ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክና ፡ ከልብነ ፡ ድንግል ፡ መሆኑ ፡ ስለሚታሰባቸው ፡ የኢትዮጵያ ንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ የሚገባው ፡ ለኔ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ያልተገለጠ ፡ የኀሊና ፡ ትግል ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ ነበራቸው ። ስለዚህ ፡ ገና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሳይባሉ ። ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሚል ፡ ማኅተም ፡ አሠርተው ፡ ማተም ፡ ዠምረው ፡ ነበር።

ይልቁኑንም ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ወዳጅነትና ፡ ስላም ፡ መሥርቶ ፡ የነበረው ፡ የራስ ፡ አርአያና ፡ የወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ጋብቻ ፡ ራስ ፡ አርአያ ፡ ባ1880 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰኔ ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ የሁለቱ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ተቋረጠ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ጋራ ፡ ለንግድና ፡ ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ በቀጥታ ፡ እየተጻጻፉ ፡ ወዳጅነት ፡ ዠመሩ።

ከዚያም ፡ በፊት ፡ የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ የሁለተኛው ፡ ቢክቶሪዮ ፡ ኤማኑኤል ፡ አናዛዥ ፡ (የንስሓ ፡ አባት) ፡ የነበሩ ፡ አባ ፡ ማስያስ ፡ የሚባሉት ፡ ሚሲዮናዊ ፡ በትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ዘመን ፡ መጥተው ፡ በጋላው ፡ አገር ፡ ሲሰብኩ ፡ ቈይተው ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጥተው ፡ ከንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ በጣም ፡ ተላምደው ፡ አንዳንድ ፡ ምክር ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ። በርሳቸውም ፡ አማካይነት ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ደብዳቤ ፡ እየተላላኩ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ አደረጉ ። ስለዚህ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ባ1870 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በታኅሥ ፡ ወር ፡ ማርኬዝ ፡ አንቲኖሪ ፡ ከሚባለው ፡ ጋራ ፡ ሌሎች ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ጨምሮ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ልኮ ፡ መልክተኞቹ ፡ በሐር ፡ አምባ ፡ ሲደርሱ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ የነዚህ ፡ የኢጣሊያ ፡ መልክተኞች ፡ አመጣጥ ፡ አገር ፡ የመሰለል ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ በማለት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ወዳገሬ ፡ የመጡት ፡ አሁንም ፡ ተመልሰው ፡ ወዳገራቸው ፡ ይግቡ ፡ ብለው ፡ አባ ፡ ማስያስን ፡ ጠርተው ፡ ተቈጧቸው። አባ ፡ ማስያስም ፡ ተነሥተው ፡ እነዚህ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጡ ፡ ኢጣሊሲያኖች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ወይም ፡ ሸዋን ፡ የሚጐዱ ፡ አይደሉም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የረዱ ፡ የአውሮፓ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ለዚሁም ፡ ማስረጃ ፡ ከአውሮፓ ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ ግራኝ ፡ አሕመድን ድል ፡ አድርገው ፡ ያባረሩ ፡ ፖርቱጊዞች ፡ ናቸው።

ቀጥሎም ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መሳፍንት ፡ ገባር ፡ ለማድረግ ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ መጥተው ፡ ድል ፡ ያደረጉ ፡ እንግሊዞች ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ የአውሮፓ ፡ ሕዝብ ፡ ይልቁኑንም ፡ አሁን ፡ እነዚህ ፡ የመጡት ፡ ፈረንጆች ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ መሣሪያና ፡ በያይነቱ ፡ ልብስ ፡ አምጥተው ፡ አገርዎን ፡ የሚያበለጥጉ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የሚጐዳ ፡ ነገር ፡ እንዳያደርጉ ፡ እኔ ፡ ዋስ ፡ ነኝ ፡ ሲሉ ፡ በንጉሥ ፡ ምኒልክና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ለመምከር ፡ በተሰበሰቡት ፡ መካከል ፡ ቆመው ፡ በተናገሩ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ነገሩ ፡ በሙሉ ፡ የታመነ ፡ ባይሆን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከመጡ ፡ እናነጋግራቸው ፡ ብለው ፡ ተቀበሏቸው።



ራስ ፡ አርአያ ፡ ሥላሴ ፡ ዮሐንስ



አባ ፡ ማስያስ ።

እንግዶቹም ፡ ፈረንጆች ፡ ሐር ፡ አምባ ፡ ሆነው ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበርና ፡ ወዲያው ፡ የአንኮበሩ ፡ አዛዥ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ አምጥተው ፡ ከንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ልቼ ፡ ላይ ፡ አገናኗቸው።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንባቢን ፡ የሚገርም ፡ ነገር ፡ አለ ። አባ ፡ ማስያስ ፡ ከወንጌል ፡ መላክተኛነት ፡ በተረፈው ፡ ጊዜያቸው ፡ ወደ ፡ ፖለቲካ ፡ እየገቡ ፡ በሸዋ ፡ መንግሥትና ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ ሆነው ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ሠርተው ፡ ነበር። ስለዚህ ፡ ቢክቶር ፡ ኤማኑኤል ፡ ሁለተኛ ፡ ስለ ፡ ሠሩት ፡ ውለታ ፡ ሽልማት ፡ «ማውሪሲዮና ፡ ላዛሮ» ፡ በሚባሉ ፡ ቅዱሳኖቻቸው ፡ የሚጠራ ፡ ኒሻን ፡ በዚሁ ፡ በማርኬዝ ፡ አንቲኖሪ ፡ እጅ ፡ ልኮላቸው ፡ ነበር ። ርሱም ፡ ነገሩ ፡ ክብር ፡ እንዲያገኝ ፡ በንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ፊት ፡ እሰጣለሁ ፡ ብሎ ፡ መዠመሥሪያ ፡ ለብቻ ፡ ሲገናኙ ፡ ነገሩን ፡ ሳይገልጽላቸው ፡ ከንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ተገናኝቶ ፡ ከኢጣሊያ ፡ አገር ፡ የተላከውን ፡ ደብዳቤና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ አቀረበና ፡ ወዲያውም ፡ ለአባ ፡ ማስያስ ፡ የተላከውን ፡ ኒሻን ፡ በዚሁ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ እንሆ ፡ ብሎ ፡ ቢሰጣቸው ፡ ርሳቸው ፡ በነገሩ ፡ አፍረው ፡ አልቀበልም ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱም ፡ አፍረው ፡ ኒሻኑን ፡ የሚያነሣው ፡ በመጥፋቱ ፡ ንጉሡና ፡ የጉባኤው ፡ መኳንንት ፡ ተገረሙ ። በኋላ ፡ ግን ፡ የአባ ፡ ማስያስ ፡ ጓደኛ ፡ ሞንሲኜር ፡ ቶሪ ፡ አነሡትና ፡ የሌላው ፡ ጒዳይ ፡ ንግግር ፡ ተዠመረ። አባ ፡ ማስያስ ፡ አልቀበልም ፡ ያሉበት ፡ ምክንያት ፡ የእግዚአብሔርና ፡ የወንጌል ፡ መላክተኛ ፡ ነኝ ፡ ሲሉ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ለኢጣሊያ ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ኒሻን ፡ ሲላክላቸው ፡ የወንጌል ፡ መላክተኛነታቸውን ፡ ስለሚያስተባብልባቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በውጭ ፡ ለብቻቸው ፡ ሰጥቷቸው ፡ ቢሆን ፡ በደስታ ፡ ሳይቀበሉት ፡ የሚቀሩ ፡ አይመስልም።

ወደ ፡ ዋናው ፡ አሳብ ፡ እንመለስ ፡ እንግዶቹ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ጒዳያቸውን ፡ በአባ ፡ ማስያስ ፡ አስተርጓሚነት ፡ ተነጋግረው ፡ ሲጨርሱ ፡ ወዲያው ፡ ለጊዜው ፡ እንዲያርፉበት ፡ አንኮበር ፡ አጠገብ ፡ ልጥ ፡ ማረፊያ ፡ የሚባለውን ፡ ማረፊያ ፡ ሥፍራ ፡ አደረጉላቸው ። ማርኬዝ ፡ አንቲኖሪ ፡ የሚባለውና ፡ ጓደኞቹ ፡ መጥተው ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ ቀጥሎ ፡ ኮንት ፡ ፔየትሮ ፡ አንቶኔሊ ፡ የሚባለው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መላክተኛ ፡ ሆኖ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥቶ ፡ ተቀመጠ። በርሱም ፡ አማካይነት ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክና ፡ የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ንግድና ፡ ስለ ፡ ወዳጅነት ፡ ብዙ ፡ ደብዳቤ ፡ ተላልከው ፡ ነበር። በመጨረሻም ፡ መሣሪያ ፡ ላክልኝ ፡ ብለው ፡ ልከውበት ፡ የኢጣሊያም ፡ ንጉሥ ፡ በዚህ ፡ ለውጥ ፡ መሬት ፡ ወይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የበላይ ፡ ጠባቂነት ፡ ለማግኘት ፡ ተስፋ ፡ አድርጎ ፡ የጠየቁትን ፡ መሣሪያ ፡ ላከላቸው።


# ምዕራፍ ፡ 31 ፡፡

## ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ ተጉዘው ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ እንዳደረጉ ፡ -ቦሩ ፡ ሜዳ ፡ ውጫሌ ፡ ላይ ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተዋዋሉ ፡ ከቦሩ ፡ ሜዳ ፡ ተመልሰው ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ እንደ ፡ ደፉ፡፡

ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ከያውራጃው ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸው ፡ በእንጦጦ ፡ ከተከማቸ ፡ በኋላ ፡ ባ1881 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በየካቲት ፡ 28 ፡ ቀን ፡ ከእንጦጦ ፡ ተነሥተው ፡ በመጋቢት ፡ 7 ፡ ቀን ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ደርሰው ፡ ከዚያም ፡ በዚሁ ፡ ወር ፡ ባ11ኛው ፡ ቀን ፡ ተነሥተው ፡ ወሎ ፡ ሲደርሱ ፡ በግሼን ፡ ሐይቅ ፡ የዐፄ ፡ ዮሕንስን ፡ ዕቃ ፡ ይጠብቁ ፡ የነበሩት ፡ የንጉሥ ፡ ዕቃ ፡ ለንጉሥ ፡ ነው ፡ ተረካቢ ፡ ይላኩልን ፡ ብለው ፡ መላክተኛ ፡ ላኩ ፡፡ ንጉሡም ፡ ዕቃውን ፡ እንዲረከቡ ፡ ደጃዝማች ፡ ወልዴ ፡ አምባውን ፡ እንዲጠብቁ ፡ አቶ ፡ ወልደ ፡ ተክሌን ፡ ላኩ፡፡

በዚሁ ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ መተማ ፡ ላይ ፡ መሞት ፡ ተሰምቶ ፡ ነበርና ፡ ሕዝቡም ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አድርጎ ፡ በፍርሃት ፡ ተገዛላቸው ፡፡ እሳቸውም ፡ ገኸሽ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ባለኸ ፡ ርጋ ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ አስነግረው ፡ በሚያዝያ ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ የጁ ፡ ተጉዘው ፡ ሐይቅ ፡ ሲደርሱ ፡ ለደጃዝማች ፡ ወሌ ፡ የራስነት ፡ ማዕርግ ፡ ጨምረው ፡ ከጨጨሆ ፡ በመለስ ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሾሟቸው፡፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዚያው ፡ አውራጃ ፡ ሳሉ ፡ የጐጃሙ ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፥ የላስታው ፡ ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ብሩ ፥ የስሜኑ ፡ ደጃች ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፥ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ልጅ ፡ ራስ ፡ መሸሻ ፡ እየመጡ ፡ እጅ ፡ እየነሡ ፡ ገቡላቸው፡፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክም ፡ ለነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ግዛት ፡ ላነሳቸው ፡ ግዛት ፡ እየጨመሩ ፡ የቀሩትንም ፡ በየአባት ፡ አገራቸው ፡ ላይ ፡ ሾመው ፡ ወደ ፡ እንጦጦ ፡ ሲመለሱ ፡ ወረይሉ ፡ ቦሩ ፡ ሜዳ ፡ በተለይ ፡ ውጫሌ ፡ እሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሰፍረው ፡ ሳለ ፡ ሚያዝያ ፡ 25 ፡ ቀን ፡ 1881 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ቀጥሎ ያለውን ፡ የውጫሌ ፡ ውል ፡ ተዋዋሉ ፡ አስተርጓሚውም ፡ ግራዝማች ፡ ዮሴፍ ፡ ናቸው፡፡ ውሉ ፡ እንደ ፡ መቅድም ፡ ከወደ መዠመሪያው ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ፡



# የውጫሌው ውል

«የኢጣልያ ፡ ንጉሥ ፡ ዑምቤርቶ ፡ በስም ፡ መዠመሪያ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥትና ፡ ለኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ የሚኖር ፡ ሰላምና ፡ ዕርቅ ፡ ለማድረግ ፡ የፍቅርና ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ ተዋዋሉ ። የኢጣልያ ፡ ንጉሥ ፡ ኮንት ፡ አንቶኔሊን ፡ ................ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ምኒልክ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ተቀብሎ ፡ የተላከ ............ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ምኒልክ ፡ የኢትዮጵያን ፡ አልጋ ፡ የወረሱ ፡ እርስዎ ፡ ስለሆኑ ፡ ይህን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈውን ፡ ውል ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ምኒልክ ፡ ጋር ፡ ተዋዋልን ።

# 1ኛ ።

በኢጣሊያና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መካከል ፡ በወራሾቻቸውም ፡ በሕዝባቸውም ፡ እነዚህንም ፡ በተጠጉ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ሰላምና ፡ ፍቅር ፡ ሳይጐድል ፡ ለዘወትር ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ይኖራል ።

# 2ኛ ።

እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ አሁን ፡ የተዋዋሉት ፡ ነገሥታት ፡ በያገራቸው ፡ በየምስለኔያቸው ፡ ይነጋገራሉ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ አገር ፡ ቆንስልም ፡ የቆንስልም ፡ ወኪል ፡ መሾም ፡ ይቻላቸዋል ። እነዚህም ፡ ሹሞች ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ ሥርዐት ፡ መታፈርና ፡ መከበር ፡ አይጐድልባቸውም።

# 3ኛ

በነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ነገሥታት ፡ ወሰን ፡ ጠብና ፡ ክርክር ፡ እንዳይነሣ ፡ በዕውቅ ፡ የተመረጡ ፡ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ልከው ፡ በማይጠፉ ፡ ምልክት ፡ የግዛቱን ፡ ድንበር ፡ ይወስናሉ ። ከድንበሩ ፡ ወዲህ ፡ የሚጨመሩት ፡ አገሮች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። የደጋው ፡ ዐፈር ፡ ከኢትዮጵያና ፡ ከኢጣሊያ ፡ መኻል ፡ ወሰን ፡ ይሆናል ። ከራፋሲ ፡ ጀምር ፡ ሐላይ ፥ ሰገነይቲ ፥ አሥመራ ፡ ሦስቱ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ መንደር ፡ ይሆናሉ ። ዳግመኛ ፡ በቦጎስ ፡ በኩል ፡ ዐዲ ፡ ነፋስ ፥ ዐዲ ፡ ሞገስ ፡ በኢጣሊያ ፡ ድንበር ፡ ውስጥ ፡ ይሆናሉ ፡ ከዐዲ ፡ ሞገስ ፡ መንደር ፡ ዝምሮ ፡ ከምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ባቀና ፡ ይከፈላል ።

# 4ኛ

የደብረ ፡ ቢዘን ፡ ገዳሙ ፡ ከነኁልቱ ፡ ከነርስቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይቀራል ፡ የጦር ፡ አምባ ፡ መሆን ፡ ግን ፡ አይቻለውም።

# 5ኛ ።

ከምጥዋ ፡ የሚመጣ ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ከ100 ፡ 8 ፡ በገቢ ፡ ዕቃ ፡ እየተገመገመ ፡ በገቢ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይከፍላሉ።

# 6ኛ ።

የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ንግድ ፡ በምጥዋና ፡ በኢትዮጵያ ፡ መካከል ፡ የሚመላለሰው ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ብቻ ፡ ይፈቀድልዎታል ። ሲያስመጡም ፡ ባለማኅተም ፡ ደብዳቤዎን ፡ ለኢጣሊያ ፡ ሹማምት ፡ እየላኩ ፡ ያስመጣሉ ፡ ነፍጡንም ፡ የያዘውን ፡ ሰፈር ፡ ከምጥዋ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ድንበር ፡ ድረስ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ወታደሮች ፡ ዘበኛ ፡ ሆነው ፡ ይሸኙሉ።

## 7ኛ።

የነዚህ ፡ የሁለቱ ፡ ውል ፡ ያደረጉ ፡ ነገሥታት ፡ ዜጎች ፡ የንግድ ፡ ዕቃቸውን ፡ ይዘው ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ አገር ፡ መሄድና ፡ መምጣት ፡ ይቻላቸዋል ። በየመንግሥቱና ፡ በየወረዳው ፡ ባለው ፡ ሹም ፡ ጥግነት ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ይመላለሳሉ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የያዘ ፡ ብዙ ፡ ሆኖ ፡ ካንዱ ፡ ድንበር ፡ ወዳንዱ ፡ ድንበር ፡ መተላለፍ ፡ ተከልክሏል ። እንዲህም ፡ ማለት ፡ አንዱ ፡ ያንዱን ፡ ከብት ፡ እንዳይዘርፍ ፡ በሁሉም ፡ ነገር ፡ እንዳይነካካ ፡ ተከልክሏል ።

## 8ኛ

የኢጣሊያ ፡ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ በኢጣሊያ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በሚገዛው ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ እንደያገሩ ፡ ልማድ ፡ መግዛት ፡ መሸጥ ፡ መከራየት ፡ ይቻላቸዋል።

## 9ኛ ።

የነዚህ ፡ የሁለቱ ፡ ነገሥታት ፡ ዜጎች ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ አገር ፡ ቢሄድ ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ይኖራሉ።

## 10ኛ

የኢጣሊያ ፡ ሰውና ፡ የኢጣሊያ ፡ ሰው ፡ የተካሰሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነዚያ ፡ በመረጡት ፡ ዳኛ ፡ ያለዚያም ፡ ተያይዘው ፡ ምጥዋ ፡ ወርደው ፡ ይዳኛሉ። የኢጣሊያና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ የተጣሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ወኪልና ፡ የኢጣሊያ ፡ የምጥዋ ፡ ሹም ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ ይዳኛሉ።

## 11ኛ ።

የኢጣሊያ ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኢትዮጵያም ፡ ሰው ፡ በኢጣሊያ ፡ አገር ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በሚገዛው ፡ አገር ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሟቹ ፡ መንግሥት ፡

ወገን ፡ ገንዘቡን ፡ የሚቀበል ፡ ሰው ፡ አስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ የሁለቱ ፡ ነገሥታት ፡ ሹማምንት ፡ ገንዘቡን ፡ ጠብቀው ፡ ያስቀምጣሉ።

## 12ኛ ።

በማናቸውም ፡ ኀጢአት ፡ ተከሶ ፡ የተያዘው ፡ የኢጣሊያ ፡ ሰው ፡ በኢጣሊያ ፡ ሹማምንት ፡ ይዳኛል ። ስለ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ታላቅ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርቶ ፡ የተገኘ ፡ የኢጣሊያን ፡ ሰው ፡ ፈጥነው ፡ ይዘው ፡ ለምጥዋ ፡ ሹማምት ፡ መስጠት ፡ ነው ። ደግሞ ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ ታላቅ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዳኛ ፡ ይዳኛሉ።

## 13ኛ ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ ብርቱ ፡ ኀጢአት ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ካንዱ ፡ ግዛት ፡ ወዳንዱ ፡ ግዛት ፡ ሸሽቶ ፡ የሄደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁለቱም ፡ እያሰሩ ፡ ይልካሉ።

## 14ኛ ።

የባሪያ ፡ ንግድ ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ የተከለከለ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በሚቻላቸው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ባገራቸው ፡ በባሪያ ፡ እንዳይነገድ ፡ ይከላከላሉ ።

## 15ኛ

ይህ ፡ አሁን ፡ የተጻፈው ፡ ውል ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ውል ፡ ነው።

## 16ኛ ።

ይህ ፡ ውል ፡ ከተደረገ ፡ ካ5 ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ከሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ አንዳቸው ፡ ውል ፡ ለመጨመር ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ የፈለጋቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካመት ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ መናገር ፡ ይገባቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ ብቻ ፡ ማረም ፡ ማስጠንቀቅ ፡ ይገባቸዋል ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ የተለየውን ፡ የድንበር ፡ ወሰን ፡ ማፍረስ ፡ አይቻላቸውም።

## 17

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከኤውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ ለሚፈልጉት ፡ ጕዳይ ፡ ሁሉ ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ አጋዥነት ፡ መላላክ ፡ ይቻላቸዋል ።

## 18ኛ ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከሌላ ፡ መንግሥት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ የጥበብ ፡ የንግድ ፡ ነገር ፡ ለመዋዋል ፡ የፈለጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሁለቱ ፡ አማርጠው ፡ ሲያበቊ ፡ የሁለቱም ፡ ውል ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለኢጣሊያ ፡ ሰው ፡ ይሰጡታል።

## 19ኛ

ይህ ፡ አሁን ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ ባማርኛና ፡ በኢጣሊያ ፡ ቋንቋ ፡ ትክክል ፡ ሆኖ ፡ ተገልብጦ ፡ ሲያበቃ ፡ የታመነ ፡ ምስክር ፡ ይሆናል ።


## 20ኛ

ይህ ፡ አሁን ፡ የተጻፈው ፡ ውል ፡ በሮማ ፡ ከተማ ፡ ፈጥኖ ፡ ይጠነቀቃል ፡ ነገር ግን ፡ ይህን ፡ ውል ፡ ኮንት ፡ ፒዬትሮ ፡ አንቶኔሊ ፡ በኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ ስም ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ ተዋውለው ፡ አትመው ፡ ጨርሰዋል ። ሚያዝያ ፡ 25 ፡ ቀን ፡ 1881 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በውጫሌ ፡ ሠፈር ፡ ተጻፈ ።


ዳሩ ፡ ግን ፡ የቀሩት ፡ አንቀጾች ፡ ነጻና ፡ ትክክል ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ መንግሥታት ፡ የሚዋዋሉት ፡ ዐይነት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ 17ኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንዳማርኛ ፡ አተረጓጐም ፡ «የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ (ፈቃዱ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ) ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ የሚያደርገውን ፡ ግንኙነት ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በኩል ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል» ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ኢጣሊያ ፡ አተረጓጐም ፡ « የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ የሚያደርገውን ፡ ግንኙነት ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ አማካይነት ፡ ማድረግ ፡ ይገባዋል » ፡ የማለት ፡ አሳብ ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ መጫናቸውን ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ በቀጥታ ፡ ባስተላለፉ ፡ ጊዜ ፡ የፈቃዱን ፡ እንደ ፡ ግዴታ ፡ ቈጥሮ ፡ ክርክር ፡ ስላነሣና ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ የኢጣሊያና ፡ ያማርኛ ፡ ትርጉም ፡ የሚሰጠው ፡ ስሜት ፡ ለየብቻ ፡ በመሆኑ ፡ ላ5 ፡ ዓመት ፡ ተጻጽፈው ፡ የነበረው ፡ ውል ፡ በጭራሽ ፡ ፈርሶ ፡ ነገሩም ፡ የዐድዋን ፡ ጦርነት ፡ አስከተለ ። ከዚህ ፡ ውል ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ከቦሩ ፡ ሜዳ ፡ ሐምሌ ፡ 9 ፡ ቀን ፡ እንጦጦ ፡ ገቡ ። በገቡ ፡ ባ4ኛው ፡ ወር ፡ ጥቅምት ፡ 25 ፡ ቀን ፡ 1882 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጳጳሱ ፡ በአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ እጅ ፡ ተቀብተው ፡ « ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትየጵያ » ፡ ተብለው ፡ እንጦጦ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነገሡ ።



የኢጣልያ ፡ ንጉሥ ፡ ዑምቤርቶ



የውጫሌውን ፡ ውል ፡ የተረጐሙት ፡ ግራዝማች ፡ ዮሴፍ ፡



የውጫሌን ውል የተዋዋለው ፒዬትሮ አንቶኔሊ

# ምዕራፍ ፡ 32 ።

## የኰዓቲት ፡ የአምባ ፡ አላጌ ፡ የመቀሌ ፡ ጦርነት ።

ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በ1881 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ስለ ፡ ገቡላቸው ፡ የትግሬንም ፡ ግዛት ፡ ሾመዋቸው ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ወራሽ ፡ በመሆናቸው ፡ አልገዛም ፡ ብለው ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ጄኔራል ፡ ጋንዶልፊ ፡ በሚባለው ፡ አማካይነት ፡ ኅዳር ፡ 29 ፡ ቀን ፡ 1884 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ወዳጅነት ፡ ውል ፡ ተፈራረሁ ።

በኋላ ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ እንዲመጡ ፡ በላኩባቸው ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ በማመንታት ፡ ቈይተው ፡ በመጨረሻ ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ከራስ ፡ አሉላና ፡ ከራስ ፡ ሐጐስ ፡ ጋራ ፡ ባ1886 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ስለ ፡ መጡ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ የትግሬን ፡ ግዛት ፡ መርቀውላቸው ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ተመለሱ ።

ስለዚህ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስንና ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክን ፡ ያጣሉ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንደዚሁ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክንና ፡ ራስ ፡ መንገሻን ፡ ለማጣላት ፡ ያሰቡት ፡ አሳብ ፡ በፍጹም ፡ ተበላሸባቸው ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ቀድሞ ፡ በዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ጊዜ ፡ ይዞት ፡ ከነበረው ፡ አገር ፡ አልፎ ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስና ፡ ከራስ ፡ አሉላ ፡ እየተጣሉ ፡ ከድተው ፡ ለኢጣሊያ ፡ ገብተው ፡ በነበሩት ፡ በነደጃች ፡ ባሕታ ፡ ሐጐሰና ፡ በነደበብ ፡ እየተመራ ፡ የውጫሌ ፡ ውል ፡ ከፈረሰ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ስፍራ ፡ ያዘ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ደጃች ፡ ባሕታ ፡ ሐጐስ ፡ ኢጣልያኖች ፡ እያደር ፡ ኢትዮጵያን ፡ መያዛቸውንና ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉትንም ፡ ውርደት ፡ ስለ ፡ ተመለከቱት ፡ ኢጣሊያኖችን ፡ ከድተው ፡ የሰገነይቲን ፡ ምስለኔ ፡ ቴኔንቴ ፡ ሳንጉይነቲን ፡ አስረው ፡ በሸፈቱ ፡ ጊዜ ፡ በማጆር ፡ ቶዜሊ ፡ የሚታዘዙ ፡ ኢጣልያኖች ፡ ተከታትለዋቸው ፡ ነበሩና ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ በሐላይ ፡ ሲዋጉ ፡ ባ1887 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ታኅሣሥ ፡ 10 ፡ ቀን ፡ ሞቱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባ1887 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ 10 ፡ ቀን ፡ ራስ ፡ መንገሻና ፡ ራስ ፡ አሉላ ፡ ከሚመጣው ፡ ከኢጣሊያ ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ ኰዓቲት ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ ገጥመው በዠግንነት ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ የኢጣሊያም ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ሸሽት ፡ ዠመረ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ተጠባባቂ ፡ የነበረው ፡ የጄኔራል ፡ አሪሞንዲ ፡ አዲስ ፡ ጦር ፡ ደርሶ ፡ ሲዋጋ ፡ ጊዜው ፡ ስለ ፡ መሸ ፡ ጦርነቱን ፡ ቆመ ። በማግስቱም ፡ እንዲሁ ፡ ተዋግተው ፡ በኋላ ፡ ለኢጣሊያኖች ፡ አዲስ ፡ ጦር ፡ እንደገና ፡ መጣ ፡ ማለትን ፡ ከሐሰተኛ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሰሙ ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ወደ ፡ ሰናዓፌ ፡ አፈገፈጉ ። በዚያም ፡ ሰፍረሁ ፡ ሳሉ ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ በግሥጋሤ

፡ ደርሶ ፡ አደጋ ፡ ጣለባቸው ። ስለዚህ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ሰፈራቸውን ፡ ከነድንኳናቸው ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሸሹ ። ኢጣሊያኖችም ፡ ካሉበት ፡ ስፍራ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ሰፍረውበት ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡ ሰናዓፌ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በራስ ፡ መንገሻ ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ዕቃና ፡ ይልቁንም ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክና ፡ ከደጃች ፡ ባሕታ ፡ ሐጐስ ፡ ጋራ ፡ የተጻጻፉትን ፡ ደብዳቤ ፡ ባገልግል ፡ ውስጥ ፡ በማግኘታቸው ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ከራስ ፡ መንገሻ ፡ ወገን ፡ 1 ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ ሲሞት ፡ እንደዚሁ ፡ ትልቁ ፡ ደጃዝማች ፡ ተድላ ፥ ደጃች ፡ በየነ ፥ ደጃች ፡ ካሳ ፥ ቀኛዝማች ፡ አንዳርጋቸው ፡ የሚባሉት ፡ መኳንንቶቻቸው ፡ አብረው ፡ ሞቱ ፡ ሹም ፡ አጋሜ ፡ ተስፋዬም ፡ ቈስለው ፡ ነበር ። የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ አዛዥም ፡ በዚህ ፡ በቀመሰው ፡ ድል ፡ የተነሣ ፡ ኩራት ፡ ተሰምቶት ፡ ሳለ ፡ ወዲያው ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ፍራንቼስኮ ፡ ክርስፒ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቴሌግራም ፡ ከኢጣሊያ ፡ አስተላለፈለት ። «የትግሬ ፡ ግዛት ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የተከፈተ ፡ ነውና ፡ ለመያዝ ፡ ባንፈልግ ፡ የኛ ፡ ስንፍና ፡ መሆኑን ፡ እንዳትዘነጋ »

ጄኔራል ፡ ባራቲዬሪም ፡ ራሱ ፡ እንደሚያስበውና ፡ ከበላዩም ፡ እንደ ፡ ተረጋገጠለት ፡ ካሥመራ ፡ የቀጠራቸውን ፡ ወታደሮች ፡ ከፊት ፡ የነጮቹን ፡ ወታደሮች ፡ ከኋላ ፡ አድርጎ ፡ እየተጓዘ ፡ እስከ ፡ ዐድዋ ፡ ድረስ ፡ መጣ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በግልቢያ ፡ ዐድዋ ፡ ድረስ ፡ ሲመጣ ፡ ለጦርነት ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ አልነበረውምና ፡ እንዲላክለት ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ አገር ፡ ላከ ። በዚያም ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ እንኳን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ የሚላክና ፡ ለዚህም ፡ አገር ፡ ጉዳይ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፡ ለክርስፒ ፡ ስላስታወቀው ፡ ክርስፒም ፡ «ናፖሊዮን ፡ ጦርነቱን ፡ ያካሂድ ፡ የነበረው ፡ በተሸናፊዎች ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ፡ አንተም ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብለሽ ፡ ከዚያው ፡ እየፈለግኸ ፡ ሥራኸን ፡ ሥራ ፡ እንጂ ፡ የገንዘብን ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ አድርገኸ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ከመግፋት ፡ እንዳትቦዝን » ፡ ብሎ ፡ ለባራቲዬሪ ፡ መልስ ፡ ላከበት።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ የኢጣሊያኖችን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ መግፋት ፡ ሰምተው ፡ ነበርና ፡ ወዳጅነቱን ፡ አፍርሶ ፡ የያዘውን ፡ አገር ፡ ለቆ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲመለስ ፡ ላኩበት ። እሱ ፡ ግን ፡ ከዐድዋ ፡ በመመለስ ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እየገፋ ፡ ከዐድዋ ፡ እስከ ፡ መቀሌ ፡ ከመቀሌ ፡ እስከ ፡ አምባላጌ ፡ ደረሰ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ አልጋቸውን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ላጎታቸው ፡ ለራስ ፡ ዳርጌ ፡ ሰጥተው ፡ ረዳትም ፡ ደጃዝማች ፡ ኀይለ ፡ ማርያምንና ፡ ወህኒ ፡ አዛዥ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅን ፡ ጨምረው ፡ በጥቅምት ፡ 2 ፡ ቀን ፡ በሺህ ፡ 888 ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ አድርገው ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ተነሥተው ፡ በጥቅምት ፡ 17 ፡ ቀን ፡ ደሴ ፡ ከተማ ፡ ገብተው ፡ ለጦርነቱ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ያዘጋጁ ፡ ዠመር ። ከጃንሆይም ፡ ጋራ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ አልለይም ፡ ብለው ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ አብረው ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ የጦር ፡ አበጋዝ ፡ ሆነው ፡ ራስ ፡ ወሌን ፥ ራስ ፡ ሚካኤልን ፥ ራስ ፡ መንገሻ ፡ አቲከምን ፥ ራስ ፡ ኣሉላን ፥ ደጃች ፡ ወልዴን ፥ ፊታውራሪ ፡ ገበየሁን ፥ ፊታውራሪ ፡ ተክሌን ፥ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ አድነውን ፥ ቀኛዝማች ፡ ታፈሰን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲጓዙ ፡ ወዲያው ፡ ኢጣሊያኖች ፡ መሽገው ፡ በተቀመጡበት ፡ በአምባላጌ ፡ ተራራ ፡ አጠገብ ፡ ደረሱ ። ወዲያው ፡ ጦሩን ፡ ያለበት ፡ አሰልፈው ፡ ደም ፡ ከመፋሰስ ፡ በፊት ፡ በሰላም ፡ እንዲለቅና ፡ የክርስቲያን ፡ ደም ፡ በከንቱ ፡ እንዳይፈስ ፡ ሲሉ ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፉለት። እርሱም ፡ ደብዳቤውን ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ በመልቀቅ ፡ ፈንታ ፡ ረዳትና ፡ መሣሪያ ፡ ላኩልኝ ፡ ብሎ ፡ ለጄኔራል ፡ አሪሞንዲ ፡ ልኮ ፡ ረዳት ፡ ከመጣለት ፡ በኋላ ፡ አለቅም ፡ ሲል ፡ ኩራት ፡ ያለበት ፡ ንግግር ፡ ጨምሮ ፡ ላከላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፍተው ፡ በኅዳር ፡ 28 ፡ ቀን ፡ እተራራው ፡ ጥግ ፡ ደረሱ ። ከዚያም ፡ የቀሩትን ፡ ራሶች ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ አሰልፈው ፡ ራሳቸው ፡ በማኸል ፡ ሆነው ፡ ተራራውን ፡ ከሰው ፡ እያጣደፉ ፡ ይወጉት ፡ ዠመር ። ጦርነቱም ፡ 2 ፡ ሰዓት ፡ ያኸል ፡ እንደ ፡ ቈየ ፡ የኢጣሊያ ፡ ወታደሮች ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ሸሽት ፡ ዠመሩ ። ማጆር ፡ ቶዜሊ ፡ ከነወታደሩ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሲሸሽ ፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ እየተከታተሉ ፡ ሲወጉት ፡ እሱም ፡ ወታደሩ ፡ እንዲሸሽ ፡ ትእዛዝ ፡ እየሰጠ ፡ አባራሪዎቹን ፡ ለማቆም ፡ በርትቶ ፡ ሲዋጋ ፡ ወዲያው ፡ በ7 ፡ ጥይት ፡ ተመቶ ፡ ስለ ፡ ሞትና ፡ የተረፈውም ፡ እየሸሸ ፡ ወደ ፡ መቀሌ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ እንደዚህ ፡ ተብሎ ፡ ተገጠመ ።

አላጌ ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፡ ማጆር ፡
እንደ ፡ ግራኝ ፡ ሁሉ ፡ በሰባት ፡ ዐረር ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጄኔራል ፡ አሪሞንዲ ፡ የሚባለው ፡ 1ኛው ፡ የጦር ፡ አዝማች ፡ ሸሽተው ፡ ከአምባላጌ ፡ ወደ ፡ መቀሌ ፡ የሚሄዱትን ፡ ለመርዳት ፡ መጥቶ ፡ ካባራሪዎቹ ፡ ጋራ ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ በኮለኔል ፡ ጁሴፔ ፡ ጋሊያኖ ፡ ኣዛዥነት ፡ እመቀሌ ፡ ላይ ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ተመለሰ ። ኮሎኔል ፡ ጁሴፔ ፡ ጋሊያኖም ፡ ብዙ ፡ ወታደርና ፡ መሣሪያ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሥንቅ ፡ ይዞ ፡ መቀሌ ፡ እንዳ ፡ ኢየሱስ ፡ ላይ ፡ መሽጎ ፡ ተቀመጠ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ «የተላከ ፡ ከራስ ፡ መኰንን ፡ ይድረስ ፡ ከኮሎኔል ፡ ጁሴፔ ፡ ጋሊያኖ ፡ ይህን ፡ አሁን ፡ መሽገኸ ፡ ያለኸበትን ፡ ስፍራ ፡ ለቀኸ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንድትመለስ ፡ በወዳጅነት ፡ አሳስብኻለሁ ። አለቅም ፡ ያልኸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ የግድ ፡ ጦርነት ፡ አድርገን ፡ የማጆር ፡ ቶዜሊ ፡ ዕድል ፡ እንዳያገኝኸ» ፡ ብለው ፡ ለኮሎኔል ፡ ጁሴፔ ፡ ጋሊያኖ ፡ 2 ፡ ጊዜ ፡ ቢልኩበት ፡ «በንጉሤ ፡ ታዝዤ ፡ የያዝኩትን ፡ አገር ፡ ለመልቀቅ ፡ አልችልም ፡ ጦርነትም ፡ ቢፈልጉ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ መድፍና ፡ መሣሪያ ፡ እንዳለ ፡ ይወቁ ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ላከባቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ወታደራቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየገፉ ፡ መቀሌ ፡ ደረሱ ። ወዲያውም ፡ ምሽጉን ፡ ከበው ፡ ካስጨነቁት ፡ በኋላ ፡ እጅኸን ፡ ብትሰጥ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ላዝማቹ ፡ ቢልኩበት ፡ እጄን ፡ አልሰጥም ፡ ብሎ ፡ ላከ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባ1888 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ እስከ ፡ ምሽጉ ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ ውጊያ ፡ ዠመሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በዠግንነት ፡ ቢዋጉ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ አስቀድመው ፡ ተዘጋጅተው ፡ እምሽግ ፡ ውስጥ ፡ ተደብቀው ፡ ይዋጉ ፡ ነበርና ፡ ጦርነቱ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደ ።




ራስ ፡ መኰንን

በኋላ ፡ ግን ፡ በውጭ ፡ የነበረው ፡ ምንጭ ፡ ስለ ፡ ተያዘበት ፡ ራስ ፡ መኰንንም ፡ በየጊዜው ፡ እየወጉ ፡ ሲያጣድፉት ፡ ወዲያው ፡ እምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ውሃ ፡ ኣልነበረምና ፡ በውድ ፡ እጄን ፡ ልስጥ ፡ አለዚያም ፡ ከነሰዌ ፡ ልልቀቅና ፡ ልረፍ ፡ እያለ ፡ ሲያመነታ ፡ ፒዬትሮ ፡ ፌልተር ፡ የሚባለው ፡ ነጋዴ ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክና ፡ በዋናው ፡ የጦር ፡ ኣዛዥ ፡ በጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ መካከል ፡ ሆኖ ፡ ምሽጉን ፡ እንዲለቅ ፡ ተላላከ ። ኮሎኔል ፡ ጁሴፔ ፡ ጋሊያኖም ፡ ኣስቀድሞ ፡ ቢለምኑት ፡ እንቢ ፡ ያለውን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ስላለቀበትና ፡ ስለ ፡ ተቸገረ ፡ ምሽጉን ፡ ለመልቀቅ ፡ መፍቀዱን ፡ ላከ ። ዐፄ ፡ ምኒልክም ፡ ለቅቄ ፡ እሄዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ከጠየቀ ፡ እናንተም ፡ ሸኙ ፡ ሰጥታችሁ ፡ ስደዱት ፡ እንጂ ፡ አትንኩት ፡ ብለው ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጡ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የጦር ፡ አዛዡ ፡ ከስፍራው ፡ ወጥቶ ፡ ከነጋዴው ፡ ከፒዬትሮ ፡ ፊልተር ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ስላወጣጡ ፡ ከራስ ፡ መኰንንና ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ተነጋግሮ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ በተከበበ ፡ በሁለት ፡ ወሩ ፡ የመቀሌን ፡ ምሽግ ፡ ለቆ ፡ መሣሪያውንና ፡ ሥንቁን ፡ ቍስለኛውን ፡ ሰብስቦ ፡ ተነሣና ፡ ወደ ፡ ዐዲግራት ፡ ሄዶ ፡ ከዋናው ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ ከጀኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ ጋራ ፡ ተደባለቀ ። ዐፄ ፡ ምኒልክም ፡ በግፍ ፡ አገራቸውን ፡ ለመውሰድ ፡ መጥቶ ፡ ጦርነት ፡ የገጠማቸውን ፡ ጠላታቸውን ፡ የያዘውን ፡ መድፍና ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ማርከው ፡ እሱንም ፡ ጦርነቱን ፡ እንደ ፡ ዠመረ ፡ ከነሠራዊቱ ፡ እዚያው ፡ እምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ለመፍጀት ፡ ሲቻላቸው ፡ ሳለ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለጠላታቸው ፡ ሥንቅና ፡ ዕቃውን ፡ የሚጭንበት ፡ አጋሰስ ፡ ሸኘ ፡ ፊታውራሪ ፡ ደሳለኝ ፡ የሚባሉትን ፡ አድርገው ፡ ከዋናው ፡ ጦር ፡ አዛዥ ፡ ከጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ እንዲገናኝ ፡ ማድረጋቸው ፡ የዓለም ፡ ሕግ ፡ ጠባቂ ፡ መሆናቸውን ፡ ያስረዳል ።

ኮሎኔል ፡ ጁሴፔ ፡ ጋሊያኖም ፡ ሄዶ ፡ ከጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ ጋራ ፡ ተገናኝቶ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከቈየ ፡ በኋላ ፡ የዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ በተደረገበት ፡ ቀን ፡ ሲዋጋ ፡ እጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞተ ።



ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዳግማዊ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ


ራስ ፡ መኰንን


ራስ ፡ ሚካኤል


ራስ ፡ ወሌ



በጅሮንድ ፡ ባልቻ




ራስ ፡ መንገሻ ዮሐንስ



ራስ ፡ አሉላ ፡ አባነጋ



ንጉሥ ፡ ኡምቤርቶ



ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡
ፍራንቼስኮ ፡ ክርስፒ



ጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ



ጄኔራል ፡ ጋንዶልፊ




፡፡

ተማራኪው ፡
ጄኔራል ፡ ማቲኦ ፡ አልቤርቶኒ



ጄኔራል ፡ አሪሞንዲ



ጄኔራል ፡ ዳቦርሜዳ



ኮሎኔል ፡ ጁሴፔ ፡ ጋሊያኖም

# ምዕራፍ ፡ 33 ፡፡

## የዐድዋ ፡ ጦርነት ፡፡


ከአምባ ፡ አላጌና ፡ ከመቀሌ ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ የጦር ፡ አዝማቹ ፡ ጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ዕርቅ ፡ ለማድረግ ፡ እንጂ ፡ በጦርነት ፡ በኩል ፡ የማይደፍርበትን ፡ ራፖር ፡ ዘርዝሮ ፡ ለመንግሥቱ ፡ አስተላልፎ ፡ ነበር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ 1ኛው ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ባይሆን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ተዋግታችሁ ፡ ድል ፡ አድርጋችሁ ፡ የተሰበረውን ፡ የኢጣሊያን ፡ የወታደርነት ፡ ስም ፡ ሳታድሱ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ ከሆናችሁ ፡ በኋላ ፡ ዕርቅ ፡ ቢደረግ ፡ ስማችን ፡ የተሰበረ ፡ ሆኖ ፡ ስንደፈር ፡ እንኖራለን ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ላከበት ፡፡

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ ዋና ፡ የጦር ፡ ኣዝማችነቱን ፡ ይዞ ፡ የቀረውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አራት ፡ ላይ ፡ ከፍሎ ፡ ላ1ኛው ፡ ክፍል ፡ ጄኔራል ፡ አሪሞንዲን ፡ ለ2ኛው ፡ ክፍል ፡ ጄኔራል ፡ ዳቦርሜዳን ፡ ለ3ኛው ፡ ክፍል ፡ ጄኔራል ፡ አልቤርቶኒን ፡ ላ4ኛው ፡ ክፍል ፡ ጄኔራል ፡ ኤሌናን ፡ ሾመ ፡፡ ከነዚሁ ፡ የመዠመሪያዎቹ ፡ ሁለቱ ፡ ጄኔራሎች ፡ የየራሳቸውን ፡ የጦር ፡ ጭፍራ ፡ ይዘው ፡ ራአዮ ፡ በሚባለው ፡ ስፍራ ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ ዐድዋን ፡ እንዲይዙ ፡ ያገር ፡ ተወላጅን ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ የሚያዘው ፡ ኢራራ ፡ በሚባለው ፡ ስፍራ ፡ በኩል ፡ አልፎ ፡ እንዲጠባበቅ ፡ አደረገ ፡፡ እነዚህን ፡ ሦስቱን ፡ አሰልፎ ፡ በጄኔራል ፡ ኤሌና ፡ የሚታዘዘውን ፡ አራተኛውን ፡ ክፍል ፡ ግን ፡ እኋላ ፡ ተጠባባቂ ፡ እንዲሆን ፡ አስቀመጠው ፡፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ቍጥር ፡ ከ20 ፡ ሺህ ፡ በላይ ፡ ነው ፡፡ እነዚህም ፡ 60 ፡ መድፍ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ብረትና ፡ ጥይት ፡ ይዘው ፡ ነበር ፡፡

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ በቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ ሲቀድሱ ፡ ቆመው ፡ ያስቀድሱ ፡ ነበርና ፡ ከቅዳሴ ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ የኢትዮጵያን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ኣሰለፉት ፡፡



በዓድዋ ፡ ጦርነት ፡ ተዋጊውን ፡ በማበረታታት ፡ የሚሸሸውን በመገዘት ፡ ያዋጉት ጳጳሱ ፡ ኣቡነ ፡ ማቴዎስ ።



## ራስ ፡ ስብሐት

በጦርነት ፡ ሰዓት ፡ የኢጣሊያኖችን ፡ ጐራ ፡ በስውር ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ወገናቸው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጦር ፡ መጥተው ፡ የተደባለቁት ፡ ራስ ፡ ስብሐት ።

1ኛ. ፡ ራሳቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዐድዋ ፡ አጠገብ ፡ በተለይ ፡ ዐዲማህለያ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ከ30 ፡ ሺህ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ጋራ ።
2ኛ. ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ ከ3 ፡ ሺህ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ጋራ።
3ኛ. ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በስተቀኝ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ የአሰምን ፡ ወንዝ ፡ ሻገር ፡ ብለው ፡ በማይ ፡ ጓጓሕ ፡ ከ6 ፡ ሺህ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ጋራ ።
4ኛ. ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ ከ3 ፡ ሺህ ፡ የጦር ፡ ወታዶር ፡ ጋራ።
5ኛ. ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በስተግራ ፡ ራስ ፡ ወሌ ፡ በማይ ፡ ደላዕታ ፡ ከ3 ሺህ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ጋራ።
6ኛ. ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ በሠናይ ፡ ጸባኦና ፡ በእንዳ ፡ ሚካኤል ፡ ከ8 ፡ ሺህ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ጋራ ።
7ኛ. ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ አቅጣጫቸውን ፡ ደአሮ ፡ ተክሌ ፡ በር ፡ አድርገው ፡ በአዲ ፡ ኣቡን ፡ ከ8 ፡ ሺሕ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ጋራ ።
8ኛ. ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ዮሐንስ ፡ ከራስ ፡ አሉላና ፡ ከራስ ፡ ሐጐስ ፡ ጋራ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ሸዋቶ ፡ ከ3 ፡ ሺህ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ጋራ ።
9ኛ. ፡ ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጓንጉል ፡ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ ከ6 ፡ ሺህ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ጋራ ።
10ኛ. ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ አቲከም ፡ ከ3 ፡ ሺሕ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ ድምር ፡ 73 ፡ ሺህ ፡ የጦር ፡ ወታደር ።

በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በጥር ፡ ወር ፡ በኢጣሊያ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ ራስ ፡ ስብሐትና ፡ ደጃች ፡ ሐጐስ ፡ ተፈሪ ፡ ካገራችን ፡ ጠላት ፡ ጋራ ፡ ሆነን ፡ አገራችንን ፡ ኣንወጋም ፡ ብለው ፡ ከነባንዳቸው ፡ መጥተው ፡ ከንጉሣቸው ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተደባለቁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኃይል ፡ ለኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ እየተጫነው ፡ ሄደ ።

ከነዚህም ፡ በቀር ፡ ጦርና ፡ ጋሻ ፡ ብቻ ፡ የያዘ ፡ ጀሌ ፡ ተከታይ ፡ ብዙ ፡ ነበር ። ከጦር ፡ አለቆችም ፡ ደጃች ፡ ወልዴ ፥ ደጃች ፡ በሻኽ ፡ አቦዬ ፥ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ አባተ ፥ ደጃች ፡ ውቤ ፥ ደጃች ፡ ተሰማ ፥ ቢትወደድ ፡ አጥናፌ ፥ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ነሲቡ ፥ ደጃች ፡ ገሠሠ ፥ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ኣድነው ፥ በጅሮንድ ፡ ከተማ ፥ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፥ ደጃች ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፥ ቱርክ ፡ ባሻ ፡ ታምሬ ፥ ኣዛዥ ፡ ዛማኔል ፥ ኢጋፋሪ ፡ (ቢትወደድ) ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልና ፡ ሌሎችም ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩ ። ለመዠመሪያው ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ወታደር ፡ በዠግንነት ፡ ስማቸው ፡ የተጠራውን ፡ ጠቅላይ ፡ የጦር ፡ ኣዛዥ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገበየሁን ፡ ኣድርገው ፡ 1888 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በየካቲት ፡ 23 ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ጦርነት ፡ ተዠመረ ። ወዲያው ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ ያገር ፡ ተወላጅን ፡ ጦር ፡ እፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ሲዋጋ ፡ በኋላ ፡ የራስ ፡ መንገሻና ፡ የራስ ፡

ሚካኤል ፡ የዋግ ፡ ሥዩም ፡ ጓንጉል ፡ ወታደሮች ፡ ከበው ፡ በጥይት ፡ ስለ ፡ ቈሏቸው ፡ ይበልጦቹ ፡ እጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞቱ ። ገሚሶቹ ፡ ዐውቀው ፡ እጃቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ወዳልተነካው ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ጄኔራል ፡ አርሞንዲ ፡ ሠራዊት ፡ በሽሽት ፡ እየሄዱ ፡ ተደባለቁ ።

የኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊትም ፡ እያቅራራና ፡ እየፎከረ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ አልፎ ፡ ጕሰሶ ፡ ከሚባለው ፡ ጕብታ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተጋጠማቸው። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባንደኛው ፡ ወገን ፡ ለመሸሽ ፡ የማይመች ፡ ገደል ፡ ሆኖ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ተከበቡ ፡ የሚሄዱበት ፡ ኣጥተው ፡ ተስፋ ፡ በቈረጡ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ውጊያ ፡ ተዠምሮ ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ሲዋጉ ፡ ከሞተው ፡ ወታደር ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ያ ፡ ስፍራ ፡ የሬሳ ፡ ክምር ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ይታይ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠግናው ፡ ፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ ከሠራዊታቸው ፡ ተለይተው ፡ እጠላት ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ ከቀኛዝማች ፡ ታፈሰ ፡ ጋራ ፡ እየፎከሩ ፡ የጠላትን ፡ አንገት ፡ በጐራዴ ፡ ሲቈርጡ ፡ በጥይት ፡ ተመተው ፡ ወደቁ።

የጦር ፡ አበጋዙ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ የዐድዋ ፡ ዕለት ፡ በሠሩት ፡ የዠግንነት ፡ ሥራ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በያለበት ፡ ስማቸው ፡ ይነገራል ። ይልቁንም ፡ ጠላት ፡ የዐድዋን ፡ ታሪክ ፡ በጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ጕብዝናቸውን ፡ ስለማይሰውር ፡ የወገኖቻቸውን ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ልብ ፡ በኩራት ፡ ይመላል ።

ስለ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ከመሞታቸው ፡ በፊት ፡ ተገጠመ ።
የዐድዋ ፡ ሥላሴን ፡ ጠላት ፡ አረከሰው ፡
ገበየሁ ፡ በሞቴ ፡ ግባና ፡ ቀድሰው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ የጦር ፡ ወታደራቸውን ፡ በሚያበረታታ ፡ ቃል ፡ ሲያደፋፍሩ ፡ እንዲሁም ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ እንደ ፡ ወንድ ፡ በጦርነቱ ፡ መካከል ፡ እየተላለፉ ፡ የቈሰለውን ፡ ሲያስነሡ ፡ ለተጠማው ፡ መጠጥ ፡ ለተራበው ፡ ምግብ ፡ ሲያሰጡ ፡ ዋሉ ። እነሊቀ ፡ መኳስ ፡ ኣባተ ፡ እነ ፡ ራስ ፡ አሉላ ፡ እነ ፡ በጅሮንድ ፡ ባልቻ ፡ እነደጃች ፡ በሻኽ ፡ አቦዬና ፡ የቀሩትም ፡ የጥንት ፡ ወታደሮች ፡ በመድፍና ፡ በጠመንዣ ፡ በዠግንነት ፡ ሲዋጉ ፡ የጠመንዣውና ፡ የመድፉ ፡ ጩኸት ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ነበር ።

የአጣሊያንንም ፡ ወታደር ፡ ከበው ፡ እየተፏከሩ ፡ በጥይትና ፡ በጐራዴ ፡ ሲደበድቡት ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ በዠግንነት ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ከተዋጋ ፡ በኋላ ፡ ሽሽት ፡ ዠመረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኢትየጵያውን ፡ እየተከታተሉ ፡ ሲወጉት ፡ ኣዝማቹ ፡ ጄኔራል ፡ አልቤርቶኒ ፡ ተቀምጦበት ፡ የነበረው ፡ በቅሎ ፡ ተመቶ ፡ ወደቀ ። ወዲያው ፡ ተነሥቼ ፡ ኣመልጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ለመነሣት ፡ ሲጥር ፡ ከቅምጡ ፡ ሳይነሣ ፡ እየተሽቀዳደሙ ፡ የሚሮጡት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ደርሰው ፡ ጄኔራሉን ፡ ማረኩት ።

ያ1ኛው ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ አዛዡ ፡ ተማርኮ ፡ ሠራዊቱ ፡ በጭራሽ ፡ ከጠፉ ፡ በኋላ ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ራአዮ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ካራት ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ የሦስተኛውን ፡ ክፍል ፡ የጄኔራል ፡ ኤሌናን ፡ ጦር ፡ ጨምሮ ፡ ተዋግቶ ፡ በመጨረሻ ፡ የጦር ፡ አዛዡ ፡ ጄኔሪል ፡ አሪሞንዲ ፡ እዚያው ፡ ጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞቶ ፡ ተገኘ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ያለው ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ በተለይ ፡ ማርያም ፡ ሸዊቶ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተጋጥሞ ፡ ከቀድሞው ፡ የበለጠ ፡ ጦርነት ፡ ተደረገ ። ይልቁንም ፡ የመጨረሻው ፡ ድል ፡ የሚፈጸምበት ፡ ለመሆኑ ፡ የሁለቱም ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ተደባልቆ ፡ በጨበጣ ፡ በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ በጨበጣ ፡ በሚደረገው ፡ ዘመቻ ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ይልቅ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በጐራዴ ፡ አሰነዛዘር ፡ የቀለጠፉ ፡ ነበሩ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ አጣሊያኖች ፡ ተስፋ ፡ በቈረጠ ፡ ኃይል ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ በጕብዝና ፡ ሲዋጉ ፡ በመጨረሻ ፡ አዛዣቸው ፡ ጄኔራል ፡ ዳቦርሜዳ ፡ በጥይት ፡ ደረቱን ፡ ተመቶ ፡ ወድቆ ፡ ባንዲት ፡ ጠብታ ፡ ውሃ ፡ ማነው ፡ አፌን ፡ የሚያርሰኝ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ ተኰነነው ፡ ነዌ ፡ ሲጮኸ ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቈየ ፡ ሞተ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ገሚሶቹ ፡ ሲሞቱ ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ደግነው ፡ ይተኩሱበት ፡ የነበረውን ፡ ብረት ፡ ኣፈሙዙን ፡ ጨብጠው ፡ ሰደፉን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እየሰቀሉ ፡ ተማረኩ ። ድሉም ፡ በማያወላውል ፡ እኳኋን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሆኖ ፡ ጦርነቱ ፡ ባ1888 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በዚሁ ፡ በየካቲት ፡ 23 ፡ ቀን ፡ ተፈጸመ ። በጦርነቱ ፡ ውስጥ ፡ 5 ፡ ሺህ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ 2 ፡ ሺህ ፡ የሐማሴን ፥ የከረን ፡ ሌሎችም ፡ ከያለበት ፡ እየተጠራቀሙ ፡ ለኢጣሊያ ፡ ተቀጥረው ፡ የነበሩ ፡ ሞቱ። 2 ፡ ሺህ ፡ 400 ፡ የሚሆኑ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ስልሳ ፡ መድፍና ፡ ብዙ ፡ ጠመንዣ ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ተማረኩ ። ቍስለኛውም ፡ እስከ ፡ 2 ፡ ሺህ ፡ 500 ፡ ይደርሳል ፡ ይባላል ።

ከኢትዮጵያ ፡ ወገን ፡ የሞተው ፡ ግን ፡ ግማሾቹ ፡ በዚሁ ፡ በኢጣሊያኖች ፡ ልክ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ አንዳንዶች ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊዎች ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ ተኝቶ ፡ መተኰስን ፡ ከነውር ፡ እየቈጠረ ፡ ቆሞ ፡ ሲዋጋ ፡ ለጠላት ፡ በመመቸቱ ፡ የሞተውና ፡ የቈሰለው ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ይበልጣል ፡ ወይም ፡ ዕጥፍ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ጽፈዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሞተውም ፡ የቈሰለውም ፡ እስከ ፡ 10 ፡ ሺህ ፡ ይደርሳል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ከሞትና ፡ ከምርኮ ፡ የተረፈው ፡ የኢጣሊያ ፡ ወታደር ፡ ከዐድዋ ፡ ወደ ፡ ዐዲ ፡ ቀይሕ ፡ ተዘበራርቆ ፡ ሲሸሽ ፡ እሸሸት ፡ ላይ ፡ ጄኔራል ፡ ኤሌና ፡ ቈሰለ ። የኢትዮጵያ ፡ ወታደርም ፡ ጠላቱን ፡ መረብን ፡ ኣሳልፎ ፡ ካባረረ ፡ በኋላ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይህነን ፡ ድል ፡ ለሰጣቸው ፡ ኣምላክ ፡ ምስጋና ፡ አቀረቡ ። ወዲያው ፡ ስለ ፡ ምርኮኞቹ ፡ ፍርድ ፡ ተዠመረ ። ቀጥሎም ፡ በዘመቻው ፡ ለተማረኩት ፡ ኢጣሊያኖችና ፡ ዐረቦች ፡ ይቅርታ ፡ አድርገው ፡ መብልና

፡ መጠጥ ፡ አዘው ፡ እናታቸውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ የወጉትን ፡ የኤርትራን ፡ ወታደሮች ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ጳጳሱን ፡ አበነ ፡ ማቴዎስን ፡ ጭምር ፡ አስፈርደው ፡ እግርና ፡ እጃቸውን ፡ እየቈረጡ ፡ ቀጧቸው ።

በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ኣቶ ፡ አውዐሎም ፡ የሚባሉ ፡ የእንቲጮ ፡ ተወላጅ ፡ በስለላ ፡ ሥራ ፡ ኣገራቸውን ፡ በጣም ፡ አገልግለዋል ።

በዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ በመላው ፡ ኣውሮፓና ፡ በኢጣሊያ ፡ አገር ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤና ፡ መገረምን ፡ አፈራ ። ወዲያው ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ግፉ ፡ እያለ ፡ ድል ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ ይልክ ፡ የነበረውን ፡ ፍራንቼስኮ ፡ ክርስፒን ፡ ወደ ፡ ኢትየጵያ ፡ ለጦርነት ፡ የመጡ ፡ የሹማምንቶቹም ፡ የወታደሮቸም ፡ ቤተሰቦች ፡ ይረግሙት ፡ ዠመር ። ወጣቶቹም ፡ ሆ ፡ እያሉ ፡ እየጮኹ ፡ ያለበትን ፡ ቤት ፡ በድንጋይ ፡ እየደበደቡ ፡ ኣስቸገሩት ። ስለዚህ ፡ ራሱ ፡ «የዚህን ፡ ድል ፡ የሆነውን ፡ የወታደርዎን ፡ ደም ፡ ጊዜ ፡ ፈልገው ፡ ይበቀሉለት ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ይኸው ፡ ከሹመቴ ፡ ተሰናብቻለሁ» ፡ ብሎ ፡ ለንጉሡ ፡ ኣስታውቆ ፡ ሽሙቱን ፡ ለቀቀ ።

ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ወጣቶችና ፡ ሠራተኞች ፡ ሞልሚንቲ ፡ በሚባል ፡ ዴፑቲ ፡ (ኣማካሪ) ፡ እየተመሩ ፡ በ600ና ፡ በ700 ፡ እየተከፈሉ ፡ በከተማው ፡ ሆ ፡ እያሉ ፡ እየጮኹ ፡ ይዞሩ ፡ ዠመር ። (ዴሞንስትራሲዮን ፡ አደረጉ) ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከተማው ፡ ተሸብሮ ፡ ነጋዴው ፡ ሁሉ ፡ ሱቁኑን ፡ እየዘጋ ፡ ይደበቅ ፡ ዠመር. ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወጣቶቹ፤ ፡ ፕሪንችፔ ፡ ኦዲስካልኪ ፡ የሚባለውን ፡ መስፍን ፡ በትሪቶኒ ፡ መንገድ ፡ ሲያልፍ ፡ አግኝተው ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ጭቃ ፡ እየረጩ ፡ ከበቡት ። ወዲያውም ፡ «ምኒልክ ፡ ሕያው ፡ ይሁን» ፡ በል ፡ ብለው ፡ አስፈራሩት ። እርሱ ፡ ኢጣሊያዊ ፡ ሆኜ ፡ ኢጣሊያ ፡ ሕያው ፡ ትሁን ፡ እላለሁ ፡ እንጂ ፡ ምኒልክ ፡ ሕያው ፡ ይሁን ፡ አልልም ፡ እያለ ፡ ሲጨቃጨቅ ፡ በመካከሉ ፡ ካራቢኔዬሪዎች ፡ ደርሰው ፡ በግድ ፡ ስላስለቀቀኍት ፡ በጋሪ ፡ ተቀምጦ ፡ አመለጠ «ምኒልክ ፡ ሕያው ፡ ይሁን ፡ » በል ፡ እያሉ ፡ ያስገደዱበት ፡ ምክንያት ። የጦርነቱን ፡ አዠማመር ፡ ከሥር ፡ ዠምረው ፡ ይከታተሉ ፡ የነበሩ ፡ የሶሲያሊስት ፡ ወገኖች ፡ የኢጣልያን ፡ አጥቂነት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ተከላካይነት ፡ የዓፄ ፡ ምኒልክን ፡ ዕርቅና ፡ ሰላም ፡ ፈላጊነት ፡ የኢጣልያን ፡ ተጋፊነት ፡ በሰፊው ፡ ተረድተው ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ላይ ፡ በዓላጌ ፡ የሞቱትን ፡ የኢጣልያ ፡ ሹማምንቶች ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደተቀበሩ ፡ ምርኮኞቹ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ እንደተቀመጡ ፡ ይልቁኑንም ፡ በመቀሌ ፡ ምሽግ ፡ ተከቦ ፡ ሁሉም ፡ ያላንድ ፡ ተስፋ ፡ በውሃ ፡ ጥም ፡ ሊያልቅ ፡ የነበረውን ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ሰጥተው ፡ በሰላም ፡ ማሰናበታቸው ፡ ተሰምቶ ፡ የደግነትና ፡ የሰላም ፡ ፈላጊነታቸው ፡ ታውቆ ፡ ስለነበረ ፡ ነው ። ወጣቶቹንም ፡ የሚመራው ፡ ዴፑቴ (የምክር ፡ ቤት ፡ አማካሪ) ፡ ጦርነትና ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ከማይፈልጉት ፡ ከሶሺያሊስት ፡ ወገን

፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የራሳቸውን ፡ የጦርና ፡ የፖለቲካ ፡ መሪዎች ፡ በመጥላትና ፡ በመበሳጨት ፡ እነዚያንም ፡ ይበልጥ ፡ ለማናደድ ፡ «ምኒልክ ፡ ሕያው ፡ ይሁን» ፡ እያሉ ፡ ጮኸዋል ፡ ማለት ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ የዚህ ፡ የጦርነት ፡ ወሬ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሲሰማ ፡ መገረምን ፡ በፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ ግን ፡ ደስታን ፡ አፈራ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንግሊዞች ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ኢጣልያንን ፡ ይደግፉ ፡ ነበር ። የዓድዋ ፡ ጦርነትም ፡ ሊዠመር ፡ አቅራቢያ ፡ የኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ለመውጋት ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በዘይላ ፡ በር ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ሐረርና ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሊመጣ ፡ አስቦ ፡ ይኸንኑም ፡ ኣሳብ ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ተነጋግሮ ፡ እንግሊዝም ፡ በዘይላ ፡ ለማሳለፍ ፡ ፈቅዶለት ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ይኸንንም ፡ ሁሉ ፡ እንግሊዝ ፡ የሚያደርገው ፡ በእውነቱ ፡ ሲመረመር ፡ ጨርሶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ጥላቻ ፡ ሳይሆን ፡ የከብርና ፡ የሥልጣን ፡ የኃይልና ፡ የግዛት ፡ ተፎካካሪውን ፡ ለማድከምና ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ፈረንሳዊን ፡ ይቃወምልኛል ፡ ብሎ ፡ የገመተውን ፡ ኢጣልያንን ፡ ለመደገፍ ፡ ያደረገው ፡ ነው። ስለዚህ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ በኢጣልያ ፡ ተሸናፊነት ፡ በጣም ፡ ኀዘን ፡ ባይሰማውም ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ አይመስልም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሌለው ፡ መሣሪያ ፡ በግዥ ፡ እንጂ ፡ ራሱ ፡ መሥራት ፡ የማይችለው ፡ ትንሹ ፡ የአፍሪካ ፡ መንግሥት የውስጥ አንድነቱን ኣጠንክሮ መሳፍንቱና ፡ መኳንንቱ ፡ በንጉሠ ነገሥቱ ፡ መሪነት ፡ አብሮ ፡ የሠለጠነውን ፡ የኢጣልያን ፡ መንግሥት ፡ ማሸነፉ ፡ ሳይገርመው ፡ አልቀረም ። የዛሬውን ፡ የኢጣልያንን ፡ ጦርነትና ፡ ድል ፡ መሆን ፡ ራሱ ፡ ከ28 ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ባፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ላይ ፡ በቀላል ፡ ያገኘውን ፡ ድል ፡ ሲያመዛዝነው ፡ ሁኔታው ፡ ሁሉ ፡ ይራራቅበታል ።

የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ በደስታ ፡ ነው ፡ የተቀበለው ፡ የጦርነቱን ፡ ሁኔታ ፡ ግራዝማች ፡ ዮሴፍ ፡ ለሙሴ ፡ ሞንዶን ፡ ቪዳዬ ፡ ሲያሳልፉ ሙሴ ፡ ሞንዶን ፡ ደግሞ ፡ የጦርነቱን ፡ ሁኔታ ፡ የራሱንም ፡ ሐተታ ፡ እየጨመረ ፡ በፈረንሳዊ ፡ ጋዜጣ ፡ ያጽፍ ፡ ነበር ። በዚያም ፡ ሕዝቡም ፡ መኳንንቱም ፡ ሚኒስትሮቹም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ተከላካይነት ፡ የኢጣልያንን ፡ አጥቂነት ፡ ተገንዝበው ፡ በወሬም ፡ በኣሳብም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ይረዱ ፡ ነበር ። የአድዋ ፡ ድል ፡ በተሰማበት ፡ ወር ፡ ሔንሪ ፡ ዶ ኦርሊንስ ፡ ዱክ ፡ ዴ ፡ ቫሎይስ ፡ (Henri

d'Orleans duc de valois) የሚባለው ፡ የፈረንሳይ ፡ መስፍን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወታደር ፡ እያመሰገነ ፡ የኢጣልያንን ፡ ወታደር ፡ በመንቀፍ ፡ በግብዣ ፡ ላይ ፡ ስለተናገረ ፡ የኢጣልያው ፡ መስፍን ፡ (Compte de turin (Torino) የሚባለው ፡ በዚሁ ፡ ተናዶ ፡ የፈረንሳዊውን ፡ መስፍን ፡ እንደዘመኑ ፡ ልማድ ፡ የሻሞላ ፡ ውጊያ ፡ ጠይቆት ፡ በዚሁ ፡ ሁለቱ ፡ ሲዋጉ ፡ የፈረንሳዊው ፡ መስፍን ፡ ቆሰለ ። ስለዚህ ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ የፈረንሳይ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡

የኢትዮጵያን ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ በደስታ ፡ ተቀብሎታል ። አዲስ ፡ አበባ ፡ ያሉት ፡ ፈረንሳዮችም ፡ ደስታቸው ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ይልቁኑንም ፡ የዓድዋ ፡ ጦርነት ፡ ዕለት ፡ ካፒቴን ፡ ክሎሼት ፡ የሚባለው ፡ የፈረንሳይ ፡ ተወላጅ ፡ በመድፈኛ ፡ ክፍል ፡ ሆኖ ፡ ራሱ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መካከል ፡ ሆኖ ፡ በጀግንነት ፡ ሲዋጋ ፡ ውሏል ።

ወደ ፡ ኢጣልያ ፡ አገር ፡ እንመለስ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሹመቱን ፡ በለቀቀው ፡ በክርስፒ ፡ እግር ፡ ዴ ፡ ሩዲኒ ፡ የሚባለው ፡ ተሾሞ ፡ ስለ ፡ ዐድዋ ፡ ድል ፡ እንዲመከር ፡ በምክር ፡ ቤቱ ፡ ስብሰባ ፡ ተደረገ ።

ገሚሱም ፡ የተረፈውን ፡ ወታደርም ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ልከን ፡ እንዋጋለን ፡ ሲል ፡ የቀረው ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ መዠመሪያ ፡ አላጌ ፡ 2ኛ ፡ መቀሌ ፡ 3ኛው ፡ 20 ፡ ሺህ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ዐድዋ ፡ ላይ ፡ አልቆብን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ቀጥለን ፡ ስንልክ ፡ ድል ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቅኝ ፡ አገርም ፡ አጥተን ፡ ኢጣሊያም ፡ በወታደር ፡ በጣም ፡ ትደኸያለች ፡ ስለዚህ ፡ በተቻለ ፡ ከንጉሡ ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ ዕርቅ ፡ አድርጎ ፡ አሥመራን ፡ ይዞ ፡ ከመቀመጥ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሚሻል ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ።

የነዚህም ፡ አሳብ ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ መላው ፡ የምክር ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ ተቀሰለው ፡ ጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ ድል ፡ በሆነ ፡ በዚያው ፡ ሰሞን ፡ ጄኔራል ፡ ባልዲሰራ ፡ አሥመራን ፡ ብቻ ፡ እንዲከላከል ፡ 15 ፡ ሺሕ ፡ የሚሆን ፡ ጦር ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ተሳፍሮ ፡ ምጥዋ ፡ ደረሰ ። ጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ ግን ፡ አሥመራ ፡ ላይ ፡ በወታደር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ተፈርዶበት ፡ ከሹመቱና ፡ ከማዕርጉ ፡ ተሻረ ።

ጄኔራል ፡ ባልዲሰራ ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ማጆር ፡ ሳልሳ ፡ የሚባልውን ፡ ዕርቅ ፡ እንዲያደርግና ፡ ወሰኑንም ፡ እንዲካለል ፡ ስለ ፡ ተማረኩትም ፡ ኢጣሊያኖች ፡ እንዲነጋገር ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ላከው ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ውሉ ፡ ሳይፈጸም ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ 12 ፡ ቀን ፡ ያኸል ፡ ቈይተው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተመለሱ ። አዲስ ፡ አበባም ፡ በታላቅ ፡ የድል ፡ አድራጊነት ፡ ግርማ ፡ ታጅበው ፡ በሚያዝያ ፡ 10 ፡ ቀን ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ በደስታና ፡ በእልልታ ፡ ተቀበላቸው ፡ ወዲያውም ፡ ግዳይ ፡ ሲጣልና ፡ ሲፎከር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተገጠመ ።

ምኒልክ ፡ ተወልዶ ፡ ባያነሣ ፡ ጋሻ ፡
ግብሩ ፡ እንቍላል ፡ ነበር ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ አበሻ ።

በሠራው ፡ ወጨፎ ፡ ባመጣው ፡ እርሳስ ፡
ተፈጠመ ፡ ጣሊያን ፡ አበሻ ፡ እንዳይደርስ ።

ምኒልክ ፡ ተጕዞ ፡ የምትጠይቀኝ ፡
ፊትም ፡ ኣላለፈ ፡ ኋላም ፡ አይገኝ ።

አባተ ፡ በመድፉ ፡ አምሳውን ፡ ሲገድል ፡
ባልቻ ፡ በመትረየስ ፡ ነጥሎ ፡ ሲጥል ፡
የጐጃሙ ፡ ንጉሥ ፡ ግፉ ፡ በለው ፡ ሲል ።

እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ እቴጌ ፡ ብርሃን ፡
ዳዊቷን ፡ ዘርግታ ፡ ስምዐኒ ፡ ስትል ።

ተማራኪው ፡ ባዙቅ ፡ ውሃ ፡ ውሃ ፡ ሲል ፡
ዳኛው ፡ ስጠው ፡ አለ ፡ ሠላሳ ፡ በርሜል ።

እንደ ፡ በላዔ ፡ ሰብእ ፡ እንደመቤታችን ፡
ሲቻለው ፡ ይምራል ፡ የኛማ ፡ ጌታችን ።

መድፉን ፡ መትረየሱን ፡ ባድዋ ፡ መሬት ፡ ዘርቶ ፡
እንክርዳዱን ፡ ነቅሎ ፡ ስንዴውን ፡ ለይቶ ፡
የተዘራውን ፡ ውል ፡ አጭዶና ፡ ወቅቶ ፡
ላንቶኔሊ ፡ አሳየው ፡ ፍሬውን ፡ አምርቶ ።

እንፋቀር ፡ ብሎ ፡ ለምኖ ፡ መሬት ፡
ንግድ ፡ ሊያስፋበት ፡ ሲዘራ ፡ ኣታክልት ፡
እያመጣ ፡ ሊሰጥ ፡ ግብሩን ፡ ለመንግሥት ፡
ለጓዙ ፡ ማረፊያ ፡ አገር ፡ ቢሰጡት ፡
ተጠማኝ ፡ ሰንብቶ ፡ ሆኖ ፡ ባለርስት ፡
ወሰን ፡ እየገፋ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡
እውነት ፡ ርስት ፡ ሆነው ፡ ተቀበረበት ።

ባሕር ፡ ዘሎ ፡ መምጣት ፡ ለማንም ፡ አትበጅ ፡
እንደ ፡ ተልባ ፡ ሥፍር ፡ ትከዳለች ፡ እንጅ ፡
አትረጋምና ፡ ያለ ፡ ተወላጅ ።

የዳኛው ፡ አሽከሮች ፡ እየተባባሉ ፡
ብልት ፡ መቆራረጥ ፡ አንድነት ፡ ያውቃሉ ፡
አድዋ ፡ ከከተማው ፡ ሥጋ ፡ ቆርጠው፡ ጣሉ ።

የእስክንድር ፡ ፈረስ ፡ መቸ ፡ ተወሰደ ፡

የምኒልክ ፡ ፈረስ ፡ በክንፎቹ ፡ ሄደ ፡
ደንገላሳ ፡ ሲል ፡ እየተጓደደ ፡
የሮማውን ፡ ኵራት ፡ በእግሩ ፡ አሰገደ ።

ኣገርህን ፡ ምኒልክ ፡ እንዳሁን ፡ ፈትሻት ፡
ባያይህ ፡ ነውና ፡ ጠላትህ ፡ የሚሻት ፡

እጇን ፡ ቀምሼ ፡ አላውቅ ፡ እያለ ፡ ሲያማህ ፡
ቀመሰና ፡ እጅህን ፡ መጥቶ ፡ ጠላትህ ፡
ሮም ፡ ላይ ፡ ተሰማ ፡ ለጋስ ፡ መሆንህ ።

በዚሁ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ አባተ ፡ በያዙት ፡ መድፍ ፡ አነጣጥረው ፡ የኢጣሊያኖችን ፡ መድፍ ፡ ባፉ ፡ አግብተው ፡ ሰባብረውት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ስለርሳቸውና ፡ ስለ ፡ በጅሮንድ ፡ ባልቻ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተገጠመላቸው ።

አባተ ፡ ኣባ ፡ ይትረፍ ፡ ነገረኛ ፡ አዋሻኪ ፡ ሰው ፡
ይህን ፡ መድፍ ፡ ከዚያ ፡ መድፍ ፡ አቈራረጠው ።

አበሻ ፡ ጕድ ፡ አለ ፡ ጣሊያን ፡ ወተወተ ፡
ዐይነ ፡ ጥሩ ፡ ተኳሽ ፡ በዋለው ፡ (ቧያለው) ፡ አባተ ።

ገበየሁ ፡ ቢሞት ፡ ተተካ ፡ ባልቻ ፡
መድፍ ፡ አገላባጭ ፡ ብቻ ፡ ለብቻ

በዐድዋ ፡ ዘመቻ ፡ የሞቱት ፡ ታላላቆቹና ፡ ለጊዜው ፡ ስማቸው ፡ የታወቀው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ።

ደጃች ፡ በሻኽ ፡ አቦዬ ፡
ደጃች ፡ ማናየ ፡
ደጃች ፡ ጫጫ ፡
ፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡
ፊታውራሪ ፡ ተክሌ ፡
ፊታውራሪ ፡ ዳምጠው ፡ ከተማ ፡
ፊታውራሪ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ቢራቱ ፡
ቀኛዝማች ፡ ታፈሠ ፡ ኣባይነኽ ፡
ቀኛዝማች ፡ አባይነኽ ፡

ፊታውራሪ ፡ ሽንኰሩ ፡ (የደጃች ፡ በሻህ)
ቀኛዝማች ፡ ተሰማ ፡ ወልዴ ፡
ቀኛዝማች ፡ በሻህ ፡ (የራስ ፡ መኰንን) ፡
ባላምባራስ ፡ በለው ፡
ባላምባራስ ፡ ሰይፉ ፡
ባላምባራስ ፡ አደራ ፡
አቶ ፡ ሙላቱ ፡ የፈረስ ፡ ዘበኛ።

# ምዕራፍ ፡ 34

## ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ መረብን ፡ አልፈው ፡ አሥመራን ፡ ያሊያዘቡበት ፡ ምክንያት ፡ የሮማው ፡ ጳጳስ ፡ ስለ ፡ ኢጣሊያ ፡ ምርኮኞች ፡ የጻፉት ፡ ደብዳቤ ፡ ስለ ፡ ዕርቅና ፡ ስለ ፡ ወሰን ፡ ክለላ ፡ የተደረገ ፡ ውል ። ስለ ፡ ምርኮኞቸ ፡ መለቀቅ ።

ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በፊት ፡ ወዳጅ ፡ መስሎ ፡ በኋላ ፡ ጠላት ፡ ሆኖ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የነፃነት ፡ ልብስ ፡ ለመግፈፍ ፡ የመጣባቸውን ፡ ጠላታቸውን ፡ መዠመሪያ ፡ አምባላጌ ፡ ቀጥሎ ፡ መቀሌ ፡ ላይ ፡ በመጨረሻም ፡ ስሙ ፡ ጠላትን ፡ ሚያሳፍረው ፡ ኢትዮጵያን ፡ እሚያኰራው ፡ ዐድዋ ፡ ላይ ፡ በታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ድል ፡ ኣድርገው ፡ መረብን ፡ አሻግረው ፡ ተመለሱ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይህንኑ ፡ ጠላታቸውን ፡ ከአሥመራ ፡ አስወጥቶ ፡ ባሕርን ፡ አሻግሮ ፡ ማባረር ፡ ባሳባቸው ፡ ውስጥ ፡ ሳይመጣባቸው ፡ አልቀረም ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ አቅንተው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጠቀለሉትና ፡ ጥንትም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ይገዛ ፡ የነበረው ፡ የያገሩ ፡ ነገድ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፡ ለመለየት ፡ የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከውጭ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ በጦርነት ፡ መዳከም ፡ ይረባው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ የአውሳ ፡ ባላባት ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ታዛዥ ፡ ሆኖ ፡ እየገበረ ፡ የኖረውን ፡ የዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ በኢጣሊያ ፡ ስብከት ፡ ተታሎ ፡ ሸፈተ ። እርሱንም ፡ ለመውጋት ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ደጃች ፡ ተሰማ ፡ ናደው ፡ ባዛዥ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ አበጋዝነት ፡ ሄደው ፡ ነበር ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ዐድዋ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ቢሆን ፡ እስኪ ፡ ምጥዋ ፡ ድረስ ፡ አባረው ፡ ካሥመራ ፡ ሊያስወጡኝ ፡ የፈለጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደግሞ ፡ 1 ፡ ጊዜ ፡ ሳልዋጋ ፡ አሥመራን ፡ አለቅም ፡ በማለት ፡ ለዚሁ ፡ በዐድዋ ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላይ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ ከነበረው ፡ ከጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ ይበልጥ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሆነውን ፡ ጄኔራል ፡ ባልዲሰራን ፡ ካ15 ፡ ሺሕ ፡ የጦር ፡ ወደር ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ላከው ፡ ርግጥ ፡ ነበር ።



ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ



ደጃች ፡ ተሰማ ፡ ናደው



አዛዥ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ

እውነት ፡ ነው ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ መረብን ፡ አልፈው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከጄኔራል ፡ ባልዲሰራ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ ከአሥመራና ፡ ከምጥዋ ፡ በጭራሽ ፡ አጥፍተውት ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ባ1928 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በጦርነት ፡ ለማጥቃትና ፡ የዐድዋ ፡ ብድሬን ፡ መለስሁ ፡ ብሎ ፡ ለመፎከር ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ከምቹ ፡ ሥፍራ ፡ ጋራ ፡ ባላጋጠመው ፡ ነበር ። ከከባድ ፡ ቀንበር ፡ በታች ፡ የተገዙትም ፡ ኤርትራውያን ፡ ለባዕድ ፡ ተላለፍን ፡ በማለት ፡ እየተበሳጩ ፡ ከወንዶሞቻቸው ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ ጋራ ፡ ደም ፡ ባልተፋሰሱም ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ አሥመራ ፡ ውስጥ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ከመጣው ፡ አዲስ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ቢዋጉ ፡ ድል ፡ ያደርጉ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አሁንስ ፡ ያን ፡ ጊዜስ ፡ በርግጥ ፡ የሚያውቀው ፡ ማን ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ምክንያትና ፡ ደግሞ ፡ የዛሬ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ ሊያውቀው ፡ የማይችለውን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ባሳባቸው ፡ ውስጥ ፡ የነበረባቸውን ፡ ችግር ፡ አመዛዝነው ፡ ይኸንኑ ፡ ድል ፡ ለሰጣቸው ፡ አምላክ ፡ ምስጋና ፡ አቅርበው ፡ በድል ፡ ኣድራጊነት ፡ እንዳማረባቸው ፡ ምርኮኞቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተመለሱ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የሮማው ፡ ጳጳስ ፡ 13ኛ ፡ ልዮን ፡ በኢጣሊያ ፡ አገር ፡ ያሉት ፡ የምርኮኞቹ ፡ ቤተሰቦች ፡ እያለቀሱ ፡ ስላስቸገሯቸውና ፡ ለራሳቸውም ፡ ወገኖቻቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ምርኮኞቹ ፡ በነፃ ፡ እንዲለቀቁ ፡ ሲሉ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትንና ፡ ክርስቲያንነትን ፡ የተደገፈ ፡ የልመና ፡ ደብዳቤ ፡ አሲዘው ፡ ሞንሲኞር ፡ ማካሪዮንን ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ላኩ ። ከደብዳቤውም ፡ ይበልጡ ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ነው ።

«ለኀያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡
ሰላም ፡ ለርስዎ ፡ ይሁን ።

ክርስቲያናዊ ፡ በሆነው ፡ ልብዎ ፡ የምመክርዎትን ፡ አመዛዝነው ፡ የልግስና ፡ ሥራ ፡ እንዲያደርጉ ፡ እለምንዎታለሁ ።

የዚህ ፡ የዘመቻ ፡ ድል ፡ በእጅዎ ፡ ብዙ ፡ የኢጣሊያ ፡ ምርኮኞች ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶዎታል ፡ የነዚህም ፡ የኢጣሊያኖች ፡ መማረክ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ያሉትን ፡ በሽህ ፡ የሚቈጠሩትን ፡ የእናቶቻቸውንና ፡ የሚስቶቻቸውን ፡ የልብ ፡ ኀዘንና ፡ ጭንቀት ፡ ከማበርከት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ኀይልና ፡ ዝና ፡ ሊያስፋፋ ፡ አይችልም ። እኛም ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተቀበልነው ፡ አደራ ፡ እንደ ፡ ልጆቻችን ፡ ያኽል ፡ እንወዳቸዋለንና ፡ እነዚህን ፡ ምርኮኞች ፡ በቶሎ ፡ በነፃ ፡ እንዲለቋቸው ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴና ፡ በድንግል ፡ ማርያም ፡ ወይም ፡ በዓለም ፡ ካለው ፡ በሚወዱት ፡ ስም ፡ እለምንዎታለሁ ።

ኀያሉ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆይ ፡

ይኸንንም ፡ የምለምንዎትን ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ እንቢ ፡ ማለትዎ ፡ በመንግሥታት ፡ ፊት ፡ የተገለጸ ፡ አይሁን ፡ ይህችንም ፡ የተከበረች ፡ ደብዳቤዬን ፡ ለምስክር ፡ እታሪክዎ ፡ መዝገብ ፡ ያግቧት ።

በዚህም ፡ በሚያደርጉት ፡ የቸርነት ፡ ሥራ ፡ ርኅሩኅና ፡ የሁሉ ፡ አባት ፡ የሆነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክስዎታል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ በብዙ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ሊያመሰግኑዎ ፡ ድምፃቸውን ፡ ያነሣሉ ፡ ከነዚሁም ፡ መዠመሪያዎቹ ፡ እኛ ፡ ነን ።

ይህ ፡ የልመና ፡ ቃል ፡ እንዲፈጸም ፡ በተስፋ ፡ ከመጠባበቅ ፡ ጋራ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ በቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ላይ ፡ በረከቱን ፡ እንዲያወርድ ፡ እንጸልያለን ፡ ሮማ ፡ እቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ (እንደ ፡ ኤ. ቍ) ፡ ግንቦት ፡ 11 ፡ ቀን ፡ 1896 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

ፊርማ ፡ ልዮን ፡ ፒፒ ፡ 13ኛ » ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ንግግር ፡ ልባቸው ፡ ቢነካ ፡ ከጦርነቱ ፡ ወዲህ ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ወሰኑና ፡ ስለ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ የታወቀ ፡ ውል ፡ አልተዋዋሉም ፡ ነበርና ፡ ውል ፡ ከማድረግ ፡ አስቀድሞ ፡ በዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ በእጃቸው ፡ ያለውን ፡ ምርኮኛ ፡ ለመልቀቅ ፡ የማይቻልበትን ፡ ምክንያት ፡ ገልጸው ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጥና ፡ የሚያጽናና ፡ ደብዳቤ ፡ አሲዘው ፡ ሞን ፡ሲኞር ፡ ማካሪዮንን ፡ መልሰው ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ላኳቸው ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ዶክቶር ፡ ኔራሲኒ ፡ የሚባለው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሄዶ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ የዕርቅ ፡ ውል ፡ እንዲያደርግ ፡ ተልኮ ፡ መስከረም ፡ 25 ፡ ቀን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገባ ።

ቀጥሎም ፡ ስለ ፡ ዕርቁና ፡ ስለ ፡ ወሰኑ ፡ ባ1889 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ተዋዋለ ።

1ኛ. ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተደረገው ፡ ያለ ፡ ጦርነት ፡ ቀርቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥትና ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ የሚቈይ ፡ የወዳጅነትና ፡ የዕርቅ ፡ ውል ፡ ተደርጓል ።

2ኛ. ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ውጫሌ ፡ ላይ ፡ ተደርጎ ፡ የነበረው ፡ ውል ፡ በፍጹም ፡ ቀርቷል ።

3ኛ. ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ ያውቃል ።

4ኛ. ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስለ ፡ ወሰኑ ፡ በንግግር ፡ ቢስማሙ ፡ ኣሁንም ፡ ይህ ፡ ውል ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ የሚካለሉላቸውን ፡ ወኪሎቻቸውን ፡ አድርገው ፡ በስምምነት ፡ ያካለላሉ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ የመረብና ፡ የበለሳ ፡ ወሰን ፡ ይሁን ፡ ተብሎ ፡ ለጊዜው ፡ የተወሰነው ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ከበረ ፡ ይቆያል ፡ እንጂ ፡ አይሻርም ።

5ኛ. ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ወሰኑን ፡ በደንብ ፡ ሳይካለል ፡ በኤርትራ ፡ የያዘውን ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ከያዘው ፡ አገር ፡ ቈርጦ ፡ ለመስጠት ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ይለቃል ፡ እንጂ ፡ ለሌላ ፡ መንግሥት ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ውል ፡ ተዋውለው ፡ የውሉ ፡ ቃል ፡ ለኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ ተልኮለት ፡ ከተስማሙበት ፡ በኋላ ፡ ከምርኮኞቹ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የመስኮብ ፡ ንጉሥ ፡ ኒኮላ ፡ ዛር ፡ የተወለዱበት ፡ ቀን ፡ ሲከበር ፡ ስለ ፡ እርሳቸው ፡ ክብር ፡ 50 ፡ የኢጣሊያ ፡ እሥረኞች ፡ ተለቀው ፡ ነበር ፡ እንዲሁም ፡ የተረፉትን ፡ ምርኮኞች ፡ በነፃ ፡ ለቀዋቸው ፡ ካ1889 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ 1890 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጥር ፡ 3 ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሁሉም ፡ በዘይላ ፡ በኩል ፡ ተሳፍረው ፡ ወዳገራቸው ፡ ገቡ ። ከምርኮኞቹም ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ባዛኝ ፡ ዛማኔል ፡ ቤት ፡ በምሪት ፡ ይኖር ፡ የነበረው ፡ አልቤርቶኔ ፡ የሚባለው ፡ ጄኔራል ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ አብሮ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ምርኮኞቹ ፡ ከመነሣታቸው ፡ በፊት ፡ የዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ ዕለት ፡ ከሞተው ፡ ከጄኔራል ፡ አሪሞንዲ ፡ የተማረከውን ፡ ሻሞላወን ፡ ለቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ አስረክብለት ፡ ብለው ፡ ለጄኔራል ፡ አልቤርቶኒ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በፊታቸው ፡ አሰጡትና ፡ ተረከቦ ፡ ይዞ ፡ ሄደ ፡ ይኸውም ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክን ፡ ልበ ፡ ሰፊነትና ፡ ቅንነታቸውን ፡ ያስረዳል ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከምጥዋ ፡ እየገሠገሠ ፡ እስከ ፡ አምባአላጌ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲሁም ፡ ከኤርትራ ፡ በስተምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየገፋ ፡ ሄዶ ፡ ከሰላን ፡ ሁሉ ፡ ይዞ ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በጦርነት ፡ ከመረብ ፡ ወዲያ ፡ እንዳሻገሩት ፡ እንዲሁም ፡ ደርቡሾች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኣጐርዳት ፡ እየወጉ ፡ ስላስቸገሩትና ፡ ኀይሉ ፡ ስለ ፡ ተዳከመ ፡ ለራሱ ፡ እስከ ፡ ሰብደራት ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ አስቀርቶ ፡ የከሰላን ፡ ግዛት ፡ ታኅሣሥ ፡ 10 ፡ ቀን ፡ 1890 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ለቀቀለት ።

# ምዕራፍ ፡ 35 ።

## የዓድዋ ፡ ድልና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡

ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደገለጽነው ፡ የዓድዋ ፡ ድል ፡ በኢጣልያ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ሽብርና ፡ ድንጋጤ ፡ ፈጥሯል ። የእንግሊዝና ፡ የፈረንሳዊ ፡ ያንዳንድ ፡ ክፍል ፡ ወታደር ፡ በእስያና ፡ በአፍሪካ ፡ በቀላል ፡ ጦርነት ፡ ሰፋፊ ፡ ግዛት ፡ ለየመንግሥታቸው ፡ ሲያተርፉ ፡ ኢጣልያንን ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ የመሰለ ፡ የመሸነፍ ፡ አደጋ ፡ ስለደረሰባት ፡ ይኸው ፡ ሁኔታ ፡ በዘመኑ ፡ ባለው ፡ በየመንግሥቱ ፡ ጋዜጣ ፡ እየተጠቀሰ ፡ ስለተጻፈ ፡ በኢጣልያኖች ፡ ዘንድ ፡ ሐፍረትና ፡ ቊጭት ፡ አሳድሮ ፡ ነበር ። በኢጣልያ ፡ አገር ፡ የሶሲያልስቱ ፡ ወገን ፡ ቀድሞውንም ፡ ጦርነቱ ፡ ቢቀርብን ፡ ይሻላል ፡ ይል ፡ ነበርና ፡ አሁንም ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ድል ፡ ከደረሰብን ፡ የኤርትራ ፡ ግዛት ፡ ለምለምና ፡ ፍሬያማ ፡ ስላልሆነ ፡ ኢጣልያን ፡ ገንዘብ ፡ ከማስወጣት ፡ በቀር ፡ የሚረባን ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ ይለቀቅ ፡ ብለው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የቀሩት ፡ አማካሪዎች ፡ ይኸን ፡ ኣሳብ ፡ ስላልተቀበሉት ፡ የኤርትራን ፡ ግዛት ፡ እንዲከላከል ጀኔራል ፡ ባልዲሥራ ፡ ተላከ ፡ እርሱም ፡ ኤርትራ ፡ ከመጣ ፡ ወዲህ ፡ አዲስ ፡ ይዞ ፡ ከመጣው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በቀር ፡ ከአድዋ ፡ ጦርነት ፡ የሸሸውን ፡ ጨምሮ ፡ 30ሺ ፡ የሚሆን ፡ ጦር ፡ አደራጅቶ ፡ ነበር ፡ በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ምናልባት ፡ የሚቻል ፡ ቢሆን ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ አገር ፡ መያዝና ፡ ያለፈውን ፡ የጦርነት ፡ ድል ፡ ለመበቀል ፡ እንዲያጠና ፡ ታዞ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ የኢትዮጵያን ፡ የውስጥ ፡ አንድነት ፡ የጦሩንም ፡ ኃይል ፡ ገምቶ ፡ 80ሺ ፡ ጦር ፡ ካልተላከልኝ ፡ አይቻልም ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ሰጠ ፡ ይባላል ።

ስለዚህ ፡ የኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ የዚህን ፡ እንደገና ፡ አገርን ፡ የመውረርና ፡ በጦርነት ፡ የመበቀልን ፡ ነገር ፡ ተወና ፡ ባለፈው ፡ ያየነውን ፡ ውል ፡ መላከተኛውን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ድረስ ፡ ልኮ ፡ ተዋዋለ ። በውሉም ፡ ውስጥ ፡ በውጫሌ ፡ ውል ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ የሚለውን ፡ ክርክር ፡ ሁሉ ፡ ሽሮ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ ማወቁን ፡ በግልጽ ፡ ፈረመ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የዚህኑ ፡ ውል ፡ ውሳኔ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ለወዳጆቻቸው ፡ ለፈረንሳዊና ፡ ለመስኮብ ፡ መንግሥት ፡ እንደዚሁም ፡ ለእንግሊዝና ፡ ለሌሎቹም ፡ እስታወቁ ። ስለዚህ ፡ መንግሥታቱ ፡ ከዚህ ፡ ውል ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስቴሮቻቸውን ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እየላኩ ፡ ያስቀምጡ ፡ ዠመር ።

ሀ _ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ሙሴ ፡ ሌዎንስ ፡ ላጋርድን ፡

ለ _ መስኮብ ፡ ገኔራል ፡ ቭላሶውን ፡

ሐ _ እንግሊዝ ፡ ሊዬተና ፡ ኮሎኔል ፡ ዢን ፡ ላን ፡ ሐሪንግተንን ፡

መ _ ኢጣልያም ፡ ካፒቴን ፡ ፌዴሪኮ ፡ ቺኮዲኮላን ፡ ላኩ ።

እነዚህም ፡ ከየራሳቸው ፡ መንግሥት ፡ የተላኩበትን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አቅርበው ፡ ሌጋሲዮናቸውን ፡ እየከፈቱ ፡ ተቀመጡ ።

በዓድዋ ፡ ጦርነት ፡ የኢጣልያ ፡ ጦር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጦር ፡ አሸንፎ ፡ ቢሆን ፡ አገሩን ፡ ሁሉ ፡ በየጊዜው ፡ ወሮ ፡ በመጨረስ ፡ ለዘለቄታ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ሊያደርገው ፡ ይችል ፡ ነበር ፡ ኢትዮጵያም ፡ በሚመጣው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለመነሻና ፡ ነፃነቷን ፡ ለማግኘት ፡ በቂ ፡ ምክንያትና ፡ ኃይል ፡ አታገኝም ፡ ነበር ። የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ሲሸነፍም ፡ ፈረንሳዊ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሲል ፡ ከኢጣልያ ፡ ይዋጋል ፡ ተብሎ ፡ አይጠረጠርም ። ከዓድዋ ፡ ድል ፡ በኋላ ፡ በ18ኛው ፡ ዓመት ፡ ትልቁ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በተነሣም ፡ ጊዜ ፡ ኢጣልያ ፡ በ2ኛው ፡ ዓመት ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ጓደኛ ፡ ሆኖ ፡ ከእንግሊዝና ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ጋር ፡ ጀርመኖችን ፡ ስለወጋና ፡ ከአሸናፊዎቹ ፡ ወገን ፡ ስለተቆጠረ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የመቀስቀሻው ፡ ጊዜ ፡ የተዘጋ ፡ ይሆን ፡ ነበር ፡ ስለዚህ ፡ በርትቶ ፡ የተዋጋውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ የድል ፡ አድራጊነቱን ፡ ዕድል ፡ የተካፈሉትን ፡ መሳፍንት ፡ ማመስገን ፡ ይገባል ። ምክንያቱም ፡ እነዚህ ፡ ወይም ፡ ከእነዚህ ፡ አንዱ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክን ፡ እንደ ፡ ሸዋ ፡ ንጉሥና ፡ እንደ ፡ ባዕድ ፡ ቆጥረው ፡ የራሳቸውን ፡ ምኞት ፡ በዚህ ፡ አስቸጋሪ ፡ ጊዜ ፡ ለመፈጸም ፡ በመሞከር ፡ ተለይተው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እነዚህም ፡ እንሸፍት ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክም ፡ ለምን ፡ በማለት ፡ ውስጥ ፡ ግጭት ፡ ተነሥቶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ለኢጣልያ ፡ ጦር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይጠቅመው ፡ እንደነበረ ፡ ለመመልከት ፡ ግልጥ ፡ ነበር ። የኢጣልያም ፡ የጦርና ፡ የፖለቲካ ፡ መሪዎችም ፡ ውስጥ ፡ ውስጥ ፡ እየተላላኩ ፡ ዡሮዋቸውን ፡ ከፍተው ፡ የጠበቁት ፡ ይኸንኑ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፡ የመኳንንቱና ፡ የመሳፍንቱ ፡ ኅብረት ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ታማኝነት ፡ ከመቸውም ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ የጠበቀ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ኢጣልያኖች ፡ አቆብቁበው ፡ የጠበቁት ፡ ነገር ፡ ብቅ ፡ ሊልላቸው ፡ አልቻለም ። ጦርነቱም ፡ ቀላል ፡ አልነበረም ፡ የኢጣልያኖችም ፡ ብዛታቸውና ፡ የመሣሪያቸው ፡ ጥራት ፡ እነርሱም ፡ ድሉን ፡ ለማግኘት ፡ ያደረጉት ፡ ትጋትና ፡ ትግል ፡ ዋዛ ፡ ኣልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ ያሉ ፡ ዝግና ፡ የሹማምንት ፡ ወታደሮች ፡ ያሉበት ፡ ጦር ፡ በዋዛ ፡ አይፈታምና ፡ የሞቱትም ፡ በሕይወት ፡ የተመለሱትም ፡ ምክርና ፡ መላ ፡ አዋቂዎቹም ፡ የጦር ፡ አርበኞቹም ፡ ተባብረው ፡ ያሳዩት ፡ የወታደርነትና ፡ የፖለቲካ ፡ አንድነት ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ሰብሮ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ የክብር ፡ አክሊል ፡ ደፋለት ።

# ምዕራፍ ፡ 36 ።

## ሱማልያና ፡ ሱማሌዎች ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ ለዚህ ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ለተደረገው ፡ ጦርነት ፡ የረዳውን ፡ ኤርትራን ፡ ካገኘ ፡ ወዲህ ፡ እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ አገር ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ በነገሩ ፡ እንዲያስብበት ፡ በአደንና ፡ በዛንዚባር ፡ በቆንሲልነት ፡ ያስቀመጣቸውን ፡ ካፒቴን ፡ አንቶኒዮ ፡ ቼኪንና ፥ ካባሊዬሪ ፡ ሬሎናርዲን ፡ አዟቸው ፡ ነበር ።

የበናዲርን ፡ ግዛት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ሲገዙት ፡ ከቈዩ ፡ ወዲህ ፡ የመስቃጥ ፡ ሡልጣን ፡ ይዛው ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የመስቃጥ ፡ ሡልጣን ፡ ኀይሉ ፡ ስለ ፡ ደከመ ፡ ግዛቱ ፡ በዛንዚባር ፡ ሡልጣን ፡ ተላለፈ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ካፒቴን ፡ አንቶኒዮ ፡ ቼኪ ፡ በዚሁ ፡ በህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ዳርቻ ፡ መሬት ፡ ቈርጦ ፡ እንዲሰጠው ፡ ሡልጣኑን ፡ ጠይቆት ፡ ከከለከሰው ፡ በኋላ ፡ ባ1878 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ ብቻ ፡ ተዋዋለ ። ስለዚህ ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በመርከብ ፡ ንግድን ፡ ምክንያት ፡ አድርገው ፡ የሚመጡት ፡ ጣሊያኖች ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ከሚገኙት ፡ ሡልጣኖችና ፡ የሱማሊያ ፡ ሹማምቶች ፡ ጋራ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ማድረግ ፡ ዠመሩ ። ወዲያውም ፡ ከመቃዲሾ ፡ በስተምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ የሱፍ ፡ ዐሊ ፡ የሚባለው ፡ የአቢያ ፡ ሡልጣን ፡ ከላይ ፡ ዐረቦች ፡ እየመጡ ፡ ያውኩት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ድጋፍ ፡ ለመፈለግ ፡ ሲል ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ የኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ጠባቂ ፡ ብቻ ፡ እንዲሆነው ፡ ውል ፡ ተዋዋለ ። እሱም ፡ ይህን ፡ ከተዋዋለ ፡ ወዲህ ፡ የርሱ ፡ ባላንጣ ፡ ዑስማን ፡ መሐመድ ፡ የሚባለው ፡ የሚጁሪቲን ፡ ሡልጣን ፡ እንዲሁ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ጠባቂ ፡ እንዲሆን ፡ ባ1882 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ተዋዋለ ። የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ እየወሰደ ፡ ለሥልጣኖች ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ ባመት ፡ ሺህ ፡ 800 ፡ ብር ፡ ሊሰጥ ፡ ፈረመላቸው ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እነዚህን ፡ እላይ ፡ የተጻፉትን ፡ አገሮች ፡ በጠባቂነት ፡ ስም ፡ ካገኘ ፡ ወዲህ ፡ ከመቃዲሾ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የወረ ፡ ሼክን ፡ አገር ፡ ለመያዝ ፡ በመርከብ ፡ ወታደሮች ፡ አውርዶ ፡ ጥቂት ፡ ሳይቈይ ፡ ወዲያው ፡ የዚሁ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ ስለ ፡ ወጓቸው ፡ በመርከብ ፡ ተሳፍረው ፡ ወደ ፡ መጡበት ፡ ስፍራ ፡ ተመልሰው ፡ ሸሹ ። በኋላ ፡ ግን ፡ በካባሊዬሪ ፡ ሬሎናርዲ ፡ አዝማችነት ፡ ወታደርም ፡ መሣሪያም ፡ ጨምረው ፡ መጥተው ፡ ጦርና ፡ ቀስት ፡ ከያዙት ፡ ሱማሌዎች ፡ ጋራ ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ባለጠመንዣዎቹ ፡ ባለቀስቶቹን ፡ አሸንፈው ፡ ስላባረሯቸው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከወዲህ ፡ ከኬንያ ፡ ድንበር ፡ ከጁባ ፡ ኣንሥቶ ፡ እስከ

፡ በርበራ ፡ ግዛት ፡ ወሰን ፡ ድረስ ፡ በጠባቂነት ፡ ስም ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ለዳር ፡ ግዛቱን ፡ አራዝሞ ፡ ይኸንኑም ፡ ለየመንግሥታቱ ፡ አስታወቀ ።

የእንግሊዝና ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በያዙት ፡ አገር ፡ በወሰን ፡ ስለ ፡ ተገናኙ ፡ ስምምነት ፡ አድርገው ፡ ወሰኑን ፡ ከተካለሉ ፡ በኋላ ፡ በህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ዳርቻ ፡ የሚገኙት ፡ የብራዋ ፥ የሜርካ ፥ የበናዲር ፥ የመቃዲሾ ፥ የወረ ፡ ሼክ ፡ የባሕር ፡ በሮች ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ይህን ፡ ኣገር ፡ በበላይነት ፡ ይገዛ ፡ ለነበረው ፡ ለዛንዚባሩ ፡ ሡልጣን ፡ ባ1884 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በነሐሴ ፡ እንደ ፡ ተዋዋሉት ፡ ባመት ፡ 160 ፡ ሺህ ፡ ሩቢስ ፡ ሊከፍለው ፡ ውል ፡ ተደረገ ።

ካፒቴን ፡ ቼኪ ፡ አፍጎይ ፡ ሄዶ ፡ ከጋለዲ ፡ ሥልጣን ፡ ጋራ ፡ እንደዚሁ ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ እዋዋላለሁ ፡ ብሎ ፡ ከነወታደሩ ፡ ሲሄድ ፡ ላፎሌ ፡ እሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ እጫካ ፡ ውስጥ ፡ ሱማሌዎች ፡ አግኝተው ፡ ከነተከታዮቹ ፡ በደፈጣ ፡ ገደሉት ፡ በጥርጣሬ ፡ ያስገደለውም ፡ ያው ፡ የጋለዲ ፡ ሡልጣን ፡ ነው ፡ ይባላል ።

እንደዚሁ ፡ በስለላ ፡ የተደበቀ ፡ አገርና ፡ ወንዝ ፡ አግኝተው ፡ ባገራቸው ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ለመመስገን ፡ የሚፈልጉ ፡ የኢጣሊያ ፡ ጉበኞች ፡ እየመጡ ፡ ብዙዎቹ ፡ በበረሓ ፡ ሙተዋል ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ ኤውጄኔዎ ፡ ሩስፓሊ ፡ የሚባለው ፡ የጁባን ፡ ወንዝ ፡ እመረምራለሁ ፡ ሲል ፡ ባ1887 ፡ ዓ ፡ ም ፡ እስከ ፡ ቦረና ፡ ጫፍ ፡ ድረስ ፡ ዘልቆ ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በኬንያና ፡ በኢትዮጵያ ፡ አዋሳኝ ፡ አገር ፡ ካለው ፡ ጫካ ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ደርሶ ፡ ዝኆን ፡ አግኝቶ ፡ ለማደን ፡ ሲፈትን ፡ ወዲያው ፡ ዝኆኑ ፡ መቀመጫውን ፡ ጫካ ፡ የሚሰልልበትን ፡ ጣሊያን ፡ ሰባብሮ ፡ ገደለው ። እንዲሁም ፡ የሱ ፡ ጓደኛ ፡ ካፒቴን ፡ ቢቶሪዮ ፡ ቦቴጎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ የሚገኘውን ፡ የኦሞን ፡ ወንዝ ፡ መነሻውንና ፡ መድረሻውን ፡ ለመመርመር ፡ ሌሎችንም ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡ አስከትሎ ፡ ሩስፓሊ ፡ የሄደበትን ፡ ዱካ ፡ እየተከተለ ፡ ሄዶ ፡ ሩስፓሊ ፡ የሞተበትንና ፡ ዐፅሙ ፡ የተቀበረበትን ፡ ስፍራ ፡ ጉብኝቶ ፡ አለፈ ። ከዚያም ፡ በጎፋ ፡ አልፎ ፡ ወለጋ ፡ እደጃዝማች ፡ ኤጀቴ ፡ አገር ፡ በተለይ ፡ ጐቢ ፡ እሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ደርሶ ፡ ሌሊት ፡ እሰፈረበት ፡ ላይ ፡ ጋሎች ፡ አግኝተውት ፡ ባ1889 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመጋቢት ፡ 10 ፡ ቀን ፡ ጦርነት ፡ አደረጉ ፡ በዚህም ፡ ውጊያ ፡ ከውስጣቸው ፡ 2 ፡ ቴኔንቴዎች ፡ ተማርከው ፡ እጃቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ ካፒቴን ፡ ቦቴጎና ፡ የቀሩት ፡ ሁሉም ፡ እዚያው ፡ እጦርነት ፡ ላይ ፡ ሞቱ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከመቃዲሾ ፡ ግዛቱን ፡ ለማስፋት ፡ እስከ ፡ ባርደሌ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ ሉክ ፡ ከነበሩት ፡ ከደጃች ፡ አሰፋ ፡ ሉልሰገድ ፡ ጋራ ፡ ተገናኘ ። ወዲያው ፡ ቡር ፡ አቃባ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባንዲራ ፡ ተተክሎ ፡ ነበርና ፡ ካፒቴን ፡ ቦንጂዎባኒ ፡ የሚባለው ፡ ብዙ ፡ የኤርትራን ፡ ወታደሮች ፡ ጭምር ፡ አስከትሎ ፡ ግዛቱ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ነውና ፡ የባርደሌን ፡ ስፍራ ፡ ልቀቁልኝ ፡ ሲል ፡ ከደጃች ፡ አሰፋ ፡ ሉል ፡ ሰገድ ፡

ጋራ ፡ ባ1900 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ውጊያ ፡ ዠመረ ፡ ደጃች ፡ አሰፋም ፡ አለቅም ፡ በማለት ፡ ተዋግተው ፡ የነበረበትን ፡ ምሽግ ፡ ጭምር ፡ ኣስለቅቀው ፡ አባረሩት ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ የሱማሊያን ፡ አገር ፡ ከኢጣሊያም ፡ ከእንግሊዝም ፡ ከኢትዮጵያውያንም ፡ እየተዋጋ ፡ ይከላከል ፡ የነበረው ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ የኖጋሉ ፡ ባላባት ፡ ሙላህ ፡ እሚባለው ፡ ከእንግሊዝ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተዋጋ ፡ 1 ፡ ጊዜም ፡ ድል ፡ ሲያደርግ ፡ 1 ፡ ጊዜም ፡ ድል ፡ ሲሆን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ባ1913 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአየር ፡ ጦርነት ፡ ጭምር ፡ ወግተውት ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ለኢጣሊያ ፡ የተመቸ ፡ ጊዜ ፡ ሆነለት ፡ ወዲያው ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አዘጋጅቶ ፡ በጠባቂነት ፡ ስም ፡ ይዞት ፡ ቈይቶ ፡ የነበረውን ፡ የኦቢያንና ፡ የማጁርቲንን ፡ አገር ፡ ውሉን ፡ ኣፍርሶ ፡ ቀጥቅጦ ፡ ለመግዛትና ፡ ቅኝ ፡ ኣገር ፡ ለማድረግ ፡ በነዚሁ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ ተዠመረ ። እነሱም ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ አንሆንም ፡ በማለት ፡ ፊት ፡ ለፊትም ፡ እየተደበቁም ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ በመሣሪያና ፡ በወታደር ፡ ብዛት ፡ ድል ፡ ስላደረጋቸው ፡ ገሚሶቹ ፡ ተስፋ ፡ በመቍረጥ ፡ ተገዥነታቸውን ፡ እያመኑ ፡ ገቡለት ፡ የቀሩት ፡ ግን ፡ አገራቸውን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ እየተሰደዱ ፡ ተቀመጡ።

ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ሱማሊያን ፡ እስከ ፡ ለቀቀበት ፡ ድረስ ፡ በታሪኩም ፡ በመሬቱም ፡ አቀማመጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሱማሌ ፡ ሊባል ፡ የሚገባው ፡ አገር ፡ የኢጣሊያ ፡ ሱማሌ ፡ እየተባለ ፡ ዓርባ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ወንዶቹም ፡ ሴቶቹም ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ከጧት ፡ ዠምረው ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ከኢጣሊያ ፡ አገር ፡ እየመጡ ፡ በሱማሊያ ፡ የተቀመጡትን ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ለማክበር ፡ ሲሠሩና ፡ ሲለፉ ፡ መኖራቸውን ፡ ይኸን ፡ መጽሐፍ ፡ የጻፈው ፡ ባ1929 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በግዞት ፡ መዠመሪያ ፡ ደናኔ ፡ ከዚያም ፡ 116 ፡ የሙዝ ፡ እርሻ ፡ (ኮንሴሲዮን) ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ወደ ፡ ገናሌ ፡ ሄዶ ፡ ባይኑ ፡ አይቷል ።



የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ የጦር ፡ ኃይል

# ምዕራፍ ፡ 37 ።

## የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ኃይል ፡ መሰብሰብና ፡ ግዛት ፡ ማስፋት ።

ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከያለበት ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እየሰበሰቡ ፡ ወታደራቸውን ፡ ያደራጁ ፡ ነበር ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥትም ፡ ተላልከው ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ ጠመንዣ ፡ ብዙ ፡ ጥይት ፡ ካገኙ ፡ ወዲህ ፡ እንዲሁም ፡ የዐድዋ ፡ ዘመቻ ፡ ሊደረግ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሲቀረው ፡ በነሙሴ ፡ ሽፍኒ ፡ አማካይነት ፡ ከፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ብዙ ፡ መሣሪያ ፡ በግዥ ፡ አግኝተዋል ።

ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በዚሁ ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ባገኙት ፡ መሣሪያ ፡ ኢጣሊያኖችን ፡ አባረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ እስከ ፡ መረብ ፡ ድረስ ፡ መሆኑን ፡ ከጦርነቱ ፡ ወዲህ ፡ በስምምነት ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከተዋዋሉ ፡ በኋላ ፡ ከዚያም ፡ በፊት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ደቡብ ፡ ያለውን ፡ ታላቀኑን ፡ የሐረርን ፡ ግዛት ፡ ራሳቸው ፡ ሄደው ፡ ባ1879 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ አሚር ፡ ዐብዱላሂን ፡ ወግተው ፡ አስመልሰው ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ አሚር ፡ ዐብዱላሂ ፡ ተሸንፎ ፡ እጁን ፡ ስለ ፡ ሰጠ ፡ አገሩን ፡ በቅንና ፡ በትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ እንዲያስተዳድሩ ፡ ራስ ፡ መኰንንን ፡ ደጃዝማች ፡ ብለው ፡ ሾመው ፡ ሐረር ፡ ትተዋቸው ፡ ተመልሰው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ተናግረናል ። ርሳቸውም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ ከሐረር ፡ ወዲያ ፡ ኢሳንና ፡ ውጋዴን ፡ አልፎ ፡ እስከ ፡ ሱማሊያ ፡ ወሰን ፡ ድረስ ፡ አቀኑ ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተዠምሮ ፡ የቈየውን ፡ አገር ፡ ለመያዝ ፡ እንዲሁ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ቍጥሩ ፡ 30 ፡ ሺህ ፡ የሚደርስ ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ አስከትለው ፡ ከፋሌ ፡ ዠምረው ፡ የሺሆጂሌን ፡ ግዛት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አድርገው ፡ እስከ ፡ ሱዳን ፡ ጠረፍ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ አስገበሩ ።

ደጃች ፡ ተሰማ ፡ ናደው ፡ በይሉባቦር ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ የባሮን ፡ መሬት ፡ እያቋረጡ ፡ እስከ ፡ ሶባትና ፡ እስከ ፡ ነጭ ፡ አባይ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ኣገር ፡ አስገበሩ ።

ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከፋን ፡ ኵሎን ፡ ኰንታን ፡ ሊሙን ፡ ከዚያም ፡ እስከ ፡ ነጭ ፡ ዓባይ ፡ ድረስ ፡ ኣልፈው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ አሰፉ።

ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ 15 ፡ ሺሕ ፡ ያኸል ፡ የጦር ፡ ወታደራቸውን ፡ ይዘው ፡ በቦረና ፡ በኩል ፡ እስከ ፡ ኬንያ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ አቀኑ።

እነዚህ ፡ እላይ ፡ የተቈጠሩት ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጊዜ ፡ ለጌታቸው ፡ በቅንነት ፡ እያገለገሉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ በማስፋታቸው ፡ ታላቅ ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ።

# ምዕራፍ ፡ 38 ።

## ስለ ፡ ወይዘሮ ፡ ባፈና ፥ ስለ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፥ ስለ ፡ ራስ ፡ ዳርጌ ፥ ስለ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፥ ስለ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፥ ስለ ፡ ራስ ፡ በዛብኽ ፥ ስለ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፥ - ስለ ፡ ራስ ፡ ወሌ ።

### ስለ ፡ ወይዘሮ ፡ ባፈና ።

ወይዘሮ ፡ ባፈና ፡ ትውልዳቸው ፡ መርሐ ፡ ቤቴ ፡ ከባላባት ፡ ወገን ፡ ነው ። ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከተጋቡ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ሴቶች ፡ ለባላቸው ፡ ክብር ፡ በመቅናትና ፡ ባላቸውን ፡ በማገልገል ፡ ፈንታ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ባላንጦች ፡ ከነደጃች ፡ መሸሻ ፡ ሰይፉ ፡ ካማቻቸው ፡ ከይማም ፡ መሐመድ ፡ ጋራ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ እየተላላኩ ፡ በባለቤታቸው ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ላይ ፡ ዐድማ ፡ ይሠሩባቸው ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ በዐፄ ፡ ዮሐንስና ፡ በንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ መካከል ፡ ግጭት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አሳባቸውን ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ እያደረጉ ፡ ይስማሙ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ይኸንንም ፡ ቢያውቁ ፡ ፍቅር ፡ የማያሸንፈው ፡ ነገር ፡ አይገኝምና ፡ ክዳታቸውንና ፡ ዐድማቸውን ፡ በፍቅር ፡ ምክንያት ፡ እየታገሡ ፡ አብረው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ወይዘሮ ፡ ባፈና ፡ ይኸንኑ ፡ ያድማ ፡ ነገር ፡ እየቀጠሉ ፡ ስለ ፡ ሄዱ ፡ ባ1875 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጭራሽ ፡ ፈቷቸው ።

### ስለ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ።

የየጁ ፡ ባላባት ፡ የደጃች ፡ ብጡል ፡ ልጆች ፡ ልጅ ፡ ወሌና ፡ ልጅ ፡ አሉላ ፡ የሚባሉት ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በኋላ ፡ ለዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ አሽከርነት ፡ ስላደሩ ፡ ልጅ ፡ ወሌ ፡ የደጃዝማችነት ፥ ልጅ ፡ አሉላ ፡ የፊታውራሪነት ፡ ማዕርግ ፡ ኣግኝተው ፡ ከየጁ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጥተው ፡ በከበሬታ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ወይዘሮ ፡ ጣይቱ ፡ እኅታቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ደስታን ፡ አስከትለው ፡ ወንድሞቼን ፡ አያለሁ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጥተው ፡ በደጃች ፡ ወሌ ፡ ቤት ፡ ተቀመጡ ። ዐፄ ፡ ምኒልክም ፡ በጐንደርና ፡ በመቅደላ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ የወይዘሮ ፡ ጣይቱን ፡ ውበትና ፡ ጠባይ ፡ ይሰሙ ፡ ነበርና ፡ በሸዋ ፡ መጥተው ፡ በደጃች ፡ ወሌ ፡ ቤት ፡ በመቀመጣቸው ፡ ደስ ፡ ስላላቸው ፡ አዲስ ፡ በመጡት ፡ በአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ እጅ ፡ በሺህ ፡ 875

፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ሚያዝያ ፡ 25 ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ሥጋ ፡ ወደሙ ፡ ተቀብለው ፡ ተጋቡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ 7 ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ አብረው ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ባ1882 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘውድ ፡ በደፉ ፡ ጊዜ ፡ ወይዘሮ ፡ ጣይቱም ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ በጳጳሱ ፡ በአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ እጅ ፡ የሚገባቸውን ፡ ዘውድ ፡ ደፍተው ፡ እቴጌ ፡ ተባሉ ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ እየተባሉ ፡ ይጠሩ ፡ ዠመር ።



እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ብጡል።

እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ባላቸውንና ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚወዱ ፡ ናቸው ፡ በመልካቸውም ፡ በጣም ፡ የተዋቡና ፡ ባለሙያ ፡ ጠባየ ፡ መልካም ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ይወዷቸውና ፡ ያከብሯቸው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ እቴጌ ፡ የጠሉት ፡ ይነቀፋል ፡ ከሹመትም ፡ ይሻራል ፡ የወደዱትም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘንድ ፡ ክብርና ፡ ሞገስ ፡ ሹመትም ፡ ያገኛል ። ስለዚህ ፡ መሳፍንቱና ፡ መኳንንቱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ እንደሚፈሩና ፡ ደጅ ፡ እንደሚጠኑ ፡ እንዲሁ ፡ እቴጌዪቱንም ፡ ደጅ ፡ ይጠኑ ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ የውጫሌ ፡ ውል ፡ ያ17ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ንግግር ፡ እንዲለወጥ ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክና ፡ በኮንቴ ፡ አንቶኔሊ ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ ሲደረግ ፡ እቴጌዪቱም ፡ በክርክሩ ፡ እየገቡ ፡ ይነጋገሩበት ፡ ነበር ።

በኋላም ፡ ባ17ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ንግግር ፡ ፈንታ ፡ «የኢትዮጵያ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥት ፡ ከመሬቱ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ባ17ኛው ፡ አንቀጽ ፡ የተባለውን ፡ ጥገኝነት ፡ ለሌላ ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ እንዳይሰጥ ፡ ግዴታ ፡ ይግባና ፡ ይለወጥ» ፡ ብሎ ፡ ሲያቀርብ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይኸንኑ ፡ አሳብ ፡ ከራስ ፡ መኰንን ፡ ጋራ ፡ ሲመካከሩ ፡ እቴጌዪቱ ፡ የፈቀድነውን ፡ ብናደርግ ፡ የኛ ፡ የግል ፡ ሥልጣናችን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እሱን ፡ በፍጹም ፡ የሚያገባው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ብለው ፡ ውሉ ፡ እንዲቀር ፡ አደረጉ ።

በኋላም ፡ በዚሁ ምክንያት ፡ የዐድዋ ፡ ዘመቻ ፡ በተቀሰቀሰ ፡ ጊዜ ፡ የግል ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ዘምተው ፡ ተዋጊውን ፡ ወታደር ፡ ሲያበረቱ ፡ ውለዋል ።

የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችም ፡ የዐድዋንና ፡ የዐፄ ፡ ምኒልክን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ ፡ ሲጽፉ ፡ የእቴጌ ፡ ጣይቱን ፡ ስም ፡ እያገነኑ ፡ ጽፈውላቸዋል ።

## ስለ ፡ ራስ ፡ ዳርጌ ።

ራስ ፡ ዳርጌ ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልጅ ፡ ናቸው። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሸዋን ፡ ለማስገበር ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክን ፡ ይዘው ፡ ሲመለሱ ፡ ራስ ፡ ዳርጌ ፡ በሸዋ ፡ ቀርተው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ኣቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ መታሠር ፡ ላቤቱታ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ሄደው ፡ ነበርና ፡ በዚያው ፡ ሳሉ ፡ አቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ ከታሰሩበት ፡ ቢያመልጡ ፡ ተጠርጥረው ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜያት ፡ ታሠሩ ፡ በኋላም ፡ እሥራቱ ፡ ቀርቶላቸው ፡ በደጅ ፡ ጥናት ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ለሸዋ ፡ እንደራሴ ፡ ሊያደርጓቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይሸፍትብዎታል ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ መከሯቸው ፡ በጥርጣሬ ፡ አስቀሩባቸው ። በዚያም ፡ ሲኖሩ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ መኳንንቱን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስበው ፡ በመቅደላ ፡ ሲያሥሩ ፡ እንደዚሁ ፡ ራስ ፡ ዳርጌንም ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ ኣሠሯቸው ። ከዚያም ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ አምልጠው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ዳርጌ ፡ በዚያው ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ ቈዩ ።

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ እንግሊዞች ፡ እሥረኛውን ፡ ሁሉ ፡ በያገሩ ፡ እንዲገባ ፡ ለቀውት ፡ ነበርና ፡ ራስ ፡ ዳርጌም ፡ ወዳገራቸው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተመልሰው ፡ በመከበርና ፡ በመፈራት ፡ ሲገዙ ፡ ኖሩ ። የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልጅ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ እንደነ ፡ ደጃች ፡ መሸሻ ፡ ሰይፉ ፥ እንደነ ፡ ፊታውራሪ ፡ ጉልላቴ ፡ ዙፋንን ፡ ሳይቀናቀኑ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ በመተማመንና ፡ በመፋቀር ፡ ኖሩ። ስለዚህ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ አክብረው ፡ በአባትነት ፡ ዐይን ፡ ይመለከቷቸው ፡ ነበር ።



ራስ ፡ ዳርጌ

## ስለ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ዮሐንስ ።


ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ መተማ ፡ በጦርነቱ ፡ ውስጥ ፡ ቈስለው ፡ ሳሉ ፡ ከዕረፍታቸው ፡ በፊት ፡ አልጋዬን ፡ የሚወርሰው ፡ ልጄ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ነውና ፡ ለርሱ ፡ ተገዙ ፡ ብለው ፡ ለመኳንንቶቻቸው ፡ አስታውቀው ፡ ነበር ፡ ስለዚህ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በመላዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ይሸፍታሉ ፡ እየተባለ ፡ ሲወራ ፡ ሳይሸፍቱ ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ተገናኙ ፡ ንጉሥም ፡ በዚሁ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ የትግሬን ፡ ግዛት ፡ መልሰው ፡ ሰጧቸው ፡ በዐድዋም ፡ ዘመቻ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጐን ፡ ተሰልፈው ፡ ኢጣሊያኖችን ፡ በመውጋት ፡ ታላቅ ፡ ሞያ ፡ ሠርተዋል ፡ ሚስታቸውም ፡ የእቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ወንድም ፡ የራስ ፡ ወሌ ፡ ልጅ ፡ ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ነበሩ ።

በኋላ ፡ ግን ፡ ባንዳንድ ፡ መካሮቻቸው ፡ ተመርተው ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ላይ ፡ ሸፈቱ ፡ ሲሸፍቱም ፡ ውስጡን ፡ ከራስ ፡ ስብሐትና ፡ ከደጃዝማች ፡ ሐጐስ ፡ ተፈሪ ፡ ጋራ ፡ ኣንድነት ፡ ለመሆን ፡ ተስማምተው ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ራስ ፡ መኰንንን ፡ ባ1891 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላኳቸው ። እርሳቸውም ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ በቆቦና ፡ በአሸንጌ ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ ኣላጌ ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ከተማመኑባቸው ፡ አንዱ ፡ ደጃች ፡ ሐጐስ ፡ በኢጋሜ ፡ ግዛት ፡ ከራስ ፡ ስብሐት ፡ አይዋደዱም ፡ ነበርና ፡ ራስ ፡ መንገሻን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ መጥተው ፡ የኢጋሜን ፡ ግዛት ፡ አገኙ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ያላቸው ፡ ኃይል ፡ የራስ ፡ መኰንንን ፡ ጦር ፡ ለመመለስ ፡ ኣለመቻሉን ፡ ተረድተውት ፡ እጃቸውን ፡ ለራስ ፡ መኰንን ፡ ሰጡ ።

ራስ ፡ መኰንንም ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ምሕረት ፡ እንዲያደርጉላቸው ፡ የልመና ፡ ደብዳቤ ፡ ጨምረው ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ላኳቸው ። ራስ ፡ መንገሻም ፡ ከትግሬ ፡ ተነሥተው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ እንዲምሯቸው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ገቡ ። ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሸፍተኽ ፡ ሳይሳካልኽ ፡ ቢቀር ፡ ወደኔ ፡ መጣኽ ፡ አሁንም ፡ ምሕረት ፡ ባደርግልሽ ፡ 3ኛ ፡ ሸፍተን ፡ የረጋውን ፡ መንግሥቴን ፡ ታነቃንቃለኽ ፡ ብለው ፡ በግዞት ፡ ወደ ፡ አንኮበር ፡ ላኳቸው።

የትግሬንም ፡ ግዛት ፡ እንዲያስተዳድሩ ፡ ለራስ ፡ መኰንን ፡ ሰጧቸው ፡ ራስ ፡ መኰንንም ፡ 1 ፡ ዓመት ፡ ከ7 ፡ ወር ፡ ያኽል ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ አገሩን ፡ ለራስ ፡ ወሌ ፡ አስረክበው ፡ ባ1892 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ።



ራስ ፡ መንገሻ ፡ ዮሐንስ

## ስለ ፡ ራስ ፡ መኰንን ።

ራስ ፡ መኰንን ፡ የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ አክሥት ፡ የወይዘሮ ፡ ተናኘ ፡ ወርቅ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። አባታቸውም ፡ የወግዳና ፡ የዶባ ፡ ባላባት ፡ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ናቸው ።

ከሕፃንነታቸው ፡ ዠምሮ ፡ በትምህርት ፡ ያደጉ ፡ ከመሆናቸው ፡ በስተቀር ፡ በተፈጥሮ ፡ ካገኙት ፡ ጠባያቸው ፡ አስተዋይና ፡ ታጋሽ ፡ ነበሩ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የጌታ ፡ ወንድማቸው ፡ ለሆኑት ፡ ለዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ በፍቅርና ፡ በእምነት ፡ ስለሚያገለግሉ ፡ በጣም ፡ ይወዷቸው ፡ ነበርና ፡ ሌሎችና ፡ ይልቁኑም ፡ የሚያፈቅሯቸው ፡ ባለቤታቸው ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ የራስ ፡ መኰንንን ፡ አገልግሎት ፡ ለማሳነስና ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ ለማጣላት ፡ ቢጥሩ ፡ በፍጹም ፡ አልሆነላቸውም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከባድ ፡ የሆነውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ያስተዳዳሪነት ፡ ቀንበር ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ በተሸከሙበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ከሌሎቹ ፡ መኳንንቶች ፡ ይበልጥ ፡ ያግዟቸው ፡ የነበሩት ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ማስተዳደሩ ፡ ችግር ፡ መስሎ ፡ ይታይ ፡ የነበረውን ፡ የሐረርጌንና ፡ የትግሬን ፡ ግዛት ፡ በማስተዳደር ፡ ይመሰገኑ ፡ ነበር ።

በምዕራብም ፡ ኢትዮጵያ ፡ እስከ ፡ አቢጋር ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ አቅንተዋል ። በዐድዋም ፡ ጦርነት ፡ የአምባ ፡ አላጌንና ፡ የመቀሌን ፡ ምሽግ ፡ አስለቅቀው ፡ የዐድዋ ፡ ዕለትም ፡ ዠግንነታቸው ፡ ታውቋል ። እንዲሁም ፡ ወደ ፡ እንግሊዝና ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እየተላኩ ፡ ሄደው ፡ ብዙ ፡ ጒዳይ ፡ ፈጽመዋል ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የአክሥታቸው ፡ ልጅ ፡ ከመሆን ፡ በስተቀር ፡ በወታደርነት ፡ ባገር ፡ አስተዳዳሪነት ፡ በዲፕሎማቲክ ፡ ጭምር ፡ በሚያደርጉላቸው ፡ አገልግሎት ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከልብ ፡ ስለ ፡ ወደዷቸውና ፡ ስላመኗቸው ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፡ አልጋዬን ፡ አወርሳለሁ ፡ እያሉ ፡ ያስቡ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አሳባችሁ ፡ ካሳቤ ፡ መሬት ፡ ከሰማይ ፡ የሚርቀውን ፡ ያኽል ፡ ይራራቃል ፡ ብሎ ፡ ለነቢዩ ፡ ለኢሳይያስ ፡ የተናገረው ፡ አምላክ ፡ የወራሹን ፡ ሕይወት ፡ ከአውራሹ ፡ በማስቀደሙ ፡ የቀረ ፡ ኣስመስሎ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለልጃቸው ፡ አልፎ ፡ እንዲጠበቅ ፡ የመለኮትነቱ ፡ ፈቃድ ፡ ሆነ ። ራስ ፡ መኰንንም ፡ የሞቱት ፡ ባ1898 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መጋቢት ፡ 13 ፡ ቀን ፡ ነው ።

ስለ ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተገጠመ ።

የራስ ፡ መኰንን ፡ ልብሱ ፡ ሁሉ ፡  
እጀ ፡ ሰፊ ፡ ነው ፡ አሉ ፡ (ቦልቦሌ)

እጀ ፡ ጠባብን ፡ እየናቀ ፡  
ሳያጠልቀው ፡ ዘለቀ ።

መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ ተጠባብቆ ፡
ወርቀኑን ፡ ኣልኖኘም ፡ ደብቆ ፡

በተናኘ ፡ ወርቅ ፡ ሐረርጌን ፡
ገዛ ፡ አሉ ፡ መኰንን ።

ራስ ፡ መኰንን ፡ መሐንዲሱ ፡
ይለዋል ፡ ሁሉም ፡ በየራሱ ፡

አስደለደለው ፡ መንገዱን ፡
መንጥሮ ፡ ውጋዴን ።

ሊቀ ፡ መልአኩ ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ ፡
ድጓውን ፡ አዘርግቶ ፡

መኰንን ፡ ቃኘው ፡ አለው ፡
ሁሉ ፡ እንዲቀበለው ።

ራስ ፡ መኰንን ፡ ሲሔድ ፡
ትልቅ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ በመንገድ ፡

የምኒልክ ፡ ቀኝ ፡ አሉት ፡
ሲወረውር ፡ ቢያዩት ።

የወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ልጅ ፡ ያረቂ ፡ መርፌው ፡
ያበሻን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጠቃቅሞ ፡ ጠቃቅሞ ፡
እንጀራ ፡ አበላው ።

## በሞቱ ፡ ጊዜ ።

ሲታሰር ፡ አየነው ፡ ብረቱ ፡ ሲመታ ፡
ምን ፡ ዋስ ፡ አገኘና ፡ ሐረርጌ ፡ ተፈታ ።
ጃንሆይ ፡ ምኒልክ ፡ ጠጕራቸው ፡ ሣሣና ፡ በራ ፡ ገለጣቸው ፡
እንግዴህ ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ራስ ፡ ኣላቸው ።



ራስ ፡ መኰንን


ራስ ፡ ሚካኤል

## ስለ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ።

ራስ ፡ ሚካኤል ፡ የወሎ ፡ ባላባት ፡ ናቸው ። ባገልግሎታቸው ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስን ፡ ደስ ፡ አሰኝተው ፡ ነበርና ፡ ባ1870 ፡ ዓ ፡ ም ፡ መሐመድ ፡ የሚባለውን ፡ ስማቸውን ፡ አስለውጠው ፡ ሚካኤል ፡ አሰኝተው ፡ የክርስትና ፡ ልጅ ፡ አድርገው ፡ በክብር ፡ ያኖሯቸው ፡ ነበር ። በኋላም ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዐርፈው ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ አካሄዳቸውን ፡ ሳይለውጡ ፡ በዐድዋም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሞያ ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ ልጃቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ሸዋ ፡ ረጋን ፡ ባ1884 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ድረው ፡ ባለሟል ፡ አደረጓቸው ።

## ስለ ፡ ራስ ፡ በዛብኽ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

ራስ ፡ በዛብኽ ፡ የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ ናቸው። ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከእምባቦ ፡ ዘመቻ ፡ ወዲህ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ በፍቅር ፡ ሲኖሩ ፡ ባ1893 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጥር ፡ 3 ፡ ቀን ፡ ዐርፈው ፡ በከተማቸው ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ተቀበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ ይገዙት ፡ የነበረውን ፡ ሰፊ ፡ ግዛት ፡ ለመግዛት ፡ ካባታቸው ፡ ተቀያይመው ፡ በሸዋ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩት ፡ የበኵር ፡ ልጃቸው ፡ ራስ ፡ በዛብኽ ፡ የማይመጥኑ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዳሞትን ፡ አገው ፡ ምድርን ፡ ሜጫን ፡ አቻፈርን ፡ አንሥተው ፡ ለራስ ፡ ቢትወደድ ፡ መንገሻ ፡ አቲከም ፡ ሰጥተው ፡ የጐጃምን ፡ ግዛት ፡ ለራስ ፡ በዛብኽ ፡ ሰጧቸው ። ወዲያውም ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ የልጃቸውን ፡ የወይዘሮ ፡ ሸዋ ፡ ረጋን ፡ ልጅ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበ ፡ ወርቅን ፡ በሚስትነት ፡ ዳሩላቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡ መጋባታቸው ፡ ደስ ፡ ቢያሰኛቸው ፡ ያባታቸው ፡ ግዛት ፡ የነበረው ፡ በመከፈሉ ፡ ቅር ፡ ብሏቸው ፡ ነበርና ፡ በዚሁ ፡ ስለ ፡ ሸፈቱ ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ አፍቀራ ፡ ተላኩ ።

## ስለ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ።

ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልጅ ፡ የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ አክሥት ፡ የወይዘሮ ፡ አያኽሉሽም ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። አባታቸውም ፡ አቶ ፡ አቦዬ ፡ ይባላሉ ። ዕድገታቸው ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ቤት ፡ ስለሆነ ፡ በታማኝነትና ፡ በመታዘዝ ፡ ለጌታቸው ፡ አገልግለዋል ። ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተባለውን ፡ ከፋን ፥ ኵሎን ፥ ኰንታን ፥ ሊሙን ፡ ስላቀኑ ፡ በከፋ ፡ የራስነት ፡ ማዕርግ ፡ አግኝተዋል ። ከዚያም ፡ እስከ ፡ ነጭ ፡ አባይ ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ ተክለዋል ።

ንጉሥ ፡ ከተባሉ ፡ ወዲህ ፡ የተገጠመላቸው ።

የንጉሥ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡

አባ ፡ ሰጉድ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
የኵሎው ፡ ደጃዝማች ፡ የከፋው ፡ ራስ ፡
ዘውዲቱን ፡ ተመኘ ፡ ዝምድና ፡ ሊያፈርስ ።

ሰጉድ ፡ ሃይማኖቱን ፡ እያለመሰከረ ፡
ጠመንጃ ፡ አልተኰሰ ፡ ጦር ፡ አልወረወረ ፡
ኵሎንና ፡ ከፋን ፡ በዘንግ ፡ አስገበረ ።

ግብር ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ የላዩም ፡ የታቹ ፡
በዘንግ ፡ ተሰብስበው ፡ መጥተው ፡ ቢከማቹ ፡
ካህን ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ያሙታል ፡ ሰዎቹ።

ፊት ፡ ኵሎንና ፡ ኰንታን ፡ አቅንተው ፡ ከፋን ፡ ሰጥተው ፡ አስለቅቀዋቸው ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ደግሞ ፡ ራስ ፡ ተሰማ ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ሞግዚትነት ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ስለሆኑ ፡ በክረምት ፡ ከፋን ፡ አስለቅቀው ፡ ጐንደር ፡ ቢሰዷቸው ፡ ገጣሚ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ኣባ ፡ ሰጉድ ፡ ወልዴ ፡ ሆድህን ፡ ሆድ ፡ አይባሰው ፡
ወትሮም ፡ ልማድህ ፡ ነው ፡ እያቀናህ ፡ ለሰው ፡

መተማና ፡ ከሰላ ፡ ይመጣሉ ፡ ብሎ ፡ ኣዳምጦ ፡ ነበረና ፡

ሁሉን ፡ እየገዛህ ፡ ብትገሠግሥ ፡
ጐንደር ፡ ዘውድ ፡ ገዝተህ ፡ ከሆንክ ፡ ንጉሥ ፡
አንድ ፡ ዓረብ ፡ ቀርቶሃል ፡ የጐራዴህ ፡ ልብስ ።

ያባ ፡ ሰጉድ ፡ ጠዶ ፡ የጣና ፡ ባሕር ፡
ቢቀዱት ፡ ቢቀዱት ፡ አይጕል ፡ ዘወትር ፡
ከፋ ፡ ተበጥብጦ ፡ ተጠጣ ፡ ጐንደር ።

ዓፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከደብረ ፡ ታቦር ፡ ጀምሮ ፡ የቈረቈሩት ፡ ከተማ ፡ 20 ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ ደንቀዝን ፡ መርጠው ፡ ቦታነቷ ፡ 4 ፡ ማዕዘን ፡ የምታሳይ ፡ ስለሆነች ፡ ዋና ፡ ከተማቸውን

፡ እሷን ፡ አድርገው ፡ ነበር ። ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስም ፡ ከጠፉች ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ስላደሷት ፡ ገጣሚ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ተመርጣ ፡ የነበር ፡ ከሐያ ፡ ከተማ ፡
ደንቀዝ ፡ ጠፋችና ፡ ድምጧ ፡ ሳይሰማ ፡
እንደገና ፡ አበበች ፡ በሰጉድ ፡ ዓላማ ።

እንደ ፡ ድብ ፡ አንበሳ ፡ ተፈራ ፡ ግርማህ ፡
ደንቀዝ ፡ ቢያጉረመርም ፡ ሰጉድ ፡ ፈረስህ ፡
ተሸበረ ፡ አሥመራ ፡ መስሎት ፡ የመጣህ ።

ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቈራጭ ፡ ይሁኑ ፡ በተባለ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ አዝማሪ ።

እጅግ ፡ ያምር ፡ ነበር ፡ የራስ ፡ ቈንደላቸው ፡
ቶሎ ፡ እንዲሸብቱ ፡ ለምን ፡ ቈረጧቸው ።

## ስለ ፡ ራስ ፡ ወሌ ።

ራስ ፡ ወሌ ፡ ብጡል ፡ የእቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ታናሽ ፡ ወንድም ፡ የየጁ ፡ ባላባት ፡ ናቸው ። በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ የተከበሩ ፡ ከመሆናቸው ፡ በስተቀር ፡ በዠግንነት ፡ ስመ ጥሩ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተገጠመላቸው ።

ሰባት ፡ ደጃዝማች ፡ ዐሥር ፡ ፊታውራሪ ፡ የጠመቀውን ፡

የወሌ ፡ ፈረስ ፡ ጠጣው ፡ ብቻውን ።

ወሌ ፡ በቡሎ ፡ ዘሎ ፡ ሲወጣ ፡
ይመስላል ፡ ሐምሌ ፡ ክረምት ፡ የመጣ ፡
ወሌ ፡ ወሌ ፡ ወሌ ፡ ቢሏችሁ ፡
የወረ ፡ ባቦ ፡ አይምሰላችሁ ፡
የሳቱ ፡ ጉማጅ ፡ መርጦ ፡ አለላችሁ።
የወሌ ፡ ፈረስ ፡ ቀጭኑ ፡ ቡሎ ፡

ኸራቱ ፡ አውሳ ፡ ግንባሩ ፡ ወሎ ።

ከነዚህም ፡ እላይ ፡ ከተባሉት ፡ በቀር ፡

- ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ተሰማ ፥
- ራስ ፡ ወልዴ ፥
- ራስ ፡ ስብሐት ፥
- ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ መንገሻ ፡ አቲከም ፥
- ራስ ፡ ጉበና ፥
- ደጃዝማች ፡ ገርማሜ ፥
- አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ነሲቡ ፥
- ራስ ፡ ደምስ ፥
- ራስ ፡ አባተ ፥
- ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፥
- ደጃዝማች ፡ በሻኽ ፡ አቦዬ ፥
- ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፥
- ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፥
- ደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ወርቄ ፥
- ደጃዝማች ፡ ለማ ፥
- ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፥
- ደጃዝማች ፡ ሉል ፡ ሰገድ ፥
- ከንቲባ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፥
- አዛዥ ፡ መታፈሪያ ፥
- ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ ተወንድ ፡ በላይና ፡

ሌሎችም ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ። ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ መኳንንት ፡ ተከብረውና ፡ ተፈርተው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸውን ፡ አሳለፉ። ዙፋናቸውንም ፡ ለመቀናቀን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ቢፈትኑ ፡ ሊከናወንላቸው ፡ አልቻለም ። ስማቸውም ፡ በዓለም ፡ ስለ ፡ ታወቀ ፡ እንደዚህ ፡ ተብሎ ፡ ተገጠመላቸው ።

ይገድሉኻም ፡ ይቈርጡኻም ፡ እንደሁ ፡ ይኸው ፡ ቆምሁልዎ ፡
ያለምጣም ፡ ምኒልክ ፡ ብዬ ፡ ሰደብኩዎ ።

ወትሮም ፡ ትልቅ ፡ ነበር ፡ ሰሎሞን ፡ ባባቱ ፡
ምኒልክ ፡ በለጠ ፡ ሰው ፡ ይዞ ፡ መብላቱ ፡፡
መካኖቹ ፡ ብዙ ፡ በሮም ፡ በሶርያ ፡
ወላድ ፡ እጅግ ፡ አየሁ ፡ በኢትዮጵያ ፡፡

# ምዕራፍ ፡ 39 ፡፡

## የጅቡቲ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሐዲድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥልጣኔ ፡ ምልክት ፡፡

ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ግንኙነታቸውን ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥትና ፡ ከመላክተኞቹ ፡ ካቋረጡ ፡ ወዲህ ፡ ከፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ወዳጅነት ፡ ዠመሩ ፡፡ ለዚሁም ፡ ለፈረንሳዊና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ወዳጅነት ፡ አማካይ ፡ የነበሩት ፡ የጅቡቲ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ የነበረው ፡ ላጋርድ ፡ የስዊስ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ መሐንዲሱ ፡ ሙሴ ፡ ኢልግ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ተወላጅ ፡ ሙሴ ፡ ሽፍኔ ፡ የመስኮብ ፡ ተወላጅ ፡ ሌዎንቴፍ ፡ ነበሩ ፡፡ እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ምንም ፡ ነገዳቸው ፡ ቢለያይ ፡ ባንድ ፡ በፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ጥላ ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ የፈረንሳዊን ፡ መንግሥት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ አዛምደው ፡ ከግል ፡ ጥቅማቸው ፡ በቀር ፡ ፈረንሳዊም ፡ ከኢጣሊያና ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ይልቅ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጥቅም ፡ እንድታገኝ ፡ ይጥሩ ፡ ነበር ፡፡

ስለዚህ ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ በምክርም ፡ በመሣሪያም ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክን ፡ እየረዱ ፡ ከውጫሌ ፡ ውልም ፡ 17ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ የመንግሥቴን ፡ የትክክለኛነት ፡ መብት ፡ ይነካብኛል ፡ ብለው ፡ ሲከራከሩ ፡ እነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ ውስጡን ፡ በመምከር ፡ ሳይደረቡ ፡ የቀሩ ፡ አይመስሉም ፡፡

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ለዐድዋ ፡ ዘመቻ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሲቀረው ፡ ባ1886 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በመጋቢት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ለመሐንዲሱ ፡ ለሙሴ ፡ ኢልግ ፡ ከጅቡቲ ፡ እስከ ፡ ሐረር ፡ ከሐረር ፡ እስከ ፡ እንጦጦ ፡ ከእንጦጦ ፡ እስከ ፡ ከፋ ፡ ከዚያም ፡ እስከ ፡ ነጭ ፡ ዓባይ ፡ ድረስ ፡ የሐዲድ ፡ መንገድ ፡ እንዲዘረጋ ፡ በውል ፡ ፈቀዱለት ፡፡ ሙሴ ፡ ኢልግም ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ ከሽፍኔና ፡ ከሌዎንቴፍ ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ውል ፡ ያገኘው ፡ ጥቅም ፡ በ4ኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ በዚሁ ፡ ሐዲድ ፡ ከሚገባውም ፡ ከሚወጣውም ፡ የንግድ ፡ ሸቀጥ ፡ ከ2 ፡ ዐሥር ፡ እንዲያገኝና ፡ ባ10ኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ከጅቡቲ ፡ ወደ ፡

ሐረር ፡ ከሐረር ፡ ወደ ፡ ጅቡቲ ፡ ሸቀጥ ፡ አመላላሹም ፡ በተለይ ፡ የርሱ ፡ ማኅበር ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ ነበር ።

ደግሞም ፡ ከዚህ ፡ ርሱ ፡ ካደረገው ፡ ውል ፡ በቀር ፡ ከህንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ባሕር ፡ ዳርና ፡ ከኤርትራ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ነጭ ፡ ዐባይ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ የሚዘረጋ ፡ የሐዲድ ፡ ውል ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ሌላ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ማኅበር ፡ እንዳይዋዋል ፡ በ3ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ተከልክሎ ፡ ነበር ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ለስሙ ፡ ከጅቡቲ ፡ እስከ ፡ ነጭ ፡ ዐባይ ፡ ድረስ ፡ ቢዋዋሉ ፡ ለጊዜው ፡ ንጉሡ ፡ እንዲሠራ ፡ የፈቀዱለት ፡ ከጅቡቲ ፡ እስከ ፡ ሐረር ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሙሴ ፡ ኢልግና ፡ ጓደኞቹ ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ቀዋሚ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ገንዘብ ፡ ካገኙ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመልሰው ፡ ሥራቸውን ፡ ሲሠሩ ፡ ቈይተው ፡ በኋላም ፡ በገንዘብ ፡ እጦት ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እያቆሙ ፡ በብዙ ፡ ችግር ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ለመሥራት ፡ ቻሉ ።

በ3ኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ የውሉ ፡ ጊዜ ፡ የሚቈየው ፡ እስከ ፡ 99 ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ዓመት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ማኅበሩ ፡ ለሥራው ፡ ያወጣውን ፡ ገንዘብ ፡ ሳይጠይቅ ፡ የሐዲዱን ፡ መንገድ ፡ ከሙሉ ፡ መሣሪያው ፡ ጋራ ፡ በጭራሽ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ለቆ ፡ እንዲሄድ ፡ ባ14ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ተረጋግጧል ።

ሙሴ ፡ ኢልግ ፡ ይህን ፡ ውል ፡ ስላገኘ ፡ በመዠመሪያ ፡ 100 ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንዲከፍል ፡ በ3ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ውል ፡ ገብቷል ።

ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ በግራኝ ፡ ጊዜ ፡ የሄደውን ፡ አገር ፡ አቅንተው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መልሰው ፡ የዐድዋንም ፡ ድል ፡ ካገኙ ፡ ወዲህ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ፍጹም ፡ የሰላም ፡ መንግሥት ፡ ሆነ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የኤውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሄደው ፡ ባይናቸው ፡ ባያዩ ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ በዦሯቸው ፡ ሰምተው ፡ ነበርና ፡ አገራቸውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደዚሁ ፡ ለማሠልጠን ፡ አስበው ፡ ከኤውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ከእንግሊዝ ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ከመስኮብ ፡ ከጀርመን ፡ ከሌሎችም ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ አድርገው ፡ ስለ ፡ ንግድና ፡ ስለ ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ ተዋዋሉ ። በኢትዮጵያም ፡ የሐኪም ፡ ቤት ፡ የስልክና ፡ የፖስታ ፡ ቤት ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ባንክ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ አውቶሞቢል ፡ የስፌት መኪና ፡ ዕንጨት የሚሠነጥቅ መኪና ፡ የእኽል ወፍጮ ፡ የሳሙና ፋብሪካና ፡ ይኸን የመሳሰለውን ፡ በዘመናቸው ፡ እያለመጡና ፡ እያሠሩ ፡ አሳዩ ። ጥቂትም ፡ ቢሆን ፡ በመልካቸው ፡ ብር ፡ አስቀረጹ

። ግቢያቸውንም ፡ ከጥንቱ ፡ ኣሻሽለው ፡ ሠራተኞችን ፡ በደመወዝ ፡ እየቀጠሩ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱንና ፡ የግብር ፡ መብሊያውን ፡ አዳራሽ ፡ አሠሩ ። ሌላም ፡ ብዙ ፡ ቤትና ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ አሳነጹ ።

እንደ ፡ ኤውሮፓም ፡ ደንብ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉትን ፡ በየክፍሉ ፡ ሚኒስትርነት ፡ ሾሙ ።

1. ፡ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ነሲቡ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትር ።
2. ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትር ።
3. ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ከተማ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ።
4. ፡ ነጋድራስ ፡ ኀይለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የውጭ ፡ ጕዳይና ፡ የንግድ ፡ ሚኒስትር።
5. ፡ በጅሮንድ ፡ ሙሉ ፡ ጌታ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ።
6. ፡ ከንቲባ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ የርሻና ፡ የመሥሪያ ፡ ሚኒስትር ።
7. ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ።
8. ፡ ኣዛዥ ፡ መታፈሪያ ፡ የግቢ ፡ ሚኒስትር ።
9. ፡ ቀኛዝማች ፡ መኰንን ፡ ተወንድ ፡ በላይ ፡ የሥራ ፡ ሚኒስትር ።
10. ፡ ደግሞ ፡ ሚኒስትር ፡ ሳይሾምባቸው ፡ ባዋጅ ፡ የተቋቋሙ ፡ ለስልክ ፡ ሚኒስትር ፡ (ልጅ ፡ በየነ ፡ ይመር ፡ ሹም ፡ ተብለውበት ፡ ነበር) ።
11. ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥራው ፡ ብቻ ፡ ታውጆ ፡ ሹም ፡ ገና ፡ አልተደረገበትም ።

# ምዕራፍ ፡ 40

## <u>የሦስቱ ፡ መንግሥታት ፡ ስምምነት ።</u>

ኢትዮጵያን ፡ በቅኝ ፡ አገራቸው ፡ የሚያዋስኗት ፡ የእንግሊዝና ፡ የፈረንሳዊ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ አድርገው ፡ ብዙ ፡ የንግድና ፡ የወዳጅነት ፡ ውል ፡ ሲዋዋሉ ፡ ቈይተዋል ። በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የክብርና ፡ የወዳጅነታቸውን ፡ ከፍተኛነት ፡ ሲያበላልጡ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የጦር ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ አሰልፈው ፡ ባይዋጉ ፡ በዲፕሎማቲክ ፡ በኩል ፡ የሦስቱ ፡ መንግሥታት ፡ የፖለቲካ ፡ መሪዎች ፡ የጠበቀ ፡ ውጊያ ፡ ሲያደርጉ ፡ ኖረዋል ። ከሦስቱ ፡ አንደኛው ፡ መንግሥት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ በውልና ፡ በወዳጅነት ፡ ሲተሳሰር ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ ኣንድነት ፡ ሆነው ፡ ባ1 ፡ ፖለቲካ ፡ በኩል ፡ እጃቸውን ፡ አግብተው ፡ የፖለቲኩን ፡ ቍጥር ፡ ይፈቱበታል ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከኢትዮጵያም ፡ ጋራ ፡ ያለኢትዮጵያም ፡ በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተዋዋሉትን ፡ ውል ፡ ከዚህ ፡ አሁን ፡ ከሚያደርጉት ፡ ውል ፡ ጋራ ፡ አስማምተው ፡ የሦስቱን ፡ መንግሥታት ፡ የቈየ ፡ ክርክር ፡ የሚያስታርቅ ፡ ውል ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ ባ1906 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ታኅሣሥ ፡ 13 ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ 1899 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ታኅሣሥ ፡ 5 ፡ ቀን ፡ የ3ቱ ፡ መንግሥታት ፡ መላክተኞች ፡ ሎንዶን ፡ ላይ ፡ «የሦስቱ ፡ መንግሥታት ፡ ስምምነት» ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ ውል ፡ ተዋዋሉ ፡፡ የውሉም ፡ ዋና ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ 3ቱ ፡ መንግሥታት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥቅም ፡ ለመካፈል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነትና ፡ የንጉሡን ፡ ሥልጣን ፡ የሕዝቡንም ፡ መብት ፡ አንነካም ፡ ሲሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንዳለ ፡ ተዋዋሉ ፡፡

1ኛ. ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በዓባይ ፡ ውሃና ፡ ከዓባይም ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ግብጽና ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ በ ሚወርደው ፡ ውሃና ፡ በዚያ ፡ ይዞታ ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ በጥቅም ፡ በኵል ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲኖረው ፡፡

2ኛ. ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ከጅቡቲ ፡ ባለው ፡ በቅኝ ፡ አገሩ ፡ ይዞታ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዠመረው ፡ የሐዲድ ፡ መንገድ ፡ መሠረት ፡ ለሐዲዱ ፡ መፈጸሚያና ፡ ለመመላለሻ ፡ የሚሆነውን ፡ መንገድና ፡ ስፍራ ፡ እንዲያገኝ፡፡

3ኛ. ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ በኤርትራና ፡ በደቡብም ፡ በሱማሊያ ፡ በኵል ፡ ያለውን ፡ ይዞታ ፡ ተከትሎ ፡ ብዙ ፡ ስፍራ ፡ እንዲያገኝ» ፡፡

ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ የሚናገረው ፡ አራተኛው ፡ አንቀጸ ፡ ሆኖ ፡ በቀሩት ፡ አንቀጾች ፡ ደግሞ ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ የሚዘረጋው ፡ ሐዲድ ፡ ከጅቡቲ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ድረስ ፡ እንጂ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ላያልፍ ፡ ከተስማሙ ፡ በኋላ ፡ እንዲሁም ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምዕራብ ፡ አገር ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ምዕራብ ፡ በኵል ፡ አድርጎ ፡ ከበናዲርና ፡ ከኤርትራ ፡ ጋራ ፡ የሚገናኝ ፡ የሐዲድ ፡ መንገድ ፡ ለመዘርጋት ፡ እንደሚችሉ ፡ የተስማሙበት ፡ ነው ፡፡

ይህንንም ፡ ውል ፡ ተዋውለው ፡ በገሃድ ፡ እንዲታወቅ ፡ በገለጹት ፡ ጊዜ ፡ የቀሩት ፡ መንግሥታት ፡ በጋዜጣና ፡ በንግግር ፡ ለመውቀሥ ፡ አልቦዘኑም ፡፡

የ3ቱ ፡ መንግሥታት ፡ ወኪሎችም ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ተፈራረሙ ፡ እርስ ፡ በእርሳቸው ፡ የየራሳቸውን ፡ ድርሻ ፡ አሳንሶ ፡ በመገመት ፡ ቅር ፡ ብሏቸው ፡ ነበር ፡፡

ይልቁንም ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ኤ ፡ ቍጥር ፡ ባ1881ና – 84 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ሎንዶን ፡ ላይ ፡ ያደረገው ፡ ውል ፡ በፕረንሲፕ ፡ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ በኢጣሊያ ፡ ውስጥ ፡ እንድትሆን ፡ ይፈቅድላት ፡ ነበር ፡ ሲሉ ፡ የ3ቱን ፡

መንግሥታት ፡ ስምምነት ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ ሆኖ ፡ የተፈራረመውንና ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትሩን ፡ ቲቶኒ ፡ የሚባለውን ፡ ብዙ ፡ የኢጣሊያ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ በምክር ፡ ቤቱ ፡ ስብሰባ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ በገሃድ ፡ ወቀሡት ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ነገሩ ፡ 1 ፡ ጊዜ ፡ በስምምነት ፡ የተፈጸመ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የ3ቱ ፡ መንግሥታት ፡ ወኪሎች ፡ ተስማምተው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ነገሩን ፡ እንዲያውቁትና ፡ ባሳቡ ፡ እንዲተባበሩበት ፡ የስምምነቱ ፡ 1 ፡ ግልባጭ ፡ ተላከላቸው ።

ዳግማዊ ፡ ምኒልክም ፡ የ3ቱን ፡ መንግሥታት ፡ ስምምነት ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ አስነብበው ፡ ከተረዱት ፡ በኋላ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ሥልጣንና ፡ መብት ፡ አንነካም ፡ በሚለው ፡ በመዠመሪያው ፡ አንቀጸ ፡ ንግግር ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ መሰኘታቸውን ፡ ከምስጋና ፡ ጋራ ፡ ገልጸው ፡ በቀረው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መላክተኛ ፡ በሌለበት ፡ ብቻችሁን ፡ በተስማማችሁበት ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ሊያስገድደኝ ፡ የሚችል ፡ የለም ፡ ብለው ፡ በዚሁ ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ 1899 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ለ3ቱ ፡ መንግሥታት ፡ መልሱን ፡ በደብዳቤ ፡ አስታወቁ ።

# ምዕራፍ ፡ 41 ።

## የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታመም ፡ - የእቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ሥልጣን ፡ -የደጃች ፡ አብርሀ ፡ አርአያ ፡ መሸፈት ።

ከመሬት ፡ የተፈጠረና ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የገነነና ፡ ስሙ ፡ የታወቀ ፡ በሕዝብም ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ቢሆን ፡ ከሕመምና ፡ ከሞት ፡ ሊያመልጥ ፡ አይችልምና ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በብዙ ፡ አኳኋን ፡ ካሻሻሏት ፡ በኋላ ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ የሚደርሰው ፡ ሕመም ፡ በእሳቸውም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ካ1900 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከነሐሴ ፡ ወር ፡ አንሥቶ ፡ ታመው ፡ እቤት ፡ መዋል ፡ ዠመሩ ። በሽታቸውም ፡ የደም ፡ መበላሸትና ፡ የአንዠት ፡ በሽታ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ወዲያው ፡ ጠበል ፡ ይፈውሳቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማለት ፡ ባ1901 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ አውርደዋቸው ፡ በዚያ ፡ ጠበሉን ፡ እየጠጡ ፡ ሲታመሙ ፡ በከተማው ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ በጥርጥር ፡ ሞተዋል ፡ እያለ ፡ ያወራ ፡ ዠመር ።

ስለዚህ ፡ የሕዝቡን ፡ ልብ ፡ ለማርጋት ፡ ሲባል ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በየካቲት ፡ 5 ፡ ቀን ፡ ተመልሰው ፡ በቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ሆነው ፡ መዠመሪያ ፡ ሙሴ ፡ ሐርሚኒዬር ፡ የሚባለው ፡ ሐኪም ፡ ቀጥሎም ፡ የኢትዮጵያው ፡ ተወላጅ ፡ ሐኪም ፡ ወርቅነሽ ፡ እሸቱ ፡ እያከሟቸው ፡ ይታመሙ ፡ ዠመር ።

እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ የራሳቸውን ፡ ዘመዶችና ፡ የወንድማቸውን ፡ የራስ ፡ ወሌን ፡ ልጆች ፡ ከየመኳንንቱ ፡ እያጋቡ ፡ ወገናቸውን ፡ አበርክተው ፡ ነበርና ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ በጃቸው ፡ ይዘው ፡ በሁሉም ፡ ነገር ፡ ለማዘዝ ፡ አሰቡ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መንግሥቱን ፡ እይዛለሁ ፡ እያሉ ፡ ያስባሉ ፡ እየተባለ ፡ ይወራ ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ በእቴጌ ፡ ጣይቱና ፡ በመኳንንቱ ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ አልተገኘም ፡ ነበርና ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ወደ ፡ እየራሳቸው ፡ ሤራ ፡ ለመማረክ ፡ የቀሩትን ፡ መኳንንቶችና ፡ ሹማምቶች ፡ በማባበል ፡ ይሻሟቸው ፡ ነበር ። ወዲያውም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በንግድ ፡ ምክንያት ፡ የመጡት ፡ ጀርመኖች ፡ በምድረ ፡ ግቢው ፡ በጣም ፡ ታውቀው ፡ ነበሩና ፡ የታመሙት ፡ በመድኀኒት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አወሩ ።

ከዚህም ፡ ከዐድማው ፡ አስቀድመው ፡ ባ1901 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግንቦት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ ደጃዝማች ፡ አባተ ፡ ዋግ ፡ ሹም ፡ ተብለው ፡ ሰቈጣን ፡ በግዛት ፡ ትግሬን ፡ በቍራጭነት ፡ ተሾሙ ።የመቀሌ ፡ ገዥ ፡ የነበሩትም ፡ ደጃዝማች ፡ አብርሀ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ነበሩ ። ክረምቱን ፡ ከርመው ፡ በጥቢው ፡ ራስ ፡ አባተና ፡ ደጃዝማች ፡ አብርሀ ፡ ወደ ፡ ግዛታቸው ፡ ለመሄድ ፡ ተነሡ ። ከመንገድም ፡ ሲደርሱ ፡ ደጃዝማች ፡ አብርሀ ፡ አስቀድመው ፡ ሄደው ፡ ላዲሱ ፡ ዋግ ፡ ሹም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ አቀባበል ፡ እንደሚያደራጁ ፡ አስመስለው ፡ ተሰናብተው ፡ ቀድመው ፡ ሄዱ ። መቀሌ ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የደጃዝማች ፡ አብርሀ ፡ መሸፈት ፡ ታወቀ ። ዋግ ፡ ሹም ፡ አባተ ፡ ኰረም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ደጃዝማች ፡ አብርሀ ፡ ጦር ፡ ሠርተው ፡ ከበቧቸውና ፡ ውጊያ ፡ ሆነ። መስከረም ፡ 29 ፡ ቀን ፡ 1902 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቅዳሜ ፡ ሌሊቱን ፡ ዠምረው ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ከቀኑ ፡ ባ4 ፡ ሰዓት ፡ ደጃዝማች ፡ አብርሀ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ተማረኩ ።

ቀጥሎም ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ተልከው ፡ በክዳታቸው ፡ ተፈርዶባቸው ፡ ጥቂት ፡ ጊዜያት ፡ ሰላሌ ፡ ሸንኲርት ፡ ላይ ፡ በእስረኛነት ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ምሕረት ፡ ተደርጎላቸው ፡ ተለቀቁ ። ቀጥሎም ፡ በአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ጊዜ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ በማዕርግ ፡ ተቀመጡ ። ደጃዝማች ፡ አብርሀ ፡ በቶሪኖ ፡ ከተማ ፡ ሲማሩ ፡ ያደጉ ፡ የትልቁ ፡ የራስ ፡ አርኣያ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። ዋግ ፡ ሹም ፡ አባተም ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ እንዲመጡ ፡ ተጠርተው ፡ ነበርና ፡ በዚያው ፡ ዘመን ፡ ባ1902 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ከኰረም ፡ ተነሥተው ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የትግሬ ፡ ቍራጭነት ፡ በእቴጌዪቱ ፡ ሥልጣን ፡ ለራስ ፡ ወሌ ፡ ተሰጣቸው ። ዋግ ፡ ሹም ፡ አባተ ፡ ጅሩ ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ የእቴጌዪቱ ፡ ምስለኔ ፡ አዛዥ ፡ ዛማኔልና ፡ የጅሩው ፡ ሻለቃ ፡ አዛዥ ፡ መሸሻ ፡ ከእቴጌ ፡ ተልከው ፡ ሄደው ፡ በዚያው ፡ ታግደው ፡ እንዲቈዩ ፡ አደረጓቸው ። እቴጌዪቱ ፡ ይህንን ፡ ማድረጋቸው ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ስለ ፡ ቤት ፡ መንግሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ በመኳንንቱና ፡ በርሳቸው ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ ተነሥቶ ፡ ነበርና ፡ ዋግ ፡ ሹም ፡ አባተ ፡ ባድማው ፡ እንዳይጨመሩ ፡ ለማቆየት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ወዲያው ፡ መጋቢት ፡ 12 ፡ ቀን ፡ የእቴጌዪቱ ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ ወደቀ ፡ ዋግ ፡ ሹም ፡ አባተ ፡ እነዚያን ፡ ሊጠብቋቸው ፡ የመጡትን ፡ 2ቱን ፡ አዛዦች ፡ እንደ ፡ እስረኛ ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገቡ ።

# ምዕራፍ ፡ 42 ።

## የአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ኣልጋ ፡ ወራሽነት ፡ የራስ ፡ ተሰማ ፡ ዕረፍት ፡ በመኳንንቱ ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ ክርክር ፡ የራስ ፡ አባተ ፡ መያዝ ፡ የአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ወደ ፡ ጊሚራ ፡ መሄድና ፡ መመለስ ፡ የፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ግጭት ፡ - የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዕረፍት ፡ የራስ ፡ ሚካኤል ፡ ንጉሥ ፡ መባል ፡ የራስ ፡ ስብሐትና ፡ የደጃች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ መዋጋት ።

ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ በዙፋናቸው ፡ የሚተካ ፡ ከባሕርያቸው ፡ የተከፈለ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ስላልነበራቸው ፡ ያክሥታቸውን ፡ የወይዘሮ ፡ ተናኘ ፡ ወርቅን ፡ ልጅ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንንን ፡ የአልጋዬ ፡ ወራሽ ፡ ይሆነኛል ፡ እያሉ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጓቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሐሳብ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ጊዜው ፡ ገና ፡ አልደረሰም ፡ ነበርና ፡ ለወራሽነት ፡ የታሰቡት ፡ ካውራሹ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ከሴት ፡ ልጃቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ሸዋረጋ ፡ ለተወለዱት ፡ ለልጅ ፡ ኢያሱ ፡ አልጋቸውን ፡ ለማውረስ ፡ ኣስበው ፡ በቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ እንዲኖሩ ፡ ኣደረጉ ። ሕመማቸው ፡ እየጸናባቸው ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ጠበል ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ባ19101 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግንቦት ፡ 10 ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ወራሻቸው ፡ ነገር ፡ የተጻፈ ፡ ቃል ፡ ለመኳንንቱና ፡ ለሕዝቡ ፡ በጃንሜዳ ፡ ላይ ፡ በጉባኤ ፡ እንዲነበብ ፡ አደረጉ ።

በዚያም ፡ በተነበበው ፡ ቃል ፡ የወራሹ ፡ ስም ፡ ተገልጾ ፡ ስላልተጠራና ፡ «ከልጄ ፡ ጋራ ፡ ሆናችሁ ፡ አገራችሁን ፡ ጠብቁ» የሚል ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ወራሹ ፡ ማን ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ ሕዝቡ ፡ በየሐሳቡ ፡ ይጨነቅ ፡ ዠመር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የወራሹ ፡ ስም ፡ እንዳይገለጽ ፡ ያደረጉ ፡ እቴጌዪቱ ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ፡ እየተባለ ፡ ይወራ ፡ ነበር ። እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ጥርጥር ፡ ክረምቱ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ጃንሆይ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ሕመማቸው ፡ እየጸናባቸው ፡ ሄደና ፡ ጥቅምት ፡ 17 ፡ ቀን ፡ 1902 ፡ ዓ ፡ ም ፡ አንደበታቸው ፡ ተይዞ ፡ የማይናገሩ ፡ ሆነ ። በዚህም ፡ ሕዝቡ ፡ አዝኖ ፡ ሳለ ፡ ከ3 ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ስለ ፡ ተሻላቸው ፡ ጥቅምት ፡ 20 ፡ ቀን ፡ የግርማዊነታቸው ፡ ቃል ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ኣዳራሽ ፡ ለመኳንንቱ ፡ ተነበበላቸውና ፡ የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ወራሽነት ፡ የራስ ፡ ተሰማ ፡ ሞግዚትነት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተረጋገጠ ።

የጃንሆይም ፡ ቃል ፡ ለመኳንንቱና ፡ ለገሚሱ ፡ ሕዝብ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አዳራሽ ፡ ከተነገረ ፡ በኋላ ፡ በግቢው ፡ ለተሰበሰበው ፡ ለመላው ፡ ሕዝብም ፡ በግልጽ ፡ ተነገረ ። በየዳር ፡ አገር ፡ ላለው ፡ መኳንንትና ፡ ሕዝብ ፡ ግልባጩ ፡ በማኅተም ፡ እየሆነ ፡ ተላለፈ ። መኳንንቱም ፡ ያዋጁን ፡ ቃል ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ጃንሆይ ፡ በጤናቸው ፡ ባይሆኑ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ኀዘን

፡ ተሰምቷቸው ፡ ነበርና ፡ ጥርጣሬ ፡ እንዳያድርባቸው ፡ በማለት ፡ ጃንሆይ ፡ ወደ ፡ ተኙበት ፡ እልፍኝ ፡ እየገቡ ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ እጅ ፡ እየነሡ ፡ እንዲያልፉ ፡ ተደረገ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ እይዛለሁ ፡ ብለው ፡ ከሚያስቡት ፡ ጋራ ፡ ይህ ፡ እላይ ፡ የተባለው ፡ ዐዋጅ ፡ ሳይስማማ ፡ በመቅረቱ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ሥልጣን ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ተሰማ ፡ በመዞሩ ፡ እቴጌዪቱ ፡ ደስ ፡ አልተሰኙም ፡ ነበር ። ለእቴጌዪቱም ፡ የምክር ፡ ረዳቶች ፡ የነበሩት ፡ በየጁ ፡ ግዛታቸው ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ወንድማቸው ፡ ራስ ፡ ወሌና ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ የነበሩት ፡ የራስ ፡ ወሌ ፡ ልጅ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ደጃች ፡ አያሌውና ፡ ዋግ ፡ ሹም ፡ ጓንጉል ፡ ዘገየ ፡ ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ተሰማ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስንና ፡ ራስ ፡ ደምስን ፡ ሌሎችንም ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ አጥቅተዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ መኳንንት ፡ ጨምረው ፡ ሕዝቡን ፡ አስነሥተው ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱን ፡ ከመንግሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ ለማስወጣት ፡ ሤራ ፡ አደረጉ ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ርዳታን ፡ ለማግኘት ፡ እቴጌዪቱ ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ መላላክ ፡ ዠምረው ፡ ነበርና ፡ ይህ ፡ ሥራቸው ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ የሕዝቡን ፡ ቍጣ ፡ እያበረታው ፡ ሄደ ።

ወዲያውም ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ በሚገኘው ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ስብሰባ ፡ አድርገው ፡ የሤራውን ፡ አኳኋን ፡ ተማክረው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ባ1902 ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጋቢት ፡ 14 ፡ ቀን ፡ እቴጌዪቱን ፡ ከመንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ እንዲርቊ ፡ መቈረጡን ፡ አስታወቋቸው ። እቴጌዪቱም ፡ እዚህ ፡ ከጠላችሁኝ ፡ ወደ ፡ ወንድሜ ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ወሌ ፡ ልሂድና ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ ልቀመጥ ፡ ብለው ፡ ልመና ፡ ቢያቀርቡ ፡ ከወንድማቸው ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ የልባቸውን ፡ ለመሥራት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዐውቀውባቸው ፡ የልመናውን ፡ ቃል ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ተሰማና ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አልተቀበሏቸውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከማናቸውም ፡ ሥልጣን ፡ ርቀው ፡ ባለቤታቸውን ፡ ጃንሆይን ፡ እያስታመሙ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ተወስነው ፡ እንዲቀመጡ ፡ ተቈረጠ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወሌ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ነበሩና ፡ የእቴጌዪቱ ፡ ዐድመኛ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ሁከት ፡ እንዳያደርጉ ፡ ተይዘው ፡ ታሰሩ ። ቀጥሎም ፡ ወደ ፡ ኣፍቀራ ፡ ተልከው ፡ ነበርና ፡ ከጥቂት ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ምሕረት ፡ አድርገውላቸው ፡ ተለቀቊ ። ደጃች ፡ አያሌውም ፡ በቤታቸው ፡ ሆነው ፡ 10 ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ በብስጭት ፡ ቈይተው ፡ ይቅርታ ፡ ለምነው ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ተሰማ ፡ መጡ ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ግንቦት ፡ 5 ፡ ቀን ፡ የከፋው ፡ ገዥ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በጌምድርንና ፡ ከጐጃም ፡ ክፍል ፡ አገውን ፡ ተሾመው ፡ በቶሎ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ እንዲዛወሩ ፡ ተደረገ ።

ከኰረም ፡ የተመለሱትም ፡ ዋግ ፡ ሹም ፡ አባተ ፡ ራስ ፡ ተብለው ፡ ከምባታንና ፡ አሩሲን ፡ ቈጫን ፡ ከመንዝ ፡ ግሼን ፡ ተሾሙ ።



ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የእቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ወንድም ፡ ራስ ፡ ወሌ ፡ በየጁ ፡ ግዛታቸው ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጋራ ፡ በግዛት ፡ ወሰን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ስለሚከራከሩ ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ ነበሩና ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ታመው ፡ ወራሹ ፡ የራስ ፡ ሚካኤል ፡ ልጅ ፡ ከሆነ ፡ አልገዛም ፡ ብለው ፡ ያምፃሉ ፡ እየተባለ ፡ ይፈራ ፡ ነበር ። በዚሁም ፡ ላይ ፡ ይኸው ፡ ሊወጋኝ ፡ ይዘጋጃል ፡ እያሉ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ስላስታወቁ ፡ ቢትወደድ ፡ ሉል ፡ ሰገድና ፡ ሊጋባ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ከየደንቡ ፡ የጦር ፡ ጭፍራ ፡ አስከትለው ፡ ራስ ፡ ወሌን ፡ ለመጥራት ፡ በክረምቱ ፡ ወደ ፡ የጁ ፡ ተጓዙ ። ከየጁ ፡ ድንበርም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የጥሪ ፡ ወረቀት ፡ ቢልኩባቸው ፡ አሁን ፡ አሞኛል ፡ እያሉ ፡ ሰላማዊ ፡ መልስ ፡ እየሰጡ ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡ በመላላክ ፡ ብቻ ፡ አሳለፉ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በበጌምድር ፡ ያለውን ፡ የራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ጦርና ፡ ከወሎ ፡ በኩል ፡ የመጣውን ፡ ጦር ፡ ተመልከተው ፡ መዋጋቱ ፡ ፍሬ ፡ እንዳይሰጣቸው ፡ አይተው ፡ እስካሁን ፡ መቄየቴ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ እንዳይወጋኝ ፡ በማለት ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ግን ፡ የጌታዬ ፡ የምኒልክ ፡ አሽከሮች ፡ ከመጣችሁ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ እሄዳለሁ ፡ ብለው ፡ በሰላማዊነት ፡ ተገናኝተው ፡ ባንድነት ፡ እየተጓዙ ፡ ባ1903 ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገቡ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከእቴጌዪቱ ፡ ጋራ ፡ ተላልከውት ፡ የነበረው ፡ ዕድማ ፡ ስለ ፡ ተገለጸባቸው ፡ ባደባባይ ፡ ተፈርዶባቸው ፡ ወደ ፡ አንኮበር ፡ እንዲሄዱና ፡ በግዞት ፡ እንዲቀመጡ ፡ ተደረገ ።

ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ተሰማ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ በሙሉ ፡ ይዘው ፡ ይሠሩ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ «ራስ ፡ ቢትውደድ ፡ ተሰማ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንንግሥት ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ» ፡ የሚልና ፡ በውስጡ ፡ አንበሳ ፡ ያለበት ፡ ማኅተም ፡ አሠርተው ፡ ያትሙ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ፍጻሜው ፡ ሞት ፡ ስለ ሆነ ፡ በድንገት ፡ ታመው ፡ ሚያዝያ ፡ 3 ፡ ቀን ፡ 1903 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዐረፉና ፡ ሬሳቸው ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሄዶ ፡ ተቀበረ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ኣቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ መኖሪያቸው ፡ በራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ተሰማ ፡ ግቢ ፡ ነበር ። ከርሳቸው ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ዋናው ፡ መኖሪያቸው ፡ ከዚያው ፡ ቢሆን ፡ በፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤትና ፡ በየሌሎቹም ፡ መኳንንት ፡ ቤት ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ አባተ ፡ መኳንንቱን ፡ ለምክር ፡ ሰብስበው ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ይዘን ፡ በምክር ፡ እያሳደግን ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ ባንድ ፡ ሞግዚት ፡ እንዲሠራ ፡ እናድርግ ፡ ሲሉ ፡ አሳብ ፡ አቀረቡ ። በዚህም ፡ አሳብ ፡ ከራስ ፡ አባተ ፡ ጋራ ፡ የተባበሩ ፡ እነጸሓፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴና ፡ እነነጋድራስ ፡ ይገዙ ፡ እነቀኛዝማች ፡ በየነ ፡ ሌሎችም ፡ ብዙ ፡ መኳንንት ፡ ነበሩ ። አቤቶ ፡ ኢያሱም ፡ ሤራ ፡ ወደ ፡ ተደረገበት ፡ ሄደው ፡ እኔ ፡ ካሳባችሁ ፡ ኣልወጣም ፡ ብለው ፡ ኣስታወቀ ። መኳንንቱም ፡ እንግዲያስ ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ባንደኛው ፡ ክፍል ፡ እንዲቀመጡ ፡ ይሁን ፡ ተብሎ ፡ ምክሩ ፡ ከተቈረጠ ፡ በኋላ ፡ ነገ ፡ እመጣለሁ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ መኖሪያቸው ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ተሰማ ፡ ቤት ፡ ተመለሱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ኣባተ

፡ የመንግሥቱ ፡ እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ አስበዋል ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡ ያልወደዱ ፡ ሰዎች ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ ቢገዙ ፡ ይሻላል ፡ እያሉ ፡ ሌላ ፡ ምክር ፡ ማደራጀት ፡ ዠመሩ ። በዚሁም ፡ ነገር ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሊጋባ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልና ፡ ራስ ፡ ሉል ፡ ሰገድ ፡ ተስማምተውበት ፡ ነበርና ፡ ወደ ፡ ኣቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ሄደው ፡ ምክራቸውን ፡ አጸኑ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ አባቴ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ግቢ ፡ ወታደሮቻቸውንና ፡ የምክር ፡ ተባባሪዎቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ተሰልፈው ፡ ተቀምጠው ፡ ነበርና ፡ ግንቦት ፡ 23 ፡ ቀን ፡ ረቡዕ ፡ በራስ ፡ አባተና ፡ በአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ መካከል ፡ ግጭት ፡ ሊደረግ ፡ ነው ፡ እየተባለ ፡ ሲፈራ ፡ ዋለ ። ነገር ፡ ግን ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ማቴዎስና ፡ ዕጨጌ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወደ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ እየተመላለሱ ፡ ነገሩን ፡ በዕርቅ ፡ ካበረዱት ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ አባተ ፡ ወደ ፡ ግዛታቸው ፡ ወደ ፡ ከምባታ ፡ እንዲሄዱ ፡ ተደረገ ።

ራስ ፡ ኣባተ ፡ ምንም ፡ እንካ ፡ በዕርቅ ፡ ቢሄዱ ፡ በዚያው ፡ ባሉበት ፡ ሆነው ፡ ወታደር ፡ ያስፎክራሉ ፡ የሚባል ፡ ወሬ ፡ ስለ ፡ ተሰማባቸው ፡ ነገሩን ፡ ለማስረገጥ ፡ ባ19104 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ቢጠሩ ፡ አሞኛል ፡ እያሉ ፡ ሳይመጡ ፡ ቀሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ከወሎ ፡ መጥተው ፡ ነበርና ፡ የራስ ፡ አባተ ፡ ግዛት ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ለፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተሰጠ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ አባተ ፡ ታኅሣሥ ፡ 19 ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ እጃቸውን ፡ ለራስ ፡ ሚካኤል ፡ ሰጡ ። እሳቸውም ፡ እስረኛ ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡ በማግስቱ ፡ ወደ ፡ ደሴ ፡ ተጓዙ ። ቀጥሎም ፡ በመቅደላ ፡ አምባ ፡ ላይ ፡ አስረዋቸው ፡ እስከ ፡ ሰገሌ ፡ ዘመቻ ፡ ድረስ ፡ በዚያው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ መቀመጫ ፡ ቤታቸውን ፡ ባባታቸው ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ ግቢ ፡ ማድረግ ፡ ዠመሩ ። ቀጥሎም ፡ በሑዳዴው ፡ ወደ ፡ ደሴ ፡ አባታቸው ፡ ዘንድ ፡ ሄደው ፡ ነበርና ፡ በዚያው ፡ ሳሉ ፡ በፋሲካው ፡ የጊሚራ ፡ ሕዝብ ፡ ባገረ ፡ ገዥው ፡ በደጃዝማች ፡ ሙሉ ፡ ጌታ ፡ ላይ ፡ ማመጡን ፡ ሰሙ ። ስለዚህም ፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ ከደሴ ፡ ተነሥተው ፡ ግንቦት ፡ 12 ፡ ቀን ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ያባታችንን ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በዓል ፡ አክብረው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሳይገቡ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ጊሚራ ፡ ተጓዙ ።

አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ጊሚራ ፡ ደርሰው ፡ ዐመፀኛውን ፡ ሕዝብ ፡ ቀጥተው ፡ ሰላማዊ ፡ ካደረጉት ፡ በኋላ ፡ ክረምቱን ፡ ከዚያው ፡ ከርመው ፡ እግረ ፡ መንገዳቸውን ፡ ዝኖን ፡ አድነው ፡ ባ1905 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ አባታቸውን ፡ ጃንሆይን ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አስወጥተው ፡ ወደ ፡ አንኮበር ፡ ሊሰዷቸውና ፡ እሳቸው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ገብተው ፡ ሊቀመጡ ፡ ነው ፡ እየተባለ ፡ የከተማ ፡ ወሬ ፡ በዝቶ ፡ ይወራ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የግቢ ፡ ዘበኞች ፡ አለቃ ፡ ፊታውራሪ ፡

ገብረ ፡ ማርያምና ፡ ምክትሉ ፡ ሹም ፡ ባሻ ፡ ደቻሳ ፡ « ክንዳችንን ፡ ሳንንተራሳት ፡ ጌታችንን ፡ ከቤቱ ፡ የሚያስወጣው ፡ የለም ፡ እያሉ ፡ ይፎክሩ ፡ ዠመር ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የከተማው ፡ ወሬ ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጽ ፡ ሚኒስትሮቹ ፡ የስብከት ፡ ቃል ፡ እያሳተሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ ይበትኑ ፡ ነበር ። ቀጥሎም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ያለፈቃድ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ እንዳይገባ ፡ በስተውጭም ፡ ዘበኛ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ በአንበሳ ፡ በር ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ክፍል ፡ የበጅሮንድ ፡ ኣሸናፊ ፡ ባልደረቦች ፡ በሌላውም ፡ ወገን ፡ የደጅ ፡ ኣጋፋሪ ፡ ክፍሎች ፡ ይጠብቁ ፡ ዠመር ። በጅሮንድ ፡ አሸናፊ ፡ የአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ባለሟል ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ ፡ ነበር ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ በከተማው ፡ ተስፋፍቶ ፡ ነበርና ፡ ከርሳቸው ፡ ወገን ፡ ባሉት ፡ ወታደሮችና ፡ በግቢ ፡ ዘበኞች ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ አይታይም ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ የካቲት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ ቅዳሜ ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ በግምት ፡ 10 ፡ ሰዓት ፡ ያኽል ፡ ሲሆን ፡ የበጅሮንድ ፡ አሸናፊ ፡ ባልደረቦች ፡ በነበሩበት ፡ ወገን ፡ ጠብ ፡ ዠማሪው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ምክንያቱም ፡ ሳይታወቅ ፡ አንድ ፡ ጥይት ፡ ተተኰሰ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የግቢ ፡ ዘበኞች ፡ በቋፍ ፡ ነበሩና ፡ እየተፏከሩ ፡ መተኰስ ፡ ዠመሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በግቢው ፡ ዙሪያ ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ሲተኰስ ፡ ከሌሊቱ ፡ እስከ ፡ 5 ፡ ሰዓት ፡ ያኽል ፡ ከቈየ ፡ በኋላ ፡ ተኵሱ ፡ እንደ ፡ መብረድ ፡ አለ። በዚህ ፡ ግጭት ፡ ካ10 ፡ እስከ ፡ 15 ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በተባራሪ ፡ ጥይት ፡ ከመሞታቸው ፡ በስተቀር ፡ እንደ ፡ ተኵሱ ፡ ብዛት ፡ ብዙ ፡ ጕዳት ፡ አልተደረገም ።በማግሥቱ ፡ እሑድ ፡ ጧት ፡ ጳጳሱና ፡ ዕጨጌው ፡ እየተመላለሱ ፡ ነገሩን ፡ በዕርቅ ፡ ስለ ፡ ፈጸሙት ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ ማርያምና ፡ ባሻ ፡ ደቻሳ ፡ ወደ ፡ ጳጳሱ ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ ደወል ፡ እንደ ፡ መደወል ፡ ሁሉ ፡ ተቀመጡ።

ቀጥሎም ፡ በያውራጃው ፡ ተልከው ፡ በግዞት ፡ እንዲቀመጡ ፡ ስለ ፡ ተፈረደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ባሻ ፡ ደቻሳም ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ለራስ ፡ ኀይሉ ፡ ተልከው ፡ እስከ ፡ ሰገሌ ፡ ዘመቻ ፡ ድረስ ፡ በዚያው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የዘበኞች ፡ አለቅነቱን ፡ ፊታውራሪ ፡ ተሰማ ፡ ገዝሙ ፡ ደጃዝማች ፡ ተብለው ፡ ተሾሙ ።

አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ በዚያው ፡ ዘመን ፡ በመጋቢት ፡ ወር ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ ለመዝመት ፡ አስበው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ መጋቢት ፡ 5 ፡ ቀን ፡ ዝቋላ ፡ ተራራ ፡ ወጥተው ፡ የአቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በዓል ፡ አከበሩ ። ከዚያም ፡ ወርደው ፡ ከተራራው ፡ ሥር ፡ ጉግስ ፡ ሲጫወቱ ፡ የአንኮበር ፡ ወህኒ ፡ አዛዥ ፡ የነበሩት ፡ ፊታውራሪ ፡ ቸርነት ፡ በዘንግ ፡ ተወግተው ፡ ወዲያው ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ እዚያው ፡ ዝቋላ ፡ ላይ ፡ ተቀበሩ ። በዘመኑ ፡ ሲወራ ፡ እንደ ፡ ነበረውም ፡ ኣቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ በጉግስ ፡ ጨዋታ ፡ ጊዜ ፡ የሚይዙት ፡ ዘንግ ፡ ቂጡ ፡ የሾለ ፡ ወይም ፡ በስውር ፡ ሹል ፡ ብረት ፡ ያለበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እሳቸው ፡ ወግተው ፡ ገደሏቸው ፡ ተብሎ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ይወራ ፡ ነበር ።

አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ከዝቋላ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ አገሩን ፡ ከጐበኙና ፡ ጤናዬ ፡ የሚባል ፡ ከተማ ፡ ከቈረቈሩ ፡ በኋላ ፡ ለፋሲካ ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ወደ ፡ ደሴ ፡ ሄደው ፡ በግንቦት ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ እንደ ፡ ታመሙ ፡ በሕይወታቸው ፡ ነበሩ።

በኋላ ፡ ግን ፡ ሕመማቸው ፡ እየጸና ፡ ሄዶ ፡ ታኅሣሥ ፡ 3 ፡ ቀን ፡ 1906 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዐረፉ ። ሞታቸውም ፡ የተሰማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አገር ፡ ይሸበራል ፡ እየተባለ ፡ ይፈራ ፡ ነበርና ፡ እንዳይወራ ፡ በጥብቅ ፡ ተከለከለ ። አቤቶ ፡ ኢያሱም ፡ በዚያ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በሞቱበት ፡ ቀን ፡ ጃንሜዳ ፡ ወጥተው ፡ ጉግስ ፡ ሲጫወቱ ፡ ውለው ፡ ነበር ።

የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዕረፍት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በየሰዉ ፡ ሕሊና ፡ ቢታወቅ ፡ በግልጥ ፡ ለማዘንና ፡ ለማልቀስ ፡ ሳይቻል ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ከመንግሥት ፡ እስከ ፡ ወጡበት ፡ ቀኝ ፡ ድረስ ፡ ከመነገር ፡ ተከልክሎና ፡ ተደብቆ ፡ ቈየ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ግንቦት ፡ 23 ፡ ቀን ፡ 1907 ፡ ዓ ፡ ም ፡ «ዘሥልጣኑ ፡ ጽሑፍ ፡ ዲበ ፡ መትከፍቱ ፡ ሚካኤል ፡ ንጉሠ ፡ ጽዮን » ፡ ተብለው ። የንጉሥነት ፡ ዘውድ ፡ ደፍተው ፡ በወሎና ፡ በትግሬ ፡ በጐጃም ፡ ላይ ፡ ነገሡ ።

በዚሁ ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የዐድዋንና ፡ የሽሬን ፡ ግዛት ፡ ደጃች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ተሾመው ፡ ሲገዙ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ተላልከዋል ፡ የሚሉ ፡ ወሬ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ተሰማ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነገሩን ፡ አጣርቶ ፡ ለመመርመር ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ እንዲመጡ ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ ተላለፈላቸው። እርሳቸውም ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ለመምጣት ፡ ጉዞ ፡ ዠምረው ፡ ሳሉ ፡ በኋላ ፡ ከራስ ፡ስብሐትና ፡ ከልጃቸው ፡ ከደጃች ፡ አስገዶም ፡ የቈየ ፡ ቂም ፡ ነበራቸውና ፡ እኔ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ስሄድ ፡ አገሬን ፡ ዐድዋን ፡ ይይዙብኛል ፡ ብለው ፡ ሲያመነቱ ፡ ቈይተው ፡ ደጃች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ መምጣትን ፡ ትተው ፡ መሣሪያ ፡ እንዲልከላቸው ፡ ለኤርትራ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ላኩበት ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የመኳንንቱ ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ መዋጋት ፡ ለኢጣሊያ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ 3 ፡ ሺሕ ፡ ጠመንዣ ፡ በፍጥነት ፡ ላከላቸው ። ይኸውም ፡ ባ1 ፡ ነፃ ፡ በሆነ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ 1 ፡ ሰው ፡ ቢሸፍት ፡ ወይም ፡ መሣሪያ ፡ ቢጠይቅ ፡ መስጠት ፡ የማይገባውን ፡ የዓለምን ፡ ሕግ ፡ ተላልፈው ፡ ይህን ፡ እላይ ፡ የተባለውን ፡ መሣሪያ ፡ ላኩላቸው ፡ እንዲያውም ፡ እንጨምርልኻለን ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ሰጧቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴና ፡ ራስ ፡ ስብሐት ፡ ጦራቸውን ፡ አሰልፈው ፡ 19106 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ አጋሜ ፡ ውስጥ ፡ ኣኮራ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ተጋጥመው ፡ ሲዋጉ ፡ ወዲያው ፡ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ቀድሞ ፡ በነበራቸውና ፡ አዲስ ፡ ከኢጣሊያ ፡

መንግሥት ፡ በተላከላቸው ፡ መሣሪያ ፡ ድል ፡ አድርገዋቸው ፡ ራስ ፡ ስብሐት ፡ ከልጆቻቸው ፡ ከደጃዝማች ፡ አስገዶምና ፡ ከደጃች ፡ አርኣያ ፡ ጋራ ፡ ተገደሉ ።

ከ6 ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ደጃዝማች ፡ ሥዩምና ፡ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ፈረስ ፡ ሜዳ ፡ በሚባል ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተጋጥመው ፡ሲዋጉ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ትእዛዝ ፡ ተላልፎላቸው ፡ ከበጌምድር ፡ ተነሥተው ፡ ጦርነቱን ፡ ለማብረድ ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ዐድዋ ፡ ተጓዙ ። የራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስንም ፡ መምጣት ፡ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከደጃዝማች ፡ ሥዩም ፡ ጋራ ፡ ጦርነቱን ፡ አቍመው ፡ በሽሽት ፡ ወደ ፡ ኤርትራ ፡ ገቡ ።

ሉካ ፡ ዴይ ፡ ሳቤሊ ፡ የሚባል ፡ ኢጣሊያዊ ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ እስከ ፡ መረብ ፡ ወሰን ፡ ድረስ ፡ አልፈው ፡ የኤርትራን ፡ ግዛት ፡ አስጨነቁት ፡ ወዲያውም ፡ የደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴን ፡ እጅ ፡ አስረክበኝ ፡ ብለው ፡ ለዋናው ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ላኩበት ። አገረ ፡ ገዥውም ፡ ላስረክብ ፡ ወይስ ፡ ልዋጋ ፡ እያለ ፡ ሲያመነታ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ኤርትራ ፡ ባሉት ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ የጭንቀት ፡ ታላቅነት ፡ ይኸንኑ ፡ ታሪክ ፡ በስፍራው ፡ የጻፉ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ አስረድተዋል ።

ይልቁንም ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የሊብያን ፡ ግዛት ፡ ወግቶ ፡ ቅኝ ፡ ለማድረግ ፡ ጦርነቱን ፡ ዠምሮ ፡ ጨርሶ ፡ ስላላስገበረ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ ሁሉ ፡ ወደዚያ ፡ ልኮ ፡ በኤርትራ ፡ የነበረው ፡ ያ1 ፡ ባታዮ ፡ ወታደር ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለመቋቋም ፡ አይችሉምና ፡ ኤርትራ ፡ ትወረራለች ፡ በማለት ፡ በጣም ፡ ይሠጋ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደጃች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴን ፡ ፍለጋ ፡ እንጂ ፡ የኢጣሊያ ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ ሚኒስትር ፡ ሌሶና ፡ ባ1927 ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንዳመካኘው ፡ ኤርትራን ፡ ለመውረር ፡ አልነበረም ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ በሰፈሩበት ፡ በረሓ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ውሃ ፡ ወታደራቸው ፡ በጠጣ ፡ ጊዜ ፡ ከውሃው ፡ መጥፎነት ፡ የተነሣ ፡ ከወታደራቸው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እየታመመ ፡ በሞት ፡ ስላለቀባቸው ፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ወደ ፡ ግዛታቸው ፡ ተመለሱ ። ይኸንንም ፡ ውሃ ፡ ከሚወርድበት ፡ ወገን ፡ 1 ፡ የኢጣሊያ ፡ ሐኪም ፡ ታዞ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ ቀን ፡ ሊደርሱ ፡ ሌሊቱን ፡ የሚገድል ፡ መርዝ ፡ በትኖበት ፡ ነበር ፡ ብለው ፡ አሁንም ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ብዙ ፡ የትግሬና ፡ የሐማሴን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይናገራሉ ። ርግጥ ፡ መሆኑ ፡ ግን ፡ አይታወቅም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ በኤርትራ ፡ ሲማሩ ፡ አብረው ፡ ካደጓቸው ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ጋራ ፡ 4 ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘውድ ፡ በጫኑ ፡ ጊዜ ፡ አማላጅ ፡ ይዘው ፡ ገብተው ፡ ታርቀው ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ በማዕርግ ፡ ተቀመጡ ።

# ዳግማዊ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ



# የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

NIGUSS DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ 43 ።

## የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ መንግሥትና ፡ አካሄዳቸው ፡ -የጀርመን ፡ ፖለቲካ ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ የሞት ፡ ሽታ ፡ በሽተታቸው ፡ ጊዜ ፡ አልጋ ፡ ወራሼ ፡ ኢያሱ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለመኳንንቱና ፡ ለሕዝቡ ፡ ስላስታወቁ ፡ ሕዝቡም ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክን ፡ ከልቡ ፡ ይወድ ፡ ነበርና ፡ ለልጅ ፡ ኢያሱ ፡ እንገዛለን ፡ በማለት ፡ የልጅ ፡ ኢያሱን ፡ አልጋ ፡ ወራሽነት ፡ በደስታ ፡ ተቀበለ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ካባታቸው ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ የተወለዱት ፡ በሥጋ ፡ እንጂ ፡ በጠባይና ፡ ባስተዋይነት ፡ ስላልተወለዱ ፡ ጠባያቸው ፡ ሁሉ ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጠባይ ፡ አልመሳሰል ፡ አለ ።

በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የማንኛውም ፡ እምነትና ፡ ሥራ ፡ የሚጣልበት ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የውጭውንም ፡ የውስጡንም ፡ ፖለቲካ ፡ በመምራት ፡ በኋላቸውና ፡ በፊታቸው ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ይጨነቁበት ፡ የነበረውን ፡ ችላ ፡ ብለው ፡ የርሳቸው ፡ ጭንቀት ፡ ለሌላ ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የተመለከተ ፡ መኳንንትና ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ደስታው ፡ ወደ ፡ ኀዘን ፡ ተለወጠ ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ሊያደርገውና ፡ ሊፈጽመው ፡ ከሚገባው ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ይበልጦቹ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተመለከቱት ፡ ናቸው ።

1ኛ. ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ በሥርዐተ ፡ ተክሊል ፡ አግብቶ ፡ መቀመጥ ።

2ኛ. ፡ ከአብርሀና ፡ ከአጽብሐ ፡ ዠምሮ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጸንቶ ፡ የኖረውን ፡ የኦርቶዶክስን ፡ ሃይማኖት ፡ ጠብቆ ፡ መኖር ።

3ኛ. ፡ ከመሳፍንት ፡ እስከ ፡ ተራ ፡ ሕዝብ ፡ ያለውን ፡ ማንኛውንም ፡ ዜጋ ፡ ዐቅድ ፡ ባለው ፡ ሕግ ፡ ማስተዳደር ።

4ኛ. ፡ ከቊጣና ፡ ያለሕግ ፡ ከመቅጣት ፡ ታጋሽ ፡ መሆን ።

5ኛ. 5 ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ለንጉሥነት ፡ የተገባውን ፡ ክብሩን ፡ በስውርም ፡ በግልጽም ፡ መጠበቅ ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ግን ፡ በነዚህ ፡ እላይ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ባንደኛው ፡ እንኳ ፡ የበጎ ፡ ሥራ ፡ ሊይዙ ፡ በፍጹም ፡ አልፈለጉም ።

እቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ወይም ፡ እቢሯቸው ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ የመንግሥቱን ፡ አስተዳደር ፡ ለማከናወን ፡ ከመድከም ፡ ይልቅ ፡ ሜዳ ፡ እየፈለጉ ፡ የፈረስ ፡ ጉግስ ፡ መጫወትንና ፡ ሰፊ ፡ ጫካ ፡ እየመረጡ ፡ ኣደን ፡ ማደንን ፡ መረጡ ።

ከዚህ ፡ በቀር ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በማገልገል ፡ የሸመገሉትን ፡ ያባታቸው ፡ የዐፄ ፡ ምኒልክን ፡ አሽከሮች ፡ በማይገባ ፡ እያዋረዱ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተቀመጡትንም ፡ ሹማምንቶች ፡ ያላንዳች ፡ ምክንያት ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ እየጠሩ ፡ ያጉላሏቸው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሥልጣናቸው ፡ ዘመን ፡ እስከ ፡ 3 ፡ ዓመት ፡ ቢደርስ ፡ ይኸውም ፡ ዘመን ፡ የጥጋብና ፡ የማን ፡ አለብኝ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ማንም ሰው ፡ ይልቁንም ፡ መኳንንቱ ፡ በሹመታቸው ፡ በትዳራቸው ፡ ወይም ፡ በሚስቶቻቸውና ፡ በሀብታቸው ፡ ላይ ፡ የተረጋገጠ ፡ እምነት ፡ አልነበራቸውም ። እንደዚህ ፡ ያለውም ፡ ጠባይ ፡ በጉልማሳነት ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ እንዳይባል ፡ ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ ከንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጠባይ ፡ ርቀው ፡ የመሪነት ፡ ሥራቸውን ፡ በጥንቃቄ ፡ እየፈጸሙ ፡ ስለሚገኙ ፡ ለልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ጥፋት ፡ ማሻሻያ ፡ ጸሓፊ ፡ ሊያገኝላቸው ፡ አይችልም ።

ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ስሕተት ፡ ሆኖ ፡ የተቈጠረባቸው ፡ በኤውሮፓ ፡ ትልቁ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ተቀስቅሶ ፡ እንደ ፡ ኤ. ቍ ፡ ካ1914 ፡ እስከ ፡ 1918 ፡ ዓ ፡ ም ፡ (ካ1906 ፡ -1911 ፡ ዓ ፡ ም) በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዙሪያ ፡ ሆነው ፡ በወዳጅነትና ፡ በውል ፡ የቈዩትን ፡ መንግሥታት ፡ የነበራቸውን ፡ ኀይል ፡ ሳይገምቱ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ድል ፡ ከሚሆነው ፡ ከጀርመን ፡ ጋራ ፡ መተባበራቸው ፡ ነው ።

በትልቁ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ለጀርመን ፡ የጦር ፡ ጓደኛ ፡ በመሆኑ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ከቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ አዛምዶ ፡ የሁለቱን ፡ ኃይል ፡ ከተደገፈ ፡ በኋላ ፡ በሰሜን ፡ አፍሪካ ፡ ያለውን ፡ የጦር ፡ ጓደኞቹን ፡ የእንግሊዝንና ፡ የፈረንሳዊን ፡ ግዛት ፡ ለመቀማት ፡ አስቦ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ልጅ ፡ ኢያሱም ፡ ለዚሁ ፡ ለጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ፖለቲካ ፡ እንደሚስማማው ፡ ወዳጅነታቸውን ፡ በተለይ ፡ ከእስላም ፡ ባላባቶች ፡ ጋራ ፡ አድርገው ፡ ከእስላም ፡ ሴቶችም ፡ ውስጥ ፡ እየመረጡ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ያስቀምጡ ፡ ዠመር ። ይልቁንም ፡ በአውሳው ፡ ባላባት ፡ በደጃዝማች ፡ አቡበከር ፡ ልጅ ፡ በፍቅሯ ፡ ተነድፈው ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ በፍጹም ፡ ዘንግተውት ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ አድራጎታቸውን ፡ የተመለከተ ፡ ከዚያ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ወደ ፡ እስላም ፡ ሃይማኖት ፡ ገብተዋል ፡ እያለ ፡ በግልጽ ፡ ያወራባቸው ፡ ዠመር ።

ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ከእስላም ፡ ባላባቶች ፡ መወዳጀት ፡ እንደ ፡ ዠመሩና ፡ የጀርመን ፡ የጦር ፡ ጓደኛ ፡ ለመሆን ፡ ባሰቡ ፡ ጊዜ ፡ መማክርቱና ፡ ጳጳሱ ፡ ርሳቸውን ፡ ከዙፋን ፡ በማውረድ ፡ ፈንታ

፡ ባሳባቸው ፡ ተባብረው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ጀርመን ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ኤ. ቀ ፡ ሰኔ ፡ 28 ፡ ቀን ፡ 1919 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጦር ፡ ጓድ ፡ የነበሩት ፡ መንግሥታት ፡ በአሜሪካኑ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ በውድሮው ፡ ዊልሶን ፡ ሰብሳቢነት ፡ በቤርሳይ ፡ ውል ፡ አድርገው ፡ እነታንጋኒካ ፡ እነኢየሩሳሌም ፡ ለእንግሊዝ ፡ እነሶርያ ፡ ለፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ሲሰጡ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነፃነቷን ፡ ጠብቃ ፡ በመኖር ፡ ከነሱ ፡ የበለጠች ፡ ብትሆን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ለጀርመን ፡ ማገዝ ፡ የጦርነቱን ፡ ድል ፡ ካላዘነበለው ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አደጋ ፡ ሳያገኛትና ፡ ሎንዶን ፡ ላይ ፡ የተደረገውም ፡ እ3 ፡ የመከፈል ፡ ውል ፡ ለመግቢያ ፡ እውነተኛውን ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሳያገኝ ፡ አይቀርም ፡ ነበር ።

ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገረው ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ ለገዥነት ፡ የማይበቁ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ሕዝቡም ፡ መኳንንቱም ፡ ስብሰባ ፡ አድርጎ ፡ ርሳቸው ፡ ሐረር ፡ ባሉበት ፡ ጊዜ ፡ በርሳቸው ፡ ፈንታ ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በቀጥታ ፡ የሚወለዱት ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ እንዲነግሡና ፡ ቀጥሎም ፡ የሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የራስ ፡ መኰንን ፡ ልጅ ፡ ደጃዝማች ፡ ተፈሪ ፡ ራስ ፡ ተብለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ እንደራሴ ፡ እንዲሆኑ ፡ በምክር ፡ ተወሰነ ። ይኸውም ፡ በመስከረም ፡ 17 ፡ ቀን ፡ 1909 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በዋናው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በነጋሪት ፡ ታውጆ ፡ ከተነገረ ፡ በኋላ ፡ የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ መንግሥት ፡ ተፈጸመ ።





ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ሚካዔል

# የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት

NIGUSS DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ 44 ።

## የወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ መሆን ፡ - ደጃዝማች ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ራስ ፡ ተብለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።

ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ የዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ 3ኛ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ፡ ርሳቸውም ፡ ባ1888 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ሚያዝያ ፡ 22 ፡ ቀን ፡ እነዋሪ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ተወለዱ ፡ እናታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ አብቺው ፡ ይባላሉ ፡ ከእምባቦ ፡ ዘመቻ ፡ በኋላ ፡ የዓፄ ፡ ዮሐንስን ፡ ልጅ ፡ ራስ ፡ አርኣያን ፡ አገቡ ። ራስ ፡ አርኣያም ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወሌን ፡ አግብተው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

በኋላ ፡ ግን ፡ አባታቸው ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ስለ ፡ ታመሙ ፡ ቤታቸውን ፡ ትተው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ከእቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክን ፡ ሲያስታምሙ ፡ ኖሩ ። ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዐርፈው ፡ ኣቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ በያዙ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ካዲስ ፡ ኣበባ ፡ ወጥተው ፡ ፋሌ ፡ ሄደው ፡ ተቀመጡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የአቤቶ ፡ ኢያሱን ፡ ኣኳኋን ፡ መኳንንቱ ፡ ገምተው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ የማይገቡ ፡ መሆናቸውን ፡ ከተረዱት ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡም ፡ መኳንንቱም ፡ ለዚሁ ፡ ምክር ፡ ስብሰባ ፡ አድርገው ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ንግሥት ፡ ተብለው ፡ በዙፋኑ ፡ እንዲቀመጡ ፡ ደጃዝማች ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ራስ ፡ ተብለው ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ የመንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ እንዲሆኑ ፡ ተመረጡ ።

ይኸውም ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ በተሰበሰቡት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ከታተመና ፡ ተፈርሞ ፡ ከተዘጋጀ ፡ በኋላ ፡ መስከረም ፡ 17 ፡ ቀን ፡ 1909 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ የመንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ ተብለው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አደባባይ ፡ በነጋሪት ፡ ታውጆ ፡ ተነገረ።


ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ማቴዎስና ፡ ዕጨጌ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱን ፡ የተከተልኽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪን ፡ የከዳኽ ፡ ውጉዝ ፡ ነኽ ፡ ብለው ፡ የዐዋጁን ፡ ቃል ፡ አጸኑ ። ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ግን ፡ በአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ፋሌ ፡ ይቀመጡ ፡ ነበርና ፡ ይህ ፡ በሆነ ፡ ባራተኛው ፡ ቀን ፡ ተጠርተው ፡ መጥተው ፡ መስከረም ፡ 21 ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ «ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ወለቱ ፡ ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ሥይምተ ፡ እግዚአብሔር » ፡ ተብለው ፡ በዙፋን ፡ ተቀመጡ ።

በዚህ ፡ ነገር ፡ ከንጉሥ ፡ ሚካኤልና ፡ የልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ጨዋታ ፡ ወዳድነት ፡ ተንተርሶ ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ ለመኖር ፡ ከፈለገው ፡ መኳንንት ፡ በስተቀር ፡ ከመሳፍንት ፡ እስከ ፡ ተራ ፡ ሕዝብ ፡ ከጳጳሱ ፡ እስከ ፡ ተራው ፡ ደብተራ ፡ ያለው ፡ ደስ ፡ ተሰኝቶ ፡ የዐዋጁን ፡ ቃል ፡ ሁሉም ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ በደስታ ፡ ተቀበለው ።

# ምዕራፍ ፡ 45 ።

## <u>የልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ መኰንን ፡ አጭር ፡ ታሪክ ።</u>

ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ባ1884 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ሐምሌ ፡ 16 ፡ ቀን ፡ ከኃህለ ፡ ሥላሴ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ከራስ ፡ መኰንንና ፡ ከወይዘሮ ፡ የሺእመቤት ፡ ሐረር ፡ አውራጃ ፡ ኤጀርሳ ፡ ጎሮ ፡ በሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ተወለዱ ።

ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽነት ፡ ከመመረጣቸው ፡ በፊት ፡ ያማርኛና ፡ የፈረንሳዊ ፡ ትምህርት ፡ እየተማሩ ፡ ስላደጉ ፡ በየተራ ፡ በሹመት ፡ የተሰጣቸውን ፡ አገር ፡ በሕፃንነታቸው ፡ ወይም ፡ በጕልማሳነታቸው ፡ ወራት ፡ በደንብ ፡ በማስተዳደራቸው ፡ የተመሰገኑ ፡ ሆኑ ፡ ገና ፡ በልጅነታቸው ፡ ልዩ ፡ አእምሮና ፡ ሰፊ ፡ አስተያየት ፡ የተለየም ፡ ተወዳጅነት ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክና ፡ ኣባታቸው ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ ይሰንብት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ይሁን ፡ በማለት ፡ ይሻሚቻው ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ገና ፡ ያሥር ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ሳሉ ፡ ባ1894 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ከሐረር ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ተገናኝተው ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ሄዱ ። በኋላ ፡ አባታቸው ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ባ1898 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ኅዳር ፡ 10 ፡ ቀን ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ የደጃዝማችነት ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥተው ፡ ጋራ ፡ ሙለታ ፡ የሚባለውን ፡ አገር ፡ ሾመው ፡ ተከታይ ፡ ልጄ ፡ ደጃዝማች ፡ ተፈሪ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለየመኳንንቶቻቸው ፡ አስታወቁ ።

ወዲያው ፡ በዚያው ፡ ዓመት ፡ መጋቢት ፡ 13 ፡ ቀን ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ በተለዩት ፡ ጊዜ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ደጃዝማች ፡ ተፈሪን ፡ ከሐረርጌ ፡ አስጠርተው ፡ ደጃዝማችነታቸውን ፡ አድሰው ፡ የሰላሌን ፡ ግዛት ፡ ሾሟቸው ። እርሳቸው ፡ ግን ፡ ለተሰጣቸው ፡ ግዛት ፡ እንደራሴያቸውን ፡ ልከው ፡ በሐረር ፡ ሳሉ ፡ ይማሩ ፡ የነበሩትን ፡ የፈረንሳዊ ፡ ቋንቋ ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይቀጥሉ ፡ ነበር ።

ባ1899 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የባሶ ፡ ግዛት ፡ ተሰጣቸው ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ባ1900 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲዳሞን ፡ ተሾሙ ፡ ቀጥሎም ፡ ባ1902 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲዳሞን ፡ ትተው ፡ ያባታቸውን ፡ ግዛት ፡ ሐረርጌንና ፡ አውራጃዋን ፡ ስለ ፡ ተሾሙ ፡ ሐረርጌ ፡ ሲገቡ ፡ ትንሹም ፡ ትልቁም ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንንን ፡ ልጅ ፡ በማግኘቱ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ተቀበላቸው ። ባ1903 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሐምሌ ፡ ወር ፡ የንጉሥ ፡ ሚካኤልን ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ወይዘሮ ፡ መነንን ፡ አግብተው፡ ባ1905 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጥር ፡ 22 ፡ ቀን ፡ ልዕልት ፡ ተናኘ ፡ ወርቅን ፡ ወለዱ ። ባ1907 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ትእዛዝ ፡ አባታቸው ፡ ያቀኑትን ፡ ግዛት ፡ ተሽረው ፡ ከሐረርጌ ፡ መጥተው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተቀመጡ ፡ ለስሙም ፡ የከፋን ፡ ግዛት ፡ ተቀብለው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አልሄዱበትም። ባ1909 ፡ ዓ ፡ ም ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ሐረር ፡ ሳሉ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ለንግሥትነት ፡ ሲመረጡ ፡ ደጃዝማች ፡ ተፈሪም ፡ ራስ ፡ ተብለው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ እንደራሴ ፡ ሆነው ፡ የራስ ፡ ወርቅ ፡ አሠሩ ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ባ1908 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሐምሌ ፡ 20 ፡ ቀን ፡ ዛሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ የሆኑትን ፡ ልዑል ፡ አስፋ ፡ ወሰንን ፡ ወለዱ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ባ1909 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሐምሌ ፡ 18 ፡ ቀን ፡ ልዕልት ፡ ዘነበ ፡ ወርቅን ፡ ባ1912 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥቅምት ፡ 2 ፡ ቀን ፡ ልዕልት ፡ ፀሓይን ፡ ባ1917 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥቅምት ፡ 5 ፡ ቀን ፡ ልዑል ፡ መኰንንን ፥ በየካቲት ፡ 20 ፡ ቀን ፡ 1923 ፡ ዓ ፡ ም ፡ አቤቶ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴን ፡ ወለዱ ።

# ምዕራፍ ፡ 46 ።

## የቶራ ፡ መስክና ፡ የሰገሌ ፡ ጦርነት ፡ የንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ መማረክ ፡ የንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ የራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ንጉሥ ፡ መባል ።

ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ በደሴ ፡ ከተማቸው ፡ ሳሉ ፡ የልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ከመንግሥት ፡ መውጣት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ ለማየት ፡ አልችልም ፡ ብለው ፡ ለጦርነት ፡ ይዘጋጁ ፡ ዠመር።

አቤቶ ፡ ኢያሱም ፡ ሐረርጌ ፡ ሆነው ፡ የንግሥት ፡ ዘውዲቱን ፡ መንገሥ ፡ ሰሙ ፡ ወዲያውም ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱን ፡ ለመውጋት ፡ እነደጃች ፡ አያሌው ፡ በባቡር ፡ ተላኩ ። ሄደውም ፡ ምዔሶ ፡ ላይ ፡ ከልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ተልኮ ፡ ከመጣው ፡ ከደጃዝማች ፡ ጉግሳ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ መለሱት ። እንደዚሁ ፡ ደግሞ ፡ ከሐረር ፡ ከልጅ ፡ ኢያሱ ፡ የተላኩትና ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ የወረዱ ፡ ሰዎች ፡ ጨለንቆ ፡ ላይ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በሩቅ ፡ እየተያዩ ፡ ሰነበቱና ፡ በመጨረሻ ፡ ግን ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ትእዛዝ ፡ የመጡት ፡ ሰዎች ፡ መዋጋቱን ፡ ትተው ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ከተላኩት ፡ ጋራ ፡ በሰላም ፡ ተደባለቁ ።

አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ከተመለከቱ ፡ በኋላ ፡ ከጥቂቶች ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ድሬዳዋ ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ በከተማው ፡ ያገኙትን ፡ ዘርፈው ፡ ወደ ፡ አውሳ ፡ ለመሄድ ፡ መንገድ ፡ ዠመሩ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ 10 ፡ ሺህ ፡ የሚያኽል ፡ ወታደር ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ጕዞ ፡ ዠምረው ፡ ነበርና ፡ አንኮበር ፡ ሲደርሱ ፡ በከተማ ፡ ያገኙትን ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ ዕቃ ፡ ዘርፈው ፡ ጕዟቸውን ፡ ይቀጥሉ ፡ ዠመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ሆነው ፡ እንዲመክቱ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ የተላኩት ፡ ራስ ፡ ሉል ፡ ሰገድና ፡ ደጃች ፡ ተሰማ ፡ ገዝሙ ፡ ጭፍራ ፡ ይዘው ፡ ሄደው ፡ ቶራ ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ከንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ ጋራ ፡ ጥቅምት ፡ 7 ፡ ቀን ፡ ተጋጥመው ፡ ሲዋጉ ፡ ራስ ፡ ሉል ፡ ሰገድና ፡ ደጃች ፡ ተሰማ ፡ ገዝሙ ፡ ከብዙ ፡ ሌሎች ፡ ጋራ ፡ ሞቱና ፡ ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ ለጊዜው ፡ አሸነፉ ።

ንጉሥ ፡ ሚካኤልም ፡ በዚህ ፡ በቀመሱት ፡ ድል ፡ ደስ ፡ ተሰኝተው ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ ቢገሠግሡ ፡ እርምጃቸውን ፡ ሊያግድ ፡ የሚችል ፡ ኃይል ፡ እንደሌለ ፡ ያኽል ፡ ቈጠሩት ። ቀጥሎ ፡ ከፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በመነኰሳት ፡ እጅ ፡ የዕርቅ ፡ ቃል ፡ ቢላክላቸው ፡ አሽከሮቻቸው ፡ አደፋፍረዋቸው ፡ የዕርቁን ፡ ቃል ፡ ሳይቀበሉ ፡ ስለ ፡ ቀሩ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ይዘው ፡ ሰገሌ ፡ ላይ ፡

ይጠባበቋቸው ፡ ዠመር ፡ የዳር ፡ አገሩም ፡ ጦር ፡ በነራስ ፡ ደምሰው ፡ እየተመራ ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ሄዶ ፡ ተደባልቆ ፡ ነበር ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ለከተማው ፡ ጥበቃ ፡ ደጃዝማች ፡ ባልቻን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ጦሩ ፡ ሰፈር ፡ ሄዱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጠራ ፡ ውስጥ ፡ ሰገሌ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ የሁለቱም ፡ ወገን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ማዶ ፡ ለማዶ ፡ ሰፍሮ ፡ ሳለ ፡ ወዲያው ፡ ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ አደጋ ፡ በማድረግ ፡ ድል ፡ እንደሚገኝ ፡ አስበው ፡ ጥቅምት ፡ 17 ፡ ቀን ፡ 1909 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዐርብ ፡ በጧት ፡ ገሥግሠው ፡ ጦርነቱ ፡ ተዠመረ ። ወዲያውም ፡ ውጊያው ፡ ተሟሙቆ ፡ እስከ ፡ 9 ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ እንደቈየ ፡ በመጨረሻ ፡ ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ እጃቸውን ፡ ሰጥተው ፡ ስለ ፡ ተማረኩ ፡ ጦርነቱ ፡ ተፈጸመ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ግዞተኞች ፡ የነበሩት ፡ እነራስ ፡ አባተ ፥ እነራስ ፡ ወሌ ፡ በነፃ ፡ ተለቀው ፡ ወደ ፡ ልዑል ፡ ኣልጋ ፡ ወራሽ ፡ መጡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ምርኮኛውን ፡ አሲዘው ፡ በድል ፡ አድራጊው ፡ ሠራዊታቸው ፡ ታጅበው ፡ በጥቅምት ፡ 21 ፡ ቀን ፡ ማክሰኞ ፡ በታላቅ ፡ ሰልፍ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሲገቡ ፡ ከሰገሌ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ገና ፡ ባይያዙ ፡ አገሩ ፡ ሰላም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ባ1909 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የካቲት ፡ 4 ፡ ቀን ፡ እንዲሆን ፡ ተወስኖ ፡ ለበዓሉም ፡ እንዲሰበሰቡ ለታላላቁ ፡ መኳንንት ፡ ትእዛዝ ፡ ተላለፈ።

ወዲያውም ፡ ስለ ፡ ንግሥ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነገር ፡ ሲዘጋጅ ፡ ሰነበተ ። ይልቁንም ፡ የኤሌክትሪክ ፡ መብራት ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ዘንድ ፡ አልነበረምና ፡ በዚህ ፡ በዓል ፡ ጊዜ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ እስከ ፡ ኣራዳ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተዘረጋው ፡ የኤሌክትሪክ ፡ መብራት ፡ በየመንገዱ ፡ ስለ ፡ በራ ፡ የከተማው ፡ ሰው ፡ ከመደነቅ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ አለው ።

በዚሁ ፡ እላይ ፡ በተባለው ፡ በየካቲት 4 ፡ ቀን ፡ አባታቸው ፡ ባሠሩት ፡ ባራዳ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ ተደርጎ ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብተው ፡ ዘውድ ፡ በደፉ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚሁ ፡ ልዑል ፡ ኣልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ለአልጋ ፡ ወራሽነት ፡ የሚገባው ፡ ሥርዐት ፡ ተደርሶላቸው ፡ ከፍተኛውን ፡ ራስ ፡ ወርቅ ፡ አሰሩ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ንግሥቲቱ ፡ በታላቅ ፡ ሠረገላ ፡ ተቀምጠው ፡ ከቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባማረ ፡ ሰልፍ ፡ ታጅበው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ደርሰው ፡ በዙፋናቸው ፡ ሲቀመጡ ፡ 1 ፡ ጊዜ ፡ መድፍ ፡ ተተኰሰ ። በዚህም ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ ነበሩ ።

በዚሁ ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የንጉሥነት ፡ ማዕርግ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ስለ ፡ ተቈረጠ ፡ የጐንደር ፡ ንጉሥ ፡ ተብለው ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ በየካቲት ፡ 11 ፡ ቀን ፡ ዘውድ ፡ ደፉላቸው ።

# ምዕራፍ ፡ 47 ።

## አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ በወሎ ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ ሰብስበው ፡ ስለ ፡ መዋጋታቸውና ፡ ድል ፡ ሆነው ስለ ፡ መሸሻቸው ፥ በኋላም ፡ ግብጽያ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መያዛቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ከሰገሌ ፡ ጦርነት ፡ የተረፉትንና ፡ የራስ ፡ ይመርን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ወሎ ፡ ገብተው ፡ ጦር ፡ ያሳብራሉ ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ተሰማ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ራስ ፡ አባተ ፡ ዋና ፡ አበጋዞች ፡ ሆነው ፡ ከነሱም ፡ ጋራ ፡ እነራስ ፡ ደምስን ፡ እነደጃች ፡ ከበደን ፡ እነደጃች ፡ ወልደ ፡ ጻድቅን ፡ አስከትለው ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ለመያዝ ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ ዘመቱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በክረምቱ ፡ ወራት ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ መጥተው ፡ ደሴ ፡ ላይ ፡ ጦርነቱ ፡ ተዠምሮ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በብርቱ ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ኣቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ሸሽተው ፡ ገቡ ። በዚያም ፡ ተከታትለው ፡ ያሉበትን ፡ የመቅደላን ፡ ምሽግ ፡ እነራስ ፡ ኣባተ ፡ በመድፍ ፡ እየደበደቡ ፡ ስላስቸገሯቸው ፡ ከመቅደላ ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ አውሳ ፡ በረሓ ፡ ሸሹ ። ከዚያም ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ኀይል ፡ ተሰብሮ ፡ ያሉበትም ፡ አገር ፡ ጠፍቶ ፡ ሲኖር ፡ ባ1913 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በትግሬ ፡ ውስጥ ፡ ግብጽያ ፡ በሚባለው ፡ ገዳም ፡ ተገኙ ። ወደዚያም ፡ የሄዱበት ፡ ምክንያት ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ ባለቤት ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበች ፡ እኅታቸው ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ በዚያ ፡ ለመሸሸግ ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ይባላል ። በኋላ ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ ግብጽያ ፡ በሚባለው ፡ ገዳም ፡ የራስ ፡ ጉግሳ ፡ አርኣያ ፡ ሰዎች ፡ አግኝተው ፡ ማረኳቸው ።

ልዑል ፡ ራስ ፡ ጉግሳም ፡ የአቤቶ ፡ ኢያሱን ፡ መያዝ ፡ ለልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ አስታወቁ ። ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽም ፡ ባ1913 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፋሲካው ፡ ወራት ፡ ወደ ፡ ደሴ ፡ ሄደው ፡ ሳሉ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ እሥረኛውን ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱን ፡ በታማኝነት ፡ አስረከቡ። ከዚያም ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ወዳዲስ ፡ ኣበባ ፡ መጥተው ፡ ሰላሌ ፡ ፍቼ ፡ በልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ እጅ ፡ እሥረኛ ፡ ሆነው መኖሪያ ፡ የሚሆን ፡ ልዩ ፡ ቤት ፡ ተሠርቶላቸው ፡ ተቀመጡ ።

# ምዕራፍ ፡ 48 ።

## የኢትዮጵያ ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ መግባት ።

ኢትዮጵያ ፡ በአፍሪካ ፡ ምሥራቅ ፡ የምትገኝ ፡ ሆና ፡ ሳለች ፡ የነገሥታቷና ፡ የአርበኞቿ ፡ ስለ ፡ ነፃነቷ ፡ ቀናተኛነታቸው ፡ እሷን ፡ ከሚያዋስኗት ፡ የአፍሪካ ፡ ግዛት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የተለየ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መሄድ ፡ የተነሣ ፡ በእስያም ፡ በአፍሪካም ፡ ያሉ ፡ የሴምና ፡ የካም ፡ ተወላጆች ፡ የሚሆኑ ፡ መንግሥታት ፡ በሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በገፉት ፡ በያፌት ፡ ልጆች ፡ መንግሥታት ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ በታች ፡ ሲወረሱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ የገዛ ፡ ልጆቿ ፡ እንደሚቀለብ ፡ ኳስ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በመቃማት ፡ ሲጋደሉባት ፡ ኖሩ ፡ እንጂ ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ የውጭ ፡ ገዥ ፡ አላስገቡባትም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በተያዙት ፡ አገሮችና ፡ በሚይዙት ፡ አገሮች ፡ አደባባይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ በሙሉ ፡ ካለመሠልጠኗ ፡ ጋራ ፡ ያሳጣ ፡ ዠመር ።

ስለዚህም ፡ ይኸንኑ ፡ አለመሠልጠን ፡ የተባለውን ፡ ምክንያት ፡ ተደግፎ ፡ የኒጄሪያ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ የነበረው ፡ ሰር ፡ ፍሬድሪክ ፡ ለጋርድ ፡ የሚባለው ፡ እንደ ፡ ኤ ፡ ቍ ፡ ባ1919 ፡ ዓ ፡ ም ፡ (በኢት ፡ ቍ ፡ 1911 ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ኣሳብ ፡ በሎርድ ፡ ሜልኑር ፡ በኩል ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ አቀረበ ።

«በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ባሪያን ፡ የመግዛትና ፡ የባሪያን ፡ ንግድ ፡ ለማስቀረት ፡ የመሣሪያውንም ፡ አገባብ ፡ ለመመርመርና ፡ በውሳጣዊ ፡ አስተዳደሯም ፡ አብሮ ፡ ለመሥራት ፡ የእንግሊዝ ፡ የፈረንሳዊ ፡ የኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ ወኪሎችን ፡ ያሻል ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ነገር ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አስተዳደር ፡ ልዩ ፡ አማካሪዎች ፡ ሊሾም ፡ ያስፈልጋል ። »

የእንግሊዝ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሰር ፡ ለጋርድ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያቀረበውን ፡ አሳብ ፡ በሰፊው ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ባሪያ ፡ ነፃነትና ፡ ስለ ፡ ሌላውም ፡ ነገር ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ ከሚያደርጋቸው ፡ አማካሪዎች ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ለመሥራት ፡ ምናልባት ፡ ፈቃዱ ፡ መሆኑን ፡ እንዲጠይቅ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ያለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ሚኒስትር ፡ ትእዛዝ ፡ ተላልፎለት ፡ ይህንኑ ፡ ጥያቄ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አቀረበ ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ እነሱ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸው ፡ ቢያስቡ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከ3ቱ ፡ መንግሥታት ፡ የጥቅም ፡ ስምምነት ፡ ወዲህ ፡ ይህንን ፡ በመሰለ ፡ አሳብ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ለመጠየቅ ፡ አልደፈሩም ፡ ነበርና ፡ ነገሩን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ችላ ፡ ሊለው ፡ አልቻለም ። ስለዚህ ፡ ለዚህ ፡ መልስ ፡ ከመስጠት ፡ በፊት ፡ የማኅበሩ ፡ ሕግ ፡ የሚያዘውን ፡

ለመፈጸም ፡ የተዘጋጀ ፡ መሆኑንና ፡ አገሩንም ፡ ለማሠልጠን ፡ ባገሩም ፡ ውስጥ ፡ ሊያስወቅስ ፡ የሚችለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እያደር ፡ በተቻለው ፡ ለማስወገድ ፡ ፈቃዱ ፡ መሆኑን ፡ ገልጾ ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ ገብቶ ፡ ማኅበረተኛ ፡ እንዲሆን ፡ ኣስቀድሞ ፡ ጽፎ ፡ ያዘጋጀውን ፡ ጥያቄ ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ 1923 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነሐሴ ፡ 12 ፡ ቀን ፡ (በኢት ፡ ቍ ፡ ባ1915 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነሐሴ ፡ 6 ፡ ቀን) ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በደጃች ፡ ናደውና ፡ ባቶ ፡ ፋሲካ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ማኅበር ፡ ላከ ።

የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ጸሓፊ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ማኅበር ፡ እንድትገባ ፡ የጠየቀችበትን ፡ ደብዳቤ ፡ በጉባኤ ፡ ካስነበበ ፡ በኋላ ፡ ትግባ ፡ በሚሉና ፡ አትግባ ፡ በሚሉ ፡ መካከል ፡ ታላቅ ፡ ክርክር ፡ ተነሣ ።

ኢትዮጵያን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ማኅበር ፡ ለመግባት ፡ አይገባትም ፡ የሚሉትም ፡ የሚያቀርቡት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሀ) በውስጧ ፡ የባሪያ ፡ አገዛዝ ፡ አለ ።
ለ) የግዛቷ ፡ ወሰን ፡ በደንብ ፡ የተከለለ ፡ አይደለም ።
ሐ) በውስጧ ፡ መጋደልና ፡ መዘረፍ ፡ አለ ።
መ) በግዛቷ ፡ ላይ ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ የሚያዘውን ፡ ሕግ ፡ ልታስፈጽም ፡ አትችልም ።

ከዚህ ፡ በቀር ፡ የአውስትራልያው ፡ መንግሥት ፡ መላክተኛ ፡ ሰር ፡ ዮሴፍ ፡ ኩክ ፡ የሚባለው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ይበልጥ ፡ በሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የገፉት ፡ መንግሥታት ፡ እዚህ ፡ ማኅበር ፡ ሳይገቡ ፡ የዚህ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበረተኞች ፡ ይዘዋቸው ፡ ሳለ ፡ ያልሠለጠነችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ከዚህ ፡ ትገባለች ፡ ሲል ፡ ክርክር ፡ አንሥቶ ፡ ነበር ።

ገሚሶችም ፡ የስዊስና ፡ የሆላንድ ፡ የኖርቤጅ ፡ መንግሥታት ፡ መላክተኞች ፡ ከመፍረዳችን ፡ በፊት ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ ልዩ ፡ መልክተኛ ፡ ልኮ ፡ አስቀድሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚደረገውን ፡ ያስመርምር ፡ ብለው ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ የሚያውቋት ፡ መንግሥታት ፡ ይልቁንም ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ እላይ ፡ የተዘረዘረው ፡ ምክንያት ፡ ገሚሱም ፡ ኣሰት ፡ መሆኑን ፡ የቀረውንም ፡ በጊዜው ፡ መሪ ፡ የሆኑት ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ ለማስቀረትና ፡ አገራቸውንም ፡ ለማሠልጠን ፡ እንደ ፡ ተነሡ ፡ በኢትዮጵያም ፡ የባሪያ ፡ ኣገዛዝ ፡ በሕግ ፡ እንደ ፡ ተሻረ ፡ በጉባኤው ፡ መካከል ፡ በሰፊው ፡ አስረድተው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከማኅበሩ ፡ ለመግባት ፡ ይገባታል ፡ ሲሉ ፡ ፈረዱ ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ መላክተኛም ፡ እንግሊዝ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ያሰበውን ፡ ፖለቲካ ፡ ለማሰናከል ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመርዳት ፡ ሳይሆን ፡ መግባት ፡ ይገባታል ፡ ሲል ፡ ፈረደ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በፖለቲካ ፡ መሪዋ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ በነፃነት ፡ የኖረችና ፡ የምትኖር ፡ መሆኗን ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ ማኅበረተኞች ፡ ፊት ፡ አረጋግጣ ፡ ባ1916 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ ከማኅበሩ ፡ ገብታ ፡ ለማኅበሩ ፡ እንዳንድ ፡ አባል ፡ ሆና ፡ ተቈጠረች ።

ይህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ማኅበረተኝነት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የተደረገባትን ፡ ማገኛውንም ፡ ስምምነት ፡ ሲሽር ፡ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለሚደረግባት ፡ የፖለቲካ ፡ ጦርነት ፡ ለመከላከል ፡ የተመቸ ፡ ምሽግ ፡ ሆነ።

# ምዕራፍ ፡ 49 ።

## የልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ የኤውሮፓን ፡ መንግሥታት ፡ ከተሞች ፡ መጐብኘት

የጄኔብ ፡ ማኅበር ፡ መግቢያ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የፖለቲካ ፡ ቁልፍ ፡ ተዘግቶ ፡ ሳለ ፡ ልዑል ፡ ኣልጋ ፡ ወራሽ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሆነው ፡ በሠሩት ፡ የፖለቲካ ፡ መክፈቻ ፡ በሩ ፡ ተከፍቶ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ በነፃ ፡ መንግሥትነት ፡ ከሚመሳሰሏት ፡ ጐን ፡ ከተቀመጠች ፡ በኋላ ፡ ልዑል ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ የዕውቀት ፡ ምርት ፡ ወደ ፡ መረተበት ፡ ወደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ሄደው ፡ ከምርቱ ፡ ለሕዝባቸው ፡ ለማትረፍ ፡ ሚያዝያ ፡ 7 ፡ ቀን ፡ 1916 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ በልዩ ፡ ባቡር ፡ ተሳፍረው ፡ ወደ ፡ ጅቡቲ ፡ ሄዱ ።

የተከተሏቸውም ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ኀይሉ ፥ ልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፥ ክቡራን ፡ ራስ ፡ ናደው ፥ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፥ ደጃዝማች ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ደጃዝማች ፡ ሙሉ ፡ ጌታ ፥ ደጃዝማች ፡ ገሰሰ ፥ ሊጋባ ፡ ወዳጄ ፥ ብላታ ፡ ኅሩይ ፥ ልጅ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፥ አቶ ፡ ሣህሌ ፡ ጸዳሉ ፡ ለዋና ፡ አስተርጓሚነት ፥ ኣቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ተገኝና ፡ ሌሎችም ፡ እነአቶ ፡ በቀለ ፡ ኪሮስ ፡ ነበሩ ።

ኤውሮፓ ፡ ደርሰው ፡ እስኪመለሱ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ቋንቋ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ቢያውቁ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ የመንግሥታቸውን ፡ ቋንቋ ፡ ለማስከበር ፡ ባማርኛ ፡ ሲናገሩ ፡ በፈረንሳዊ ፡ ያስተረጉሙ ፡ የነበሩት ፡ አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ተገኝ ፡ ነበሩ ።

ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ እነዚህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ መሳፍንቶችና ፡ መኳንንቶች ፡ አስከትለው ፡ ከጅቡቲ ፡ በመርከብ ፡ ተሳፍረው ፡ ፖርት ፡ ሳይድ ፡ ሲደርሱ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ጒዟቸውን ፡ በመቀጠል ፡ ፈንታ ፡ ወደ ፡ ተስፋዪቱ ፡ አገር ፡ ወደ ፡

ኢየሩሳሌም ፡ ሄደው ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሕይወትና ፡ ቤዛ ፡ የሆነው ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተወለደበትን ፡ ናዝሬትን ፡ ያስተማረበትን ፡ የገሊላን ፡ ወረዳ ፡ ማሕየዊ « ደሙ ፡ የፈሰሰበትን ፡ ቀራንዮንና ፡ ሞት ፡ የማይገባውን ፡ የጌታችንን ፡ ሥጋ ፡ ለ3 ፡ ቀን ፡ የተሸከመውን ፡ የጎልጎታን ፡ ቅዱስ ፡ ስፍራ ፡ ተሳልመው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ግብጽ ፡ ሄዱ ። ከዚያም ፡ አልፈው ፡ ኤውሮፓ ፡ ሲደርሱ ፡ የፈረንሳዊን ፥ የቤልጅግን ፥ የስዊድንን ፥ የኢጣሊያን ፥ የእንግሊዝን ፥ የግሪክን ፡ ዋና ፡ ከተሞችንና ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ የቆመበትን ፡ የጄኔብን ፡ ከተማ ፡ እየዞሩ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ጐበኙ ።

ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መሪነት ፡ ከያዙ ፡ ወዲህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለማስኬድ ፡ የወጠኑትን ፡ የሥራ ፡ ዕቅድን ፡ ሁሉ ፡ የኤውሮፓ ፡ የመንግሥታት ፡ መሪዎች ፡ ሰምተው ፡ ከማድነቅ ፡ ጋራ ፡ ሰውነታቸውንም ፡ ለማየት ፡ ናፍቆት ፡ ነበራቸውና ፡ የየራሳቸውን ፡ ከተማ ፡ በአበባና ፡ በባንዲራ ፡ እያስጌጡ ፡ ደርሰው ፡ ለመቼ ፡ አይተናቸው ፡ እያሉ ፡ በናፍቆት ፡ ይጠባበቋቸው ፡ ነበር ። በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ በሚገዛው ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ ሬፑብሊክ ፡ በሚገዛው ፡ አገር ፡ ፕሬዚዳኑ ፡ በእግርም ፡ በኦቶሞቢልም ፡ በሚሄዱበት ፡ ጊዜ ፡ በቀኛቸው ፡ እያስቀመጡ ፡ ከተማቸውን ፡ ያስጐበኗቸው ፡ ነበር ።

በሻይ ፡ ወይም ፡ በራት ፡ ጊዜ ፡ ተቀባዩ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ፕሬዚዳኑ ፡ ለልዑልነታቸው ፡ ክብር ፡ ዲስኩር ፡ ሲያደርግ ፡ ልዑል ፡ ኣልጋ ፡ ወራሽ ፡ ይመልሱት ፡ የነበረው ፡ መልስ ፡ ተቀባዮቻቸውን ፡ በደስታ ፡ ተከታይ ፡ መኳንንቶቻቸውን ፡ በኩራት ፡ የሚመላ ፡ ነበር ።

ደግሞ ፡ የኤውሮፓ ፡ ገዥዎች ፡ ለልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሻችን ፡ ያደረጉላቸው ፡ ኣክብሮና ፡ ፍቅር ፡ የመላበት ፡ የወዳጅነት ፡ አቀባበል ፡ ጉዳይን ፡ ሊያዘነጋ ፡ የሚችል ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ የደስታ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ እያገቡ ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ይነጋገሩበት ፡ ነበር ።

ይኸውም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ለሕዝቧ ፡ ሕይወት ፡ ከሚሆነው ፡ ውስጥ ፡ በጅቡቲ ፡ በኩል ፡ ስላለው ፡ ጉዳይ ፡ ከፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ በዐሰብ ፡ በኩል ፡ ስላለው ፡ የወደብ ፡ ከተማ ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ተነጋገሩ ።

የጉዳዩ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከምትጠይቀው ፡ ይልቅ ፡ ከነሱ ፡ ወገን ፡ ለዚሁ ፡ እንደ ፡ መወዳደሪያ ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ የከበደ ፡ በመሆኑ ፡ ለማንኛውም ፡ የጊዜ ፡ ቀጠሮ ፡ ተደረገለት ፡ እንጂ ፡ የተፈጸመ ፡ ነገር ፡ አልተገኘም ።

ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽም ፡ በታላቅ ፡ ክብርና ፡ አቀባበል ፡ የኤውሮፓን ፡ ከተሞች ፡ እየዞሩ ፡ ጐብኝተውና ፡ ጉዳያቸውን ፡ አከናውነው ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በነሐሴ ፡ 24 ፡ ቀን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመልሰው ፡ ሲገቡ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ መሳፍንቱና ፡ መኳንንቱ ፡ ሕዝቡም ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተቀበሏቸው ።

# ምዕራፍ ፡ 50 ።

## ስለ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘውድ ፡ መመለስ ።

በምዕራፍ ፡ 13ና ፡ 14 ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ የእንግሊዝ ፡ ቆንስልና ፡ የወንጌል ፡ መላክተኞቹ ፡ በታሰሩበት ፡ ምክንያት ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ እነዚሁ ፡ እሥረኞች ፡ እንዲፈቱለት ፡ በደብዳቤ ፡ ለምኖ ፡ ሳይለቀቁለት ፡ ስለ ፡ ቀረ ፡ በጄኔራል ፡ ናፒዬር ፡ የሚታዘዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ላከ ። ዐፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ በመጨረሻ ፡ በነበረው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ጊዜ ፡ ጭካኔና ፡ ደም ፡ ማፍሰስ ፡ አብዝተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከበታቾቻቸው ፡ የነበሩት ፡ መሳፍንት ፡ ከድተዋቸው ፡ ነበር ፡ ስለዚህ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ የታመኑትን ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ ብቻ ፡ ይዘው ፡ ከእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ መሆናቸውን ፡ በተረዱት ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸውን ፡ በሽጉጥ ፡ ገድለው ፡ ወደቁ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥታቸውን ፡ ሀብት ፡ ሰብስበው ፡ በዚሁ ፡ በመቅደላ ፡ አስቀምጠው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እንግሊዞች ፡ እየበረበሩ ፡ ወዳገራቸው ፡ ለመውሰድ ፡ ሲያከማቹ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ መጥቶ ፡ የነበረው ፡ ሮልፍስ ፡ የሚባለው ፡ የጀርመን ፡ (የፕሩስ) ፡ ተወላጅ ፡ የንጉሡን ፡ የወርቅ ፡ ዘውድ ፡ አግኝቶ ፡ ጦር ፡ አዛዡ ፡ ለጄኔራል ፡ ናፒዬር ፡ ሳያስረክብ ፡ ደብቆ ፡ ወስዶ ፡ በሱዌዝ ፡ ካናል ፡ ለሚቀመጠው ፡ ለጀርመን ፡ ቆንስል ፡ ሰጠው ። ቆንስሉም ፡ ይህንኑ ፡ ዘውድ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ከደብዳቤ ፡ ጋራ ፡ አድርጎ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ ለነበረው ፡ ለቢስማርክ ፡ ሔርበርት ፡ ላከለት ።

በኋላ ፡ ግን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ይህ ፡ ዘውድ ፡ በጀርመን ፡ መንግሥት ፡ እጅ ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ሰማ ፡ እንዲመለስለት ፡ ጥያቄ ፡ አቀረበ ። የጀርመን ፡ መንግሥትም ፡ የዚህ ፡ ዘውድ ፡ ባለቤት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የሚፈቅድለት ፡ ምክንያት ፡ እንደሌለው ፡ ተገንዝቦ ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ መለሰ ። የእንግሊዝ ፡ መንግሥትም ፡ ተቀብሎ ፡ የቢክቶርያና ፡ የአልቤርት ፡ ሙዚዬውም ፡ በሚባለው ፡ ቤት ፡ በከበሬታ ፡ አስቀምጦት ፡ ሲኖር ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በአልጋ ፡ ወራሽነታቸው ፡ ዘመን ፡ ኤውሮፓን ፡ እየዞሩ ፡ ሲጐበኙ ፡ ሎንዶን ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ይኸው ፡ ዘውድ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ተመላሽ ፡ እንዲሆን ፡ ከግርማዊ ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ከጆርጅ ፡ 5ኛ ፡ ተስፋ ፡ ተቀብለው ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ተስፋ ፡ ይኸንኑ ፡ ዘውድ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ አድርጎ ፡ በላካቸው ፡ በክቡር ፡ ቻርል ፡ ቤንቲግ ፡ እጅ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ላከው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታትና ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ከሌሎቹ ፡ ሚኒስትሮችና ፡ መኳንንቶች ፡ ጋራ ፡ በዋናው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጠባበቁ ፡ የእንግሊዙ ፡ ሚኒስትር ፡ በሐምሌ ፡ 4 ፡ ቀን ፡ 1917 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዘውዱን ፡ ባ4 ፡ ፈረስ ፡ በሚሳብ ፡ ሠረገላ ፡ እመካከል ፡ አስቀምጠው ፡ ባ4 ፡ ሰዓት ፡ ደርሰው ፡ ዘውዱን ፡ በከበሬታ ፡ ከሠረገላው ፡ ላይ ፡ አንሥተው ፡ እግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ፊት ፡ አስቀምጠው ፡ ወዲያው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ዲስኩር ፡ ተናገሩ ፡፡

## «ግርማዊት ፡ ሆይ ፡

በንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ኤ ፡ ቍ ፡ ባ1888 ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እንደ ፡ ኢት ፡ 1808 ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ከመቅደላ ፡ የተወሰደውን ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ዘውድ ፡ የታላቂቱ ፡ ብሪታንያና ፡ የአይርላንድ ፡ ከባሕርም ፡ ማዶ ፡ ያሉት ፡ ግዛቶች ፡ ንጉሥ ፡ የህንድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በሆኑት ፡ በግርማዊ ፡ ጌታዬ ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ በማክበር ፡ እመልሳለሁ ፡፡

የዚህ ፡ የዘውድ ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ሳያስደንቅዎ ፡ እንደማይቀር ፡ ርግጥ ፡ ነው ፡ መቅደላ ፡ ከተያዘ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘውድ ፡ ሮልፍስ ፡ በሚባል ፡ ባንድ ፡ የፕረሺያ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ገብቶ ፡ ነበር ፡፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ከሎርድ ፡ ናፒዬር ፡ በታች ፡ ይታዘዝ ፡ ከነበረው ፡ ዘማች ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ለመሄድ ፡ የተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይኸንኑ ፡ ዘውድ ፡ ሱኤዝ ፡ ላይ ፡ ይቀመጥ ፡ የነበረው ፡ የፕረሺያ ፡ ዋይስ ፡ ቆንስል ፡ ቤርሊን ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ የነገሥታት ፡ ዕቃ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቤት ፡ እንዲቀመጥ ፡ ብሎ ፡ ለፕሪንስ ፡ ቢስማርክ ፡ ላከባቸው ፡፡ የእንግሊዝ ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ ይኸንኑ ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ዘውዱ ፡ እንዲመለስልን ፡ እያሉ ፡ ከፕረሺያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ መጻጻፍ ፡ ዠመሩ ፡፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ይኸው ፡ ዘውድ ፡ በፕረሺያ ፡ ንጉሥ ፡ ፈቃድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ እንዲያዝበት ፡ ሆኖ ፡ ተመለሰ ፡፡ በተመለሰም ፡ ጊዜ ፡ ኮንት ፡ ቢስማርክ ፡ በዘውዱ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ የሚሆነው ፡ መስቀል ፡ ጐድሏል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ እኛም ፡ እንደዚሁ ፡ ነውና ፡ ያገኘነው ፡ ይኸው ፡ መልሰናል ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈው ፡ ላኩ ፡፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ይኸንኑ ፡ ዘውድ ፡ ከመጋቢት ፡ 30 ፡ ቀን ፡ ሺህ ፡ 889 ፡ ዓ ፡ ም ፡ (ሺህ ፡ 881) ፡ ኣንሥቶ ፡ 57 ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በቢክቶርያና ፡ በአልቤርት ፡ ሙዜዬውም ፡ አስቀምጦት ፡ ሲኖር ፡ በሚያዝያ ፡ 29 ፡ ቀን ፡ ሺህ ፡ 925 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሺህ ፡ 917) ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይዤው ፡ እንድመለስ ፡ ተብሎ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ስፍራ ፡ ወጣ ፡ የዚህም ፡ ዘውድ ፡ አኳኋን ፡ በሺህ ፡ 889 ፡ ዓ ፡ ም ፡ (ሺህ ፡ 881) ፡ በሙዜዬውም ፡ ሲገባ ፡

ልክ ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አሁንም ፡ እንደዚያው ፡ መሆኑን ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ አረጋግጥ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ተቀብያለሁ ።

የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ ማየታቸው ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሥና ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አሰኝቷቸዋል ።

ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ጆርጅ ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያንና ፡ የታላቋ ፡ ብሪታንያን ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶች ፡ እንዲህ ፡ በደስታ ፡ ያስተሳሰራቸውን ፡ የወዳጅነት ፡ ማሰሪያ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እያጸኑና ፡ እያጠበቁ ፡ ለመሄድ ፡ ምኞታቸው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ዘውድ ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ እመልስላቸዋለሁ ፡ ብለው ፡ ቃላቸውን ፡ ለልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ሰጡ ። አሁንም ፡ እንዲህ ፡ ለመሰለውና ፡ ታሪክም ፡ ሆኖ ፡ በሚቈየው ፡ ነገር ፡ የንጉሤን ፡ ትእዛዝ ፡ በመፈጸሜና ፡ ይኸንንም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘውድ ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝዎና ፡ ይኸንኑም ፡ ስጦታ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ጆርጅ ፡ በተለየ ፡ የወዳጅነታቸውና ፡ የአክብሮታቸው ፡ ምልክት ፡ ሆኖ ፡ እንዲቀበሏቸው ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋሉ ።

አሁንም ፡ እንደዚሁ ፡ የንጉሡን ፡ ትእዛዝ ፡ እየፈጸምኩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥትን ፡ እንዲባርክና ፡ እንደ ፡ ታላቂቱ ፡ ንግሥታችን ፡ በረከት ፡ ለመላበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መታሰቢያ ፡ እንደ ፡ ሆኑትና ፡ የልጅ ፡ ልጃቸውም ፡ ይኸንን ፡ የወዳጅነት ፡ ምልክት ፡ እንደ ፡ ላኩልዎ ፡ እንደ ፡ ንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ ያለ ፡ ረዥም ፡ ዕድሜና ፡ የደኅንነትም ፡ መንግሥት ፡ እንዲያደርግልዎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እለምናለሁ ።

ደግሞም ፡ ለልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በረከቱን ፡ ይስጣቸው» ።

ለዚህም ፡ መልስ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ተናገሩ ።

## « ክቡር ፡ ሚኒስትር ፡ ሆይ ፥

ከኤውሮፓ ፡ መንገዴ ፡ በተመለስሁ ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ጆርጅ ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ዘውድ ፡ እመልሳለሁ ፡ ብለው ፡ ስሰናበታቸው ፡ የነገሩኝን ፡ ቃል ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ባመለከታቸው ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ አድርገው ፡ ነበር ።

አሁንም ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ጆርጅ ፡ ቃላቸው ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥትና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በመላው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በቸርነቱ ፡ እናመሰግነዋለን ። ይህ ፡ ዘውድ ፡ ከ17 ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ኤውሮፓ ፡ በመሄዴ ፡ ምክንያት ፡ በግርማዊት ፡ ንግሥት

፡ በመንግሥታቸው ፡ ዘመን ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ መጣልን ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለን ።

## ክቡር ፡ ሚኒስትር ፡ ሆይ ፡

እዚህ ፡ ላይ ፡ የማስታውስዎ ፡ ይህ ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘውድ ፡ ተመልሶ ፡ ስለ ፡ መጣልን ፡ ከትልቅ ፡ መታሰቢያ ፡ እንቈጥረዋለን ። ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዘውድ ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ ከብሮ ፡ የኖረና ፡ አሁንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ባለተስፋ ፡ መሆኑ ፡ ከዕውቀትም ፡ እንዳይሰወርዎ ፡ በፍጹም ፡ አምናለሁና ፡ ለዚህ ፡ ታሪኩን ፡ ኣስረዝሜ ፡ ልነግርዎ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መስሎ ፡ አይታየኝም ። ይኸውም ፡ የዘውድ ፡ ነገር ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ክፍል ፡ የተገናኘ ፡ በመሆኑ ፡ በታላቅ ፡ ደስታና ፡ ክብር ፡ ይቀበሉዎታል ።

## ክቡር ፡ ሚኒስትር ፡ ሆይ ፡

ይህ ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ጆርጅ ፡ ስጦታ ፡ የሚደነቅ ፡ የወዳጅነት ፡ ምልክት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ በፍጹም ፡ ልባቸው ፡ ምስጋናቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ያቀርባሉና ፡ ይህንኑ ፡ ምስጋናቸውን ፡ ገልጸው ፡ እንዲያስታውቁላቸው ፡ በብዙ ፡ ይለምኑዎታል ። እኔም ፡ ራሴ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ጆርጅን ፡ ለማየት ፡ ሄጄ ፡ በታላቁ ፡ ከተማቸው ፡ ሳለሁ ፡ ይኸንን ፡ ታላቅ ፡ ቸርነታቸውን ፡ ስላሳዩኝ ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ለዘለዓለም ፡ ከልቤ ፡ ተጽፎ ፡ መታሰቢያ ፡ ሆኖኝ ፡ ይኖራል ። በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናዬን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ አቀርብላቸዋለሁ ።

ቸርነቱ ፡ የማያልቅበት ፡ እግዚአብሔር ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ጆርጅ ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ማሪ ፡ እንደዚሁም ፡ ለቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ ሁሉ ፡ ሰላምና ፡ ጤና ፡ ክብርና ፡ ደስታ ፡ ለዘወትር ፡ እንዲሰጣቸው ፡ በታላቅ ፡ ተስፋ ፡ እንለምናለን ። »

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዘውዱ ፡ ከንግሥት ፡ ፊት ፡ ተነሥቶ ፡ እሚገባው ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጠና ፡ ለዚሁ ፡ የተሰበሰበውን ፡ መኳንንትና ፡ መሳፍንት ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥትና ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ አሰናበቱ ።

# ምዕራፍ ፡ 51 ።

## ልዑል ፡ ኣልጋ ፡ ወራሽ ፡ አገራቸውን ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ስለ ፡ መምራታቸውና ፡ ስለ ፡ ገጠማቸው ፡ ዕንቅፋት ።

በኢትዮጵያ ፡ ዙፋን ፡ የተቀመጡት ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ በደግነትና ፡ ለሰው ፡ በመራራት ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መሳለምና ፡ ጸሎትን ፡ ማዘውተራቸው ፡ ለመነኰሳትና ፡ ተስፋ ፡ ለሌላቸው ፡ ድኾች ፡ ተስፋ ፡ መሆናቸው ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በስግደት ፡ የተፀመዱና ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የሚያመልኩ ፡ መሆናቸው ፡ ለማንም ፡ የተገለጸ ፡ ነው ።

የእንጀራ ፡ እናታቸው ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ በፖለቲካም ፡ በጦርነትም ፡ እየገቡ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይሠሩ ፡ ነበረ ። ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ግን ፡ ባባታቸው ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጠው ፡ የተደላደለ ፡ ሥልጣን ፡ እያላቸው ፡ ሥልጣናቸውን ፡ አጋነው ፡ ሊሠሩበትና ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፖለቲካ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ አልፈለጉም ።

ስለዚህ ፡ በወንድምና ፡ በልጅ ፡ ዐይን ፡ ለሚመለከቷቸው ፡ ለልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሻቸው ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ይዘው ፡ እንዲያስኬዱ ፡ ሙሉ ፡ ፈቃድ ፡ ሰጥተው ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲተ ፡ እላይ ፡ በተባለው ፡ የበጎ ፡ ተግባር ፡ ጊዜያቸውን ፡ ስለሚያሳልፉ ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚወደው ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ የተስፋውን ፡ ዐይን ፡ በልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ላይ ፡ ጣለ ። ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በቀር ፡ የኤውሮፓ ፡ መንግሥታትም ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጐብኝተውና ፡ የልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽን ፡ አያያዝ ፡ አስተውለው ፡ ከተመለከቱት ፡ መላክተኞቻቸው ፡ እየተረዱ ፡ ብዞዎቹ ፡ የኤውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ስለ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ኀዥነት ፡ ደስታቸውን ፡ የሚገልጸ ፡ ብዙ ፡ ደብዳቤ ፡ ይልኩባቸው ፡ ነበር ።

ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ያስተዳዳሪነት ፡ ከባድ ፡ አደራ ፡ ከተሸከሙ ፡ ወዲህ ፡ በሌትና ፡ በቀን ፡ በሰዓትና ፡ በደቂቃ ፡ የሚሠሩት ፡ ኢትየጵያ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ እንደ ፡ አፍሪካ ፡ መንግሥታት ፡ በግርጌ ፡ እንዳትቀር ፡ በልዑልነታቸው ፡ መሰላልነት ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ተራራ ፡ ወጥታ ፡ ከሠለጠኑት ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ እንድትገናኝና ፡ ከሥልጣኔያቸው ፡ መሳተፍን ፡ እንድታገኝ ፡ ነው ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የልዑል ፡ ኣልጋ ፡ ወራሽን ፡ የማሠልጠን ፡ ሥራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣትና ፡ አስተዋይ ፡ የሆነው ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ በደስታ ፡ ተቀብሎት ፡ ከመኳንንቱም ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዱ ፡ ይኸንኑ ፡ የልዑልነታቸውን ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ለማገዝ ፡ ሲሞክር ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃቸውን ፡ ለማሰናከል ፡ ይጥሩ ፡ ነበር ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ታግሠው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሁኔታ ፡ የሚሻሻልበትንና ፡ ከባዱም ፡ አስተዳደር ፡ የሚከናወንበትን ፡ በኋላቸውም ፡ በፊታቸውም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ተመልክተው ፡ ያለፈውንና ፡ መጪውን ፡ ጊዜ ፡ አመዛዝነው ፡ ውልውል ፡ በሌለው ፡ ቊርጠኛነት ፡ የኤውሮፓን ፡ የምዕራብ ፡ ሥልጣኔ ፡ ባገራቸው ፡ ለማስገባት ፡ ከነዚሁ ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ አደረጉ ። ወዲያውም ፡ የሠለጠነው ፡ ዓለምና ፡ ያልሠለጠነችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ልዩነታቸው ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሰፊው ፡ ለመረዳት ፡ ኤውሮፓ ፡ ሄደው ፡ የከተማውንና ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቱን ፡ የፋብሪካውንም ፡ ድርጅት ፡ እየዞሩ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ኤውሮፓ ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለማሠልጠን ፡ ለደቀኑት ፡ አሳብ ፡ የተረጋገጠ ፡ ምክንያት ፡ ሰጣቸው ።

ከዚያም ፡ ተመልሰው ፡ ያሰቡትን ፡ ሥራ ፡ ለመግለጽ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ታሪክ ፡ በስማቸው ፡ ሲያስታውሰው ፡ የሚኖረውን ፡ አቋቋመ ።

## ፩ኛ. የጽሕፈት ፡ ማኅተምና ፡ ጋዜጣ ።

የሰው ፡ ተዳሳሽ ፡ ሰውነቱ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምግብ ፡ ሕይወት ፡ ሲያገኝ ፡ ከዚያም ፡ ጋራ ፡ ላይኛውን ፡ አካሉን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ልብስ ፡ ሲያስጌጥ ፡ እንዲሁ ፡ ውሳጣዊ ፡ ሰውነቱ ፡ (አእምሮው)፡ የሚታደሰው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍትን ፡ ሲያስተውልና ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ በጋዜጣ ፡ ሲያነብ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ አገራችን ፡ እስከዚህ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የተበደለች ፡ በመሆኗ ፡ ብዙውን ፡ ነገር ፡ ሕዝባችን ፡ ከማስተዋል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ዘገየ ። በኤውሮፓ ፡ ባ1ዱ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ እስከ ፡ 30 ፡ የሚደርስ ፡ ጋዜጣ ፡ እየወጣ ፡ ባንዳንድ ፡ ቤሳ ፡ ለመላው ፡ ሕዝብ ፡ በየቀኑ ፡ ለማደል ፡ በተቻለበት ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ 1 ፡ መንፈሳዊ ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ መጽሐፍ ፡ ባመትና ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ በብራና ፡ ላይ ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ተጽፎ ፡ የኢትዮጵያን ፡ አንዳንዶቹ ፡ መኳንንት ፡ ወይም ፡ ቀሳውስት ፡ ከውስጤ ፡ ያለውን ፡ ጥቅስ ፡ እየቈጠቡ ፡ ለጠያቂያቸው ፡ ለማስረዳት ፡ ከመጥቀም ፡ በቀር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በጽሕፈትና ፡ በንባብ ፡ በኩል ፡ ሊረዳው ፡ ስላልቻለ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ስሙ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በዓለም ፡ የታወቀውን ፡ ብርሃንና ፡ ሰላም ፡ የሚባለውን ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ባ1914 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መስከረም ፡ 3 ፡ ቀን ፡ አቋቋሙ ። በዚህም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ የሥጋዊና ፡ የመንፈሳዊ ፡ መጻሕፍት ፡ ታትመው ፡ ብዙ ፡ ጠቀሜታ ፡ ሰጥተዋል ። ዳግም ፡ ጣፋጭ ፡ ንግግርና ፡ ምክር ፡ ለሕዝብ ፡ የሚመግቡ ፡ አንቀጾችን ፡ የያዙ ፡ ጋዜጦች ፡ እየታተሙ ፡ በየሳምንቱ ፡ ይወጣሉ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ማተሚያ ፡ ቤት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚደረገው ፡ ማንኛውም ፡ ምክርና ፡ ተግሣጽ ፥ የዕለት ፡ ወሬ ፥ ሹም ፡ ሽር ፥ ዐዋጅ ፥ ማስታወቂያ ፥ ያስተዋዮች ፡ አሳብ ፡ እየታተመ ፡ ሲወጣ ፡ እንዲሁ ፡ በኤውሮፓ ፡ የሚደረገውን ፡ በቀጥታ ፡ ለማስረዳትና ፡

ሊቃውንቱም ፡ ከሚጽፉት ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ በማጣራት ፡ የሚያትም ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ የሚባለው ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ቆመ ።

## 2ኛ. የወታደር ፡ ድርጅት ።

ያንድ ፡ መንግሥት ፡ የነፃነቱ ፡ መሠረት ፡ የንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ የክብሩ ፡ ቀናተኛ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ነው ። በጠቅላላው ፡ ሲታሰብ ፡ ነጋዴም ፡ አራሽም ፡ አገሩን ፡ ይወዳል ። ነገር ፡ ግን ፡ ላገራቸው ፡ ነጻነት ፡ ለንጉሣቸው ፡ ክብር ፡ ሕይወታቸውን ፡ ለማሳለፍ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ የሚሰለፉ ፡ ወታደሮች ፡ ናቸው ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ የድል ፡ ሚዛን ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ሲያዘነብል ፡ ለጠላት ፡ እጅን ፡ በመስጠት ፡ ፈንታ ፡ ሕይወታቸውን ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ አጥፍተው ፡ የወታደርነታቸውን ፡ ክብር ፡ ያለማሉ ። የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ከተቋቋመ ፡ ዠምሮ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዠግኖችና ፡ ሞትን ፡ የሚንቁ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ወታደሮች ፡ በየጊዜው ፡ ከሚነሣ ፡ ጠላታቸው ፡ ጋራ ፡ እየተዋጉ ፡ አገራቸውንና ፡ ንጉሣቸውን ፡ አገልግለው ፡ ሕይወታቸውን ፡ ያሳለፉ ፡ ተርፈዋል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ በዠግንነት ፡ ስሙ ፡ የተጠራው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ እንግዳ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ በሚመጣበትና ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ በሆነ ፡ ቀን ፡ ኩታውን ፡ እንደ ፡ ለበሰ ፡ አንዱ ፡ ጠመንዣውን ፡ በትከሻው ፡ ሲይዝ ፡ 1ኛው ፡ በጐኑ ፡ ሲያንጠለጥል ፡ ጭፍራው ፡ ኣለቃውን ፡ ሲቀድመው ፡ ለማየት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ አልነበረም። በሰልፍም ፡ ቀን ፡ በንጉሥ ፡ ነገሥቱና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ፊት ፡ ተዥመልምሎ ፡ ገሚሱ ፡ እያቅራራ ፡ ገሚሱ ፡ ከሰልፉ ፡ እየተለየ ፡ ቆሞ ፡ ሲፎክር ፡ የጥንትን ፡ ልማድ ፡ ያስታውስ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በሌሎች ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ ከመቶ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ከሚደረገው ፡ የሰልፍ ፡ ዐቅድ ፡ ጋራ ፡ ሲመዘን ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ይኸው ፡ ዠግንነት ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ 1 ፡ ልብ ፡ ሆኖ ፡ ባንድ ፡ አሳብና ፡ መንፈስ ፡ ተመርቶ ፡ አገሩን ፡ ለማገልገል ፡ በቂ ፡ እንዲሆን ፡ ከሚሠሩት ፡ ጋራ ፡ እንዲሁም ፡ አዲሱን ፡ የሰልፍ ፡ ትምህርት ፡ ተምሮ ፡ ባንድ ፡ ዐይነት ፡ አረማመድ ፡ ባንድ ፡ ዐይነት ፡ ልብስ ፡ አምሮ ፡ በተመልካቹ ፡ ፊት ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝ ፡ ከኤውሮፓ ፡ የሰልፍ ፡ ኣስተማሪዎች ፡ አስመጥተው ፡ በጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የወታደር ፡ ድርጅት ፡ ተደረገ ። እነዚህንም ፡ ባዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ የተደራጁትን ፡ የክብር ፡ ዘበኞች ፡ በሚሰለፉበት ፡ ቀን ፡ ሕዝቡ ፡ ለማየት ፡ እየናፈቀ ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ትከሻ ፡ ላይ ፡ ይንጠላጠል ፡ ነበር ።

በዚሁ ፡ በክብር ፡ በኞች ፡ ውስጥ ፡ በሥራቸው ፡ ተመስግነው ፡ ጥር ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1927 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግርማዊነታቸው ፡ የንጉሥ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ ከደፉ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ማዕርጋቸው ፡ ኒሻን ፡ የተቀበሉት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ።

1ኛ. ፡ ቀኛዝማች ፡ መኩሪያ ፡ ባንት ፡ ይርጉ ፡ (አሁን ፡ ደጃዝማች ፡ የተባሉት) ።
2ኛ. ፡ የሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ (አሁን ፡ ደጃዝማች ፡ የተባሉት) ።
3ኛ. ፡ » ኀይለ ፡ ማርያም ።
4ኛ. ፡ » ዳኜ ፡ ወዳጆ ፡ (ማይጨው ፡ በዠግንነት ፡ የሞተው) ።
5ኛ. ፡ » ሰይፉ ።
6ኛ. ፡ » ካሳ ፡ አብርሀ ።
7ኛ. ፡ » ክፍሌ ፡ ዕርገቱ ፡ (ኣሁን ፡ ኮሎኔል ፡ የተባሉት) ።
8ኛ. ፡ የሻምበል ፡ ዠዎዢሉዊ።
9ኛ. ፡ » ገብረ ፡ ማርያም ።
10ኛ. ፡ » አሻግሬ ።
11ኛ. ፡ » ውቤ ፡ ኀይለ ፡ ማርያም።
12ኛ. ፡ » ንገሻ ፡ ዐሊ ።
13ኛ. ፡ » ሺበሺ ፡ ደያስ ፡ (ማይጨው ፡ በታላቅ ፡ ዠግንነት ፡ የወደቀው)።
14ኛ. ፡ » ለገሰ ፡ አያኔ ፡ (ማይጨው ፡ በዠግንነት ፡ የሞተው) ።
15ኛ. ፡ » ዐወቀ ፡ ወልደ ፡ መድኅን ።
16ኛ. ፡ ሻምበል ፡ መኰንን ፡ አደፍርሰው ።
17ኛ. ፡ » ኣርኣያ ፡ ዘረፉ።
18ኛ. ፡ » ኀይሌ ፡ ሮባ ።
19ኛ. ፡ » ወርቄ ፡ ደስታ።
20ኛ. ፡ » ገብረ ፡ ማርያም ፡ ይብሳ ።
21ኛ. ፡ » ዘውዴ ፡ ወዳጄ ።
22ኛ. ፡ » ረታ።
23ኛ. ፡ » በቀለ ፡ ኀይሌ ።
24ኛ. ፡ » ገብሬ ፡ ድረስ ።
25ኛ. ፡ » ይማም ።
26ኛ. ፡ » በዛብህ ፡ ረታ ።
27ኛ. ፡ » ዘውዴ ፡ ተሰማ ።
28ኛ. ፡ » መብራቴ ፡ ኮላሴ ፡ (ማይ ጨው ፡ በዠግንነት ፡ የወደቀው) ።
29ኛ. ፡ » ተሰማ ፡ ያኔ ፡ (ማይ ጨው ፡ በዠግንነት ፡ የሞተው) ።

30ኛ. ፡ » ወርቁ ፡ አየለ ፡፡
31ኛ. ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ጋሻው ፡ በዛ ፡ አባ ፡ ናዳ ፡፡
32ኛ. ፡ » ገብረ ፡ ማርያም ፡ ፍላቴ ፡፡
33ኛ. ፡ » ተበጀ ፡ ካሳ ፡፡
34ኛ. ፡ » ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘመዴነኸ ፡፡
35ኛ. ፡ » ኀይሌ ፡ በዛብሽ ፡፡
36ኛ. ፡ » ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ በላይነኸ ፡፡
37ኛ. ፡ » ለጥ ፡ ይበሉ ፡ ተሣገይ ፡፡
38ኛ. ፡ » ዓለማየሁ ፡ ጣሴ ፡፡
39ኛ. ፡ » ይቁም ፡ ኣባተ ፡፡
40ኛ. ፡ » አመነ ፡ መርሻ ፡፡
41ኛ. ፡ » ከተማ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡፡
42ኛ. ፡ » ከተማ ፡ ፋንታዬ ፡፡
43ኛ. ፡ » ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በላይነኸ
44ኛ. ፡ » ኀይሌ ፡ ታዴዎስ ፡፡
45ኛ. ፡ » ለማ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡፡
46ኛ. ፡ » አዝምቴ ፡ ኣንዳርጌ ፡፡
47ኛ. ፡የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡፡
48ኛ. ፡ » መኰሪያ ፡ ኣባ ፡ ሻውል ፡፡
49ኛ. ፡ » ጐርፌ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡፡
50ኛ. ፡ » መንገሻ ፡ እሸቴ ፡፡
51ኛ. ፡ » ደመቀ ፡ ወረደ፡፡
52ኛ. ፡ » ዓለሙ ፡ ጣሹ ፡፡
53ኛ. ፡ » ደመቀ ፡ ደግነኸ ፡፡
54ኛ. ፡ » በላቸው ፡ ወልዴ፡፡
55ኛ. ፡ » ሰሙ ፡ ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡፡
56ኛ. ፡ » መታፈሪያ ፡ ይግለጡ ፡፡
57ኛ. ፡ » ደስታ፡ ቡልቡላ ፡፡
58ኛ. ፡ » ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡፡

59ኛ. ፡ » አበጋዝ ፡ ጸጋዬ ።
60ኛ. ፡ » ወልዴ ፡ ይመር ።
61ኛ. ፡ » ደምሴ ፡ ብሩ ።
62ኛ. ፡ » ኣዳሬ ፡ አረዶ ።
63ኛ. ፡ » ገሰሰ ፡ ኀይለ ፡ ማርያም ።
64ኛ. ፡ » ተፈራ ፡ መሸሻ ።
65ኛ. ፡ » ተክለ ፡ ማርያም ።
66ኛ. ፡ » አየለ ፡ መቻቺ ።
67ኛ. ፡ » ከበደ ፡ ይርጋ ።
68ኛ. ፡ » ኣበጋዝ ፡ ወልዴ ።
69ኛ. ፡ » ኣበበ ፡ ዳዲ ።
70ኛ. ፡ » ኪዳነ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ።
71ኛ. ፡ » ዕንቈ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ።
72ኛ. ፡ » ክፍሌ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ።
73ኛ. ፡ » እንግዳ ፡ ወርቅ ፡ ርገጤ ።
74ኛ. ፡ » ሥዩም ፡ ዘለቀ ።
75ኛ. ፡ » ገብረ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ።
76ኛ. ፡ » ተሾመ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ።
77ኛ. ፡ » አስፋው ፡ ሺበሺ ።
78ኛ. ፡ » መንግሥቱ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ።
79ኛ. ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ።
80ኛ. ፡ » ገብረ ፡ መድኅን ፡ በላቸው ።
81ኛ. ፡ » ተፈራ ፡ አየለ ።
82ኛ. ፡ » ሙላቱ ፡ አብጤ ።
83ኛ. ፡ » አየለ ፡ ወልደየስ ።
84ኛ. ፡ » አበባየሁ ፡ በላይነሽ ።
85ኛ. ፡ » ደስታ ፡ ሉል ፡ ሰገድ ።
86ኛ. ፡ » ወልደ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ።
87ኛ. ፡ » ብርሃኑ ፡ ደስታ።

88ኛ. ፡ » ሺበሺ ፡ ቸኰል ።
89ኛ. ፡ » ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ ተክሌ ።
90ኛ. ፡ » ዘውዴ ፡ ወርዶፋ።
91ኛ. ፡ » አስፋው ፡ ወርዶፋ ።
92ኛ. ፡ » ከበደ ፡ አይችሉሽም ።
93ኛ. ፡ » ተክለ ፡ ማርያም ፡ ጅማ ።
94ኛ. ፡ » ቱሉ ፡ ዳዲ።
95ኛ. ፡ » ወርቁ ፡ መንገሻ ።

ነገር ፡ ግን ፡ የነዚሁ ፡ ወታደሮች ፡ ድርጅት ፡ ደስ ፡ ያሰኘው ፡ በበዓል ፡ ቀን ፡ ባደረጉት ፡ ሰልፍ ፡ ብቻ ፡ አይደለም። ነገር ፡ ግን ፡ ከበላዮቻቸው ፡ እንደ ፡ ተሰበከላቸው ፡ ሁሉ ፡ በኩራትና ፡ በታላቅ ፡ ቊርጠኛነት ፡ በማይጨው ፡ ጦርነት ፡ ታሪክ ፡ ለዘለዓለም ፡ የማይረሳባቸውን ፡ ሥራ ፡ ሠርተዋል ። ይኸንም ፡ በስፍራው ፡ ስደርስ ፡ ለመጻፍ ፡ ስል ፡ አሁን ፡ ባጭሩ ፡ እተዋለሁ።

## 3ኛ. የትምህርት ፡ ቤት ።

ኢትዮጵያ ፡ በመዠመሪያ ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ መጥተው ፡ የኦሪትን ፡ ሕግ ፡ በሚያስተምሩ ፡ እየተመራች ፡ እውነተኛውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማምለክ ፡ ስትኖር ፡ በኋላም ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡ የተገኘው ፡ ክርስትና ፡ ከሐዋርያት በብዙ ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተሰበከ ፡ እንዲሁም ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በ330ኛው ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኣባ ፡ ሰላማ ፡ (ፍሬምናጦስ) ፡ ዠማሪነት ፡ ወንጌል ፡ ተሰብኮላት ፡ በኣፍሪካ ፡ ምሥራቅ ፡ እንደ ፡ ውቅያኖስ ፡ ባሕር ፡ በሰፋው ፡ የእስላም ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ በክርስቲያንነት ፡ እንደ ፡ ደሴት ፡ ሆና ፡ ራሷን ፡ ችላ ፡ ተቀምጣ ፡ ኖረች ።

የኤውሮፓ ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥታት ፡ ከሠሯቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ በቁጥር ፡ የሚበዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ አሠራች ። በየቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጠው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕፃናት ፡ የሚያስተምሩ ፡ መምህራን ፡ ብዙዎች ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ መምህራን ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚገባውን ፡ ተማሪ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተሰኘው ፡ ዕድሜው ፡ ሊበቃው ፡ የማይችለውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ በማስተማር ፡ ኖሩ ። ፊደል ፥ ፊደለ ፡ ሐዋርያ ፥ ግብረ ፡ ሐዋርያት ፥ ዳዊት ፥ አርጋኖን ፥ ውዳሴ ፡ ማርያም ፥ በንባብና ፡ በዜማ ፥ ምዕራፍ ፡ በያይነቱ ፡ ጾመ ፡ ድጓ ፥ ድጓ ፥ መዋሥዕት ፥ ዝማሬ ፥ ቅዳሴ ፥ አቋቋም ፥ ቅኔ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስን ፡ « በአንድም» ፡ አተረጓጐም ።

የኢትዮጵያ ፡ ተማሪ ፡ ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘረውን ፡ ሲማር ፡ በናት ፡ ባባቱ ፡ መጋቢነት ፡ ባቅራቢያው ፡ ባለ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ እየተማረ ፡ ከሚያድገው ፡ ይልቅ ፡ ከናት ፡ ካባቱ ፡ ተለይቶ ፡ በሩቅ ፡ አገር ፡ ተሰዶ ፡ በቀፈፋ ፡ እንጀራ ፡ የሚማረው ፡ ይበልጣል ። ይህንንም ፡ ከልጅነቱ ፡ እስከ ፡ ሽምግልናው ፡ ያለውን ፡ ጊዜ ፡ የፈጀበትን ፡ ትምህርት ፡ በተለይ ፡ ቤተ ፡ ክህነትን ፡ በማገልገል ፡ ሲፈጽም ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

ይኸውም ፡ እስከ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ የተለወጠ ፡ ነገር ፡ ሳይገኝለት ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ዛሬ ፡ ባይናችን ፡ የምናየው ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ሕንፃ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ ተመሥርቶ ፡ አስተማሪዎችም ፡ ተማሪዎችም ፡ በወንበር ፡ ተቀምጠው ፡ በደንብ ፡ ማስተማር ፡ ሲዠምሩ ፡ ታየ ።

ይኸውም ፡ እንደ ፡ ብርቅ ፡ በሚታይበት ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ በልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ትጋት ፡ ካ1917 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ አንሥቶ ፡ ከዚህ ፡ ግርጌ ፡ ያሉት ፡ ተማሪ ፡ ቤቶች ፡ ኣዲስ ፡ አበባ ፡ በየስፍራው ፡ ተከፈቱ ።

1ኛ. የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ተማሪ ፡ ቤት ።
2ኛ. የቅዱስ ጊዮርጊስ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ።
3ኛ. የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ።
4ኛ. የሆለታ ፡ የወታደር ፡ ተማሪ ፡ ቤት ።
5ኛ. የእቴጌ ፡ መነን ፡ ትምህርት ፡ ቤትና ፡ ሌሎችም ፡ ተማሪ ፡ ቤቶች ፡ በያውራጃው ።

በነዚህም ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ተቀጥረው ፡ የመጡት ፡ መምህራን ፡ ካገራችን ፡ ተወላጆች ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ በየክፍሉ ፡ ሒሳብ ፥ ታሪክ ፥ ሥዕል ፥ ጅዖግራፊ ፥ ሲያንስ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ትምህርት ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ጋራ ፡ ሰዓት ፡ እያቀያየሩ ፡ የዓለም ፡ ሥልጣኔ ፡ ያለበትን ፡ ትምህርት ፡ በመልኩና ፡ ባገባቡ ፡ ያስተምሩ ፡ ዠመር ።

በውጭ ፡ አገር ፡ ተምረው ፡ ከተመለሱት ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ እላይ ፡ የተዘረዘረው ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በየክፍላቸው ፡ ለማስተዳደር ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ አዘጋጅቷል ።

ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ለመንግሥታቸው ፡ ሥልጣኔ ፡ መዠመሪያ ፡ የሚሆነውን ፡ አቋቁመው ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ ታየ ፡ ተብሎ ፡ የሚደነቀውን ፡ ባስፋፉ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከመኳንንት ፡ እስከ ፡ መሳፍንት ፡ ከሊቃውንት ፡ እስከ ፡ ጳጳሳት ፡ ያለው ፡ ባንድነት ፡ የንጉሥ ፡ ዘውድ ፡ ይገባቸዋል ፡ ብሎ ፡ በማስታወቁ ፡ ላይ ፡ እንዲሁም ፡ የግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ መስከረም ፡ 27 ፡ ቀን ፡ 1921 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ መካነ ፡ ሥላሴ ፡ የንጉሥነት ፡ ዘውድ ፡ ጫኑ ።

ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ መዠመሪያ ፡ ባልጋ ፡ ወራሽነት ፡ 2ኛ ፡ በንጉሥነት ፡ 3ኛ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ እላይ ፡ ከተመለከተው ፡ በቀር ፡ በየጊዜው ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ አቋቋሙ ። ከዚሁ ፡ ውስጥ ፡ 1921 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በነሐሴ ፡ 12 ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አይሮፕላን ፡ አስመጡ ። 19123 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመስከረም ፡ 1 ፡ ቀን ፡ የወንጀለኛን ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ አቋቋሙ ። በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ጥቅምት ፡ 22 ፡ ቀን ፡ ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ሐውልት ፡ አቆሙ ። በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ሐምሌ ፡ 9 ፡ ቀን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አቆሙ ። በዚሁ ፡ ዓመትና ፡ በዚሁ ፡ ወር ፡ 14ኛ ፡ ቀን ፡ የነፋስ ፡ ስልክ ፡ መሠረቱ ። ባ1924 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጥቅምት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ባንክ ፡ አቆሙ ። በዚሁ ፡ ዓመትና ፡ በዚሁ ፡ ወር ፡ 23 ፡ ቀን ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ ከፈቱ ።

# ምዕራፍ ፡ 52 ።

## የራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወሌ ፡ መሸፈትና ፡ በጦርነት ፡ መሞት ።

3 ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ባርበኝነት ፡ ነጻነቷን ፡ ይዛ ፡ የኖረችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይጐድላት ፡ የነበረውን ፡ የኤውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትጋት ፡ ለማግኘት ፡ በሯን ፡ በከፈተች ፡ ጊዜ ፡ አሮጌውን ፡ ዘመንና ፡ አዲሱን ፡ ዘመን ፡ በተቀላቀለ ፡ አሳብ ፡ የሚወዱ ፡ ሕዝቦች ፡ ባሉበት ፡ መንግሥት ፡ የሚደርሰው ፡ ችግር ፡ እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ አልቀረም ።

የአሮጌው ፡ ዘመን ፡ ወዳጆች ፡ አዲሱን ፡ ሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ሃይማኖትና ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ እያስደገፉ ፡ በናትና ፡ በልጅነት ፡ የሚተያዩትን ፡ ልብ ፡ ለመክፈል ፡ አበክረው ፡ ከመጣራቸው ፡ በቀር ፡ በውሳጣዊ ፡ ፖለቲካ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በገሃድ ፡ እየገለጹ ፡ ለብዙም ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ መፍሰስ ፡ ምክንያት ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ምስጋና ፡ የሚገባው ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ የፖለቲካ ፡ አካሄድ ፡ የሥልጣኔውን ፡ እርምጃ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ነገሩን ፡ በልበ ፡ ሰፊነት ፡ በመመልከት ፡ ሁሉንም ፡ ይታገሣቸው ፡ ነበር ። ያፈቀሯቸውን ፡ ብቻ ፡ አፍቅረው ፡ ለደጉ ፡ ተግባራቸው ፡ ዕንቅፋት ፡ የሆኑትን ፡ በጠብ ፡ ዐይን ፡ ሳይመለከቱ ፡ ዐይነቱ ፡ በርከቶ ፡ የሚታየውን ፡ ሰብአዊ ፡ ጠባይ ፡ አድልዎ ፡ በሌለበት ፡ አስተያየት ፡ እየተመለከቱ ፡ ሁሉንም ፡ በትዕግሥት ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ አኳኋን ፡ በፊቱ ፡ የሰመረ ፡ በመሆኑ ፡ ያሳባቸውንና ፡ የሥራቸውን ፡ ፍጻሜ ፡ አምላካዊ ፡ ሥልጣን ፡ አከናወነላቸው ።

እንዲሁም ፡ ከፉውን ፡ በክፉ ፡ ሳያሸንፉ ፡ ክፉውን ፡ በደግ ፡ አሸንፈው ፡ ሐሰትም ፡ በእውነት ፡ ጉረሮ ፡ በተዋጠ ፡ ጊዜ ፡ የቀሩት ፡ ነገሩን ፡ በመረዳት ፡ ሥልጣኔውን ፡ በጠብ ፡ ዐይን ፡ የሚመለከቱበትን ፡ ስፍራ ፡ እያደር ፡ እየለቀቁ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ መንፈስ ፡ ሲጐዳኙ ፡ በዚያ ፡ መንገድ ፡ በዳንዴነት ፡ የግድ ፡ ለመዝለቅ ፡ የጣሩ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወሌ ፡ ብቻ ፡ ሆነው ፡ ተገኙ ። ርሳቸውም ፡ ላሮጌው ፡ ልማድ ፡ ጠበቃና ፡ ተከራካሪ ፡ ለመሆን ፡ መሸፈታቸው ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ያላገባብ ፡ ለሚፈሰው ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ በማሰብ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ታላቅ ፡ ሐዘን ፡ ተሰማው ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አጥፊውን ፡ የሚቀጣበትን ፡ ከንዱን ፡ ከመሰንዘሩ ፡ በፊት ፡ ደብዳቤና ፡ መልክተኛ ፡ መነኰሳትም ፡ ሳይቀሩ ፡ እየላከ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ የምሕረት ፡ እጁን ፡ ለራስ ፡ ጉግሳ ፡ ዘርግቶ ፡ ከክፉ ፡ ሥራቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ ለመናቸው ። ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ግን ፡ የምሕረቱንና ፡ የሰላሙን ፡ ቀን ፡ ለጦርነት ፡ የመዘጋጃ ፡ ጊዜ ፡ አደረጉት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለኢጣሊያ ፡ የቁሳር ፡ ግዛት ፡ እንድትሆን ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በሚደክመው ፡ በባሮን ፡ ራይሞንዶ ፡ ፍራንኬቲና ፡ በፖሌራ ፡ በኩል ፡ የሚደረገው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ፖለቲካ ፡ ከኋላ ፡ ይቀሰቅሳቸው ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እጃቸውን ፡ እንዲሰጡና ፡ እንዲታረቁ ፡ ተስፋ ፡ ተደርጎ ፡ በደብዳቤም ፡ በመነኰሳትም ፡ ተለምነው ፡ ለመልካም ፡ ግብ ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ ሁሉ ፡ በቍርጥ ፡ እንቢ ፡ ማለታቸው ፡ ስለ ፡ ታወቀ ፡ ደጃዝማች ፡ ሙሉጌታ ፡ ወታደር ፡ ይዘው ፡ ሄደው ፡ እንዲወጓቸው ፡ ያዝ ፡ ዘንድ ፡ ለቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሐዘን ፡ ያለበት ፡ ግዴታ ፡ ሆነበት ።

ደጃዝማች ፡ ሙሉጌታም ፡ (በኋላ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቀጥሎ ፡ ራስ ፡ የተባሉት) ፡ የጦር ፡ ሰራዊታቸውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ተነሥተው ፡ በደሴ ፡ አድርገው ፡ ጕዟቸውን ፡ ቀጠሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወሌና ፡ በራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ የሚታዘዘው ፡ ያ1 ፡ እናት ፡ ልጅ ፡ የሆነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ በጌምድርና ፡ ዋድላ ፡ ወሰን ፡ ዘቢጥ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ባ1922 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመጋቢት ፡ 22 ፡ ቀን ፡ ጦርነት ፡ ተዠምሮ ፡ ሲዋጉ ፡ ወዲያው ፡ ራሳቸው ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወሌ ፡ በጦርነቱ ፡ ውስጥ ፡ ሞተው ፡ የእንቢተኛነት ፡ ዋጋቸውን ፡ ተቀበሉ ።

# ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ




ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገስት ፡ ዘኢትዮጵያ

# የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ 53 ።

## የንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዕረፍት--- የግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ተፈሪ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ መድሩት ።

ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ባባታቸው ፡ ዙፋን ፡ ባ1909 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መስከረም ፡ 17 ፡ ቀን ፡ ተቀምጠው ፡ እስከ ፡ 1922 ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ «ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ወለቱ ፡ ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ» ፡ እየተባሉ ፡ በደግነትና ፡ በርኅራኄ ፡ 13 ፡ ዓመት ፡ ከ6 ፡ ወር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲገዙ ፡ በመጨረሻ ፡ ሕመም ፡ አድሮባቸው ፡ ነበርና ፡ በመጋቢት ፡ 24 ፡ ቀን ፡ 1922 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ዐርፈው ፡ በታላቅ ፡ ሐዘንና ፡ ፍታት ፡ ባባታቸው ፡ መቃብር ፡ በመታሰቢያ ፡ ቤት ፡ ተቀበሩ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ተፈሪ ፡ «ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ» ተብለው ፡ መንግሥትን ፡ ያዙ ።

የዘውዱም ፡ በዓል ፡ እንዲከበር ፡ የተወሰነው ፡ ንግሥት ፡ ካረፉ ፡ በኋላ ፡ በ7ኛው ፡ ወር ፡ በጥቅምት ፡ 23 ፡ ቀን ፡ 1923 ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ነበርና ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ አከባሪ ፡ ለመሆን ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገኝ ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አኳኋን ፡ ሲያጌጥና ፡ እንዲሁም ፡ ለበዓሉ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደሚገባው ፡ ሲጋጅ ፡ ቈየ ።

በዚህም ፡ በዘውዱ ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ ከሚገኘው ፡ ደስታ ፡ ተሳታፊ ፡ ለመሆን ፡ ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ውስጥ ፡ የታወቁት ፡ እንደራሴዎቻቸውን ፡ ልከው ፡ ነበር ።

የመጡትም ፡ ዝርዝራቸው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

1ኛ፡- ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ልዑል ፡ ሔንሪ ፡ የግሎስተር ፡ መስፍን ።
2ኛ፡- ከአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ክቡር ፡ ሀ ፡ መሪ ፡ ጀኮፔ ።
3ኛ፡- ከፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ክቡር ፡ ማርሻል ፡ ፍራንሺ ፡ ዳስፒሬ ።
4ኛ፡- ከጃፓን ፡ መንግሥት ፡ አምባሳደሩ ፡ ክቡር ፡ ሙሴ ፡ ኤዝቡር ።
5ኛ፡- ከጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ክቡር ፡ ባሮን ፡ ቦን ፡ በልተሐውዘን ።
6ኛ፡- ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ልዑል ፡ ፌርዲናንዶ ፡ የኡዲኒ ፡ መስፍን ።



# የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ።

7ኛ፡- ከግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ክቡር ፡ ኮንት ፡ ፒ ፡ መታክሳስ ።

8ኛ፡- ከስዊድን ፡ መንግሥት ፡ ክቡር ፡ ሆክ ፡ አርድ ፡ ዳቤልሳ ።

9ኛ፡- ከሆላንድ ፡ መንግሥት ፡ ክቡር ፡ ዮንሐሪ ፡ ል ፡ መንን ፡ ሔርስማድ።

10ኛ፡-ከቤልጅግ ፡ መንግሥት ፡ ክቡር ፡ ሙሴ ፡ ምክስም ፡ ዝራር ።


11ኛ፡-ከግብጽ ፡ መንግሥት ፡ ክቡር ፡ መሐመድ ፡ ቶፊቅ ፡ ነሲም ፡ ባሻ ።

እነዚህንም ፡ እላይ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ መንግሥታት ፡ እንደራሴዎች ፡ እያንዳንዳቸውን ፡ ተከትለው ፡ የመጡ ፡ ብዙ ፡ ሌሎችም ፡ ሹማምንቶች ፡ ነበሩ፥ እነሱም ፡ የንግሡ ፡ በዓል ፡ 15 ፡ ቀን ፡ ያኸል ፡ ሲቀረው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገብተው ፡ ከየመንግሥታቸው ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተላከውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ከደብዳቤ ፡ ጋራ ፡ አበረከቱ ።

እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኣውራጃ ፡ ያሉ ፡ አገረ ፡ ገዥዎችና ፡ ሹማምንቶች ፡ ከነጭፍሮቻቸው ፡ መጥተው ፡ ከተማውን ፡ በሰው ፡ ሞልተውት ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የዘውዱ ፡ በዓል ፡ እንዲሆን ፡ ከተወሰነው ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ በጥቅምት ፡ 22 ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ልዑላን ፡ ልጆቻቸውን ፡ ይዘው ፡ በመናገሻ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄደው ፡ አደሩ ። ሌሊቱንም ፡ ቀሳውስቱና ፡ ጳጳሱ ፡ ሥርዐተ ፡ ንግሥ ፡ ሲያደርሱ ፡ አደሩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በማግስቱ ፡ ጥቅምት ፡ 23 ፡ ቀን ፡ 1923 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡

1. ዲያቆናትና ፡ ቀሳውስት ፡ ጕሥዐ ፡ ልብየን ፡ ቅንት ፡ ሰይፈከ ፡ እስከሚለው ፡ ድረስ ፡ እያዜሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ከተደረደረው ፡ ላይ ፡ ሰገባው ፡ በወርቅና ፡ ባልማዝ ፡ ያጌጠውን ፡ ሰይፍ ፡ አንሥተው ፡ በዚሁ ፡ ሰይፍ ፡ ዐመፀኞችን ፡ ቅጣበት ፡ ፈቃደኞችን ፡ ሹምበት ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ ፍረድበት ፡ ብለው ፡ ባርከው ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሰጥተው ፡ በቀኝ ፡ ጐናቸው ፡ ታጠቁት ።
2. አርትዕ ፡ ተሠራሕ ፡ ወንገሥ ፡ በትረ ፡ ጽድቅ ፡ ወበትረ ፡ መንግሥትከ ፡ እያሉ ፡ አዚመው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱም ፡ በትረ ፡ ኃይል ፡ ይፌኑ ፡ ለከ ፡ የሚለውን ፡ ደግመው ፡ ከባረኩ ፡ በኋላ ፡ በትረ ፡ መንግሥቱን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሰጥተው ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ ያዙ ።
3. ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ ባለአልማዝ ፡ ቀለበት ፡ ሁለት ፡ ባለወርቅ ፡ ጦሮች ፡ በወርቅ ፡ ያጌጠ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይዘው ፡ ልብሰ ፡ መንግሥቱን ፡ ከለበሱ ፡ በኋላ ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብተው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ እግዚአ ፡ በኀይልከን ፡ እየደገሙ ፡ የሚገባውን ፡ ጸልየው ፡ ሲጨርሱ ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቀርበው ፡ ይኸን ፡ ዘውድ ፡ የጽድቅና ፡ የምስጋና ፡ ዘውድ ፡ ያድርግልዎ ፡ ብለው ፡ ደፉላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥቱን ፡ ተቀብተው ፡ የወርቁን ፡ ዘውድ ፡ ከጫኑ ፡ በኋላ ፡ ንኡስ ፡ አነ ፡ እምአኀውየ ፡ የሚለውን ፡ ወቀብዐኒ ፡ ቅብዐ ፡ ቅዱስ ፡ እስከሚለው ፡ አንብበው ፡ ተቀመጡ ።



ሣህለ ሥላሴ ንጉሠ ሸዋ

በጊዜው ካለው የክሊሼ አኳኋንና ከስፍራው አቀማመጥ ኣለመመቸት የተነሳ በዚህ የዘር ፡ ግንድ ውስጥ ስማቸው ላይጻፍ የቀሩት በዚህ ዓይነት እንኳን የማይቻል ሲሆን ወደፊት ፡ በሚ ጻፍ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ዘርዝረን ፡ ለመጻፍ ፡ የተዘጋጀን ፡ ነን ፡ 10 . 7 . 36 ፡ ተ . ጻ . መ ፡

እንደዚሁም ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ የሚገባው ፡ ሥርዐት ፡ ተደርጎ ፡ ባለአልማዝ ፡ ቀለበት ፡ አድርገው ፡ ልብሰ ፡ መንግሥት ፡ ለብሰው ፡ መዘምራኑ ፡ ኣዋልደ ፡ ንግሥት ፡ ለከብርከ ፡ ወትቀውም ፡ ንግሥት ፡ በየማንከ ፡ የሚለውን ፡ አድርሰው ፡ ሲጨርሱ ፡ ዘውዱን ፡ ሁለት ፡ ቆሞሳት ፡ ለጃንሆይ ፡ አቀረቡ ። ጃንሆይም ፡ ለእቴጌዪቱ ፡ ይደፉላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ሰጧቸው ፥ ሊቀ ፡ ጳጳሱም ፡ የሚገባውን ፡ ጸሎት ፡ አድርሰው ፡ በእቴጌ ፡ መነን ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ጫኑላቸው ። እቴጌም ፡ ዘውዱን ፡ እንደ ፡ ደፉ ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ ባንገት ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ወዲያው ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ በተዘረጋው ፡ የወርቅ ፡ ወንበር ፡ ተቀመጡ ።

በዚሁም ፡ ቀን ፡ ልዑል ፡ ኣስፋ ፡ ወሰን ፡ ለአልጋ ፡ ወራሽነት ፡ የሚገባው ፡ ወግ ፡ ተፈጽሞ ፡ የወርቅ ፡ አክሊል ፡ ደፉ ።

ከዚህ ፡ በኋላም ፡ መሳፍንቱም ፡ መኳንንቱም ፡ ሁሉ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ያንግሥዎ ፡ እያሉ ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ሁሉም ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አጨበጨቡና ፡ ሥርዐተ ፡ ንግሡ ፡ ተፈጽሞ ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ጉዞ ፡ ተዠመረ ።

ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ ተልከው ፡ የመጡት ፡ መሳፍንቱ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መሳፍንት ፡ መኳንንቱ ፡ ከመኳንንት ፡ ጋራ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አውቶሞቢል ፡ ተቀምጠው ፡ እንደየማዕርጋቸው ፡ ተከታትለው ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ በወርቅ ፡ ሠረገላ ፡ ተቀምጠው ፡ በሰልፉና ፡ በጭብጨባው ፡ በእልልታው ፡ መካከል ፡ ሲያልፉ ፡ የማማሩ ፡ አኳኋን ፡ ከግምት ፡ በላይ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ አጀብ ፡ ባይን ፡ ታይቶ ፡ ካለመጠገቡ ፡ የተነሣ ፡ በዘበኝነት ፡ በደንብ ፡ ከተሰለፈው ፡ ወታደር ፡ በስተቀር ፡ የቀረው ፡ አንዳንዱ ፡ ሕዝብ ፡ በተሰለፈበት ፡ ስፍራ ፡ ሆኖ ፡ ግርማ ፡ ያለውን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱንና ፡ የእቴጌዪቱን ፡ አጀብ ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ ድጋሜ ፡ እየፈለገ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሩጫ ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለማየት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ደርሰው ፡ በዙፋናቸው ፡ ሲቀመጡ ፡ 101 ፡ ጊዜ ፡ መድፍ ፡ ተተኰሰና ፡ ወዲያውም ፡ ለመሳፍትንና ፡ ለመኳንንት ፡ ለውጭ ፡ ነገር ፡ መኰንኖች ፡ ለካህናት ፡ ጭምር ፡ ግሩም የሆነ ፡ ግብር ፡ ሲያደርጉ ፡ ሰነበቱ።

እንደዚሁም ፡ ያለ ፡ ያማረ ፡ ሥርዐተ ፡ ንግሥ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከነገሡት ፡ ነገሥታት ፡ ለማንም ፡ ንጉሥ ፡ መደረጉን ፡ በማንኛውም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ አናገኝም ።

በዚህም ፡ ቀንና ፡ ሰሞን ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የመጡት ፡ እንግዶችና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ኣውራጃ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሹማምንቶች ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ተሰብስበው ፡ ተድላና ፡ ደስታ ፡ ሲያዩ ፡ ሰነበቱ።

ያዲስ ፡ ኣበባም ፡ ከተማ ፡ በሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ በግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ፎቶግራፍ ፡ አጊጦ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለምና ፡ አበባ ፡ ደምቆ ፡ ነበር ። ሌሊትም ፡ በኤሌትሪክ ፡ ብርሃን ፡ ከተማው ፡ ሲያሸበርቅ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።




## የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የመጡት ፡ መላክተኞች ፡ ወደ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ እየቀረቡ ፡ መንግሥታቸው ፡ ጽኑ ፡ ሰላም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በየመንግሥታቸው ፡ ስም ፡ የጋለ ፡ ምኞታቸውን ፡ ገልጸው ፡ እየተሰናበቱ ፡ ወዳገራቸው ፡ ተመለሱ ።

# ምዕራፍ ፡ 54 ።

## ስለ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መቆም ፥ በምክር ፡ ቤቱ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተናገሩት ፡ ዲስኩር ።

አጥፊ ፡ የሚቀጣበት ፡ አልሚ ፡ ዋጋ ፡ የሚያገኝበትና ፡ በጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ የሚተዳደርበት ፡ ትንሹም ፡ ትልቁም ፡ ደንብ ፡ ተጣርቶና ፡ ተከናውኖ ፡ በምክር ፡ ቤት ፡ ይወሰናል ። ይኸውም ፡ ሕግ ፡ በንጉሥና ፡ በመሳፍንት ፡ በመኳንንትና ፡ በሹማምንት ፥ በወታደርና ፡ በሌላው ፡ ሕዝብ ፡ በነጋዴና ፡ በገበሬ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ለይቶና ፡ አስተናብሮ ፡ የሚያስተዳድር ፡ ነው ።

በዚህም ፡ ደንብና ፡ ሕግ ፡ 1 ፡ የጐላ ፡ ግጭት ፡ ወይም ፡ ጦርነት ፡ እስኪያነቃንቀው ፡ ድረስ ፡ የማንኛውም ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

በዚህም ፡ ሕግ ፡ ፊት ፡ በዚያ ፡ መንግሥት ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ የትክክለኛነት ፡ መብት ፡ ስላለው ፡ ተርታው ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ የሚገባውን ፡ ከመፈጸም ፡ ጋራ ፡ ሊኰራበትና ፡ ሊመካበት ፡ ይችላል ።

ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ መንግሥቱ ፡ ከፍ ፡ የሚልበትና ፡ ካደጋ ፡ የሚሰወርበት ፡ መንገድ ፡ በዲፕሎማቲክ ፡ በኩል ፡ ይዘጋጃል ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በደንብ ፡ የተቀመጡ ፡ መማክርትና ፡ የሚመክሩበት ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ ባለመኖሩ ፡ ባለፈው ፡ ለነበሩት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነገሥታትና ፡ ሕዝብ ፡ ታላቅ ፡ ጒዳት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያለፈ ፡ ታሪክ ፡ ሳያስረዳን ፡ አይቀርም።

በዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የነበሩትን ፡ የወንጌል ፡ መላክተኞች ፡ ይልቁንም ፡ የእንግሊዝን ፡ መንግሥት ፡ ቆንስል ፡ ካፒቴን ፡ ካሜሮንን ፡ ሲያስሩ ፡ ነገሩ ፡ ለጊዜው ፡ በተደረገባቸው ፡ የአክብሮት ፡ ጒድለት ፡ የንዴት ፡ ማብረጃ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ጦርነት ፡ ሊያበቅል ፡ የሚችለው ፡ የነዚህ ፡ የውጭ ፡ መንግሥት ፡ ዜጋዎች ፡ እሥራት ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ተመከረበት ፡ የሚነግረን ፡ ታሪክ ፡ የለም።

ይኸም ፡ እሥራት ፡ ጦርነት ፡ ከማብቀሉ ፡ በፊት ፡ ንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ መላክተኞቹንና ፡ ቆንስሉን ፡ ፈተው ፡ ወደኔ ፡ ይላኩልኝ ፡ ብለው ፡ የልመና ፡ ደብዳቤ ፡ በጻፉ ፡ ጊዜ ፡ ይኸውም ፡ በምክር ፡ ቤት ፡ ተመክሮ ፡ እስረኞቹ ፡ ተለቀው ፡ በያገራቸው ፡ ገብተው ፡ ቢሆን ፡ የመቅደላ ፡ ጦርነት ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስንና ፡ የብዙ ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ እልቂት ፡ ባላስከተለም ፡ ነበር ።

እንዲሁም ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በምክር ፡ ቤት ፡ ሳያስመክሩ ፡ በሃይማኖትና ፡ በትምባሆ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሲያጉላሉ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመሆን ፡ አልችልም ፡ ብሎ ፡ የቈረጠውንም ፡ እስላም ፡ በቅጣት ፡ ካገሩ ፡ ሲያሳድዱት ፡ ይልቁንም ፡ ደርቡሾች ፡ ካገራቸው ፡ ለማስወጣት ፡ የከበቧቸውን ፡ ግብጾችን ፡ ለመርዳት ፡ አሽከራቸውን ፡ ሹም ፡ ዳኅና ፡ ፈንታን ፡ ልከው ፡ ከሱዳኖች ፡ ጋራ ፡ ከመተማ ፡ በፊት ፡ ሲዋጉ ፡ በምክር ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ በጣም ፡ ታስቦበት ፡ የተቈረጠ ፡ ባለመሆኑ ፡ ይህ ፡ የርዳታ ፡ ጦርነት ፡ የመተማን ፡ ጦርነት ፡ ሲወልድ ፡ እንዲሁም ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስና ፡ የብዙ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ሞት ፡ ከመተማ ፡ ጦርነት ፡ ተወለደ ። በግድም ፡ እስላሞችን ፡ ክርስቲያን ፡ ካልሆናችሁ ፡ ብለው ፡ ግፍ ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእስላሞች ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፡ እስከ ፡ መባል ፡ ደረሱ ።

ይህንንም ፡ የማስታውስበት ፡ ምክንያት ፡ የምክር ፡ ቤትንና ፡ የሕግን ፡ ጠቃሚነት ፡ ለመግለጽና ፡ ደግሞ ፡ የታላላቆቹ ፡ የሁለቱ ፡ ነገሥታቶች ፡ ሕይወት ፡ ባልታሰበ ፡ ጊዜ ፡ በመቈረጡ ፡ ስለሚያሳዝነኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እድገትና ፡ ለራሳቸው ፡ ክብር ፡ ሲሉ ፡ በዠግንነት ፡ የሞቱትን ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ ነገሥታት ፡ ለመንቀፍ ፡ አይደለም ።

ደግሞም ፡ በምክር ፡ ቤት ፡ የተቈረጠ ፡ በብዙ ፡ መማከርትም ፡ አእምሮ ፡ የታሰበበትና ፡ ሕዝብም ፡ የተቀበለው ፡ ሲሆን ፡ ኅሊናን ፡ አይወቅሥም ፡ ማለትነው ፡ እንጂ ፡ ተመክሮበት ፡ በተደረገ ፡ ዘመቻም ፡ ብዙ ፡ ነገሥታትና ፡ ሕዝብ ፡ እንደሚጠፉ ፡ አይሳትም ።

የሕግም ፡ ለሰው ፡ አስፈላጊነት ፡ የታወቀው ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ከመሆኑ ፡ ይልቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ መሆኑ ፡ ይገለጽ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቦቹን ፡ እስራኤልን ፡ በሙሴና ፡ በአሮን ፡ መሪነት ፡ ከምድረ ፡ ግብጽ ፡ ባወጣቸው ፡ ጊዜ ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ለኑሯቸው ፡ የሚጠቅማቸውን ፡ ዐሥር ፡ ሕግ ፡ በጁ ፡ ጽፎ ፡ በሙሴ ፡ አማካይነት ፡ ሰጣቸው ።

ይህም ፡ ሕግ ፡ አንዱ ፡ አድርግ ፡ (አባትሽንና ፡ እናትኽን ፡ አክብር ፡ አንዱ ፡ አታድርግ ፡ (አትግደል) ፡ ሲል ፡ ሁለቱም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የሕይወቱን ፡ መንገድ ፡ የሚያስተካክሉለት ፡ የክፉ ፡ አድራጎት ፡ ፍሬ ፡ ከሚያስገኘው ፡ አደጋ ፡ ፊት ፡ የሚከልሉት ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የሕይወቱ ፡ ጨቋኝ ፡ አይደሉም ።

ስለዚህ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ እያስፋፉና ፡ እየጨመሩ ፡ ሕዝባቸውን ፡ ለማስተዳደር ፡ የተወሰነ ፡ ሕግ ፡ አቆሙ ።

በኢትዮጵያም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ሕጉ ፡ የጊዜው ፡ የነገሥታቱ ፡ ፈቃድ ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሕግም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሲሠራበት ፡ ኖሯል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አንዱ ፡ ንጉሥ ፡ የገነባውን ፡ ቀጥሎ ፡ የሚነግሠው ፡ ንጉሥ ፡ አፍርሶ ፡ ሌላ ፡ የመሰለውን ፡ ሕግና ፡ ደንብ ፡ በማቆሙ ፡ ነገሥታት ፡ በተለዋወጡ ፡ ጊዜ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ችግር ፡ ሆኖ ፡ ይኖር ፡ ነበርና ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ከተቀመጡ

፡ ወዲህ ፡ ከኤውሮፓ ፡ ደንብና ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ የተያየና ፡ የተጣራ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ሕግ ፡ በምክር ፡ ቤት ፡ አስመክረው ፡ አቋቋሙ

ሕገ ፡ መንግሥቱም ፡ ባ55 ፡ አንቀጾች ፡ ተሰናድቶ ፡ በሐምሌ ፡ 4 ፡ ቀን ፡ 1921 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተገለጸና ፡ በፈረሙበት ፡ ጊዜ ፡ በተሰበሰበው፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ በጳጳሳቱና ፡ በቀሳውስቱ ፡ መካከል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ዲስኩር ፡ ተናገሩ።

«እኛ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመጠበቅ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተቀበልነው ፡ ኣደራና ፡ ለዚህ ፡ ለታላቁ ፡ ክብር ፡ ላበቃን ፡ አምላክ ፡ ባንደበት ፡ ብቻ ፡ ማመስገን ፡ ለዕለት ፡ በሚሆንና ፡ በሚጠፋ ፡ በቀላል ፡ አደራረግ ፡ መደለል ፡ አይበቃም ፡ በማለት ፡ ለዘለቄታ ፡ ቀዋሚ ፡ ለትውልድ ፡ ተሻጋጋሪ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚደርስ ፡ ጠቀሜታ ፡ የሚሆን ፡ ሕግ ፡ አቁመን ፡ ብንደክምበት ፡ ምንም ፡ ለአምላክ ፡ ወረታ ፡ ሆኖ ፡ ለመመለስ ፡ የበቃ ፡ ባይሆን ፡ እኛ ፡ ዠምረን ፡ መጨረሱን ፡ ለእግዚኣብሔር ፡ እንድንሰጠው ፡ ያሰብነውን ፡ ልንገልጥላችሁ ፡ ወደን ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ በዚህ ፡ በታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ የሰበሰብናችሁ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ሕግ ፡ ለሰው ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ የሚጠቅም ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ አይስተውም ፡ መከበርም ፡ መጠቀምም ፡ የሚገኙት ፡ በሕግ ፡ መተካከል ፡ የተነሣ ፡ ነው ። መዋረድም ፡ መጐዳትም ፡ የሚመጡት ፡ ከሕግ ፡ መጓደል ፡ የተነሣ ፡ ነው ። ግፍና ፡ በደልም ፡ የሚበዙት ፡ ሕግ ፡ ባለመቆሙ ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ ከፍጡር ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ በቃሉ ፡ ብቻ ፡ ማዘዝ ፡ የማይቸግረው ፡ ሲሆን ፡ ሕግን ፡ መሥራቱ ፡ ሕግ ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ገዥ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ።

ከሰው ፡ ትክክለኛ ፡ ለመባል ፡ የሚገባው ፡ አሳቡ ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ቢሆን ፡ የተቃና ፡ የሆነና ፡ ዋናውን ፡ አሳብ ፡ አዝልቆ ፡ ሲሆን ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ሳይሆን ፡ የሚበዛውን ፡ ለመጥቀም ፡ ባለው ፡ ዕውቀት ፡ የተጣጣረና ፡ የቻለ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

አሳባችን ፡ ምንም ፡ ባንዳንድ ፡ ምክንያት ፡ ሳይፈጸም ፡ ቢቈይ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ የዠመርነው ፡ ድካማችን ፡ ሁሉ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ሕግ ፡ እንዲቆምለት ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ለኢትዮጵያም ፡ ለተወደደው ፡ ሕዝባችን ፡ የምናስብለት ፡ በጽኑም ፡ የምንከተለው ፡ አሳባችን ፡ አሁን ፡ የምንገልጽላችሁ ፡ ነው ።

## መዠመሪያ ።

ሕግን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለሁሉም ፡ መስጠት።

## ሁለተኛ ።

ይህንኑ ፡ ሕግ ፡ ኣጠንክሮ ፡ መከተልና ፡ መጠበቅ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በምንሰጠው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚዘረዘሩት ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ኣሳቦች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

1ኛ፡- ኢትዮጵያ ፡ ወገን ፡ ያልተለየባት ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ሆና ፡ ሕዝቡ ፡ ባንድ ፡ ሕግ ፡ ተወስኖ ፡ ባንድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተገዝቶ ፡ በመተባበር ፡ እንዲኖር ፡ ይኸውም ፡ የመተባበሩ ፡ ኀይል ፡ ለዘለቃ ፡ በሚያስተሳስር ፡ ጥቅም ፡ ተጠብቆ ፡ እንዲኖር ፡ ለሰውም ፡ የግል ፡ ጥቅሙ ፡ ሳይቀርበት ፡ የመተባበር ፡ ኀይል ፡ እንዲያመዝንና ፡ የበለጠ ፡ እንዲሆን ፡ ይኸውም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ለየራሱ ፡ የሚሆነው ፡ መጠቀም ፡ ሳይቀርበት ፡ የተለያየ ፡ ግለኛነት ፡ ፈላጊ ፡ እንዳይሆን ፡ ለማድረግ ፡ ነው

2ኛ፡- የሕግ ፡ ጠቃሚነቱ ፡ ወይም ፡ ቀጪነቱ ፡ ለማንም ፡ ቢሆን ፡ የማያዳላ ፡ ትክክል ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ ነው ።

3ኛ፡- ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከሌሎች ፡ አገር ፡ ሕዝቦች ፡ ተለይቶ ፡ በመኖሩ ፡ ታላቁ ፡ የዛሬው ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚሰጠውን ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ሳይችል ፡ በመቈየቱና ፡ የወትሮውን ፡ ሥልጣኔ ፡ በመከተሉ ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ለሕዝቡ ፡ እንደ ፡ መልካም ፡ አባት ፡ ሆነው ፡ የማስተዳደር ፡ ሥራቸውን ፡ እየሠሩ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።
አሁን ፡ ግን ፡ ሕዝባችን ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ እጅግ ፡ እየገፋ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ቀድሞ ፡ ነገሥታቱ ፡ ብቻቸውን ፡ ይደክሙበት ፡ የነበረውን ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ ከድካማቸው ፡ እንዲካፈል ፡ ለማድረግ ፡ ስላልተቻለ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለማቆም ፡ ጊዜው ፡ ፈቀደልን ።
የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ተባብሮ ፡ እንዲሠራ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በዚሁ ፡ አሳብ ፡ የሚገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለሥራው ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ እንዲችሉ ፡ ሁለት ፡ የምክር ፡ ቤቶች ፡ አቁመናል ። በነዚህም ፡ የምክር ፡ ቤቶች ፡ የሚመክሩ ፡ አማካሪዎች ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፈቃድ ፡ ከያውራጃው ፡ እየተመረጡ ፡ ይመጣሉ ፡ ምክሩም ፡ የሚቈረጠው ፡ በቃል ፡ ብዛት ፡ እየሆነ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወዶ ፡ ሲቀበለው ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

4ኛ፡- በምክር ፡ ቤት ፡ የተመከረውንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወዶ ፡ የተቀበለውን ፡ ሚኒስትሮቻችን ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እያከናወኑ ፡ ኀላፊ ፡ እየሆኑ ፡ የመንግሥቱንና ፡ የሕዝቡን ፡ ጕዳይ ፡ እንዲያስፈጽሙ ፡ ተደርጓል ።

5ኛ፡- ሁከት ፡ እንዳይነሣና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጉዳት ፡ እንዳያመጣ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ መቼውንም ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከተፈጸመበት ፡ ትውልድ ፡ እንዳይወጣ ፡ በሕግ ፡ ተወስኗል ።

6ኛ፡- ሕግ ፡ ማስፈለጉ ፡ ማንኛውም ፡ የትዳር ፡ ኣኳኋን ፡ ተሻሽሎ ፡ የተደላደለና ፡ በታመነ ፡ መሠረት ፡ የጸና ፡ እንዲሆን ፡ ነውና ፡ ሁሉንም ፡ አሻሽሎ ፡ የሚያደላድል ፡ ዕውቀት ፡ ነው ። የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ወደ ፡ ዕውቀት ፡ የተመራ ፡ እንዲሆን ፡ ዕውቀትን ፡ ሁሉ ፡ በያይነቱ ፡ እያማረጡ ፡ መቀበል ፡ መቼውንም ፡ የምንፈልገው ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ ነው ።

7ኛ፡- ይኸውም ፡ ያቆምነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ሳይሆንና ፡ ካገር ፡ ልማድ ፡ ሳይፋለስ ፡ ከሠለጠኑት ፡ መንግሥታት ፡ ሕዝቦች ፡ ትምህርት ፡ ጋራ ፡ የተያያዘና ፡ የተቀራረበ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከመሳፍንቶቻችን ፡ ከመኳንንቶቻችን ፡ ዕውቀት ፡ ካላቸው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተወላጆችም ፡ አሳቡን ፡ እየረዱን ፡ ተስማምተንበታል ።

ሰው ፡ ይዠምራል ፡ እንጂ ፡ የመጨረስ ፡ ኃይል ፡ ያለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህንን ፡ ያቆምነውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲያበቃን ፡ እምነታችንን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ እንጥለዋለን ።

እናንተም ፡ ከቡራን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሚኒስትሮችና ፡ ቆንስሎች ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ ያቆምንበትንና ፡ የፈረምንበትን ፡ ይህን ፡ ዕድለኛውን ፡ ቀን ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ለማክበርና ፡ ለመካፈል ፡ ስለ ፡ መጣችሁ ፡ እናመሰግናችኋለን» ።

# ምዕራፍ ፡ 55 ።

## <u>አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ከፍቼ ፡ ኣምልጠው ፡ እንደ ፡ ተያዙ ፡ - የራስ ፡ ኀይሉ ፡ መታሰር ።</u>

አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ስለ ፡ መዋጋታቸውና ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ስለ ፡ መሸሻቸው ፡ ቀጥሎም ፡ ስለ ፡ መያዛቸው ካሁን ፡ በፊት ፡ ተጽፏል ። እስረኛ ፡ ሆነው ፡ ፍቼ ፡ በልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ እጅ ፡ በከበሬታ ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ የልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰንን ፡ ሠርግ ፡ ለማክበር ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ በመጡበት ፡ ሰዓት ፡ ባ1929 ፡ ዓ ፡ ም

፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ከልዑል ፡ ራስ ፡ ኀይሉ ፡ በተላከላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠባቂዎቻቸውን ፡ አባብለው ፡ ከእሥር ፡ ቤት ፡ ኣመለጡ ፡፡



ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ

ማምለጣቸውም ፡ እስከ ፡ 10 ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሳይሰማ ፡ ቈይቶ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ለቀድሞ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ አምልጫለሁና ፡ ተከተሉኝ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈውላቸው ፡ ኖሮ ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ገሚሶቹ ፡ ተይዘው ፡ ቢመረመሩ ፡ በርግጥ ፡ ማምለጣቸውንና ፡ እንዲያመልጡም ፡ በገንዘብም ፡ በምክርም ፡ የረዷቸው ፡ ራስ ፡ ኀይሉ ፡ መሆናቸውን ገልጸው ፡ ተናገሩ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩን ፡ በመጠራጠር ፡ ራስ ፡ ኀይሉን ፡ ወዲያው ፡ እንዲታሠሩ ፡ ኣላደረጉም ።

ራስ ፡ ኀይሉም ፡ የልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ደብዳቤ ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ አሽከራቸውን ፡ ፊታውራሪ ፡ ጊንዶን ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ አምልጠው ፡ ወደ ፡ ተቀመጡበት ፡ ስፍራ ፡ ልከው ፡ ርሳቸው ፡ ታማኝ ፡ መስሎ ፡ ለመታየት ፡ ወይም ፡ ሂድ ፡ ኣባረኸ ፡ ያዝልኝ ፡ ተብለው ፡ ታዘው ፡ ሄደው ፡ ለመደባለቅ ፡ እንዲመቻቸው ፡ እዚሁ ፡ እግቢ ፡ ተቀመጡ ። እንዲያውም ፡ ፍጹም ፡ ታማኝ ፡ መሆናቸውን ፡ በሰፊው ፡ ለማስረዳት ፡ በርሳቸው ፡ ርዳታ ፡ ለማምለጥ ፡ የቻሉት ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ኣምነው ፡ የላኩላቸውን ፡ ደብዳቤ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አሳዩ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ደብዳቤና ፡ የተመረመሩት ፡ የዘበኞች ፡ ቃል ፡ ባንድነት ፡ ሆኖ ፡ የራስ ፡ ኀይሉን ፡ ከአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ጋራ ፡ መመሳጠር ፡ ስለ ፡ መሰከረ ፡ ወዲያው ፡ ራስ ፡ ኀይሉ ፡ ተያዙ ። ቀጥሎም ፡ ያው ፡ ከራስ ፡ ኀይሉ ፡ ወደ ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ተልኮ ፡ የነበረው ፡ ፊታውራሪ ፡ ጊንዶ ፡ ሲመለስ ፡ በጠቋሚ ፡ ከነደብዳቤው ፡ ተይዞ ፡ ቢመረመር ፡ ራስ ፡ ኀይሉ ፡ ባድማው ፡ እንዳሉበት ፡ ገልጦ ፡ ተናገረ ። ከራስ ፡ ኀይሉ ፡ አሽከሮችም ፡ ውስጥ ፡ በነገሩ ፡ ገብተው ፡ የነበሩ ፡ እነቀኛዝማች ፡ መርሻ ፡ እንደዚሁ ፡ የራስ ፡ ኀይሉን ፡ ከአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ጋራ ፡ ማደም ፡ ተናገሩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ደጃዝማች ፡ የነበሩት ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱን ፡ ለመያዝ ፡ ፍለጋቸውን እየተከታተሉ ፡ ሄደው ፡ ግንደበረት ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከሰላሌ ፡ የተላከው ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ ጦር ፡ ከልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ጋራ ፡ ተገናኝቶ ፡ ሲዋጋ ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ፈሶ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ከዚያ ፡ አምልጠው ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ መሻገራቸው ፡ ተሰማ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጐጃም ፡ ሰው ፡ እንዳይቀበላቸውና ፡ ይዞ ፡ እንዲያስረክብ ፡ ባላገሩንና ፡ ባላባቱን ፡ የሚያስጠነቅቅ ፡ ያዋጅ ፡ ቃል ፡ በከንቲባ ፡ ማተቤ ፡ እጅ ፡ ተላከ ። የጐጃምም ፡ መኳንንትና ፡ ሕዝብ ፡ ያዋጁን ፡ ቃል ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ባንድነት ፡ ተባብሮ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ይዞ ፡ ለመንግሥት ፡ ለመስጠት ፡ ሲሽቀዳደም ፡ ወዲያው ፡ ፊታውራሪ ፡ ገሡሠ ፡ በለው ፡ (የራስ ፡ ኀይሉ ፡ የወንድም ፡ ልጅ) ፡ የሊበንን ፡ አገር ፡ ይገዛ ፡ ነበርና ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ በዚያው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሲያልፉ ፡ አግኝቶ ፡ ይዞ ፡ ለክቡር ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ አስረከባቸው ። ልጅ ፡ ኢያሱንም ፡ ከዚያ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ካመጧቸው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጋራ ፡ ሙለታ ፡ አልፈው ፡ በእስረኛነት

፡ እንዲቀመጡ ፡ ተደረገ ፡ በዚያም ፡ ሳሉ ፡ ባ1927 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ኣዲስ ፡ አበባ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ኀዘን ፡ ተደረገላቸው ።






ልዑል ራስ ኀይሉ ልጅ ፡ ኢያሱ

ራስ ፡ ኀይሉም ፡ በዚህ ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ በግንቦት ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 1924 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተይዘው ፡ ሰንብተው ፡ ነበርና ፡ ወዲያው ፡ የመጨረሻውን ፡ ፍርድ ፡ እንዲቀበሉ ፡ በሰኔ ፡ 22 ፡ ቀን ፡ 1929 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አደባባይ ፡ ቀረቡ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እኔን ፡ አሳሪውን ፡ ለማጥፋት ፡ ነውና ፡ ራስ ፡ ኀይሉ ፡ ያደሙት ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ የምፋረዳቸው ፡ ብለው ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ተነሥተው ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ፈቃድ ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ ተፋራጅነት ፡ ቀርቶ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሊጋባ ፡ ደጃዝማች ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ እንዲፋረዱ ፡ ተደረገ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የራስ ፡ ኀይሉ ፡ ከልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ጋራ ፡ ማደም ፡ በብዙ ፡ ምስክርና ፡ ደብዳቤ ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ተዠመረ።

እየተነሣ ፡ የሚፈርደውም ፡ መኳንንት ፡ ራስ ፡ ጎያሉ ፡ ከጥንት ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዠምሮ ፡ የሠሩትን ፡ ተንኰል ፡ አያይዞ ፡ እየተረከ ፡ አሁንም ፡ የረጋውን ፡ መንግሥት ፡ ለማፍረስ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ ከተገኙ ፡ ይሰቀላሉ ፡ ወይም ፡ በሰይፍ ፡ ይቈረጣሉ ፡ ሲል ፡ ሁለም ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ እየተነሣ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረደባቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እንደዚሁ ፡ ከጥንት ፡ የቈየውን ፡ የራስ ፡ ጎያሉን ፡ ተንኰል ፡ ጠቅሰው ፡ አሁንም ፡ ባ1 ፡ ወገን ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ እንዲያመልጡ ፡ እየተላላኩ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ለማታለል ፡ ልዕልት ፡ ፀሓይን ፡ ለልጃቸው ፡ እንዲድሩላቸው ፡ መለመናቸውን ፡ ገልጸው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ዘር ፡ ደሙን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ ለማፍሰስ ፡ አልፈልግምና ፡ ገንዘባቸው ፡ ተወርሶ ፡ ይታሰራሉ ፡ ብለው ፡ የሞቱን ፡ ፍርድ ፡ ወደ ፡ እስራት ፡ ለወጡላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ጎይሉ ፡ ታስረው ፡ ወደ ፡ ደንዲ ፡ ሄዱ ።

# ምዕራፍ ፡ 56 ።

## ኢትዮጵያና ፡ ፫ቱ ፡ የኤውሮፓ ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ።

ባለፉት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከፈረንሳዊ ፥ ከእንግሊዝ ፡ ይልቁንም ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ በጦርነት ፡ ወይም ፡ በወዳጅነት ፡ ተስበው ፡ ለመግባትና ፡ ወደ ፡ ራሳቸው ፡ ግዛት ፡ ለመደባለቅ ፡ ይኸውም ፡ ቢቀር ፡ ጥቅሟን ፡ ለመካፈል ፡ ከሚፈልጉ ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ የፖለቲካ ፡ ጦርነት ፡ ስታደርግ ፡ ቈየች ።

ኢትዮጵያም ፡ ጥቅሟን ፡ ለማንም ፡ አላስነካም ፡ እንዳትል ፡ ያለችበት ፡ ስፍራ ፡ ከሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መሆኑን ፡ ራሷ ፡ ስለምትገነዘበው ፡ ጥረቷ ፡ ነፃነቷና ፡ ሥልጣኗ ፡ መብቷም ፡ እንዳይነካባት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከመሬቷ ፡ የሚገኘውን ፡ የጥቅም ፡ ሰብል ፡ አካፋይ ፡ ወይም ፡ ተካፋይ ፡ ሆና ፡ አብራ ፡ ለመሥራት ፡ አልነፈገችም ፡ ይኸውም ፡ በየጊዜው ፡ ያደረገችው ፡ ስምምነት ፡ ይመሰክራል ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በጥቅም ፡ ረገድ ፡ በመወሰን ፡ ፈንታ ፡ ወደ ፡ ገዥነትና ፡ ወደ ፡ ጠባቂነት ፡ ጐዳና ፡ ሲያመሩ ፡ ስለምታይ ፡ ይኸንኑ ፡ መንገዳቸውን ፡ ለመቃወም ፡ ባላት ፡ የፖለቲካ ፡ ጉልበት ፡ ስትቋቋም ፡ ኖረች ።

ኢትዮጵያ ፡ ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ የሚነሣባትን ፡ ጠላት ፡ ከነዚሁ መካከል ፡ በየተራ ፡ በሚያጋጥማት ፡ የወዳጅነት ፡ ርዳታ ፡ ጭምር ፡ እየታገለች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡

በተያዙት ፡ የአፍሪካ ፡ ግዛቶች ፡ መካከል ፡ ሆና ፡ ሙሉ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ግዛቷን ፡ ጠብቃ ፡ በመኖሯ ፡ ያላደነቃት ፡ የለም ። ነፃነቷንም ፡ ጠብቆ ፡ ያቈየላት ፡ ሁለት ፡ ነገር ፡ ነው ።

1ኛ፡- መሪዎቿ ፡ ያላቸው ፡ የተፈጥሮ ፡ የፖለቲካ ፡ ዕውቀት ።

2ኛ፡- የወታደሮቿ ፡ ዠግንነት ፡ ነው ።

በዚህም ፡ ውጊያ ፡ ጊዜ ፡ ከመሪዎቿ ፡ ብልህነት ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ቀኝ ፡ ክንድ ፡ ሆኖ ፡ ይረዳት ፡ የነበረው ፡ የሷ ፡ አንድነት ፡ የፈላጊዎቿ ፡ ሦስትነት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከ3ቱ ፡ አንደኛው መንግሥት ፡ ከሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ ተለይቶ ፡ የወዳጅነት ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የጠላትነት ፡ ፖለቲካ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሲሠራ ፡ ሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ የጥቅም ፡ ተሻሚ ፡ ባላጋራቸውን ፡ ለማሸነፍ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መልካም ፡ ስሜታቸውን ፡ ሲገልጹ ፡ ኢትዮጵያም ፡ የነሱን ፡ ምክርና ፡ ወዳጅነት ፡ ተደግፋ ፡ ጠላቷን ፡ በጦርነትም ፡ በፖለቲካም ፡ ግንባር ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ ሲመቻት ፡ መኖሩን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በየጊዜው ፡ የተደረገው ፡ ነገር ፡ ያስረዳል ።

## ለምሳሌ ።

1ኛ፡- ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ ከደፉ ፡ በኋላ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ኮምፓኒም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ወዳጅ ፡ ሆኖ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ እስከ ፡ ጅቡቲ ፡ ያለው ፡ የሐዲድ ፡ መንገድ ፡ በውል ፡ ሲሰጠውና ፡ ደግሞም ፡ በደቡብና ፡ በምዕራብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ የጦር ፡ ጭፍራ ፡ እየላኩ ፡ ሲያስገብሩ ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥትም ፡ ያ1 ፡ ክፍል ፡ ጭፍራ ፡ ኣብሮ ፡ እየላከ ፡ ከሚያዘው ፡ አገር ፡ ለመካፈል ፡ ሲያስብ ፡ በፋሾዳም ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ሲከራከር ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ይህ ፡ የፈረንሳዊና ፡ የእንግሊዝ ፡ አያያዝ ፡ እንደማይስማማ ፡ በወዳጅነት ፡ ስፍራ ፡ ሆኖ ፡ ይመክር ፡ ነበር ።

2ኛ፡- የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከዐድዋ ፡ በፊት ፡ በሚደረገው ፡ ፖለቲካና ፡ በውጫሌም ፡ ውል ፡ ከዚያም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ዐድዋ ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ በመሣሪያም ፡ በምክርም ፡ ዋና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ረዳት ፡ ሆኖ ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆኖበት ፡ ነበር ።

3ኛ፡- ኢትዮጵያ ፡ ነጻነቷን ፡ ከሚያስፈራሩባት ፡ እጅ ፡ ለመዳን ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ጥያቄ ፡ አድርጋ ፡ ከ3ቱ ፡ ባንደኛው ፡ (በእንግሊዝ) ፡ መንግሥት ፡ የተመሩ ፡ መንግሥታት ፡ መግባት ፡ አይገባትም ፡ ብለው ፡ ክርክር ፡

ሲያቀርቡ ፡ የፈረንሳዊና ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የተፎካካሪያቸውን ፡ እርምጃ ፡ ለማሰናከል ፡ ሲሉ ፡ መግባት ፡ ይገባታል ፡ ብለው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አግዘዋል ።

4ኛ፡- አሁን ፡ በቅርቡ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወዳጅነት ፡ ለማግኘት ፡ ፈትኖ ፡ ሳይሆንለት ፡ ከቀረ ፡ ወዲህ ፡ በወታደርነት ፡ ለመውረር ፡ ባሰበና ፡ በወረራት ፡ ጊዜ ፡ ከፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ይበልጥ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የማኅበሩን ፡ ሕግ ፡ ለማስከበር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከኢጣሊያ ፡ ወረራ ፡ ለማዳን ፡ በፖለቲካም ፡ ረድቶ ፡ በጦርነትም ፡ ጭምር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሊያግዝ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ርግጥ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት « ሕግና ፡ ውል ፡ አፍርሰኽ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በመውጋት ፡ ለምን ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ ታፈሳለኽ » ፡ ቢለው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ «አንተስ ፡ ግዛትኽን ፡ ያሰፋኽው ፡ የሰው ፡ ዐጥንት ፡ ከምረኽ ፡ አይደለምን» ፡ ብሎ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ መለሰለት ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥትም ፡ «የኔ ፡ ግዛት ፡ የቀናው ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ ከመቆሙ ፡ ከፊት ፡ ነው» ፡ ሲል ፡ መልሶለታል ።

5ኛ፡- በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ በራሱ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የፈቃዱን ፡ ሊያደርግ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ከነዚህ ፡ ከ3ቱ ፡ መንግሥታት ፡ በስተቀር ፡ በጥቅም ፡ በኩል ፡ አብሮ ፡ ለመሥራት ፡ ከአሜሪካንና ፡ ከጃፓን ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ንግግር ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ 3ቱ ፡ መንግሥታት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ይዞታ ፡ ደስ ፡ አላሰኛቸውም ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ 3ቱ ፡ መንግሥታት ያንድነት ፡ ስምምነት ፡ አድርገው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አያያዝ ፡ ለመምከር ፡ ባንድ ፡ ገበታ ፡ ሳይቀመጡ ፡ አልቀሩም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሁለቱ ፡ የፈረንሳዊና ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥታት ፡ በዚህ ፡ የተነሣ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ በደል ፡ ሳያደርጉ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በተለይም ፡ የፋሺስት ፡ መንግሥት ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ እንደናንተ ፡ ብዙ ፡ የለኝም ፡ በትልቁ ፡ ጦርነት ፡ የመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ በተደረገውም ፡ ያገር ፡ ክፍያ ፡ ተበድያለሁ ፡ ሕዝቤም ፡ በርክቶ ፡ የሚስፋፋበት ፡ ትልቅ ፡ አገር ፡ ያስፈልገኛል ፡ ብሎ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥቅም ፡ ማንም ፡ ሳይካፈለው ፡ ብቻውን ፡ ለመውሰድና ፡ በዚያውም ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ የዐድዋን ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ ደንፍቶ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ለመሬቷና ፡ ለቤቷ ፡ ባለቤት ፡ የሆነችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብቻዋን ፡ በዠግንነት ፡ ተቋቋመች ፡ እንጂ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ መጠቀም ፡ የዠመሩትም ፡ ለጥቅምም ፡ ጥሪ ፡ የተደረገላቸውም ፡ መንግሥታት ፡ ብቻዬን ፡ ልጕረሥ ፡ ብሎ ፡ ከተነሣው ፡ ከፋሺስት ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ሊዋጉ ፡ አልፈለጉም ።

የፊት ፡ ለፊት ፡ ጦርነት ፡ እንኳ ፡ ቢቀር ፡ ወዳጃቸው ፡ የነበረችውና ፡ ጥቅሟንም ፡ ለማካፈል ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ የጨበጠውን ፡ እጅዋን ፡ የዘረጋችላቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በዚህ ፡ ሳታስበው ፡ በተደረገባት ፡ የዘመቻ ፡ ወራት ፡ የርዳታ ፡ እጃቸውን ፡ እንደሚገባ ፡ አልዘረጉላትም ።

# ምዕራፍ ፡ 57 ።

## የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ አጭር ፡ ታሪክና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ጠላትነት ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ባለፈው ፡ ታሪክ ፡ እንደ ፡ ተጠቀሰው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከኤውሮፓ ፡ መንግሥቱ ፡ ከነምሳ ፡ አጥቂነት ፡ ከወጣ ፡ ወዲህ ፡ በቅርቡ ፡ ዘመን ፡ ባ1800 ፡ ዓ ፡ ም ፡ መንግሥቱ ፡ የተከፋፈለ ፡ ሆኖ ፡ በሳርዴኝ ፡ አንድ ፡ መስፍን ፡ በሲሲል ፡ 1 ፡ መስፍን ፡ በፒየሞንት ፡ 1 ፡ መስፍን ፡ እንዲሁም ፡ ሌላው ፡ አውራጃ ፡ በየመሳፍንቱ ፡ ተከፋፍሎ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በሳርዴኛው ፡ መስፍን ፡ በካርሎ ፡ አልቤርቶና ፡ በልጁ ፡ በቪክቶር ፡ ዔማኑኤል ፡ 2ኛ ፡ እንዲሁም ፡ በጋሪባልዲ ፡ ብርታት ፡ በፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ በናፖሊዮን ፡ 3ኛ ፡ ርዳታ ፡ በብዙ ፡ ድካምና ፡ ጦርነት ፡ 1 ፡ የንጉሥ ፡ አገር ፡ ካደረገ ፡ ወዲህ ፡ አገር ፡ የመያዝ ፡ አሳቡን ፡ ወደ ፡ አፍሪካ ፡ አዞረ ።

እርሱም ፡ ነፃነቱን ፡ ከነምሳ ፡ መንግሥት ፡ ለማስጣልና ፡ የተከፋፈለውን ፡ ግዛቱን ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ ሲዋጋ ፡ ኖሮ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ የአፍሪካ ፡ ምድር ፡ በአሠልጣኝነት ፡ በጠባቂነት ፡ በቅኝ ፡ አገርነት ፡ በእንግሊዝና ፡ በፈረንሳዊ ፡ እጅ ፡ ተከፋፍሎ ፡ ደረሰ ። ስለዚህ ፡ የተያዘውን ፡ አገር ፡ በመፈለግ ፡ ከሚፈራቸው ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ ከመጣላት ፡ በነፃነት ፡ በተቀመጠችው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ በመሬት ፡ መያዝ ፡ ያሣሣውን ፡ ዐይኑን ፡ መጣል ፡ መረጠ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከምጥዋ ፡ ቱርኮችና ፡ ግብጾች ፡ የገዥነታቸው ፡ ዘመን ፡ ኣልቆ ፡ የሚሄዱበት ፡ ጊዜ ፡ ስላጋጠመው ፡ በእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጠቃሽነት ፡ ወታደር ፡ ምጥዋ ፡ ላይ ፡ እያመጣ ፡ አሰፈረ ። በዚያ ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጠው ፡ ይገዙ ፡ የነበሩት ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ክርክር ፡ አንሥተው ፡ በመጡት ፡ በኢጣሊያ ፡ ወታደሮችና ፡ በራስ ፡ ኣሉላ ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ጦርነት ፡ ተደርጎ ፡ በዶጋሌ ፡ ጦርነት ፡ ብቻ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ሞቱ ። ከዚህም ፡ ድል ፡ በኋላ ፡ የያዘውን ፡ አገር ፡ ለመልቀቅ ፡ በሚያወላውልበት ፡ በኢጣሊያም ፡ አገር ፡ አማካሪዎቹ ፡ ገሚሶቹ ፡ እንግፋ ፡ ገሚሶቹ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ይቅርብን ፡ ብለው ፡

በሚከራከሩበት ፡ ዘመን ፡ የሱዳኖች ፡ በዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ላይ ፡ መነሣትና ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ የነበራቸው ፡ የፖለቲካ ፡ ዝምድና ፡ አደፋፍሯቸው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየገሠገሡ ፡ እስከ ፡ አምባላጌ ፡ ደረሱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ የነበራቸው ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ተቋረጠና ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ጦርነት ፡ ሆኖ ፡ በየተራ ፡ መዠመሪያ ፡ አምባላጌ ፡ ከዚያም ፡ መቀሌ ፡ በመጨረሻም ፡ ዐድዋ ፡ ላይ ፡ በፍጹም ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ የተረፈውም ፡ በሽሽት ፡ ከመረብ ፡ ወዲያ ፡ ተሻገረ።

በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ከነበረው ፡ ያንድነት ፡ መታጣትና ፡ መጠራጠር ፡ የተነሣ ፡ የኢጣሊያን ፡ ሰራዊት ፡ ከዐድዋ ፡ ወዲህ ፡ በኤርትራ ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ ተመሥርቶ ፡ ተቀመጠ። የኤርትራንም ፡ ግዛት ፡ በመዠመሪያ ፡ ያገኛት ፡ በመሆኑ ፡ «የበኵር ፡ ቅኝ ፡ አገሬ» ፡ የሚል ፡ ስም ፡ አወጣላት ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የዐድዋ ፡ ድል ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ የወታደርነት ፡ ስሙን ፡ ሰብሮበት ፡ በዚሁ ፡ ሌሎቹ ፡ መንግሥታት ፡ ተሣልቀውበት ፡ ነበርና ፥ በዚሁ ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ለዐድዋ ፡ ብድር ፡ መመለሻ ፡ የሚሆን ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ መሣሪያ ፡ ከማዘጋጀት ፡ ጋራ ፡ ይጠባበቅ ፡ ዠመር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ መካከል ፡ የቱርክን ፡ ዐቅም ፡ መዝኖ ፡ ሊቢያን ፡ ከቱርክ ፡ ቀምቶ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ለማድረግ ፡ በ1905 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጦርነት ፡ ዠመረ ። የሊቢያም ፡ ሕዝብ ፡ ከቱርክ ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ ተባብሮ ፡ የኢጣሊያን ፡ ወታደር ፡ በዠግንነት ፡ ስላቆመው ፡ መላውን ፡ ሊቢያን ፡ ሳይዝ ፡ ወዲያው ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ትልቁ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ተነሣ ። ጦርነቱም ፡ በተዠመረ ፡ ባመቱ ፡ ኢጣሊያ ፡ አንድነት ፡ ለሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ለነፈረንሳዊ ፡ የጦር ፡ ጓድ ፡ ሆና ፡ በጦርነቱ ፡ መግባቷን ፡ ስታስታውቅ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥትም ፡ ከዚያ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ገብቶ ፡ በጀርመን ፡ ጐን ፡ ተሰልፎ ፡ ነበር ። ጦርነቱም ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ቈይቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ጀርመን ፡ ከነጓደኞቹ ፡ ድል ፡ ሲሆን ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የፈረንሳዊንና ፡ የእንግሊዝን ፡ ወዳጅነት ፡ ተደግፎ ፡ ዠምሮት ፡ የነበረውን ፡ የሊቢያን ፡ አገር ፡ ለማቅናት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይቀጥል ፡ ዠመር ። የሊቢያም ፡ አርበኞች ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ተከላክለው ፡ ድል ፡ ሆኑ ። ለመነሣትም ፡ የሚቀናቀነውንና ፡ ታላላቁን ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ እየተፈላለገ ፡ በጭካኔ ፡ አጥፍቶ ፡ ሊቢያን ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ አደረገ ። ከዚህም ፡ ጋራ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ተሰጠው ፡ ተስፋ ፡ ለጦር ፡ ጓደኝነቱ ፡ እንዲዋጋ ፡ እንዲሆነው ፡ በያዘው ፡ በሱማሌ ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ የኪስማዮን ፡ ግዛት ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጨመረለት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዓለም ፡ ጦርነት ፡ የመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ፋሽዝም ፡ የሚባለውን ፡ ሕግ ፡ ለመመሥረት ፡ ሙሶሊኒ ፡ የሚመስሉትን ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ይዞ ፡ ሸፈተ ። ንጉሡም ፡ ሙሶሊኒንና ፡ ተከታዮቹን ፡ ኢጣሊያኖች ፥ ኢጣሊያኖች ፡ በሆኑት ፡ ወታደሮች ፡ ሲያስወጋ ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ የሚወድቁት ፡ ኢጣሊኖች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ኢጣሊያ ፡ በሰው ፡ ደኸይታ ፡ ተመልሰን ፡ የነምሳ

፡ ተገዢዎች ፡ እንሆናለን ፡ በማለት ፡ ንጉሥነቱን ፡ ብቻ ፡ ላይቀናቀንበት ፡ ቃል ፡ አስገብቶ ፡ ከልብ ፡ ያልፈቀደውን ፡ የሙሶሊኒን ፡ ገዥነትና ፡ የፋሽዝምን ፡ ሕግ ፡ ተቀበለ ።

ሙሶሊኒም ፡ ከምስኪንነት ፡ ተነሥቶ ፡ የኢጣሊያ ፡ 1ኛ ፡ ሚኒስትር ፡ ሆኖ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ኵራትና ፡ ምኞት ፡ አደረበት ። ኢጣሊያንም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ የቄሳር ፡ ዘመን ፡ እመልሳታለሁ፥ ንጉሡም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ (የቄሳርነት) ፡ ስም ፡ ያገኛል ፡ ሲል ፡ ተስፋ ፡ አስደረገ ። ይሁንና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ አድርጎ ፡ ደም ፡ ከመፋሰስ ፡ በወዳጅነት ፡ ገብቶ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ መውሰድ ፡ ይሻላል ፡ ሲል ፡ ፖለቲኩን ፡ ለወጠ ። ስለ ፡ ኢትዮጵያም ፡ መያዝ ፡ ከሌሎቹ ፡ ይበልጥ ፡ እንዲያስብበት ፡ ባሮን ፡ ራይሞንዶ ፡ ፍራንኬቲ ፡ የሚባለውን ፡ ኣዘዘ።

ስለዚህ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተሠራጭተው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ውሳጣዊ ፡ ሁኔታ ፡ የሚሰልሉና ፡ ከሕዝቡም ፡ ከመኳንንቱም ፡ ጋራ ፡ በጅ ፡ መንሻ ፡ እየተወዳጁ ፡ የኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ ደግነት ፡ ፕሮፓጋንድ ፡ የሚያደርጉ ፡ መላክተኞች ፡ ላከ። ባንድ ፡ ወገን ፡ ለዕድዋ ፡ ብድር ፡ መመለሻ ፡ የሚያስችል ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በኢጣሊያ ፡ አገር ፡ ባሉት ፡ የፋብሪካ ፡ ቤቶች ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ያለዕረፍት ፡ እንዲሠራ ፡ በጥብቅ ፡ ታዘዘ ።

ባንድ ፡ ወገን ፡ እ ፡ ኤ ፡ ቍ ፡ ባ1921ና ፡ 24 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሎንዶን ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ስምምነት ፡ ደጋግሞ ፡ እየጠቀሰ ፡ መላው ፡ ወይም ፡ ይበልጡ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ በኢጣሊያ ፡ ግዛት ፡ እንድትሆን ፡ ይፈቅድላታል ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ እናንተ ፡ ብዙ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ስላላችሁ ፡ እንዳትፈልጉብኝ ፡ በማለት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በቅኝ ፡ አገር ፡ ከሚያዋስኗት ፡ ከሁለቱም ፡ የምዕራብ ፡ ኤውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ በጥብቅ ፡ ይከራከር ፡ ነበር ።

ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ ፍቅር ፡ አድርጌ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ለመስማማት ፡ እፈልጋለሁና ፡ የንግድና ፡ የወዳጅነት ፡ ውል ፡ እንዋዋል ፡ ሲል ፡ ጠየቀ ። ወዲያውም ፡ ለመግቢያ ፡ እንዲመቸው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በዐሰብ ፡ በኩል ፡ ሸቀጥ ፡ እንደ ፡ ልቧ ፡ የምታመላልስበት ፡ በር ፡ እሰጣለሁና ፡ ለኔም ፡ ከዐሰብ ፡ እስከ ፡ ደሴ ፡ የሚደርስ ፡ የካሚዎን ፡ መንገድ ፡ ሥራው ፡ በውል ፡ ይሰጠኝ ፡ ሲል ፡ እንደ ፡ ኤ ፡ ቍ ፡ ባ1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የውል ፡ ድርድር ፡ አቅርቦ ፡ በዚህም ፡ መንገድ ፡ ከሸቀጥና ፡ ንግድ ፡ ከሚያስፋፋ ፡ ነገር ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አይመላለስበትም ፡ ሲል ፡ አረጋገጠ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የሚያደርገው ፡ ፖለቲካ ፡ ሁሉ ፡ ተንኰል ፡ እንዳለበት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ፥ ይህን ፡ የውል ፡ ድርድር ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀረ ፡ ስለዚህ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በሌላው ፡ ኣኳኋንና ፡ በሐቅ ፡ መንገድ ፡ ለሚመጣበት ፡ በር ፡ እየሰጡ ፡ ለመግቢያ ፡ የሚያስኬደውን ፡ የፖለቲኩን ፡ መንገድ ፡ በፖለቲካ ፡ ዘጉበት ። በዚህም ፡ ተስፋ ፡ ቈርጦ ፡ ሳለ ፡ እውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በሠራው ፡ ፖለቲካም ፡ የርስ ፡

በርስ ፡ ጠብና ፡ ግጭት ፡ ይነሣል ፡ ብሎ ፡ እዳር ፡ ቆሞ ፡ ሊመለከት ፡ በከፈተበት ፡ ዐይኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አንድነቱ ፡ እየጠና ፡ በሥልጣኔም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየገፋ ፡ ሲሄድ ፡ ብቻ ፡ ተመለከተ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ያለጦርነት ፡ ለመያዝ ፡ ከሌላ ፡ መንግሥት ፡ የተዋሰነውን ፡ ፖለቲካ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ደጋግሞ ፡ ቢፈትነው ፡ እንደ ፡ ከሸፈበት ፡ በተረዳ ፡ ጊዜ ፡ ፕሮፓጋንድና ፡ ገንዘብ ፡ መንዛቱን ፡ ሳይለቅ ፡ የወዳጅነት ፡ ፖለቲካን ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ለማዞር ፡ ሲል ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፡ የጦርነት ፡ ዋዜማ ፡ የሆነውን ፡ ግጭት ፡ አሾትሎ ፡ ይፈልግ ፡ ዠመር ።

# ምዕራፍ ፡ 58 ።

## <u>የጐንደር ፡ ቆንስል ፡በዘበኞች ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ ጠብ ።</u>

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ በቆንስልነት ፡ ካስቀመጣቸው ፡ ውስጥ ፡ በጐንደር ፡ ካስቀመጠው ፡ የጥብቅና ፡ ትምህርት ፡ ያለው ፡ ራፋኤል ፡ ዴ ፡ ላውሮ ፡ የሚባለው ፡ ነበር።


እርሱም ፡ የኢጣሊያ ፡ ቆንስል ፡ ሆኖ ፡ በጐንደር ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ለመመርመር ፡ እንዲመቸው ፡ በፈረስ ፡ እየሆነ ፡ መንደር ፡ ለመንደር ፡ እየዞረ ፡ ካገረ ፡ ገዥዎችና ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ በንግግርና ፡ አብሮ ፡ በመብላት ፡ ተላመደ ። ስሜም ፡ ወልደ ፡ ሩፋኤል ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ከካህናቱና ፡ ከቀሳውስቱ ፡ ከጳጳሱም ፡ ጋራ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ማድረጉን ፡ የምዕራብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጳጳስ ፡ የነበሩት ፡ አቡነ ፡ አብርሃም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የጻፉለት ፡ ያስረዳል ።

«መልእክት ፡ ዘፈነዋ ፡ አባ ፡ ኣብርሃም ፡ ጳጳስ ፡ ዘምዕራበ ፡ አትዮጵያ ።

ይድረስ ፡ ከካባሌር ፡ ዴ ፡ ላውሮ ፡ ወልደ ፡ ሩፋኤል ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሰንብተኻል ፡ እኔ ፡ ደኅና ፡ ነኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ። ወዳገርኽ ፡ ልትሄድ ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ ሰማሁ ፡ ምነው ፡ ሳትልከብኝ ፡ አሁንስ ፡ የምትነሣበት ፡ ቀን ፡ መቼ ፡ ነው ፡ አምላከ ፡ ማርቆስ ፡ ይጠብቅኻ ። ጳጉሜ ፡ 5 ፡ ቀን ፡ 1927 ፡ ዓ ፡ ም» ፡

እንዲሁም ፡ በጐንደር ፡ ከተማ ፡ በቆንስሉ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ የኢጣሊያና ፡ ያማርኛ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ አቁሞ ፡ ወደዚያ ፡ የሚመጡትን ፡ ተማሪዎች ፡ የኢጣሊያ ፡ ፍቅር ፡ እንዲያድርባቸው ፡ ከቆንስሉ ፡ ገንዘብ ፡ እያወጣ ፡ ለተማሪ ፡ ቤቱና ፡ ለልጆች ፡ ልብስ ፡ እያሰፋ ፡ ያለብሳቸው ፡ ነበር

፡፡ የፋሺስትንም ፡ ሰላምታ ፡ ኣሰጣጥ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማስተማር ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እየሰቀለ ፡ ያስጠናቸው ፡ ነበር ፡፡



ራፋኤል ፡ ዴ ፡ ላውሮ ፡ ታጅቦ ፡ ሲሄድ ፡፡

በተረፈ ፡ በየድግሱ ፡ ቤት ፡ እየገባ ፡ አብሮ ፡ እየበላ ፡ በየክብረ ፡ በዓሉም ፡ ልክ ፡ እንዳንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መኳንንት ፡ ቀሚስ ፡ ለብሶ ፡ በጥበብ ፡ ኩታ ፡ ላይ ፡ ካባ ፡ እየደረበ ፡ ሰፊ ፡ ዝርግ ፡ ባርሜጣ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ እየደፋ ፡ ባበሻ ፡ ኮርቻ ፡ የተጫነች ፡ በቅሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ከፊትና ፡ ከኋላ ፡ ታጅቦ ፡ መለከት ፡ እያስነፋ ፡ ለመስቀል ፡ ወደ ፡ ደመራ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ፡ ግብርም ፡ ላንዳንድ ፡ ካህናትና ፡ ሕዝብ ፡ ማድረግ ፡ ዠምሮ ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ብዙ ፡ ወሬ ፡ ከያለበት ፡ በተጠራቀመለት ፡ ጊዜ ፡ በጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ገብቶ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ትልቅ ፡ ራፖር ፡ ወዳዲስ ፡ አበባው ፡ ሚኒስትርና ፡ ወደ ፡ ሮማው ፡ የውጭ ፡ ጕዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ ለሚገቡበት ፡ አሳብ ፡ የሚረዳቸውን ፡ ይጽፍ ፡ ነበር ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ድንገት ፡ ታደሰ ፡ ዓለሙ ፡ የሚባለው ፡ ለቆንስሉ ፡ በዘበኝነት ፡ ተቀጥሮ ፡ የነበረውና ፡ የከተማ ፡ ፖሊስ ፡ የነበረው ፡ በላይ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብዙነሽ ፡ ነጋሽ ፡ በምትባል ፡ ሴት ፡ ምክንያት ፡ አምባጓሮ ፡ አንሥተው ፡ ሲታኰሱ ፡ ቾኰለ ፡ ታየ ፡ የሚባለው ፡ ዘበኛ ፡ በጥይት ፡ ስለ ፡ ተመታ ፡ ይህንኑ ፡ ዕለቱን ፡ ለመንግሥቱ ፡ ኣስተላልፎ ፡ ነበርና ፡ በዚሁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ታላቅ ፡ በደል ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ በደለው ፡ አስመስሎ ፡ ክርክርና ፡ ጥያቄ ፡ አቀረበ ። ርሱም ፡ የጠየቀበት ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባልበደለው ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ የጠየቀውን ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ አልችልምና ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ ለማንሣት ፡ ይመቸናል ፡ በማለት ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ እንደዚህ ፡ የመሰለውን ፡ ሁሉ ፡ ፖለቲካ ፡ ዱካ ፡ በዱካ ፡ ይከታተል ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ምክንያት ፡ እንዳያገኝ ፡ ሲል ፡ ሊያደርገው ፡ የማይገባውን ፡ ነገር ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ የጐንደሩን ፡ ከንቲባ ፡ አዞ ፡ ከንቲባውም ፡ የከተማውን ፡ ዘበኞች ፡ አሰልፈው ፡ ወደ ፡ ቆንስሉ ፡ ግቢ ፡ ሄደው ፡ ይቅርታ ፡ ጠየቁ ፡ የደም ፡ ዋጋም ፡ ለሟቹ ፡ ዘመዶች ፡ ከሚገባቸው ፡ በላይ ፡ ተከፈለ ።

ይኸውም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በፖለቲካ ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ የድል ፡ እርምጃ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ለመውጋት ፡ ምክንያት ፡ ቢያጣም ፡ ቢያገኝም ፡ ባዘጋጀው ፡ ወታደርና ፡ መሣሪያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚወጋበት ፡ ወቅቱ ፡ ደርሶ ፡ ነበርና ፥ የጐንደሩ ፡ ግጭት ፡ ይቅርታ ፡ በመጠየቅና ፡ ጥያቄውም ፡ በመፈጸሙ ፡ ነገሩ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዳይል ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የግጭት ፡ መንገድ ፡ በሱማሊ ፡ በኩል ፡ ከፈተ ።

በጐንደር ፡ በኩል ፡ ዴላውሮ ፡ በጠብ ፡ ቀስቃሽነት ፡ ስሜን ፡ ባገሬና ፡ በሌሎች ፡ መንግሥታት ፡ አገር ፡ አስጠራለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲያስብ ፡ የዠመረው ፡ ጠብ ፡ በመፋፋም ፡ ፈንታ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሊፈጽመው ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ያሰበውን ፡ ጥያቄ ፡ ሰላማዊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ፈጸመ ፡ የዴላውሮ ፡ ኣሳብ ፡ ሳይፈጸም ፡ ቀረና ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ በሱማሌ ፡ በኩል ፡ ካፒቴን ፡ ኣልቤርቶ ፡ ቺማሩታ ፡ ተቀብሎ ፡ ስለ ፡ ሠራበት ፡ ዛሬ ፡ ከጐንደር

፡ ግጭት ፡ ይልቅ ፡ የወልወል ፡ ግጭት ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ ይጠራል ። እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ጠብ ፡ ቀስቃሽነት ፡ ከዴላውሮ ፡ ይልቅ ፡ ቺማሩታ ፡ በኢጣሊያ ፡ አገር ፡ ታወቀ ።



ፊታውራሪ ፡ ዓለማየሁ።

# ምዕራፍ ፡ 59 ።

## የወልወል ፡ ግጭት — ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወደ ፡ ዤኔብ ፡ ያስተላለፉት ፡ ቃል ።

በነፃነቱና ፡ በታሪኩ ፡ ኰርቶ ፡ የሚኖረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በጊዜው ፡ ባለበት ፡ ችግር ፡ የተነሣ ፡ ካገሩ ፡ ተወላጅ ፡ ብዙዎቹን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ወይም ከውጭ ፡ ብዙ ፡ መምህራን ፡ ባገሩ ፡ አስገብቶ ፡ ሳያስተምር ፡ በመቅረቱ ፡ የተከታተሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሲጠቅም ፡ ሺህ ፡ 800 ፡ ዓመት ድረስ ፡ የራቀችውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሳይጠቅማት ፡ ከመቅረቱ ፡ ይልቅ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዙፋን ፡ ለሚቀመጠው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የከበደ ፡ ነገር ፡ ቈየው ፡

ይሁን እንጂ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጊዜ ፡ የፈጠረውን ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በመታገሥ ፡ በዚሁ ፡ ባጭሩ ፡ ዘመን ፡ ሥራውን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚመራ ፡ አግኝታ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ሆስፒታል ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አቋቁማ ፡ የመገናኛ ፡ መንገድ ፥ ስልክ ፥ ራዲዮ ፡ ዘርግታ ፡ ወታደርንም ፡ ባዲስ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጐዳና ፡ እንዲራመድና ፡ ማንኛውንም ፡ ጥበብ ፡ በየመልኩ እንዲስፋፋ ፡ የምትጥርበት ፡ ጊዜ ፡ ነበርና ፡ ይኸንኑም ፡ ውጥኗን ፡ እፍጻሜ ፡ ባላደረሰችበት ፡ ሰዓት ፡ ያላገባብም ፡ ቢሆን ፡ ሊዋጋት ፡ የፈለገውን ፡ ጠላቷን ፡ ወዲያው ፡ ገጥማ ፡ ለመዋጋት ፡ ባለመፈለጓ ፡ በጐንደር ፡ የራሷ ፡ ተወላጆች ፡ በተጣሉባት ፡ ምክንያት ፡ የውጭ ፡ መንግሥት ፡ 1ኛው ፡ በኔ ፡ ዜግነት ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ተበደልሁ ፡ ቢል ፡ ይቅርታ ፡ ጠየቀች ።

ይኸም ፡ ለጠላቷ ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የሚያኰራው ፡ ሆነና ፡ ከጐንደሩ ፡ ግጭት ፡ ወዲህ ፡ በ8ኛው ፡ ወር ፡ በኅዳር ፡ 26 ቀን ፡ 1927 ፡ በወል ፡ ወል ፡ ሌላ ፡ ታላቅ ፡ ግጭት ፡ ተደረገ ፡ የግጭቱም ፡ ምክንያት ፡ እንዲህ ፡ ነው ።

የእንግሊዝ ፡ መንግሥትና ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በእንግሊዝ ፡ ሱማሊያና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ያለውን ፡ ወሰን ፡ በደንብ ፡ ለመካለል ፡ ስምምነት ፡ አድርገው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ ኮሎኔል ፡ ክሊፎርድ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ወገን ፊታውራሪ ፡ ተሰማ ፡ ባንቴ ፡ ዋና ፡ ወሰን ፡ ተካላዮች ፡ ሆነው ፡ በውጋዴን ፡ ውስጥ ፡ በወልወል ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ የሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ ነገዶች ፡ ከብቶቻቸውን ፡ የሚያግጡበትንና ፡ ውሃ ፡ የሚያጠጡበትን ፡ ስፍራ ፡ ለመመርመር ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ሲያልፉ ፡ ካፒቴን ፡ ቺማሩታ ፡ የሚባለው ፡ የኢጣሊያ ፡ ተወላጅ ፡ «ዱባት» ፡ የሚባሉትን ፡ ብዙ ፡ የሱማሌ ፡ ወታደሮች ፡ ይዞ ፡ እንደ ፡ ኤ ፡ ቍ ፡ ባ1928 ፡ እንደ ፡ ኢት. ቍ ፡ 1920 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከተደረገው ፡ የወሰን ፡ ስምምነት ፡ መቶ ፡ ኪሎ

፡ ሜትር ፡ የሚያኽል ፡ አልፎ ፡ እንደ ፡ ጠብ ፡ አጫሪነት ፡ ሱማሌዎቹን ፡ አስደፍጦ ፡ መተላለፊያ ፡ ከለከለ ።

ወዲያው ፡ እነፊታውራሪ ፡ ተሰማ ፡ ያሉበት ፡ ስፍራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ መሆኑን ፡ ቢያረጋግጡለት ፡ ከመንግሥቱ ፡ ታዝዤ ፡ ነውና ፡ የያዝሁት ፡ ከዚህ ፡ እልፍ ፡ ለማለት ፡ አልችልም ፡ ብሎ ፡ ወዲያው ፡ እነዚህንም ፡ ተካላዮችን ፡ አደጋ ፡ እንዳያገኛቸው ፡ ይጠብቋቸው ፡ በነበሩት ፡ በፊታውራሪ ፡ ሺፈራና ፡ በፊታውራሪ ፡ ዓለማየሁ ፡ ላይ ፡ ድንገት ፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ በአይሮፕላን ፡ በእግረኛ ፡ ወታደርም ፡ ጭምር ፡ ውጊያ ፡ ዠመሩ ። የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮችም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ያልተጠነቀቁበት ፡ ቢሆን ፡ በዠግንነት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ድረስ ፡ ተዋግተው ፡ ከአይሮፐላን ፡ በሚወርደው ፡ ቦንብ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ተጐዳባቸው ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ተመለሱ ። በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ፊታውራሪ ፡ ዓለማየሁ ፡ ባርበኝነት ፡ እውጊያው ፡ ላይ ፡ ሕይወታቸውን ፡ አሳለፉ ። ከርሳቸውም ፡ ጋራ፡ 107 ፡ የሚሆኑ ፡ ሞተው ፡ ተገኙ ። ከነዚያ ፡ ወገንም ፡ እንደዚሁ ፡ 75 ፡ የሚሆኑ ፡ ሞቱ 70 ፡ የሱማሊያ ፡ ወታደሮች ፡ ቈሰሉ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ባ1920፡ ዓ ፡ ም ፡ የተደረገውን ፡ የወሰን ፡ ውል ፡ አልፎ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ጦርነት ፡ ማድረጉ ፡ ሳያሳፍረው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ እንዲፈጽምለት ፡ ጥያቄ ፡ አቀረበ ።

የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ 200 ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ካሳ ፡ እንዲከፍል ፡ ዑመር ፡ ሰመተርን ፡ እጁን ፡ ለኢጣሊያ ፡ ይዞ ፡ እንዲሰጥ ፡ እነፊታውራሪ ፡ ሺፈራ ፡ ከሹመታቸው ፡ እንዲሻሩ ፡ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ወልወል ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ ቺማሩታን ፡ ይቅርታ ፡ እንዲጠይቁ ፡ ሲል ፡ እርሱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሊያደርግ ፡ የሚገባውን ፡ ጠየቀ ፡ ወዲያውም ፡ ነገሩን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ማኅበር ፡ አደረሰ ። ለዚህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የሚገባውን ፡ መልስ ፡ ለዓለም ፡ ማኅበር ፡ እያቀረበ ፡ ነገሩ ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ በሰላም ፡ እንዲፈጸም ፡ በሚጥርበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ወታደርና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወደ ፡ ኤርትራና ፡ ወደ ፡ ሱማልያ ፡ በመርከብ ፡ እያመጣ ፡ ያከማች ፡ ዠመር።

የዚህንም ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሮማ ፡ ባለው ፡ ሚኒስትሩ ፡ በኩል ፡ ቢያስጠይቅ ፡ የዐድዋ ፡ ብድራችንን ፡ ልንመልስበት ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ኢትዮጵያን ፡ በቅኝ ፡ አገርነት ፡ ልናስገብርበት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ በኤርትራና ፡ በሱማሊያ ፡ ያለውን ፡ ቅኝ ፡ አገራችን ( ኢትዮጵያ ፡ እንዳትነጥቀን) ልናስጠብቅበት ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ሐሰት ፡ ያለበትን ፡ መልስ ፡ ሰጠ ።

ኢትዮጵያም ፡ ሥልጣኔ ፡ ለማግባት ፡ የወጠነችው ፡ ዕቅድ ፡ እንዳይበላሽባት ፡ ይህ ፡ ግጭት ፡ ወደ ፡ ዕርቅ ፡ እንዲመለስ ፡ ሰላም ፡ ፈላጊነቷን ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ገለጠች ።

ይኸውም ፡ በኢጣሊያ ፡ ዘንድ ፡ ጐልቶ ፡ የታወቀ ፡ ነበርና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወገን ፡ ሰላም ፡ በሚፈለገው ፡ ልክ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ወገን ፡ ጠቡ ፡ እየተጋነነ ፡ ይሄድ ፡ ዠመር ። ባ1920፡ ዓ ፡ ም

፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ውል ፡ ባ5ኛው ፡ አንቀጽ ፡ የወልወልን ፡ ግጭት ፡ ሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ በዕርቅ ፡ ሊጨርሱ ፡ ይችሉ ፡ የነበረውን ፡ የሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ አስተያየት ፡ 1ዱ ፡ ወደ ፡ ሰላም ፡ 1ኛው ፡ ወደ ፡ ጠብ ፡ የሚመለከት ፡ በመሆኑ ፡ ሳይቻል ፡ ቀረ ። ስለዚህ ፡ ይኸንኑ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ግንቦት ፡ 8 ፡ ቀን ፡ 1927 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከሐረር ፡ ወደ ፡ ዤኔብ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ አስተላለፉ ።

«ለመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ አማካሪዎች ፡ ፕሬዚዳን ፡ ዤኔብ ።

እኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥያቄ ፡ በሚመረመርበት ፡ ባሁኑ ፡ ጉባኤ ፡ ይህን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈውን ፡ መልክት ፡ ክቡርነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ እንዲነበብ ፡ እንዲያደርጉ ፡ እንጠይቃለን ።

ከኛ ፡ በኩል እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ወታደርም ፡ መሣሪያም ፡ ሳናስከትት ፡ ነገርም ፡ ሳናነሣ ፡ ኢጣሊያ ፡ ካለፈው ፡ መስከረም ፡ በፊት ፡ ዠምራ ፡ በወሰናችን ፡ አቅራቢያ ፡ ወታደር ፡ የጦር ፡ አቢዮን ፡ ታንክ ፡ ሌላም ፡ በያይነቱ ፡ የጦርመሣሪያ ፡ ትሰበስባለች ፡ ይኸንንም ፡ ማድረጓን በኢትዮጵያ ፡ የሚኖር ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የማንኛውም ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ያውቀዋል ። ወልወል ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ከሆነበት ጊዜ ፡ ወዲህ ፊት ፡ ከገባችው ፡ ከኢንተርናሲዮናል ፡ ግዴታዋ ፡ ሁሉ ፡ ለመሠወር ፡ በሁለታችን ፡ መካከል ፡ የተነሡት ፡ ጠቦች ፡ ሁሉ ፡ በትክክለኛው ፡ መንገድ ፡ እንዳይመረመሩ ፡ ለማድረግ ፡ በታወቀው ፡ በዲፕሎማቲክ ፡ መሣሪያ ፡ እየፈለገች ፡ በማይገባ ፡ መንገድ ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ ከግዛታችን ፡ መያዧ ፡ የታወቀ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላላጠፋችው ፡ ጥፋት ፡ ካሳ ፡ እንድትሰጣት ፡ ትጠይቅ ፡ ዠመረች ። ከኢትዮጵያም ፡ ግዛት ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ መያዧ ፡ ኢትዮጵያንም ፡ ማጥቃቷና ፡ ሕዝቡንም ፡ ለማግኘት ፡ መመኘቷ ፡ በሚገባ ፡ ለማሠልጠን ፡ ነው ፡ በአረመኔም ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ለማድረግ ፡ የሚገባ ፡ ነው ፡ ለማሰኘት ፡ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ አቆመች ፡ ኢጣሊያ ፡ በኢትዮጵያ፡ ወይም ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ የምታቀርበው ፡ ክስ ፡ ቢኖር ፡ በሚያስፈልገው ፡ ጊዜና ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ የሚገባውን ፡ ምላሽ ፡ ለመስጠት ፡ የተዘጋጀን ፡ ነን ። አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ለሽምግልናውና ፡ ለርቁ ፡ ዳኝነት ፡ የመንግሥቷ ፡ ሠራተኞች ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ያገሯን ፡ ሰዎች ፡ መረጠች ። የነሱንም ፡ መመረጥ ፡ ነገራችን ፡ በትክክል ፡ መንገድ ፡ መመርመሩን ፡ የሚከለክል ፡ ባይሆን ፡ እንኳ ፡ ምርምሩ ፡ እንዲያስቸግር ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ለሽማግሌዎቹ ፡ እንዲመረምሩት ፡ የሚቀርበውን ፡ ነገር ፡ ኢጣሊያ ፡ መወሰኗ ፡ በሽምግልና ፡ ለመታየት ፡ የሚገባውን ፡ ዋና ፡ የሆነውን ፡ በግንቦት ፡ 8 ፡ ቀን ፡ 1909 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የውል ፡ ትርጉም ፡ ነገር ፡ ሳይጨረስ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። እውነተኛና ፡ ትክክለኛ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ተስማምቶ ፡ ለማቆም ፡ ባሁኑ ፡ በኢጣሊያ አሳብ ፡ በዲፕሎማቲክ ፡ መንገድ ፡ አልተቻለም ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ አይቻልም።

ኢትዮጵያ ፡ የሽምግልናውን ፡ ዳኝነት ፡ አልቀበልም ፡ አለች ፡ ብላ ፡ ኢጣሊያ ፡ አመካኝታ ፡ በመንግሥታት ፡ ውል ፡ የተቀበለችውን ፡ ግዴታ ፡ ለማስወገድ ፡ የሚፈቅድላት ፡ መንገድ ፡

እንዳታገኝ ፡ በማለት ፡ ነገራችን ፡ በትክክልና ፡ በፍጥነት ፡ ማለቁ ፡ እንዲረጋገጥልን ፡ ችላ ፡ ሳንል ፡ በማሰብ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅ ፡ ያልሆኑ ፡ ሁለት ፡ ሽማግሌዎች ፡ መምረጣችንን ፡ ለኢጣሊያ ፡ አስታውቀናል ። ምንም ፡ ይህ ፡ ጎረቤታችን ፡ የሆነ ፡ መንግሥት ፡ ጦር ፡ ማዘጋጀቱም ፡ ባያቋርጥና ፡ በየወሰናችን ፡ ላይ ፡ መታኮሱ ፡ ባይቀር ፡ በወሰን ፡ ላይ ፡ ግጭት ፡ እንዳይሆን ፡ ተጠንቅቀንበት ፡ በሙሉ ፡ በግዛታችን ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ ነፃ ፡ ቦታ ፡ ለማቆም ፡ ፈቃዳችን ፡ ሆኖ ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ቃል ፡ እንዲፈጸምና ፡ በውነት ፡ ለመከላከያ ያልሆነው ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ማዘጋጀት ፡ እንዲቆም ፡ እንዲያደርጉ ፡ አማካሪዎቹን ፡ አጥብቀን ፡ እንጠይቃለን ። ካለፈው ፡ ወር ፡ ታኅሣሥ ፡ ዠምሮ ፡ በሱማሌና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወሰን ፡ አቅራቢያ ፡ የተደረገውም ፡ አደጋ ፡ ሁሉና ፡ በግንቦት ፡ 8 ፡ ቀን ፡ 1909፡ ዓ ፡ ም ፡ የተደረገውን ፡ የውል ፡ ትርጉም ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ መርምረው ፡ እንዲፈርዱ ፡ ኢጣሊያ ፡ አልቀበልም ፡ የምትል የሆነ እንደሆን ፡ ግን አማካሪዎቹ ፡ ነገሩን ፡ ራሳቸው ፡ በጃቸው ፡ አድርገው ፡ መርማሪ ፡ እንዲያደርጉበትና ፡ የመንግሥታት ፡ ውል 15ኛውን ክፍል ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ በሙሉ ፡ መርምረው ፡ እንዲጨርሱት ፡ እንጠይቃለን ።

ይህን ፡ ጥያቄ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምታቀርብበት ፡ ምክንያት ፡ ነገሩ ፡ በሕግ ፡ በሙሉ ፡ በፍጥነትና ፡ በሰላም ፡እንዲያልቅ ፡ በመፈለግ ፡ ብቻ ፡ ነው» ።

# ምዕራፍ ፡ 60 ።

## ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የተናገሩት ፡ ዲስኩር ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ያቀረበው ፡ የዕርቅ ፡ አሳብ ።

ከኢጣሊያ ፡ አጥቂነትና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተከላካይነት ፡ መካከል ፡ ተወራርሶ ፡ ከመጣው ፡ ጠብና ፡ ግድያ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሁም ፡ ለዋናው ፡ ዘመቻ ፡ በር ፡ ከፋች ፡ የነበረው ፡ ሙሶሊኒ፡ «ምልክት ፡ የሚሰጠው ፡ ደወል» ፡ ብሎ ፡ የሰየመው ፡ የወልወል ፡ ግጭት ፡ ነው።

የዚህም ፡ ጠብ ፡ ባ1920፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ እንዳደረጉት ፡ ውል ፡ እንደ ፡ 5ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ቃል ፡ ሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ በራሳቸው ፡ ሽማግሌ ፡ ሊታረቁ ፡ ሲችሉ ፡ ሳለ ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እንቢተኛነት ፡ ከቀረ ፡ በኋላ ፡ የሚገባውን ፡ ፍጻሜ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ነገሩ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ማኅበር ፡ ቀረበ ።

የኢጣሊያ፡መንግሥትም ፡ 40 ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ሲዘጋጅ ፡ በቈየው ፡ መሣሪያ ፡ የዐድዋን ፡ የአምባላጌን ፡ የመቀሌን ፡ የዶጋሌን ፡ የሰሓጢን ፡ የድል ፡ አድራጊዎችን ፡ ልጆች ፡ አጥፍቶ ፡

መሬታቸውን ፡ ለተሸናፊዎቹ ፡ ልጆች ፡ ለማውረስ ፡ እንዲመቸው ፡ የዓለም ፡ ማኅበር የኢትዮጵያን ፡ የተጠቂነት ፡ አቤቱታ ፡ በፍጹም ፡ እንዳይሰማ ፡ የመንግሥታቶቹን ፡ መላክተኞች ፡ በማባበል ፡ ይደክም ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ቅን ፡ ፍርድ ፡ የሚፈልጉት ፡ አስታራቂዎች ፡ በግልጽ ፡ እየፈረዱበት ፡ ተስፋ ፡ በቈረጠ ፡ ጊዜ ፡ የኤውሮፓን ፡ ወጣት ፡ በፖለቲካ ፡ መሪዎቹ ፡ ላይ ፡ ባድማ ፡ ለማስነሣት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጥሪ ፡ አደረገ ። «እኔ ፡ ከኤውሮፓ ፡ ርቆ ፡ በሚገኘው ፡ የአፍሪካ ፡ ክፍል ፡ ሀገር ፡ ላይ ፡ ለመስፋፋት ፡ ስፈልግ ፡ የኤውሮፓ ፡ የፖለቲክ መሪዎች ፡ በማያገባቸው እኔን ፡ ለመከላከል ፡ የሚጭሩት ፡ እሳት የኤውሮፓን ፡ ወጣት ፡ እንጂ እነሱን ፡ እጅግም ፡ አያገኛቸውም ። ስለዚህ ፡ መላው ፡ የኤውሮፓ ፡ ወጣት ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ አደጋ ፡ እንዲከለል ፡ በነዚህ ፡ የፖለቲክ ፡ አስኪያጆች ፡ ላይ ፡ ባንድነት ፡ መነሣት ፡ ያስፈልገዋል» ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ ሐሰት ፡ በመላበት ፡ ራሱ ፡ ባቀረበው ፡ ራፖር ፡ ተመርቶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባረመኔነት ፡ ተመልክቶ ነገሩን ፡ ችላ ፡ እንዲለው ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ጣረ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ እንዳይገባ ፡ በሚያደርገው ፡ ግድያ ፡ ድል ፡ የሆነው ፡ ግን ፡ አስቀድሞ ፡ ባ1917 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በማኅበሩ ፡ ገብታ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ አባል ፡ የተቈጠረች ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ኢጣሊያ ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ማኅበሩ ፡ መግባት ፡ ይገባታል ፡ ብሎ ፡ መፍረዱን ፡ የዘነጋው ፡ ይመስላል ።

ስለዚህ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ምንም እንኳ ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ ሠራዊትና ፡ መሣሪያ ፡ በኤርትራ ፡ ጠረፍ ፡ አከማችቶ ፡ ለጦርነት ፡ በቍርጥ ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ቢያውቀው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በማንኛውም ፡ ሰላም ፡ ፈላጊነቷን ፡ ኣስቀድሞ ፡ እንዳስታወቀችው ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ሆነው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰላም፡ ፈላጊነት ፡ የሚያስረዳ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናገሩ ።

«ያለፈው ፡ የዓለም ፡ ታሪክ ፡ በፊታችን ፡ የቀረበውን ፡ ችግር ፡ መፈጸሚያ ፡ ለማግኘት ፡ የሚያገለግል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፍጻሜው ፡ በዘመኑ ፡ በነበሩት ፡ ላይ ፡ አልፏል ። አሁን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያኛት ፡ ችግር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በዘመኑ፡ የደረሰበት ፡ ነውና ፡ ዛሬ ፡ ብቻ ፡ መዠመሪያ ፡ የሚታይ ፡ ኣይደለም ። በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ዛሬ ፡ ገናና ፡ ሆነው ፡ የሚታዩት ፡ መንግሥቶች ፡ እንደ ፡ ዕድላቸው ፡ እንደ ፡ ደረሰላቸው ፡ ኢትዮጵያም ፡ የደከመችበትንና ፡ የገነነችበትን ፡ ታሪክ ይቈጥረዋል ። በጦርነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በፖለቲክም ፡ እንደዚሁ ፡ ችግር ፡ እየገጠማት ፡ ያለፈችው ፡ ፈተና ፡ብዙ ፡ ነው። አሁንም ፡ በዘመናችን ፡ ዕድሏ ፡ በሚሰጣት ፡ ስሟን ፡ ከፍ ፡ በሚያደርገው ፡ መንገድ ፡ አሳባችንን ፡ መምራት ፡ አለብን ።

የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ሁላችሁም ፡ እንደምታውቁት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥቶችና ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግ ፡ የሁሉንም ፡ ጥቅም ፡ እየጠበቀ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዕድገት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ በማከናወን ፡ ቈየ ። እንደዚሁም ፡ የኢጣሊያ ፡ ጥቅም ፡ እንዲጐድል ፡

ክብሯም ፡ እንዲዋረድ ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፡ የለም ። የዛሬው ፡ ፈተና ፡ በዘመናችን ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ በብርታትና ፡ በርጋታ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ ተጠብቆላት ፡ የምትኖርበትን ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ መሠረት ፡ በማድረግና ፡ በመከተል ፡ የደረሰውን ፡ ችግር ፡ ለማሸነፍ ፡ መጣጣር ፡ የሁላችንም ፡ ዋና ፡ ሥራችን ፡ ነው ። ክርስቲያን ፡ ተስፋ ፡ መቍረጥ ፡ አይገባውም ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ በሥራችን ፡ ሁሉ ፡ የሚያበረታታ ፡ ነው ። ብርታታችንና ፡ ቈራጥነታችን ፡ የሚገጥመንን ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ አሸናፊ ፡ አድርጎ ፡ ለደስታ ፡ የሚለውጥልን ፡ መሣሪያ ፡ መሆኑ የሚዘነጋ ፡ አይደለም ። ይህም ፡ የቀድሞ ፡ አባቶቻችን ፡ አገራቸውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለማስከበር ፡ የሠሩትን ፡ ሥራ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ገናና ፡ ታሪክ ፡ የሕዝቡን ፡ ዝግንነት ፡ ያንድነታቸውን ፡ ኀይል ፡ በማስታወስ ፡ ጥቅሙና ፡ ፍሬው ፡ ይገኛል።

ባለፈው ፡ ንግግራችን ፡ በኢትዮጵያና ፡ በኢጣሊያ ፡ መካከል ፡ የተነሣውን ፡ ነገር ፡ የደረሰበትን ፡ ገልጠን ፡ እንዳስታወቅናችሁ ፡ የግልግል ፡ ዳኞች ፡ እንዲቆሙ ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ ቢደረግ ፡ በመጨረሻው ፡ ተመርጠው ፡ ነገሩን ፡ ከመረመሩ ፡ በኋላ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የመረጣቸው ፡ የኢጣሊያ ፡ ተወላጅ ፡ የሆኑ ፡ የግልግል ፡ ዳኞች እኛ ፡ ከመረጥናቸው ፡ የፈረንሳዊና ፡ የአሜሪካ ፡ ተወላጅ ፡ ከሆኑ ፡ የግልግል ፡ ዳኞች ፡ ጋራ ፡ በሐሳብ ፡ ሳይስማሙ፡ ስለ ፡ ቀሩ ፡ ምንም ፡ ሳይቈረጥ ጉባኤው፡ተበተነ ። ይህም፡ ነገሩን ፡ እያበረታው ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ተቋርጦ ፡ የነበረውን ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ሥራ ፡ ፍሬውን ፡ ለመመርመር ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ለተሰበሰቡት ለመንግሥታት ፡ ማኀበር ፡ አማካሪዎች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አስታውቀን ፡ በወልወል ፡ የተደረገው ፡ አደጋ ፡ እንዲጨረስ ፡ 5ኛ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኛ ፡ ተመርጦ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንዲዠመር ፡ ኢትዮጵያና ፡ ኢጣሊያ ፡ ያልተስማሙበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በነሐሴ ፡ 29 ፡ ቀን ፡ በሚደረገው ፡ መንግሥታት ፡ ማኀበር ፡ ጉባኤ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲመረመር ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ተቈረጠ ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነገር ፡ ባ1906 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የተደረገውን ፡ ውል ፡ የፈረሙ ፡ የእንግሊዝ ፡ የፈረንሳዊና ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ መላክተኞቻቸውን ፡ ልከው ፡ በነሐሴ ፡ 9 ፡ ቀን ፡ ፓሪስ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ ይህንኑ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ለመነጋገር ፡ ተስማምተው ፡መቍረጣቸውን ፡ ሰማን ።

ይህም ፡ ውል ፡ በጥቅም ፡ ረገድ ፡ ሦስቱ ፡ መንግሥቶች ፡ ከተስማሙበት ፡ ስምምነት ፡ በቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ተጠብቆ ፡ እንዲኖር ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ቃል ፡ አለበት ። የዚህም ፡ የታሰበው ፡ የሦስቱ ፡ መንግሥቶች ፡ ንግግር ፡ መጨረሻ ፡ ፍሬው ፡ ምንም ፡ ገና ፡ ባይታወቅ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በኢጣሊያ ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ ጠብ ፡ በጦርነቱ ፡ ኀይል ፡ ሳይሆን ፡ በሰላም ፡ እንዲፈጸም ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ ሲፈለግ ፡ የክረምቱ ፡ ወራት በመጨረሻ ፡ ደረሰ ። ኢጣሊያም ፡ ወታደርና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ መላኳን ፡ እስካሁን አላቋረጠችምና ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ እየበረታና ፡ እየገፋ ፡ መሄዱ ፡ ነው ።

ስለ፡ ሆነ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በኢጣሊያ ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ የሚያሳዝን ፡ ጠብ ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ እንዲጨረስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተስፋ ፡ ከማድረግ ፡ አላቋረጠችም ። የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ማኅበረተኞች ፡ የሆነ ፡ መንግሥታቶችና ፡ ትልቅ ፡ ትንሽም ፡ ቢሆኑ ፡ በመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ባይገዙ ፡ በዓለም ፡ ያሉ ፡ መንግሥታቶች ፡ ሁሉ ፡ አሁን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያለችበትን ፡ የሚያስፈራ ፡ አኳኋን ፡ ተመልከተው ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድና ፡ ቅን ፡ አስተያየት ፡ ኣያሳጧትም ፡ ብለን ፡ እንተማመናለን ።

ዓለም ፡ በታላቁ ፡ ጦርነት ፡ ከተፈተነ ፡ በኋላ ፡ ሰላምን ፡ አጽንቶ ፡ ለማቆምና ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ መልካም ፡ ኑሮ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ለማዘጋጀት ፡ በተዠመረበትና ፡ በሚታሰብበት ፡ ዘመን ፡ ለዓለም ፡ የሚሰማ ፡ ታላቅ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ ጦርነት ፡ መነሣቱ ፡ ሲቃረብ ፡ ይታያል ። የሕዝብን ፡ ዕድልና ፡ ኑሮ ፡ ለማሻሻል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አደራ ፡ የተቀበሉ ፡ ሁሉ ፡ የተቀደሰ ፡ ፈቃዱን ፡ በመፈጸም ፡ በዓለም ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ሰላምን ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ እንዲወርድላቸው ፡ ወደሱ ፡ በምናደርገው ፡ ጸሎት ፡ እንተማመናለን ።

በዩናይትድ ፡ እስቴት ፡ አሜሪካ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የቆመው ፡ ማኅበር ፡ ለሰላምና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ በአሜሪካ ፡ ባሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ በነሐሴ ፡ 12 ፡ ቀን ፡ በሚመጣው ፡ እሑድ ፡ ጸሎት ፡ እንዲደረግና ፡ የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፡ ጸሎት ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን ፡ በጸሎቱ ፡ እንዲተባበራቸው ፡ ስለ ፡ ጠየቁ ፡ ከአሜሪካ ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ በዚህ ፡ በተቀደሰው ፡ አሳብ ፡ ለመገናኘት ፡ በኛም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ በተለየ ፡ ስለ ፡ ሰላምና ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ጸሎት ፡ እንዲደረግ ፡ አዘናል ።

የአሜሪካ ፡ ፕሬዚዳን ፡ ሙሴ ፡ ሩዝቤልት ፡ ሰላም ፡ እንዲጠበቅ ፡ ለባለጋዜጠኞች ፡ ስላስታወቁ ፡ ምስጋና ፡ አቅርበንላቸዋል ።

ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ በመቀራረብና ፡ በመረዳዳት ፡ እየሠራች ፡ አገሯን ፡ ለማልማት ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ ሙሉና ፡ የጠነከረ ፡ ፈቃድ ፡ ያላት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሥራዋና ፡ መልካም ፡ አሳቧ ፡ እንዲከናወንላት ፡ ሰላምና ፡ ጸጥታ ፡ ያስፈልጋታል ። ሰላምን ፡ ኣጥብቃ ፡ ትወዳለች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከታሪኳ ፡ ጋራ ፡ በሚስማማትና ፡ በምትችለው ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየቀደመች ፡ ትሄዳለች ። በዓለም ፡ የሚገኙ ፡ መንግሥቶች ፡ ታላላቆች ፡ ሆነው ፡ የሚታዩት ፡ ለመሠልጠንና ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ጊዜ ፡ ስላገኙ ፡ ነው ።

ኢትዮጵያም ፡ ወደዚሁ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ ዘርና ፡ ወገን ፡ ሳትለይ ፡ በንጹሕ ፡ ልብና ፡ በመልካም ፡ ፈቃድ ፡ ከሚረዱ ፡ ከማናቸውም ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ እየተባበረች ፡ ለመሥራትና ፡ ወዳጅነታቸው ፡ የሚያስፈልጋት ፡ መሆኑን ፡ ተረድተናል ። መረዳዳት ፡ ከሌለ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ነዋሪና ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ አይቻልም ።

ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በውስጧ ፡ ማንኛውም ፡ ሁከትና ፡ የሚያናውጥ ፡ ነገር ፡ እንዳይነሣ ፡ ነፃነቷን ፡ የሚነካ ፡ ግዛቷን ፡ የሚያሳጣ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቷንና ፡ የሕዝቧን ፡ የጦር ፡ ሠራዊቷንም ፡ ክብር ፡ የሚነካውን ፡ ማንኛውንም ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ አትቀበልም ። ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እየመላለሰች ፡ በመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ትክክለኛነት ፡ ሰላምና ፡ የሚገባት ፡ ነገር ፡ የማይጐድልባት ፡ ፍርድ ፡ እንዲገኝ ፡ በዓለም ፡ ያሉ ፡ መንግሥቶች ፡ ሁሉ ፡ በሚያደርጉት ፡ ርዳታ ፡ መተማመኗን ፡ ትገልጣለች ።

ኢትዮጵያ ፡ ምንም ፡ በምክሩ ፡ ውስጥ ፡ እንድትገኝ ፡ ባይደረግ ፡ በነሐሴ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ በፓሪስ ፡ በሚደረገው ፡ ጉባኤ ፡ ሰላም ፡ የሚጸናበት ፡ ነገር ፡ እንዲገኝበት ፡ እያሰበች ፡ በተለየ ፡ በእንግሊዝና ፡ በፈረንሳዊ ፡ ተስፋ ፡ ታደርጋለች ።

ታላቅና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የተከበረ ፡ አሳብ ፡ ያለው ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ እንዳይጐድልበትና ፡ ተከብሮ ፡ እንዲኖር ፡ ዋና ፡ ተከላካይ ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ።

ባለፈው ፡ ክብር ፡ በተመላበት ፡ ታሪክ ፡ የሚመካው ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የደግነት ፡ ሥራ ፡ እንዳይጐድልበት ፡ ጠባቂ ፡ የሆነው ፡ ለመንግሥቱ ፡ ምልክት ፡ የተሰጠውን ፡ ለመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ የትክክልነት ፡ የወንድማማችና ፡ የነፃነት ፡ አሳብ ፡ የሚዘራ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ሕዝብ ፡ ትልቅም ፡ ትንሽም ፡ ቢሆን ፡ ማንኛውም ፡ መንግሥት ፡ ባንድ ፡ ዐይነት ፡ አስተያየት ፡ እንዲታይ ፡ ይህም ፡ የመንግሥቱ ፡ ምልክት ፡ የሆነው ፡ ቃል ፡ በፈረንሳዊ ፡ ተወላጆች ፡ መካከል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በመላው ፡ ለዓለም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲደርስ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምኞቱ ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ።

እነዚህም ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ መንግሥቶች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተባለውን ፡ የተከበረ ፡ ኣሳብ ፡ ጠብቀው ፡ ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ በመረዳዳት ፡ ለመሥራት ፡ ሰላምን ፡ ለማጽናት ፡ ዋና ፡ ፈቃዳቸው ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ።

ስለዚህ ፡ ሰላምን ፡ ኣስከባሪ ፡ የሆነ ፡ ሁለቱ ፡ መንግሥቶች ፡ ጦርነቱን ፡ ለማስቀረት ፡ በሚያደርጉትና ፡ በሚደከሙት ፡ ድካም ፡ እንዲቀናቸው ፡ ከልባችን ፡ እንመኛለን ።

ነገር ፡ ግን ፡ እኛም ፡ በበኩላችን ፡ የዓለም ፡ መንግሥቶችም ፡ በበኩላቸው ፡ ጦርነቱን ፡ ለማስቀረት ፡ የሚደከምበት ፡ ድካም ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ የሰይጣን ፡ ኀይል ፡ አሸንፎ ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ መከራና ፡ ነውር ፡ የሚያመጣው ፡ ዓለምን ፡ የሚያዋርደውና ፡ የሚያደኸየው ፡ ጦርነት ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቷን ፡ ይዛ ፡ ሕዝቧን ፡ አስቀድማ ፡ ከብዙ ፡ ሺህ ፡ ዘመናት ፡ ዠርምሮ ፡ ብርታቱና ፡ ጉልበቱ ፡ የታወቀው ፡ ሕዝቧ ፡ እምነቱን ፡ በፍጹም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፍጥረት ፡ ምሽግ ፡ አድርጎ ፡ የሰጠውን ፡ በረሓና

፡ ተራራ ፡ ተጠግቶ ፡ ከሚደረግበት ፡ ግፍ ፡ ለመከላከልና ፡ ለመዳን ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ጠብታ ፡ ደሙን ፡ ለማፍሰስ ፡ ሳይቈጥብ ፡ ይከላከላል ።

ስለዚህ ፡ ሁለቱን ፡ ማኅበረተኛና ፡ ጠበኛ ፡ የሆኑትን ፡ መንግሥታት ፡ ጠባቸውን ፡ መርምሮ ፡ ማስታረቅ ፡ ወይም ፡ በደለኛውን ፡ መርምሮ ፡ ለመቅጣት ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ጸሓፊ ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ የቀረበለትን ፡ ራፖር ፡ ምርምር ፡ ዝምሮ ፡ የወልወል ፡ ግጭት ፡ የሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ ጥፋት ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ ለምርመራ ፡ የተቀመጡት ፡ 5ቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ አስታወቁ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በኢትዮጵያና ፡ በኢጣሊያ ፡ ጠብ ፡ የተነሣ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ተቀስቅሶ ፡ ፍጡር ፡ እንዳያልቅ ፡ በማለት ፡ በሁለቱ ፡ ጠበኞች ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቸርነትና ፡ መልካም ፡ ስሜት ፡ ያለበትን ፡ አሳብ ፡ አቀረበ ።

« ኢትዮጵያ ፡ በውጋዴን ፡ በኩል ፡ አገር ፡ ቈርጣ ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ልትሰጥ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ከባሕር ፡ የምትገናኝበት ፡ የዘይላን ፡ በር ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ልታገኝ» ፡ ይኸውም ፡ ሐሳብ ፡ ለሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ ተልኮ ፡ ሲመረመር ፡ ወዲያው ፡ ሙሴ ፡ ሙሶሊኒ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከበረሓ ፡ ጋራ ፡ ጉዳይ ፡ የለውምና ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ዕርቅ ፡ አልቀበልም ፡ ሲል ፡ አስታወቀ ። ቀጥሎም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ባሠልጣኝነት ፡ ለመግባት ፡ የማያጸድቅለትን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የክስ ፡ ወረቀት ፡ ለዓለም ፡ ማኅበር ፡ አቅርቦ ፡ ነበርና ፡ ማኅበሩም ፡ ይህንኑ ፡ ራፖር ፡ ተመልክተው ፡ የመሰላቸውን ፡ የሚቈርጡ ፡ 5 ሽማግሌዎች ፡ የእንግሊዝን ፥ የፈረንሳዊን ፥ የእስፓኝን ፥ የቱርክን ፡ መንግሥት ፡ መልክተኞች ፡ መረጠ ። እነሱም ፡ እንደ ፡ ታዘዙት ፡ መርምረው ፡ ኢጣሊያ ፡ ያሠልጥን ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ እየሠራ ፡ ሊያሠለጥን ፡ የሚገባው ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ የመጨረሻ ፡ አሳባቸውን ፡ ቈረጡ።

# ምዕራፍ ፡ 61 ።

## የአጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ ቤኒቶ ፡ ሙሶሊኒ ፡ ጦርነቱን ፡ እንዳስታወቀ ፡ ጳጳሱም ፡ ካሳቡ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተባበሩለትና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ጋዜጣ ፡ ጸሓፊዎች ፡ እንደ ፡ ተወቀሱ ።

የኢጣሊያ ፡ 1ኛ ፡ ሚኒስትር ፡ ሙሴ ፡ ሙሶሊኒ ፡ በግልጽም ፡ በስውርም ፡ በሠራው ፡ ፖለቲካ ፡ ይልቁንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነበሩት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መኳንንትና ፡ ባላባት ፡ ወዳጅ ፡ ይመስሉ ፡ የነበሩት ፡ የኢጣሊያ ፡ ቆንስሎችና ፡ ሚሲዮኖች ፡ ሰብስበው ፡ በላኩለትና ፡ እርሱም ፡

በጐደለ ፡ ሞልቶ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ማኅበር ፡ በላከው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኀጢአት ፡ በሚዘረዝር ፡ የክስ ፡ ወረቀት ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ ለገላጋይነት ፡ የመረጣቸው ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሐሰት ፡ በመላበት ፡ በኢጣሊያ ፡ ክስ ፡ ምክንያት ፡ ተጐትተው ፡ ለኢጣሊያ ፡ እንዲፈርዱላትና ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንዲፈርዱባት ፡ በሴኔሲያ ፡ ስም ፡ በሚጠራው ፡ አዳራሽ ፡ ሆኖ ፡ ያለትዕግሥት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ገላጋዮቹ ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ፈረዱ ፡ መላክተኛው ፡ ሙሴ ፡ ባሮን ፡ አሉዋዜ ፡ አስተላለፈለት ። ሙሴ ፡ ሙሶሊኒም ፡ ባዳራሹ ፡ ግንባር ፡ መላው ፡ የሮማ ፡ ሕዝብ ፡ ተሰብስቦ ፡ ጦርነት ፡ ለማስታወቅ ፡ የሚያደርገውን ፡ ዲስኩር ፡ እንዲሰማ ፡ ከንዴት ፡ ጋራ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶ ፡ በሚሊዮን ፡ የሚቈጠር ፡ ሕዝብ ፡ ከተሰበሰበ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ተናገረ ።

«ጥቁር ፡ ለባሽ ፡ የሆናችሁ ፡ ወንዶችም ፡ ሴቶችም ፡ በኢጣሊያ ፡ አገር ፡ ከኢጣሊያም ፡ አገር ፡ ውጭ ፡ ያላችሁ ፡ ስሙ ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ኻያ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚሆኑ ፡ የኢጣሊያ ፡ ሕዝቦች ፡ በየከተማው ፡ ለመስማት ፡ ተሰብስበዋል ። ይኸንንም ፡ የመሰለ ፡ ስብሰባ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተደርጎ ፡ ኣይታወቅም ። እነዚህም ፡ ኻያ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚሆኑ ፡ ሕገቦች ፡ ኣንድ ፡ ፈቃድ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ ስለሆኑ ፡ የኢጣሊያን ፡ ቈራጠኝነትና ፡ አለመለወጥ ፡ ለዓለም ፡ ሊያሳዩ ፡ ይችላሉ። ...

ከብዙ ፡ ወራት ፡ ወዲህ ፡ ዕድላችን ፡ ወዳመለከተበት ፡ ስፍራ ፡ ለመድረስ ፡ የሚፋጠነው ፡ የጦር ፡ ሠራዊታችን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የመላው ፡ ያ44 ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝባችን ፡ ሐሳብ ፡ ወደዚያው ፡ ይፈጥናል ። በዚህም ፡ ሕዝባችን ፡ ላይ ፡ ጠማማ ፡ የሆነ ፡ ፍርድ ፡ በዤኔብ ፡ ይዘጋጅበታል ፡ ይኸውም ፡ ፀሓይ ፡ ከምናገኝበት ፡ ስፍራ ፡ ሊያስወግዱን ፡ ነው ። ...

በዓለም ፡ ማኅበር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያለውን ፡ መብታችንን ፡ በማወቅ ፡ ፈንታ ፡ እኛን ፡ ለመጨቈን ፡ ያስባሉ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ጨቋኞቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ በፖለቲካም ፡ ቢመጡ ፡ በፖለተካ ፡ በጦርነትም ፡ ቢመጡ ፡ በጦርነት ፡ እንመልሳቸዋለን ።

እነሱን ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ኢትዮጵያን ፡ 40 ፡ ዓመት ፡ ታገሥን ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በቃ ።

አስቀድመን ፡ ደኅና ፡ አድርገን ፡ ሳንዋጋ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሊመልሰን ፡ የሚችል ፡ እንደሌለ ፡ ሁሉም ፡ ይወቅ ።

ባንድ ፡ ዘርና ፡ በፋሺስትነት ፡ የጸናሽው ፡ የቢቶሪዮ ፡ ቤኔቶ ፡ ኢጣሊያ ፡ በእግርሽ ፡ ቁሚ ፡ የቁርጠኝነትሽም ፡ ጩኸት ፡ ሰማይን ፡ መልቶ ፡ በአፍሪካ ፡ ሆነው ፡ ለሚጠባበቁት ፡ ወታደሮች ፡ መጽናኛ ፡ በዓለም ፡ ላለው ፡ ወዳጆችን ፡ መመኪያ ፡ ለጠላታችን ፡ ማስፈራሪያ ፡ የሚሆነውን ፡ ድምፅሽን ፡ አሰሚ ። »

ይህንንም ፡ በዓለም ፡ ላሉ ፡ መንግሥታት ፡ ይልቁንም ፡ ለመጨቈን ፡ በሚደራጁበት ፡ በዤኔብ ፡ መልክተኞች ፡ ላይ ፡ የሚያስፈራራ ፡ ዲስኩር ፡ እ ፡ ኤ. ቀ. ጥቅምት ፡ 2 ፡ ቀን ፡ ከማድረጉ ፡ በፊት ፡ በነሐሴና ፡ በመስከረም ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከኢጣሊያ ፡ በመርከብ ፡ እየመጡ ፡ ኣሥመራ ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ ተከማችተው ፡ « ተዋጉ» የሚለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ከተጨመሩለት ፡ በቀር ፡ በጠቅላላው ፡ የጦር ፡ ኀይሉ ፡ 33 ፡ ሺ ፡ ወታደር ፡ ነው ። ከነዚህ ፡ 200ው ፡ ሺ ፡ የነጭ ፡ 100ው ፡ ሺ ፡ የጥቁር ፡ ወታደር ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ ከልዩ ፡ ጠመንዣና ፡ መትረየስ ፡ ከመድፉም ፡ በቀር ፡ 500 ፡ አይሮፕላን ፡ 300 ፡ ታንክ ፡ ነበራቸው ። ጠቅላይ ፡ የጦር ፡ አዛዡም ፡ ዠኔራል ፡ ኤሚሊዮ ፡ ደቦኖ ፡ ነው ።

ለዚህም ፡ ዘመቻ ፡ የተነሣው ፡ የፋሺስት ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እየተባለ ፡ ባንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ አፍ ፡ እንደሚነገረው ፡ ሳይሆን ፡ ጳጳሱ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በካቶሊክነት ፡ ለማግኘት ፡ ንጉሡም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥታት ፡ ስም ፡ ለመውረስ ፡ ተስፋ ፡ ስለ ፡ ተደረገላቸው ፡ ወገኖቻቸውን ፡ ልከዋል ። እነሱም ፡ ከዚሁ ፡ ከፋሺስት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጋራ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ የቤተ ፡ ክህነቱም ፡ ወገን ፡ ሚኒስትሮችም ፡ ጭምር ፡ የአልጋ ፡ ወራሽ ፡ ባለቤት ፡ ሳትቀር ፡ በመጨረሻ ፡ የጥቅም ፡ ተካፋይ ፡ ብቻ ፡ እንዳይሆኑ ፡ በመዠመሪያ ፡ የድሉ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ ከዱቼ ፡ ኩራት ፡ የሚሰጥ ፡ ንግግር ፡ እየተቀበሉ ፡ በመርከብ ፡ ተሳፍረው ፡ «ኢጣሊያ ፡ ሆይ ፡ ከባሕር ፡ ወዲያ ፡ አልፈን ፡ ተራራና ፡ መሬት ፡ እናወርስሻለን» ፡ የሚለውን ፡ መዝሙር ፡ እየዘመሩ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ መጡ ።

ይልቁንም ፡ የቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ወገን ፡ በዓለም ፡ ሰላም ፡ እንዲሆን ፡ ሁለቱን ፡ ጠበኞች ፡ በማስታረቅ ፡ ወይም ፡ ሙሶሊኒን ፡ በመንፈሳዊ ፡ አባትነታቸው ፡ በመገሠጽ ፡ ፈንታ ፡ ይኸም ፡ ቢቀር ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራቸውን ፡ በማስኬድ ፡ ፈንታ ፡ በመንበረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐዋርያ ፡ ተቀምጠው ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ ክርስቲያን ፡ አባትነታቸውን ፡ የሚያጸድቁት ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ለሙሶሊኒ ፡ እንደ ፡ ቀኝ ፡ ክንድ ፡ ሆነው ፡ ይህ ፡ ዘመቻ ፡ የተቀደሰ ፡ ዘመቻ ፡ ነውና ፡ በርታ ፡ እያሉ ፡ ያጽናኑት ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

የርሳቸውንም ፡ አሳብ ፡ በመከተል ፡ ብዙ ፡ የበታቾቻቸው ፡ ጳጳሳት ፡ ለዘመቻው ፡ ርዳታ ፡ የሚሆን ፡ ብዙ ፡ ወርቅና ፡ ገንዘባቸውን ፡ ሰጡ ።

ስለዚህ ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ በዚህ ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ የዓለም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ተገረሙበት ። ከዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ሲሞን ፡ ረስቲን ፡ እንደ ፡ ተረጐሙልን ፡ ኤሊክ ፡ ሲንድሩም ፡ የሚባሉት ፡ የስዊድን ፡ ጋዜጣ ፡ ጸሓፊ ፡ ልብን ፡ እንደ ፡ ጦር ፡ በሚወጋ ፡ ንግግር ፡ ወቅሠዋቸዋል ። ቃሉም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው።

«ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ በሰሜን ፡ አገር ፡ የተወለድሁ ፡ አንድ ፡ ፕሮቴስታንት ፡ ነኝ ፡ ባገራችንም ፡ በስዌድን ፡ በግንባራችን ፡ የምንደፋው ፡ በእልፍኛችን ፡ ሆነን ፡ ከእግዚአብሔር ፡

ካምላካችን ፡ ጋራ ፡ ስንናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ ብንናገር ፡ ቁመን ፡ እንነጋገራለንና ፡ በእግርዎ ፡ ላይ ፡ ወድቄ ፡ ጫማዎን ፡ ስለ ፡ ማልስምዎ ፡ አይቈጡብኝ ።

ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ አንድ ፡ ምስኪን ፡ ኀጢአተኛ ፡ ነኝ ፡ እርስዎ ፡ ግን ፡ የመድኀኒታችን ፡ ምትክ ፡ ነዎት ፡ የማይሳሳቱም ፡ ነዎት ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ እነቅፍዎታለሁ ።

እርስዎ ፡ የካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዋና ፡ ነዎት ፡ ካቶሊካዊት ፡ ማለትም ፡ የሁሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። ዛሬ ፡ እንግዴህ ፡ የርስዎ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በውነት ፡ የሁሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናት? እርስዎ ፡ ከሙሶሊኒ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ከሌላው ፡ ዓለም ፡ ጋራ ፡ በጠብ ፡ አሉ ፡ ርስዎና ፡ ከርስዎ ፡ በታች ፡ ያሉት ፡ ሌሎችም ፡ ጳጳሳት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለኢጣሊያ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ እንድትሆን ፡ የሚገባ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። ርስዎ ፡ መቼም ፡ የሐዋርያው ፡ የጴጥሮስ ፡ ተከታይ ፡ ነዎትና ፡ አይሳሳቱም ። እንግዴህ ፡ ሌላው ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ቃልዎን ፡ ሳይሰማ ፡ በኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ « ሳንክሲዮ » ፡ ቢያደርግ ፡ መሳሳቱ ፡ ነው?

ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ ኢጣሊያ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ ትሠራለች ፡ ብለው ፡ ሰብከዋል ። የመሲና ፡ የቢረንዲቤም ፡ ጳጳሳት ፡ ወርቃቸውን ፡ ሁሉ ፡ ለጦርነቱ ፡ ከሳራ ፡ እንደ ፡ ሰጡ ፡ ሰማን ። እናንተ ፡ ጳጳሳት ፡ ይህንን ፡ ስታደርጉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከኢጣሊያ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ የማለት ፡ ያኽል ፡ ይመስለኛል ። እንግዴህ ፡ ሌላው ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ የኢጣሊያንን ፡ ሥራ ፡ ቢቃወም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፍርድ ፡ ይቃወም ፡ ይሆን?? ኢትዮጵያውያንስ ፡ አገራቸውን ፡ ሲጠብቁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡ ይኸንን ፡ ርስዎ ፡ እንዳሉ ፡ ኢጣሊያ ፡ የጽድቅ ፡ ውጊያ ፡ የምትዋጋ ፡ ከሆነ ፡ ሌላውም ፡ ዓለም ፡ ይኸንን ፡ የጽድቅ ፡ ጦርነት ፡ ቢቃወም ፡ መቼም ፡ ከናንተ ፡ በቀር ፡ ሌላው ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የካደ ፡ ይመስላል ።

እንግዴህ ፡ ርስዎ ፡ እንደሚሉት ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ቃሉን ፡ ሊያፈርስ ፡ መሐላውንም ፡ ሊሰብር ፡ ፈቅዷል ። ርስዎ ፡ እንደሚሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ አገራቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ቢሰበሰቡ ፡ የኢጣሊያ ፡ አይሮፕላን ፡ ጥርግ ፡ አድርጎ ፡ ቢያጠፋቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሥራ ፡ ነው ። ሴቶችንና ፡ ሕፃናትን ፡ በቦምብ ፡ ሲያጠፉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግላሉ ። ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ በመጸሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ አላገኘንም ፡ ነበርና ፡ ርስዎ ፡ አሁን ፡ ስላስተማሩን ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ይህንን ፡ ሁሉ ፡ የምታስተምረን ፡ ቅድስቲቱ ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናት ። በዱሮ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሰው ፡ ይልቅ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መታዘዝ ፡ ይገባል ፡ ብላ ፡ ታስተምር ፡ ነበር ።

ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ የርስዎ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ አይደለችም ፡ የሁሉም ፡ አይደለችም ፡ እግዚአብሔር ፡ መሐላን ፡ ማፍረስ ፡ ይወዳል ፡ ብለው ፡ ቢያስተምሩን ፡ ውሸትዎ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እንመልስልዎታለን ። ርስዎም ፡ የዓለም ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ሲሉ ፡ ሳሉ ፡ የሙሶሊኒ ፡ ባሪያ

፡ ሆነዋል ። በኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ ሥጋዊ ፡ «ሳንክሲዮ» ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ እንደዚሁም ፡ በርስዎ ፡ ላይ ፡ መንፈሳዊ ፡ « ሳንክሲዮ» ፡ ማድረግ ፡ የግድ ፡ ነው ። ርስዎ ፡ የሚያመልኩት ፡ አምላክ ፡ ጣዖት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አምላክ ፡ አይደለም ። ኢትዮጵያ ፡ ርስዎ ፡ ለሚያመልኩት ፡ አምላክ ፡ ጸሎት ፡ ልታሳርግ ፡ ኣትችልም ። ሌላው ፡ ዓለም ፡ እንደዚሁ ፡ ወደ ፡ ርስዎ ፡ አምላክ ፡ ሊጸልይ ፡ አይችልም ። ርስዎ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይልቅ ፡ ለሰውዬው ፡ ለሙሶሊኒ ፡ የሚታዘዙ ፡ ሆነዋልና።

ርስዎ ፡ መናገር ፡ በተገባዎ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ አሉ ፡ ዘም ፡ ማለትም ፡ በተገባዎ ፡ ጊዜ ፡ ተናገሩ ። አሁንም ፡ ከሌሎች ፡ ጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ የሙሶሊኒን ፡ ጫማ ፡ ስመዋል ።

የዓለምን ፡ ሰላም ፡ የሚያውከውን ፡ ወንበዴውን ፡ ቢያወግዙት ፡ ኖሮ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንዎ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ በሆነ ፡ ነበር ። ምናልባት ፡ እርስዎም ፡ በታሰሩ ፡ ነበር ፡ ምናልባትም ፡ እንደ ፡ ዱሮ ፡ ዘመን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ወደ ፡ ሰማዕትነት ፡ ሞት ፡ በደረሱ ፡ ነበር ። ዓለምም ፡ ሁሉ ፡ ከርስዎ ፡ ጋራ ፡ በሆነ ፡ ነበር ። ክርስቲያን ፡ ቢሆን ፡ አረመኔም ፡ ቢሆን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እርስዎ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በተረዳ ፡ ነበር ።

አሁንም ፡ በቅርብ ፡ የገና ፡ በዓል ፡ ነው ። ለግፍ ፡ ጦርነት ፡ ወርቃቸውን ፡ የሰጡ ፡ ጳጳሳትም ፡ እንግዴህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ይሁን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሰላም ፡ ይሁን ፡ ለሰውም ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ሊዘምሩ ፡ ናቸው ። ይኸንንም ፡ ሲዘምሩ ፡ በደረታቸው ፡ የወርቅ ፡ መስቀል ፡ ሳያደርጉ ፡ አይቀርም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዠርባቸው ፡ ላይ ፡ የዕንጨት ፡ መስቀል ፡ ቢሸከሙ ፡ ይሻል ፡ ነበር ።

ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ በዓሉን ፡ ያሳምርልዎ ፡ ብዬ ፡ ምኞቴን ፡ እገልጻለሁ » ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሮማ ፡ ጳጳስ ፡ በነገሩ ፡ ተጸጽተው ፡ ሰላም ፡ እንዲሆን ፡ የረዱት ፡ ነገር ፡ የለም ።

ዘመቻውንም ፡ የተቀደሰ ፡ ዘመቻ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ወዲህ ፡ ለዘመቻ ፡ የሚሻገረውን ፡ ታንክና ፡ መሣሪያ ፡ ባረኩ ።

ሙሶሊኒም ፡ በውሳጣዊ ፡ አገሩ ፡ የንጉሡና ፡ የጳጳሱ ፡ ኣሳብ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተባበረለት ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ በሮማ ፡ እ. ኤ. ቍ ፡ ጥቅምት ፡ 2 ፡ 1935 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መስከረም ፡ 21 ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጦርነተን ፡ ባስታወቀ ፡ በማግስቱ ፡ ወሰኑን ፡ አልፎ ፡ ጦርነት ፡ እንዲዠመር ፡ ለጄኔራል ፡ ደቦኖ ፡ ቴሌግራም ፡ አስተላለፈለት ።

ርሱም ፡ መላውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሰብስቦ ፡ ጦርነት ፡ እንዲዠመር ፡ የንጉሥና ፡ የዱቼ ፡ ፈቃድ ፡ መሆኑን ፡ አስታውቆ ፡ መላውን ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ እሦስት ፡ ላይ ፡ ከፈለው ።

አንደኛው ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በጄኔራል ፡ ሳንቲን ፡ እየታዘዘ ፡ ወደ ፡ ዐዲግራት ፡ 2ኛው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ (ያገር ፡ ተወላጅ ፡ ወታደር) ፡ በጄኔራል ፡ ፐሮሊ ፡ እየታዘዘ ፡ ወደ ፡ እንቲጮ ፡ 3ኛው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በጄኔራል ፡ ማራቢኛ ፡ እየታህ ፡ ወደ ፡ ዐድዋ ፡ እየተጓዙ ፡ የሚቃወማቸውን ፡ እየወጉ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዲያልፉ ፡ ትእዛዝ ፡ አደረገ ።



**ቤኒቶ ፡ ሙሶሊኒ**

# ምዕራፍ ፡ 62 ።

## የመዠመሪያው ፡ ጦርነት ፡ የዐድዋ ፡ መያዝ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ስለ ፡ መከላከል ፡ የተናገሩት ፡ ዲስኩር ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ በጠረፍ ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ቢኖር ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሰላም ፡ በዓለም ፡ እንዲጠበቅ ፡ አጥቂውን ፡ ባንድነት ፡ እናጠቃለን ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ችላ ፡ ብለው ፡ በማኅበሩ ፡ ግዴታ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ማኅበረተኛዪቱን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲወጋ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡

አይመለከቱም ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ የጦርነት ፡ ስፍራ ፡ በማመራረጥ ፡ በጠረፍ ፡ ያሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ እንዲያፈገፍጉ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሰራዬ ፡ ባንዳ ፡ የሚባለው ፡ በመዠመሪያ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ ደዐሮ ፡ ተክሌ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተጋጥመው ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ፡ የኢጣሊያን ፡ ባንዳ ፡ ያዝ ፡ የነበረው ፡ ሞርጋንቲን ፡ የሚባለው ፡ «ሌተና» ፡ ከብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ በጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ሞተ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ በዚህ ፡ በደዐሮ ፡ ተክሌ ፡ ምሽግ ፡ ባሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ ላይ ፡ የቦምብ ፡ ዝናም ፡ እንዲጣል ፡ ባቸው ፡ አዞ ፡ ወዲያው ፡ ብዙ ፡ አይሮፕላኖች ፡ መጥተው ፡ ያንን ፡ ከጠመንዣ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የሌለውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በቦምብ ፡ ሲመቱት ፡ እንደዚሁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮችም ፡ በያዙት ፡ ጠመንዣ ፡ ሽቅብ ፡ በአይሮፕላኑ ፡ ላይ ፡ በድፍረት ፡ እስፍራቸው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ይተኩሱ ፡ ነበር፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ እየተመላለሰ ፡ የአይሮፕላን ፡ ቦምብ ፡ ስላጠቃው ፡ የኛ ፡ ወታደሮች ፡ ትእዛዝ ፡ ተላልፎላቸው ፡ ያንን ፡ ስፍራ ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ወደ ፡ ጋሻ ፡ ወርቂ ፡ ተመለሱ ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በየመንገዱ ፡ በዠግንነት ፡ ከታች ፡ ወታደሩን ፡ የሚመታበትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከሰማይ ፡ ባለው ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ እየመታ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፍቶ ፡ የወንድነት ፡ ሥራ ፡ ለማንኛው ፡ ሠራዊት ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚመሰከረውን ፡ የዐድዋን ፡ ከተማ ፡ ያዘ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጕዳይ ፡ ሊፈጽሙ ፡ ለተላኩት ፡ ለክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያትና ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ለሚነጋገሩት ፡ ለሜትር ፡ ዤዝ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ባ12ኛውና ፡ ባ13ኛው ፡ እንዲሁም ፡ ባ15ኛው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ ጥሶ ፡ ጦርነት ፡ ስላደረገ ፡ ያ16ኛውን ፡ አንቀጽ ፡ ቃል ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ በኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ እንዲፈጽሙበት ፡



ፊታውራሪ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት

እንዲያመለክቱ ፡ አስተላለፉ ። ከዚህም ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ በሐምሌ ፡ 11 ፡ ቀን ፡ 1927 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢትዮጵያን ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ ሚኒስትሮች ፡ የቤተ ፡ ክህነቱም ፡ ሹማምንቶች ፡ በምክር ፡ ቤት ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ አዘው ፡ ከተሰበሰቡ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ተናገሩ።

«ከአርባ ፡ ዘመናት ፡ ይበልጥ ፡ ዠምሮ ፡ ኢጣሊያ ፡ አገራችንን ፡ ለመውሰድ ፡ ያላትን ፡ ምኞት ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ አላቋረጠችም ፡ ነበር ። በዚሁም ፡ ዘመናት ፡ ሁሉ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አኳኋን ፡ ዘወትር ፡ ይታይ ፡ የነበረው ፡ ይኸው ፡ ምኞቷ ፡ ባለፈው ፡ ባ1927 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በክረምቱ ፡ ውስጥ ፡ በሥራዋ ፡ እየተገለጸ ፡ መታየት ፡ ዠመረ ። ይኸውም ፡ ርግጥ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ በነሐሴ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ አላንዳች ፡ ምክንያት ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በወሰኖቻችን ፡ አቅራቢያ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በብዙ ፡ ማከማቸት ፡ ዠመረ ።

ይኸንኑ ፡ ነገር ፡ ሰምተን ፡ ምክንያቱ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጠይቅ ፡ ብለን ፡ ሮማ ፡ ላለው ፡ ጕዳይ ፡ ፈጻሚያችን ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲያልፍለት ፡ አደረግን ። ይኸን ፡ የጦር ፡ መዘጋጀት ፡ ያደረግነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኤርትራንና ፡ የሱማሌን ፡ ቅኝ ፡ አገሮቻችንን ፡ ለመውጋት ፡ ሐሳብ ፡ ስላላት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ከመዠመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ሐሰት ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ምላሽ ፡ አድርገው ፡ ሰጡ ። ምንም ፡ ይኸ ፡ የተሰጠው ፡ ምላሽ ፡ ጨርሶ ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ ብንገልጽ ፡ ኢጣሊያ ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዠምራ ፡ የምትከተለው ፡ ሐሳቧ ፡ በረዥሙ ፡ መርምራ ፡ በቈረጠችው ፡ ፕላን ፡ ነበርና፡ ምንም ፡ በፍጹም ፡ የወሰነችው ፡ አሳቧ ፡ እኛን ፡ በማጥቃት ፡ ለመውጋት ፡ ቢሆን ፡ ለመከላከያ ፡ ነው ፡ እያሰኘች ፡ የጦር ፡ ማዘጋጀቷን ፡ እየገፋች ፡ ከመሄዷ ፡ አላቋረጠችም ።

ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ግፈኛ ፡ የሆነ ፡ ሐሳብ ፡ በዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ አስመስሎ ፡ ለማሳየት ፡ ለዚሁ ፡ የሚጠቅም ፡ ምክንያት ፡ ማግኘት ፡ ለኢጣሊያ ፡ የማያስፈልጋት ፡ ነበር ።

ግማሾቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሠራተኞቹ ፡ በሆኑና ፡ ግማሾቹ ፡ የኢጣሊያ ፡ የንግድ ፡ አጃንሲያ ፡ አሽከሮች ፡ በሆኑ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ መካከል ፡ ባለፈው ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ጐንደር ፡ ላይ ፡ በሴት ፡ ምክንያት ፡ አምባጓሮ ፡ ተነሣ ፡ በእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ በራሳቸው ፡ ጕዳይ ፡ ይህ ፡ ጠብ ፡ ተነሥቶ ፡ ደም ፡ ቢፈስ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ያለው ፡ የኢጣሊያ ፡ ሌጋሲዮን ፡ በዲፕሎማቲክ ፡ መንገድ ፡ በብርቱ ፡ በነገሩ ፡ ገብቶበት ፡ መንግሥታችን ፡ ሰላም ፡ ፈላጊ ፡ በመሆኑ ፡ የከረረ ፡ ጠብ ፡ እንዳይነሣ ፡ ሲል ፡ ኢጣሊያኖች ፡ የጠየቁት ፡ እንዲፈጸምላቸው ፡ አደረገ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ላሁኑ ፡ ጠባችን ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ የወልወል ፡ አደጋ ፡ ወደቀ ።

ኢጣሊያ ፡ የኛን ፡ ግዛት ፡ ቀንሳና ፡ የሀገራችንን ፡ ነጻ ፡ ተገዥነትን ፡ እንደማክበር ፡ ሁሉ ፡ ጥላ ፡ ባ19፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በሁለቱ ፡ መንግሥቶች ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ የወሰነውን ፡ ወሰን ፡ መቶ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ያኸል ፡ አልፋ ፡ ወልወል ፡ በሚባለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ወታደርና ፡ ብዙ ፡ መሣሪያ ፡ አስቀመጠች ።

ከእንግሊዝ ፡ ሱማሌና ፡ ከእኛ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ወሰን ፡ በመወሰኑ ፡ ምክንያት ፡ በውል ፡ እንደ ፡ ተፈቀደላቸው ፡ የእንግሊዝ ፡ ሱማሌ ፡ ጐሣዎች ፡ ከብት ፡ የሚያግጡበትን ፡ ቦታ ፡ ሄደው ፡ አይተው ፡ ለመወሰን ፡ ከኢትዮጵያም ፡ መንግሥት ፡ ከእንግሊዝም ፡ መንግሥት ፡ ሰዎች ፡ ታዘው ፡ ነበር ።

እነዚህ ፡ መንግሥታት ፡ ለሥራ ፡ የላኳቸው ፡ መላከተኞች ፡ የታዘዙትን ፡ ሥራ ፡ በግዛታችን ፡ ላይ ፡ ሲሠሩ ፡ የሚጠብቃቸው ፡ መንግሥታችን ፡ ስለነበረ ፡ ተከታዮች ፡ ወታደሮች ፡ ተሰጥተዋቸው ፡ ነበረ ። በነዚህም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ እንደምታውቁት ፡ ሁሉ ፡ በኅዳር ፡ 26 ፡ ቀን ፡ አደጋ ፡ በድንገት ፡ ተጥሎባቸው ፡ አርበኞች ፡ ወታደሮቻችን ፡ በኢጣሊያ ፡ መትረየስ ፡ በታንኮና ፡ በአቢዮኑ ፡ መውደቃቸው ፡ የኢጣሊያ ፡ አጥቂዎች ፡ ቀድሞ ፡ አስበው ፡ የፈጸሙት ፡ ግፍ ፡ መሆኑን ፡ እንደሚበቃ ፡ የሚመሰክር ፡ ነው ።

እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ በገዛ ፡ ግዛታችን ፡ ላይ ፡ ወታደሮቻችንን ፡ ወግተው ፡ ኢጣሊያ ፡ የገዛ ፡ ሰዎቿ ፡ የሠሩትን ፡ ግፍ ፡ አዛውራ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ለማድረግና ፡ እኛን ፡ ለመውቀስ ፡ አሰበች ። ወታደሮቻችንን ፡ መግደሏ ፡ የማይበቃት ፡ ሆነና ፡ መንግሥታችንን ፡ ይቅርታ ፡ እንዲጠይቃትና ፡ ካሳ ፡ እንዲከፍል ፡ ከመጠየቅ ፡ ደረሰች ።

ኢትዮጵያም ፡ የሚገባትን ፡ ሙብት ፡ ህሊናዋ ፡ ያውቅላታልና ፡ ኢጣሊያ ፡ ለዘለዓለም ፡ በመካከላችን ፡ ሰላምና ፡ ወዳጅነት ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ በመካከላችንም ፡ ጠብ ፡ ቢነሣ ፡ ይኸው ፡ ጠብ ፡ በሽማግሌ ፡ ሥልጣን ፡ በሰላም ፡ እንዲያልቅ ፡ ቃል ፡ የገባችበትን ፡ ባ1920 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተደረገውን ፡ ውል ፡ ጠቅሰን ፡ ነገሩን ፡ በውል ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ ለመጨረስ ፡ ጥያቄያችንን ፡ ወዲያው ፡ አቀረብንላት ።

ለዚህ ፡ ላቀረብነውም ፡ ጥያቄያችን ፡ ምላሹ ፡ ፍጹም ፡ እንቢታ ፡ ሆኖ ፡ ኢጣሊያ ፡ ሳይመረመርና ፡ በሚገባው ፡ መንገድ ፡ ሳይፈረድ ፡ ያቀረበችውን ፡ ጥያቄ ፡ በሙሉ ፡ ለማስፈጸም ፡ ጥብቅ ፡ አሳቧን ፡ ገለጸች ።

እኛም ፡ ክብር ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ እንዳይነካ ፡ ቈርጠን ፡ ነበርና ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ በሙሉ ፡ ፈቃዱ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ጠብ ፡ ለተገባው ፡ አለመድሎ ፡ ለሚፈርድ ፡ ለመንግሥት ፡ ዳኛ ፡ አቅርቦ ፡ ቢፈርድ ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ መፈጸም ፡ ይህንኑ ፡ መንግሥት ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳየው ፡ እንጂ ፡ የማያዋርደው ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተረዳነው ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆና ፡ የተገኘች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተፈረደባትን ፡ ፍርድ ፡ በሙሉ ፡ ወዲያው ፡ የምትፈጽም ፡ መሆኗን ፡ በግልጽ ፡ አስታወቅን ።

ኢጣሊያ ፡ ነገሩ ፡ በሽማግሌ ፡ እንዲያልቅ ፡ የማትፈልግ ፡ ከመሆኗ ፡ የተነሣ ፡ ነገሩ ፡ በሕግና ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ እንዲያልቅ ፡ ፈቃዳችን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ይህንኑ ፡ ሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ በመፈለግ ፡ ነገሩን ፡ ወደ ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ አማካሪዎች ፡ ለማድረስ ፡ የሚያስፈልገን ፡

ሆነ ። ይህንም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ያደረስንበት ፡ ምክንያት ፡ በዝርዝሩ ፡ በጽሕፈ ፡ አድርገን ፡ ለኢጣሊያ ፡ ንጉሥና ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ሹም ፡ ለሙሶሊኒ ፡ አስታወቅን ።

ባለፈው ፡ በጥር ፡ ወር ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ኣማካሪዎች ፡ በተሰበሰቡበት ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ነገሩ ፡ ታይቶ ፡ ነገሩ ፡ በሽማግሌ ፡ እንዲያልቅ ፡ ኣሳቡን ፡ ኢጣሊያ ፡ ሲቀፋት ፡ ተቀበለች ።

ነገር ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ በጥር ፡ ወር ፡ 11 ፡ ቀን ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ አማካሪዎች ፡ የቈረጡትን ፡ ቃል ፡ ተከትለን ፡ ሽማግሌዎቹን ፡ ለመምረጥ ፡ ተዠምሮ ፡ የነበረው ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ንግግር ፡ ያላደረግነውን ፡ ጥፋት ፡ ለማሳመን ፡ እየተጣጣረ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ሚኒስትር ፡ ነገሩን ፡ እየጐተተው ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ በመጋቢት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ነገሩን ፡ ወደ ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ አማካሪዎች ፡ ማድረስ ፡ የሚያስፈልገን ፡ ሆነ ።

በውነትም ፡ ኢጣሊያ ፡ በዲፕሎማቲክ ፡ መንገድ ፡ መንግሥታችንን ፡ በማይገባ ፡ ለመጫን ፡ ስትጣጣር ፡ ደግሞ ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ በየቀኑ ፡ በራዲዮ ፡ የሚመጣው ፡ ወሬ ፡ በየቀኑ ፡ ወታደር ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ጥይት ፡ ወደ ፡ ኤርትራና ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ ሱማሌ ፡ ወሰናችን ፡ ባለማቋረጥ ፡ መላኩን ፡ እየሰማን ፡ ጦር ፡ ይሆናል ፡ የማለትን ፡ አሳብ ፡ በየጊዜው ፡ የሚያረጋግጥልን ፡ ሆነ ።

ነገሩን ፡ ሁለተኛ ፡ ወደ ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ በማድረሳችን ፡ የተነሣ ፡ በግንቦት ፡ 17 ፡ ቀን ፡ 1927 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በርግጡ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ እንዲመረጡ ፡ ተቈረጠ ።

ኢትዮጵያ ፡ የሚፈረደው ፡ ፍርድ ፡ በፍጹም ፡ በሕግ ፡ መሠረትና ፡ አለመድሎ ፡ እንዲሆን ፡ ምኞቷ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከእሷ ፡ ወገን ፡ ሽማግሌ ፡ የሚሆኑትን ፡ በመንግሥታት ፡ ሕግ ፡ በዕውቀታቸውና ፡ በሥልጣናቸው ፡ እጅግ ፡ የታወቁ ፡ አንድ ፡ የፈረንሳዊ ፡ የሕግ ፡ ሊቅና ፡ 1 ፡ የአሜሪካ ፡ ሕግ ፡ ዐዋቂ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መረጠች ።

ኢጣሊያ ፡ በበኩሏ ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ሹማምንቶች ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ የኢጣሊያ ፡ ሰዎች ፡ መረጠች ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ምንም ፡ የምንቃወመው ፡ ነገር ፡ ባይኖር ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ያገሩን ፡ ሰዎች ፡ መምረጡ ፡ ክርክሩ ፡ በሕግና ፡ ኣድልዎ ፡ በሌለበት ፡ መንገድ ፡ እንዲያልቅ ፡ አለመፍቀዱን ፡ ማሰብ ፡ የሚገባ ፡ መስሎ ፡ ስለታየን ፡ ምክንያቱም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ እንዲከራከርላት ፡ በመረጠችው ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ኣድልዎ ፡ የሌለበት ፡ ፍርድ ፡ ይፈርዳል ፡ ተብሎ ፡ የማይጠረጠር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የመረጠቻቸው ፡ ጨዋዎች ፡ የታያቸውን ፡ እንዲፈርዱ ፡ ነፃነት ፡ የሌላቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ምክንያት ፡ ክርክሩ ፡ በሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ እንደሚያልቅ ፡ የሚያሠጋ

፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ መሠረቱ ፡ የዓለም ፡ ሰላም ፡ መሆኑን ፡ ተመልክቶ ፡ ደግሞ ፡ ዋና ፡ ምኞቱ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሰላም ፡ እንዲጸድቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የመታረቂያ ፡ መንገድ ፡ ይገኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማለት ፡ በበኩሉ ፡ መሞከር ፡ ዠመረ ። ምንም ፡ የውጋዴን ፡ አውራጃ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሆኑ ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ የማያጠራጥር ፡ ቢሆን ፡ ምንም ፡ ኢጣሊያ ፡ ተጋፍቶ ፡ መጥቶ ፡ በርስታችን ፡ ክፉ ፡ አደጋ ፡ ቢጥልብን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ያቀረበውን ፡ የዕርቅ ፡ ሐሳብ ፡ እኛ ፡ ከውጋዴ ፡ ግዛታችን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ቈርሰን ፡ ለኢጣሊያ ፡ እንድንሰጥና ፡ ለዚሁም ፡ ለውጥ ፡ እንግሊዝ ፡ የዚይላንበርና ፡ ኣንድ ፡ ክፍል ፡ ከግዛቱ ፡ ቈርሶ ፡ ለኛ ፡ እንዲሰጥ ፡ ነበር ። እኛም ፡ ሰላም ፡ ለመፈለጋችን ፡ ወሰን ፡ የለውምና ፡ ይህን ፡ የቀረበውን ፡ የዕርቅ ፡ ሐሳብ ፡ ለመመርመር ፡ ተዘጋጅተን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የዕርቅ ፡ ሐሳብ ፡ ገና ፡ ከመቅረቡ ፡ ሙሴ ፡ ሙሶሊኒ ፡ በፍጹም ፡ አልቀበለውም ፡ ስላለ ፡ በነገሩ ፡ እንድናስብበት ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆነ ።

አሁንም ፡ ጨዋዎቹ ፡ የተመረጡበትን ፡ ጕዳይ ፡ ለመፈጸም ፡ አልተቻላቸውም ። የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ያቀረበውን ፡ የዕርቅ ፡ ሐሳብ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ዋና ፡ ሹም ፡ ባጭሩ ፡ ቈረጠው ።

ኢጣሊያኖችም ፡ መሰናዳታቸውን ፡ አላቋረጡም ። የኢጣሊያ ፡ መንግሥትም ፡ ታላላቁ ፡ ሹማምንቶች ፡ በልባቸው ፡ ያለው ፡ ዋናው ፡ ሐሳባቸው ፡ አገራችንን ፡ ለመውሰድ ፡ መሆኑን ፡ በግልጥ ፡ ይናገራሉ ። ስለዚህ ፡ ከእንግዴህ ፡ ወዲያ ፡ የጦርነት ፡ ሰዓት ፡ እየቀረበ ፡ መሄዱ ፡ ነው ።

ባለፈው ፡ ሰኔ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ዋና ፡ ሹም ፡ የአፍሪካ ፡ ምሥራቅ ፡ ተብሎ ፡ አዲስ ፡ ወደ ፡ ተሰየመው ፡ ወደ ፡ ኤርትራና ፡ ወደ ፡ ሱማሊያ ፡ በታዘዘው ፡ 3 ፡ ሺ ፡ ወታደር ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ለኢጣሊያ ፡ ሕዝብ ፡ ሲሰብክ ፡ የጦር ፡ ፈላጊነት ፡ መንፈሳቸውን ፡ ለማነቃነቅ ፡ ብሎ ፡ እናንተ ፡ የምትሄዱት ፡ ለታሪካችን ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የዠግንነት ፡ ነገር ፡ ልትጽፉ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተናገረ።

ሙሴ ፡ ሙሶሊኒ ፡ እንደሚሉት ፡ ኢጣሊያ ፡ የምትፈልገው ፡ የኛን ፡ ሕዝብ ፡ ለማሠልጠን ፡ ነው ። ነገሩ ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ እንዳያልቅ ፡ ለማድረግ ፡ ኢጣሊያ ፡ ካሁኑ ፡ ቈርጣለች ፡ ሐሳቧ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ፈሶ ፡ የቀድሞውን ፡ የዐድዋን ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ ነው ።

አረመኔ ፡ ሕዝብ ፡ እያለች ፡ ስሙን ፡ የምታጠፋው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ የሚያከብርና ፡ የፈረመውን ፡ ውል ፡ የሚያጸድቅ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።

ኢትዮጵያ ፡ ጦርነት ፡ እንዲሆን ፡ አትፈልግም ፡ የመጣውን ፡ ግን ፡ መከላከሏ ፡ አይቀርም ። በዐድዋ ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ጠብ ፡ አንሺ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አልነበረችም ። ጦርነቱ ፡ የሆነበት ፡

ምክንያቱም ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ወሰን ፡ አልፈው ፡ በግዛቷ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ተገኙ ፡ ነው ። ምናልባት ፡ ደግሞ ፡ ነገ ፡ እንደዚሁ ፡ ያደርጉ ፡ ይሆናል ።

በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ባርበኞቿ ፡ ዠግንነት ፡ የመጣባትን ፡ መከታ ፡ ምንም ፡ ባ1888 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ድል ፡ ብትነሣ ፡ (ብታደርግ) ፡ የሚገባትን ፡ ሁሉ ፡ አልጠየቀችም ። የግዛቷ ፡ ማስፋፊያ ፡ ምክንያት ፡ አላደረገችውም ።

ከቀን ፡ እስከ ፡ ቀን ፡ የማይቀር ፡ መስሎ ፡ የሚታየው ፡ ጦርነት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሕሊናው ፡ አይወቅሰውም ፡ ሰላም ፡ እንዲጠበቅ ፡ የተቻለውን ፡ ሁሉ ፡ አድርጓል ።

ኢትዮጵያ ፡ በሌሎች ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ይኑረኝ ፡ የማለት ፡ ሐሳብ ፡ የላትም ፡ በግዛቷ ፡ ውስጥ ፡ ባለቤት ፡ ሆና ፡ ሥልጣኗና ፡ ወሰኗ ፡ ሳይደፈር ፡ ለነፃነቷ ፡ ስትል ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ሰው ፡ ድረስ ፡ ለመከላከል ፡ የተዘጋጀች ፡ ነች ።

ተጋፊ ፡ የሆነው ፡ የኢጣሊያ ፡ ሕዝብ ፡ ዘመኑ ፡ ያመጣውን ፡ ያጥቂነት ፡ መሣሪያ ፡ ይዞ ፡ ሥልጣኔ ፡ ላስተምራችሁ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሲመጣ ፡ ለንጉሡ ፡ ነገሥቱና ፡ ላገሩ ፡ ለመሞት ፡ የተዘጋጀ ፡ አንድነት ፡ ያደረበት ፡ ሕዝብ ፡ ተሰልፎ ፡ ይጠብቀዋል ።

ወታደር ፡ ሆይ ፡ በጦርነት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ የተከበረና ፡ የተወደደ ፡ አለቃ ፡ ለነፃነታችን ፡ ብሎ ፡ ሞተ ፡ ሲባል ፡ አትዘን ፡ ተስፋ ፡ አትቍረጥ ። ላገሩ ፡ የሚሞት ፡ ሁሉ ፡ ዕድለኛ ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ተመልከት ፡ እንጂ ፡ ሞት ፡ ሳያማርጥ ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ፡ በጦርነት ፡ የፈቀደውን ፡ ይወስዳል ። ያለነፃነት ፡ ከመሞት ፡ ነፃነትን ፡ ይዞ ፡ መሞት ፡ ይሻላል ።

አባቶቻችን ፡ አገራችንን ፡ በነፃነት ፡ ያቈዩልን ፡ ሕይወታቸውን ፡ እየሠዉ ፡ ነው ፡ እነሱ ፡ አብነት ፡ ይሁኗችሁ ።

ወታደር ፥ ነጋዴ ፥ ገበሬ ፥ ልጅም ፥ ሽማግሌም ፥ ወንድም ፥ ሴትም ፡ አንድነት ፡ ይደርባችሁ ። እየተረዳዳችሁ ፡ ላገራችሁ ፡ ተከላከሉ ። እንደ ፡ ጥንት ፡ ጊዜ ፡ ልማድ ፡ ሴቶችም ፡ ወታደሩን ፡ በማደፋፈር ፡ ቍስለኛ ፡ በማስታመም ፡ ላገራቸው ፡ ይከላከሉ ። እርስ ፡ በርሳችን ፡ እንድንለያይ ፡ ምንም ፡ ኢጣሊያ ፡ የተቻላትን ፡ ሁሉ ፡ ብታደርግ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እስላም ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ይመከታል ።

ምሽጋችንና ፡ ጋሻችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። የአጥቂዎቻችን ፡ አዲስ ፡ መሣሪያ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ከመካከላችሁ ፡ ከተቀደሰ ፡ ሐሳባችሁ ፡ አያዘነብላችሁም ።

ዛሬ ፡ የሚናገራችሁ ፡ ንጉሣችሁ ፡ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ በመካከላችሁ ፡ ይገኛል ። ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ደሙን ፡ ለማፍሰስ ፡ ተዘጋጅቷል ።

ሳንጨርስ ፡ ዳግመኛ ፡ አንድ ፡ የምንነግራችሁ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ ለሰላም ፡ አጥብቀን ፡ መጣጣራችን ፡ ነው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ለሰላም ፡ መድከሙን ፡ እናሳስባችኋለን ። በዲፕሎማቲክም ፡ መንገድ ፡ ሰላማዊ ፡ የሆነና ፡ ለሁለታችንም ፡ ክብር ፡ ያለበት ፡ የመስማሚያ ፡ መንገድ ፡ መፈለጉን ፡ አላቋረጠም ። ኢጣሊያ ፡ በፈቃዱ ፡ የፈረመውን ፡ የወዳጅነትና ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ውል ፡ እንዲያከብር ፡ እንዲያደርግ ፡ የመንግሥታትን ፡ ማኅበር ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ጠይቋል ።

ደግሞ ፡ ጦርነት ፡ በፍጹም ፡ እንዲቀር ፡ ተብሎ ፡ የቀረበውን ፡ ውል ፡ ኢትዮጵያም ፡ ኢጣሊያም ፡ ከሌሎች ፡ መንግሥቶች ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ፈረሙ ፡ የውሉም ፡ መሥራች ፡ አሜሪካ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ለአሜሪካን ፡ መንግሥት ፡ አስታውቀናል ።

ደግሞ ፡ አሁን ፡ ሆላንድ ፡ ነገር ፡ የሁለታችንም ፡ ጨዋዎች ፡ ክርክራችንን ፡ ሲመረምሩ ፡ የኢጣሊያ ፡ ጨዋዎች ፡ ስላስቸገሩ ፡ ፓሪስ ፡ ያለው ፡ ሚኒስትራችን ፡ 3 ፡ ጊዜ ፡ ለመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ እንዲያመለክት ፡ አዘነዋል ።

እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ሰላም ፡ እንዲሆን ፡ እንጣጣራለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ድካማችንና ፡ መልካም ፡ አሳባችን ፡ ፍሬ ፡ ያገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሕሊናችን ፡ አይወቅሰንም ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በእምነት ፡ ተባብሮ ፡ ላገራችን ፡ ነፃነት ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ለመከላከል ፡ እግዚአብሔር ፡ ያርበኞቻችንን ፡ ኀይል ፡ እንዲያጸና ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይዘረጋል ።

# ምዕራፍ ፡ 63 ።

## የጦር ፡ ወታደር ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ እንደ ፡ ተሰበሰበ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ለመኳንንቱና ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ የሰጡት ፡ ምክር ።

ካ1927 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኅዳር ፡ ከተደረገው ፡ ከወልወል ፡ ግጭት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ዤኔብ ፡ የተቀመጡት ፡ ማኅበረተኞች ፡ ሁለቱን ፡ ጠበኞች ፡ መንግሥታት ፡ ለማስታረቅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፈተኑ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ የሚያቀርቡትን ፡ ዕርቅ ፡ እየተቀበለ ፡ ገላጋዮቹን ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ መላዋን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ያሠልጥን ፡ ብላችሁ ፡ ካልፈቀዳችሁልኝ ፡ በቀር ፡ ሌላውን ፡ ዕርቅ ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ የነሱንም ፡ የመጨረሻ ፡ አሳብ ፡ ሳይጠብቅ ፡ ጦርነቱን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዐድዋ ፡ ድረስ ፡ መጣ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በውጭ ፡ ኣገር ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ በያገሪ ፡ ገዥውና ፡ በያለቃው ፡ እየተሰለፈ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ እንዲመጣ ፡ ትእዛዝ ፡ አስተላልፈው ፡ ነበርና ፡ በጥቅምት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የከምባታ ፡ ጦር ፡ በደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ወልዴ ፡ መሪነት ፥ በጥቅምት ፡ 7 ፡ ቀን ፡ የደጃዝማች ፡ አውራሪስ ፡ ጦር ፥ በጥቅምት ፡ 30 ፡ ቀን ፡ የደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በእንደራሴያቸው ፡ በፊታውራሪ ፡ ንጋቱ ፡ መሪነት ፥ ኅዳር ፡ 6 ፡ ቀን ፡ የክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ ደምሰው ፡ ጦር ፡ በራሳቸው ፡ መሪነት ፡ ዝግናው ፡ እየፎከረና ፡ እያቅራራ ፡ በየሻለቃውና ፡ በየሻምበሉ ፡ ተሰልፎ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ አለፈ ።

የክቡር ፡ ቢትወደድም ፡ ሰልፍ ፡ ከሌሎቹ ፡ የበለጠ ፡ ኣምሮ ፡ ይታይ ፡ ነበር ፡ ይኸውም ፡ የመዝመሪያ ፡ ወታደር ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ነጋሪቱ ፡ ውጋ ፡ ውጋ ፡ በሚል ፡ ድምፅ ፡ እየተመታ ፡ መድፍና ፡ መትረየሱ ፡ ተጭኖ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ዝግናው ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ ደምሰው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ሁለት ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማዎች ፡ አሲዘው ፡ በኤውሮፓ ፡ ዐይነት ፡ የተሰፋ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ የክብር ፡ ኒሻናቸውን ፡ አድርገው ፡ ሰይፋቸውን ፡ በግራ ፡ ጐናቸው ፡ አንግበው ፡ በድንጉላ ፡ ፈረስ ፡ ሆነው ፡ በሚያምርና ፡ በሚያስፈራ ፡ ግርማ ፡ ብቅ ፡ አሉ ። ወዲያው ፡ እድንጉላ ፡ ፈረሳቸው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ ሻምላቸውን ፡ መዘው ፡ «እኔ ፡ አሽከርሽ ፡ እኔ ፡ ባሪያሽ ፡ በመንግሥትሽ ፡ በመጣው ፡ ጠላት ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ የተቻለኝን ፡ እሠራለሁ ። ይኸውም ፡ ቀን ፡ ለኔ ፡ ሠርጌ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሞቴ ፡ አልለውም» ፡ ብለው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ ፎከሩ ።

የኮንታ ፡ ጦር ፡ በደጃች ፡ በየነ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ መሪነት ፡ ሲገባ ፡ ዥግናው ፡ ደጃች ፡ በየነ ፡ በሠጋር ፡ በቅሏቸው ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተንቈራጠጡ ፡ እኔ ፡ የኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አሽከር ፡ ለውድ ፡ አገሬ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መሞት ፡ ትልቅ ፡ ክብሬ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ፎከሩ።

እንዲሁም ፡ የጐሬ ፡ ጦር ፡ በደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ መሪነት ፥ የከፋ ፡ ጦር ፡ በራስ ፡ ጌታቸውና ፡ በደጃዝማች ፡ ደበበ ፡ አንዳርጋቸው ፡ መሪነት ፥ የወለጋ ፡ ጦር ፡ በደጃዝማች ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሪነት ፡ እየተሰለፈ ፡ ከገባ ፡ ወዲህ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ እንደዚሁ ፡ ሰልፋቸውን ፡ አሳይተው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩና ፡ ሌሎቹ ፡ መኳንንቶች ፡ ከጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ጋራ ፡ በተሰበሰቡበት ፡ አደባባይ ፡ ምክር ፡ ጭምር ፡ ያለበትን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ተናግረው ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ አሰናበቷቸው

«ላገርኽ ፡ ነፃነትና ፡ እኛ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥትኽ ፡ ክብር ፡ ደምኽን ፡ ለማፍሰስ ፡ ቈርጠኽ ፡ መነሣትኽን ፡ ማየታችን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ።

ጌታ ፡ ገንዘቡን ፡ የሚያስጠብቀው ፡ ላመነው ፡ አሽከሩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አንተም ፡ እምነትኽን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ አድርገኽ ፡ የጦር ፡ ሠራዊታችንን ፡ እየጠበቅኽ ፡ በማንኛውም ፡ ችግራቸውን ፡ ሁሉ ፡ እየረዳኽ ፡ ለጠላት ፡ እንድትመክት ፡ አዘንኻል ።

አሁንም ፡ የመጣብን ፡ ጠላት ፡ ደም ፡ የተቃባነው ፡ ከጥንት ፡ የቈየ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አዲስ ፡ ድንገተኛ ፡ ጠላት ፡ አይደለም ፡ ሰላም ፡ ፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የመንግሥታትን ፡ ማኅበር ፡ ኣምነን ፡ ጦራችንን ፡ ወደ ፡ ግንባር ፡ ባለማስቀደማችን ፡ አሁን ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ በጭካኔ ፡ ከመግደል ፡ በቀር ፡ እንኳን ፡ ለወታደር፡ለሽማግሌ ፡ ለሴት ፡ ለሕፃንም ፡ ይራራል ፡ ተብሎ ፡ አይጠረጠርም ። ለሴቶችና ፡ ለሕፃናትም ፡ አለመራራቱን ፡ ባዝማመሩ ፡ ሰምተነዋል ።

በማንኛውም ፡ ቢሆን ፡ ሞት ፡ አይቀርምና፡ እገሌ ፡ በሳልና ፡ በጉንፋን ፡ በተስቦ ፡ ሞተ ፡ ከመባል ፡ ላገሩ ፡ ነፃነት ፡ ለንጉሡ ፡ ክብር ፡ ለትውልድ ፡ ስም ፡ ደሙን ፡ አፍሶ ፡ ሞተ ፡ መባል ፡ ትልቅ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባም ። በጦርነት ፡ ላይ ፡ አንዱ ፡ ቢሞት ፡ ተራውን ፡ ተወጣ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ እገሌ ፡ ሞቷል ፡ ብሎ ፡ መደናገጥ ፡ የዠግንነትን ፡ ክብር ፡ የሚያዋርድመሆኑን ፡ ማወቅ ፡ ነው ።

ለወታደርም ፥ ለባላገርም ፥ ለነጋዴም ፡ ቢሆን ፡ ትልቁ ፡ ኵራቱ ፡ ያገሩ ፡ ነፃነት ፡ መሆኑ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ከመካከላችሁ ፡ ጠብና ፡ ተንኰል ፡ እንዲጠፋ ፡ ፍቅርና ፡ አንድነት ፡ እንዲሰፋ ፡ ሎሌ ፡ ለጌታው ፡ ጭፍራ ፡ ላለቃው ፡ መታዘዝን ፡ እንዲያውቅ ፡ በሚቻላችሁ ፡ ሁሉ ፡ ማስረዳት ፡ ነው ። ኢጣሊያኖች ፡ በመሣሪያቸው ፡ ቢኰሩብን ፡ እኛም ፡ ትልቁ ፡ መሣሪያችን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ርዳታ ፡ በመሆኑ ፡ እንኰራባቸዋለን ።

ቀይና ፡ ብጫ ፡ አረንጓዴ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማችን ፡ ሞዐ ፡ አንበሳ ፡ የሚለው ፡ ማኅተማችን ፡ የነፃነታችን ፡ ምልክት ፡ ነውና ፡ ይህ ፡ የነፃነታችን ፡ ምልክት ፡ እንዳይጠፋ ፡ እስከ ፡ መጨረሻዋ ፡ ጠብታ ፡ ደማችንን ፡ እያፈሰስን ፡ ብንሞትም ፡ ለስማችንና ፡ ለታሪካችን ፡ ትልቅ ፡ ክብር ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ስላችሁ ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ዐይነት ፡ ጦርነት ፡ እየተዋጋችሁ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከጠላት ፡ እጅ ፡ ለማዳን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባለመጠባበቅና ፡ በንዴት ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ራት ፡ በጦርነት ፡ ውስጥ ፡ እየገባችሁ ፡ በመሞት ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጠላት ፡ የተመቸ ፡ ይሆናል ።

የምታደርጉትም ፡ ጥንቃቄ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

1ኛ፡- ድንኳን ፡ ስትተክሉ ፡ በየሻምበሉ ፡ እየተለየ ፡ ስፍራ ፡ ቢያጋጥም ፡ በጐድጓዳና ፡ በዛፍ ፡ በዱር ፡ ውስጥ ፡ መትከል ፡ ነው ። አተካከሉም ፡ ካንዱ ፡ ድንኳን ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ እንዲራራቅ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

2ኛ፡- አይሮፕላን ፡ ሲበር ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ ገላጣውንና ፡ ትልቁን ፡ መንገድ ፡ ሰፊውንም ፡ ሜዳ ፡ ትቶ ፡ በዘብጥና ፡ በጐድጓዳ ፡ በዘወርዋራ ፡ መንገድ ፡ ዛፍና ፡ ዱር ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ መጓዝ ፡ ነው ።

3ኛ፡- አይሮፕላን ፡ ቦምብ ፡ ለመጣል ፡ ሲመጣ ፡ 3 ፡ ሜትር ፡ ያኸል ፡ ዝቅ ፡ ካላለ ፡ አይመቸውምና ፡ ለዚሁ ፡ ሥራው ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በመልካም ፡ በረዣዥም ፡ ጠመንዣ ፡ እሮምታ ፡ ተኵሶ ፡ በፍጥነት ፡ መበታተን ፡ ነው ። 3 ፡ ወይም ፡ አራት ፡ ጥይት ፡ ከመታው ፡ አይሮፕላኑ ፡ መውደቁ ፡ አይቀርም ፡ ለዚህ ፡ ተኵስ ፡ የተመረጠውን ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ ለመተኰስ ፡ የታዘዙት ፡ ብቻ ፡ ይተኵሱ ፡ እንጂ ፡ ጠመንዣ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ቢተኵስ ፡ ጥይት ፡ ከማባከንና ፡ ያሉበትን ፡ ስፍራ ፡ ከማሳየት ፡ በስተቀር ፡ ጥቅም ፡ የለውም ።

4ኛ፡- አይሮፕላኑ ፡ ገና ፡ ብቅ ፡ ሲል ፡ የተበታተናችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የምትበታተኑበትን ፡ አቅጣጫ ፡ እንዳያየው ፡ ጥቂት ፡ ቀረብ ፡ እስኪል ፡ ቈይቶ ፡ መበታተን ፡ ነው ። ጦርነት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ጣፋ ፡ ጋሻ ፡ ጒሜ ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ለምድ ፡ ግምጃ ፡ ቀሚስ ፡ ይህንን ፡ የመሳሰለ ፡ ሁሉ ፡ ለጠላት ፡ ጠመንዣ ፡ ማነጣጠር ፡ ይመቻልና ፡ ኮት ፡ ያለው ፡ ኮቱን ፡ የሌለው ፡ ያደፈ ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ ብቻ ፡ መልበስ ፡ ነው ። ይህም ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ሽማልታችሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ ረድቶን ፡ ስንመለስ ፡ ታደርጉታላችሁ፡ አሁን ፡ እየተዋችሁ ፡ መሄድ ፡ ነው ። ይህንም ፡ ሁሉ ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ ማስታወቃችን ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ ትልቅ ፡ ጒዳት ፡ እንዳያገኛችሁ ፡ ብለን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሐምሌ ፡ 11 ፡ ቀን ፡ በተናገርነው ፡ ዲስኩር ፡ እንዳስረዳናችሁ ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ በመካከላችሁ ፡ ሆነን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ደማችንን ፡ ለማፍሰስ ፡ የተዘጋጀን ፡ መሆናችንን ፡ ስናረጋግጥላችሁ ፡ ደስ ፡ ይለናል» ፡ በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ግጥም ፡ ከናቶ ፡ ተሰማ ፡ እሸቴ ፥ ከናለቃ ፡ መርሻ ፡ ተገጠመ ።

ተፈታትኖት ፡ ነበር ፡ ቀድሞም ፡ ኣባትኸን ፡
እንደ ፡ ምንም ፡ ታግለኸ ፡ ጣል ፡ ያን ፡ ጠላትኸን ።

አባት ፡ ያቈየንን ፡ አድርጎ ፡ እጅ ፡ ከፍንጅ ፡
ዋቢ ፡ አናሳልፍም ፡ እኛው ፡ እንፍጅ ፡ እንጅ ።

ፍርድን ፡ ለማግኘት ፡ ነው ፡ በዳኛ ፡ መግጠም ፡
ዋቢ ፡ አናሳልፍም ፡ ሳንፈጣጠም ።

የሽማግሌን ፡ ዕርቅ ፡ እሱ ፡ ከጠላው ፡
በካሳ ፡ አስፈጥመን ፡ ሥዩም ፡ አሰኘው ፡

በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የማያምን ፡ ሰው ፡
አጋሜን ፡ አጥሬ ፡ ልጠባበቀው ።

ይመችኻልና ፡ ለመሥራት ፡ ሰርዲን ፡
ዓሣ ፡ ባሣ ፡ እንድትሆን ፡ ጣል ፡ ያን ፡ መረብኸን ።

ኢጣሊያ ፡ ሥዩምን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ጠላው ፡
መረቡን ፡ አስጥሎ ፡ ዓሣ ፡ ባበላው ።

ታውቀዋለኸና ፡ ሥዩም ፡ መልካውን ፡
መረባርብ ፡ ጥለኸ ፡ ተሻግረኸ ፡ ቈየን ።

ብችልኸ ፡ ብችልኸ ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡
ከመቼ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ መስፈርኸ ፡ እንደርታ ፡
እውነት ፡ መሰለኸ ፡ ወይ ፡ አንት ፡ ደፋር ፡ ወስላታ ፡
አያሌ ፡ ሰው ፡ አለኝ ፡ አንተን ፡ የሚመታ ።

ኣንተን ፡ ሽሬ ፡ ሽሬ ፡ ደግሞ ፡ ባንተ ፡ ፈንታ ፡
እንዳንት ፡ ያልጐደለ ፡ ይግባ ፡ ሙሉጌታ ፡
አባ ፡ ይርጋ ፡ ሥዩም ፡ ባባ ፡ ነጋ ፡ ቦታ ።

አወይ ፡ መቀናጣት ፡ መቀሌ ፡ መድረስ ፡
ጋልያኖን ፡ ጠይቀው ፡ እንዳ ፡ ኢየሱስ ፡
እየተጨነቀ ፡ እንባውን ፡ ሲያፈስ ፡
ሜዳውን ፡ ሲያጠልቀው ፡ የዳኛው ፡ ፈረስ ፡
ያ ፡ ቃኘው ፡ መኰንን ፡ ኰረብታ ፡ ሲያፈርስ ፡
ያ ፡ ይትረፍ ፡ ኣባተ ፡ መድፍ ፡ ሲተኵስ ፡
አባ ፡ ነፍሶ ፡ ባልቻ ፡ ይዞ ፡ መትረየስ ፡
እየነዱ ፡ ወስደው ፡ እንኪጨው ፡ ድረስ ፡
ከዘመዱ ፡ ጋራ ፡ ሲቈሉት ፡ በርሳስ ።

አይዟችሁ ፡ ጋሞቼ ፡ አርበኞች ፡ አይዟችሁ
ለሥንቅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሳብ ፡ አይግባችሁ ።
የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሆኗል ፡ እራታችሁ ፡
ጧት ፡ ማታ ፡ ያቀርባል ፡ ግርማዊ ፡ ኣባታችሁ ፡
ለውጊያውስ ፡ እኔም ፡ አልጠረጥራችሁ ።

እግዚአብሔር ፡ መዝኖ ፡ የሰጠው ፡ ለሕዝቡ ፡
የተቀባ ፡ ንጉሥ ፡ ወዬው ፡ መለዘቡ ፡
ሕዝቡን ፡ ለማዳን ፡ ነው ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ አሳቡ፡

ከጥበበኞችም ፡ ይበልጣል ፡ ጥበቡ ።

እንዲህ ፡ አርጎ ፡ መቻል ፡ አዬ ፡ መታገሥ ፡
ቶሎ ፡ እማይቈጣ ፡ የሕፃን ፡ ንጉሥ ።

ያኑርልን ፡ እንጂ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
እንበለው ፡ በለው ፡ በሠንጋ ፡ ፈረስ ፡
ቈይተው ፡ ቢሆን ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡
ምድር ፡ ባዶ ፡ ሆኖ ፡ ሰማይ ፡ ሲታረስ ።

የዘመኑን ፡ ነገር ፡ መላውን ፡ ሳያውቁ ፡
እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ዠግና ፡ ሁሉ ፡ በታነቁ፡
የኛማ ፡ ግርማዊ ፡ ታላቁ ፡ ታላቁ ፡
ያለም ፡ ጌታ ፡ ሆነው ፡ ዓለምን ፡ የናቁ ፡
ሌት ፡ እንደ ፡ ታጠቁ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ታጠቁ ፡
ከረቂቆች ፡ ጋራ ፡ እየተራቀቁ ፡
ከኀይለኞችም ፡ ጋር ፡ እየተናነቁ ፡
ሰማይ ፡ ያፈራውን ፡ በምድር ፡ እየውቁ ፡
ይመጋግቡናል ፡ ወይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድንቁ ።



## ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በኋላ ፡ በንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመን ፡ ንጉሥ ፡ የተባሉት ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ወደ ፡ ጦሩ ፡ ግንባር ፡ ካሰናበቱ ፡ በኋላ ፡ በኅዳር ፡ 18 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጦርነቱ ፡ መካከል ፡ ለመገኘት ፡ በሚያምር ፡ ግርማ ፡ ታጅበው ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ባ4 ፡ ሰዓት ፡ ተነሥተው ፡ ዋና ፡ የጦር ፡ መሳፈሪያ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ደሴ ፡ ሄደው ፡ በኅዳር ፡ 20 ፡ ቀን ፡ ባ1 ፡ ሰዓት ፡ ገቡ ።

ሌላው ፡ ዘማች ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ ተከትለዋቸው ፡ የነበሩትም ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፥ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፥ ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አባይነኸ ፥ ደጃዝማች ፡ ወንድ ፡ ይራድ ፥ ደጃዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ ናቸው ።

ግርማዊነታቸውም ፡ ደሴ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ አይሮፕላኖች ፡ መጥተው ፡ ከነዋሪው ፡ ሕዝብ ፡ ውስጥ ፡ ሲጐዱ ፡ የቀይ ፡ መስቀሉንም ፡ አብረው ፡ መቱት ።

ከውጭ ፡ አገርም ፡ ተልከው ፡ በቀይ ፡ መስቀል ፡ ውስጥ ፡ መጥተው ፡ በየጦሩ ፡ ሰፈር ፡ ለሕክምና ፡ የሄዱት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ።

1. ፡ ከእንግሊዝ ፡
2. ፡ ከነምሳ ፡
3. ፡ ከሆላንድ ፡ በሰሜን ፡ ግንባር ፡
4. ፡ ከፈረንሳዊ ፡
5. ፡ ከግብጽ ፡ በሐረርና ፡ በጅጅጋ ፡
6. ፡ ከስዊድን ፡ የመጡት ፡ ከሁለት ፡ ተከፍለው ፡ በቦረናና ፡ በባሌ ።

ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ የገንዘብና ፡ የመድኀኒት ፡ ርዳታ ፡ አድርገዋል ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| የጀርመን ፡ | የቀይ ፡ | መስቀል ፡ | ማኅበር ፡ |
| የጃፓን ፡ | » | » | » |
| የኖርቤዥ ፡ | » | » | » |
| የአሜሪካን ፡ | » | » | » |
| የቼኮስሎቫኪያ | » | » | » |
| የኤስፓኝ ፡ | » | » | » |
| የቤልጅክ ፡ | » | » | » |

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ደሴ ፡ ሆነው ፡ ለሰሜንም ፡ ለደቡብም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መሣሪያና ፡ ማንኛውንም ፡ ጉዳይ ፡ ያዘጋጁ ፡ ነበር ። የጦር ፡ ሹማምንቶችንና ፡ ያገር ፡ ባላባቶችን ፡ እየተቀበሉ ፡ ሽልማት ፡ እየሸለሙ ፡ የጦሩን ፡ ፕላን ፡ ሲያቃኑ ፡ ሰነበቱ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከመቀሌ ፡ ከዐድዋ ፡ ከሺሬ ፡ ስለ ፡ ውጊያውና ፡ ስለ ፡ ሌላውም ፡ ጉዳይ ፡ ቴሌግራም ፡ የተማረከ ፡ መሣሪያና ፡ የኢጣሊያ ፡ ወታደርም ፡ በየቀኑ ፡ ይመጣላቸው ፡ ነበር ። ደግሞ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቦምብ ፡ የጫኑ ፡ አይሮፕላኖች ፡ እላይ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ እየመጡ ፡ በደሴ ፡ ሲጥሉ ፡ ሰነበቱ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንንና ፡ የቀይ ፡ መስቀልን ፡ ከመጉዳት ፡ በቀር ፡ በወታደርና ፡ በመሣሪያ ፡ ላይ ፡ የከበደ ፡ ጥፋት ፡ አላደረጉም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የራስ ፡ ደምስና ፡ የራስ ፡ ኀይሉ ፡ አሽከር ፡ የነበረው ፡ ደጃች ፡ ገሠሠ ፡ በለው ፡ የሚባለው ፡ መዠመሪያ ፡ ላገሬ ፡ እሞታለሁ ፡ ብሎ ፡ የከቡር ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ዘምቶ ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የኢጣሊያኖችን ፡ አይሮፕላኖች ፡ ሲያይ ፡ ፈርቶ ፡ አገሩን ፡ ከድቶ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ዐዋጅ ፡ ጥሶ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ መመለሱ ፡ ተሰማ ፡ ስለዚህ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ እነግራዝማች ፡ ሣህሌ ፡ እንዲወጉት ፡ ከታዘዙ ፡ በኋላ ፡ ደግሞም ፡ ለጐጃም ፡ ሕዝብ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ዐዋጅ ፡ ተላለፈ ።

«ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

የጐጃም ፡ ሰው ፡ ከርስትኽ ፡ የሚነቅል ፡ ሚስትኽንና ፡ ሴት ፡ ልጅሽን ፡ በኀይል ፡ እየወሰደ ፡ የሚያረክስ ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ ሃይማኖትኽን ፡ የሚለውጥ ፡ ኢጣሊያን ፡ ያኽል ፡ ጨካኝ ፡ ጠላት ፡ መጥቶ ፡ ሳለ ፡ ስላገርኽ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነፃነትና ፡ ስለ ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ ሃይማኖት ፡ ደምኽን ፡ ከማፍሰስ ፡ በቀር ፡ ትከዳኛለኽ ፡ ብዬ ፡ አልጠረጥርም ። ነገር ፡ ግን ፡ ደጃች ፡ ገሠሠ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታምራት ፡ ፊታውራሪ ፡ ገሠሠ ፡ ንጉሤ ፡ ፊታውራሪ ፡ ዘለቀ ፡ ካሳ ፡ ፊታውራሪ ፡ ዘለቀ ፡ ወሌ ፡ ቀኛዝማች ፡ አየለ ፡ ኀይሉ ፡ ቀኛዝማች ፡ መርድ ፡ ዋሴ ፡ ቀኛዝማች ፡ ዘለቀ ፡ አሥጌ ፡ አገራቸውን ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸውን ፡ እኔን ፡ ከድተው ፡ ከዘመቻ ፡ መመለሳቸው ፡ እንክርዳድ ፡ በስንዴ ፡ መካከል ፡ እንደሚበቅል ፡ ያኽል ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ለጊዜው ፡ ያገርኽን ፡ የጐጃምን ፡ ስም ፡ ለማጥፋት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላውን ፡ ይቅርና ፡ ራሳቸውንም ፡ ለማዳን ፡ እንዳይችሉ ፡ ታውቀዋለኽ ።

እነደጃች ፡ ገሠሠንና ፡ እነፊታውራሪ ፡ ታምራትን ፡ ተከትለኽ ፡ ከዘመቻው ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ የተመለስኽ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጥፋቱ ፡ ባለቆችኽ ፡ በይሁዳዎቹ ፡ ላይ ፡ ነውና ፡ ባለፈው ፡ ምሬኻለሁ። ነገር ፡ ግን ፡ የኛን ፡ ዐዋጅ ፡ ጥሰው ፡ የጳጳሱን ፡ ውግዘት ፡ አፍርሰው ፡ አገራቸውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከደው ፡ መሪ ፡ ሆነው ፡ ከዘመቻ ፡ የመለሱኽን ፡ እነዚህን ፡ ጠላቶቼን ፡ በሄዱበት ፡ ስፍራ ፡ እየተከታተልኽ ፡ ያዝልኝ ። ይህን ፡ ዐዋጅ ፡ ከሰማኽ ፡ በኋላ ፡ ወታደር ፡ በወታደርነትኽ ፡ እነዚህን ፡ ጠላቶቼን ፡ ተከትለን ፡ ስትወሳልት ፡ ባላገርም ፡ ለኛ ፡ ሳትረዳ ፡ ቀርተኽ ፡ በቤትኽ

፡ አሳድረኽ ፡ እኽልና ፡ ውሃ ፡ ሰጥተኽ ፡ የተገኘኽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምሕረት ፡ የሌለው ፡ ቅጣት ፡ እቀጣኻለሁ ፡፡ »

ታኅሣሥ ፡ 17 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንደዚሁ ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ በመንፈሳዊ ፡ አባትነታቸው ፡ አገሩን ፡ የከዳውን ፡ ገሠሠንና ፡ ተከታዮቹን ፡ የተከተለ ፡ የአርዮስ ፡ ርግማን ፡ ትድረስበት ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ጽፈው ፡ ለጐጃም ፡ ሕዝብ ፡ ላኩ ፡፡ በኋላም ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ጦር ፡ ተልኮ ፡ ከደጃች ፡ ገሠሠ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ እነግራዝማች ፡ ሣህሌ ፡ ሞቱ ፡ እሱም ፡ በሚያውቀው ፡ አገር ፡ እየተባረረ ፡ ሲባዝን ፡ ከርሞ ፡ እስከ ፡ ኢጣሊያ ፡ መምጣት ፡ ቈይቶ ፡ በኋላ ፡ ሞተ ፡፡

እንደዚሁ ፡ ኀይለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ የሚባል ፡ 28 ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ሰርቆ ፡ እንዲከፍል ፡ ተፈርዶበት ፡ ነበርና ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ሲላላክ ፡ ተገኝቶ ፡ በቃሉም ፡ ስላመነ ፡ ተሰቀለ ፡፡

# ምዕራፍ ፡ 64 ፡፡

የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ መላክተኛ ፡ ሙሴ ፡ ሳሙኤል ፡ ሆዋር ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ መላክተኛ ፡ ሙሴ ፡ ላባል ፡ ያቀረቡት ፡ የዕርቅ ፡ ሐሳብ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ የሚነኩት ፡ ያ12ቱና ፡ ያ13ቱ ፡ ያ15ቱ ፡ ያ16ቱ ፡ አንቀጾች ፡ ንግግር፡ ማኅበሩ ፡ ኢጣሊያን ፡ ባጥቂነት ፡ ፈርዶ ፡ ያደረገባት ፡ ጭቈና ፡፡

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ የኢጣሊያንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ መርምረው ፡ እንዲያስታርቁ ፡ የተመደቡት ፡ አምስቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በወልወል ፡ ግጭት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በደለኛ ፡ አድርጎ ፡ የነበረውን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በዚህ ፡ ግጭት ፡ ምንም ፡ በደል ፡ እንደሌለባት ፡ ለማኅበሩ ፡ ኣስታውቀዋል፡፡ ቀጥሎ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባሠልጣኝነት ፡ ስም ፡ ለማግኘት ፡ ግረየፍስ» ፡ የተባለውን ፡ የክስ ፡ ማስታወሻ ፡ ለገላጋዮቹ ፡ አቀረበ ፡፡ የክሱም ፡ ቃል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውል ፡ አፍራሽ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ በውስጧም ፡ ሽፍትነት ፡ ዘረፋ ፡ የባሪያ ፡ አገዛዝ ፡ እንዳለ ፡ የሚናገር ፡ ነበር ፡፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ በፍጹም ፡ ያልተደረገ ፡ ነገር ፡ እነባሮን ፡ ፍራንኬቲና ፡ ሌሎችም ፡ ቆንሲሎችና ፡ ሚሲዮኖች ፡ ከኢትዮጵያ ፡ እየሰለሉ ፡ ሰብስበው ፡ የወሰዱት ፡ ክስ ፡ ነበር ፡፡ የዚህም ፡ ክስ ፡ መደምደሚያው ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደዚህ ፡ ያለች ፡ ከሆነች ፡ እኔ ፡ አሠለጥናት ፡ ዘንድ ፡ ይገባኛል ፡ የሚል ፡ ነበር ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚ ፡ ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ፡ ጠበቃ ፡ ይዘው ፡ የክሱ ፡ ቃል ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ በውነተኛ ፡ መልስ ፡ ካስተባበሉ ፡ በኋላ ፡ ገላጋዮቹም

፡ ሲወራረስ ፡ የመጣ ፡ የጠላት ፡ መንግሥት ፡ ባሠልጣኝነት ፡ አንደኛውን ፡ መንግሥት ፡ ሊይዝ ፡ አይችልምና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ልትሠለጥን ፡ የሚገባው ፡ ማኅበሩ ፡ በሚልካቸው ፡ አማካሪዎችና ፡ በማኅበሩ ፡ ተመልካችነት ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ፈረዱ ።

ቀጥሎም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የቀረበውን ፡ የዕርቅ ፡ ሐሳብ ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ ጦርነት ፡ በመዠመሩ ፡ እንደ ፡ 16ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ቃል ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ውል ፡ አፍራሽ ፡ በመሆኑ ፡ በመዠመሪያ ፡ 5 ፡ ከዚያ ፡ 6 ፡ ቀጥሎም ፡ 13 ፡ አባል ፡ ሆነው ፡ የጭቈናውን ፡ ኣኳኋን ፡ በሚያዘጋጁበት ፡ ጊዜ ፡ እላይ ፡ የተባሉት ፡ ሙሴ ፡ ሆዋርና ፡ ሙሴ ፡ ላባል ፡ በዳይን ፡ የሚያኰራና ፡ ተበዳይን ፡ የሚያሳዝን ፡ የዕርቅ ፡ ሐሳብ ፡ እንደሚከተለው ፡ አቀረቡ።

« ኢትዮጵያ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ የአኩስምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ራሷ ፡ አስቀርታ ፡ በዐድዋ ፡ ምዕራብና ፡ ምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ግባ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገርና ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ከኢትዮጵያና ፡ ከኢጣሊያ ፡ ሱማሌ ፡ ወሰን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ቆራሔ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ግዛት ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ልትለቅ ።

በበኩሉ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የዐሰብን ፡ በርና ፡ በደቡብ ፡ በፈረንሳዊ ፡ ሱማሌ ፡ ሰሜን ፡ የሚገኘውን ፡ ስፍራ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሊለቅ ። ደግሞ ፡ በዚሁ ፡ በደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አዛዥነትና ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ በሚያደርጋቸው ፡ አማካሪዎች ፡ የሚተዳደር ፡ ሰፊ ፡ ስፍራ ፡ ለመስፋፊያ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ሊያገኝ» ።

የዚህም ፡ የዕርቅ ፡ ድርድር ፡ 1 ፡ ግልባጭ ፡ ታኅሣሥ ፡ 6 ፡ ቀን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ተልኮ ፡ የቀሩትም ፡ መንግሥታት ፡ ነገሩን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ግፍ ፡ ያለበት ፡ የዕርቅ ፡ ሐሳብ ፡ መሆኑን ፡ እየገለጹ ፡ እነዚህን ፡ ሁለት ፡ መላከተኞች ፡ መላው ፡ ዓለም ፡ ወቀሣቸው ። የኢትዮጵያ ፡ መንግሥትም ፡ የዚህን ፡ ሐሳብ ፡ በፍጹም ፡ አለመቀበሉን ፡ በታኅሣሥ ፡ 8 ፡ ቀን ፡ ኣስታወቀ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ ወዲያው ፡ ሙሴ ፡ ሆዋርን ፡ ከውጭ ፡ ጒዳይ ፡ ሚኒስትርነታቸው ፡ ሽሮ ፡ በርሳቸው ፡ እግር ፡ ሐቀኛና ፡ ትክክለኛ ፡ የሆኑትን ፡ ሙሴ ፡ አንቶኒ ፡ ኤደንን ፡ ሾመ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በማኅበሩ ፡ ውል ፡ ባ12ና ፡ ባ13 ፡ እንዲሁም ፡ ባ15ኛው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ አፍርሶ ፡ በጦርነት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በመግፋቱ ፡ ያ16ኛውን ፡ አንቀጽ ፡ ሕግ ፡ ተከትለው ፡ በኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ ጭቈና ፡ ለማድረግ ፡ ቀርጥ ፡ ሐሳብ ፡ አደረጉ ።

ያ12 ፡ ያ13 ፡ ያ15ቱ ፡ አንቀጽ ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ነው ።

« ማኅበረተኛ ፡ የሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ በመካከላቸው ፡ ጠብ ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ራሳቸው ፡ በስምምነት ፡ ይጨርሳሉ ። ሁለቱም ፡ ሳይስማሙ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁለቱ ፡

መንግሥታት ፡ ገላጋይ ፡ መርጠው ፡ ወይም ፡ ነገሩን ፡ ወዶ ፡ ዓለም ፡ ማኅበር ፡ አድርሰው ፡ ይታረቃሉ ።

ሽማግሌዎቹ ፡ ወይም ፡ ማኅበሩ ፡ የቀረበው ፡ ዕርቅ ፡ ተፈጽሞ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሳይሆን ፡ ከሁለት ፡ አንዳቸው ፡ ዘመቻ ፡ ሊያነሡ ፡ አይችሉም ።

ሁለቱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ጠባቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ወይም ፡ ማኅበሩ ፡ በመረጣቸው ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሳይታረቁ ፡ ቀርተው ፡ ጠብ ፡ የሚቀሰቅስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነገሩ ፡ ወደ ፡ ማኅበሩ ፡ ጉባኤ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይቀርባል ።

ማኅበሩም ፡ የሁለቱን ፡ ወገን ፡ ምክንያት ፡ መርምሮ ፡ በደለኛውን ፡ ይገልጻል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እስከ ፡ ተቻለው ፡ ድረስ ፡ ጠቡ ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ያደርጋል ። ይህንንም ፡ ሳይችል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያ16ኛውን ፡ አንቀጽ ፡ ቃል ፡ በደለኛ ፡ አድርጎ ፡ በፈረደበት ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ይፈጽምበታል» ።

## ያ16ኛው ፡ አንቀጽ ንግግር ።

« 1ዱ ፡ መንግሥት ፡ ባ12 ፡ ባ13 ፡ ባ15ኛው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፈውን ፡ ሕግ ፡ ተላልፎ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በሆነው ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ የዠመረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መላውን ፡ የዓለምን ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ እንደ ፡ ወጋ ፡ ያኸል ፡ ተቈጥሮ ፡ የማኅበሩን ፡ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እነዚህ ፡ መንግሥታት ፡ በንግድና ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበራቸውን ፡ ግንኙነት ፡ ያቋርጣሉ ። በገንዘብም ፡ በሌላውም ፡ አኳኋን ፡ ጭቈና ፡ ያደርጉበታል ። ወዲያውም ፡ የማኅበሩን ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ ከባሕርም ፡ ካየርም ፡ ከመሬትም ፡ የጦር ፡ ኀይላቸውን ፡ እንደየድርሻቸው ፡ አዋጥተው ፡ ባንድነት ፡ ጥፋተኛውን ፡ ለመውጋትና ፡ የማኅበሩን ፡ ሕግ ፡ ለማስከበር ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይረዳዳሉ» ።

በዚህ ፡ እላይ ፡ በተባለው ፡ መሠረት ፡ 12ቱ ፡ መንግሥታት ፡ ለጦርነትና ፡ ለኑሮ ፡ የሚረዳውን ፡ ማንኛውንም ብረታብረት ፡ ሸቀጥ ፡ ቤንዚን ፡ ይህንን ፡ የመሳሰለው ፡ በንግድም ፡ በሌላም ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ አገር ፡ እንዳይገባ ፡ ከሱም ፡ እንዳይገዙ ፡ የገንዘብም ፡ ብድር ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ የኢጣሊያ ፡ ዜጋ ፡ ለሆነ ፡ እንዳይሰጥ ፡ ወሰኑ ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ የኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ በወታደርነትም ፡ አኳኋን ፡ የጦርነት ፡ እርምጃ ፡ ውን ፡ ለማገድ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ በሜዲቴራኒ ፡ ላይ ፡ ይንሳፈፉ ፡ ነበር ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ 1ኛ ፡ ሚኒስትር ፡ የሥጋ ፡ ልደት ፡ የደም ፡ ጥልቀት ፡ ያላቸውን ፡ መንግሥታት ፡ ወይም ፡ በዓለም ፡ ከተደረገው ፡ ጦርነት ፡ እንዳጋጣሚ ፡ የጦር ፡

ጓድ ፡ ሆኖ ፡ የረዳቸውን ፡ እያስታወሰ ፡ ላንድ ፡ የአፍሪካ ፡ መንግሥት ፡ ስትሉ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ጭቄና ፡ ታደርጉብኛላችሁ ፡ እያለ ፡ ዛቻ ፡ ጭምር ፡ ያባብላቸው ፡ ነበር ።

ይልቁንም ፡ ከፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ በላቲንነት ፡ ያለውን ፡ ዝምድና ፡ እየገለጸ ፡ ደግሞም ፡ ለፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ምክንያት ፡ በቢሊኝ ፡ የሞቱትን ፡ 6 ፡ ሺህ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ እየጠቀሰ ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ከጨቋኞቹ ፡ መንግሥታት ፡ እንዲለይለት ፡ ይጥር ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ላይ ፡ የላባል ፡ በግል ፡ በኩል ፡ ከሙሶሊኒ ፡ የተደረገው ፡ መመሳጠር ፡ ስለ ፡ ተጨመረ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በጠቅላላው ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ከማኅበሩ ፡ ቃል ፡ አልወጣም ፡ ሲል ፡ ቃል ፡ ቢሰጥ ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ ወገን ፡ አዘንብሎ ፡ ነበር ።

እንደዚሁ ፡ የነምሳ ፡ (የኦትሪሽ) ፡ መንግሥት ፡ መላከተኛ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ጋራ ፡ ከጥንት ፡ የቈየውን ፡ ጠላትነቱን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ አድርጎ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ጋር ፡ ከጥንት ፡ ተያይዞ ፡ በመጣው ፡ ወዳጅነታችን ፡ የተነሣ ፡ መንግሥቴ ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ጭቄና ፡ ማድረግን ፡ አይፈቅድም ፡ ሲል ፡ አስታወቀ ። እንደዚህም ፡ ብሎ ፡ ጠላትነቱን ፡ በወዳጅነት ፡ ለውጦ ፡ የዋሸበት ፡ ምክንያት ፡ ከላይ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ የነምሳን ፡ ግዛት ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ለመደረብ ፡ ያስብ ፡ ነበርና ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ይረዳኛል ፡ በማለት ፡ ተስፋ ፡ አድርጎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ጋራ ፡ ከወዳጅነታቸው ፡ ይልቅ ፡ በመቶ ፡ ዓመት ፡ በሚቈጠር ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ውጊያና ፡ ደም ፡ መፋሰስ ፡ እንደ ፡ ነበራቸው ፡ መላከተኛው ፡ ቢሳሳት ፡ ወይም ፡ ዐውቆ ፡ ቢዋሽ ፡ የሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ሊዋሽና ፡ ሊሳሳት ፡ አይችልም ።

ለዚያውም ፡ የሂትለር ፡ ጀርመን ፡ የነምሳን ፡ መንግሥት ፡ በቢየና ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ 400 ፡ አይሮፕላን ፡ በመሬት ፡ ቍጥር ፡ በሌላቸው ፡ ታንክ ፡ አስፈራርቶ ፡ ያለዘመቻ ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ መንግሥት ፡ በደባለቀ ፡ ጊዜ ፡ የቀሩት ፡ መንግሥታት ፡ ስለ ፡ ታላቁ ፡ የነምሳ ፡ መንግሥት ፡ መደረብ ፡ ሲያዝኑ ፡ ሙሶሊኒ ፡ አበጀሽ ፡ ብሎ ፡ ለሂትለር ፡ ፈቀደለት ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ምሳ ፡ ነጻነት ፡ አንዳች ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፡ የለም ።

የቀሩት ፡ መንግሥታትም ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሊመጣ ፡ እንጂ ፡ ሊቀር ፡ የማይቻለውን ፡ የዓለምን ፡ ጦርነት ፡ ቅስቃሴ ፡ በመፍራት ፡ ከተጠቂዋ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ አጥቂውን ፡ ኢጣሊያን ፡ ሊወጉ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሚያስገድዳቸው ፡ አንቀጽ ፡ ቢኖር ፡ እነሱ ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ አድርገው ፡ በገንዘብና ፡ በሌላው ፡ ረገድ ፡ ብቻ ፡ ኢጣሊያን ፡ ለማስቸገር ፡ አሰቡ ።

በመጨረሻም ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ለጦርነት ፡ የቀሩት ፡ መንግሥታት ፡ እንዳልተባበሩለት ፡ በተገነዘበው ፡ ጊዜ ፡ መርከቦቹን ፡ ከሜዲቴራኒ ፡ አስነሣ ። የኢጣሊያም ፡ ሕዝብ ፡ « አውታርኪያ ፡ ሁሉን ፡ ከራስ ፡ ማግኘት» ፡ የሚባለውን ፡ አቋሞ ፡ የኢጣሊያ ፡ ዘር ፡ ከሊቅ ፡ እስከ ፡ ደቂቅ ፡ ከንጉሥ ፡ እስከ ፡ ተራው ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ያለንን ፡ ንብረትና ፡

የጣት ፡ ቀለበታችንን ፡ ሳይቀር ፡ ሰጥተን ፡ የሚደረግብንን ፡ ጭቈና ፡ እናሸንፋለንና ፡ ጦርነቱን ፡ ቀጥል ፡ ብሎ ፡ ለሙሶሊኒ ፡ ጮኸለት ።

ሙሶሊኒም ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ ጕዳይ ፡ ፈጻሚ ፡ አድርጎት ፡ የነበረውን ፡ ሙሴ ፡ ባሮን ፡ አሎዋዚን ፡ ተዋቸውና ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ና ፡ የሚል ፡ ቴሌግራም ፡ አስተላልፎለት ፡ ነበርና ፡ ሙሴ ፡ አንቶኒ ፡ ኤደን ፡ የፕሬዚዴንትነቱ ፡ ተራ ፡ የርሳቸው ፡ በነበረት ፡ ቀን ፡ የሁለቱን ፡ መንግሥታት ፡ ጕዳይ ፡ ፈጻሚዎች ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ኣስቀምጠው ፡ የመጨረሻውን ፡ ፍርድ ፡ ለማሰማት ፡ ጠርተውት ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከኢትዮጵያዊው ፡ ጕዳይ ፡ ፈጻሚ ፡ ጋራ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ተቀምጬ ፡ አልነጋገርም ፡ ሲል ፡ ከተቀመጠበት ፡ ተነሥቶ ፡ በድፍረት ፡ ባርኔጣውንና ፡ ካቦርቱን ፡ ካስቀመጠበት ፡ ቦታ ፡ አንሥቶ ፡ የማኅበሩን ፡ ጉባኤ ፡ ረግጦ ፡ ወጣ ።


ሙሶሊኒም ፡ በአፍሪካ ፡ ጠረፍ ፡ ላለው ፡ ለዋናው ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ ጦርነቱን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዲቀጥል ፡ አዘዘው ።

ኢትዮጵያም ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ህሊና ፡ ፊት ፡ በዡኔብ ፡ ማኅበረተኞች ፡ አደባባይ ፡ በፖለቲካ ፡ ጦርነት ፡ ድል ፡ ካደረገች ፡ በኋላ ፡ ይህንን ፡ በስውር ፡ የተዘጋጀባትንና ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ለመዛትና ፡ ለማስፈራራት ፡ በቂ ፡ የሆነውን ፡ የዘመቻ ፡ ቀንበር ፡ ሌሎቹ ፡ ወደዚሁ ፡ ቀንበር ፡ እስኪጐተቱ ፡ ድረስ ፡ ብቻዋን ፡ ተሸከመች ።

# ምዕራፍ ፡ 65 ።

## የደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከዳት ።

ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጉግሳ ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ከልዑል ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ በመወለዱ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ከበሬታ ፡ አግኝቶ ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ አባቱ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ለምነው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ልጅ ፡ ልዕልት ፡ ዘነበ ፡ ወርቅን ፡ ለማግባት ፡ ችሎ ፡ ነበር ። በኋላም ፡ ልዕልት ፡ ዘነበ ፡ ወርቅ ፡ ካረፉ ፡ ወዲህ ፡ በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ ያገኘው ፡ ከበሬታ ፡ እንዳይጐድልበት ፡ ከማይለወጠው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አፍ ፡ ሰምቶ ፡ ነበር ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በሌሎች ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ፡ እየተባለ ፡ ሲፈረድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሰጡትን ፡ ተስፋ ፡ ይፈጽሙለት ፡ ዘንድ ፡ ያባቱን ፡ ግዛትና ፡ የመቀሌን ፡ ከተማ ፡ ጨምረው ፡ ሾሙት ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ ጋር ፡ በግዛትም ፡ በማዕርግ ፡ ስምም ፡



ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴና ፡ ጄኔራል ፡ ደቦኖ ።

ካልተካከልሁ ፡ ብሎ ፡ በሚያስብበት ፡ ሰዓት ፡ እኛ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ድል ፡ ብናደርግ ፡ ሙሉ ፡ የትግሬን ፡ ግዛት ፡ ከራስ ፡ ሥዩም ፡ ነጥቀን ፡ ላንተ ፡ እንሰጥኻለን ፡ ብለው ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ልከውበት ፡ ኖሮ ፡ ይህንኑ ፡ የጠላት ፡ ስብከት ፡ ተንተርሶ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ለመዞር ፡ የሚችልበትን ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ።

ይህንኑም ፡ የሰሙ ፡ ሰዎች ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ሳያመለክቱ ፡ አልቀሩም ። ነገር ፡ ግን ፡ ተርታ ፡ ሰው ፡ የማያደርገውን ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጉግሳ ፡ ተወልዶ ፡ ያደገባትን ፡ ማዕርግ ፡ ያየባትን ፡ እናቱን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከድቶ ፡ ያያት ፡ የቅድም ፡ አያት ፡ ጠላቶቹ ፡ ወደ ፡ ሆኑት ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ይገባል ፡ ብለው ፡ በፍጹም ፡ ስላልጠረጠሩ ፡ እንዲያዝ ፡ የመከሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሐሳብ ፡ ሳይከተሉ ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ለጦርነቱ ፡ የሚሆነውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያ ፡ ማዕርግ ፡ ያለው ፡ የጦርነት ፡ ልብስ ፡ ይልኩለት ፡ ነበር ። ርሱም ፡ ለዚሁ ፡

ምስጋና ፡ እየጨመረ ፡ ብዙ ፡ ደብዳቤ ፡ ይጽፍ ፡ ነበር ። ከነዚሁም ፡ ደብዳቤዎች ፡ ውስጥ ፡ 1ዱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ኣስቦ ፡ የላከልኝ ፡ የጦርነት ፡ ልብስ ፡ ደረሰልኝ። ስለዚህ ፡ ዐሥር ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ፡ እንደ ፡ መጣልኝም ፡ ወዲያው ፡ ለብሻለሁ ። የባርሜጣውም ፡ መለዮ ፡ መጥቶልኝ ፡ ለወደ ፡ ፊትም ፡ እንደዚሁ ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ የተዘጋጀሁ ፡ ነኝ ። መስከረም ፡ 16 ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡

ባሪያዎ ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጉግሳ ።

ይህንን ፡ በመሳሰለ ፡ ደብዳቤ ፡ ከወዲህ ፡ የሚደረግበትን ፡ ጥርጣሬ ፡ እያቀዘቀዘ ፡ ከወዲያ ፡ ደግሞ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ የደረሱበትን ፡ ስፍራ ፡ ሄዶ ፡ ለመደባለቅ ፡ ያሰልል ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ ኢጣሊያኖች ፡ የመረብን ፡ ጠረፍ ፡ ጥሰው ፡ ጦርነት ፡ አድርገው ፡ ዐድዋ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ለመያዝ ፡ ከሚያስቡት ፡ ካባቶቹ ፡ አሽከሮች ፡ አምልጦ ፡ ሌሊቱን ፡ ወደ ፡ ዕዳጋ ፡ ኀሙስ ፡ ሄዶ ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ተደባለቀ ። ወዲያውም ፡ ከጄኔራል ፡ ደቦኖ ፡ ተገናኝቶ ፡ ድሉ ፡ የሚከናወንበትንና ፡ መቀሌም ፡ የሚያዝበትን ፡ መንገድ ፡ ያመለከት ፡ ዠመር ።

የዚህም ፡ ወሬ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የፖለቲካ ፡ አካሄድ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ አጠፋ፡ ምክንያቱም ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኀጢአት ፡ በዝርዝር ፡ ጽፎ ፡ ለዓለም ፡ ማኅበር ፡ ካቀረባቸው ፡ አንቀጾች ፡ ውስጥ ፡ አንደኛው ፡ መኳንንቶቹ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ኣንድነት ፡ የላቸውም ፡የኔንም ፡ አሠልጣኝነት ፡ ይወዳሉ ፡ ብሎ ፡ ባቀረበው ፡ ምክንያት ፡ የምሥራቅ ፡ ትግሬ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የተወለደው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋብቻ ፡ የነበረው ፡ ይኸው ፡ በጦርነቱ ፡ የመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ወደኛ ፡ ገባ ፡ ሲሉ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ዘንድና ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ ፊት ፡ የኢጣሊያን ፡ ክስ ፡ ለማስተባበል ፡ በቆሙት ፡ መላክተኞቻችን ፡ ፊት ፡ የሚያሳፍር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ርግጥ ፡ ነው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሱ ፡ ከዳት ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ የሚያሳፍረው ፡ ለዚያ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅ ፡ ክርስቲያኑና ፡ ፈላሻው ፡ እስላሙና ፡ ሌላው ፡ ሕዝብ ፡ በጦርነቱም ፡ ከጦርነቱም ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ነፃነቱ ፡ ተጋድሎ ፡ ሲያደርግ ፡ የዮሐንስ ፡ ዘር ፡ ነኝ ፡ የሚለው ፡ እናቱን ፡ ከድቶ ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ጠላቶች ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ ርሱን ፡ ሲያሳፍረው ፡ ይኖራል ። አሁንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ መመለስ ፡ በሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ የደስታ ፡ ጭብጨባ ፡ ሲሰማ ፡ ሕይወቱ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ የገዛ ፡ ኅሊናውን ፡ በወቀሣ ፡ ጅራፍ ፡ ሲገርፈው ፡ ይኖራል ። ርሱም ፡ ቢያልፍ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ በደል ፡

ያልበደሉትን ፡ ተወላጆቹን ፡ ሲያሰቅቅበት ፡ የሚኖርና ፡ መድኀኒት ፡ ይገኝለታል ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ የማይደረግለትን ፡ ጥፋት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለዘለዓለም ፡ ኣጠፋ።

ሐሳቡ ፡ ግን ፡ እመቤቲቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኢጣሊያ ፡ ደንገጡር ፡ ሆና ፡ እሱም ፡ የደንገጡሪቱ ፡ ባል ፡ ለመሆን ፡ ይሆናል ። ይህንንም ፡ ተስፋ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሰንብቶ ፡ በደሴና ፡ በየጁ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ግዛቱ ፡ በመመለስ ፡ ፈንታ ፡ ለመንገድ ፡ ቅርበት ፡ አስመስሎ ፡ በጅቡቲና ፡ በምጥዋ ፡ ኣድርጎ ፡ ባሥመራ ፡ በኩል ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ካሥመራው ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ሳይቀበል ፡ አልቀረም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ኢጣሊያኖች ፡ መሐላና ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፍርሰው ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲወጉ ፡ በመሐላ ፡ በሰጡት ፡ ተስፋ ፡ ኢትዮጵያን ፡ መያዝ ፡ እስኪችሉ ፡ ድረስ ፡ ተደግፎ ፡ ቈየ ። በመጨረሻም ፡ ኢጣሊያኖች ፡ በደጋዐሌ ፡ በሰሓጢ ፡ በዐድዋ ፡ የሞቱትን ፡ የወንድሞቻችንን ፡ ደም ፡ ተበቅለን ፡ ወዲያውም ፡ ሰፊ ፡ የቄሳር ፡ አገር ፡ ለሕዝባችን ፡ አወረስን ፡ ብለው ፡ ለርሱ ፡ የሰጡትን ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ተመልክተው ፡ በካዱት ፡ ጊዜ ፡ አገሩን ፡ መክዳት ፡ ያወቀው ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጉግሳ ፡ ያገሩ ፡ ጠላቶች ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ መሐላ ፡ ያፈረሱበትን ፡ ጠላቶቹን ፡ ሊከዳቸው ፡ አልፈለገም ።

በዚሁም ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ አገራቸውን ፡ የሚወዱ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከዚህ ቀደም ፡ በጋዜጣ ፡ ተጽፎ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ግጥም ፡ ገጠሙበት ።

አላያችሁም ፡ ወይ ፡ በመዓራ ፡ ሜዳ ፡
በወዴት ፡ አለፈ ፡ ዳግማይ ፡ ይሁዳ ፡
ማተቡን ፡ በጥሶ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የከዳ ፡
ምን ፡ ያሸሽገዋል ፡ እሱ ፡ ለተጐዳ ።

ያጋሜው ፡ ደጃዝማች ፡ የእንደርታው ፡ ባልጋዳ ፡
አቁማዳ ፡ አውልቀኸ ፡ አርገኸ ፡ አቀማዳ ፡
አዬ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ የገባኸው ፡ ዕዳ ።

እንዴት ፡ ትታዘብን ፡ ዕዳጋ ፡ ኅሙስ ፡
ጠርቡሸኸን ፡ አጥልቀኸ ፡ ስትመላለስ ።

ምንኛ ፡ ይረግሙን ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡
የጽላተ ፡ ሙሴን ፡ ሥርዐት ፡ ስታፈርስ ፡
ዐድዋ ፡ ከተማቸው ፡ ሲነድ ፡ ሲጨስ ፡
የሥሑል ፡ ሚካኤል ፡ ቅጽራቸው ፡ ሲፈርስ ፡
በክንፍም ፡ አታመልጥ ፡ እንኳን ፡ በፈረስ ።

መጨነቅ ፡ ሳይመጣ ፡ መጠበብ ፡ ሳይደርስ ፡
የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

አትቀርምና ፡ ያች ፡ ፀአተ ፡ ነፍስ ፡
ነውር ፡ አይምሰልኽ ፡ ይልቅ ፡ ተመለስ ፡
ግድ ፡ የለውምና ፡ መሓሪው ፡ ንጉሥ ፡
ይቅርታ ፡ ልምዱ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ።

ምንድን ፡ ያስጮኽኻል ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ አራስ ፡
ተውሻ ፡ ተውሻ ፡ ተውሻ ፡ ታገሥ ።

ለውድ ፡ እመቤትኽ ፡ ላገርኽ ፡ ያልሆንኽ ፡
እንዴት ፡ ለሰው ፡ አገር ፡ ትታመናለኽ ፡
አንድ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ የምጠይቅኽ ፡
ውቢቱን ፡ ደጊቱን ፡ አገርኽን ፡ ጠልተኽ ፡
ከቶ ፡ የሰው ፡ አገር ፡ ምን ፡ አስወደደኽ ።

አገር ፡ እንደሌለው ፡ አገር ፡ እያለው ፡
እንዴት ፡ በሰው ፡ አገር ፡ ይሞታል ፡ ወይ ፡ ሰው ።

መልክእ ፡ መልካቸውን ፡ ፈጽሞ ፡ ኣይመስል ፥
ቋንቋኽ ፡ ከቋንቋቸው ፡ አይመሳሰል ፡
ደምሽ ፡ ከደማቸው ፡ አይቀላቀል ፥
እንደ ፡ ምን ፡ ተዋዋልኽ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ውል ።

እስኪ ፡ ልብ ፡ አድርገው ፡ ይሁዳ ፡ በውነት፥
እንድ ፡ ሣር ፡ ቢመዘዝ ፡ ያፈሳል ፡ ወይ ፡ ቤት ።

እየው ፡ ተመልከተው ፡ ያንተም ፡ እንዲህ ፡ ነው፥
-ልብ ፡ የለኽም ፡ እንጂ ፡ ዞረኽ ፡ ብታየው ።

እነሱ ፡ ሳይሉኽ ፡ እማኝ ፡ ሳይቈጥሩኽ ፡
እንዴት ፡ ለማኝነት ፡ ወደኽ ፡ ተመረጥኽ ።

ዐይንኽ ፡ ብርሃን ፡ አይችል ፡ አንተ ፡ ገመምተኛ ፡
ይቈረቍርኻል ፡ ና ፡ ተመለስ ፡ ተኛ ።

# ምዕራፍ ፡ 66 ።

## የውጋዴን ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ የቆራሔ ፡ ጦርነት ፡ የደጃዝማች ፡ አፈወርቅ ፡ ሞት ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከቀድሞው ፡ ዘመቻ ፡ የወረሰው ፡ በኤርትራ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ጠረፍ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ለሚያደርገው ፡ ጦርነት ፡ እንደ ፡ ረዳው ፡ እንዲሁም ፡ በደቡብና ፡ በምሥራቅ ፡ ያለ ፡ የሱማሊያ ፡ ግዛቱ ፡ ለጦር ፡ ማሳረፊያና ፡ ክዚያ ፡ ወታደር ፡ እየላከ ፡ አይሮፕላንም ፡ እያስነሣ ፡ ለመዋጋት ፡ ተመችቶት ፡ ነበርና ፡ በሰሜን ፡ ግንባር ፡ ካከማቸው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መሣሪያ ፡ በቍጥር ፡ አነስተኛ ፡ የሚሆን ፡ ወታደርና ፡ መሣሪያ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ አዘጋጅቶ ፡ ነበር ። ለዚህም ፡ የጦር ፡ አዛዡ ፡ ጄኔራል ፡ ሮዶልፎ ፡ ግራዚያኒ ፡ ነው ። ርሱም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የችሬናይካን ፡ አገር ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ ካደረገ ፡ ወዲህ ፡ ባላባቶቹን ፡ በብልኀትና ፡ በጭካኔ ፡ አጥፍቶ ፡ አገሩን ፡ ሰላማዊ ፡ በማድረግ ፡ ተመስግኖ ፡ ነበርና ፡ በዚያው ፡ አያያዝ ፡ በሱማሊያ ፡ ግንባር ፡ በኩል ፡ ሆኖ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ የሊቢያንና ፡ የሱማሊያን ፡ ተወላጆች ፡ ይዞ ፡ እንዲዋጋ ፡ ታዞ ፡ ነበር።

ደግነትና ፡ ርኅራኄ ፡ ጭምር ፡ ያለበት ፡ ዠግንነት ፡ የወታደርነትን ፡ ክብር ፡ እንደማያጐድል ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ማፍሰስና ፡ የደም ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ ደግሞ ፡ የዚያኑ ፡ ያኽል ፡ ከተጠይነት ፡ ጋራ ፡ እንዲሁም ፡ ክብርንም ፡ ያስገኛልና ፡ በዚህ ፡ በመጨረሻው ፡ ዐይነት ፡ ሮዶልፍ ፡ ግራዚያኒ ፡ በኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ ከልብ ፡ የተወደደ ፡ ሳይሆን ፡ የተከበረና ፡ የተፈራ ፡ ነበር ። በርሱም ፡ ታዛዥነት ፡ ውስጥ ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ ጄኔራሎች ፡ ነበሩ ፡ በሰሜን ፡ ግንባር ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጉግሳ ፡ አገሩንና ፡ ወገኑን ፡ የራሱንም ፡ ኢትዮጵያዊነት ፡ ክዶ ፡ ከጄኔራል ፡ ደቦኖ ፡ እንደ ፡ ተደባለቀ ፡ እንዲሁም ፡ በሱማሊያ ፡ በኩል ፡ ወሎል ፡ ጂሌ ፡ የሚባለው ፡ ቀንደኛ ፡ ሱማሌ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ከድቶ ፡ በግራዚያኒ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጐን ፡ ተሰልፎ ፡ ወገኖቹን ፡ ይወጋ ፡ ነበር ። ርሱንም ፡ በዠግንነት ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሲዋጉ ፡ የኖሩት ፡ የመጀርቲኖች ፡ ዐፅም ፡ ሳይወቅሠው ፡ አይቀርም።

በዚህም ፡ ግንባር ፡ ያለውን ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ የሚከላከሉ ፡ በውጋዴን ፡ ዋናው ፡ የጦር ፡ አበጋዝ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ነሲቡ ፡ በሲዳሞ ፡ በኩል ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፡ በባሌ ፡ (በጊንር) ፡ በኩል ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ መርድ ፡ ነበሩ ። እነዚህንም ፡ ለመርዳት ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ዐምዴ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤልና ፡ ሌሎችም ፡ የጦር ፡ አለቆችና ፡ ሹማምንቶች ፡ ነበሩ ።

የጦር ፡ መሳፈሪያውም ፡ ጅጅጋ ፡ ሆኖ ፡ ደግሞም ፡ በሱማሊያ ፡ ጠረፍ ፡ በቆራሔ ፡ በዳፐረይ ፡ በገርለጉቤ ፡ ላይ ፡ ካ1 ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ግራዝማች ፡ አፈወርቅ ፡ ወልደ ፡ ሰማዕት ፡ መሽገው ፡ ሲከላከሉ ፡ ቈይተው ፡ ነበርና ፡ በመጨረሻም ፡ ዋናው ፡ ጦርነት ፡ በተዠመረ ፡ ጊዜ ፡ በቆራሔ ፡ ምሽግ ፡ ከሚወዷቸው ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ በአንበሳነት ፡ እየተከላከሉ ፡ ብዙ ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ መልሰዋል ። ስለዚህ ፡ የግራዝማች ፡ አፈወርቅ ፡ የዠግንነት ፡ ዝና ፡ በዚያ ፡ ግንባር ፡ ባሉት ፡ በኢጣሊያና ፡ በሱማሊያ ፡ ወታደሮች ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ የገነነና ፡ የሚያስፈራ ፡ ነበር ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ግራዚያኒ ፡ እግረኛ ፡ ሠራዊት ፡ ወደ ፡ ቆራሔ ፡ ሲልክ ፡ ግራዝማች ፡ ኣፈወርቅ ፡ ድል ፡ እየመቱ ፡ ስለ ፡ መለሷቸው ፡ በሱማሊያ ፡ ያለውን ፡ መላውን ፡ አይሮፕላን ፡ አስነሥቶ ፡ በ30 ፡ በ30 ፡ እየከፈለ ፡ መሽገው ፡ የተቀመጡበትን ፡ ቆራሔን ፡ ያስደበድብ ፡ ዠመር ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ዠግናው ፡ ግራዝማች ፡ አፈወርቅ ፡ እግረኛውን ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ የሚወጉበትን ፡ መሣሪያ ፡ አስቀምጠው ፡ የአይሮፕላን ፡ ማውረጃ ፡ መድፍ ፡ ይዘው ፡ እያንከባለሉ ፡ በቈራጠኝነት ፡ ሲዋጉ ፡ በቦምብ ፡ ብትር ፡ ቅልጥማቸውን ፡ ተመቱ ። ከቈሰሉም ፡ በኋላ ፡ ወታደሮቻቸው ፡ ቍስሉ ፡ የበረታ ፡ ነውና ፡ ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ ኣንሥተን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ከተማ ፡ እናዛውርዎ ፡ ብለው ፡ ቢያማክሯቸው ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ የወታደርነታቸውን ፡ ክብር ፡ ሲያለመልም ፡ የሚኖረውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ንግግር ፡ ተናገሩ ። «እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከጠላት ፡ በጽኑ ፡ ተከላከለን ፡ ባቈየነው ፡ ምሽግና ፡ እናንተ ፡ የጦር ፡ ጓደኞቼ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በምትዋጉበት ፡ መካከል ፡ አስቀምጡኝ ፡ ስሞትም ፡ ከአይሮፕላን ፡ አደጋ ፡ ለመከላከያ ፡ በተቈፈረው ፡ ጕድጓድ ፡ ቅበሩኝ ፡ እንጂ ፡ አደራችሁን ፡ ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ እንዳትወስዱኝ » ። ይህንም ፡ ተናግረው ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ ለሀገር ፡ ኣፍቃሪነታቸውና ፡ ለታማኝነታቸው ፡ ለግንነታቸው ፡ የሚያጠራጥር ፡ ረቂቅ ፡ ኣየር ፡ የሚያልፍበት ፡ ቀዳዳ ፡ ሳያስገቡ ፡ ከዚህ ፡ ከሚያልፈው ፡ ዓለም ፡ ወደማያልፈው ፡ ዓለም ፡ ሄዱ ።

በሞቱም ፡ ጊዜ ፡ በእልቅናቸው ፡ ሳይመኩ ፡ ምክርም ፡ ሲሳይም ፡ እንደ ፡ ወንድማማቾች ፡ ይካፈሏቸው ፡ የነበሩት ፡ ወታደሮች ፡ እያለቀሱ ፡ በመሪር ፡ ኀዘን ፡ ቀበሯቸው ።

የዚህን ፡ ወሬ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ደሴ ፡ ከመጓዛቸው ፡ በፊት ፡ ሰምተው ፡ ነበርና ፡ በኅዳር ፡ 9 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ተነሥተው ፡ በ2 ፡ ሰዓት ፡ ጅጅጋ ፡ ደረሱ ። በዚያም ፡ ዋናው ፡ የጦር ፡ አበጋዝ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ነሲቡ ፡ ዛማኔል ፡ ተቀብለው ፡ በርሳቸው ፡ መሪነት ፡ የተሰለፈውን ፡ ጦርና ፡ በአኔሌይ ፡ ጦርነት ፡ የተዋጉትን ፡ ወታደሮችና ፡ ቍስለኞች ፡ እየዞሩ ፡ ከጐበኙ ፡ በኋላ ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ነገሩት ።

« የዛሬ ፡ 40 ፡ ዓመት ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በግፍ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ ለማጥፋት ፡ ስለ ፡ ተነሣ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የነበራችሁት ፡ አሁንም ፡ በሕይወት ፡ ያላችሁ ፡ አርበኞች ፡ በዐድዋም ፡ ጦርነት ፡ ያልነበራችሁ ፡ በዚያው ፡ የነበሩት ፡ አባቶቻችሁ ፡ ደማቸውን ፡ በማፍሰስ አርበኝነታቸውን ፡ አሳይተው ፡ ያገራቸውንና ፡ የርስታቸውን ፡ ነፃነት ፡ ከጠላታቸው ፡ ከኢጣሊያ ፡ አዳኑ። አሁን ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ያንኑ ፡ የዛሬ ፡ 40 ፡ ዓመት ፡ ድል ፡ የሆነበትን ፡ ጦርነት ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ አልቋልና ፡ አለችግር ፡ እንዋጋቸዋለን ፡ ብሎ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሰብኮ ፡ ያልሞታችሁትን ፡ እንደ ፡ ሞታችሁ ፡ አድርጎ ፡ የታወቀውንና ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ልጆች ፡ ዠግንነት ፡ አዋርዶ ፡ ነፃነታችሁን ፡ ለማጥፋት ፡ ርስታችሁንና ፡ ቤታችሁን ፡ ለመውረር ፡ አሮጌ ፡ አባት ፡ እናታችሁን ፡ ስደተኞች ፡ ለማድረግ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዠግኖች ፡ እንደ ፡ ሌሉ ፡ አድርጎ ፡ ለማስቈጠር ፡ በሰሜንም ፡ በደቡብም ፡ ጦር ፡ አምጥቶ ፡ ለማጥቃት ፡ ዠመረ ። የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ ኢጣሊያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ በግፍ ፡ መነሣቷን ፡ ዐውቀው ፡ ሁሉም ፡ ለኛ ፡ ረዳቶች ፡ ሆነዋል ። ኢጣሊያ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ምንም ፡ ያለቁ ፡ ቢመስላትና ፡ ያሉትንም ፡ ከምንም ፡ ሳትቈጥራቸው ፡ ብትቀር ፡ በዘራችሁና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የተደረገባትን ፡ ግፍ ፡ ጠላታችንን ፡ በማሸነፍና ፡ በግፍ ፡ ከያዙት ፡ ግዛታችን ፡ በማባረር ፡ ዠግንነታችሁን ፡ ማደስ ፡ ዋና ፡ የተገባችሁ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ሰው ፡ ለዘለዓለም ፡ ነዋሪ ፡ ሊሆን ፡ አልተፈጠረም ፡ በመጨረሻውም ፡ ከዓለም ፡ የሚለየው ፡ ሞት ፡ ነው ። ይህ ፡ ሞት ፡ ይቀድማል ፡ ይከተላል ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ አይቀርለትም ። ከመቃብር ፡ በላይ ፡ እየሰፈፈ ፡ የሚታይ ፡ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ መታሰቢያ ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ ስም ፡ ነው ።

የዛሬ ፡ 40 ፡ ዓመት ፡ በዐድዋ ፡ ይህ ፡ ጠላታችን ፡ በተዋጋን ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዠግኖች ፡ ድል ፡ ስለ ፡ መቱት ፡ እንኳንስ ፡ በሕይወት ፡ ያላችሁት ፡ በዚያውም ፡ የቀሩት ፡ ቢሆኑ ፡ ስማቸው ፡ ሳይረሳ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሲጠራ ፡ ይኖራል። አሁንም ፡ ላለው ፡ ትውልድ ፡ ዋና ፡ የሚያኰራ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ለወንድ ፡ ልጅ ፡ እንኳንስ ፡ አገሩንና ፡ ርስቱን ፡ የሚቀማ ፡ ወገኑን ፡ ወደ ፡ ስደት ፡ የሚያደርስ ፡ ጠላት ፡ ተነሥቶበት ፡ እንዲያውም ፡ ቢሆን ፡ ዋና ፡ ምኞቱና ፡ የሚያኰራው ፡ ሞት ፡ በጦርነት ፡ የሚደርስበት ፡ ነው ። ዶሮ ፡ እንኳ ፡ ጫጩቶቿን ፡ ካሞራ ፡ ለማዳን ፡ ትተናነቃለች ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ በአእምሮም ፡ በጒልበትም ፡ ብዙ ፡ ሺ ፡ ጊዜ ፡ የሚበልጠው ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ መታገል ፡ እንደሚገባው ፡ ዕወቁ ። እንግዴህ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሞት ፡ በመጨረሻው ፡ የማይቀርለት ፡ ከሆነ ፡ የማይጠፋ ፡ ስሙን ፡ ለመትከል ፡ አሮጌ ፡ አባትና ፡ እናቱ ፡ ሚስቱ ፡ ልጆቹ ፡ እንዳይሰደዱበትና ፡ ዛሬ ፡ በነፃ ፡ አገራቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተከብረው ፡ ሲኖሩ ፡ ነፃነት ፡ ያጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ክብራቸው ፡ ቀርቶ ፡ በውርደት ፡ እንዳይወድቁ ፡ ለማድረግ ፡ የመጣውን ፡ ጠላት ፡ በመውጋት ፡ ሕይወታችሁን ፡ ብታሳልፉ ፡ ክብራችሁ ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ ይሆን !። የከበረ ፡ ስማችሁም ፡ በልጆቻችሁና ፡ በወገኖቻችሁ ፡

ዘንድ ፡ ሲመሰገንና ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ሲጠራ ፡ ይኖራል ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ጠላታችን ፡ ይህንኑ ፡ ያጥቂነት ፡ ሐሳቡን ፡ ለመፈጸም ፡ ማሰቡን ፡ ዐውቀን ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ የምንገዛችሁ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችሁ ፡ በጦርነትም ፡ ጊዜ ፡ ከመካከላችሁ ፡ ሆነን ፡ ደማችንን ፡ ለማፍሰስ ፡ መቍረጣችንን ፡ ነግረናችሁ ፡ ነበር። ይኸው ፡ አሁንም ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ አለን ።

ኢጣሊያኖች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ቢያበዙ ፡ ካወቃችሁበት ፡ ምንም ፡ ሊጐዱችሁ ፡ አይችሉም ። አይሮፕላንም ፡ የተባለው ፡ በቦምብ ፡ ጩኸት ፡ ለማስደንገጥና ፡ ልብ ፡ ለማስነፍ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ አይሠራም ። ስለ ፡ ዛሬው ፡ ዘመን ፡ የጦርነት ፡ አኳኋን ፡ ብዙ ፡ ጒዳት ፡ ሳያገኛችሁ ፡ ጠላታችሁን ፡ ለማጥፋት ፡ እንድትችሉ ፡ በያሉቃችሁ ፡ በኩል ፡ የሰጠናችሁን ፡ ምክር ፡ መከተል ፡ ነው ። ላገራችሁ ፡ ነፃነት ፡ ለመከላከል ፡ በዚህም ፡ ባላችሁበት ፡ ስፍራ ፡ በችግራችሁ ፡ ሁሉ ፡ በገንዘብም ፡ በስንቅም ፡ ችግራችሁን ፡ ለማቅለል ፡ ርዳታችንን ፡ አናጓድልባችሁም ፡ ላገራቸውና ፡ ለወገናቸው ፡ ክብር ፡ የተገባ ፡ ሲሠሩ ፡ ሕይወታቸውን ፡ ላሳለፉ ፡ አርበኞች ፡ ለወገኖቻቸውና ፡ ለቤተ ፡ ዘመዳቸው ፡ ሁሉ ፡ ችግር ፡ እንዳያገኛቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትም ፡ አባትም ፡ ሆነን ፡ እንጠብቃቸዋለን ። ስለዚህም ፡ በያለቃቸው ፡ ስማቸው ፡ ተጽፎ ፡ እንዲቀርብልን ፡ የጦር ፡ እንደራሴዎቻችንን ፡ አዘናል ፡ እኛም ፡ ሕይወታችን ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ዘወትር ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ነን» ።

ንግግራቸውንም ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ እነሌይ ፡ በፊታውራሪ ፡ ጓንጉል ፡ ኮላሴ ፡ መሪነት ፡ በዠግንነት ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ላይ ፡ ተዋግተው ፡ አራት ፡ ታንክና ፡ መትረየስ ፡ ካሚዮን ፡ ጭምር ፡ የማረኩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ እግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሥራቸውን ፡ ከመግለጽ ፡ ጋራ ፡ ፎከሩ ። ግርማዊ ፡ ጃንሆይም ፡ እነሱን ፡ ሽልመውና ፡ አመስግነው ፡ ቀጥለው ፡ የነዚሁ ፡ የጐበዞች ፡ አለቃ ፡ ፊታውራሪ ፡ ጓንጉል ፡ ኮላሴ ፡ በዚሁ ፡ ጦርነት ፡ በዠግንነት ፡ ሲዋጉ ፡ ቈስለው ፡ ወደ ፡ ተኙበት ፡ ስፍራ ፡ ሄደው ፡ ከሽልማት ፡ ጋራ ፡ የሚያጽናና ፡ ንግግር ፡ ኣድርገውላቸው ፡ ከዚያም ፡ ግራዝማች ፡ አፈወርቅ ፡ ወደ ፡ ተቀበሩበት ፡ ስፍራ ፡ ሄደው ፡ በመቃብሩ ፡ ላይ ፡ ያበባ ፡ አክሊል ፡ ካስቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ዘርና ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ሲጠፋ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሳይጠፋ ፡ ለሚኖረው ፡ ስማቸው ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲሆን ፡ «የውጋዴን ፡ ደጃዝማች ፡ አፈወርቅ» ፡ ብለው ፡ ሰየሟቸው ።

እንዲሁም ፡ ለደጃዝማች ፡ አፈወርቅ ፡ ልጅና ፡ ለሌሎቹ ፡ በጦርነት ፡ ሰዓት ፡ የዠግንነት ፡ ሥራ ፡ ለሠሩት ፡ የማዕርግ ፡ ስምና ፡ ሽልማት ፡ ሰጥተው ፡ በኅዳር ፡ 11 ፡ ቀን ፡ ተመልሰው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገቡ ።

ደጃዝማች ፡ አፈወርቅም ፡ ዐርፈው ፡ የግራዚያኒ ፡ ሳምባ ፡ በሰፊው ፡ ከተነፈሰ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ እየሆነ ፡ የተመለሰበትን ፡ የቆራሔን ፡ ምሽግ ፡ ፍሩሺና ፡ ማለቱ ፡ በሚባሉ ፡ በሁለት ፡ ጄኔራሎች ፡ የሚታዘዝ ፡ አዲስ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ልኮ ፡ በአየርም ፡ ልክ ፡ በሌለው ፡ ቦምብ ፡ እየደበደበ ፡ በመጨረሻ ፡ ለመያዝ ፡ ቻለ ።

# ምዕራፍ ፡ 67 ።

## ስለ ፡ መቀሌ ፡ መያዝ ፥ ስለ ፡ ጄኔራል ፡ ደቦኖ ፡ መለወጥ ።

የጄኔራል ፡ ደቦኖ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ዐድዋን ፡ ይዞ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ እንዳረፈ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፍቶ ፡ መቀሌን ፡ ደግሞ ፡ እንዲይዝ ፡ ከሙሶሊኒ ፡ ትእዛዝ ፡ ተላለፈለት ።

እርሱም ፡ እንደ ፡ ታዘዘ ፡ የሁለት ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ 1ኛው ፡ ከዐድዋ ፡ በሐውዜን ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ መቀሌ ፡ 2ኛው ፡ ከዐዲግራት ፡ ተነሥቶ ፡ በዕዳጋ ፡ ኀሙስ ፡ በኩል ፡ የሚጓዝ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ላከ ። እነዚህንም ፡ እፊት ፡ እፊት እየቀደሙ ፡ ይመሩ ፡ የነበሩት ፡ የከዳተኛው ፡ የደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጉግሳ ፡ አሽከሮች ፡ ነበሩ ።

ከዐድዋ ፡ የተነሣውም ፡ ጦር ፡ ሐውዜንና ፡ ሞንቴ ፡ ጉንዲ ፡ (የጉንዲ ፡ ተራራ) ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ሲደርሱ ፡ ከደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሕይወትና ፡ ከደጃዝማች ፡ ወረስ ፡ ከፊታውራሪ ፡ አሥጋሽኝ ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ገጥመው ፡ የኛ ፡ ወታደሮች ፡ ብዙ ፡ የኢጣሊያ ፡ ሹማምንቶችና ፡ ብዙ ፡ የኤርትራ ፡ ወታደሮች ፡ ገደሉ ።

8 ፡ ድንጉላ ፡ ፈረስና ፡ 13 ፡ በቅሎዎችም ፡ ማረኩ ፥ እንደዚሁ ፡ በሓውዜን ፡ በኩል ፡ የሚጓዘውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በግራ ፡ በኩል ፡ ሆኖ ፡ ለመጠበቅ ፡ ያ1 ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በደንከል ፡ በረሓ ፡ ይጓ ፡ ነበርና ፡ ይኸንኑ ፡ ጦር ፡ ደጃዝማች ፡ ካሳ ፡ ስብሐት ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ገጥመዋቸው ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ አደረጉ ፡ በዚህም ፡ ጦርነት ፡ አዝማቹ ፡ ሲቈስል ፡ እንደዚሁ ፡ ሁለት ፡ ሹማምንቶችና ፡ 300 ፡ የሚሆኑ ፡ የኢጣሊያና ፡ የኤርትራ ፡ ወታደሮች ፡ ሞቱ።

በኋላ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በያለበት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ በጕብዝና ፡ ቢመከቱ ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ በመሸገበት ፡ በዚሁ ፡ በመቀሌ ፡ አጠገብ ፡ ሆኖ ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ማድረግ ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነበርና ፡ በዚያ ፡ ሆነው ፡ ይከላከሉ ፡ የነበሩት ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ መቀሌን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲመለሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ተላልፎላቸው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ በኅዳር ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መቀሌ ፡ ገብቶ ፡ የኢጣሊያን ፡ ባንዲራ ፡ ተከለ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጄኔራል ፡ ደቦኖ ፡ ዐድዋንና ፡ መቀሌን ፡ ሲይዝ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የበረታ ፡ ጦርነት ፡ ሳያደርጉ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ማፈግፈጋቸው ፡ ከደስታ ፡ ይልቅ ፡ ሥጋትን ፡ አሳድሮበት ፡ ነበር ። በየቀኑ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ግፋ ፡ እያለ ፡ ከሮማ ፡ አንደኛው ፡ ሚኒስትር ፡ ቴሌግራም ፡ ሲያስተላልፍለት ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ጕብዝና ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ያውቃልና ፡

እንደ ፡ 1888 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጄኔራል ፡ ባራቲዬሪ ፡ ዕድል ፡ እንዳይገጥመው ፡ ፈርቶ ፡ የያዝኩትን ፡ ሳላጠብቅ ፡ መንገድና ፡ መገናኛው ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ሳይዘጋጅ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እቀጥላለሁ ፡ አለዚያም ፡ እዚህ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ የሚያኽል ፡ ከኢጣሊያ ፡ አገር ፡ ላኩልኝና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እቀጥላለሁ ፡ እያለ ፡ የሙሶሊኒን ፡ ትእዛዝ ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ አስቸግሮ ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሙሶሊኒ ፡ በደቦኖ ፡ ቅርታ ፡ ገብቶት ፡ ነበር፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ቅርታውን ፡ በልቡ ፡ ይዞ ፡ በዐድዋና ፡ በመቀሌ ፡ የፈሰሰውን ፡ የወንድሞቻችኸን ፡ ደም ፡ ተበቅለኸ ፡ እነዚህን ፡ ሁለት ፡ ከተሞች ፡ መያዝኸ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ነው ። በዚህም ፡ ሥራኸ ፡ ማሬሻል ፡ ተብለኻል ፥ አሁን ፡ ግን ፡ ባንተ ፡ ስፍራ ፡ ይኸው ፡ ማሬሻል ፡ ፒየትሮ ፡ ባዶሊዮ ፡ መጥቷልና ፡ የጦር ፡ አዛዥነቱን ፡ ስፍራ ፡ ለርሱ ፡ አስረክበኸ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ተመለስ ፡ ብሎ ፡ አስተላለፈለትና ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ ተመለሰ ።

# ምዕራፍ ፡ 68 ።

## የማሬሻል ፡ ባዶሊዮ ፡ መምጣትና ፡ የደምበጉና ፡ ጦርነት ።

የኢጣሊያ ፡ 1ኛ ፡ ሚኒስትር ፡ ቤኒቶ ፡ ሙሶሊኒ ፡ በዤኔብ ፡ ማኅበሩ ፡ በኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ ጭቈና ፡ ለማድረግ ፡ መቍረጣቸውን ፡ ያውቃልና ፥ እነሱ ፡ ጭቈና ፡ ቢያደርጉ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በቶሎ ፡ ከያዝኩ ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ያልቃል ፡ ለሕይወታችን ፡ የሚያስፈልገውንም ፡ ሁሉ ፡ ከዚያው ፡ እናገኛለንና ፡ በቶሎ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጦርነት ፡ መጨረስ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ለፊተኛው ፡ አዝማች ፡ ምሥጢሩን ፡ በቴሌግራም ፡ ከገለጸለት ፡ በኋላ ፡ ጄኔራል ፡ ደቦኖ ፡ ግን ፡ በፊቱ ፡ ያለውን ፡ ችግር ፡ እየገለጠ ፡ ትእዛዙን ፡ ስላቃለለበት ፡ በርሱ ፡ እግር ፡ በኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ የታወቀውን ፡ ማሬሻል ፡ ፒየትሮ ፡ ባዶሊዮን ፡ መረጠ ።

ወዲያው ፡ ሙሴ ፡ ሙሶሊኒ ፡ በፓላሶ ፡ ቬኔሲያ ፡ ቢሮው ፡ ማሬሻል ፡ ባዶሊዮን ፡ ጠርቶ ፡ በቈይታ ፡ ነገረው ። ባዶሊዮ ፡ በመጽሐፉ ፡ እምነቱን ፡ ካገኘሁ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ልቤ ፡ ማንኛውንም ፡ እንድሠራ ፡ ቻልሁ ፡ ሲል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ ያስረዳል ።

«ይኸው ፡ አሁን ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አግዞ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ጭቈና ፡ እንዳደረገብን ፡ ታውቃለኸ ። እኔም ፡ ይኸንኑ ፡ ጭቁና ፡ ለማሸነፍ ፡ ደቦኖን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ግፋ ፡ ብዬ ፡ ብልክበት ፡ ምክንያት ፡ እያበዛ ፡ ቃሌን ፡ ሊፈጽም ፡ ኣልቻለም ። ስለዚህ ፡ ርሱን ፡ ሽሬ ፡ በመላው

፡ በአፍሪካ ፡ ላለው ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ አድርጌኻለሁና ፡ ሄደኽ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብለኽ ፡ በማንኛውም ፡ መሣሪያ ፡ ተዋግተኽ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጦርነት ፡ በቶሎ ፡ እንዲፈጸም ፡ አድርግልኝ ፡ ይልቁንም ፡ የዐድዋ ፡ ድል ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ ሲያሳፍረን ፡ እንደ ፡ ኖረ ፡ ደግሞ ፡ አሁን ፡ ድል ፡ የሆንን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታላቅ ፡ ኀፍረት ፡ ነውና ፡ የዓለምን ፡ ሕግና ፡ ደንብ ፡ እከታተላለሁ ፡ ሳትል ፡ በታንክና ፡ በቦምብ ፡ በጋዝ ፡ መርዝም ፡ ጭምር ፡ የኢትዮጵያን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ እያጠፋኽ ፡ ድል ፡ አድርግ ፡ ያለውም ፡ ሠራዊት ፡ በቂኽ ፡ ባይሆን ፡ አንተ ፡ ኤርትራ ፡ እንደ ፡ ደረስን ፡ የሁለት ፡ ዲቪዚዮን ፡ (ክፍል ) ፡ ጭፍራ ፡ እልክልኻለሁ» ።

ማሬሻል ፡ ባዶሊዮም ፡ ይህነን ፡ የመሰለና ፡ ከዚህም ፡ የተረፈውን ፡ ንግግር ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ትእዛዝኽን ፡ ለመፈጸም ፡ የተዘጋጀሁ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ከሙሶሊኒና ፡ ከንጉሥ ፡ ተሰናብቶ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ተነሥቶ ፡ ኅዳር ፡ 19 ፡ ቀን ፡ በመርከብ ፡ ተጒዞ ፡ አሥመራ ፡ ገባ ። ደቦኖም ፡ በጣም ፡ ቅር ፡ እያለው ፡ ምጥዋ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ተቀበለው ።

ርሱም ፡ አሥመራ ፡ ደርሶ ፡ የተያዘውን ፡ የዐድዋንና ፡ የመቀሌን ፡ ከተማ ፡ እየዞረ ፡ ሲጐበኝ ፡ የራስ ፡ እምሩና ፡ የደጃዝማች ፡ አያሌው ፡ ጦር ፡ የተከዜን ፡ ወንዝ ፡ አልፎ ፡ ሺሬ ፡ ውስጥ ፡ በተለይ ፡ ደምበጒና ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ የሰፈረውን ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ ፊታውራሪ ፡ ሺፈራው ፡ ከነወታደሮቻቸው ፡ ከበው ፡ እየወጉ ፡ አስጨነቋቸው ። እነዚህም ፡ የተከበቡት ፡ ኢጣሊያኖች ፡ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ ሆነው ፡ ሲዋጉ ፡ በመጨረሻ ፡ የቀራቸው ፡ እጃቸውን ፡ መስጠት ፡ አለዚያም ፡ እዚሁ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ማለቅ ፡ ነበርና ፡ ተስፋ ፡ በሚያስቈርጥ ፡ ጒልበት ፡ ሲዋጉ ፡ ቈይተው ፡ በመጨረሻ ፡ ፈጣን ፡ የሆኑ ፡ ታንኮች ፡ ለርዳታ ፡ ደርሰውላቸው ፡ ባ1 ፡ ወገን ፡ ሰብረው ፡ ጥቂቶች ፡ ብቻ ፡ ሲያመልጡ ፡ 4oo ፡ የሚሆኑ ፡ የኢጣሊያ ፡ ወታደሮች ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡ ሞተው ፡ ተገኙ ። ብዙ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ካ10 ፡ ታንክና ፡ ከ2 ፡ መድፍ ፡ ጋራ ፡ ከነሕይወታቸው ፡ እጃቸውን ፡ ሰጥተው ፡ ተማረኩ ። በዚሁ ፡ ጦርነት ፡ ፊታውራሪ ፡ ሺፈራው ፡ እስከ ፡ ታንኩ ፡ አፍ ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ በዠግንነት ፡ ተዋግተው ፡ ሕይወታቸውን ፡ አሳለፉ።

በዚህ ፡ በደምበጒና ፡ ጦርነት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በጠላታቸው ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ካገኙ ፡ በኋላ ፡ ጠላትን ፡ እያባረሩ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየገፉ ፡ ሄደው ፡ እስከ ፡ ዐቢይ ፡ ዐዲ ፡ ደረሱ ። ከዚያም ፡ አምባ ፡ ደለሬ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ከእጣሊያኖች ፡ ጋራ ፡ ታላቅ ፡ ውጊያ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ዠምረው ፡ ሙሉውን ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ፡ አጣሊያኖች ፡ መሽገው ፡ የተቀመጡበትን ፡ የአምባጸለሬን ፡ ምሽግ ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ሰለክለካና ፡ ወደ ፡ ኣፍጋጋ ፡ ሔዱ።

# ምዕራፍ ፡ 69 ።

## የመዠመሪያው ፡ የተንቤን ፡ ጦርነትና ፡ የአምባ ፡ አራዳም ፡ ጦርነት ።

የኢትየጵያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በልዑላን ፡ ራስ ፡ ካሳና ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ የሚታዘዘው ፡ ጦር ፡ ከዐድዋና ፡ ከመቀሌ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ (በተንቤን) ፡ በራስ ፡ እምሩ ፡ የሚታዘዘው ፡ ጦር ፡ ከዐደዋና ፡ ከመቀሌ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ (በሽሬ) ፡ በጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ በራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ የሚታዘዘው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከዐደዋና ፡ ከመቀሌ ፡ በደቡብ ፡ ምሥራቅ ፡ እንዲሁ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የክብር ፡ ዘበኞችንና ፡ ሌሎችን ፡ ወታደሮች ፡ ይዘው ፡ በደቡብ ፡ (በአሸንጌ) ፡ ተሰልፈው ፡ ነበር ።

ከዚሁ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ በራስ ፡ እምሩ ፡ የሚታዘዘው ፡ ጦር ፡ ደምበጉናና ፡ አምባ ፡ ድራሬ ፡ ላይ ፡ መሽጎ ፡ የተቀመጠውን ፡ የኢጣሊያኖችን ፡ ጦር ፡ ወግተው ፡ ድል ፡ አደርገው ፡ እስከ ፡ ዐድዋ ፡ አጠገብ ፡ ደርሰው ፡ ወደ ፡ ኤርትራ ፡ ጠረፍ ፡ ሲያቃኑ ፡ እንዲሁ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ተንቤን ፡ ያለው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፍቶ ፡ እንዲዋጋ ፡ ያስፈልግ ፡ ነበርና ፡ ሁለቱ ፡ ልዑላን ፡ አብረዋቸው ፡ ያሉትን ፡ ደጃዝማች ፡ ወንድ ፡ በወሰንንና ፡ ደጃዝማች ፡ አበራን ፡ ደጃዝማች ፡ አድማሱ ፡ ብሩን ፡ በጅሮንድ ፡ ለጥ ፡ ይበሉን ፡ ደጃዝማች ፡ ወርቅነሽን ፡ ፊታውራሪ ፡ አንዳርጌን ፡ በያለበት ፡ አሰልፈው ፡ እስከ ፡ ተንቤን ፡ ከተማ ፡ እስከ ፡ ዐቢይ ፡ ዐዲ ፡ ድረስ ፡ ተጓዙ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ እንደዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በየክፍሉ ፡ የተሰለፈበትን ፡ ስፍራ ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ፡ ጦርነት ፡ ካንደኛው ፡ ጋራ ፡ በሚያደርግበት ፡ ጊዜ ፡ 1ኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፡ ወታደር ፡ ለሚዋጋው ፡ ለርዳታ ፡ እንዳይደርስለት ፡ መንገድና ፡ በር ፡ የሆነውን ፡ ስፍራ ፡ ታንክና ፡ መድፍ ፡ መትረየስ ፡ የጅ ፡ ቦምብ ፡ የያዙ ፡ ወታደሮች ፡ ኣስቀድሞ ፡ እየላከ ፡ ያሲዝ ፡ ነበር ። ራስ ፡ ካሳና ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ ተንቤን ፡ ሆነው ፡ ከኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውጊያ ፡ ሲገጥሙ ፡ ከእንደርታ ፡ ራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ ርዳታ ፡ እንዳይልኩ ፡ ጥር ፡ 12 ፡ ቀን ፡ ደብረ ፡ ነጋይዳን ፡ ስላሲያዘ ፡ እነሱም ፡ የሸለቆትን ፡ መተላለፊያ ፡ ደኅና ፡ ኣድርገው ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ዐይነት ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ ከሽሬ ፡ ለርዳታ ፡ እንዳይደርሱ ፡ ወይም ፡ እንዳይልኩ ፡ የሀዲ. ፡ ደናጉልን ፡ መተላለፊያ ፡ ያ1 ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ልኮ ፡ ያስጠብቅ ፡ ነበር ።

አንዳንዱን ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ሠይራዊት ፡ በየተራ ፡ መዋጋት ፡ እንዲመቸው ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ አንደኛውን ፡ እንዳይረዳ ፡ መንገድና ፡ በሩን ፡ ካሲያዘ ፡ ወዲህ ፡ ኀይለኛውንና ፡ ብዙውን ፡ ተንቤን ፡ ያለውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ለመግጠም ፡ ቈርጦ ፡ ዋሪዬጠና ፡ መልፉ ፡

በሚባለው ፡ ምሽጉ ፡ ጥር ፡ 14 ፡ ቀን ፡ በ3 ፡ ተከፍሎ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ከሚጓዘው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሥራዊት ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ዠመረ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ ማይ ፡ መርታ ፡ ከሚባለው ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ዘባን ፡ ቀርካህታ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ በዠግንነት ፡ ይከላከሉ ፡ ዠመር ። ሩቅ ፡ በሩቅ ፡ ሆነው ፡ በመድፍ ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ የሁለቱም ፡ ወገን ፡ የጦር ፡ ሥራዊት ፡ እያደር ፡ እየተጠጋጋ ፡ ጦርነቱን ፡ በጋለ ፡ አኳኋን ፡ ይዋጋ ፡ ዠመር ። ይልቁንም ፡ ወደ ፡ መቀሌ ፡ የሚወስደውን ፡ የመሐኖን ፡ መንገድ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እንውሰድ ፡ እነዚያ ፡ ኣናስወስድም ፡ በማለት ፡ እየደጋገሙ ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ያደርጉ ፡ ዠመር ። በመጨረሻም ፡ ዠግናው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ መሽጎ ፡ የሚዋጋበትን ፡ ስፍራ ፡ እየለቀቀ ፡ እየፎከረ ፡ በሩጫ ፡ እጠላት ፡ ምሽግ ፡ ድረስ ፡ እየገባ ፡ በጐራዴ ፡ ይጨፋጨፍ ፡ ዠመር ።

ይኸውም ፡ ሰዓት ፡ ለኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ የጭንቅ ፡ ሰዓት ፡ ነበርና ፡ አስቀድሞ ፡ ሽሬንና ፡ ተንቤንን ፡ ድል ፡ ሳያደርግ ፡ በመቀሌ ፡ ውስጥ ፡ መሽጎ ፡ መቀመጡን ፡ እንደ ፡ ስሕተት ፡ ቈጥሮት ፡ ነበርና ፡ በዚሁ ፡ በጨበጣ ፡ በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ድል ፡ አደረጉ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ድል ፡ ሆኑ ፡ እያሉ ፡ መቀሌ ፡ ያሉት ፡ የኢጣሊያ ፡ ወታደሮች ፡ ድንገት ፡ የተንቤኑ ፡ ድል ፡ ለኢጣሊያኖች ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሽሽት ፡ እንዲመቻቸው ፡ አራግፈው ፡ ተቀምጠው ፡ የነበረውን ፡ ሥንቅና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እከብትና ፡ እመኪና ፡ ላይ ፡ ጭነው ፡ ለመሸሽ ፡ ዡሯቸውን ፡ ከፍተው ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ገሚሱ ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ተደባልቆ ፡ የቀረውም ፡ እምሽጉ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሲዋጋ ፡ ገሚሱ ፡ ደግሞ ፡ ደጀን ፡ ሆኖ ፡ ሲጠባበቅ ፡ የኢጣሊያ ፡ አይሮፕላኖች ፡ ቦምብ ፡ እየተሸከሙ ፡ መጥተው ፡ እምሽጉ ፡ ሆነው ፡ በሚዋጉትና ፡ ደጀን ፡ በሆኑት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ ላይ ፡ እየደጋገሙ ፡ ቦምብ ፡ ያዘንቡባቸው ፡ ዠመር ። ለነዚያም ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ ጋራ ፡ ተደባልቀው ፡ ለሚዋጉት ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ኣዲስ ፡ ጦር ፡ እየመጣ ፡ ያግዛቸው ፡ ነበር።

በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ዘባን ፡ ቀርካህታ ፡ ሞንቴ ፡ ላታ ፡ አባሮ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ 10 ፡ ቀን ፡ 3 ፡ ሌሊት ፡ ያለዕረፍት ፡ ሲዋጉ ፡ ስፍራውን ፡ በየተራ ፡ ይቀማሙ ፡ ነበር ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ለዚህ ፡ ለገጠመው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ ከሌላ ፡ ዘንድ ፡ ርዳታ ፡ ሳይደርስለት ፡ ደጀን ፡ ጠባቂ ፡ እንዲሆን ፡ የተቀመጠውንም ፡ እየመላለሰ ፡ በቦንብና ፡ በመትረየስ ፡ ከሚመታው ፡ ኣኤሮፕላን ፡ ጋር ፡ በጠመንዥ ፡ ሽቅብ ፡ እየተኰሰ ፡ ሲዋጋ ፡ ለኢጣሊያኖች ፡ ግን ፡ የሚዋጉት ፡ ድል ፡ በሆኑ ፡ ቍጥር ፡ ሌላ ፡ ኣዲስ ፡ ጦር ፡ ይጨመርላቸው ፡ ነበር ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጦር ፡ ከግባ ፡ ወንዝ ፡ ወዲያ ፡ ለማባረር ፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ መቀሌን ፡ ለመያዝ ፡ ተዋግተው ፡ ሁለቱም ፡ ወገን ፡ ኣሳባቸውን ፡ ከፍጻሜ ፡ ሳያደርሱ ፡ ትልቅ ፡ የወታደር ፡ እልቂት ፡ ስላገኛቸው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ወደየምሽጋቸው ፡ ተመለሱ ።

በዚህም ፡ ቀን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወገን ፡ 1 ፡ ሺህ ፡ ሞተው ፡ 2 ፡ ሺህ ፡ በቦምብ ፡ ቈሰሉ ፤ ከኢጣሊያኖች ፡ ወገን ፡ 1 ፡ ሺህ ፡ 500 ፡ የሚሆኑ ፡ ሞቱ ። ብዙም ፡ የኢጣሊያ ፡ ምርኮኞች ፡ በኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ በድንኳኑ ፡ በዘበኛ ፡ ይጠበቁ ፡ ነበር ።

ቀጥሎም ፡ ከዳተኛው ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጉግሳ ፡ የአምባ ፡ አራዳም ፡ ተራራ ፡ በጦርነት ፡ ተይዞ ፡ የኢጣሊያ ፡ ባንዲራ ፡ እስኪሰቀልበት ፡ ድረስ ፡ የመቀሌ ፡ መያዝ ፡ ሊረጋገጥ ፡ አይችልም ፡ ሲል ፡ ለማሬሻል ፡ ባዶሊዮ ፡ አመልክቶት ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ባዶሊዮ ፡ የራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ ጦር ፡ የሰፈረበትን ፡ የአምባ ፡ አራዳምን ፡ ተራራ ፡ እንዲይዙ ፡ አርባ ፡ ባታዮ ፡ የሚሆኑ ፡ ወታደሮች ፡ በፍጥነት ፡ አዘጋጀ ። እነዚህም ፡ ባዲሱ ፡ ዐይነት ፡ የተሠራ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መድፍና ፡ መትረየስ ፡ የእጅ ፡ ቦምብ ፡ የያዙ ፡ ነበሩ።

ጦርነቱም ፡ በዐዲ ፡ ማራና ፡ በታጋታጋ ፡ ላይ ፡ የካቲት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ ተዠርምሮ ፡ እስከ ፡ የካቲት ፡ 9 ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ሲያደርጉ ፡ ሰነበቱ ፡ ። በየካቲት ፡ 4 ፡ ቀን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ ሌሊቱን ፡ በኢጣሊያ ፡ ምሽግ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ታላቅ ፡ የተቃና ፡ ሥራ ፡ ሠርተዋል ። በየካቲት ፡ 5 ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ያሉበትን ፡ የአምባ ፡ አራዳምን ፡ ተራራ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ከያለበት ፡ ከበው ፡ ከታች ፡ በመድፍና ፡ በመትረየስ ፡ ሲወጉት ፡ እንደዚሁ ፡ ከላይ ፡ ደግሞ ፡ የቦምብ ፡ እሳት ፡ ሲዘንብበት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ በዚህ ፡ እሳት ፡ መካከል ፡ ሆኖ ፡ ተስፋ ፡ ሳይቈርጥ ፡ በዠግንነት ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ጠመንዣውን ፡ ትቶ ፡ በፉከራ ፡ እየገገ" ፡ እስከ ፡ ታንኩና ፡ እስከ ፡ መድፉ ፡ አፍ ፡ ድረስ ፡ እየሄደ ፡ ጠላቴን ፡ በጁ ፡ ጨብጦ ፡ በጐራደና ፡ በሰይፍ ፡ ይገድል ፡ ነበር ። በዚህም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ ደፋርነት ፡ በኢጣሊያ ፡ ወታደር ፡ አጠገብ ፡ ያሉት ፡ ጋዜጣ ፡ ጸሓፊዎችና ፡ ራሳቸው ፡ ኢጣሊያኖች ፡ በጣም ፡ ይገረሙ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ባጠገባቸው ፡ ያለው ፡ የቦምብ ፡ ክምርና ፡ በዓለም ፡ የተከለከለው ፡ የጋዝ ፡ መርዝ ፡ በንዴት ፡ እየተጋፈጠ ፡ የሚዋጋቸውን ፡ ጠላታቸውን ፡ እንደሚያጠፉላቸው ፡ ርግጠኞች ፡ ነበሩና ፡ መጽናኛቸው ፡ ይህ ፡ መርዝ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የሁለቱ ፡ ወገን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ገጥሞ ፡ ጥቂት ፡ ሳይዋጋና ፡ አሸናፊው ፡ ሳይታወቅ ፡ የኢጣሊያ ፡ አይሮፕላን ፡ ነጂዎች ፡ በፍጥነት ፡ ብዙ ፡ አይሮፕላኖች ፡ እያስነሡ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ የቦምብና ፡ የመርዝ ፡ ዝናም ፡ ያዘንቡበት ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ዠግና ፡ ቢሆን ፡ ዠግንነቱ ፡ ፍሬ ፡ ለመስጠት ፡ የማያደርሰው ፡ መሆኑን ፡ በተገነዘበው ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ስፍራና ፡ ጊዜ ፡ ማማረጡና ፡ ሁኔታውን ፡ ለማሻሻል ፡ መሞከሩ ፡ አይቀርም ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ 5 ፡ ቀን ፡ ጠላትን ፡ ተዋግተው ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ማለቁን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ወደሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ተዛውረው ፡ ወይም ፡

ከነልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ ጋራ ፡ ተደባልቀው ፡ ለመዋጋት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሲመለሰ ፡ እንደዚሁ ፡ የኢጣሊያ ፡ አይሮፕላኖች ፡ እየተከታተሉ ፡ በቦምብና ፡ በመትረየስ ፡ በጦርነት ፡ የደከመውን ፡ ሠራዊት ፡ ይመቱ ፡ ነበር ። ወዲያውም ፡ አስቀድመው ፡ በሰላሙ ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በቃል ፡ ስብከትና ፡ በገንዘብ ፡ የደለላቸውን ፡ የራያና ፡ የአዘቦ ፡ ሕዝቦች ፡ ብረት ፡ ጭምር ፡ እየሰጠ ፡ ሂዱ ፡ ተዋጉ ፡ እያለ ፡ ይልካቸው ፡ ነበር ። ከነዚሁም ፡ ውስጥ ፡ የተተኰሰች ፡ ጥይት ፡ ረዥምና ፡ ሰፊ ፡ አሳብ ፡ ለነበረው ፡ ለሚኒስትሩ ፡ ሕይወት ፡ ኣጥፊ ፡ ሆነች ።

ነገር ፡ ግን ፡ ራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ እላይ ፡ በተባለው ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ በዚሁ ፡ ባ5 ፡ ቀን ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ በዠግንነት ፡ ሲዋጉ ፡ ሰንብተው ፡ ነበርና ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ እኔ ፡ የነሲቡ ፡ የደምሰው ፡ ልጅ ፡ የኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አሽከር ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ፊቴን ፡ ወደ ፡ ኋላዬ ፡ መልሼ ፡ ዠርባዬን ፡ ለጠላቴ ፡ አላሳየውም ፡ ብለው ፡ እየፎከሩ ፡ ያን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ፊት ፡ መዘው ፡ የፎከሩበትን ፡ ሻሞላ መዘው ፡ ጠላት ፡ መሽጎ ፡ እሚዋጋበት ፡ እሽለቆት ፡ ምሽግ ፡ ድረስ ፡ ገብተው ፡ ከጠላታቸው ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ከጣሉ ፡ በኋላ ፡ በጥይት ፡ ተመተው ፡ ወደቁ ።

ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ታማኝ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክብር ፡ ከጌታቸው ፡ ጋራ ፡ ወደቁ ።

ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ውለታ ፡ ኢትዮጵያና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ሊረሳባቸው ፡ አይችልም ።

ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ ደምሰው ፡ ይህን ፡ ከሠሩ ፡ በኋላ ፡ ሕያው ፡ ሆነው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ያገኙት ፡ ከነበረው ፡ ማዕርግና ፡ ክብር ፡ ይበልጥ ፡ እንደዚሁ ፡ በያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አፍ ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ ሲነገር ፡ ለሚኖረው ፡ ስማቸው ፡ የበለጠ ፡ ማዕርግና ፡ ክብር ፡ መስጠት ፡ የተገባ ፡ ነው ።

# ምዕራፍ ፡ 70 ።

## 2ኛው ፡ የተንቤን ፡ ጦርነትና ፡ የሺሬ ፡ ጦርነት ።

የመዠመሪያው ፡ የተንቤን ፡ ጦርነት ፡ ምንም ፡ ለሁቱለ ፡ ወገን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ የተለየ ፡ ድል ፡ ሳይሰጣቸው ፡ ቢቀር ፡ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ ታላላቅ ፡ ጦርነት ፡ አድርገው ፡ በመጨረሻም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ በዚሁ ፡ በተንቤን ፡ ተሰልፎ ፡ ሁለተኛውን ፡ ጦርነት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ።

ኢጣሊያኖችም ፡ ሁለተኛ ፡ በተንቤን ፡ ጦርነት ፡ ሲያደርጉ ፡ አምባ ፡ አራዳም ፡ ያለው ፡ የራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ ጦር ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ መጥቶ ፡ ድል ፡ እንዳያደርጋቸው ፡ የተንቤንን ፡ ጦር ፡ እንዳለ ፡ ትተው ፡ በመዠመሪያ ፡ የአምባ ፡ አራዳምን ፡ ስፍራ ፡ በጦርነት ፡ ያዙ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ያኸል ፡ ዕረፍት ፡ እንዳደረጉ ፡ ቀጥለው ፡ ሁለተኛ ፡ በተንቤን ፡ ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ የሁለት ፡ ዲቪዚዮን ፡ ወታደር ፡ ለየብቻው ፡ አንዱ ፡ በአላጌ ፡ አቅጣጫ ፡ ሁለተኛው ፡ በዐቢይ ፡ ዐዲ ፡ መንገድ ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ ኃየላ ፡ ተጓዘ ።

ልውል ፡ ራስ ፡ ካሳና ፡ ልውል ፡ ራስ ፡ ሥዩምም ፡ በመዠመሪያው ፡ የተንቤን ፡ ጦርነት ፡ አብረዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ከነርሱም ፡ በስተቀር ፡ እነደጃዝማች ፡ በየነ ፡ ሀብተ ፡ ማርያምን ፡ እነደጃዝማች ፡ ኀይሉ ፡ ከበደን ፡ እነደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ይልማን ፡ ይዘው ፡ ለውጊያ ፡ ተሰልፈው ፡ ነበር ። የውጊያውም ፡ ስፍራዎች ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ፓሶ ፡ ዋሪዩው ፡ የሚሉትና ፡ ቀጨም ፡ መልፋ ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ስፍራዎች ፡ ለጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የሚረዱ ፡ በሮችና ፡ መንገዶች ፡ ስለ ፡ ነበሩባቸው ፡ የሁለቱም ፡ ወገን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ እነዚህኑ ፡ መንገዶች ፡ ለመያዝ ፡ ታላቅና ፡ የበረታ ፡ ጦርነት ፡ አደረጉ ። ጦርነቱም ፡ ከየካቲት ፡ 11 ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ የካቲት 15 ፡ ቀን ፡ ቈይቶ ፡ የፈራረቃ ፡ ድል ፡ ካገኙ ፡ ወዲህ ፡ እንደዚሁ ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በቦምብና ፡ በጋዝ ፡ ጭስ ፡ በታንክ ፡ እየተረዳ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፍቶ ፡ ከእጅ ፡ መሣሪያ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ የሌለውን ፡ የኢትየጵያን ፡ ወታደር ፡ እያጠፋ ፡ ጒዞውን ፡ ይቀጥል ፡ ዠመር ።

በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ልውል ፡ ራስ ፡ ካሳና ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ እንደሚገባቸው ፡ ከተከላከሉ ፡ በኋላ ፡ ትርፉ ፡ ሰው ፡ ማስጨረስ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የተረፈውን ፡ ወታደራቸውን ፡ እየያዙ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ለመዋጋት ፡ ሄዱ ።

በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮችና ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡ እየተፋከሩ ፡ እጦርነቱ ፡ መካከል ፡ እየገቡ ፡ ተዋግተው ፡ በዠግንነት ፡ ተባብረው ፡ ወደቀ ። ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ወልዴም ፡ በዚሁ ፡ ጦርነት ፡ ሲዋጉ ፡ ቈስለው ፡ ነበርና ፡ በመጋቢት ፡ 16 ፡ ቀን ፡ ዐረፉ ። ይልቁንም ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ባ1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ መስከረም ፡ 17 ፡ ቀን ፡ በተደረገው ፡ የመስቀል ፡ በዓል ፡ እግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ባማረ ፡ ሠጋር ፡ በቅሎ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተንቆራጠጡ ፡ ፍከራቸውን ፡ ሲደቀድቁት ፡ «በዲፕሎማቲክ ፡ በኩል ፡ እንዳልረዳኸ ፡ ዕውቀቴ ፡ ያነሰ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በደሜ ፡ እክስኻለሁ» ፡ ብለው ፡ ተናግረው ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ በዚህ ፡ በተንቤን ፡ ጦርነት ፡ የቀረው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከቦምብና ፡ ከጋዝ ፡ መርዝ ፡ ከታንክ ፡ ጋራ ፡ ሲዋጋ ፡ ኖሮ ፡ ገሚሱ ፡ እዚያው ፡ አልቆ ፡ ሲመለስ ፡ እኔ ፡ በየነ ፡ ጠላቴን ፡ በፊቴ ፡ አስቀምጬ ፡ ልመለስ ፡ አልችልም ፡ ብለው ፡ በመዠመሪያ ፡ በመትረየስና ፡ በመድፍ ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ተዋግተው ፡ ሲጨርሱ ፡ ወዲያው ፡ ጐራዴያቸውን ፡ መዘው ፡ መድፍና

፡ መትረየስ ፡ ከያዙት ፡ ጣሊያኖች ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ በጥይት ፡ ተመተው ፡ ወድቀው ፡ የመጨረሻ ፡ ትንፋሻቸውን ፡ እስኪተነፍሱ ፡ ድረስ ፡ በሳንጃ ፡ ሊወጓቸው ፡ የሚቃጡትን ፡ ኢጣሊያኖች ፡ በቅልጥፍና ፡ እየቀደሙ ፡ ብዙዎቹን ፡ ጥለው ፡ ርሳቸውም ፡ በመጨረሻ ፡ ወደቁ ።

ይህ ፡ ሁለተኛው ፡ የተንቤን ፡ ጦርነት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ሽሬ ፡ ካለው ፡ ከራስ ፡ እምሩ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ የኢጣሊያ ፡ ወታደር ፡ እንደዚሁ ፡ ውጊያ ፡ እንዲያደርግ ፡ የጦር ፡ አዛዡ ፡ ትእዛዝ ፡ አስተላልፎ ፡ ነበር ።

የራስ ፡ እምሩ ፡ ጦር ፡ በመዠመሪያ ፡ ደምበጉና ፡ ላይ ፡ ኢጣሊያኖችን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ አባሮ ፡ እስከ ፡ ሺሬ ፡ ከተማ ፡ እስከ ፡ ሰለክላካ ፡ ደርሶ ፡ ነበር ። ይህም ፡ የራስ ፡ እምሩ ፡ ጦር ፡ ያለበት ፡ ርቀቱ ፡ ከአኵስም ፡ 25 ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በተንቤን ፡ ጦርነቱ ፡ ተፋፍሞ ፡ በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ እነራስ ፡ ካሳን ፡ ለመርዳት ፡ ከሽሬ ፡ ወደ ፡ ተንቤን ፡ እንዳይመጡ ፡ ወዲያው ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ሽሬ ፡ ሄዶ ፡ ጦርነት ፡ እንዲያደርግ ፡ ታዘዘ ። ሌላውም ፡ የጦር ፡ ስፍራ ፡ ከሰለክላካ ፡ በስተምዕራብ ፡ ብዙ ፡ መንገድ ፡ በሚመሳቀልበት ፡ በቆይዳ ፡ አጠገብ ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለመግፋት ፡ ሲያስቡ ፡ ራሳቸው ፡ ኢጣሊያኖች ፡ እንደ ፡ መሰከሩላቸው ፡ ብልኀት ፡ ባለው ፡ የጦር ፡ ዐቅድ ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ጠላትን ፡ እየተቋቋሙ ፡ መለሱ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ተለመደ ፡ ግንባር ፡ ቀደሙ ፡ የእግረኛ ፡ ወታደር ፡ ጦርነት ፡ በሚያደርግበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የኢጣሊያ ፡ ቦምብ ፡ ጣይ ፡ አይሮፕላኖች ፡ እየመጡ ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ እያጕረመረሙ ፡ ቦምብና ፡ የጋዝ ፡ መርዝ ፡ ሲነዙባቸው ፡ ገሚሶቹ ፡ ወታደሮች ፡ ነፍሳቸውን ፡ ላገራቸው ፡ ነፃነት ፡ እየሰጡ ፡ ሕይወታቸውን ፡ በዚያው ፡ በጦርነቱ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ሠዉ ።

የቀሩት ፡ ግን ፡ ከላይና ፡ ከታች ፡ ከሚውዘገዘገው ፡ ከእሳተ ፡ ነበልባል ፡ የተነሣ ፡ እየተሸበሩ ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ወደ ፡ ተከዜ ፡ በመመለሳቸው ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፍቶ ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ይሠጋበት ፡ የነበረውን ፡ የሺሬን ፡ አገር ፡ ያዘ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ በተከዜ ፡ ሳሉ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩምና ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ በጅሮንድ ፡ ለጥ ፡ ይበሉ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ይልማ ፡ ወደ ፡ አሸንጌ ፡ ሄደው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ የመጨረሻውን ፡ ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ ከአምባ ፡ አራዳም ፡ ጦርነት ፡ የተረፉትም ፡ እነሻለቃ ፡ ዳኘ ፡ ወዳጄ ፡ ሁሉ ፡ ኣብረው ፡ ሄደው ፡ ተደባለቁ።

# ምዕራፍ ፡ 71 ።

## ክቡር ፡ ራስ ፡ ደስታና ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ መርድ ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ያደረጉት ፡ ጦርነት ።

በ60 ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ በታንክና ፡ በቦምብ ፡ እየተረዳ ፡ ሰሰበኒን ፡ ገርሎግቢን ፡ ቆራሔን ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ ጦርነቱን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለመቀጠል ፡ ይዘጋጅ ፡ ነበር ።

ከመቃዲሾ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ የሚያስመጣው ፡ በሁለት ፡ በኩል ፡ ነው ።

እንደኛው ፡ ከመቃዲሾ ፡ በለደ ፡ ወይን ፡---ቆራሔ ፡---ደጋሀቡር ፡---ጅጅጋ ፡---ሐረር ፡ አዲስ ፡ አበባ ።

ሁለተኛው ፡ ከመቃዲሾ ፡--- በይደዋ ፡--- ሉክ ፡--- ዶሎ ፡---ነገሌ ፡---ይርጋ ፡ ዓለም ፡--- ሞጆ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ነው ።

የግራዚያኒ ፡ ጦር ፡ ዋና ፡ ሐሳቡ ፡ በቆራሔና ፡ በደጋሀቡር ፡ በኩል ፡ አልፎ ፡ ሐረርጌን ፡ ለመያዝ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ጅጅጋ ፡ በሚያመራበት ፡ ጊዜ ፡ የራስ ፡ ደስታ ፡ ጦር ፡ በዠርባው ፡ በኩል ፡ አልፎ ፡ ሱማሊያን ፡ እንዳይወርበት ፡ በቆራሔ ፡ ግንባር ፡ ተከላካይ ፡ ወታደር ፡ ብቻ ፡ አስቀምጦ ፡ ዋናውን ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ዶሎ ፡ ሄዶ ፡ እንዲከላከል ፡ አደረገ ።

ክቡር ፡ ራስ ፡ ደስታም ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ኣሽከሮቻቸውን ፡ ፊታውራሪ ፡ አደመንና ፡ ፊታውራሪ ፡ ታደመን ፡ እፊት ፡ አስቀድመው ፡ ርሳቸው ፡ በኋላ ፡ ደጀን ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየገፉ ፡ እስከ ፡ ኢጣሊያ ፡ ግዛት ፡ እስከ ፡ ዶሎ ፡ ጫፍ ፡ ደርሰው ፡ ነበር ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ሱማሊያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ፍርሃት ፡ ተነዝቶ ፡ ነበር ።

በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ግራዚያኒ ፡ በሱማሊያ ፡ ያለው ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ጦር ፡ የሚበቃኝ ፡ አይደለምና ፡ ሌላ ፡ ረዳት ፡ ላኩልኝ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ሙሶሊኒና ፡ ወደ ፡ ባዶሊዮ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ቴሌግራም ፡ ያስተላልፍ ፡ ነበር። ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በሱማሊያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በመቃዲሾ ፥ በሜርካ ፥ በጀናሌ ፥ በአውደግሌ ፥ በቡሎ ፥ ቡርቲ ፡ በበለደ ፡ ወይንና ፡ በሌላውም ፡ በየመንደሩ ፡ ነዋሪ ፡ ሱማሌዎችን ፡ ባዋጅ ፡ እየሰበሰበ ፡ ይኸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሱማሊያን ፡ ለመውረር ፡ ተሰልፈዋል ። እኛም ፡ እንደሚገባ ፡ ተዋግተን ፡ ድል ፡ የሆንን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመርከባችን ፡ ተሳፍረን ፡ ወዳገራችን ፡ እናመልጣለን ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ የምትሄዱበት ፡ ስፍራ ፡ የላችሁምና ፡ በወረሯችሁ ፡ ጊዜ ፡ ወንዶቻችን ፡ እየሰለቡ ፡ ሴቶቻችን ፡ ጡታቸውን ፡ እየቈረጡ ፡ ይበሉታል ፡



ክቡር ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ።

ምግባቸውም ፡ የሰው ፡ ሥጋ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እኛ ፡ ድል ፡ ሳንሆን ፡ ነጋዴ ፡ ነን ፡ ገበሬ ፡ ነን ፡ ሳትሉ ፡ ባንድነት ፡ እንዋጋ ፡ እያለ ፡ ሐሰት ፡ የመላበትን ፡ ወሬ ፡ እየዞረ ፡ ይሰብክ ፡ ያሰብክ ፡ ነበር ። የሱማሊያ ፡ ሕዝብም ፡ እውነት ፡ እየመሰለው ፡ ገበሬውም ፡ ነጋዴውም ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ መጋዘን ፡ እየቀረበ ፡ ስሙን ፡ እያጸፈ ፡ ብረት ፡ እየተቀበለ ፡ በሃይማኖት ፡ ከሚመስሉት ፡ ከሊቢያ ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ለውጊያ ፡ ተሰለፈ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የባሌ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ መርድ ፡ ጦራቸውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ከጊንር ፡ ወደ ፡ ዋቢ ፡ ሸበሌና ፡ ወደ ፡ ባረይ ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ።

ከኢጣሊያ ፡ ወገን ፡ ወሎል ፡ ጂሌ ፡ ብዙ ፡ የሱማሊያን ፡ ወታደሮችና ፡ የራሱን ፡ ሰዎች ፡ ይዞ ፡ በጥቂቶች ፡ ኢጣሊያኖች ፡ መሪነት ፡ በድምሩ ፡ 7 ፡ ሺህ ፡ ወታደር ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይጓዝ ፡ ነበር ።

ወሎል ፡ ጂሌም ፡ በእግረኛ ፡ ወታደር ፡ የደጃዝማች ፡ በየነን ፡ ጦር ፡ ለመግጠም ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ ውጊያውን ፡ ወዲያው ፡ ሲዠምር ፡ ብዙ ፡ ኣይሮፕላን ፡ መጥቶ ፡ እንዲረዳው ፡ ለግራዚያኒ ፡ ልኮ ፡ ነበር ። ግራዚያኒም ፡ በእግር ፡ በቶሎ ፡ ግጠም ፡ እንጂ ፡ አይሮፕላኖቹ ፡ ወዲያው ፡ ይደርሱልኻል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ላከበት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታኅሣሥ ፡ 17 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጦርነቱ ፡ ተዠመረ ። እንደ ፡ ተባለውም ፡ የእግረኛው ፡ ወታደር ፡ ገጥሞ ፡ ሲዋጋ ፡ 19 ፡ አይሮፕላኖች ፡ 7 ፡ ቶን ፡ ክብደት ፡ ያለው ፡ የሚያቃጥል ፡ ቦምብ ፡ በደጃዝማች ፡ በየነ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ነዙበት ። ደግሞም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጦር ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ በቦምብና ፡ በመትረየስ ፡ ለመምታታት ፡ እንዲመቻቸው ፡ ዝቅ ፡ ብለው ፡ ሲተኩሱ ፡ ካ19ኙ ፡ አይሮፕላኖች ፡ አንደኛውም ፡ ሳይቀር ፡ ሁሉም ፡ ተመቱ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ 1ዱ ፡ አይሮፕላን ፡ ብቻ ፡ ወድቆ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ እጅ ፡ ሲገባ ፡ 18ቱ ፡ እንደ ፡ ተመታ ፡ በረው ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ለመመለስ ፡ ቻሉ ።

እግረኛውም ፡ ጦር ፡ ሲዋጋ ፡ ከወሎል ፡ ጂሌ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ 300 ፡ ሱማሊያዎች ፡ ከድተው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጡ ። በተረፈ ፡ ከደጃዝማች ፡ በየነም ፡ ከኢጣሊያን ፡ ባንዶችም ፡ ወገን ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ወሎል ፡ ጂሌ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመለሰ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የግራዚያኒ ፡ ጦር ፡ በብዙ ፡ ጄኔራሎች ፡ እየተመራ ፡ በዶሎ ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ነገሌ ፡ አቅጣጫ ፡ ያመራ ፡ ዠመር ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የክቡር ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ጦር ፡ በፊታውራሪ ፡ ዐደመና ፡ በፊታውራሪ ፡ ታደመ ፡ በሙሳ ፡ ሳባ ፡ እየተመራ ፡ በጎንሩ ፡ በጋልጋሎ ፡ በቦኅል ፡ ማኞ ፡ በቃሌቻ ፡ በፊልቱ ፡ ተሰልፎ ፡ ነበር ።

ጦርነቱም ፡ ከመዠመሩ ፡ አስቀድሞ ፡ የኢጣሊያ ፡ ሰላይ ፡ አይሮፕላኖች ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሣሪያና ፡ ጦር ፡ የሰፈረበትን ፡ ነገሌንና ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ለውጊያ ፡ የተሰለፈበትን ፡ እየመረመሩ ፡ ሲመለሱ ፡ ወዲያው ፡ በምብ ፡ ጣይ ፡ አይሮፕላኖች ፡ እየመጡ ፡ ነገሌንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጦር ፡ በታላላቅ ፡ ቦምብ ፡ ሲደበድቡት ፡ ዋሉ ። የኛም ፡ ወታደሮች ፡ ሽቅብ ፡ በአይሮፕላኑ ፡ እየተኰሱ ፡ አንድ ፡ አይሮፕላን ፡ ሲጥሉ ፡ የቀሩትንም ፡ ደግሞ ፡ ጉድተዋቸዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የራስ ፡ ደስታ ፡ ተዋጊ ፡ ወታደሮች ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ጥር ፡ 1 ፡ ቀን ፡ ዠምረው ፡ እስከ ፡ ጥር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሲዋጉ ፡ በጠላታቸው ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ጉዳት ፡ አደርገው ፡ ሰነበቱ ፡ ። በመጨረሻም ፡ ራሳቸው ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ከሰሜን ፡ ከተላኩት ፡ ከደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ጋራ ፡ ተባብረው ፡ ሲዋጉ ፡ የኢጣሊያ ፡ አይሮፕላኖችና ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱም ፡ እየተዋጉ ፡ መልሰው ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ አድርገዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የኋለኛው ፡ ደጀን ፡ በቦምባ ፡ ተደብድቦ ፡ ሲበታተን ፡ እመዠመሪያው ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ያሉት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ያሉበትን ፡ ስፍራ ፡ ሳይለቁ ፡ ሙያቸውን ፡ ሲዋጉ ፡ ውለው ፡ በመጨረሻም ፡ ሕይወታቸውን ፡ እዚያው ፡ እምሽጋቸው ፡ ላይ ፡ በዠግንነት ፡ አሳለፉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሞት ፡ የተረፈው ፡ ሳይዋጋ ፡ ሥንቅ ፡ መቸገርን ፡ እያመካኘ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ሲመለስ ፡ የኢጣሊያ ፡ አይሮፕላኖች ፡ እየተከታተሉ ፡ በጭካኔ ፡ ይደበድቡት ፡ ዠመር ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይም ፡ ስሜን ፡ ሆነው ፡ ይኸንኑ ፡ የወታደሩን ፡ መመለስ ፡ ሰምተው ፡ ነበርና ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ላኩባቸው ።

« ይህ ፡ ዓለም ፡ ኀዘንና ፡ ደስታ ፡ የተቀላቀለበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ 1 ፡ ቀን ፡ ሲበረታ ፡ 1 ፡ ቀንም ፡ ሲደክም ፡ ነው ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ እበረሃ ፡ ወርደኸ ፡ ለጦር ፡ ለበሽታ ፡ ለቦምብ ፡ መመከትኸን ፡ በየጊዜው ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ አስታውቆኛል ። እንኳን ፡ ለግዛትኸ ፡ ለሌላው ፡ አገር ፡ ተርፈኸ ፡ ሥራ ፡ የምትሠራውን ፡ እንዴት ፡ ጠላት ፡ ሲዳሞን ፡ ወንድ ፡ እንደሌለበት ፡ አድርጎ ፡ ይግባበት ፡ አሁንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንኳን ፡ ወታደር ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ለብረት ፡ የደረሰኸ ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ አስታወቀኸ ፡ ድረስ ፡ ከተሸ ፡ ርዳ ፡ ጥር 1928 ፡ ዓ ፡ ም» ።

ይኸንንም ፡ የመሰለ ፡ ዐዋጅና ፡ የሚያበረታ ፡ ቃል ፡ ለባሌ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ አስተላለፉ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ በቦምብና ፡ በጋዝ ፡ መርዝ ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፍቶ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ 2ኛ ፡ ለመግጠም ፡ ያሰበ ፡ አልነበረምና ፡ ሁሉም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሸሸ ።

ግራዚያኒም ፡ በጦርነቱ ፡ ሰዓት ፡ እኋላ ፡ ሆኖ ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ ሲጠባበቅ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ድል ፡ አድርገናል ፡ ብለው ፡ በጦርነቱ ፡ ግንባር ፡ የነበሩት ፡ ጄኔራሎች ፡ ላኩበት ። እሱም ፡ ካለበት ፡ ተነሥቶ ፡ ተዋግተውበት ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ስፍራ ፡ ሄዶ ፡ የሞቱትን ፡ ኢጣሊያኖችና ፡ ሱማሌዎች ፡ የሊቢያንም ፡ ዐረቦች ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ በምሽጋቸው ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ተነባብረው ፡ የወደቁትን ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ሬሳ ፡ እየዞረ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ከዠግንነታቸው ፡

የተነሣ ፡ በጣም ፡ ተደነቀ ። በዠግንነት ፡ ተዋግተው ፡ ለወደቁትም ፡ ለቀኛዝማች ፡ መኩሪያ ፡ ተሰማ ፡ ለሬሳቸው ፡ የሚገባ ፡ የክብር ፡ ሰላምታ ፡ ሰጣቸው ።

በዚሁ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ሆነን ፡ አገራችንን ፡ አንወጋም ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ የኤርትራ ፡ ወታደሮች ፡ ከሰሜንም ፡ ከደቡብም ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ከጠላት ፡ ተለይተው ፡ መጥተው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጋራ ፡ ተደባለቁ ። ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ ስማቸውን ፡ ያገኘነው ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ፡- | ፊታውራሪ ፡ ጸጋይ ፡ ንጉሤ ፡ | የሞተ ፡ |
| 2ኛ፡- | ቀኛዝማች ፡ ሰለባ ፡ | >> |
| 3ኛ፡- | >> አንዶም ፡ | >> |
| 4ኛ፡- | >> ኣሰፋ ፡ ባሕታ | >> |
| 5ኛ፡- | ግራዝማች ፡ ሥዩም ፡ ሰሎሞን ፡ | >> |
| 6ኛ፡- | ባላምባራስ ፡ ሀብቱ ፡ ኀይሉ | >> |
| 7ኛ፡- | የመቶ ፡ አለቃ ፡ ስብሐቱ ፡ ተሰፋ ፡ ሚካኤል | >> |
| 8ኛ፡- | >> >> ነጋር ፡ አብ ፡ | >> |
| 9ኛ፡- | >> >> ተከሎም ፡ | >> |
| 10ኛ፡- | >> >> ሀብቱ ፡ | >> |
| 11ኛ፡- | ሻምበል ፡ ማና ፡ | >> |
| 12ኛ፡- | >> ተክሌ ፡ | >> |
| 13ኛ፡- | >> ተሰፋ ፡ ሚካኤል | >> |
| 14ኛ፡- | የመቶ ፡ ኣለቃ ፡ ካሕሳይ ፡ | >> |
| 15ኛ፡- | መቶ ፡ ኣለቃ ፡ ዘርዐ ፡ ጋብር ፡ | ያለ |
| 16ኛ፡- | ባሻይ ፡ ኤልያስ ፡ | >> |
| 17ኛ፡- | ወታደር ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ | >> |
| 18ኛ፡- | >> ገብረ ፡ ወልድ ፡ ሃምቢር ፡ | >> |
| 19ኛ፡- | አምሳ ፡ አለቃ ፡ ዘሙይ ፡ | >> |
| 20ኛ፡- | ወታደር ፡ በርሄ ፡ ኀደጉ ፡ | >> |
| 21ኛ፡- | >> ተክለ ፡ ሐደራ ፡ | >> |
| 22ኛ፡- | >> ስብሐቱ ፡ ባራኺ ፡ | >> |

23ኛ፡->> በረከት ፡ አብ ፡ >>
24ኛ፡->> ተክለ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ >>

1ኛ-፤ ሌተና ፡ ኮሎኔል ፡ ገብራይ ፡ ያለ
2ኛ-፤ ሻምበል ፡ ረዳ ፡ ተክሌ ፡ >>
3ኛ-፤ >> አርኣያ ፡ ሰሎሞን ፡ >>
4ኛ-፤ >> ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ክንፉ ፡ >>
5ኛ-፤ >> በርሄ ፡ አርኣያ ፡ >>
6ኛ-፤ >> ዝግታ ፡ መሓሪ ፡ >>
7ኛ-፤ >> ዑቅባ ፡ ሚካኤል ፡ >>
8ኛ-፤ >> ገብረ ፡ ጻድቅ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ >>
9ኛ-፤ >> ሥዩም ፡ ደረስ ፡ >>
10ኛ-፤የሻምበል ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ መንግሥቴ ፡ >>
11ኛ-፤ሰ>> ሎሞን ፡ >>
12ኛ-፤>> ደበሳይ ፡ >>
13ኛ-፤የመቶ ፡ አለቃ ፡ ነጋሽ ፡ ተፈሪ ፡ >>
14ኛ-፤>> >> ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ መሓሪ ፡ >>
15ኛ-፤>> >> አርኣያ ፡ ዘወልዴ ፡ >>
16ኛ-፤>> >> መሐመድ ፡ ግደይ ፡ >>
17ኛ-፤ >> >> በርሄ ፡ ተግባሩ ፡ >>
18ኛ-፤>> >> አብርሀ ፡ በየነ ፡ >>
19ኛ-፤>> >> ኀይሌ ፡ በየነ ፡ >>
20ኛ-፤>> >> ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ >>
21ኛ-፤>> >> መብርሀቱ ፡ >>
22ኛ-፤መቶ ፡ ኣለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልደየስ ፡ >>
23ኛ-፤>> >> ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ግደይ ፡ >>

# ምዕራፍ ፡ 72 ።

## የውጋዴን ፡ ጦርነት ።

በውጋዴን ፡ ግንባር ፡ በክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ነሲቡ ፡ ዛማኔል ፡ አበጋዝነት ፡ በውሂብ ፡ ባሻ ፡ አማካሪነት ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸውና ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ዐምደ ፡ ሚካኤል ፡ ከጅጅጋ ፡ በስተደቡብ ፡ በሐርጌሳ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ በሰሰበኔ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡ በይጋሜዳ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ የየራሳቸውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር ።

እንደዚሁ ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ አራት ፡ ላይ ፡ ተከፍሎ ፡ 1ኛውና ፡ 2ኛው ፡ ክፍል ፡ በጄኔራል ፡ ናዚና ፡ በጄኔራል ፡ ናባራ ፡ እየታዘዘ ፡ በጃናቆቦ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ይጋሜዳ ፡ 3ኛው ፡ በጄኔራል ፡ ፍሩሺ ፡ እየታዘዘ ፡ ከቀብሪደሐር ፡ ተነሥቶ ፡ በሐማንለይ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ደጋሀቡር ፡ 4ኛው ፡ ክፍል ፡ በጄኔራል ፡ አጎስቲን ፡ እየታዘዘ ፡ ከዋርደር ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ደጋሀቡር ፡ ይጓዝ ፡ ነበር ። ለነዚሁም ፡ የጦር ፡ ሠራዊቶች ፡ በኋላቸው ፡ እንደ ፡ ደጀን ፡ ሆነው ፡ የሚጠብቋቸው ፡ በሌሎች ፡ ጄኔራሎች ፡ የሚታዘዙ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቶች ፡ ነበሩ ።

እንደ ፡ ተለመደ ፡ የእግረኛ ፡ ጦርነት ፡ ከመደረጉ ፡ ኣስቀድሞ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኀይል ፡ በአየር ፡ ጦርነት ፡ ለመስበር ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ ሰላዮች ፡ አይሮፕላኖች ፡ ተነሥተው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሰፈር ፡ ላይ ፡ እያንዣበቡ ፡ የኢትዮጵያም ፡ ጦር ፡ ሰፍሮ ፡ የተቀመጠበትን ፡ ወይም ፡ ከሰፈሩ ፡ ተቀስቅሶ ፡ የሚያመራበትን ፡ አቅጣጫና ፡ የሠራዊቱን ፡ መጠን ፡ ጭምር ፡ በግምት ፡ እየሰለሉ ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ በምብ ፡ የጫኑ ፡ አይሮፕላኖች ፡ እየተነሡ ፡ሄደው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሠራዊት ፡ ይደበድቡ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠውና ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ ግንኙነት ፡ አድርገው ፡ ለመከላከል ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወደ ፡ ጃንቆቦና ፡ ወደ ፡ ኮራቅ ፡ ይጓዙ ፡ ዠመር ። ወዲያው ፡ የኢጣሊያጦር ፡ ደናን ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ተጉዞ ፡ ጦርነቱ ፡ ኮራቅ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሚያዝያ ፡ 10 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ትዠምሮ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በታላቅ ፡ ኃይል ፡ ይዋጉ ፡ ዠመር ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ፡ ወዲያው ፡ ናዚና ፡ ናባራ ፡ በጦርነቱ ፡ ለመድከም ፡ ቅርብ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ ጄኔራል ፡ ፍሩሽ ፡ የታዘዘበትን ፡ አቅጣጫ ፡ ትቶ ፡ ጦር ፡ በበረታበት ፡ በዚህ ፡ ግንባር ፡ በኩል ፡ መጥቶ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ለዠግንነት ፡ ምሳሌ ፡ መሆን ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ ፊታውራሪ ፡ ሚሊዮን ፡



ደጃዝማች ፡ ነሲቡ ፡ ዛማኤል



ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው



ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው

ሌሎችም ፡ ደጃዝማቾች ፡ በኮራቅ ፡ በደጋሜይ ፡ በጃንቆቦ ፡ በቢርኩት ፡ በደጋህቡር ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ እየመላለሱ ፡ ሲዋጉ ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ አለቀ ።

በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ 29 ፡ የሚሆኑ ፡ የኢጣሊያ ፡ አይሮፕላኖች ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጦር ፡ ከመዋጋቱ ፡ በፊት ፡ በሚዋጋበትም ፡ ጊዜ ፡ ከተዋጋም ፡ በኋላ ፡ ያለዕረፍት ፡ እየተመላለሱ ፡ በቦምብና ፡ በመትረየስ ፡ ሲፈጁት ፡ ዠግናውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ በያዘው ፡ ብረት ፡ እየተኰሰ ፡ ከአይሮፕላኖቹ ፡ መካከል ፡ እየነጠለ ፡ ያወርድ ፡ ዠመር ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ጅጅጋን ፡ በቦምብ ፡ ለመምታት ፡ መጥቶ ፡ በጠመንዣ ፡ ተመቶ ፡ 1 ፡ አይሮፕላን ፡ ከወደቀ ፡ በኋላ ፡ ከብታቸው ፡ በቦምብ ፡ ያለቀባቸው ፡ ባላገሮች ፡ አግኝተው ፡ አንገቱን ፡ ቈርጠው ፡ በገደሉት ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ አይሮፕላኖች ፡ በቦምብና ፡ በመትረየስ ፡ ፈንታ ፡ የጋዝ ፡ ጭስ ፡ እየጫኑ ፡ መጥተው ፡ በዚህ ፡ በጋዝ ፡ ጭስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደማይረሳው ፡ ያኸል ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጦር ፡ ያለርኅራኄ ፡ ፈጁት ፡ <u>የጋዝ ፡ ጭስ ፡ መጣላቸውን ፡ ራሳቸው ፡ ኢጣሊያኖች ፡ አልካዱም ፡ ግራዚያኒ ፡ የጻፈውን ፡ ( የደቡብ ፡ ግንባር) ፡ የሚለውን ፡ መጽሐፍ ፡ 220 ፡ ገጽ 30ኛውን ፡ መሥመር ፡ ተመልከት ።</u>

በውጋዴን ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ ከጠላቱ ፡ ሲጋደል ፡ በሰሜን ፡ ያለው ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ እንደዚሁ ፡ በዠግንነት ፡ በኩል ፡ ሳይሆን ፡ በቦምብና ፡ በጋዝ ፡ ጉልበት ፡ ገፍቶ ፡ ደሴ ፡ መድረሱ ፡ ተሰማ ። ይህም ፡ ወሬ ፡ በደቡብ ፡ ያለውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጦር ፡ ሲያሳዝን ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ ደስ ፡ ስላሰኘ ፡ ግራዚያኒ ፡ ያለውን ፡ የመጠባበቂያ ጦር ፡ እየጨመረ ፡ የሚቋቋመውን ፡ በመሬትም ፡ በአየርም ፡ እየመታ ፡ በመዠመሪያ ፡ ደጋህቡርን ፡ ከዚያም ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ቈየ ፡ ጅጅጋን ፡ ያዘ ።

# **ምዕራፍ ፡ 73 ።**

## <u>የማይጨው ፡ ጦርነት ።</u>


ቅኝ ፡ አገር ፡ የጠማው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥትና ፡ የቈየ ፡ ነፃነቱን ፡ በዠግንነት ፡ እየተዋጋ ፡ ማዳን ፡ የለመደው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጠባቸው ፡ ከጥንት ፡ የቈየ ፡ ነው ። የሁለቱም ፡ መንግሥት ፡ ወታደሮች ፡ ከ፳ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ በየጊዜው ፡ ተዋግተው ፡ ከኵዓቲት ፡ በስተቀር ፡ የመጨረሻው ፡ ድል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ሰሓጢና ፡ ደጓዓሊ ፡ ዐድዋና ፡ መቀሌ ፡ ከአምባ ፡ አላጌ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ይመሰክራሉ ። ራስ ፡ ኣሉላና ፡ ቶማሶ ፡ ዲክሪስቶፎርስ ፡ ጄኔራል ፡ ባራቲዬሪና ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ማጆር ፡ ቶሊና ፡ ራስ ፡

መኰንን ፡ ሞተዋል ። እነዚህ ፡ ስፍራዎች ፡ ግን ፡ ሰማይና ፡ መሬት ፡ አልፎ ፡ እነሱም ፡ በመሬትነታቸው ፡ እስኪያልፉ ፡ ድረስ ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ጉብዝና ፡ ሲመሰክሩ ፡ ይኖራሉ ።

በዚህ ፡ እላይ ፡ በተባለው ፡ ጦርነት ፡ በሁለተ ፡ ወገን ፡ እጅ ፡ ያለው ፡ መሣሪያ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ በመሆኑ ፡ ድል ፡ ያደርግ ፡ የነበረው ፡ ወኔ ፡ (ጉብዝና) ፡ ያለው ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እነዚያው ፡ ወኔ ፡ ያላቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እየመላለሱ ፡ ጠላታቸውን ፡ ድል ፡ አደረጉ ።

ስለዚህ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በዓርባ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ በጉብዝና ፡ የመለሰውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወታደር ፡ በምን ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ እንደሚችል ፡ አስቦ ፡ በብሬሺያ ፡ በቶሪኖ ፡ ፋብሪካ ፡ ቤቶች ፡ ከሌላው ፡ መንግሥት ፡ እያስተያየ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቦምብ ፡ በማደራጀት ፡ ኖረ ።

ቦምቡንም ፡ ከጋዝ ፡ መርዝ ፡ ጋራ ፡ በስውር ፡ አዘጋጅቶ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ይኸን ፡ በሚያዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ችላ ፡ ለማሰኘት ፡ በቀጥታ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ በኩል ፡ ያደረገውን ፡ ውልና ፡ መሐላ ፡ አፈረሰ ። የውሉንና ፡ የመሐላውንም ፡ አንቀጽ ፡ ማኅበሩና ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ደጋግመው ፡ ቢጠቅሱለትም ፡ እንደማያውቀው ፡ ሆኖ ፡ ይኸን ፡ ጦርነት ፡ የሚያደርግበት ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ ይህነን ፡ ባዲስ ፡ ዐይነት ፡ የተዘጋጀውን ፡ መሣሪያና ፡ የቦምብ ፡ ክምር ፡ የጋዝ ፡ መርዙን ፡ ጭምር ፡ በበርሚል ፡ እየመረገ ፡ በመርከብ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ አጉዞ ፡ ወዲያው ፡ ጦርነቱን ፡ ዠመረ ።



የቦምብ ፡ ክምር ።

የኢትዮጵያም ፡ ወታደር ፡ በዐድዋ ፡ በተንቤን ፡ በሽሬ ፡ በእንደርታ ፡ ሆኖ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከሚያስበው ፡ በላይ ፡ የሚርከፈከፈው ፡ የጋዝ ፡ መርዝ ፡ ሊያግዘው ፡ እንጂ ፡ ሊያጠፋው ፡ በማይችለው ፡ በቦምቡ ፡ ነበልባልና ፡ በመድፉ ፡ ፍላጻ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ በተለመደ ፡ ዠግንነቱ ፡ ተከላከለ ፡፡ አንድ ፡ መርዝ ፡ የያዘ ፡ ደካማ ፡ ሰው ፡ ጉራዴ ፡ በጐኑ ፡ ጠመንገግ ፡ በትከሻው ፡ ያነገተውን ፡ ዠግና ፡ ለመግደል ፡ እንደሚችል ፡ እንደዚሁ ፡ በመርዝ ፡ የኢጣሊያ ፡ ወታደር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወታደር ፡ እያጠፋ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፍቶ ፡ እስከ ፡ ማይጨው ፡ ደረሰ ፡፡

በማይጨው ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከሌላው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጋራ ፡ በቀኛዝማች ፡ መኩሪያና ፡ በግራዝማች ፡ ኣበራ ፡ ግዛው ፡ የሚታዘዘውን ፡ የክብር ፡ ዘበኛን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ከተንቤን ፡ ጦርነት ፡ የተመለሱትን ፡ ልዑላን ፡ ራስ ፡ ካሳንና ፡ ራስ ፡ ሥዩምን ፡ ደግሞም ፡አቡነ ፡ ጴጥሮስን ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ከቡራን ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልን ፡ ራስ ፡ ከበደ ፡ መንገሻን ፡ ራስ ፡ ጌታቸው ፡ አባተን ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ይልማን ፡ ደጃዝማች ፡ ወንድ ፡ ይራድን ፡ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ዐማኑኤልን ፡ ደጃዝማች ፡ አበራ ፡ ተድላን ፡ ፊታውራሪ ፡ አሸናፊን ፡ ደጃዝማች ፡ ወንድ ፡ በወሰንን ፡ ደጃዝማች ፡ አበራ ፡ ካሳን ፡ አለ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስንና ፡ ሌሎችንም ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶችና ፡ በፖለቲካና ፡ በምክር ፡ የሚረዱትን ፡ ይዘው ፡ ተሰልፈው ፡ ነበር ፡፡

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የኢጣሊያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በዠግንነት ፡ ሳይሆን ፡ በቦምብና ፡ በጋዝ ፡ መርዝ ፡ በፊትም ፡ በተንቤንና ፡ በእንደርታ ፡ በሺሬ ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ ሕዝባቸውን ፡ እንዳጠፋ ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ በሚያደርጉት ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ የባሰ ፡ እንደሚያደርግ ፡ ቢረዱት ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያለ ፡ ዠግንነቱ ፡ በታሪክ ፡ የታወቀ ፡ መንግሥት ፡ አስቀድሞ ፡ እንደሚገባው ፡ ሳይዋጋ ፡ አገሩን ፡ ለጠላት ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ ዕርቅ ፡ መጠየቅ ፡ አይችልም ፡ ሲሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ሌላ ፡ አዲስና ፡ ስሙ ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚጠራ ፡ ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ ተዘጋጁ ፡፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጦርነቱ ፡ ከመዠመሩ ፡ በፊት ፡ የጦር ፡ ሽማምንቶቸ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ባሉበት ፡ ተሰብስበው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ በጽሕፈት ፡ ከጃንሆይ ፡ ተቀበሉ ፡፡

« ስንኳን ፡ ይህ ፡ ያሁኑ ፡ የመጨረሻው ፡ የታላቁ ፡ ጠላታችን ፡ ጦርነትና ፡ የአውሬ ፡ ኣደን ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ቈራጥ ፡ ለመሆን ፡ ከቂም ፡ ከበቀል ፡ መራቅ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ፡፡

ለጦር ፡ የቀረበ ፡ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ባለፈው ፡ ሁለት ፡ ልብ ፡ በሆነው ፡ ወታደር ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈረደበትን ፡ አይታችኋልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈርድብኛል ፡ ብሎ ፡ ልቡን ፡ ታዛቢ ፡ አድርጎ ፡ ሥራ ፡ ካልሠራ ፡ በነጂና ፡ በትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡፡ ቈርጦ ፡ ካልሠሩ ፡ ሲሸሹም ፡ መሞት ፡ አለ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የሚረዳው ፡ ልቡ ፡ ለቈረጠ ፡ ጨክኖ ፡ ለሠራ ፡ ነውና ፡ ስላገራችሁ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የነፃነቷ ፡ ባንዲራ ፡

እንዳይቀደድ ፡ ግዝቱን ፡ ጥሳችሁ ፡ ሞት ፡ ላይቀር ፡ የነፍሳችሁንም ፡ የሥጋችሁንም ፡ ዋጋ ፡ አበላሽታችሁ ፡ አትሙቱ።

አለቃዬ ፡ ሸሸ ፡ ሞተ ፡ ሬሳ ፡ ቁስለኛ ፡ አነሣለሁ ፡ ማለት ፡ ለቁስለኛው ፡ አዝኖ ፡ አይደለም ። አለቃው ፡ ሲሞት ፡ ጠንክሮ ፡ የተዋጋ ፡ አንዱ ፡ ወታደር ፡ አለቃ ፡ ይሆን ፡ የለምን ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀኙን ፡ ቢሰጠን ፡ ገንዘባችንና ፡ ሀብታችን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መቆም ፡ ነውና ፡ ለገንዘብ ፡ መሻማት ፡ አትቸኩሉ ።

የቈሰለም ፡ ምርኮኛ ፡ ፈረንጅ ፡ ብታገኙ ፡ ምርኮኛ ፡ መገኘቱ ፡ የጠላትን ፡ ምሥጢር ፡ ለማወቅ ፡ ይረዳናልና ፡ በጁ ፡ ጩቤ ፡ ሽጉጥ ፡ ወይም ፡ የሚፈነዳ ፡ ነገር ፡ ይዞ ፡ የሚያበላሻችሁ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አትጨርሱት ።

ሎሌ ፡ ከጌታው ፡ ጭፍራ ፡ ካለቃው ፡ ከተለየ ፡ ሸሸት ፡ መዠመሩ ፡ ነውና ፡ የኔም ፡ የኢትዮጵያም ፡ ጠላት ፡ መሆኑን ፡ ዕወቁት ። ጦርነቱም ፡ ሲዠመር ፡ በግዳይም ፡ በምርኮም ፡ የቀናው ፡ ሰው ፡ በመጨረሻ ፡ ድሉ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ገድሎ ፡ መምጣት ፡ ብቻ ፡ ጠላትን ፡ ድል ፡ ከማድረግ ፡ አይቈጠርም ፡ ጦርነቱ ፡ እስኪያልቅ ፡ መግፋት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ግዳይ ፡ ለመጣል ፡ ኣይመለስ ።

ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ በምትቀርቡበት ፡ ጊዜ ፡ ሌሊት ፡ ተጉዛችሁ ፡ ነውና ፡ ጠላት ፡ ድምጣችሁን ፡ የሰማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መብራት ፡ ይዛችሁ ፡ ያየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጠላትን ፡ በገዛ ፡ እጅ ፡ ማንቃትና ፡ ማስጠንቀቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ተኵስ ፡ እስኪዠመር ፡ ርስ ፡ በርሳችሁ ፡ እንዳትጣሩ ፡ እንዳትጮኹ ፡ እንዳታቅራሩ ፡ መብራት ፡ እንዳታበሩ ፡ ይሁን ። ገንዘብና ፡ መሣሪያችን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መዳን ፡ ነውና ፡ ብረት ፡ እማርካለሁ ፡ ብላችሁ ፡ እየተሸከማችሁ ፡ ጠላት ፡ እንዳታባርሩ ፡ ጉልበታችሁን ፡ እንዳታደክሙ ።

ወደ ፡ ጦርነቱም ፡ በምትሄዱበት ፡ ጊዜ ፡ እዚህ ፡ የሚቀረው ፡ ጓዝ ፡ በብዙ ፡ ተበታትኖ ፡ እሳት ፡ ያንድድ ፡ ምክንያቱም ፡ ጠላት ፡ መጠጋታችንን ፡ እንዳይጠረጥርና ፡ ሰዉ ፡ በየሰፈሩ ፡ ነው ፡ ያለው ፡ በሉ ፡ እንዲያምን ፡ ነው ፡ »

ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ መላውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከሦስት ፡ ላይ ፡ ከፈሉት ፡ ያከፋፈሉም ፡ አኳኋን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ነው ።

1ኛ፡- ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ አበጋዝ ፡ ሆነው ፡ የራስ ፡ ከበደን ፥ የጐላን ፡ የሊጋባን ፥ የፊታውራሪ ኣርኣያን ፥ የርሻ ፡ ሚኒስቴርን ፥ የሰይፈ ፡ ጃግሬን ፥ ያዣዥ ፡ ቦጋለን ፡ የነጋድራስ ፡ ወዳጆን ፥ የደጃች ፡ አበራ ፡ ተድላን ፥ የግቢ ፡ ሚኒስቴርን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ በመካከል ።

2ኛ፡- ልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ አበጋዝ ፡ ሆነው ፡ የሰናድር ፡ ያዥን ፥ የወሊጋን ፡ የፈረስ ፡ ዘበኛን ፥ የሊቀ ፡ መኳስ ፡ ኀይለ ፡ ማርያምን ፥ የቀኛዝማች ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስን ፥ የፊታውራሪ ፡ ተድላን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ በቀኝ ፡ በኩል ።

3ኛ፡- ራስ ፡ ጌታቸው ፡ አባተ ፡ አበጋዝ ፡ ሆነው ፡ የከምባታን ፥ የዕቃ ፡ ቤትን ፥ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴርን ፥ የቀኛዝማች ፡ አበበ ፡ ረዴን ፡ (ማለፊያ ፡ ጠመንዣ ፡ ያዥ) ፡ የቀኛዝማች ፡ በየነን ፡ (ባልደራስ) ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ በግራ ፡ በኩል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተከፈለው ፡ አኳኋን ፡ መጋቢት ፡ 22 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ማክሰኞ ፡ ሠራዊቱ ፡ ሌሊቱን ፡ ተጠግቶ ፡ ሲነጋ ፡ ጦርነቱ ፡ እንዲዠመር ፡ አዘዙ ። ወታደሩም ፡ በየክፍሉ ፡ እየተጓዘ ፡ ማይጨው ፡ ቦሖራና ፡ መሖን ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ተጠጋ ።

ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥትም ፡ ከሌሊተ ፡ 10 ፡ ሰዓት ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ ሲጓዙ ፡ የቀደመው ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ መሽጎ ፡ ከተቀመጠው ፡ ከኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ገጥሞ ፡ ውጊያው ፡ ተዠመረ ።

ወዲያው ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ደርሰው ፡ በመነጸር ፡ እያዩ ፡ ጦር ፡ ለቀለለበት ፡ ስፍራ ፡ እየጨመሩ ፡ በዚህ ፡ እለፍ ፡ በዚህ ፡ ቅደም ፡ እያሉ ፡ ሲዋጉና ፡ ሲያዋጉ ፡ ዋሉ ። ጦርነቱም ፡ ጧት ፡ የዠመረ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ቈየ ።

ኢትዮጵያና ፡ ኢጣሊያም ፡ ጦርነት ፡ ካደረጉ ፡ ዠምሮ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጦርነት ፡ አድርገው ፡ አያውቁም ፡ ይባላል ። የኢትዮጵያ ፡ ጀግና ፡ ከጠላት ፡ ወገን ፡ ከሚውዘገዘገው ፡ የመድፍ ፡ ፍላጻ ፡ ከመትረየሱ ፡ ፀረር ፡ ከቦምቡ ፡ ነበልባል ፡ ጋራ ፡ እየተመሳቀለ ፡ በሚያጠላው ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ በቈራጥነት ፡ ተዋግቶ ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚያኰራና ፡ ኅሊናን ፡ የማይወቅሥ ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ይበልጡ ፡ ደግሞ ፡ የወኒውን ፡ ቅስቃሴ ፡ ሳይታገሥ ፡ ዘራፍ ፡ የጠቅል ፡ አሽከር ፡ እያለ ፡ እመካከል ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ ተለመደ ፡ የመድፉንና ፡ የመትረየሱን ፡ አፈ ፡ ሙዝ ፡ እየጨበጠ ፡ ጠላቱን ፡ በጐራዴ ፡ ይጨፈጭፍ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ የጋለ ፡ ጦርነት ፡ ሰዓት ፡ እንዲሁ ፡ ተዋቸውና ፡ ጐበዙ ፡ ይለይ ፡ የሚል ፡ ሽማግሌ ፡ በሌለበት ፡ ስፍራ ፡ የድሉም ፡ ዕድል ፡ ወደ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሳይታወቅ ፡ ማሬሻል ፡ ቦዶሊዮ ፡ በሰሜን ፡ ያሉትን ፡ መላውን ፡ አይሮፕላኖች ፡ አስነሥቶ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ቊጥራቸው ፡ ከመቶ ፡ ኣምሳ ፡ የሚበልጡ ፡ አይሮፕላኖች ፡ ቦምብና ፡ ኤፕሪት ፡ የሚባለውን ፡ የጋዝ ፡ ጭስ ፡ እየጫኑ ፡ ደርሰው ፡ በተዋጊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደርና ፡ በደጀኑ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ እየጮኹ ፡ ያዘንቡበት ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ ከመሬት ፡ ጠላቱን ፡ ሲያጠቃ ፡ ከሰማይ ፡ ደግሞ ፡ የጠላት ፡ ቦምብ ፡ መልሶ ፡ ስላጠቃው ፡ የጦርነቱ ፡ ስፍራ ፡ የሬሳ ፡ መነባበሪያ ፡ ሆነ ። እነዚህ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ኣይሮፕላኖች ፡ የሚጥሉት ፡ ቦምብ ፡ ትልቅና ፡ ትንሽ ፡ መካከለኛ ፡ ሆኖ ፡ ገሚሱ ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡ የሚፈነዳ ፡ ገሚሱ ፡ ከወደቀ ፡ ቈይቶ ፡ የሚፈነዳ ፡ የጋዝ ፡ መርዙም ፡ ገሚሱ ፡ በሽታው ፡ የሚገድል ፡ ገሚሱ

፡ ዐይን ፡ የሚያሳውር ፡ ገሚሱ ፡ አካላት ፡ የሚያጕረበርብ ፡ ነበር ። መሬቱ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ እጅ ፡ ሆኖ ፡ የዚያ ፡ መሬት ፡ ሰማዩ ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ በመሆኑ ፡ ማሬሻል ፡ ባዶሊዮም ፡ የጦርነቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ይኸ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያሉበት ፡ መሆኑን ፡ ያውቃልና ፡ በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ሰዓት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ በጥይታቸው ፡ መተው ፡ ካሰናከሉት ፡ በስተቀር ፡ የሚሠራው ፡ አይሮፕላን ፡ በሰሜን ፡ አይሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ እንዳይውል ፡ አዞ ፡ ነበርና ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ ትእዛዙ ፡ ቃል ፡ ሁሉም ፡ አይሮፕላኖች ፡ ባንድነት ፡ እየተነሡ ፡ እላይ ፡ የተባለውን ፡ ዐይነቱ ፡ የበዛውን ፡ ቦምብና ፡ የጋዝ ፡ መርዝ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ እየደጋገሙ ፡ አዘነቡበት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የክብር ፡ ዘበኞውና ፡ ገሚስ ፡ ሠራዊት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እየተመራ ፡ ያለቀው ፡ እያለቀ ፡ የተረፈውም ፡ ሲዋጋ ፡ የቀረው ፡ ነጭ ፡ ለባሽ ፡ ደግሞ ፡ በዚሁ ፡ በቦምብና ፡ በጋዝ ፡ መርዝ ፡ ስለ ፡ ተሸበረ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ መመለስ ፡ ዠመረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ጕራዴያቸውን ፡ መዘው ፡ የቦምብና ፡ የመድፍ ፡ ነበልባል ፡ የመትረየስና ፡ የጥይት ፡ ዐረር ፡ በሚያፏጭበት ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተንጐራደዱ ፡ ሲዋጉና ፡ ሲያዋጉ ፡ ሳሉ ፡ ይህን ፡ የሚሸሸውን ፡ ጦር ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ባዳራሹ ፡ ምን ፡ ብለሽ ፡ ፎከረኸልኝ ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ እኔ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትኸ ፡ ፊቴን ፡ ሳልመልስ ፡ እንዴት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ታፈገፍጋለኸ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ወቀሡት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እየተመለሰ ፡ በጦርነቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ሠራ ። ይህንም ፡ የመሰለ ፡ ታላቅ ፡



ግርማዊነታቸው ፡ በጦርነት ፡ መካከል ።

ጦርነት ፡ የተደረገው ፡ የወታደርነት ፡ ክብር ፡ እንዳይዋረድና ፡ የኢትዮጵያም ፡ የዠግንነት ፡ ታሪክ ፡ እንዳይተባበል ፡ ያኸል ፡ ለመጋደል ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ የድሉ ፡ እጅ ፡ የዞረው ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ጠላቷ ፡ እንደ ፡ ኢጣሊያ ፡ ቦምብና ፡ መርዝ ፡ ከመሥራት ፡ የተጓደለች ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

የኢጣሊያም ፡ የዚያ ፡ ዕለት ፡ ድል ፡ አድራጊነትና ፡ የኢትዮጵያም ፡ ተሸናፊነት ፡ በዚህ ፡ እላይ ፡ በተባለው ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ መላው ፡ ዓለምና ፡ ኢጣሊያኖች ፡ በቃላቸውና ፡ በኀሊናቸው ፡ ፈርደዋል ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ የሚጻፍ ፡ ታሪክም ፡ አይስተውም ።

በዚህም ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ (መጋቢት ፡ 22 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም) ፡ በዠግንነት ፡ እየተዋጉ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ከወደቁት ፡ መኳንንቶችና ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ተራ ፡ ወታደሮች ፡

ውስጥ ፡ ለጊዜው ፡ ስማቸው ፡ የታወቀው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። (በተንቤን ፡ በእንደርታ ፡ በሺሬ ፡ በአምባ ፡ አርዐዶም ፡ ከወደቁት ፡ በስተቀር) ።

* ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ይልማ ፡
* » ደጃዝማች ፡ ወንድ ፡ ይራድ ፡
* » ደጃዝማች ፡ አበራ ፡ ተድላ ፡
* ፊታውራሪ ፡ አሸናፊ ፡
* » ኀይለ ፡ ማርያም ፡
* ቀኛዝማች ፡ በየነ ፡ በላይነሽ ፡
* ፊታውራሪ ፡ ነጋሽ ፡ ተስፋዬ ፡
* ግራዝማች ፡ ተናኘ ፡ ዳርጌ ፡ ከልጁ ፡ ከበቀለ ፡ ጋራ ፡

## ከክብር ፡ ዘበኞች ፡ ውስጥ ፡

* የሻለቃ ፡ ዳኜ ፡ ወዳጆ ፡
* » ሺበሺ ፡ ደያስ ፡ (ማይጨው በደፋርነት ፡ ሲዋጋ ፡ ቈስሎ ፡ ሕይወቱ ፡ በቦምብ ፡ በትር ፡ የተፈጸመ) ፡
* የሻምበል ፡ ለማ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡
* » ረታ ፡ በረደድ ፡
* » ለገሠ ፡ አያኔ ፡
* » ይማም ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ (ማይጨው ፡ ቈስሎ ፡ አገሩ ፡ ገብቶ ፡ ሞተ) ።
* » መብራቴ ፡ ኰላሴ ፡ (ማይጨው ፡ ቈስሎ ፡ ሲመለስ ፡ ሞተ) ።
* » ተሰማ ፡ አያኔ ፡
* የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሥዩም ፡ ዘለቀ ፡
* » » ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ወልደ ፡ ዮሓንስ ፡
* » » ከበደ ፡ ይርጋ ፡

* » » በላይነኽ ፡ ሮባ ፡
* » » ኣብተየስ ፡ ሣርጌ ፡
* » » ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በላይነሽ ፡
* » » አባ ፡ ሸኘው ፡ ገዳ ፡
* » » ደስታ ፡ ወርቅነኽ ፡ (በውጋዴን)
* » » ኣካለ ፡ ወልድ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡
* ያ50 ፡ አለቃ ፡ ወርቁ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡
* » » ከበደ ፡ ይርጋ ፡ (ቆራሔ) ፡
* » » ኀይለ ፡ ማርያም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
* » » ፈይሳ ፡ ቦሩ ፡
* » » ነጋሽ ፡ ሞገድ ፡
* » » አየነው ፡ ተሻለ ፡
* ያ10 ፡ አለቃ ፡ አጐናፍር ፡ ኃይሌ ፡
* » » ከተማ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡
* » » አስፋው ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ (ቆራሔ) ፡
* » » መኩሪያ ፡ እዝነኽ
* » » መለሰ ፡ መኰንን ፡
* » » ረታ ፡ ርገጤ ፡
* ተራ ፡ ወታደር ፡ ጀማነህ ፡ ወርቄ ፡
* » » ወንድ ፡ አፍራሽ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ።

ከነዚህ ፡ በቀር ፡ በማይጨው ፡ ጦርነት ፡ ለትውልድ ፡ ምሳሌ ፡ በመሆን ፡ ሕይወታቸውን ፡ ያሳለፉ ፡ በሺ ፡ የሚቈጠሩ ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶችና ፡ ተራ ፡ ወታደሮች ፡ ስላገራቸው ፡ የወታደርነት ፡ ክብራቸውን ፡ ተንተርሰው ፡ ወደቁ ። « አገሩን ፡ በሰላምም ፡ በጦርነትም ፡ ጊዜ ፡ የሚከዳ ፡ የሙት ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲሁ ፡ ስላገሩ ፡ የሚሞት ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ ነው» ፡ በተባለው ፡ ቃል ፡ እነዚህም ፡ ስላገራቸውና ፡ ስላገራችን ፡ ነፃነት ፡ በዚያ ፡ በቦምብና ፡ በመድፍ ፡ ፊት ፡ የሞቱት ፡ ሰዎች ፡ መታሰቢያቸው ፡ ባሉትና ፡ በሚወለዱት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ልብ ፡ ለዘለዓለም ፡ ተቀርጾ ፡ ሲነበብና ፡ ሲነገር ፡ ይኖራል ።

# ምዕራፍ ፡ 74 ።

## የኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መፈታት ።

የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ በግፍ ፡ የመጣበትን ፡ ጠላቱን ፡ በመሣሪያ ፡ ልዩነት ፡ (በቦምብና ፡ በመርዝ ፡ በትር) ፡ የተነሣ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ለመመለስ ፡ ባይችል ፡ በያዘው ፡ መሣሪያና ፡ በተለመደ ፡ ዠግንነቱ ፡ በዐድዋ ፡ በመቀሌ ፡ በሸሬ ፡ በእንደርታ ፡ በተንቤን ፡ ጎሊናውን ፡ በማይወቅሥበት ፡ አኳኋን ፡ እንደሚገባ ፡ ተዋጋ ። በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ከደረሰበት ፡ አደጋ ፡ የተነሣ ፡ ተስፋ ፡ ሳይቈርጥ ፡ ከየጦሩ ፡ ግንባር ፡ እየተመለሰ ፡ በማይጨው ፡ ተጠራቅሞ ፡ የመጨረሻ ፡ ደሙን ፡ ለማፍሰስ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥተ ፡ ዙሪያ ፡ ተሰለፈ ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴም ፡ እነዚያን ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሆኑትን ፡ የክብር ፡ ዘበኞቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ታላቅ ፡ ውጊያ ፡ አደረጉ ። የግርማዊነታቸውንና ፡ የክብር ፡ ዘበኞቻቸውን ፡ የመኳንንቶቻቸውንም ፡ የማይጨውን ፡ ውሎ ፡ በኢጣሊያኖችና ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ሠራዊት ፡ መካከል ፡ ሆነው ፡ የዐይን ፡ ምስክር ፡ የነበሩት ፡ ጋዜጣ ፡ ጸሓፊዎች ፡ በጣም ፡ አድንቀዋል ። ራሳቸውም ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ምንም ፡ እንካ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ድሉ ፡ በወንድነት ፡ በኩል ፡ ሲያጋድልባቸው ፡ በቦምብና ፡ በመርዝ ፡ በኩል ፡ ለማቃናት ፡ ቢችሉ ፡ «ይህ ፡ የአየር ፡ ጦር ፡ ባይኖረን ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ ዐይኑን ፡ ጨፍኖ ፡ እመድፍ ፡ አፍ ፡ ድረስ ፡ እየመጣ ፡ የሚዋጋ ፡ ወታደር ፡ በምን ፡ እንመልሰው ፡ ኖሯል » ፡ እያሉ ፡ መደነቅና ፡ መደመማቸውን ፡ አልሸሸጉትም ።

ጀርመን ፡ በትልቁ ፡ ጦርነት ፡ ከወደቀ ፡ ወዲህ ፡ በስውር ፡ ባዘጋጀው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ያውም ፡ ቢሆን ፡ ተወራሪዎቹ ፡ መንግሥታት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በቊጥር ፡ ባይወዳደሩት ፡ የአየር ፡ ጦር ፡ እያላቸው ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ የነምሳን ፡ መንግሥት ፡ ያለጦርነት ፡ ባ1 ፡ ቀን ፡ ያዘ ። የቼኮስሎቫኪያን ፡ መንግሥት ፡ ባ1 ፡ ቀን ፡ የፖሎኝን ፡ መንግሥት ፡ በ30 ፡ ቀን ፡ የዳነማርክን ፡ መንግሥት ፡ ባ5 ፡ ቀን ፡ የኖርቤዥን ፡ መንግሥት ፡ በ9 ፡ ቀን ፡ የሆላንድን ፡ መንግሥት ፡ በ8 ፡ ቀን ፡ የቤልጅግን ፡ መንግሥት ፡ በ20 ፡ ቀን ፡ የፈረንሳይን ፡ መንግሥት ፡ በ2 ፡ ወር ፡ ከ3 ፡ ቀን ፡ የዩጎስላቪን ፡ መንግሥት ፡ በ20 ፡ ቀን ፡ ጦርነት ፡ ያዘ ።

እነዚህም ፡ የተያዙ ፡ መንግሥታት ፡ በመሣሪያ ፡ ልዩነትና ፡ ብዛት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጀርመን ፡ ዠግንነት ፡ ጐድሏቸው ፡ አይደለም ።

ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ኢጣሊያን ፡ በሺ ፡ 888 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በዐድዋ ፡ ድል ፡ አድርጋ ፡ ከመለሰች ፡ ወዲህ ፡ በስውር ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በመሬትና ፡ በአየር ፡ የሚወጋትን ፡ ጠላቷን ፡ በመሬት ፡ ጦርነት

፡ ብቻ ፡ 7 ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ አቆመች ። ስለ ፡ ድሉ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያም ፡ ልጆች ፡ በዚህ ፡ በአይሮፕላን ፡ ሥራ ፡ ትክክል ፡ በመሬትና ፡ በሰማይ ፡ ለመዋጋት ፡ በሚችሉበት ፡ ጊዜ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ጦርነት ፡ ቢያነሡ ፡ እውነተኛው ፡ ዠግና ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይታወቅ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ ሆኖ ፡ ማይጨው ፡ በተደረገው ፡ ጦርነትም ፡ ቢሆን ፡ ድሉ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አዘንብሎ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ምንም ፡ አይጠረጠርም ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በጠላት ፡ ላይ ፡ የድል ፡ ርምጃ ፡ የዠመረውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወታደር ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ በሰሜን ፡ የሚገኙት ፡ አይሮፕላኖች ፡ በ70ና ፡ በ150 ፡ እየተከፈሉ ፡ መጥተው ፡ ገሚሶቹ ፡ የሚያቃጥል ፡ ገሚሶቹ ፡ የእሳተ ፡ ገሞራው ፡ ፍንጣሪ ፡ ሰውን ፡ የሚፈጅ ፡ ቦምብ ፡ ያፈሱበት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ተደፍሮ ፡ የማያውቀውና ፡ ድል ፡ ከመሆን ፡ መሞትን ፡ የሚመርጠው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ መመለስ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ።

ለዚህም ፡ አንድ ፡ ተራ ፡ ወታደር ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ሸለለ ፡ ይባላል ።

« በማይጨውም ፡ በመቀሌም ፡... በኩል ፡ መች ፡ ይገባ ፡ ነበር ፡

በሰማይ ፡ ላይ ፡ ገባ ፡ በማናውቀው ፡ አገር» ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትም ፡ በዚሁ ፡ በእሳተ ፡ ገሞራ ፡ ውሽንፍር ፡ መካከል ፡ ሆነው ፡ ከተዋጉና ፡ ካዋጉ ፡ በኋላ ፡ ወታደሩ ፡ ከቦምብ ፡ ዝናም ፡ እየሸሸ ፡ በላያቸው ፡ ሲመጣ ፡ ልብን ፡ በሚነካ ፡ በዠግንነት ፡ ንግግር ፡ ሲገሥጹት ፡ ገሚሱ ፡ እየተመለሰ ፡ ተዋግቶ ፡ ሞተ ። የቀረው ፡ ግን ፡ ከሽሽቱ ፡ ሊገታ ፡ አልቻለም ። ግርማዊ ፡ ጃንሆይም ፡ አጠገባቸው ፡ ካሉት ፡ ቈራጥ ፡ ወታደሮቻቸው ፡ ጋራ ፡ እጦርነቱ ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ በሞታቸው ፡ ቈርጠው ፡ ይዋጉ ፡ ዠመር

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የነፃነት ፡ ሕይወት ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ መንጠልጠሉንና ፡ ሞታቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሞት ፡ ሕይወታቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕይወት ፡ መሆኑ ፡ ያልተዘነጋቸው ፡ መሳፍንቶችና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹማምንቶች ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሄደው ፡ በጠላታቸው ፡ ፊት ፡ ለመሞት ፡ ሲገሠግሡ ፡ ከፊታቸው ፡ እየቀደሙ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ለመኗቸው ። ቀጥለውም ፡ ከንዴትና ፡ ከብስጭት ፡ የተነሣ ፡ አልመለስም ፡ ብለው ፡ እፊታቸው ፡ ያለውን ፡ ሲገፉ ፡ ወዲያው ፡ ቀሳውስቱ ፡ የሥላሴን ፡ ስም ፡ ጠርተው ፡ ገዘቷቸው ። ሌሎችም ፡ ታላላቅ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ በጃንሆይ ፡ ዙሪያ ፡ ሆነው ፡ « ዛሬ ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ጊዜ ፡ እንዳገኘ ፡ እኛም ፡ ጊዜ ፡ እናኛለንና ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰን ፡ ጊዜ ፡ እያራዘምን ፡ እንዋጋ » ፡ ብለው ፡ አመለከቱ ፡ ጃንሆይም ፡ « እኔ ፡ ቀድሞውንም ፡ የመጣሁት ፡ ድል ፡ አደርጋለሁ ፡ ማለትን ፡ ብቻ ፡ ታምኜ ፡ አይደለም ። ድልም ፡ ብሆን ፡ ሕይወቴ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ እንድሠራ ፡ ነውና ፡ የፈቀደ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ይሙት ፡ ያልፈቀደም ፡ ይሂድ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኋላዬ ፡ አልመለስም » ፡ አሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሌሎቹ ፡ አለቆችና ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ ደጃች ፡ ወልደ ፡ ህማኑኤል

፡ « ንጉሥ ፡ ልክ ፡ ለመወጣት ፡ ስሞት ፡ ኣገሩን ፡ መጕዳት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አይጠቅመውም ፡ ሞትን ፡ እንደሆነ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አናጣውም ፡ ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ ለቀን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰን ፡ ጊዜና ፡ ስፍራ ፡ እያለዋወጥን ፡ ብንዋጋ ፡ ይሻላል » ፡ ሲሉ ፡ ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ተናገሩ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከማይጨው ፡ ተመልሰው ፡ ኰረም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመዋጋት ፡ አሰቡ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ (አሁን ፡ ራስ) ፡ ሌሎችም ፡ መኳንንቶች ፡ የግርማዊነታቸው ፡ ኰረም ፡ ላይ ፡ መዋጋትና ፡ መሞት ፡ ጠላትን ፡ ከመጥቀም ፡ በቀር ፡ ኢትዮጵያን ፡ በምንም ፡ በኩል ፡ እንደማይጠግናት ፡ ደጋግመው ፡ አስረድተው ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ እንዲመለሱ ፡ ለመኗቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የኔ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ መመለስ ፡ ለሕይወቴ ፡ መሳሳት ፡ ሳይሆን ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ለሕዝቧ ፡ ጠቀሜታ ፡ ያደረጋችሁት ፡ መሆኑን ፡ ቃል ፡ ግቡልኝ ፡ ብለው ፡ በጳጳሱ ፡ ከገቡላቸው ፡ ወዲህ ፡ እንግዲያውስ ፡ የተረፈውም ፡ ጦር ፡ እንዲመለስ ፡ ንገሩ ፡ ብለው ፡ ከተሰበሰበ ፡ በኋላ ፡ ደጅን ፡ እየሆኑ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ። የጠላት ፡ አይሮፕላኖችም ፡ በግድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲጠፉ ፡ ዝቅ ፡ እያሉ ፡ በቦምብና ፡ በመትረየስ ፡ 7 ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ ከቦምብና ፡ ከመርዝ ፡ ጋራ ፡ በመዋጋት ፡ የደከመውን ፡ ጦር ፡ ሲሙቱት ፡ አለቃና ፡ ጭፍራው ፡ ተለያይቶና ፡ ተበታትኖ ፡ ቅጥ ፡ ኣጥቶ ፡ ሁሉም ፡ የሚድንበትን ፡ መንገድ ፡ እየፈለገ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የማይጨውና ፡ የየጁ ፡ የዋጅራት ፡ ባላገሮች ፡ ስለ ፡ ነፃነቱና ፡ ስለ ፡ ነፃነታቸው ፡ ከዘመቻ ፡ ደክሞ ፡ የተመለሰውን ፡ የወገናቸውን ፡ ወታደር ፡ እኽል ፡ ውሃ ፡ እየሰጡ ፡ በመሸኘት ፡ ፈንታ ፡ አንዳንዶቹ ፡ የያዘውን ፡ ብረት ፡ ለመቀማት ፡ ሲሉ ፡ በደናቸውና ፡ በስፍራቸው ፡ እያደቡ ፡ ያጠፉት ፡ ወታደር ፡ ልክ ፡ የለውም ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ብዙ ፡ እየሆኑ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እየሆኑ ፡ ባጀቡ ፡ ላይ ፡ ተኰሱ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ መኖራቸውን ፡ አላመኑም ፡ ነበርና ፡ ከባላገሮቹ ፡ ቀንደኛ ፡ የሆኑት ፡ መጥተው ፡ ጃንሆይን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ «እኛ ፡ ሰራዊቱ ፡ ንጉሥን ፡ ከድቶ ፡ የመጣ ፡ መስሎን ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ መች ፡ ዐወቅን » ፡ ብለው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ እየሄዱ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ አምጥተው ፡ ለወታደሩ ፡ ሰጥተዋል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የጠላት ፡ ቦምብና ፡ የጋዝ ፡ መርዝ ፡ እየዘነበ ፡ በግርማዊነታቸው ፡ አጠገብ ፡ የሚሄዱትን ፡ ሲገድል ፡ ከባላገር ፡ የተተኰሰውም ፡ እነልጅ ፡ ገሠሠ ፡ ጅማን ፡ ሲገድል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ትንሣኤ ፡ የተደገፈውን ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ ሕይወት ፡ ሊቃወም ፡ አልቻለም ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ቸል ፡ በማይላት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሥልጣን ፡ ተጠብቀው ፡ በሚወዷቸው ፡ ታማኝ ፡ ወታደሮቻቸው ፡ ታጅበው ፡ በኰረምና ፡ በየጁ ፡ በወሎና ፡ በፍቼ ፡ አድርገው ፡ ሚያዝያ ፡ 22 ፡ ቀን ፡ ኀሙስ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገቡ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በከተማው ፡ ያለው ፡ መኳንንትና ፡ ሕዝብ ፡ በደስታ ፡ ተቀበላቸው ። ያን ፡ ጊዜም ፡

«ግርማዊነትዎ ፡ ሕያው ፡ ከሆነ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ሕያው ፡ ትሆናለች» ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የተናገሩት ፡ በኋላ ፡ በመፈጸሙ ፡ በጣም ፡ ያስደንቃል ።

# ምዕራፍ ፡ 75 ።

## የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ መሄድ ፡ በዤኔብ ፡ ጉባኤ ፡ የተናገሩት ፡ ዲስኩር ።

ግፈኛው ፡ ጠላት ፡ አሳቡን ፡ ለመፈጸም ፡ ባደረገውና ፡ ሕግን ፡ ተላልፎ ፡ በሠራበት ፡ መሣሪያ ፡ እየተዋጋ ፡ እስከ ፡ ደሴ ፡ ደርሶ ፡ ከዚያም ፡ ስመ ፡ ጥሩዋን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ከተማ ፡ አዲስ ፡ ኣበባን ፡ ለመያዝ ፡ በብዙ ፡ ታንክና ፡ በብረት ፡ ለበስ ፡ መኪናዎች ፡ የሚረዱ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቶች ፡ አዘጋጅቶ ፡ ጕዞውን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይቀጥል ፡ ዠመር ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ስብሰባ ፡ ተደርጎ ፡ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ሲመከር ፡ 1ኛው ፡ ወገን ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ወደ ፡ ጐሬ ፡ ተዛውሮ ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ለመከላከል ፡ 2ኛው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የዚህኑ ፡ የግፈኛ ፡ ጠላት ፡ ወራሪነት ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ራሳቸው ፡ አውሮፓ ፡ ሄደው ፡ ለማኅበሩ ፡ እንዲያመለክቱ ፡ 3ኛው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ጣርማ ፡ በር ፡ ለመከላከያ ፡ የተመቸ ፡ ስፍራ ፡ በመሆኑ ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ጠላትን ፡ ለመቋቋም ፡ መከሩ ። ሌሎቹም ፡ ጠላት ፡ የሚለውን ፡ ፈጽመን ፡ እንስማማ ፡ ያሉ ፡ ጥቂቶች ፡ አሉ ።

1ኛውና ፡ 3ኛው ፡ አሳብ ፡ በጊዜው ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ ሲታይ ፡ ሳለ ፡ ኢጣሊያ ፡ ሕግ ፡ ተላልፎ ፡ የሚሠራባቸው ፡ መሣሪያዎች ፡ ይህን ፡ አሳብ ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያስችሉ ፡ አይደሉም ።

በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ በርና ፡ እንደ ፡ ተራራ ፡ ያሉትን ፡ ለጦርነት ፡ የሚረዱትን ፡ ስፍራዎች ፡ ይዞ ፡ መዋጋት ፡ እንደሚጠቅም ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከተዋጊዎቹ ፡ 1ኛው ፡ በአየር ፡ መጥቶ ፡ መሸጎ ፡ የተቀመጠበትን ፡ ስፍራ ፡ በመርዝ ፡ ወይም ፡ በቦምብ ፡ ሲመታበት ፡ ይህንኑ ፡ የሚከላከልበት ፡ የአየር ፡ ጦር ፡ ከሌለው ፡ መልካምነቱ ፡ ወደ ፡ መጥፎ ፡ ዠግንነቱም ፡ ፍሬ ፡ ወደሌለው ፡ እልቂት ፡ ከማዘንበል ፡ በቀር ፡ ለዚያ ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠው ፡ ጥቅም ፡ አልነበረም።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከሁሉም ፡ አሳብ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ አውሮፓ ፡ ሄደው ፡ ለዚህ ፡ በመርዝና ፡ በቦምብ ፡ ለተጠቃው ፡ ሕዝባቸው ፡ ፍርድ ፡ እንዲጠይቁ ፡ የተባለው ፡ አሳብ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ትንሣኤ ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተስማሙበት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የጦርነት ፡ ባህል ፡ የሚያውቁትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ተራራና ፡ ጫካ ፡ ተገን ፡ አድርገው ፡ እየተከላከሉ ፡ እንዲቈዩ ፡ አዘው ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነንን ፥ ልዑል ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰንን ፥ ልዑል ፡ መኰንን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፥ ልዕልት ፡ ተናኘ ፡ ወርቅን ፥ ልዕልት ፡ ፀሓይን ፥ ልዑል ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴን ፥ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳን ፥ ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩን ፥ ራስ ፡ ጌታቸውን ፥ ደጃዝማች ፡ ይገዙን ፥ ደጃዝማች ፡ አደፍርሰውን ፥ ደጃዝማች ፡ ነሲቡ ፡ ዛማኔልን ፥ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸውን ፥ ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠውን ፥ ደጃዝማች ፡ ዐምዴንና ፡ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ዐማኑኤልን ፥ ጸሓፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ኅይሌን ፥ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይን ፥ ፊታውራሪ ፡ ታፈሰን ፥ አቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስን ፥ አቶ ፡ ሎሬንሶ ፡ ታእዛዝንና ፡ ሌሎችንም ፡ አስከትለው ፡ በሚያዝያ ፡ 24 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሚወዱትን ፡ ሕዝባቸውን ፡ የሚወዷትን ፡ አገራቸውን ፡ በመሪር ፡ ሐዘን ፡ ትተው ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ በባቡር ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ጅቡቲ ፡ ሄዱ ። ጅቡቲም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የጅቡቲ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ በክብር ፡ ተቀብሎ ፡ ሲያነጋግራቸው ፡ ወዲያው ፡ በተወሰነው ፡ ሰዓት ፡ የወዳጃቸው ፡ የእንግሊዝ ፡ መርከቦች ፡ ሲመጡ ፡ በሩቅ ፡ ታዩ ። ወዲያው ፡ የመርከቡ ፡ ሹም ፡ ከመርከቡ ፡ ወርዶ ፡ የመርከብ ፡ ዘበኞቹን ፡ ግርማዊነታቸው ፡ እስካሉበት ፡ ድረስ ፡ አሰልፎ ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ የሚገባ ፡ ሰላምታ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በሰልፉ ፡ መካከል ፡ ከመርከቡ ፡ ሹም ፡ ጋራ ፡ እየተነጋገሩ ፡ አልፈው ፡ «ኢንተርፕሪዝ » ፡ በሚባለው ፡ መርከብ ፡ ተሳፍረው ፡ ጉዟቸውን ፡ ቀጠሉ ። በመርከብም ፡ ተጉዘው ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ መርከቦች ፡ የእንግሊዝን ፡ መርከቦች ፡ ወግተው ፡ ለመማረክ ፡ እንደሚያስቡ ፡ ሁሉ ፡ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ ሲንሳፈፉ ፡ ታዩ ። ወዲያው ፡ የመርከቡ ፡ ሹም ፡ ለጥንቃቄ ፡ ሲል ፡ ነገሩን ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ አካፍሎ ፡ ወታደሮቹ ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲያደርጉ ፡ አዘዘ ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይም ፡ መትረየሳቸውን ፡ በመርከቡ ፡ መስኮት ፡ ላይ ፡ ደግነው ፡ ሲጠባበቁ ፡ ወዲያው ፡ እነዚያ ፡ ከጠመንጃ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ የሌለውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወታደር ፡ ማይጨው ፡ ላይ ፡ በቦምብና ፡ በመርዝ ፡ ለመምታት ፡ ዠግኖች ፡ የሆኑት ፡ ኢጣሊያኖች ፡ በዚህ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ አደጋ ፡ ለማድረግ ፡ ቢፈትኑ ፡ የሚሰጣቸው ፡ መልስ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ያውቁ ፡ ነበርና ፡ ጠብ ፡ እንዳልፈለገ ፡ ሁሉ ፡ በሩቅ ፡ ተሣሥቀው ፡ ተላለፉ ፡ ይባላል ።

ከዚያም ፡ ተጉዘው ፡ « ስዌዝ ፡ ደ ፡ ካናልን» ፡ አልፈው ፡ ሐይፋ ፡ ከተማ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ባገር ፡ ምክንያት ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዠምረው ፡ ይዋጉ ፡ የነበሩት ፡ አይሁዶችና ፡ ዐረቦች ፡ ስለ ፡ ጃንሆይ ፡ ክብር ፡ ሲሉ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ጦርነቱን ፡ አቁመው ፡ ዋሉ ፡ ይባላል ።




ኢንትርፕሪዝ ፡ ምትባለው ፡ መርከብ



ሐይፋንም ፡ አልፈው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ በዤኔብ ፡ የሚያመለክት ፡ መላክተኛ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ በሰፊው ፡ ለማመልከት ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ መጥቻለሁ ፡ ሲሉ ፡ ወደ ፡ ዤኔብ ፡ ቴሌግራም ፡ አስተላለፉ ። ኢየሩሳሌምም ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ ሕዝባቸው ፡ መገፋት ፡ በጸሎት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ሲነጋገሩ ፡ ቈይተው ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ ሎንዶን ፡ ጉዟቸውን ፡ ቀጠሉ ። ሎንዶንም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የሎንዶን ፡ ሕዝብ ፡ በሰልፍና ፡ በክብር ፡ ተቀበላቸው ። እንደ ፡ ገናም ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ያጽናኗቸው ፡ አሉ ። ከዚያም ፡ የኢትዮጵያና ፡ የኢጣሊያ ፡ ጠብ ፡ ሲመረመርበት ፡ ወደ ፡ ቈየው ፡ ወደ ፡ ዤኔብ ፡ ሄደው ፡ ቀጠሮ ፡ ጠይቀው ፡ ተመለሱ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ አስቀድሞ ፡ በጦርነቱ ፡ ሰዓት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ ችላ ፡ እንዲሉ ፡ የሚያደርገውን ፡ ፖለቲካ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አስፋፍቶ ፡ ይዞት ፡ ነበር ። ማኅበሩም ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ስም ፡ ስብሰባ ፡ አድርጎ ፡ የሚያቀርቡትን ፡ ማመልከቻ ፡ እንዳይሰማ ፡ መላነክተኛውን ፡ ሁሉ ፡ ያባብል ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ማኅበሩ ፡ ውልና ፡ እንደ ፡ ዐሥራ ፡ ስድስተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ንግግር ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ መንግሥታት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ አጥቂውን ፡ ኢጣሊያን ፡ እንኳ ፡ ለመውጋት ፡ ቢቀር ፡ የተጠቂውን ፡ አቤቱታ ፡ አልሰማም ፡ ማለት ፡ ከሰውነት ፡ ወይም ፡ ከሕሊና ፡ ሕግ ፡ ነገሩ ፡ የራቀ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚወዱ ፡ እነሙሴ ፡ ኮልሶን ፡ እነሙሴ ፡ ጋስቶቼዝ ፡ በበኩላቸው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ይረዱ ፡ ነበርና ፡ በመጨረሻ ፡ በዚያው ፡ በተቀጠረው ፡ ቀን ፡ የምክር ፡ ቤቱ ፡ ስብሰባ ፡ አደረገ ። ካማካሪዎቹም ፡ በስተቀር ፡ ጋዜጣ ፡ ጸሓፊዎችና ፡ ብዙ ፡ ሕገዝቦች ፡ የምክር ፡ ቤቱን ፡ አዳራሽ ፡ መልተውት ፡ ነበር ። ደግሞ ፡ ግርማዊነታቸውን ፡ ለማየትና ፡ ንግግራቸውን ፡ ለመስማት ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተሰብስቦ ፡ አዳራሽ ፡ ስላልበቃ ፡ በበሩና ፡ በየመስኮቱ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ታላቅና ፡ በሚያስፈራ ፡ ጉባኤ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አቶ ፡ (ብላቴን ፡ ጌታ) ፡ ሎሬንሶን ፡ (ያን ፡ ጊዜ ፡ ዋና ፡ ጸሓፊያቸው ፡ የነበሩትን ፡ አሁን ፡ የጽሕፈትና ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ፡ የሆኑትን) ፡ አቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስን ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ ምክሩ ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ በመናገሪያው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ እውነትና ፡ ጽድቅ ፡ ባለበት ፡ ንግግር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ ከሥር ፡ እስከ ፡ ጫፍ ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝረው ፡ ሰኔ ፡ 23 ፡ ቀን ፡ 1929 ፡ ዓ ፡ ም ፡ አስታወቁ ። ንግግራቸውም ፡ እውነትና ፡ ጽድቅን ፡ የተደገፈ ፡ ባንደበት ፡ ኀይልና ፡ ባምላካዊ ፡ ረድኤት ፡ የታገዘ ፡ በመሆኑ ፡ እዚያ ፡ ካሉት ፡ ከፋሺስት ፡ ጋዜጣ ፡ ጸሓፊዎች ፡ በስተቀር ፡ በዚህ ፡ ታሪክ ፡ በሚያስታውሰው ፡ ዲስኩር ፡ ልቡ ፡ ያልተነካና ፡ ያላዘነ ፡ በሕሊናው ፡ ዳኝነት ፡ ተወቅሦ ፡ ያልተረታ ፡ መላክተኛ ፡ አይገኝም ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝረው ፡ ያስታወቁበት ፡ የዤኔብ ፡ ጉባኤ

ከንግግራቸውም ፡ ይበልጡ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

« ክቡር ፡ ፕሬዚዳን ።

ማናቸውንም ፡ ርዳታ ፡ የተከለከለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ብቻውን ፡ ፍኖተ ፡ መስቀሉን ፡ ይከተላል ። ባጥቂው ፡ ምክንያት ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ማናቸውም ፡ ውርደት ፡ ተደረገበት ። አጥቂው ፡ ወገን ፡ እንደሚጠይቀው ፡ ለማድረግ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ለማስወገድ ፡ ማናቸውም ፡ የደንብ ፡ አፈጻጸም ፡ ብልኀት ፡ ተደረገ ። እንደዚህም ፡ ሆኖ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ ዡምሮ ፡ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ፊት ፡ የመላው ፡ ዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቧል ። ሕግ ፡ ኀይልን ፡ ያሸንፋል? ወይስ ፡ ኀይል ፡ ሕግን ፡ ያሸንፍ ፡ ይሆን?

ምክንያት ፡ በሌለው ፡ አጥቂ ፡ የተጐዳችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበረተኞች ፡ በፈረሙበት ፡ ፊርማ ፡ እምነቷን ፡ አድርጋ ፡ ነበር ። የሚገባትና ፡ ቃል ፡ የተቀበለችበት ፡ ርዳታ ፡ በሙሉ ፡ አልተሰጣትም ። ካ1927 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዠምሮ ፡ በማኅበሩ ፡ ውል ፡ ላይ ፡ የተፈረሙበት ፡ ፊርማዎች ፡ በየተራ ፡ ሲፈርሱ ፡ በኀዘን ፡ ትመለከታለች ። አጥቂን ፡ የሚያሠጉት ፡ ብዙ ፡ ትንንሽ ፡ መንግሥቶች ፡ ደካማ ፡ መሆናቸውን ፡ በማሰብ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ተዋት ። እያንዳንድኽ ፡ የምትችለውን ፡ አድን ፡ በማለት ፡ በድንጋጤና ፡ በመሸነፍ ፡ ድምጥ ፡ ጮኹ ። በከንቱ ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ አጥቂውን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ አስበው ፡ ባንድነት ፡ ጸጥታ ፡ መጠባበቂያ ፡ ተዋውለው ፡ በነበሩት ፡ ውል ፡ ከገቡት ፡ ግዴታ ፡ እንደ ፡ ተፈቱ ፡ ሆነው ፡ እንዲቈጠሩ ፡ አደረጉ ። እንደዚህም ፡ በማድረጋቸው ፡ ኑሯቸው ፡ የተመሠረተበትን ፡ መሠረታዊ ፡ ነገር ፡ ራሳቸው ፡ አፈረሱት ። ነፃነታቸውን ፡ የሚያረጋግጡ ፡ የነበሩትን ፡ አጥቂነት ፡ እንዳይደረግ ፡ የሚከለክሉትን ፡ ውሎች ፡ የመንግሥታትን ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ የፓሪስን ፡ ውል ፡ ቀደዱ ። የፈረሟቸውን ፡ ውሎች ፡ ከምንም ፡ እንደማይገቡ ፡ ወረቀቶች ፡ ከቈጠሯቸው ፡ በነዚህ ፡ ውሎች ፡ የተመለከቱትን ፡ ግዴታዎች ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ ለማስከኀት ፡ ይችሉ ፡ ይሆን?

ያጥቂነት ፡ ሥራዎች ፡ እየበዙ ፡ ሄዱ ። ይኸም ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ እየተጋባ ፡ እየበዛ ፡ ሄደ ። አንዳንድ ፡ መንግሥቶች ፡ አሁንም ፡ በሙሉ ፡ ትግል ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። ሌሎችም ፡ የሚያሠጋቸው ፡ ሆኗል ። ፍርሀት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ነገሠ ። አሁን ፡ ተጠቂ ፡ የሆኑት ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ እንዳይጠቁ ፡ የሚሠጉት ፡ ለሚመጣው ፡ ጊዜ ፡ ይንቀጠቀጣሉ ። የአጥቂነት ፡ ሥራ ፡ ያደርጉብናል ፡ ብለው ፡ የሚያሠጓቸውን ፡ መንግሥቶች ፡ በማባበል ፡ ኑሯቸውን ፡ ያጠኑ ፡ ይመስላቸዋል ። የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ መልካም ፡ ተግባር ፡ ጠፋ ። እነዚህም ፡ ደካማ ፡ መንግሥቶች ፡ የሚያቀርቡት ፡ ሰበብ ፡ ደካሞች ፡ ነን ፡ ማለትንና ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ተጣለች ፡ እንጣላለን ፡ ማለትን ፡ ሆነ ፡ ከሁለት ፡ በሽታ ፡ ትንሽ ፡ መስሎ ፡ የሚታያቸውን ፡ ያጥቂነት ፡ መፍራትን ፡ ይመርጣሉ ። እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይበላቸው ።

ፈተናችን ፡ ከተዠመረበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ባለማቋረጥ ፡ ባሳቢነት ፡ ርዳታቸውን ፡ ለሰጡን ፡ መንግሥታት ፡ የማኅበሩን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለመጠበቅ ፡ ልባቸውን ፡ ሳያደክሙ ፡ ጥንካሬያቸውን ፡ ላረጋገጡ ፡ ለመስኮብ ፡ ለቻይና ፡ ለሜክሲኮና ፡ ለኔውዜላንድ ፡ መንግሥቶች ፡ በሕዝቤ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ስለ ፡ ታመነ ፡ ወዳጅነታቸው ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ምስጋናዬን ፡ አቀርባለሁ ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ እንዳስታወቅሁ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በሚበዛው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የመቈጣጠር ፡ ሥራ ፡ አይሠራም ። ከኤርትራ ፡ በቀረበው ፡ በትግሬ ፡ አገር ፡ እንካ ፡ የኢጣሊያ ፡ ወታደሮች ፡ በከተማና ፡ ሰው ፡ ባንድነት ፡ ላይ ፡ ተሰብስቦ ፡ በሚኖርበት ፡ ብቻ ፡ ተቀምጠዋል ። ሌላውን ፡ አገር ፡ ግን ፡ አይገቡበትም ። በየቦታውም ፡ የተቀመጡት ፡ ወታደሮች ፡ ሥንቅና ፡ ጥይት ፡ በአይሮፕላን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ አይላክላቸውም ። በጐንደርና ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ ብቻ ፡ ወታደር ፡ አለበት ። እነርሱም ፡

ከሌላው ፡ ለመገናኘት ስላልቻሉ ፡ ሥንቃቸው ፡ በአይሮፕላን ፡ ይላክላቸዋል ። በጐጃም ፡ ምንም ፡ የኢጣሊያ ፡ ገዥ ፡ የለበትም ። በሸዋ ፡ የኢጣሊያ ፡ ወታደሮች ፡ ያሉበት ፡ ባዲስ ፡ አበባና ፡ ባንኮበር ፡ ወደ ፡ ጅቡቲ ፡ በሚሄደው ፡ የባቡር ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ ነው ። በወለጋ ፡ ውስጥ ፡ በጐሬ ፡ በሰዮ ፡ በለቀምት ፡ ሦስት ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ከተማውን ፡ ብቻ ፡ የያዙ ፡ አሉ ። ሌላውን ፡ ግን ፡ አይገቡበትም ። በጅማ ፡ በቦረና ፡ በሲዳሞ ፡ በባሌና ፡ በወላሞ ፡ ያገሩ ፡ አኳኋን ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ጅረን ፡ ይርጋ ፡ ዓለም ፡ ሜጋ ፡ ጐባ ፡ ጊኒርን ፡ ይዘውታል ። ሌላውን ፡ አገር ፡ ግን ፡ በጦረኞቻችን ፡ ገፊነት ፡ ለቀዋል ። በሐረርጌ ፡ የሐረር ፡ ከተማ ፡ ጅጅጋና ፡ የባቡር ፡ መንገዱ ፡ ተይዟል ። ሌላውን ፡ ግን ፡ አልገቡበትም። በደንከሌና ፡ በአውሳም ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ምንም ፡ አይቈጣጠሩም ።

ከዚህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ጋራ ፡ ተጨማሪ ፡ ሆኖ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ አቤቱታ ፡ ይገኛል ። ይኸም ፡ አቤቱታ ፡ የጊዜውን ፡ አኳኋን ፡ እያስረዳ ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበርንና ፡ የእንግሊዝን ፡ መንግሥት ፡ ርዳታ ፡ ይለምናል ። እነዚህ ፡ አገሮች ፡ ሁሉም ፡ በግልጥ ፡ የታወቁ ፡ ወሬውም ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አዋሳኝ ፡ ከሆኑት ፡ ከእንግሊዝና ፡ ከፈረንሳይ ፡ ቅኝዎች ፡ ከሚመጡት ፡ ወሬዎች ፡ ጋራ ፡ የተገጣጠመ ፡ ነው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ራሱ ፡ ባ1935ና ፡ ባ1936 ፡ ዓመት ፡ ካወጣው ፡ ከ26 ፡ ሚሊያርድ ፡ ሊሬ ፡ በቀር ፡ ባመት ፡ ባመቱ ፡ አገር ፡ ለመያዝ ፡ የሚያወጣው ፡ በብዙ ፡ ሚሊያርድ ፡ የሚታሰብ ፡ መሆኑን ፡ አምኗል ። ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ ጥቅም ፡ የሚያመጣ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የማይቻለው ፡ ሆነ ። የመንገድ ፡ ሥራውንም ፡ ፕሮግራም ፡ ሊፈጽም ፡ አልቻለም ። ያልቻለውም ፡ በገንዘብ ፡ ችግር ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ኢጣሊያኖች ፡ አገሩን ፡ ለቀው ፡ እስቲሄዱ ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በጭራሽ ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ያላቋረጠና ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ የማያቋርጥ ፡ ጦርነት ፡ ባለበት ፡ አገር ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የማይቻል ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ አኳኋን ፡ ሲታይ ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ነገሩ ፡ የተጣራ ፡ ነው ። የመንግሥታት ፡ ሕግ ፡ በጦር ፡ ጊዜ ፡ አንደኛው ፡ ተዋጊ ፡ በያዘው ፡ ባንዳንድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ያልተረጋገጠ ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ ይሆንና ፡ የተወሰነ ፡ ሥልጣን ፡ ይፈቅድለታል ። ከጦርነቱ ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ መንግሥቶች ፡ አገር ፡ ከያዘው ፡ የጦር ፡ ወይም ፡ ሰላማዊ ፡ ባለሥልጣን ፡ ጋራ ፡ በተያዘው ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ዜጎቻቸውን ፡ ጥቅም ፡ ለመጠበቅ ፡ ለጊዜው ፡ የሆነና ፡ የተወሰነ ፡ መገናኛ ፡ ሊያቆሙ ፡ ይችላሉ ። የራሱ ፡ ያልሆነውን ፡ አገር ፡ ተዋጊው ፡ መንግሥት ፡ ለግዛቱ ፡ ተጨማሪ ፡ እንዳያደርገውና ፡ ከጦርነቱም ፡ ውጭ ፡ የሆኑት ፡ መንግሥቶች ፡ አገር ፡ የያዘውን ፡ ተዋጊ ፡ በሕግ ፡ የተገባው ፡ ገዥ ፡ አድርገው ፡ እንዳይቈጥሩት ፡ በፍጹም ፡ ይከለከላል ።

ስለዚህ ፡ አንዱ ፡ አገሬ ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ የሌላው ፡ አገር ፡ በሕግ ፡ ማወቅ ፡ በኀይል ፡ የተያዘ ፡ አገር ፡ ይርጋ ፡ ከማለት ፡ የሚቈጠር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበርና ፡ የፓሪስ ፡

ውል ፡ በሕግ ፡ እንዳይታወቅ ፡ ይከለክላል ። በኢትዮጵያ ፡ ዛሬ ፡ ያለው ፡ አኳኋን ፡ የነዚህን ፡ ውሎች ፡ ቃል ፡ የሚያበረታ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ከነዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ መንገዶች ፡ ለማማረጥ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ አጥብቃ ፡ ታምናለች ። ማኅበሩ ፡ የተመሠረተው ፡ ሰላም ፡ በሕግ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ማናኛውንም ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠት ፡ ይህን ፡ መሠረታዊ ፡ ኣሳብ ፡ ጥሎ ፡ ባጥቂው ፡ እግር ፡ ሥር ፡ ኣንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆነ ፡ መንግሥት ፡ እንዲሠዋ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ራሱን ፡ ከመግደል ፡ ይቈጠራል ።

ለሕዝቤ ፡ ለመከላከል ፡ ባለኝ ፡ ዐቅምና ፡ በመንፈሴ ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ልብም ፡ ይህን ፡ ማስረጃ ፡ ሳቀርብ ፡ የንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥቴን ፡ በመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ የገባበትን ፡ ዘመን ፡ 1923 ፡ ዓመትን ፡ አስታውሳለሁ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አገሬ ፡ ደርሶበት ፡ ከነበረው ፡ ሥልጣኔ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ይታየኝ ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሕዝቤን ፡ ለመምራት ፡ ግዴታ ፡ ገባሁ ። ከዚያም ፡ ጊዜ ፡ ዠምሬ ፡ ይኸን ፡ ለማድረግ ፡ አላረፍሁም ፥ ታላላቅም ፡ ፍሬ ፡ አፍርቶ ፡ ነበረ ። ኢጣሊያ ፡ ባደረገችው ፡ ያጥቂነት ፡ ጦርነት ፡ ሥራዬ ፡ ሁሉ ፡ በመበላሸቱና ፡ በመገለባበጡ ፡ በኀዘን ፡ እመለከታለሁ ። በሌላውም ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ደረሰው ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያም ፡ ያጥቂው ፡ ጦርነት ፡ ሰው ፡ የማይጠብቀው ፡ ፍሬ ፡ አፈራ ። የኢጣሊያ ፡ አጥቂነት ፡ ከሌላው ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሹማምንቶች ፡ በንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ ዙሪያ ፡ እንዲጠጉ ፡ አደረጋቸው ። ለመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ በማስተላልፋቸው ፡ ዐይነተኛ ፡ ወረቀቶች ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሽማምንቶችና ፡ ሕዝብ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥታቸው ፡ ፍቅራቸውን ፡ የገለጡበት ፡ ደብዳቤዎች ፡ ይገኛሉ ።

እኔ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ በጦረኞቼ ፡ ሹማምንቶች ፡ ታማኝነትና ፡ በሕዝቤ ፡ ፍቅር ፡ ተደግፌ ፡ የተቻለ ፡ ያኸል ፡ ለሥቃያቸው ፡ ፍጻሜ ፡ እንዳገኝ ፡ ስለ ፡ መፍቀድ ፡ ለመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያቀረብሁትን ፡ አሳብ ፡ ደግሜ ፡ አቀርባለሁ ። ሕዝቤ ፡ ሥልጣኔውን ፡ በሙሉ ፡ ነፃነት ፡ እያሰለፈ ፡ እንዲሄድ ፡ በሚፈቅድለት ፡ መንገድ ፡ ማስማሚያ ፡ አሳብ ፡ ቢገኝ ፡ ለመመርመር ፡ ዛሬም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ የተዘጋጀሁ ፡ ነኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጥያቄዬ ፡ ምላሽ ፡ ባያገኝ ፡ ለማናቸውም ፡ ቢሆን ፡ ሕግን ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ እስኪያሸንፍ ፡ ድረስ ፡ በኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ የማያቋርጥ ፡ መሆኑን ፡ እገልጻለሁ ። አጥቂ ፡ የሆነችው ፡ ኢጣሊያ ፡ ተጠቂውን ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠት ፡ የምትበረታበትን ፡ የመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ እንዲጠይቅ ፡ የምታስበውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ማኅበሩ ፡ እንዳይቀበል ፡ እጠይቃለሁ» ።

ግርማዊነታቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ እንደ ፡ መሆናቸው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጠበቃ ፡ ሆነው ፡ ከገባበት ፡ ባርነት ፡ አርነት ፡ የሚወጣበትን ፡ መንገድ ፡ አራቱ ፡ የዓለም ፡ ማዕዘን ፡ ባፈራቸው ፡ ታላላቅ ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ መላክተኞች ፡ መካከል ፡ ቊመው ፡ ተከራከሩ ። ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ከግርማዊ ፡ ኣንደበታቸው ፡ የሚወጣውም ፡ ንግግር ፡

ያድማጮቹን ፡ መላክተኞች ፡ መንፈስ ፡ ይጫን ፡ ነበር ። በየኅሊናቸውም ፡ እየዘለቀ ፡ ያለፈውን ፡ ቸልተኛነታቸውን ፡ እያስታወሰ ፡ ይዘልፋቸው ፡ ነበር ።

ይልቁንም ፡ « ማናቸውንም ፡ ርዳታ ፡ የተከለከለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ብቻውን ፡ ፍኖተ ፡ መስቀሉን ፡ ይከተላል ።

ከሁለት ፡ በሽታ ፡ ትንሽ ፡ መስሎ ፡ የሚታያቸውን ፡ ያጥቂነት ፡ መፍራትን ፡ ይመርጣሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይበላቸው ።

ኀይል ፡ ሕግን ፡ ያሸንፋል? ወይስ ፡ ሕግ ፡ ኀይልን ፡ ያሸንፋል?

ባንድ ፡ ውል ፡ ግርጌ ፡ የተፈረመ ፡ ፊርማ ፡ የሚረጋው ፡ ፈራሚዎቹ ፡ መንግሥቶች ፡ የሚጠቅማቸው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነውን? እግዚአብሔርና ፡ ታሪክ ፡ ፍርዳችሁን ፡ ሲያስታውሱት ፡ ይኖራሉ» ፡ በሚለው ፡ ንግግር ፡ ልቡ ፡ ያልተነካ ፡ መላክተኛ ፡ አይገኝም ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ባለፈው ፡ ባ1927 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጦርነት ፡ በኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ ብናነሣ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ተያይዞ ፡ ይቀሰቀሳል ፡ የሚሉት ፡ ፖለቲካ ፡ እውነተኛን ፡ ሕግና ፡ ፍርድ ፡ ለመፈጸም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያደናቅፋቸው ፡ ነበርና ፡ ወራሪውንና ፡ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡ የሆነውን ፡ መንግሥት ፡ መውጋት ፡ ቀርቶ ፡ የጠየቁትን ፡ መሣሪያ ፡ እንኳ ፡ በቸርነትም ፡ ሆነ ፡ በግዥም ፡ ሆነ ፡ አልፈቀዱላቸውም ። ስለዚህ ፡ በማይጨው ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ « አምላክነሰ ፡ አምላከ ፡ አድኅኖ » ፡ ብለው ፡ ተማምነውበት ፡ የነበረው ፡ አምላክ ፡ የራሱን ፡ ቸርነት ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ ሊገልጽ ፡ ስለ ፡ ወደደ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንርዳ ፡ ለኢትዮጵያስ ፡ መሣሪያ ፡ እንስጥ ፡ ወይስ ፡ እንከልክል ፡ ብለው ፡ በኅሊናቸው ፡ የሚሟገቱትን ፡ ልባቸውን ፡ ኣጸና ።

ኀይል ፡ በሕግ ፡ ሊሸነፍ ፡ ይገባዋል ፡ ብለው ፡ ባንደበታቸው ፡ ሲፈርዱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኢጣሊያን ፡ በሕግ ፡ ስታሸንፍ ፡ ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በኀይል ፡ ሲወር ፡ በባለሕጉ ፡ ጐን ፡ ተሰልፈው ፡ ሕግን ፡ በኃይሉ ፡ የደመሰሰውን ፡ ሊቃወሙት ፡ አልፈለጉም ። የዚህም ፡ ምክንያት ፡ በኀይል ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ የሚታየውን ፡ መንግሥት ፡ ለመውረር ፡ ላቈበቈበው ፡ ለጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ ሰጥቶት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ቈዩ ። ግርማዊ ፡ ጃንሆይም ፡ የፖለቲካ ፡ ትግላቸውን ፡ ሳያቋርጡ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ተስፋ ፡ ሲጠባበቁ ፡ ቈዩ ።

# ምዕራፍ ፡ 76 ።

## የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ያ5 ፡ ዓመት ፡ አገዛዝ ፡ የግራዚያኒ ፡ አደጋ ፡ ደናኔና ፡ ጀናሌ ።

ደሴ ፡ ገብቶ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ ለመያዝ ፡ የሚዘጋጀው ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ከደሴ ፡ ተነሥቶ ፡ በየበሩ ፡ እየጠበቀ ፡ የሚዋጋውን ፡ በቦምብና ፡ በመርዝ ፡ እያጠፋ ፡ በጣርማ ፡ በርና ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ አድርጎ ፡ ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገባና ፡ « ዛሬ ፡ ግንቦት ፡ 5 ፡ ቀን ፡ ባሸናፊዎች ፡ ወታደሮቼ ፡ ታጅቤ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገባሁ» ፡ ሲል ፡ ባዶሊዮ ፡ ለሙሶሊኒ ፡ ቴሌግራም ፡ ላከ ። ከዚያም ፡ የቀረውን ፡ አገር ፡ ለመያዝ ፡ ሠራዊት ፡ ላከ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከመግባቱ ፡ በፊትም ፡ ላርበኝነት ፡ የተዘጋጁት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መኳንንቶችና ፡ ወጣቶች ፡ ከከተማ ፡ ያገኙትን ፡ ብረትና ፡ መሣሪያ ፡ እየያዙ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በሚገኘው ፡ በቈላና ፡ በደጋው ፡ በጫካና ፡ በተራራው ፡ ነፃነታቸውን ፡ ለመከላከል ፡ ከያለበት ፡ እየተሰበሰቡ ፡ በያለበት ፡ ተሠማሩ ። ከተማውን ፡ ግን ፡ ጃንሆይ ፡ በለቀቁበትና ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ሳይገባ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ በዘረፋ ፡ ምክንያት ፡ ተሸብሮ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ ። ብዙ ፡ ቤቶችም ፡ ለጠላት ፡ እንዳያገለግሉ ፡ ተቃጠሉ ። ባዶሊዮ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በገባ ፡ ባራተኛው ፡ ቀን ፡ ሙሶሊኒ ፡ የኢትየጵያ ፡ ጦርነት ፡ መፈጸሙንና ፡ ሰላም ፡ መመሥረቱን ፡ ኢጣሊያም ፡ በመጨረሻ ፡ ሰፊ ፡ የቄሳር ፡ ግዛት ፡ ማግኘቷን ፡ ለኢጣሊያ ፡ ሕዝብና ፡ ለመላው ፡ ዓለም ፡ አስረድቶ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉትን ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ በሕግና ፡ ባዋጅ ፡ አስታወቀ ።

«1 ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሬትና ፡ በውስጡም ፡ የሚገኙት ፡ ሕዝቦች ፡ በሙሉ ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ተገዥዎች ፡ ናቸው ።

2 ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ (የቄሳር) ፡ ስም ፡ ለኢጣሊያ ፡ ንጉሥና ፡ ለተከታዮቹ ፡ ዞሯል » ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሙሶሊኒ ፡ የንጉሥ ፡ እንደራሴነት ፡ ሥራኽን ፡ ለግራዚያኒ ፡ አስረክበኽ ፡ አንተ ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ተመለስ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ለማሬሻል ፡ ባዶሊዮ ፡ አስተላልፎለት ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ተመለሰ ። ግራዚያኒም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ የሊቢያን ፡ አስተዳደር ፡ በመሠረተበት ፡ በግፍና ፡ በወርጅነት ፡ ሥራው ፡ አኳኋን ፡ 3 ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ በነፃነቱ ፡ ኰርቶ ፡ በዦግንነቱ ፡ ታፍሮ ፡ የኖረውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ሊያስተዳድር ፡ አሰበ ። በከተማም ፡ የሚገኘውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነገሥታት ፡ መታሰቢያና ፡ ሐውልት ፡ እያፈረሱ ፡ የሙሶሊኒንና ፡ የንጉሡን ፡ ሐውልትና ፡ ሥዕል ፡ ይሠሩ ፡ ዠመር ። የዳግማዊ ፡ ምኒልክንም ፡ ሐውልት ፡ በጦር ፡ ከበው ፡ አፈረሱት ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ሀገራቸው ፡ ነፃነት ፡ ለመከላከል ፡ በየገጠሩ ፡ የተሠማሩት ፡ አርበኞች ፡ አውራጃውን ፡ ለመያዝ ፡ የሚላከውን ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ መንገድ ፡ እየሰበሩ ፡ ፊት ፡ ለፊትም ፡ እየገጠሙ ፡ ይመልሱት ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ግራዚያኒ ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ ሊያደርግ ፡ የፈለገውን ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ ሊፈጽም ፡ ኣልቻለም ።

ይልቁንም ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ፍቅረ ፡ ማርያም ፡ በየካ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ኣበራ ፡ ካሳ ፥ በስሉልታ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፥ በወጨጫ ፥ ግራዝማች ፡ ዘውዴ ፡ ኣስፋውና ፡ የሻለቃ ፡ መስፍን ፥ በገፈርሳ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ ከጠላት ፡ ለማስለቀቅ ፡ ስምምነት ፡ አድርገው ፡ በከበቡ ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ በኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ዘንድ ፡ ድንጋጤና ፡ ሽብር ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያለበት ፡ ድንጋይና ፡ አሸዋ ፡ እየረበረቡ ፡ መሽገው ፡ እምሽጋቸው ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ የሚመጣባቸውን ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር ። ባዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ያለውም ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝብ ፡ ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ላርበኞች ፡ እንዳይረዳ ፡ በማለት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ በሩን ፡ ዘግቶ ፡ እንዲተኛ ፡ ያለዚያ ፡ እንዲገደል ፡ በጥብቅ ፡ አዘው ፡ ነበርና ፡ ለነዋሪው ፡ ሕዝብ ፡ የዚያ ፡ ዕለት ፡ ቀኑ ፡ ሌሊት ፡ ሆኖበት ፡ ዋለ ።

አርበኞችም ፡ በያለቃቸው ፡ እየተመሩ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ዳር ፡ ገብተው ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ባንደኛው ፡ ወገን ፡ የመጣው ፡ አርበኛ ፡ ከሌላው ፡ ጋራ ፡ የመገናኛ ፡ ዘዴ ፡ ስላልነበረው ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ የመያዝ ፡ ፕሮግራማቸው ፡ ሳይከናወን ፡ ቀረ ፡ ቢሆንም ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ፍቅረ ፡ ማርያም ፡ እስከ ፡ ትልቁ ፡ ግቢ ፡ ጫፍ ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ የልባቸውን ፡ ሠርተው ፡ ተመለሱ ።

ዝግናው ፡ የወሎው ፡ ጳጳስ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከዘመቻ ፡ ከተመለሱ ፡ ወዲህ ፡ ከነደጃች ፡ አበራ ፡ ጋራ ፡ ሰላሌ ፡ ቈይተው ፡ ነበርና ፡ በዚያ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ እያሳበሩ ፡ እያበረታቱና ፡ አልዋጋም ፡ የሚለው ፡ እንዲዋጋ ፡ እየገዘቱ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገብተው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ የነደጃዝማች ፡ አበራ ፡ ጦር ፡ የተቻለውን ፡ ያኽል ፡ ተዋግቶ ፡ ሲመለስ ፡ ርሳቸው ፡ ግን ፡ አልመለስም ፡ ብለው ፡ በራስ ፡ ኀይሉ ፡ በኩል ፡ በኢጣሊያኖች ፡ እጅ ፡ ተያዙ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጦር ፡ አዛዥ ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እገዛለሁ ፡ በልና ፡ እንልቀቅኽ ፡ አሏቸው ። እርሳቸው ፡ ግን ፡ እንኳን ፡ ሊያምኑ ፡ በዚያ ፡ ያቆመውን ፡ ሁሉ ፡ ለኢጣሊያ ፡ የተገዛችሁ ፡ ውጉዝ ፡ ሁኑ ፡ መሬቷም ፡ እንዳትገዛኽ ፡ ገዝቻለሁ ፡ ብለው ፡ ተናገሩና ፡ እንደ ፡ ወታደርም ፡ እንደ ፡ ሐዋርያም ፡ ሆነው ፡ መዝመሪያ ፡ በመትረየስ ፡ ቀጥሎ ፡ በሽጉጥ ፡ ተደብድበው ፡ ሞቱ ፥ ስማቸው ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ ነው ።

በጐሬም ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ተገደሉ ። የዐድዋም ፡ ዝግና ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ ካሉበት ፡ ስፍራ ፡ « ሬሳዬን ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አደባባይ ፡ ፈልጉ» ፡ ብለው ፡ በግምጋሜ ፡ መጥተው ፡ ነበር ፡ ይባላል ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ተመልሰው ፡ በሽምግልናቸው ፡ ወራት ፡ እንደ ፡ ወጣት ፡ ዝግና ፡ ሙያ ፡ ሠርተው ፡ ሕይወታቸውን ፡ አበቤ ፡ (በቾ) ፡ ከሚባለው

፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ኣሳለፉ ። እንዲሁም ፡ ከቡር ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ በዋናው ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደሚገባ ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ተመልሰው ፡ በጐሬ ፡ በኩል ፡ አገራቸውን ፡ ማገልገል ፡ ባልፈለጉ ፡ ሰዎች ፡ ምክንያት ፡ ተከበው ፡ በፈቃዳቸው ፡ እጃቸውን ፡ እስኪሰጡ ፡ ድረስ ፡ በጠላት ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ አድርገዋል ።

የቀሩትም ፡ በውጭ ፡ ያሉት ፡ አርበኞች ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ አናስወጣ ፡ አናስገባ ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አውከውት ፡ ቈዩ ። የከቡራን ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ማርያምና ፡ ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ ጦርም ፡ ለጊዜው ፡ የማይበገርለት ፡ ሆነ ፡ ሲዳሞ ፡ ሄዶ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ ጄኔራል ፡ ግራዚያኒ ፡ በውስጡ ፡ ተገዝተን ፡ እንኖራለን ፡ ብለው ፡ ከተጠጉት ፡ መኳንንቶችና ፡ የተማሩ ፡ ወጣቶች ፡ መካከል ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ እያሰረ ፡ ያረመኔነት ፡ ሥራውን ፡ ፈጸመባቸው ። በሕያውነት ፡ በፊቱ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ እያየ ፡ ይንቃቸው ፡ ዠመር ። በየቀኑ ፡ በሚያደርገውም ፡ ዲስኩር ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥትን ፡ ኀያልነት ፡ በማውራት ፡ እየደነፋ ፡ ያስፈራራቸው ፡ ነበር ። ከንግግሩም ፡ ውስጥ ፡ ኣንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ። «ዛሬ ፡ ኢትዮጵያና ፡ እናንተ ፡ መዳፌ ፡ ውስጥ ፡ ገብታችኋል ፡ ከመዳፌ ፡ ውስጥ ፡ ፈልቅቆ ፡ አውጥቶ ፡ የሚያድናችሁ ፡ የለም» ። ባጠገቡ ፡ ያሉትን ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ እብሪትና ፡ ትምክሕት ፡ በመላበት ፡ ንግግር ፡ ይወቅሣቸው ፡ ነበር ።

በኋላ ፡ ለድኾች ፡ ምጽዋት ፡ እሰጣለሁ ፡ ብሎ ፡ መኳንንቱን ፡ በሰበሰበበት ፡ ቀን ፡ አብርሀ ፡ ደቦጭና ፡ ሞገስ ፡ ኣስገዶም ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ ወጣቶች ፡ የካቲት ፡ 12 ፡ ቀን ፡ 1929 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የእጅ ፡ ቦምብ ፡ ወርውረው ፡ ርሱን ፡ ሲያቈስሉ ፡ ባጠገቡ ፡ ከቆሙትም ፡ ጄኔራሎች ፡ ውስጥ ፡ የአይሮፕላን ፡ ጄኔራል ፡ የነበረው ፡ ከሌሎቹ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ቈሰለ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ያለው ፡ የግራዚያኒ ፡ መንግሥት ፡ በዓለም ፡ እንደሚደረገው ፡ እነዚህን ፡ ቦምብ ፡ የጣሉትን ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ በምርመራ ፡ ኣግኝቶ ፡ በመቅጣት ፡ ፈንታ ፡ ከዚያ ፡ ሰዓት ፡ ዠምሮ ፡ መትረየስና ፡ ጠመንዣዎች ፡ በዚያ ፡ ምንም ፡ በማያውቀውና ፡ በእጁ ፡ አንዳች ፡ መሣሪያ ፡ ባልጨበጠው ፡ ሰላማዊ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ አፋቸውን ፡ ከፈቱ ፡ ። በቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ግቢ ፡ ያለው ፡ በውጭ ፡ በመንገድም ፡ የሚሄደው ፡ በቤቱም ፡ የተቀመጠው ፡ ሕዝብ ፡ በጠቅላላው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያ ፡ በያዙት ፡ በኢጣሊያኖች ፡ ዐይን ፡ የሚገባው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሁሉ ፡ ይገደል ፡ ዠመር ። በመንገድ ፡ የሚሄደው ፡ በመትረየስ ፡ በጠመንዣ ፡ በሳንጃ ፡ ባካፋ ፡ በመዶሻ ፡ እየተመታ ፡ በባቡር ፡ መንገድ ፡ እየተረፈረፈ ፡ ወደቀ ። በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የተገኘ ፡ ወንድም ፡ ቢሆን ፡ ልጅ ፡ ታቅፋ ፡ የተቀመጠች ፡ ሴትም ፡ ብትሆን ፡ ከውጭ ፡ በራቸው ፡ እየተቈለፈባቸው ፡ በቤንዚን ፡ ተቃጠሉ ። የቀረውንም ፡ በመኪና ፡ እየከመሩ ፡ ወስደው ፡ በየካ ፡ በእንጦጦ ፡ በፉሪ ፡ በአቃቂ ፡ በገፈርሳ ፡ በመትረየስ ፡ ቈሉት። የዚያም ፡ ቀን ፡ ዐይናቸው ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ቀን ፡ ሁሉ ፡ እስላምንና ፡ ክርስቲያንን ፡ ሽማግሌንና ፡ ሕፃንን ፡ ወንድንና ፡ ሴትን ፡ አለየም ። እንደ ፡ ፋሲካ ፡ ሌሊት ፡ ዶሮ ፡ ወይም ፡ በፋሲካ ፡ ንጋት

፡ በያለበት ፡ እንደሚታረድ ፡ በግ ፡ መሳሪያውን ፡ አስረክቦ ፡ ሰላማዊ ፡ ሆኖ ፡ የተቀመጠው ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ ሕዝብ ፡ የቈራ ፡ ከብት ፡ ሆኖ ፡ ታረደ ፡ መደበቂያና ፡ መኖሪያም ፡ እንዳያገኝ ፡ ቤቱን ፡ እየዞሩ ፡ ቤንዚን ፡ እያርከፈከፉ ፡ አቃጠሉት ።

በዚያ ፡ ሰሞን ፡ በባቡር ፡ መንገድ ፡ የተዘረጋውና ፡ በየዛፉ ፡ በየሰንሰሉ ፡ ውስጥ ፡ የተኛው ፡ ሬሳ ፡ ቁጥር ፡ አልነበረውም ፡ ይህም ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ የሚረሳ ፡ ታሪክ ፡ ኣይደለም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሞት ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውሮ ፡ ያስነበተውን ፡ መኳንንትና ፡ ተራ ፡ ሕዝብ ፡ የተማረውንም ፡ ያልተማረውንም ፡ ሰብስበው ፡ በየስፍራው ፡ ያከማቹ ፡ ዠመር ። ክቡር ፡ ራስ ፡ ደስታና ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ በዠግንነት ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ሕይወታቸው ፡ ድረስ ፡ ተዋግተው ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ከነርሱ ፡ ጓዝ ፡ የማረኩትን ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ሕፃን ፡ ከየባላገሩ ፡ እየሰበሰቡ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አምጥተው ፡ ከታሰረው ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ደባልቀው ፡ አሰሩት ። እንደዚህ ፡ እየሰበሰቡ ፡ በፈረስ ፡ ቤት ፡ በአቃቂ ፡ በደጃዝማች ፡ ውቤ ፡ ሰፈር ፡ ወህኒ ፡ ቤትና ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ እያገቡ ፡ ዘጉበት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከየታሰረበት ፡ እየገቡ ፡ የሚፈልጉትን ፡ እያወጡ ፡ በየጫካው ፥ ሲገድሉ ፡ ሰነበቱ ።

በመጨረሻ ፡ ግን ፡ መላውን ፡ የታሰረውን ፡ ሰው ፡ በመኪና ፡ እያሳፈሩ ፡ ገሚሱን ፡ ወደ ፡ ናኩራ ፡ ገሚሱን ፡ ወደ ፡ ደናኔ ፡ (መቃዲሾ) ፡ ገሚሱን ፡ ወደ ፡ አዚናራ ፡ (ኢጣሊያ) ፡ አጓዙት።

በየታሰረበትም ፡ ስፍራ ፡ ማናቸውንም ፡ የውርደት ፡ ሥራ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ፈጸሙበት ፡ እኔም ፡ ራሴ ፡ እንደዚሁ ፡ ታስሬ ፡ ወደ ፡ ደናኔ ፡ ስሄድ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ባይኔ ፡ ተመለከትሁ ።

በዚህ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ከፈረስ ፡ ቤት ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ከታሰርን ፡ በኋላ ፡ በመጋቢት ፡ 12 ፡ ቀን ፡ ከፈረስ ፡ ቤት ፡ በመኪና አሳፍረው ፡ እንፋስ ፡ ስልክ ፡ ወሰዱን ፡ በዚያም ፡ ስንደርስ ፡ ባሰሩን ፡ ቦታ ፡ ብዙ ፡ የተጠመዱ ፡ መትረየሶች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ የመገደያችን ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ መሰለን ፡ ለሕይወታችን ፡ በፍጹም ፡ ተስፋ ፡ ቈርጠን ፡ ነበር። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እጠራ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አስቀምጠውን ፡ ዝናብ ፡ ሲደበድበን ፡ አደረ ፡ እንጂ ፡ ሰብስበው ፡ ባንድነት ፡ ሊፈጁን ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ገምተነው ፡ የነበረውን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሳይፈጽሙ ፡ ቀሩ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መጋቢት ፡ 13 ፡ ቀን ፡ ጧት ፡ 120 ፡ የሚሆኑ ፡ መኪናዎች ፡ አምጥተው ፡ ባርባ ፡ ባርባ ፡ እየቈጠሩ ፡ አሳፈሩን ። ወዲያው ፡ የተቀመጥንበት ፡ መኪና ፡ ተቀጣጥሎ ፡ ከቆመና ፡ የሚጠብቁን ፡ ዘበኞች ፡ በየመኪናችን ፡ ከወጡ ፡ በኃላ ፡ ይዞን ፡ የሚሄደው ፡ ኮሎኔል ፡ ጋርሶ ፡ በርትተው ፡ እንዲጠብቁ ፡ ለዘበኞቹ ፡ ትእዛዝ ፡ አደረገላቸውና ፡ መኪናው ፡ መሄድ ፡ ዠመረ ። የገሚሶቹም ፡ ታሳሪ ፡ ዘመዶች ፡ ፍጻሜውን ፡ ለማወቅ ፡ ሌሊት ፡ መጥተው ፡ በየመኪናው ፡ ኣጠገብ ፡ ቁመው ፡ በሩቅ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበርና ፡ መኪናው ፡ ጕዞውን ፡ ሲዠምር ፡ በሩቅ ፡ እያዩ ፡ ያለቅሱ ፡ ዠመር ። እኛም ፡ እነሱንና ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ እያየን ፡ እያለቀስን ፡ ትተናቸው ፡ ሄድን ።

ወዴት ፡ እንደሚወስዱንም ፡ ለይተን ፡ አናውቅም ፡ ነበር ። በመኪናም ፡ ስንሄድ ፡ ውለን ፡ ማታ ፡ የሚሰጡን ፡ የተፈጨ ፡ ዱቄት ፡ ነበርና ፡ መኪናው ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ዱቄት ፡ እንዴት ፡ ኣድርጎ ፡ አብስሎ ፡ መብላት ፡ ባለማወቅና ፡ በበረሓ ፡ ምጣድና ፡ ውሃ ፡ በማጣት ፡ በልቶ ፡ ከሚያድረው ፡ ሳይበላ ፡ የሚያድረው ፡ ይበልጣል ። በዚህም ፡ ጉዞ ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ የሚያሳዝኑት ፡ ልጅ ፡ የታቀፉት ፡ ሴቶች ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ ከመኪናው ፡ ጥበት ፡ ጋራ ፡ ከበረሓው ፡ ከሚሰማው ፡ ሙቀትና ፡ ከሞተሩ ፡ ግለት ፡ የተነሣ ፡ ሕፃናቶቹ ፡ በየቀኑ ፡ በየሰዓቱ ፡ ይሞቱ ፡ ነበር። እነዚህንም ፡ አውርዶ ፡ ለመቅበር ፡ መኪና ፡ ሊቆም ፡ አይችልም ፡ እያሉ ፡ ችግር ፡ ነበርና፡ እናቶቻቸው ፡ ብዙ ፡ መንገድ ፡ የሕፃን ፡ ሬሳቸውን ፡ በክንዳቸው ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ሲቆም ፡ ከመኪናው ፡ ወርደው ፡ አልታወቀ ፡ በረሓ ፡ ላይ ፡ እንደሚገባ ፡ ሳይቀብሩ ፡ ይመለሳሉ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ መኪናና ፡ መንገድ ፡ ሲበላሽ ፡ በየበረሓው ፡ 3 ፡ ቀን ፡ 2ም ፡ ቀን ፡ እያደርን ፡ እየተራብን ፡ እየተጠማን ፡ መፈጠራችንን ፡ እስክንጠላ ፡ ድረስ ፡ እየተደበደብን ፡ በሚያዝያ ፡ 4 ፡ ቀን ፡ መቃዲሾ ፡ አጠገብ ፡ ደናኔ ፡ ከምትባለዋ ፡ ስፍራ ፡ ደርሰን ፡ እግራችንን ፡ ዘርግተን ፡ ዐርፈን ፡ ስለ ፡ ዋልን ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለን ።

ከዚያም ፡ ስንደርስ ፡ የስር ፡ ቤት ፡ ሹሞች ፡ መጥተው ፡ በጽሕፈት ፡ ተረክበው ፡ አስገቡን ። ከገባንም ፡ በኋላ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ሰሌን ፡ ለመኝታ ፡ አንድ ፡ የመብሊያ ፡ ሳሕን ፡ አንድ ፡ ውሃ ፡ መጥለቂያ ፡ እየጨመሩ ፡ አደሉን ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከመካከላችን ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ሰሌን ፡ አሁን ፡ እንተኛበታለን ፡ ብንሞትም ፡ እንቀበርበታለን ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ ሁላችንንም ፡ ኣስደነቀን ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለሰባት ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ጐጆ ፡ ሰጥተው ፡ በዚያ ፡ እየገባን ፡ ተቀመጥን ። ቊጥራችንም ፡ በኋላ ፡ ከተጨመሩት ፡ ጋራ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ይደርሳል ። ከዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ገሚሱ ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ገሚሱ ፡ መኳንንት ፡ ገሚሱ ፡ ተራ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፡ ለቤታቸው ፡ ወለል ፡ ስጋጃ ፡ የሚያነጥፉት ፡ በነጠላ ፡ ሰሌን ፡ ላይ ፡ ተኙ ። አሽከሮቻቸውን ፡ ጠጅና ፡ ጠላ ፡ የሚያጠጡት ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ያንን ፡ የጨው ፡ ውሃ ፡ እየጠለቁ ፡ ጠጡ ። መኳንንቱም ፡ ከኋላው ፡ የሱማሌ ፡ ዘበኛ ፡ እየረገጠው ፡ ከተራው ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ከሩቅ ፡ እየሄደ ፡ ዕንጨትና ፡ ውሃ ፡ በትከሻው ፡ ይሸከም ፡ ዠመር ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ እስካንድ ፡ ዓመት ፡ ከቈየን ፡ በኋላ ፡ በሰፈሩ ፡ ውስጥ ፡ የትኩሳትና ፡ የተስቦ ፡ በሽታ ፡ ገብቶ ፡ ገሚሱን ፡ እያቃዠ ፡ ገሚሱን ፡ እያሳበደ ፡ ይገድለው ፡ ዠመር ። ባራት ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፡ 1 ፡ ሺሕ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ሞተ ። እነሱንም ፡ በየቀኑ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እያወጣን ፡ በአሸዋ ፡ ውስጥ ፡ በሚተኙበት ፡ ሰሌንና ፡ በሚለብሱት ፡ ኣቡጀዲድ ፡ እየጠቀለልን ፡ ቀበርናቸው ።

ኣንድ ፡ ዓመት ፡ ተኩል ፡ ደናኔ ፡ ተቀምጠን ፡ ይበልጡ ፡ ሕዝብ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የተረፈው ፡ ሕዝብ ፡ ጀናሌ ፡ ከሚባል ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ እየሠራ ፡ እንዲበላ ፡ እንጂ ፡ ደናኔ ፡ ሆኖ ፡ በምግብ ፡ በኩል ፡ መንግሥትን ፡ እንዳያስቸግር ፡ ታሰበ ።

ጀናሌ ፡ የሚባለው ፡ ስፍራ ፡ 117 ፡ የሙዝ ፡ ኮንሴስዮን ፡ ያለበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የሞቃዲሾ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ከባለኮንሴስዮኖቹ ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ አድርጎ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ኮንሴስዮን ፡ 50 ፡ ወይም ፡ ዐርባ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከመካከላቸው ፡ ሹም ፡ እያደረገ ፡ እንዲያስረክብ ፡ ለወህኒ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ አዘዘው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባ40ና ፡ ባ50 ፡ በ25ም ፡ እየተቈጠረ ፡ አንዱ ፡ አሥሪ ፡ እየጨመረ ፡ ለመውሰጃ ፡ መኪና ፡ ይዘው ፡ ለመጡት ፡ የኮንሴስዮን ፡ ባለቤቶች ፡ ኣስረከበን ።

ከደናኔ ፡ ተነሥተን ፡ ሠላሳ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ አልፈን ፡ ጀናሌ ፡ ወደሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ደረስን ፡ በደረስን ፡ በማግስቱ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ እያዞረ ፡ አሳየን ፡ ሥራውም ፡ ቦይ ፡ መቈፈር ፡ ሙዝ ፡ መኰትኰት ፡ ነው ። ከደናኔ ፡ የሄደው ፡ ሰው ፡ በኮንትራት ፡ የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ሲጨርስና ፡ ምግቡን ፡ ሲቀበል ፡ ሲያድርበትም ፡ ጦሙን ፡ ሲያድር ፡ ሰነበተ ።

ከኢትዮጵያውያን ፡ ጋራ ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ ሱማሌዎች ፡ ወንዶቹም ፡ ሴቶቹም ፡ ከኢጣሊያ ፡ አገር ፡ ሀብት ፡ ለመፈለግ ፡ ለመጡት ፡ ኢጣሊያኖች ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ይሠራሉ ። በጀናሌ ፡ ያለው ፡ 117 ፡ ኣዚዬንዳ ፡ (ኮንሴስዮን) ፡ በያንዳንዱ ፡ 100 ፡ ወይም ፡ 200 ፡ የሱማሌ ፡ ሠራተኛ ፡ አለው ።

እነዚህም ፡ ለየጌታቸው ፡ 7 ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ያለ ፡ ዕረፍት ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ይሠራሉ ። እኛ ፡ እንሥራ ፡ ሴቶቻችን ፡ እቤት ፡ ምግባችንን ፡ ያዘጋጁልን ፡ ብለው ፡ ወንዶቹ ፡ ቢያመለክቱ ፡ አይፈቀድላቸውም ። ሴቶቹ ፡ ከወንዶቹ ፡ እኩል ፡ ዶማቸውን ፡ እየያዙ ፡ ወጥተው ፡ የኢጣሊያኖቹን ፡ እርሻ ፡ ሲቈፍሩ ፡ ይውላሉ ፡ ምሳቸውንም ፡ በ6 ፡ ሰዓት ፡ እዚያው ፡ እርሻቸው ፡ ላይ ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ አብስለው ፡ ይበላሉ ፡ እንጂ ፡ እቤታቸው ፡ እንዳይሄዱ ፡ ክልክል ፡ ነው ። ደከመን ፡ ቢሉም ፡ ሊያርፉ ፡ አይችሉም ። ከፊት ፡ አጐንብሰው ፡ ሲሠሩ ፡ ከኋላ ፡ ፈረንጁና ፡ የሱማሌው ፡ አሠሪ ፡ ኣንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቆም ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይደበድቧቸዋል ። ያመማቸውም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እዚያው ፡ እርሻ ፡ ላይ ፡ ይተኛሉ ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ይዟቸው ፡ የሄደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሐኪሙ ፡ ባለኮንሴስዮኑን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ዋሽተኸ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ዋሽተሽ ፡ ነው ፡ አልታመማችሁም ፡ ብሎ ፡ እጁን ፡ እፊታቸው ፡ ላይ ፡ ለመመርመር ፡ አስመስሎ ፡ ያስጠጋና ፡ ወዲያው ፡ በጥፊ ፡ ብሎ ፡ ይመልስና ፡ ለባለኮንሴስዮኑ ፡ ያስረክበዋል ። ርሱም ፡ በቶሎ ፡ እዚያው ፡ ወደ ፡ ርሻው ፡ አምጥቶ ፡ ከሠራተኞች ፡ ጋራ ፡ ይደባልቃቸዋል ። በውነት ፡ ታመዋል ፡ ተብለው ፡ የሚመሰክርላቸው ፡ ብርቆች ፡ ናቸው ። እንደዚሁም ፡ ደከመን ፡ ወይም ፡ ታመምን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ሬዚዴንቴው ፡ (ወደ ፡ ገዥው) ፡ ላቤቱታ ፡ የሄዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተደብድበው ፡ በዘበኛ ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ ሥራቸው ፡ ይመለሳሉ ። ወይም ፡ እወህኒ ፡ ቤት ፡ ታስረው ፡ ሲወጡ ፡ ይመለሳሉ ፡ እንጂ ፡ ጣሊያን ፡ የሆነውን ፡ ጌታቸውን ፡ ጣሊያን ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ሄደው ፡ አንዳች ፡ ፍርድ ፡ ሊያገኙ ፡ አይችሉም ፡ ነበር ።

ከሴቶቹ ፡ ሠራተኞች ፡ መካከል ፡ ገሚሶቹ ፡ ያረገዙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነሱም ፡ እንደ ፡ ሐኪሙ ፡ ቃል ፡ መውለጃቸው ፡ 5 ፡ ወይም ፡ 10 ፡ ቀን ፡ ቢበዛም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ ሲቀረው ፡ ዕረፍት ፡ ይሰጣቸዋል ። ሊወልዱ ፡ ሄደውም ፡ በተሰጠው ፡ ቀን ፡ ተጠብቀው ፡ ሳይወልዱ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ሥራቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ ይገደዳሉ ።

እኔም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ የተመለከትሁ ፡ ስለ ፡ ሆንሁ ፡ ሁኔታውን ፡ ዛሬ ፡ ደኅና ፡ አድርጌ ፡ ለመግለጽ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የፎቶግራፍ ፡ ማንሻ ፡ መኪና ፡ ስለሌለኝና ፡ ማንሣት ፡ ስላልቻልሁ ፡ አዝናለሁ ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ በጄ ፡ ቢኖርና ፡ ለማንሣት ፡ ብችል ፡ ግን ።

1. ከፊት ፡ ሲሠሩ ፡ ከኋላ ፡ ሲደበደቡ ።
2. ወላዷ ፡ ሴት ፡ ጨቅላ ፡ ሕፃኗን ፡ በሙዝ ፡ ሥር ፡ አስደግፋ ፡ ርሷ ፡ ስትሠራ ።
3. ሐኪም ፡ አልታመምኽም ፡ ብሎ ፡ የመሰከረበት ፡ ግደለኝ ፡ እንጂ ፡ አልሠራም ፡ ብሎ ፡ በርሻው ፡ ውስጥ ፡ ተኝቶ ፡ ሲያቃስት ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ኣንሥቼ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ እንዲታይ ፡ ባደረግሁ ፡ ነበር ።

እነዚህም ፡ ሱማሌዎች ፡ ከዚህ ፡ ሥቃይ ፡ ቢታመሙ ፡ ሐኪም ፡ ደከመን ፡ ቢሉ ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ ሊያድኗቸው ፡ አይችሉም ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ ሥቃይ ፡ ለመዳኛ ፡ አንድ ፡ ተስፋ ፡ ብቻ ፡ ነበራቸው ። ይኸውም ፡ ቀን ፡ በረሓ ፡ ለብሰው ፡ እየዋሉ ፡ ሌሊት ፡ እየተጓዙ ፡ አምልጠው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ መግባት ፡ ነበረ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይኸውም ፡ እንደ ፡ ብርቅ ፡ የሚያዩት ፡ ተስፋቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ የተያዘች ፡ ጊዜ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ምናልባት ፡ እንኳን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ይኸንን ፡ ዐውቆ ፡ ባይከራከርበት ፡ ሙሶሊኒ ፡ ግን ፡ በግዛቱ ፡ ይህ ፡ መሠራተን ፡ እያወቀ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባሪያ ፡ ትገዛለች ፡ ብሎ ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ ፊት ፡ መክሰሱ ፡ ይገርማል ፡ በማለት ፡ ኣሳቤን ፡ ወስኜ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ነገሬ ፡ እመለሳለሁ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በተለይ ፡ መኳንንቱና ፡ ወጣቱ ፡ ያገሩንና ፡ የውጭን ፡ አገር ፡ ትምህርት ፡ ጨምሮ ፡ የሚያውቀው ፡ እንዲሁም ፡ ከተራው ፡ ሕዝብም ፡ ውስጥ ፡ እየሰበሰቡ ፡ በያለበት ፡ ሲያግዙ ፡ ሕዝቡም ፡ በየሄደበት ፡ አገር ፡ ገሚሱን ፡ በሽታ ፡ ገሚሱን ፡ የሥራ ፡ ድካም ፡ ከጨረሰው ፡ በኋላ ፡ በኤውሮፓ ፡ የሚደረገው ፡ ፖለቲካና ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ጽናት ፡ የኢጣሊያን ፡ መንግሥት ፡ የፖለቲካ ፡ ኀይሉን ፡ ወደ ፡ ሰላማዊነት ፡ እንዲያዞር ፡ አስገደደው ።

# ምዕራፍ ፡ 77 ።

## የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የኀይል ፡ ፖለቲኩን ፡ ለመለወጥ ፡ እንደ ፡ ተገደደ ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ለመያዝ ፡ ችሎት ፡ ከሰጠው ፡ መሣሪያ ፡ በቀር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመግዛት ፡ ሌላ ፡ ተስፋ ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፡ ነበር ፡ ይኸውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የነገድ ፡ ልዩነት ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ አሳብ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ከሴም ፡ ዘር ፡ የመጣው ፡ የትግሬና ፡ የሸዋ ፡ የጐጃም ፡ የበጌምድርና ፡ በጠቅላላው ፡ አማራ ፡ የሚባለው ፡ 2ኛው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምዕራብና ፡ ደቡብ ፡ የሚገኙት ፡ እነወለጋ ፡ እነጅማ ፡ እነሲዳሞ ፡ እነአሩሲና ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉት ፡ አገሮች ፡ ከካም ፡ ዘር ፡ የመጡ ፡ በነገድም ፡ በቋንቋም ፡ በሃይማኖትም ፡ የተለዩ ፡ ናቸውና ፡ 1ኛው ፡ ወገን ፡ ቢያምጥብኝ ፡ 2ኛውን ፡ ወገን ፡ ይገዥ ፡ አጠፋዋለሁ ፡ የማለት ፡ ተስፋ ፡ ነበረውና ፡ ይኸንንም ፡ ሊሠራበት ፡ እንደ ፡ ጣረ ፡ በጕልሕ ፡ ታይቷል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ 3ሺህ ፡ ዓመት ፡ ባለው ፡ የነፃነቱ ፡ ዘመን ፡ በታሪኩ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ የሚያሳፍር ፡ ገጽ ፡ የሌለበት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ይኸው ፡ ሕዝብ ፡ አንድነቱን ፡ አሳይቶ ፡ ለጠላቱ ፡ ፕሮግራም ፡ ሳይመች ፡ ቀረ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የዠግንነት ፡ ዝናው ፡ ሲነገር ፡ የቈየውን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ ለማስመስከር ፡ ሲል ፡ በጠላቱ ፡ እጅ ፡ የሚያስፈራ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያ ፡ ሕግንም ፡ ተላልፎ ፡ የሚሠራበት ፡ ቦምብና ፡ የጋዝ ፡ መርዝ ፡ መኖሩን ፡ እያውቀ ፡ ይህንኑ ፡ ጠላቱን ፡ ሊከላከል ፡ ከከተማም ፡ ከባላገርም ፡ ከታላላቅና ፡ ከታናናሽም ፡ አውራጃዎች ፡ ከገበሬም ፡ ከነጋዴም ፡ ከጸሓፊም ፡ ከወታደርም ፡ ከቤተ ፡ ክህነትም ፡ ከጋላም ፡ ካማራም ፡ ከሴትም ፡ ሳይቀር ፡ ከየነገዱ ፡ ሁሉ ፡ አለቃና ፡ ጭፍራው ፡ እየተስማማ ፡ በያለበት ፡ ተሠራጨ ፡ ከነዚህም ፡ ከብዙዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ለጊዜው ፡ ስማቸው ፡ የታወቀው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ተጽፈዋል ።

### ሸዋ ።

ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡

ደጃዝማች ፡ ፍቅረ ፡ ማርያም ፡

>> ወልደ ፡ ማርያም ፡

>> መስፍን ፡ ስለሺ ፡

ከንቲባ ፡ ታከለ ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡

ደጃዝማች ፡ ዘውዱ ፡ አባ ፡ ኰራን ፡

>> አውራሪስ ፡

>> መንገሻ ፡ ወሰኔ ፡

>> ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡

>> ከፈለው ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡

>> ኀይሉ ፡ ወልደ ፡ መድኅን ፡

>> ተሰማ ፡ ሸንቀጥ ፡ (በቡልጋ) ፡

>> ዘውዴ ፡ አስፋው ፡

>> ገረሱ ፡ (በወሊሶ ፡ ባመያ) ፡

>> በቀለ ፡ (በሶዶ ፡ በጕራጌ) ፡

ወይዘሮ ፡ ከበደች ፡ ሥዩም ፡

>> ሸዋ ፡ ረገድ ፡ ገድሌ ፡

>> ቀለመ ፡ ወርቅ ፡ ጥሩነኽ ፡

ፊታውራሪ ፡ ኃይሌ ፡ አባ ፡ መርሳ ፡ (በኮንታ) ፡

>> ገዛኸኝ ፡

>> ተድላ ፡ መኰንን ፡

>> ፀሓዩ ፡ ዕንቍ ፡ ሥላሴ ፡

>> ወልደ ፡ ጻድቅ ፡

>> ወዳጆ ፡

>> ተረፈ ፡

>> ከበደ ፡ ካሳ ፡

>> ኀይለ ፡ ማርያም ፡ ማናኽሌ ፡

>> ታደሰ ፡ ጌታ ፡ ብቻኽ ፡

>> ከበደ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡

>> መኰንን ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡

>> ተሰማ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡

>> ታደሰ ፡ ኀይሌ ፡

>> ዳርጌ ፡

>> ዝቅ ፡ አርጌ ፡

>> ይለ ፡ ማርያም ፡ ቸሬ ፡

>> ተወንድ ፡ በላይ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡

>> ደባልቄ ፡

>> ዳርጌ ፡

>> ኪዳኔ ፡ ወልደ ፡ መድኀን ፡

>> ሞገስ ፡ መኵሪያ ፡ ( በአሳግርት) ፡

>> አጐናፍር ፡

>> ደምሴ ፡ ወልደ ፡ ዐማኑኤል ፡

>> አማረ ፡

>> ይልማ ፡ በሼ ፡ (በእንሳሮ) ፡

>> ከበደ ፡ ብዙነሽ ፡ (ሜታ) ፡

>> ወንድምነኽ ፡ ገብረ ፡ ኪዳን ፡

ፊታውራሪ ፡ ደስታ ፡ ሽዋርካብኽ ፡ (በሐር ፡ አምባ) ፡

>> ኪዳኔ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡

ወህኒ ፡ አዛዥ ፡ አየለ ፡ ኀይሌ ፡

ከንቲባ ፡ ከበረ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ልጅ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ማሞ ፡

ቀኛዝማች ፡ ጐበዜ ፡

>> መንግሥቴ ፡

>> ዳኜ ፡ ደጋጋ ፡

>> ታችበሌ ፡

>> በቀለ ፡ ወልደ ፡ መድኅን ፡

>> ኀይለ ፡ ማርያም ፡

>> ተስፋዬ ፡ ዕንቁ ፡ ሥላሴ ፡

>> ታደሰ ፡ ገነሜ ፡

ግራዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በላይነኽ ፡

>> ሽንቁጤ ፡

ባላምባራስ ፡ በሻኽ ፡

ባሻ ፡ ወልዴ ፡ (ጣርማ ፡ በር) ፡

>> ኤፍሬም ፡

የሻለቃ ፡ ጃገማ ፡

ልጅ ፡ ግዛቸው ፡ ኀይሌ ፡

>> ተኩላ ፡ ድል ፡ ነሣሁ ፡

>> ሣህሌ ፡ ዕንቁ ፡ ሥላሴ ፡

አቶ ፡ ኪዳኔ ፡ በልሁ ፡

>> አበበ ፡ ሸንቀጥ ፡

>> ተሰማ ፡ ርገጤ ፡

>> ጅማ ፡ ሰንበቴ ፡

>> በሻህ ፡ ኃይሌ ፡

>> በንቲ ፡ ጉሮ ፡

>> በቀለ ፡ ወሰኔ ፡

## በትግሬ ።

ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡

>> ዐባይ ፡ ካሳ ፡

>> ከበደ ፡

## በጐጃም ።

ራስ ፡ ኀይሉ ፡ በለው ፡

ቢትወደድ ፡ ነጋሽ ፡ በዛብሽ ፡

ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡

>> በላይ ፡ ዘለቀ ፡

ፊታውራሪ ፡ ኀይለ ፡ ኢየሱስ ፡ ፍላቴ ፡

>> ዘለቀ ፡ ደስታ ፡

>> አያሌው ፡ መኰንን ፡

>> ደረሰ ፡ ሺፈራው ፡ (ሜጫ) ፡

>> በየነ ፡ ቢሻው ፡

>> ሺፈራው ፡ ረታ ፡

>> በቀለ ፡ አምባዬ ፡

>> በቀለ ፡ ካሳ ፡

## በሰቈጣ ።

ደጃዝማች ፡ ኀይሉ ፡ ከበደ ፡ (በዋናው ፡ ጦርነት ፡ ጊዜና ፡ ባርበኝነት ፡ ሕይወታቸውን ፡ የሠዉ)

ደጃዝማች ፡ ወንድ ፡ በወሰን ፡ ካሳ ፡ (በአርማጭሆ) ፡

ደጃዝማች ፡ ውብነኸ ፡ ተሰማ ፡

## በጐንደር ።

ደጃዝማች ፡ አዳነ ፡

## በበጌምድር ።

ደጃዝማች ፡ አስፋው ፡ ቦጋለ ፡ (በመና ፡ መቀጠዋ) ፡

>> ዳኘው ፡ ተሰማ ፡

ፊታውራሪ ፡ አስፋው ፡ ይግዛው ፡ (በስማዳ) ፡

>> በረደድ ፡ አስፋው ፡

>> ይማም ፡ ተሰማ ፡ (በእስቴ) ፡

ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ አሁን ፡ በተጠሩበት ፡ ሹመታቸው ፡ በሕይወት ፡ ያሉ ፡ ገሚሾቹ ፡ የሞቱ ፡ አሉ ።

ሰልችቷቸው ፡ ከገቡት ፡ ከጥቂቶቹ ፡ በቀር ፡ እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩትና ፡ ከነዚህም ፡ ሌላ ፡ ስማቸውን ፡ ለጊዜው ፡ ያላገኘነው ፡ አርበኞች ፡ ጭፍራ ፡ ጭፍራቸውን ፡ እየያዙ ፡ በያለበት ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ፊት ፡ ለፊትም ፡ እየገጠሙ ፡ በደፈጣም ፡ እየሆኑ ፡ ሲዋጉ ፡ ኖሩ ። ድል ፡ ከሚሆኑበትም ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፡ ድል ፡ እያደረጉ ፡ የሚመለሱበት ፡ ጊዜ ፡ ይበልጣል ።

የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ አዛዥም ፡ ከኋላ ፡ የነጩን ፡ ከፊት ፡ ያገር ፡ ተወላጁን ፡ ወታደር ፡ እያደረገ ፡ ዘንድሮ ፡ ያርበኛን ፡ ነገር ፡ እጨርሳለሁ ፡ እያለ ፡ በኀይል ፡ ሲነሣ ፡ እነሱም ፡ ኀይሉን ፡ በኀይል ፡ እየሰባበሩ ፡ ይመልሱት ፡ ዠመር ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የዓለም ፡ ማኅበርን ፡ አሸንፎ ፡ በኀይል ፡ ጦርነት ፡ እንደ ፡ ዠመረ ፡ የተንቤንንና ፡ የማይጨውን ፡ ጦርነት ፡ በኀይልና ፡ ባረመኔነት ፡ እንደ ፡ ፈጸመ ፡ መናገሻ ፡ ከተማዋንም ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ ታማኝ ፡ ሆኖ ፡ የገባለትን ፡ ሕዝብ ፡ በኀይል ፡ ለማስተዳደር ፡ አርበኞችንም ፡ በኀይል ፡ ለማጥፋት ፡ ተነሣ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ አርበኛን ፡ መደምሰስ ፡ ሊዋጥ ፡ የማይቻል ፡ መራራ ፡ ጕርሻ ፡ ሆነበት ።

ከ1928 ፡ ዓ ፡ ም ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ 1930 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ በታማኝነት ፡ የተቀመጠውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ደም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አኳኋን ፡ እስከሚቻለው ፡ ድረስ ፡ አፈሰሰ።

ራሱ ፡ በቀጥታ ፡ ከሚያፈሰው ፡ ደም ፡ በቀር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ክርስቲያኑን ፡ በእስላም ፡ ጋላውን ፡ ባማራ ፡ ኣዳሉን ፡ በሱማሌ ፡ የተማረውን ፡ ባልተማረ ፡ ወጣቶቹን ፡ በሽማግሌዎች ፡ ጌታውን ፡ ባገልጋይ ፡ እመቤቲቱን ፡ ካገልጋዩቱ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ሊያዋጋና ፡ በመጨረሻም ፡ ለምለሙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስፍራ ፡ ባዶ ፡ ሲሆን ፡ የራሱን ፡ ሕዝብ ፡ አምጥቶ ፡ ለመተካት ፡ የተረፈውንም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ በረሓ ፡ ለማዛወር ፡ መሠረታዊ ፡ አሳቡ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ለዚሁ ፡ ፕሮግራሙ ፡ እንዲመቸው ፡ በጋላው ፡ አገር ፡ ያማራ ፡ ወታደር ፡ አስቀመጠ ። እንደዚሁ ፡ ላማራ ፡ አገር ፡ የጋላ ፡ ወታደር ፡ የጋላ ፡ ዘርነት ፡ ላለው ፡ አርበኛ ፡ ያማራውን ፡ ወታደር ፡ በሸዋ ፡ ላለውም ፡ አርበኛ ፡ የኤርትራንና ፡ የጋላን ፡ ወታደር ፡ እየላከ ፡ ሲያዋጋ ፡ ኖረ ። በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኣጠገብ ፡ የእስላም ፡ መስጊድ ፡ በጳጳሱ ፡ አጠገብ ፡ ቃዲ ፡ እያደረገ ፡ በመፎካከርና ፡ በመመቀኛኘት ፡ እንዲጣሉ ፡ አደረገ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ የሚያደርገው ፡ ስብከት ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በጠብ ፡ ዐይን ፡ እየተያዩ ፡ በመካከሉ ፡ የራሱ ፡ ገዥነት ፡ እንዲጸድቅ ፡ የሚያደርግለት ፡ ነበር ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የወገን ፡ መለየት ፡ ፖለቲኩ ፡ በገሚስ ፡ እንደ ፡ ጠቀመው ፡ ወገን ፡ ለይቶ ፡ ይተላለቅልኛል ፡ ብሎ ፡ እዳር ፡ ቁሞ ፡ ቢመለከት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጋላውም ፡ አማራውም ፡ ውስጡን ፡ የመተባበር ፡ መንፈስ ፡ አደረበት ። የሚያምረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ገጹን ፡ ሳይለውጥ ፡ በሸዋ ፡ ብዙ ፡ አርበኞች ፡ በራስ ፡ አበበ ፡ እየተመሩ ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ በየጊዜው ፡ ሲሰብሩ ፡ እንዲሁም ፡ በሰቈጣ ፡ በደጃዝማች ፡ ኀይሉ ፡ ከበደ ፡ መሪነት ፡ በትግሬ ፡ በደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ መሪነት ፡ በጋላ ፡ አገር ፡ በደጃዝማች ፡ ገረሱ ፡ መሪነት ፡ በጉራጌ ፡ በደጃዝማች ፡ በቀለ ፡ ወያ ፡ መሪነት ፡ በጐጃም ፡ በነደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጃምበሬ ፡ መሪነት ፡ በቦረናና ፡ በገሙ ፡ በነደጃች ፡ ተስፋዬ ፡ ወልዴ ፡ መሪነት ፡ እንዲሁም ፡ በያውራጃው ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኛ ፡ እየተነሣ ፡ የጠላቱን ፡ ኃይል ፡ ይሰብር ፡ ዠመር ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ «ኢትዮጵያን ፡ ያዝሁ ፡ ጦርነቱ ፡ አለቀ ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሰላም ፡ ሥራ ፡ ተመሥርቷል ፡ የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፡ የኔን ፡ ገዥነት ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ወዶ ፡ ተቀብሏል » ፡ ብሎ ፡ አስታውቆ ፡ ነበርና ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በኤውሮፓ ፡ ሆነው ፡

በፖለቲካ ፡ ክርክር ፡ ወታደሮቻቸውም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተራራና ፡ ጫካ ፡ ሆነው ፡ በጦርነት ፡ በተከላከሉና ፡ ይህንኑም ፡ ዓለም ፡ በግልጽ ፡ በተረዳ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩ ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የሚያሳፍረው ፡ ሆነ ። ስለዚህ ፡ «እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ የነዚህን ፡ የአርበኞች ፡ ድምፅ ፡ የምሰማው ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብላችሁ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ባለው ፡ ኀይላችሁ ፡ ጨርሱልኝና ፡ ከጭቅጭቅ ፡ አሳርፉኝ» ፡ ሲል ፡ ሙሶሊኒ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ወዳሉት ፡ ወደ ፡ ዱካ ፡ ዳዎስታና ፡ ወደ ፡ ጄኔራል ፡ ናዚ ፡ ላከ ፡ ይባላል ። እነሱም ፡ ባታዮ ፡ በባታዮ ፡ እያከታተሉ ፡ አርበኞችን ፡ ለመጨረስ ፡ ቢልኩ ፡ አርበኞች ፡ ድል ፡ እየመቱ ፡ ይመልሷቸው ፡ ዠመር ። በዚህም ፡ ዐይነት ፡ 3ቱን ፡ ዓመት ፡ ቢደግሙት ፡ ቢደጋግሙት ፡ ምንም ፡ የተለወጠ ፡ ነገር ፡ አላገኙም ። ጥቂቶች ፡ በእጃቸው ፡ የወደቁ ፡ አርበኞች ፡ እያገኙ ፡ ቢሰቅሏቸው ፡ ራሳቸውንም ፡ ባረመኔነት ፡ ቢያስቈርጡ ፡ ይልቁንም ፡ ይኸው ፡ አረማዊ ፡ ሥራቸው ፡ የአርበኛን ፡ ኀይል ፡ አስጨከኖ ፡ አበረታው ፡ እንጂ ፡ ሊያላላው ፡ አልቻለም ። በብዙ ፡ ማባበልና ፡ በብዙ ፡ ተስፋ ፡ መስጠት ፡ አሥር ፡ አርበኞች ፡ አስገብተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከ2 ፡ የሚበልጡ ፡ ተገዥዎች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ አርበኝነት ፡ ይወጣሉ ። በመጨረሻም ፡ የአርበኝነት ፡ ስም ፡ እያማረ ፡ እየገነነ ፡ የባንድነት ፡ ስም ፡ እያስቀየመ ፡ ይሄድ ፡ ዠመር።

የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ በውጭ ፡ አርበኞቹ ፡ በመትረየስና ፡ በጠመንዣ ፡ ሲቈሉት ፡ እንደዚሁ ፡ በውስጡ ፡ ያሉ ፡ ሕዝቦች ፡ ካርበኛም ፡ በመላላክ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ በመሰባበክ ፡ መንግሥቱን ፡ በነገር ፡ ይቈሉት ፡ ዠመር ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ራሱ ፡ የዞረ ፡ ያኸል ፡ ሆኖ ፡ ማስተዳደር ፡ አቃተው ። በሾማቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ እምነት ፡ ባልሾማቸው ላይ ፡ ካለው ፡ ልዩነት ፡ አጣ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ እውነተኞች ፡ ሰላዮችና ፡ ባንዶች ፡ ቢኖሩ ፡ ለዚያ ፡ ጊዜ ፡ ባንዳውና ፡ አርበኛው ፡ ሰላዩና ፡ ተሰላዩ ፡ ተዘባረቀበት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የፋሺስት ፡ ፌዴራሲዮን ፡ ሹም ፡ በመበሳጨት ፡ ያለውን ፡ ሕዝብ ፡ እስላሙንና ፡ ክርስቲያኑንም ፡ አማኙንም ፡ ሁሉንም ፡ ባንድነት ፡ እንፍጅና ፡ በፊታችን ፡ ያለውን ፡ ጠላታችንን ፡ እንደ ፡ ልባችን ፡ እንግፋ ፡ የማለት ፡ አሳብ ፡ ኣድሮበት ፡ ሲያመዛዝኑ ፡ በመካከሉ ፡ ዱካ ፡ ዳዎስታና ፡ ጄኔራል ፡ ናዚ ፡ ፍራንካ ፡ የሚባሉት ፡ የነዚህን ፡ ፖለቲካ ፡ ተቃውመው ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ፖለቲካ ፡ ለመመሥረት ፡ ተስማሙ ፡ ይባላል ።

ይኸውም ፡ የኀይሉንና ፡ የደም ፡ ማፍሰሱን ፡ ሥራ ፡ አቁመው ፡ ካርበኛ ፡ ጋር ፡ ዕርቅ ፡ ማድረግ ፡ በያገሩ ፡ የታሰረውን ፡ እስረኛ ፡ መፍታት ፡ ርስቱን ፡ የተቀማውን ፡ መመለስ ፡ ወጣቱን ፡ ላገሩ ፡ አሳቢ ፡ የሆነውን ፡ ወገን ፡ መኳንንቱንና ፡ ሴት ፡ ወይዘሮውን ፡ በገንዘብና ፡ በሹመት ፡ በሽልማት ፡ ማሸነፍ ።

እነዚህም ፡ የዚህን ፡ ፕሮግራም ፡ አደራጅተው ፡ ለመሥራት ፡ ሲዠምሩ ፡ እነዚያ ፡ የደም ፡ ሰው ፡ የሆኑት ፡ ፋሺስቶች ፡ የሰላማዊውን ፡ ሕዝብ ፡ የሽማግሌውንም ፡ የሕፃኑንም ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ለመዱ ፡ ለማፍሰስ ፡ ኣቈብቀኀበው ፡ ሳለ ፡ ለጊዜው ፡ የነናዚና ፡ የነፍራንካ ፡ ፕሮግራም ፡

እንዲሠራበት ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ስለ ፡ ተቀበለው ፡ የኤውሮፓና ፡ ያርበኞች ፡ ጦርነት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ መሣሪያቸውን ፡ በየመጋዘናቸው ፡ እያስቀመጡ ፡ ይጠባበቁ ፡ ዥመር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በኢጣሊያ ፡ በናኩራ ፡ በደናኔ ፡ ታስሮ ፡ ከሞት ፡ የተረፈውን ፡ እየፈቱ ፡ ወዳገሩ ፡ መለሱት ። ቤቱን ፡ ርስቱን ፡ እየቀሙ ፡ አባረውት ፡ የነበረውን ፡ መለሱለት ፥ ወይም ፡ ኪራይ ፡ እንዲቀበል ፡ አደረጉ ። በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የከበረውን ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ራስ ፡ ደጃዝማች ፡ ፊታውራሪ ፡ እያሉ ፡ የማይገባውን ፡ ሁሉ ፡ ሾሙት ። አሥመራን ፡ ሲገዙ ፡ ላገር ፡ ተወላጅ ፡ ሰጥተውት ፡ የማያውቁትን ፡ የኮማንዳቶርና ፡ የካባሌሪነት ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ለተርታ ፡ አስተርጓሚዎችና ፡ ምስለኔዎች ፡ ሰጧቸው ። ላንድ ፡ አስተርጓሚ ፡ ወይም ፡ ምስለኔ ፡ ከ150 ፡ ወይም ፡ ከ350 ፡ ሊሬ ፡ በላይ ፡ ሰጥተው ፡ የማያውቁትን ፡ ካ1 ፡ ሺህ ፡ እስከ ፡ 3 ፡ ሺህ ፡ ሊሬ ፡ ቀለብ ፡ ይሰጡ ፡ ዥመር ። ቸግሮኛል ፡ ብሎ ፡ ለሚያመለክታቸው ፡ ላንድ ፡ ጊዜ ፡ ጉርሻ ፡ እስከ ፡ 20 ፡ ሺህ ፡ ዳራጎት ፡ ይሰጡ ፡ ዥመር ። ጥቊርን ፡ ለመቅረብ ፡ ይጠየፉ ፡ የነበሩትን ፡ እስከ ፡ ቤቱ ፡ ድረስ ፡ እየሄዱ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ እየጠሩ ፡ ኣብረው ፡ እየተጋበዙ ፡ የኀዘኑም ፡ የደስታውም ፡ ተካፋይ ፡ መሰሉ ። ፊት ፡ ለፊት ፡ እየተዋጋ ፡ የበደላቸውን ፡ አርበኛ ፡ በዘመዱ ፡ በኩል ፡ አባብለው ፡ ከገባላቸው ፡ በኋላ ፡ ገበርዲን ፡ እያለበሱ ፡ መትረየስ ፡ ሽጉጥ ፡ እየስታጠቁ ፡ ለሽርሽር ፡ ኦቶ ፡ ሞቢል ፡ እየጨመሩ ፡ ለቀቁት። ከመኳንንቱም ፡ ከወጣቱም ፡ ከካህናቱም ፡ ከወይዛዝሩም ፡ መካከል ፡ ገሚሱን ፡ ሮማ ፡ ድረስ ፡ በከበሬታ ፡ እየወሰዱ ፡ የሮማን ፡ ከተማ ፡ በማሳየትና ፡ በዚያ ፡ ያለውን ፡ ኀይላቸውን ፡ በመመልከት ፡ በልቡ ፡ እንዲረታ ፡ ከሙሶሊኒም ፡ እያገናኙ ፡ መለሱት ። በተቻላቸው ፡ መጠን ፡ ሕዝቡ ፡ ከሕዝባቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ እንዲቀራረብና ፡ በማይጨው ፡ ጦርነትና ፡ በግራዚያኒ ፡ የተነሣ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የጠላትነት ፡ ቊስል ፡ እንዲድን ፡ አሰቡ ።

ምክንያቱም ፡ የኤውሮፓ ፡ ጦርነት ፡ ተፈጽሞ ፡ በውጭ ፡ ያለው ፡ አርበኛም ፡ ስደተኛውም ፡ ተመልሶ ፡ በገባላቸው ፡ ጊዜ ፡ በጠባያቸውና ፡ በደም ፡ ሥራቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ እውነተኛውን ፡ የጭካኔ ፡ ሥራቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ እንጂ ፡ በውነት ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ደኅንነትና ፡ ክብረት ፡ አስበው ፡ አልነበረም ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ወጥመድ ፡ በሕዝቡና ፡ ይልቁንም ፡ ባርበኞች ፡ ዘንድ ፡ የተሰወረ ፡ አልነበረም ። ያርበኞችንም ፡ ድካም ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ሎንዶን ፡ መኖርና ፡ ከዚያ ፡ በየጊዜው ፡ የሚላከው ፡ ደብዳቤና ፡ ጋዜጣ ፡ እያጽናና ፡ ያበረታቸው ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መሣ ፡ ለመሣ ፡ እንደሚተያይ ፡ ሁለት ፡ መንግሥት ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጦርነቱ ፡ እንዲቆምና ፡ ዕርቅ ፡ እንዲደረግ ፡ ወደ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበና ፡ ወደ ፡ ሌሎችም ፡ ያርበኛ ፡ ኣለቆች ፡ መላክተኛ ፡ ላከ ፡ ለራሳቸውና ፡ ለጭፍሮቻቸውም ፡ ገበርዲን ፡


ሱካር ፡ ዱቄት ፡ በያይነቱ ፡ ዐረቄ ፡ በየጊዜው ፡ እያስጫነ ፡ ይልክላቸው ፡ ዠመር ፡ ቀጥሎም ፡ የኔ ግዛት ፡ ከዚህ ፡ አያልፍም ፡ የናንተም ፡ ግዛት ፡ ከዚህ ፡ ይደርሳል ፡ እያለ ፡ ይካለላቸው ፡ ዠመር

ከኢጣሊያኖቹም ፡ መላክተኛ ፡ እየሄደ ፡ ባርበኞች ፡ ዘንድ ፡ ካርበኞችም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ዘንድ ፡ እየሄደ ፡ እንደ ፡ ጕዳይ ፡ ፈጻሚ ፡ ይቀመጥ ፡ ዠመር ፡ ኢጣሊያኖቹም ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ለመጣው ፡ አርበኛ ፡ እነሱን ፡ ከልቡ ፡ ካገለገላቸው ፡ ይበልጥ ፡ ክብር ፡ ሰጥተው ፡ ኣቈላመጡት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ለኢጣሊያ ፡ ተገዥ ፡ የሆኑትና ፡ ስለ ፡ ኢጣሊያ ፡ የሚሠሩት ፡ መኳንንቶችና ፡ ወጣቶች ፡ በርግጥ ፡ ስላገር ፡ መሥራት ፡ በመጨረሻ ፡ ምን ፡ ያኸል ፡ እንደሚያስከብር ፡ ተገነዘቡት ። ምነው ፡ እኛም ፡ የሱ ፡ ታማኝ ፡ ሆነን ፡ ከመገዛት ፡ ከርሱ ፡ ሽፍተን ፡ አርበኛ ፡ በሆን ፡ ኖሮ ፡ ብሎ ፡ ያልተመኘ ፡ የለም ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ የወጣ ፡ አለ ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ይኸን ፡ በመሰለ ፡ አኳኋን ፡ ጦርነቱን ፡ ለማቆምና ፡ አርበኞቸን ፡ ለማዘንጋት ፡ ወይም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተለያይተው ፡ እንዲገቡለት ፡ ሲጥር ፡ አርበኞች ፡ ግን ፡ በንግግሩ ፡ ተሰብከው ፡ በስጦታው ፡ ተሸንፈው ፡ አልገቡለትም ። ጦርነቱንም ፡ ለማቆም ፡ ስንኳን ፡ አልፈለጉም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዱካ ፡ ዳዎስታ ፡ ጄኔራል ፡ ናዚ ፡ ዶክተር ፡ ፍራንካ ፡ ተስፋ ፡ ባለመቁረጥና ፡ በጠንካራነት ፡ ይኸንን ፡ ፖለቲካ ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ ያለዕረፍት ፡ ተከታተሉት ። ለዚያ ፡ ጊዜ ፡ ፍሬ ፡ ሊያፈራላቸው ፡ ዠምሮ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አርበኞች ፡ ጦሩን ፡ በጦርነት ፡ ፖለቲኩን ፡ በፖለቲካ ፡ እየመለሱ ፡ ጠንክረው ፡ ይከራከሩት ፡ ዠመር ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኤውሮፓ ፡ የጦርነት ፡ ወሬ ፡ እየገነነ ፡ መሄዱ ፡ በያለበት ፡ ከመሰማቱ ፡ ይልቅ ፡ ራሱ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የሚያደረገው ፡ ማባበልና ፡ መለማመጥ ፡ ነገሩን ፡ በሰፊው ፡ ስለሚገልጸው ፡ አርበኞች ፡ እየፋፉና ፡ ኵራት ፡ እየተሰማቸው ፡ ሄደ ።

በውስጡ ፡ ተገዥ ፡ ሆነው ፡ የተቀመጡትም ፡ ሕዝቦች ፡ ያርበኞችን ፡ ስም ፡ ከፍ ፡ በማድረግ ፡ የነርሱን ፡ ስም ፡ ዝቅ ፡ በማድረግ ፡ በገሃድ ፡ ማውራት ፡ ዠመሩ ። የኢጣሊያም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ኣርበኞችም ፡ በዘፈን ፡ ሌላውም ፡ ሕገብ ፡ በጉባኤና ፡ በየመሸታ ፡ ቤት ፡ ያወራ ፡ ዠመር ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ብዙ ፡ ሰላይ ፡ አድርጎ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ወሬ ፡ ከሰላዮቹ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ቅጣት ፡ እንዳይዠምርና ፡ ያመነበት ፡ ፖለቲካ ፡ እንዳይሰናከልበት ፡ በጭካኔ ፡ ታገሠ ። ለበደሉት ፡ ካገለገሉት ፡ ለተሰላዩ ፡ ከሰላዩ ፡ ለአርበኛው ፡ ከባንዳው ፡ ይበልጥ ፡ ሽልማትና ፡ ስጦታ ፡ ያደርግ ፡ ዠመር ፡ የመሬት ፡ ግብርና ፡ የንግድ ፡ ቀረጡንም ፡ ሁሉ ፡ ከመቀበል ፡ ታግዶ ፡ ቸርነት ፡ ያደርግ ፡ ገዠመር ።



ከአርበኞቹ ፡ አንዱ ፡ ፊታውራሪ ፡ ኃይሌ ፡ ኣባ ፡ መርሳ ።

ገንዘቡን ፡ ለጳጳስ ፡ ለቀሳውስት ፡ ለካህናት ፡ ለመኳንንት ፡ ለተራ ፡ ሕዝብ ፡ ለሴት ፡ ወይዘሮ ፡ « የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ቸር ፡ ነው» ፡ ብቻ ፡ እንዲባል ፡ እንዳለወገን ፡ በተነው ።

በኢጣሊያ ፡ አገር ፡ ይልቁንም ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያሉት ፡ ኢጣሊያኖች ፡ የሚለብሱትና ፡ የሚበሉት ፡ እያጡ ፡ በባዶ ፡ እግራቸው ፡ ሲሄዱ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ መቼም ፡ በመጨረሻ ፡ አያጡትም ፡ በማለት ፡ እነሱን ፡ ትቶ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በገበርዲን ፡ በቦት ፡ ጫማ ፡ ሲያስጌጥ ፡ ነገሩ ፡ ማንንም ፡ ሊያሳስት ፡ አይችልም ።

አሳቡም ፡ በኤውሮፓ ፡ ጦርነት ፡ መጨረሻ ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ድምፅ ፡ ሲታጣ ፡ የአርበኞችም ፡ ኃይል ፡ ሲደመሰስ ፡ ዓለም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃ ፡ መንግሥትነት ፡ ረስቶ ፡ ለኢጣሊያ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ መሆኗን ፡ ሲያውቅ ፡ የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፡ ያላንዳች ፡ ተስፋ ፡ በኢጣሊያ ፡ ድኳ ፡ በታች ፡ ሲቀጠቀጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ለምለም ፡ መሬት ፡ የኢጣሊያን ፡ ሕዝብ ፡ እየጠቀመ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲኖር ፡ ነበር ።


ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ የኤውሮፓ ፡ ጦርነት ፡ መነሣትና ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ሠራዊት ፡ ይዘው ፡ የመምጣታቸው ፡ ድምፅ ፡ በያለበት ፡ ስለ ፡ ተሰማ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በያለበት ፡ የሚያደርገው ፡ ፖለቲካ ፡ የጥር ፡ ፀሓይ ፡ እንደ ፡ መታው ፡ በረዶ ፡ እየሟሟ ፡ ሄደ ። ስለዚህ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ገዥነታቸውን ፡ ከማሰብ ፡ ይልቅ ፡ በዚህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ስላፈሰሱት ፡ ደምና ፡ ገንዘብ ፡ አጥብቀው ፡ ይጸጸቱ ፡ ዠመር ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ራሳቸው ፡ ሁኔታ ፡ ያስቡ ፡ ዠመር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ መውደቃቸውን ፡ በኅሊናቸው ፡ እያወቁ ፡ ድል ፡ እናደርጋለን ፡ እያሉ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሰበኩ ፡ ሕዝቡ ፡ ግን ፡ ስብከታቸውን ፡ አልተቀበላቸውም ።

# ምዕራፍ ፡ 78 ።

## የአክሲስ ፡ መንግሥቶች ፥ የኢጣሊያ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ መግባት ።

የጀርመንና ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ ጠላት ፡ ነበሩ። ይልቁንም ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ ባ1914 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጦርነት ፡ ተነሥቶ ፡ ጀርመን ፡ ለነምሳ ፡ መንግሥት ፡ አግዞ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ዓለምን ፡ የመግዛት ፡ አሳብ ፡ እየገፋው ፡ አንድነት ፡ ከሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ ኣራት ፡ ዓመት ፡ በተዋጋ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከጀርመን ፡ ጋራ ፡ ያንድነት ፡ ውል ፡ ኣስቀድሞ ፡ ቢኖረው ፡ ይህንኑ ፡ ውል ፡ አልፎ

፡ ከጀርመንና ፡ ከነምሳ ፡ ጋራ ፡ ካ1916 ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ 1919 ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ አንድነት ፡ ከሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ጐን ፡ ሆኖ ፡ ተዋግቷል ።



ሙሶሊኒ ፡ ሂትለርና ።

ከዚያ ፡ በፊትና ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ እስከ ፡ 1935 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ በሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ የበቃ ፡ ጠላትነት ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ከሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ ተራ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ሂትለርና ፡ ሙሶሊኒ ፡ ከድኽነት ፡ ተነሥተው ፡ የየመንግሥታቸውን ፡ ሥልጣን ፡ ለመጨበጥ ፡ በበቁ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ጠላት ፡ የነበሩትን ፡ መንግሥታት ፡ ፖለቲካና ፡ ምኞት ፡ አዛመዳቸው ።

የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ከነምሳ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ አላገባብ ፡ የቀሰቀሰው ፡ ጦርነት ፡ ራሱን ፡ በማስጠቃት ፡ ተፈጽሞ ፡ በቬርሳይ ፡ (የፈረንሳዊ ፡ የጥንት ፡ ከተማ) ፡ ዕርቅ ፡ በተደረገ

፡ ጊዜ ፡ አላገባብ ፡ ተቀስቅሶ ፡ ላስነሣው ፡ ጦርነት ፡ እንደ ፡ መቀጫ ፡ እንዲሆነው ፡ ከኤውሮፓ ፡ ሰአር ፡ የሚባለው ፡ ለፈረንሳዊ ፡ ደነሲካ ፡ ነፃ ፡ ከተማ ፡ ሆኖ ፡ የፖሎኝ ፡ መንግሥት ፡ እንዲሠራበት ፡ በአፍሪካም ፡ ያለው ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ እንግሊዝና ፡ ቤልጅግ ፡ እንዲያስተዳድሩት ፡ ተደረገ ።

ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድል ፡ ድረስ ፡ ሊያዘልቅ ፡ የሚያስችል ፡ የመሰለውን ፡ የመሣሪያ ፡ ድርጅት ፡ አደረገ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በትልቁ ፡ ጦርነት ፡ ጠላት ፡ የነበሩት ፡ መንግሥታት ፡ «የሮማና ፡ የቤርሊን ፡ ዝምድና» ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረጉ ። ከሁለቱም ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ ይልቅ ፡ የሁለቱ ፡ ዲክታተር ፡ (የሙሶሊኒና ፡ የሂትለር) ፡ ወዳጅነትና ፡ ስምምነት ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የጀርመንን ፡ ከተማ ፡ እንዲጐበኝ ፡ ሂትለር ፡ ለሙሶሊኒ ፡ ጥሪ ፡ ኣደረገለት ። ሙሶሊኒም ፡ ጥሪውን ፡ በደስታ ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቊጥር ፡ መስከረም ፡ 24 ፡ ቀን ፡ 1937 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ ቤርሊን ፡ ሄደ ። ታላቅም ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ ተደረገለት ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ሁለቱ ፡ መሪዎች ፡ በሚያወካላቸው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሆነው ፡ ከመደሰት ፡ ጋራ ፡ እየዞሩ ፡ ከተማውን ፡ ጐበኙ ። ወዲያው ፡ 3 ፡ ሚሊዮን ፡ ወታደር ፡ እተሰለፈበት ፡ ግንባር ፡ እከፍተኛው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ቊልቊል ፡ በፈገግታ ፡ ሲመለከቱ ፡ ከታችም ፡ የጀርመን ፡ ሹማምቶችና ፡ ወታደሮች ፡ 2 ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ካሬ ፡ የሚሆነውን ፡ ስፍራ ፡ ጥቅጥቅ ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡ በጃቸው ፡ ሳንጃቸውን ፡ እየመዘዙ ፡ ሽቅብ ፡ የመሪዎቻቸውን ፡ ስም ፡ እየጠሩ ፡ ያወኩላቸው ፡ ነበር ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ መሪዎች ፡ ሂትለርና ፡ ሙሶሊኒ ፡ ታላቅ ፡ ኩራት ፡ ተሰማቸው ። የሁለታቸውንም ፡ መንግሥት ፡ ሕዝብ ፡ ቊጥር ፡ ደምረው ፡ 115ቱ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ባ1 ፡ አሳብ ፡ ተመርቶ ፡ የሚገጥመውን ፡ ጠላቱን ፡ አሸንፎ ፡ የዓለም ፡ ጌታ ፡ ሊያደርገንና ፡ ኤውሮፓም ፡ እኛ ፡ በምንሰጠው ፡ አዲስ ፡ ሕግ ፡ ሊተዳደር ፡ ይችላል ፡ ሲሉ ፡ ተማመኑ ። ጦርነትም ፡ ሰላምም ፡ ከኛ ፡ ነው ፡ የሚወጣው ፡ ሲሉ ፡ አረጋገጡ ። ሁለቱ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሆነው ፡ እተነሡበት ፡ ፎቶግራፍ ፡ ግርጌ ፡ «የሰላም ፡ ዋሶች» ፡ የሚል ፡ ጽሕፈት ፡ ተደረገ ።

ወዲያውም ፡ ለሁለቱ ፡ መሪዎች ፡ የሚያወካው ፡ ሕዝብ ፡ ዝም ፡ እንዲል ፡ ዶክተር ፡ ጐየበልስ ፡ ከጠቀሰ ፡ ወዲህ ፡ ዲስኩር ፡ ተዠምሮ ፡ ሂትለር ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ።

« ማኅበረተኛ ፡ ከሆኑት ፡ ከፋሺስትና ፡ ከናሲዮናል ፡ ሶሲያሊስት ፡ ሬቦሊሲዮን ፡ መካከል ፡ የሥራ ፡ ጭምር ፡ እንጂ ፡ ያሳብ ፡ ብቻ ፡ ያልሆነ ፡ አንድነት ፡ ተወለደ ። ዓለም ፡ ሊፈርስና ፡ ሊወድቅ ፡ በሚንገደገድበት ፡ ጊዜ ፡ ይኸንን ፡ አንድነት ፡ ማየት ፡ ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ነው ።

የነዚህም ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ኀይል ፡ አፍራሾች ፡ በሆኑት ፡ (በእንግሊዝና ፡ በፈረንሳዊ) ፡ ምክንያት ፡ ኤውሮፓ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ከምትፈጽመው ፡ የሥልጣኔ ፡ ሥራ ፡ እንዳትወድቅ ፡ እንደ ፡ ዋስ ፡ ሆኖ ፡ እያረጋገጠ ፡ ይደግፋታል ። በመሪዋ ፡ በሙሶሊኒ ፡ የተነሣ ፡ ትንሽ ፡ የነበረችው ፡ ኢጣሊያ ፡ ታላቅ ፡ የቁሳር ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ እንዲሁ ፡ ሙሴ ፡ ሙሶሊኒ ፡ ዛሬ ፡ ባይናቸው ፡ እንዳዩት ፡ ጀርመንም ፡ በወታደርነት ፡ በኩል ፡ ከዓለም ፡ ውስጥ ፡ ኃያል ፡ ሆናለች ። »

ሙሶሊኒም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰ ።

« በተደረገልኝ ፡ ኣቀባበል ፡ ልቤ ፡ በጥልቅ ፡ ተነክቷል ።

ወዳጅነት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ መዝለቅ ፡ የራሴና ፡ የፋሺዝም ፡ ጠባይ ፡ ነው ። ...

እኔም ፡ ከኢጣሊያ ፡ መጥቼ ፡ እዚህ ፡ እመካከላችሁ ፡ የተገኘሁት ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ በመሆኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያንድ ፡ ሬቦሊሲዮን ፡ አለቃ ፡ በመሆኔና ፡ ይህንኑም ፡ የኔን ፡ አነሣሥ ፡ (ሬቦሊሲዮን) ፡ ከናንተ ፡ ሬቦሊሲዮን ፡ ጋራ ፡ በጥብቅ ፡ እንዲገናኝ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ።

የሁለታችንም ፡ ያነሣሡ ፡ (የሬቦሊሲዮን) ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ እንዲሁም ፡ ሥራውም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ነው ። በኢትዮጵያ ፡ ምክንያት ፡ 52 ፡ መንግሥታት ፡ በኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ ጭቈና ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ እነዚሁ ፡ መንግሥታት ፡ ቢያቻኩሉት ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ አልተደረበም ። ይኸውም ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚረሳ ፡ አይደለም ። »

ሂትለርና ፡ ሙሶሊኒ ፡ ለ3 ፡ ሚሊዮን ፡ ወታደር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውንና ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ የሁለቱን ፡ መንግሥታት ፡ በፍቅር ፡ መተሳሰር ፡ የጦራቸውን ፡ ድርጅት ፡ የወታደሮቻቸውን ፡ ኀይል ፡ በሰፊው ፡ የሚገልጽ ፡ በየተራ ፡ ሲናገሩ ፡ የሁለቱ ፡ አገር ፡ ሕዝቦችና ፡ የመላው ፡ ዓለም ፡ ሕዝብ ፡ በራዲዮ ፡ ያዳምጣቸው ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሙሶሊኒ ፡ በቤርሊን ፡ ከተማ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ ከሂትለር ፡ በቈይታና ፡ በግልጽ ፡ ማናቸውንም ፡ ሲመካከር ፡ ከሰነበተ ፡ በኋላ ፡ በመስከረም ፡ 29 ፡ ቀን ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ሄደ ።

ሂትለርም ፡ የሙሶሊኒን ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ በግንቦት ፡ 2 ፡ ቀን ፡ 1938 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ሄደ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ሙሶሊኒ ፡ በቤርሊን ፡ የተደረገለትን ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ ለማገዳደርና ፡ ሂትለርን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ በብዙ ፡ ይጥር ፡ ነበር ። ሂትለርም ፡ 6 ፡ ቀን ፡ በእንግድነት ፡ እንደ ፡ ቈየ ፡ ተመልሶ ፡ በግንቦት ፡ 4 ፡ ቀን ፡ ሌሊቱን ፡ ወደ ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ ተመለሰ ።

ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ የሂትለርና ፡ የሙሶሊኒ ፡ የጀርመንና ፡ የኢጣሊያ ፡ አንድነት ፡ እየጠበቀ ፡ ሄደ ። በየጊዜው ፡ የሚያደርጉት ፡ የፉከራና ፡ የድንፋታ ፡ ንግግራቸውም ፡ ለዓለም ፡ ጕሮ ፡ ሰልችቶ ፡ ነበር ። ሂትለርም ፡ የዛሬው ፡ ያ1938 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀርመን ፡ እንደ ፡ 1914ቱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያለ ፡ ጀርመን ፡ አይምሰላችሁ ፡ እያለ ፡ ያስፈራራ ፡ ነበር ።

ቀጥሎም ፡ የቬርሳይ ፡ ውልና ፡ በዚህም ፡ ውል ፡ ጊዜ ፡ የተመሠረተው ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ ለጀርመን ፡ መንግሥት ፡ አጥቂው ፡ ነውና ፡ ይህ ፡ ውል ፡ እንዲለወጥ ፡ ካልተደረገ ፡ በአፍሪካም ፡ በኤውሮፓም ፡ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ በኔ ፡ እጅና ፡ ስም ፡ የነበረው ፡ ቅኚ ፡ አገር ፡ ካልተመለሰልኝ ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ የሚነሣው ፡ ጦርነት ፡ ዓለምን ፡ ሊያስገዛኝ ፡ ይችላል ሲል ፡ ደንፍቶ ፡ ተነሣ ።

እንደዚሁም ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በትልቁ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሕዝቤን ፡ በሞት ፡ እንደ ፡ ገበርኩበት ፡ መጠን ፡ የሚገባኝን ፡ አላገኘሁም ፡ ኢትዮጵያንም ፡ ስይዝ ፡ የዓለም ፡ ማኅበርን ፡ ሕግ ፡ እናስከብራለን ፡ በማለት ፡ ተቃውመውኛል ፡ እንዲያውም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በቀር ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ላይ ፡ ንኢሳንና ፡ ሳቦያን ፥ ቱኒዝያንና ፡ ጅቡቲን ፥ ኮርሲካን ፡ በውድ ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ መቀማት ፡ ያስፈልገኛል ፡ ሲል ፡ መሪው ፡ ሙሶሊኒ ፡ በሂትለር ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ የምኞት ፡ ጩኸቱን ፡ አሰማ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ምንም ፡ ያኸል ፡ ውጊያ ፡ ሳያደርግ ፡ የነምሳን ፡ አገር ፡ በታንክና ፡ በአየር ፡ ጦርነት ፡ አስፈራርቶ ፡ ወረረ ። በዚያም ፡ ጊዜ ፡ የእንግሊዝና ፡ የፈረሳንዊ ፡ መንግሥት ፡ ጀርመንን ፡ ምንም ፡ አላደረጉትም ። ቀጥሎም ፡ ቼኮዝሎባኪያን ፡ ወረረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የፈረንሳዊና ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ለመዋጋት ፡ ሲዘጋጁ ፡ ሳለ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ 1ኛ ፡ ሚኒስትር ፡ ምስተር ፡ ሻምበርሊን ፡ የፈረንሳዊ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ፕሬዚዳን ፡ ሙሴ ፡ ዲሊዲዬሪ ፥ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ መሪ ፡ ሂትለር ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ ሙሴ ፡ ሙሶሊኒ ፡ ሞናኮዲ ፡ ባቢዬር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ኤ ፡ ቍ ፡ ባ1939 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመስከረም ፡ ስብሰባ ፡ አደረጉ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በኤውሮፓ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ የጦርነት ፡ ደመና ፡ ከብዶ ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ እንደሚዘንም ፡ በመጠባበቅ ፡ የዓለም ፡ ልብ ፡ ተጨንቆ ፡ ነበር ፡ ከዚህስ ፡ ስብሰባ ፡ የሚወለደው ፡ ጦርነት ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ሰላም ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ በግንጋኔ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነዚሁ ፡ መሪዎች ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ የማይቆይ ፡ ሰላም ፡ በመካከላቸው ፡ ማድረጋቸው ፡ ተገለጸ ። ይህም ፡ የሞናኮ ፡ ስምምነት ፡ ሰላምን ፡ በመከተል ፡ ሳይዘጋጅ ፡ ለቈየው ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጥቂት ፡ የማዘጋጃ ፡ ጊዜ ፡ ከመስጠት ፡ በቀር ፡ የጀርመንን ፡ ወራሪነት ፡ ሊያቆመው ፡ ባለመቻሉ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከጀርመን ፡ በኩል ፡ የጦርነት ፡ መዘጋጀትና ፡ ወራሪነት ፡ እየተፋፋመ ፡ ሄደ ።

ስለዚህም ፡ የአሜሪካን ፡ ፕሬዚዳን ፡ ምስተር ፡ ሩዝቬልት ፡ የሆላንድ ፡ ንግሥት ፡ ገልዩልሚን ፥ የሮማው ፡ ጳጳስና ፡ የቤልጅክ ፡ ንጉሥ ፡ ጭምር ፡ ጦርነት ፡ አጫሪ ፡ የሆኑትን ፡ የአክሲስን ፡ መንግሥታት ፡ ሰላም ፡ እንዲሆን ፡ ኣጥብቀው ፡ ይለምኗቸው ፡ ነበር ። ጦርነት ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ተዋጊውንም ፡ ተከላካዩንም ፡ አሸናፊውንም ፡ ተሸናፊውንም ፡ ከጦርነት ፡ ውጭ ፡ (ነትር) ፡ የሆነውን ፡ መንግሥት ፡ ሳይቀር ፡ እንደሚያሠቀየውና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በጥበቡ ፡ የሠራው ፡ ሕንፃና ፡ ከተማዎች ፡ እንደሚፈርሱ ፡ የዚህም ፡ ፍዳ ፡ የመንግሥት ፡ ኣለቆች ፡ በሆኑት ፡ ላይ ፡ መድረሱን ፡ እያስረዱ ፡ ኣብዝተው ፡ ለመኗቸው ። ሂትለር ፡ ግን ፡ ከትልቁ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ የተወሰደው ፡ ቅኝ ፡ አገሬ ፡ ካልተመለሰ ፡ 80 ፡ ሚሊዮን ፡ የሚሆነውን ፡ የጀርመንን ፡ ሕዝብ ፡ የማስተዳድርበት ፡ ሀብት ፡ የለኝም ፡ ሲል ፡ ምንም ፡ ቢያባብሉት ፡ ጦርነቱን ፡ ማቆም ፡ አልቻለም ።

ስለዚህ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ የዳንዚክን ፡ መተላለፊያ ፡ ከፖሎኝ ፡ እጅ ፡ ለመቀማት ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ላከ ። ፖሎኝም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በመሣሪያም ፡ በሠራዊትም ፡ ከጀርመን ፡ መንግሥት ፡ አለመተካከሏን ፡ ብታውቅ ፡ 30 ፡ ቀን ፡ በዠግንነት ፡ የጀርመንን ፡ መንግሥት ፡ ተዋጋች ፡ ከጀርመን ፡ የጦር ፡ አለቆችና ፡ ሠራዊት ፡ ብዙ ፡ ቀነሰች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ጠንክራ ፡ ብትዋጋ ፡ እንግሊዝና ፡ ፈረንሳዊ ፡ ርዳታ ፡ ቢያደርጉላት ፡ ከመወረር ፡ አልዳነችም ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ከቤልጅግ ፥ ከሆላንድ ፥ ከዳኒማርክ ፥ ኖርቤዥ ፥ ከእንግሊዝና ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ገጥሞ ፡ ሲዋጋ ፡ ሙሶሊኒ ፡ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ «የሮማና ፡ የቤርሊን ፡ ዝምድና» ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያደረጉ ፡ ጊዜ ፡ «የሁለታችን ፡ መንግሥታት ፡ ሕዝቦች ፡ ለሞትም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ለሕይወት ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ ይራመዳሉ» ፡ ሲል ፡ ለሂትለር ፡ ካረጋገጠለት ፡ ወዲህ ፡ በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ «ዝም ፡ ብሎ ፡ ሥራን ፡ መሥራት» ፡ የሚል ፡ ማስታወቂያ ፡ አውጥቶ ፡ ለሕዝቡ ፡ እየበተነ ፡ ከጦርነት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ያኽል ፡ ይመስል ፡ ነበር ፡ ይኸውም ፡ ከሂትለር ፡ ተስማምተው ፡ ነው ፡ ይባላል ።

ጀርመንም ፡ ከፈረንሳዊና ፡ ከእንግሊዝ ፡ ጋራ ፡ በማዥኖ ፥ በዱንኬርክ ፡ ከተዋጋ ፡ በኋላ ፡ ኀይሉ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ከሌሎቹ ፡ መንግሥታት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ፊት ፡ ብልጫ ፡ ስላገኘ ፡ ቤልጅክንና ፥ ዳኒማርክን ፥ ሆላንድን ፥ ኖርቤትን ፡ ወረረ ። የፈረንሳዊንም ፡ ሠራዊት ፡ በማዥኖ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ፓሪስን ፡ ለመያዝ ፡ በመሬትና ፡ በአየር ፡ በሚያስፈራ ፡ አኳኋን ፡ ሲገሠግሥ ፡ ዠግንነታቸው ፡ የታወቀው ፡ ፈረንሳዮች ፡ ለመቋቋም ፡ ስላልቻሉ ፡ ወይም ፡ በመሪዎቻቸው ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ሰነፉ ፡ ፓሪስ ፡ ተያዘች ። እነማሬሻል ፡ ፔቴም ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ ባ1940 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ የዕርቅ ፡ ቃል ፡ (አርሚስቲስ) ፡ ተቀብለው ፡ ጦርነቱን ፡ አቆሙ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ አንድነት ፡ የሆኑት ፡ መንግሥታት ፡ ድል ፡ ለመሆን ፡ የቀረቡ ፡ ስለ ፡ መሰለውና ፡ ከድል ፡ በኋላ ፡ የሚገኘውን ፡ ምርኮና ፡ መሬት

፡ ከጀርመን ፡ ጋራ ፡ መካፈል ፡ እንዳይቀርበት ፡ ባ1940 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰኔ ፡ 10 ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ መግባቱን ፡ አስታውቆ ፡ ጀርመን ፡ የጣላትን ፡ ፈረንሳዊን ፡ በማርሴይ ፡ በኩል ፡ ለመውጋት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ላከ ። በዚህም ፡ ብልጠትና ፡ ፍራት ፡ በተደባለቀበት ፡ በኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጉብዝና ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሣቀበት ። ጋዜጣ ፡ ጸሓፊዎችም ፡ ጀርመን ፡ የገደለውን ፡ የፈረንሳዊን ፡ ሬሳ ፡ ጣሊያን ፡ በሳንጃ ፡ ሊወጋ ፡ ተነሣ ፡ እያሉ ፡ ጻፉበት ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦርነት ፡ መግባት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ጕዳይ ፡ ከሆኑት ፡ ውስጥ ፡ ዋናው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ነበርና ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥትም ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ርዳታ ፡ ሰጥቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያለውን ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ ለመውጋት ፡ የበቃ ፡ ምክንያት ፡ አገኘ።

# ምዕራፍ ፡ 79 ።

## የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ መመለስና ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ መግባት ።

የኢትዮጵያ ፡ የተወራሪነት ፡ ፍጻሜ ፡ የጦርነት ፡ መደምደሚያ ፡ (ፍጻሜው) ፡ ቢሆን ፡ ራሱን ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለየመንግሥታቱ ፡ ሁሉ ፡ የሚከፋ ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። በቀጥታ ፡ የራሱ ፡ ጕዳይ ፡ ካልተጨመረበት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተጠቂነት ፡ ቈጭቶት ፡ ይህንን ፡ ጥቃት ፡ ሊበቀል ፡ የሚነሣ ፡ መንግሥት ፡ አይገኝም ፡ ይህ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እነዚያ ፡ በዓለም ፡ ማኅበር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኢጣሊያ ፡ ላይ ፡ የሚናገሩት ፡ ያ12 ፡ 13 ፡ 15 ፡ 16ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ንግግሮች ፡ ችላ ፡ ባልተባለም ፡ ነበር ።

ከኢትዮጵያም ፡ ወረራ ፡ በኋላ ፡ የኤውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጭምር ፡ ፍጹም ፡ ሰላም ፡ ፈላጊዎች ፡ ሆኑ ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብና ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያለው ፡ ሰላም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ አስረስቶ ፡ እንዳይኖር ፡ ከሰላም ፡ ይልቅ ፡ የጦርነቱን ፡ መነሣት ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ከጦርነት ፡ አጫሪዎቹ ፡ አንደኛው ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰፊ ፡ ግዛት ፡ አግኝቶ ፡ ሙሉ ፡ ደስታ ፡ ሲያገኝ ፡ ከርሱ ፡ የበለጠው ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ጕዳይ ፡ ገና ፡ አልተነካም ፡ ነበር። በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ በኤውሮፓና ፡ በአፍሪካ ፡ ያሉት ፡ የቀድሞ ፡ የጀርመን ፡ ግዛቶች ፡ እንዲመለሱለት ፡ ወይም ፡ እንዳይመለሱለት ፡ በጋዜጣና ፡ በቃል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከተከራከሩበት ፡ በኋላ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ 1939 ፡ ዓ

፡ ም ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ 1940 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከቱርክና ፡ ከስዊድን ፡ ከኤስፓኝ ፡ ወይም ፡ ለርሱ ፡ የጦር ፡ ጓድ ፡ ከሆኑት ፡ በቀር ፡ የኤውሮፓን ፡ መንግሥታት ፡ በየተራ ፡ እየወጋ ፡ ወረራቸው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ከጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ተስማምቶ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በሰላም ፡ ተቀምጦ ፡ ሥራውን ፡ ይሠራ ፡ ነበር ። የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ ወረራውን ፡ እየቀጠለ ፡ እስከ ፡ ፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ ደረሰ ። ፈረንሳዮችም ፡ በቀድሞ ፡ ዝግንነታቸው ፡ እንደሚገባ ፡ ሳይዋጉ ፡ ስመ ፡ ጥሩይቱ ፡ ከተማቸው ፡ ፓሪስ ፡ ተያዘጭ

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ቢመለከት ፡ በጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ፊት ፡ የሚቆም ፡ አጣ ፡ የእንግሊዝንና ፡ የአሜሪካንን ፡ መንግሥት ፡ ጥብቅነትና ፡ ተዋጊነት ፡ ከፍ ፡ ያለውንም ፡ ሞራላቸውን ፡ ዘነጋ ። እነሱም ፡ ቀጥለው ፡ እንደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ የሚወድቁ ፡ መሰለው ፡ በመስኮብም ፡ በኩል ፡ በመጨረሻ ፡ የሆነውንም ፡ አልገመተም ።

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ምቹ ፡ የምርኮ ፡ ጊዜ ፡ በከንቱ ፡ እንዳይባክንበት ፡ የሰላሙን ፡ ሥራ ፡ አቁሞ ፡ ባ1940 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ጦርነት ፡ በፈረንሳዊና ፡ በእንግሊዝ ፡ ላይ ፡ ማንሣቱን ፡ በገሃድ ፡ አስታወቀ ። የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጦርነቱን ፡ ጀርመን ፡ እንደ ፡ ዝመረ ፡ አብሮ ፡ ዝምሮ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ቈየ ፡ ዘግይቶ ፡ የጓደኛውን ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ወራሪነት ፡ እንግሊዞች ፡ ጠንክረው ፡ በተቋቋሙ ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ ቢሆን ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ ግምት ፡ አያጣም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ የፈረንሳዊን ፡ መንግሥት ፡ ከሰሜን ፡ በኩል ፡ ወሮ ፡ ፓሪስን ፡ ይዞ ፡ ከጣለ ፡ በኋላ ፡ ከደቡብ ፡ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በወደቀችው ፡ ፈረንሳዊ ፡ ላይ ፡ መነሣቱ ፡ በማንም ፡ ዘንድ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ዝቅተኛነት ፡ ተገመተ ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ የኢጣሊያ ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ መግባት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የነፃነት ፡ በር ፡ ከፈተ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ችላ ፡ ተብሎ ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተቀሰቀሰና ፡ ሎንዶን ፡ ላይ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ በእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ የጦር ፡ ጓደኝነት ፡ ተደረገ ።

ወዲያው ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ባ1932 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ማለቂያ ፡ ላይ ፡ ከተከታዮቻቸው ፡ ጋራ ፡ በአይሮፕላን ፡ ሆነው ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ ጉዞ ፡ በኋላ ፡ እሱዳን ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ካርቱም ፡ ገቡ ። ይህንንም ፡ የሰማ ፡ ስደተኛ ፡ እየሄደ ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ዙሪያ ፡ ተሰበሰበ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ለአርበኞች ፡ በራዲዮ ፡ አሰሙ ።

«ይህ ፡ የምትሰሙት ፡ ድምፅ ፡ የኔ ፡ የንጉሣችሁ ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ነው ።

# ያገሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፥

አባቶቻችን ፡ ደማቸውን ፡ አፍሰው ፡ ዐጥንታቸውን ፡ ከስክሰው ፡ በነፃነት ፡ ያቈዩልንን ፡ አገራችንን ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ለማራመድ ፡ የምንደክምበት ፡ ጊዜ ፡ ከጥንት ፡ ዝሞሮ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ደመኛ ፡ ጠላታችን ፡ ኢጣሊያ ፡ ይህንን ፡ አይታ ፡ ወሰናችንን ፡ ጥላ ፡ የግፍ ፡ ጦርነት ፡ እንዳደረገችብን ፡ ሁላችሁም ፡ የምታውቁት ፡ ነው ። እኛም ፡ በተቻለን ፡ ከተከላከልን ፡ በኋላ ፡ ርዳታ ፡ ለመጠየቅ ፡ ወደ ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ወደ ፡ ወዳጆቻችን ፡ መንግሥቶች ፡ መጣን ፡ እዚህ ፡ ስንነጋገር ፡ በቈየንበት ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ሰይፋችሁን ፡ ሳትከቱ ፡ ፊታችሁን ፡ ሳትመልሱ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማችሁን ፡ ሳታጥፉ ፡ ለባዕድ ፡ አንገዛም ፡ በማለት ፡ በመሣሪያ ፡ ብዛት ፡ ከሚበልጣችሁ ፡ ጨካኝ ፡ ጠላት ፡ ጋራ ፡ የባሕርይ ፡ የሆነውን ፡ ዠግንነታችሁን ፡ መሣሪያ ፡ አድርጋችሁ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ተማምናችሁ ፡ በዠግንነት ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ ስትጋደሉ ፡ ቈይታችሁ ፡ ይኸው ፡ አሁን ፡ እንደምታዩት ፡ የማያቋርጥ ፡ ያ5 ፡ ዓመት ፡ ትግላችሁ ፡ የድካማችሁንና ፡ የመሥዋዕትነታችሁን ፡ ፍሬ ፡ ለማየት ፡ እንድትበቁ ፡ አደረጋችሁ ።

ኢጣሊያ ፡ ወሰናችንን ፡ ጥላ ፡ አገራችንን ፡ በወረረች ፡ ጊዜ ፡ በገንዘብ ፡ ችግር ፡ እንድትቀጣ ፡ ባደረጓት ፡ በታላቋ ፡ ብሪታኒያና ፡ በፈረንሳዊ ፡ ላይም ፡ ጀርመንን ፡ ተጠግታ ፡ ጦርነት ፡ ስላነሣች ፡ እነርሱም ፡ ርዳታቸውን ፡ ስለ ፡ ሰጡን ፡ የተመኘነውን ፡ አግኝተን ፡ ደረስንላችሁ ። የእንግሊዝና ፡ የፈረንሳዊ ፡ ኀይለኛ ፡ የጦር ፡ አይሮፕላኖች ፡ በኢጣሊያ ፡ ግዛት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኣየር ፡ ውስጥ ፡ ያንዣብባሉ ። ኢጣሊያም ፡ በኤውሮፓ ፡ በአይሮፕላን ፡ በመድፍ ፡ ምላሹን ፡ ትቀበላለች ። እግረኞች ፡ ወታደሮቿም ፡ ከምታምንባችሁ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ዠግኖች ፡ አያልፉም ። በማናቸውም ፡ ስፍራ ፡ ያለኸ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኛ ፡ ኢጣሊያን ፡ በርትተኸ ፡ ውጋ ። ደግሞ ፡ በውድም ፡ በግድም ፡ ቢሆን ፡ በኢጣሊያ ፡ ውስጥ ፡ ያላችሁ ፡ የሀገሬ ፡ ሰዎች ፡ ኢጣሊያ ፡ እንግሊዝና ፡ ፈረንሳዊ ፡ ድል ፡ ይሆናሉ ፡ እያለች ፡ በሐሰት ፡ የምትሰብክላችሁን ፡ አትመኑ ። ከእንግዴህ ፡ ወዲህ ፡ የኢጣሊያ ፡ መሣሪያ ፡ በመሆን ፡ አገራችሁን ፡ የምትበድሉ ፡ ለዘራችሁ ፡ ከታሪካችሁ ፡ የማይፋቅ ፡ ርግማን ፡ ታቈያላችሁ ።

በሱዳንም ፡ ሳሉ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ያርበኞች ፡ ሹማምቶች ፡ ጋራ ፡ እየተላላኩ ፡ ለጦርነት ፡ ተዘጋጅተው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ በጥር ፡ ወር ፡ 1933 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ያንን ፡ ሁሉ ፡ በረሓ ፡ ቈርጠው ፡ የጠላታቸውን ፡ ምሽግ ፡ እየጣሱ ፡ ከጐጃም ፡ ግዛት ፡ ገቡ ። በዚሁም ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ በጥር ፡ 14 ፡ ቀን ፡ አሜድላ ፡ በሚባል ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ በመዠመሪያ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዐለማ ፡ ሰቀሉ ።



የግርማዊነታቸው ፡ ጉዞ ፡ በበረሃ ።

የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጐጃም ፡ መግባት ፡ በቃልና ፡ በደብዳቤ ፡ በያለበት ፡ ተሰማ ፥ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ድንጋጤና ፡ ፍርሀት ፡ አድሮባቸው ፡ ሲቀዘቅዙ ፡ በያውራጃው ፡ ያለ ፡ አርበኛ ፡ በደስታ ፡ ተመልቶ ፡ ልቡ ፡ ደነደነ ። የደከመው ፡ ሰውነቱ ፡ ጠነከረ ፡ ካርበኛው ፡ በቀር ፡ ከኢጣሊያኖች ፡ ጋራ ፡ 5 ፡ ዓመት ፡ በሥቃይ ፡ የተቀመጠው ፡ ሕዝብ ፡ በየቤቱ ፡ ውስጥ ፡ እየገባ ፡ ነገሩን ፡ እየተወያየ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ይሳሳም ፡ ዠመር ። ለስለላ ፡ ወዳዲስ

፡ አበባ ፡ የሚመጡትንም ፡ የእንግሊዝ ፡ አይሮፕላኖች ፡ ቦምብ ፡ ይጥሉብናል ፡ ብሎ ፡ በመፍራት ፡ ፈንታ ፡ ነፃነትን ፡ እንደሚያበሥሩ ፡ መላእክት ፡ እያሻቀበ ፡ በናፍቆት ፡ ዐይን ፡ ይመለከታቸው ፡ ዠመር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሸዋ ፥ በትግሬ ፥ በጐንደር ፥ በጐጃም ፥ በጋላ ፡ ኣገር ፡ ያለ ፡ አርበኛ ፡ በያለበት ፡ መሸጎ ፡ የተቀመጠውን ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ እየከበበ ፡ ይዋጋው ፡ ዠመር ። ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ በራሪ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አባራሪ ፡ ሆኑ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ገሚሱን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወታደር ፡ በስብከትና ፡ በገንዘብ ፡ እያታለሉ ፡ ለጦርነት ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ እየወሰዱ ፡ እነሱም ፡ ያለ ፡ የጦር ፡ ኀይላቸውን ፡ ይዘው ፡ ቢሄዱ ፡ በጐጃም ፥ በከረን ፥ በሲዳሞ ፥ በከሰላ ፥ በበርበራ ፡ ድል ፡ እየተመቱ ፡ ተመለሱ ። ስለዚህ ፡ በወታደሩም ፡ በተቀማጭም ፡ የኢጣሊያ ፡ ሕዝብ ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ ተስፋ ፡ የመቍረጥ ፡ ምልክት ፡ ይታይባቸው ፡ ዠመር ። ዱካ ፡ ዳዎስታ ፡ ወይም ፡ ጄኔራል ፡ ናዚ ፡ እየጮኹ ፡ ቢሰብኩ ፡ ገንዘብም ፡ ቢያፈሱለት ፡ ገንዘቡን ፡ እየተቀበለ ፡ ስብከቱንም ፡ እየሰማ ፡ ዘወር ፡ እያለ ፡ ይወጋቸው ፡ ዠመር ፡ እንጂ ፡ የሚያምናቸውና ፡ የሚያዳምጣቸው ፡ ጠፋ ። ይህ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ሲሰብኩ ፡ ስብከታቸውን ፡ በቃል ፡ በቃል ፡ እየተረጐመ ፡ ያስተባብላቸው ፡ ዠመር ።

በዚህም ፡ ላይ ፡ መጥቶ ፡ ያድነናል ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ የሚያደርጉት ፡ የግራዚያኒ ፡ ጦር ፡ በግብጽና ፡ በሊቢያ ፡ በረሓ ፡ በእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ድል ፡ እየተመታ ፡ ገሚሱን ፡ በረሓ ፡ እንደ ፡ በላው ፡ ገሚሱን ፡ እንደ ፡ ተማረከ ፡ በየጊዜው ፡ ይሰሙ ፡ ዠመር ።

እንኳን ፡ ግብጽን ፡ አልፎ ፡ መጥቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያሉትን ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ሊያድን ፡ እዚያው ፡ ያለበትን ፡ ምሽግ ፡ ይዞ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ሳይከላከል ፡ በባርዲያ ፡ በቶብሩክ ፡ ድል ፡ እየሆነ ፡ በጦርነት ፡ ከሚሞተው ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እየሰቀለ ፡ የሚማረከው ፡ በለጠ ። በሊቢያ ፡ የነበሩ ፡ 14 ፡ ሺህ ፡ ወታደሮች ፡ 1 ፡ ጥይት ፡ ሳይተኩሱ ፡ በ50 ፡ ታንክ ፡ ውስጥ ፡ ለነበሩ ፡ 200 ፡ እንግሊዞች ፡ እጃቸውን ፡ ሰጡ ፡ ይባላል ።

እንደዚሁ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በአፍሪካ ፡ ይኹን ፡ የመሰለ ፡ ዕድል ፡ ሲገጥመው ፡ በኣውሮፓ ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ የባሰ ፡ ነበር ፡ ጠቅላላ ፡ ተቀማጩ ፡ ሕዝብ ፡ 6 ፡ ሚሊዮን ፡ የማይሞላው ፡ የግሪክ ፡ መንግሥት ፡ እነዚያ ፡ ጥቂቶች ፡ ወታደሮች ፡ ከባዶልዮ ፡ በኋላ ፡ ራሱ ፡ ሙሶሊኒ ፡ አዝማች ፡ የሆነበትን ፡ ብዙውን ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ እያባረሩ ፡ ድል ፡ መቱት ።

በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ጣሊያኖች ፡ ተስፋ ፡ አጡ ። ሕገዝቡም ፡ በገሃድ ፡ ድል ፡ መሆናቸውን ፡ ከመሸበራቸውና ፡ ከመለማመጣቸው ፡ ላይ ፡ ተገነዘበው ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ካርቱም ፡ ሲገቡ ፡ ስደተኛ ፡ በዙሪያቸው ፡ እንደ ፡ ተሰበሰበ ፡ እንደዚሁ ፡ ጐጃም ፡ ሲገቡ ፡ ከያውራጃው ፡ አርበኛ ፡ ሁሉ ፡ እየጐረፈና ፡

እየተሽቀዳደመ ፡ እጫማቸው ፡ ላይ ፡ እየወደቀ ፡ ተገናኛቸው ። እንደዚሁም ፡ በየገደሉ ፡ በየዱሩ ፡ በየቅጠሉ ፡ ተደብቆ ፡ የነበረው ፡ በከተማም ፡ የነበረው ፡ እየወጣ ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይጓዝ ፡ ዠመር ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትም ፡ የጦር ፡ ሰራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ በእንግሊዝ ፡ ታንኮች ፡ እየተረዱ ፡ ጠላትን ፡ ከቡሬ ፡ ከብር ፡ ከጨረቃ ፡ ከጉሊት ፡ ላይ ፡ በታላላቅ ፡ ውጊያ ፡ አባረው ፡ መጋቢት ፡ 21 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ባጀብና ፡ በእልልታ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ገብተው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ ተከሉ ፡ ለአርበኛውም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ዲስኩር ፡ አሰሙት ።

«ለባዕድ ፡ አንገዛ ፡ በማለት ፡ መገደል ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መሰደድ ፡ መከራ ፡ መቀበል ፡ መራብና ፡ መጠማት ፡ እንዲደርስለት ፡ የሚመኘውን ፡ ለማየት ፡ ይበቃል ። ይኸው ፡ ስትጋደሉለት ፡ ለነበረው ፡ ነፃነታችሁ ፡ ቀዋሚ ፡ ሆኖ ፡ የሚያሳየውን ፡ ሁለቱን ፡ ምልክት ፡ በጐጃም ፡ ለማየት ፡ በቃችሁ ፡ እነዚህንም ፡ ሁለቱን ፡ የነፃነት ፡ ምሳሌዎች ፡ ባጭር ፡ ዘመን ፡ ለማየት ፡ መብቃት ፡ እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ ያደረገው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከተአምር ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በማናቸውም ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ታሪክ ፡ ታይቶ ፡ ተሰምቶ ፡ የማይታወቅ ፡ ጎላፊ ፡ መጪም ፡ የሌለው ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ ለሠራልን ፡ ቸሮታ ፡ ሁላችንም ፡ የተገባን ፡ ሆነን ፡ መገኘት ፡ አለብን ። ውለታውንም ፡ የምንመልስበት ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ረስተን ፡ የፍቅርና ፡ የመተባበር ፡ መንገድ ፡ ተከትለን ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በጨካኝ ፡ አጥቂ ፡ ስትሠቃይ ፡ የቈየችውን ፡ አገራችንን ፡ በማገልገል ፡ ወደ ፡ ከፍተኛውም ፡ ሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ አደርሰን ፡ የሚከተለው ፡ ትውልዳችን ፡ ከወራሪ ፡ ፈተና ፡ የሚድንበትን ፡ ሠርተን ፡ በማቈየት ፡ ነው ። አገሩን ፡ ለሚወድና ፡ በቅንነት ፡ ለሚያገለግል ፡ በሰንደቅ ፡ ዐላማችን ፡ ጥላ ፡ ለሚኖር ፡ ታማኝ ፡ ለሆነ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሁሉ ፡ ምሕረታችንንም ፡ ቸርነታችንንም ፡ አንነሣውም ፡ ይህም ፡ ልዩነት ፡ ላናደርግ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የምንሠራበት ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡ ዕወቁ ።

ባንዳ ፡ ሽፍታ ፡ መባባል ፡ ካልቀረ ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ መፋቀር ፡ ካልተገኘ ፡ ይህ ፡ ምኞት ፡ አይፈጸምምና ፡ አገር ፡ እንዳይዘረፍ ፡ ሕዝብ ፡ እንዳይጕላላ ፡ ነጋዴም ፡ እንዲነግድ ፡ ገበሬውም ፡ እንዲያርስ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ማናቸውም ፡ ወንበዴ ፡ እንዳይገኝ ፡ በርትታችሁ ፡ ጠብቁ ። እናንተም ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ዛሬ ፡ የሥራችሁን ፡ አክሊል ፡ በመድፋታችሁ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ለወደ ፡ ፊቱም ፡ ለበለጠው ፡ አክሊል ፡ የምትሽቀዳደሙ ፡ ሁኑ ። ስለ ፡ ዓለም ፡ ነፃነት ፡ የሚዋጋው ፡ የእንግሊዝ ፡ ጦር ፡ አፊሰሮች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ወዳገራችን ፡ ገብተው ፡ በብርጋዲዬር ፡ ሳንድፎርድና ፡ በኮሎኔል ፡ ዊንጌት ፡ መሪነት ፡ የሚረዱትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ የማይዘነጋው ፡ ነው ።

በተለየ ፡ እናንት ፡ የሁለተኛው ፡ ባታዮን ፡ ወታደሮቼ ፡ ስለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችሁና ፡ ለሰንደቅ ፡ ዐላማችሁ ፡ ክብር ፡ ላገራችሁ ፡ ፍቅር ፡ በስደት ፡ ቈይታችሁ ፡ አሁን ፡ ጠላትን ፡

ለማባረር ፡ የሠራችሁትን ፡ የዠግንነት ፡ ሥራ ፡ በወንድሞቻችሁ ፡ መካከል ፡ ስናነሣው ፡ ደስ ፡ ይለናል ። ሥራችሁም ፡ ከቍጥራችሁ ፡ ግምት ፡ ይበልጣል ። በሞት ፡ የተለዩዋችሁንም ፡ አንረሳቸውም ። የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ከሥራ ፡ በኋላ ፡ የጠበቃችሁት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ ደማቅ ፡ ጌጥ ፡ የሆነው ፡ የነፃነት ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥታችሁ ፡ ፊት ፡ በፊታችሁም ፡ ሲውለበለብ ፡ ለማየት ፡ ስለ ፡ በቃችሁ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ። ኢትዮጵያ ፡ በነጻነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር » ።

ለጐንደርና ፡ ለበጌምድር ፡ አርበኛና ፡ ሕዝብም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ በልዑል ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ እጅ ፡ ተላከለት ።

« በዚህ ፡ የታላቅ ፡ ደስታ ፡ ምልክት ፡ በሚታይበት ፡ ቀን ፡ በሰንደቅ ፡ ዐላማችን ፡ ዙሪያ ፡ ተሰብስባችሁ ፡ በአየር ፡ ሲውለበለብ ፡ የምትመለከቱት ፡ ኣርማ ፡ የተጌጠውን ፡ የነፃነት ፡ ምልክት ፡ ለማየት ፡ ሲወረወሩ ፡ ልባችሁ ፡ የሚሰማውን ፡ የደስታ ፡ ወለልታ ፡ መላ ፡ በጌምድር ፡ እንደሚሰማው ፡ ለኛም ፡ ይሰማናል ። በዚህች ፡ ሰዓት ፡ በተወደደ ፡ ልጃችን ፡ አማካይነት ፡ ስንናገራችሁ ፡ በመካከላችሁ ፡ እንዳለን ፡ ቍጠሩት ።

ባለፉት ፡ ዓመቶች ፡ የደረሰውን ፡ ፈተና ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ ለመሆንና ፡ በጐንደር ፡ ከተማ ፡ በዛሬ ፡ ቀን ፡ ይህን ፡ ምልክት ለማየት ፡ ስትችሉ ፡ መሪር ፡ መንገድ ፡ አልፋችኋል ። ወደዚሁ ፡ ቦታ ፡ ለመድረስ ፡ የበቃችሁ ፡ አርበኞቻችን ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ የተመሰገኑ ፡ ዠግኖቻችንን ፡ ሬሳና ፡ ዐፅም ፡ ተራምዳችሁ ፡ ነው ። ይህም ፡ ዛሬ ፡ የምታዩት ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ በነዚያ ፡ ደምና ፡ በናንተ ፡ ገበሬነት ፡ በለሰለሰ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በቅሎ ፡ ለምልሞ ፡ ያደገ ፡ የነፃነት ፡ ሕይወት ፡ ዛፍ ፡ ነው ።

ያለፉት ፡ መታሰቢያ ፡ የኛና ፡ በሕይወት ፡ የተረፋችሁት ፡ ድካም ፡ አልጠፋምና ፡ እኛን ፡ ደስ ፡ እንዳለን ፡ እናንተም ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ። ይህ ፡ በወገኖቻችን ፡ ደም ፡ የበቀለው ፡ የሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ ዛፍ ፡ የዘለዓለም ፡ የሕይወት ፡ ዛፍ ፡ እንዲሆን ፡ ያለፉት ፡ በመሥዋዕትነት ፡ የደከሙትን ፡ ያኸል ፡ በሕይወት ፡ የቀረነው ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ የሚመጣው ፡ ትውልድ ፡ ባስፈለገ ፡ ጊዜ ፡ በመሥዋዕትነት ፡ የሚሰጥበት ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ምልክት ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ባሳባችን ፡ ወደ ፡ ስመጥሩው ፡ ወደ ፡ ታላቂቱ ፡ ብሪታኒያ ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ፊታችንን ፡ እንመልሳለን ።

በዓለም ፡ ላይ ፡ የሰውን ፡ ዘር ፡ ለመምተርና ፡ የሕዝብን ፡ ነፃነት ፡ ለማጥፋት ፡ የተነሡትን ፡ የቶታሊቴርን ፡ ጦር ፡ ክንድ ፡ ለመስበር ፡ የተነሣው ፡ የግርማዊ ፡ ብሪታንያ ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በመሥዋዕትነት ፡ የተሰጠበትን ፡ የተቀደሰውን ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ሥራውን ፡ ዛሬ ፡ ፈጸመ ። የዛሬ ፡ ቀን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነበረው ፡ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ መጨረሻ ፡ ድል ፡ የሆነበት ፡ ነው ። ለመጥፋት ፡ መዠመሪያ ፡ የነበረችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በግርማዊ ፡ የብሪታንያ ፡ መንግሥት

፡ ሕዝብ ፡ ቈራጥነትና ፡ በጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ዠግንነት ፡ ባገኘችው ፡ ርዳታ ፡ ለትንሣኤ ፡ መዠመሪያ ፡ ለመሆን ፡ በቃች ። ስለዚህም ፡ ለታወቁት ፡ ለጐንደር ፡ ጦር ፡ መሪ ፡ ለሜጀር ፡ ጄኔራል ፡ ፎክስ ፡ ምስጋናችንን ፡ እያቀረብን ፡ በውስጣቸው ፡ ላለው ፡ በጐንደር ፡ ለሠራው ፡ ጦራቸው ፡ ምስጋናችንን ፡ በርሳቸው ፡ በኩል ፡ እናቀርባለን» ።

# ምዕራፍ ፡ 80 ።

## የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መግባት ።

በጄኔራል ፡ ካኒንግሃም ፡ መሪነት ፡ በሲዳሞ ፡ በኩል ፡ የመጣው ፡ የታላቋ ፡ ብሪታኒያ ፡ ጦር ፡ ባ1933 ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጋቢት ፡ 28 ፡ ቀን ፡ ባ11 ፡ ሰዓት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገባ ። የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማም ፡ በቤተ መንግሥቱ ፡ ላይ ፡ ተተከላ ፡ ስትውለበለብ ፡ አይቶ ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ታላቅ ፡ ደስታውን ፡ ገለጸ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ደስታው ፡ ፍጹምነት ፡ የሚያገኘው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ባሳብና ፡ በስሜት ፡ ባይለዩት ፡ በሥጋ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የተለዩትን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ነበርና ፡ ይኸንኑ ፡ ቀን ፡ በናፍቆት ፡ በሚጠብቅበት ፡ ጊዜ ፡ ዘንድሮ ፡ ባይኔ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አሳየኸኝ ፡ አሁንም ፡ የንጉሤን ፡ ዐይን ፡ ሳታሳየኝ ፡ አትግደለኝ ፡ ብሎ ፡ ለፈጣሪው ፡ ስለት ፡ ያላደረገ ፡ አይገኝም ።

ስለዚህ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጐጃም ፡ ሆነው ፡ ያገራቸውን ፡ ነፃነት ፡ 5 ፡ ዓመት ፡ ለተከላከሉ ፡ ለጐጃም ፡ ሹማምንቶችና ፡ ወታደሮች ፡ የሚገባቸውን ፡ ዋጋ ፡ ሰጥተው ፡ ሚያዝያ ፡ 14 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ድምብቅ ፡ በይ ፡ ከሚባለው ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ተዋግቶ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ማረከ ።

በየመንገዳቸውም ፡ ዠግናውና ፡ ተስፋ ፡ የማይቈርጠው ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኛ ፡ በያለበት ፡ መሽጎ ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረውን ፡ የኢጣሊያን ፡ ወታደር ፡ እየማረከ ፡ በፊታቸው ፡ እየቀረበ ፡ ይፎክር ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ በየጊዜው ፡ የቀረቡት ፡ ምርኮኞች ፡ እነዚያ ፡ በማይጨውና ፡ በተንቤን ፡ እንዲሁም ፡ በደቡብ ፡ ግንባር ፡ በኢትዮጵያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ የመርዝ ፡ ጋዝ ፡ እየረጩ ፡ ግፍ ፡ የሠሩት ፡ ኢትዮጵያንም ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ለመያዝ ፡ ከቻሉ ፡ በኋላ ፡ አማናዊውን ፡ ሕዝብ ፡ እያሰሩ ፡ በመትረየስ ፡ የቈሉት ፡ ቤቱን ፡ በቤንዚን ፡ እያቃጠሉ ፡ ያሠቃዩት ፡ ናቸው ፡

ነገር ፡ ግን ፡ በሰፈሩት ፡ ቀና ፡ መልሶ ፡ መስፈር ፡ ዋጋቸው ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ እንዲለውና ፡ ዓለምም ፡ በሙሶሊኒና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የጠባይ ፡ ልዩነት ፡ ዐውቆ ፡ እንዲገረም ፡ አባታቸው ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ከዐድዋ ፡ ድል ፡ በኋላ ፡ ለተገኙት ፡ ምርኮኞች ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ እንዳዘዙላቸው ፡ እንዲሁ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ልቡን ፡ አደንድኖ ፡ ሊዋጋቸው ፡ ያሰበውን ፡ ብቻ ፡ ወግተው ፡ ድል ፡ ሲያደርጉ ፡ እጁን ፡ ሰጥቶ ፡ በተማረከው ፡ በኢጣሊያ ፡ ወታደር ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከመግባታቸው ፡ በፊትና ፡ ከገቡም ፡ በኋላ ፡ ግፍ ፡ እንዲደረግባቸው ፡ አልፈቀዱም ። ከፊታቸውም ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ግፍ ፡ እንዳይደረግባቸው ፡ በትእዛዝ ፡ አስጠነቀቁ ።

እንደዚህም ፡ ሆኖ ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ግርማ ፡ ባለው ፡ ጕዞ ፡ ተጉዘው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የመግቢያቸው ፡ ቀን ፡ ጠላት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በገባበት ፡ በሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፡ መሆኑ ፡ ተሰማ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ ቀደም ፡ብለው ፡ ሐረር ፡ ሄደው ፡ ስለ ፡ ታዩ ፡ የሕዝቡ ፡ ደስታ ፡ ታላቅ ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ ኣስቀድመው ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይን ፡ መምጣት ፡ ለሕዝቡ ፡ ያበሠሩት ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ አስቀድመው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገብተው ፡ ላቀባበል ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሲያዘጋጁ ፡ ቈይተው ፡ ዝግጅቱ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ በተባለው ፡ ቀን ፡ ግርማዊነታቸው ፡ እንጦጦ ፡ መድረሳቸው ፡ ተሰማ ።

ሕዝቡም ፡ በሞላው ፡ ከታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ እስከ ፡ እንጦጦ ፡ ተሰልፎ ፡ ይኸውም ፡ አልበቃ ፡ ብሎት ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ዠርባ ፡ ላይ ፡ ተደጋግፎ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ፡ በሰልፉ ፡ መካከልም ፡ እየተመላለሰ ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ መቃረብ ፡ በሚያጐላ ፡ ድምፅ ፡ የሚናገር ፡ ራዲዮ ፡ ግራማፎን ፡ ነበር ። ግርማዊነታቸው ፡ እመካከል ፡ ከጄኔራል ፡ ፕላት ፡ ጋራ ፡ በትልቅ ፡ አቶሞቢል ፡ ተቀምጠው ፡ ሙዚቃ ፡ እየተነፋ ፡ በፈረሰኛና ፡ በእግረኛ ፡ ወታደር ፡ ታጅበው ፡ በየደረሱበት ፡ የተዠመረው ፡ ጭብጨባና ፡ እልልታ ፡ እየተቀጣጠለ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ይዘልቅ ፡ ነበር ።

የለበሱት ፡ የወታደር ፡ ልብስ ፡ ነው ። መልካቸውም ፡ በረሓ ፡ የመታው ፡ መልክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በግልጥ ፡ ያስታውቃል ። አቶሞቢሉ ፡ የእግር ፡ እርምጃ ፡ ያኸል ፡ እያዘገመ ፥ ጃንሆይም ፡ ሕዝባቸውን ፡ የናፈቁበትን ፡ ዐይናቸውን ፡ በያንዳንዱ ፡ ሰልፈኛ ፡ ላይ ፡ እየጣሉት ፡ ሲያልፉ ፡ ናፋቂው ፡ ሕዝባቸውም ፡ እያያቸው ፡ የደስታ ፡ ለቅሶ ፡ አለቀሰ ፥ ሴቶቹም ፡ እጃቸውን ፡ እያርገበገቡ ፡ መሬት ፡ ይስሙ ፡ ነበር ።

ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እንደዚያ ፡ የመሰለ ፡ ደስታ ፡ ይመለስለታል ፡ ተብሎ ፡ አይታሰብም ። 5 ፡ ዓመት ፡ የተጐዳውን ፡ ጕዳት ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ ዐይኑ ፡ ተካሰ ።

የኢጣሊያ ፡ መንግሥትም ፡ 45 ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በምኞትና ፡ ባሳብ ፡ ከተቀጠቀጠ ፡ በኋላ ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ ኣሳቡንና ፡ ምኞቱን ፡ አጣ ።


ልዑል ፡ ኣልጋ ፡ ወራሽ ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ገብተው ፡ ትልቁን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ ከተከሉ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ታሪካዊ ፡ ዲስኩራቸውን ፡ ተናገሩ።

«የሰማይ ፡ መላእክት ፡ የምድር ፡ ሠራዊት ፡ ሊያስቡትና ፡ ሊያውቁት ፡ ይቻላቸው ፡ ባልነበረ ፡ በዚህ ፡ በዛሬ ፡ ቀን ፡ ቸር ፡ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችሁ ፡ ለመገኘት ፡ ስላበቃኝ ፡ በሰው ፡ አፍ ፡ የሚነገር ፡ ምስጋና ፡ የሚበቃ ፡ አይደለም ። ከማናቸውም ፡ አስቀድሞ ፡ ለሁላችሁ ፡ ልነግራችሁና ፡ ልትረዱ ፡ የምፈልገው ፡ ይህ ፡ ቀን ፡ ላዲሲቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያዲስ ፡ ታሪክ ፡ ዘመን ፡ መክፈቻ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ባዲስ ፡ ዘመን ፡ ሁላችን ፡ መፈጸም ፡ ያለብን ፡ አዲስ ፡ ሥራ ፡ ይዠመራል ።

በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ የደረሰባትን ፡ መከራ ፡ ለማስታወስ ፡ ስንፈልግ ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘውን ፡ ታሪኳን ፡ ብቻ ፡ ባጭር ፡ እንናገራለን ፡ ከብዙ ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ ነፃነቷን ፡ ጠብቃ ፡ የምትኖር ፡ ኢትዮዮጵያ ፡ ኢጣሊያ ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ በነበራት ፡ አጥቂነት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ ለማጥፋት ፡ ስለ ፡ ተነሣች ፡ ባ1888 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በዐድዋ ፡ ላይ ፡ ዥግኖቿ ፡ ጦርነት ፡ አድርገው ፡ ነፃነቷን ፡ አዳነች ። በዐድዋ ፡ ላይ ፡ ለተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ የውጫሌ ፡ ውል ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግንከዚያ ፡ በፊት ፡ ኣትየጵያን ፡ ለመግዛት ፡ አጣሊያ ፡ የነበራት ፡ ያላቋረጠ ፡ ምኞት ፡ ሲጠብቅ ፡ የነበረውን ፡ ምክንያት ፡ ያገኘ ፡ መስሎት ፡ ነበር ። አጣሊያ ፡ በዐድዋ ፡ ድል ፡ ከሆነች ፡ በኋላ ፡ እውነት ፡ ለምን ፡ ድል ፡ አደረገኝ ፡ በማለት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ባፍ ፡ ወዳጅ ፡ መስላ ፡ ስታዘጋጀው ፡ የነበረውን ፡ ምንም ፡ የኤውሮፓ ፡ ያለፈው ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ቢያቋርጣት ፡ ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ ገለጠጭ

አጣሊያ ፡ በአትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ያጥቂነት ፡ ጦርነት ፡ ባደረገች ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ተወዳዳሪ ፡ ኣለመሆናችንን ፡ ብናውቀው ፡ በግፍ ፡ አገራችንን ፡ ለመንጠቅ ፡ የመጣብንን ፡ ጠላት ፡ መከላከል ፡ የተገባን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በነበረን ፡ ዐቅም ፡ ተከላክለን ፡ የዓለም ፡ ሕግ ፡ በከለከለውም ፡ መሣሪያ ፡ በጋዝ ፡ ጪስ ፡ ሕዝባችንን ፡ የምትጨርስብን ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ለማሰማትና ፡ ፍርድ ፡ ለመቀበል ፡ ሄድን ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ኢጣሊያ ፡ ያነሣችው ፡ ጠብ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ የሚዘረጋ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዓለምን ፡ አሁን ፡ ከደረሰበት ፡ ጥፋት ፡ ለማዳን ፡ ለመንግሥት ፡ መሪነት ፡ አላፊነት ፡ የተቀበሉ ፡ ሁሉ ፡ የሚጣጣሩበት ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ይህ ፡ እሳት ፡ እንዳይቃጠል ፡ በዓለም ፡ ስምምነት ፡ እንዲገኝ ፡ ሲደክሙበት ፡ ቈዩ ። በዚያም ፡ ዘመን ፡ የልብ ፡ ወዳጃችን ፡ የሆነችው ፡ ታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ በመልካም ፡ ወዳጅነት ፡ ተቀብላን ፡ ቈየች ። በዚያም ፡ ያለፍርድና ፡ ያለርኅራኄ ፡ በከንቱ ፡ ደማቸው ፡ በኢጣሊያ ፡ እጅ ፡ የሚፈሰውን ፡ ያገሬን ፡ ሰዎችና ፡ በከንቱ ፡ የሚቃጠሉትን ፡ አድባራትና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በሰው ፡ አገር ፡ ተሰደው ፡ ባገራቸውም ፡ ላይ ፡ በዱር ፡ በገደልና ፡ በጫካ ፡ መከራና ፡ ሥቃይ ፡ ያዩ ፡ የነበሩትን ፡ ባሳብ ፡ ሳንለያቸው ፡ በሥራ ፡ ቈየን ።



ልዑል ፡ መኰንን።

ኣቤቶ ፡ ሁን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፡ የሐረር ፡ ዱክ ።

በነዚህ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ኢጣሊያ ፡ በጭካኔ ፡ የፈጃቸው ፡ ወጣቶችና ፡ ሴቶች ፡ ካህናትና ፡ መነኰሳት ፡ ስንት ፡ ናቸው? ባ1929 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የየካቲት ፡ ሚካኤል ፡ ዕለት ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ብቻ ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ በ3 ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ማለቃቸውን ፡ ታውቁታላችሁ ። በአካፋና ፡ በዶማ ፥ በምሣርና ፡ በመዶሻ ፡ የተፈለጡት ፡ በሳንጃ ፡ የተወጉት ፥ በዱላና ፡ በደንጊያ ፡ የተወገሩት ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡ ከሕፃናት ፡ ልጆቻቸው ፡ ጋራ ፡ በእሳት ፡ የተቃጠሉት ፡ ታስረውም ፡ በረኃብና ፡ በውሃ ፡ ጥም ፡ ያለቁት ፡ ደማቸውና ፡ ዐጥንታቸው ፡ አቤቱታውን ፡ ሲያቀርብ ፡ ቈየ ። ይህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ የአረመኔና ፡ የጨካኝነት ፡ ሥራ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የባሰውን ፡ በቀሩቱ ፡ በሌሎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ሲሠራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ማንም ፡ የሚያውቀው ፡ ነው ። ተይዞ ፡ ያልተደበደበ ፡ ያልተረገጠና ፡ ያልተዋረደ ፡ ያልታሰረ ፡ አይገኝም።

አሁን ፡ በፊታችን ፡ ወዳለው ፡ ወዳዲሱ ፡ ታሪክ ፡ እንተላለፋለን ። የዛሬ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ልክ ፡ በዛሬዪቱ ፡ ቀን ፡ የፋሺስት ፡ ወታደር ፡ ከዋናው ፡ ከተማችን ፡ ገባ ። ቀጥሎም ፡ ሙሶሊኒ ፡ በኛ ፡ አገር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሮማን ፡ ኣምፒር ፡ አቁሜአለሁ ፡ ብሎ ፡ ለዓለም ፡ አስታወቀ ። አቀናሁላችሁ ፡ ብሎ ፡ ያስታወቀውም ፡ አገር ፡ ለዘለዓለም ፡ በእጁ ፡ የሚኖር ፡ መስሎት ፡ አምኖ ፡ ነበር ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዠግንነት ፡ በታሪክ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለሕዝባችን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የዘመኑን ፡ መሣሪያ ፡ የምናገባበት ፡ ጠረፍ ፡ ባለመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ ለማግኘት ፡ ሳይቻለን ፡ ቀረ ። ሙሶሊኒ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ 52 ፡ መንግሥታት ፡ ፈረዱበት። ርሱ ፡ ግን ፡ ይህነን ፡ የግፍ ፡ ሥራውን ፡ ተመካበት ፡ እንጂ ፡ ፍርዳቸውን ፡ ከምንም ፡ አልቈጠረም ። ያለፉት ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ለናንተ ፡ ለሕዝቦቼ ፡ የጨለማ ፡ ጊዜያቶች ፡ ነበሩ ። እናንተ ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ ሳትቈርጡ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እየዠመራችሁ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኰረብቶች ፡ ላይ ፡ ተሠማራችሁ።

በነዚህ ፡ ባምስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ እናንተ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ማናቸውንም ፡ መከራና ፡ ጭንቀት ፡ ችላችሁ ፡ነፃነታችሁን ፡ ጠብቃችሁ ፡ ወደ ፡ ተሠማራችሁባቸው ፡ ተራሮች ፡ ለመምጣት ፡ ጠላታችን ፡ ከቶ ፡ ሊደፍር ፡ አልቻለም ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ሀገሩን ፡ ለማቅናት ፡ ባይችል ፡ የያዘውን ፡ አሠለጥናለሁ ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ሚሊዮን ፡ ሊሬ ፡ አፈሰሰ ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ማውጣቱ ፡ የተጠቃውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ሁኔታ ፡ ከፍ ፡ ለማድረግና ፡ ወይም ፡ የሠራውን ፡ ግፍ ፡ ለማሻሻል ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ በቅድስት ፡ አገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፋሺስት ፡ ኮሎኒ ፡ ለማቆም ፡ እሱ ፡ እንዳሰበው ፡ ያለ ፡ የጭካኔ ፡ ኣገዛዝ ፡ ለመትከል ፡ ነበር ። የኢትዮጵያን ፡ ዘር ፡ ለመጨረስ ፡ ተጣጣረ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ላንድ ፡ ነፃ ፡ መንግሥት ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ቢሆን ፡ የማንዳ ፡ ወይም ፡ የፕሮቴክተራ ፡ አስተዳደር ፡ እንኳ ፡ አላሰበላትም ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚቈጠር ፡ ገንዘብና ፡ የተዘጋጀው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ ሙሶሊኒ ፡ ላሰበው ፡ መንገድ ፡ መዋሉ ፡ ቀርቶ ፡ በፍጹም ፡ ላላሰበው ፡ ጉዳይ ፡ ሆነ ። ኢጣሊያ ፡ ድል ፡ ከሆነችው ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ላይ ፡ የተቻላትን ፡ ያኸል

፡ ለመንጠቅ ፡ አስባ ፡ ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ መቁረጧን ፡ በገለጠች ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያጓዘችው ፡ ሰው ፡ የላከችው ፡ ገንዘብና ፡ መሣሪያ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ነበር ። የሰበሰበችውም ፡ ደንበኛ ፡ ጦር ፡ ቍጥሩ ፡ ከ200 ፡ ሺህ ፡ አያንስም ። የተከበብሁም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብላ ፡ የብዙ ፡ ዓመት ፡ ሥንቅ ፡ ኣከማችታ ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ ባዘጋጀችው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በመተማመን ፡ ማንም ፡ ሊያሸንፈኝ ፡ አይችልም ፡ ብላ ፡ ስለ ፡ ተመካች ፡ የፋሺስት ፡ መንግሥት ፡ የቶታሊታሪያን ፡ አገዛዝ ፡ ባገራችን ፡ ውስጥ ፡ ለመትከል ፡ ዝምሮ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የፋሺስት ፡ መንግሥት ፡ ያላሰበው ፡ ነገር ፡ መጣ። ለዛሬው ፡ ዘመን ፡ ጦርነትና ፡ ዋና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ የተዋጊነት ፡ መንፈስ ፡ በናንተ ፡ ተገለጠ ።

ዝግንነትና ፡ ርኅራኄ ፡ ያለው ፡ ያንድ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ከመሆናችሁ ፡ ጋራ ፡ ርስ ፡ በርሳችሁ ፡ በመረዳዳታችሁና ፡ የጦር ፡ ዐቅድ ፡ በማወቃችሁ ፡ በመሣሪያና ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ከናንተ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ጠላት ፡ ለማጥፋት ፡ በቃችሁ ።

ለሰው ፡ ልጅ ፡ የነፃነት ፡ መብት ፡ ሲሉ ፡ በሌላ ፡ ክፍል ፡ ይዋጉ ፡ የነበሩት ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደሮች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመርዳትና ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ እስቲዘጋጁና ፡ እስቲታጠቁ ፡ ድረስ ፡ ጊዜ ፡ አስፈልጓቸው ፡ ነበር ። የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ግን ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ መገናኛ ፡ መንገዱን ፡ እየቈረጣችሁ ፡ ጠላታችንን ፡ እያስጨነቃችሁ ፡ ከየምሽጉ ፡ እንዳይወጣ ፡ አደረጋችሁት ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የተማመነበት ፡ ወታደር ፡ ቍጥሩ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ቢሆን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እሱንና ፡ አገዛዙን ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ እንደ ፡ ጠላው ፡ በቶሎ ፡ ተረድቶ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ አገርና ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ መኖር ፡ የማይቻለው ፡ መሆኑ ፡ ታወቀው ። እንደ ፡ ልማዱም ፡ የመርዝ ፡ ጋዝ ፡ ቦምቡን ፡ እየጣለ ፡ ያረመኔነትና ፡ የጭከና ፡ ሥራውን ፡ እየሠራ ፡ ውስጡ ፡ በመነመነ ፡ በላይነት ፡ እኖራለሁ ፡ ብሎ ፡ ለማሰብ ፡ የማይቻል ፡ ሆነበት ። በያለበት ፡ ከቦ ፡ የያዘው ፡ ወታደር ፡ ከርሱ ፡ የበለጠ ፡ ኀይለኛ ፡ ባለጋራ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳው ። ይህነንም ፡ ባለጋራውን ፡ ለመግጠም ፡ ያችኑ ፡ ተርፋ ፡ የነበረችውን ፡ ድፍረትና ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የምጠጋበት ፡ ደኅና ፡ ቦታ ፡ አገኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማለት ፡ ሞከረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንድም ፡ የሚጠጋበት ፡ ቦታ ፡ አላገኘም ።

ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ረዳታችን ፡ ታላቁ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጠላታችንን ፡ በሚገባ ፡ ለመውጋት ፡ ተደራጀ ። እኔም ፡ ይህን ፡ እንዳወቅሁ ፡ ወታደሮቼን ፡ ይዤ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ከሚዋሰነን ፡ ሩቅ ፡ ከሆነው ፡ አገር ፡ ከሱዳን ፡ ተነሥቼ ፡ ወደ ፡ ማኸል ፡ ጐጃም ፡ ገባሁ ። ጠላታችን ፡ በጐጃም ፡ መሬት ፡ ብርቱ ፡ ምሽጎችና ፡ ኀይለኞች ፡ ወታደሮች ፡ አይሮፕላኖችና ፡ መድፎችም ፡ ነበሩት ። የኛንና ፡ የጠላታችንን ፡ ወታደሮች ፡ ቍጥር ፡ ስንገምተው ፡ የብልጫው ፡ ከፍተኛነት ፡ የኛ ፡ 1 ፡ የርሱ ፡ 20 ፡ ይሆን ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ፈቃዳችን ፡ የምናዝበት ፡ መድፍና ፡ አይሮፕላን ፡ አልነበረንም ። የኔ ፡ ባርበኞቼ ፡ መካከል ፡ መገናኘት ፡ ብቻ ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳበ ። የጠላታችንም ፡ ፍርሀቱና ፡ መጨነቁ

፡ በዚያ ፡ መጠን ፡ እየበዛ ፡ ሄደ ። ወታደሮቼ ፡ እየገሠገሡ ፡ የጠላታችንን ፡ መገናኛ ፡ መንገድ ፡ እየቈረጡ ፡ ወታደሮቹንም ፡ እያባረሩ ፡ ከዓባይ ፡ ወዲያ ፡ ማዶ ፡ አሻግረው ፡ ወደ ፡ ሸዋና ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ሲከታተሉት ፡ ሳሉ ፡ የእንግሊዝ ፡ እምፔሪያል ፡ ወታደሮች ፡ ማንም ፡ ሊተካከለው ፡ በማይቻል ፡ ሁኔታ ፡ እየገሠገሡ ፡ ዋና ፡ ከተማችንን ፡ መያዛቸውንና ፡ በስተሰሜን ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ደሴ ፡ በስተደቡብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ጅማ ፡ የመግፋታቸውን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ወሬ ፡ ሰማሁ ። እንደዚሁም ፡ ከሱዳን ፡ የዘመቱት ፡ ወታደሮች ፡ እጅግ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ኀይል ፡ የከረንን ፡ ምሽግ ፡ አፍርሰው ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ በፍጹም ፡ ድል ፡ አደረጉት ። እኔም ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ከተማዬ ፡ የምገባበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ጠላታችንን ፡ ለማባረር ፡ በየቦታው ፡ ተበታትነው ፡ የነበሩትን ፡ ወታደሮቼን ፡ ሰብስቤ ፡ ዛሬ ፡ በዋናው ፡ ከተማዬ ፡ ተገኘሁ ፡ ወታደሮቼን ፡ እየመራሁ ፡ በመንገዴ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ጠላት ፡ ድል ፡ እየሆነ ፡ እስከዚህ ፡ በመድረሴና ፡ የጋራ ፡ ጠላታችንን ፡ ኀይል ፡ በመስበሬ ፡ ደስታዬ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ይመነጫል ። የፋሺስት ፡ መንግሥት ፡ ጥሎት ፡ በሸሸው ፡ ቤተ ፡ መንግሥቴ ፡ ውስጥ ፡ ዛሬ ፡ በመካከላችሁ ፡ በመገኘቴ ፡ ሁሉን ፡ ቻይ ፡ ለሆነ ፡ አምላክ ፡ የማቀርብለት ፡ የልቤ ፡ ምስጋና ፡ ሊወሰን ፡ አይቻልም ።

## የሀገሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ።

ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘርግታ ፡ እልል ፡ እያለች ፡ ምስጋናዋን ፡ የምታቀርብበት ፡ ደስታዋን ፡ ለልጆቿ ፡ የምትገልጽበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ ከባድ ፡ የመከራ ፡ ቀንበርና ፡ ከዘለዓለም ፡ ባርነት ፡ ነፃ ፡ የወጡበት ፡ ቀንና ፡ እኛም ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ተለይተነው ፡ ከነበርነው ፡ ከምንወደውና ፡ ከምናፈቅረው ፡ ሕዝባችን ፡ ጋራ ፡ ለመቀላቀል ፡ የበቃንበት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ቀን ፡ የተከበረና ፡ የተቀደሰ ፡ በያመቱም ፡ ታላቁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ በዓል ፡ የሚውልበት ፡ ነው ። በዚህም ፡ ቀን ፡ ለሚወዷት ፡ ላገራቸው ፡ ነፃነት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥታቸውና ፡ ለሰንደቅ ፡ ዐላማቸው ፡ ክብር ፡ ካባቶቻቸው ፡ የተላለፈውን ፡ ጥብቅ ፡ አደራ ፡ አናስወስድም ፡ በማለት ፡ መሥዋዕት ፡ ሆነው ፡ ደማቸውን ፡ ያፈሰሱትን ፡ ዐጥንታቸውን ፡ የከሰከሱትን ፡ ግኖቻችንን ፡ እናስታውሳለን ። ለዚህም ፡ ለግኖቻችን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ምስክር ፡ ይሆናል ።

ባለፉት ፡ አምስቱ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ ተነግረውና ፡ ተቈጥረው ፡ የማያልቁ ፡ ያገኘናቸው ፡ መከራና ፡ ሥቃይ ፡ ትምህርት ፡ ሆነውን ፡ ሠራተኛነት ፡ አንድነት ፡ ኅብረትና ፡ ፍቅር ፡ በልባችሁ ፡ ተጽፈው ፡ ለምናስበው ፡ ለኢትዮጵያ ። ጕዳይ ፡ ረዳቶች ፡ ለመሆን ፡ ዋና ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጣችሁ ፡ ነው። ባዲሷ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከእንግዴህ ፡ ወዲያ ፡ የማትነጣጠሉ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ትክክልነትና ፡ ነፃነት ፡ ያላችሁ ፡ ሕዝቦች ፡ እንድትሆኑ ፡ እንፈልጋለን ።



ግርማዊነታቸው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገብተው ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡
መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ አላማ ፡ ሲሰቅሉ።

አገር ፡ የሚለማበትን ፡ ሕዝብ ፡ የሚበለጽግበትን ፡ እርሻ ፡ ንግድ ፡ ትምህርትና ፡ ጥበብ ፡ የሚሰፋበትን ፡ የሕዝባችን ፡ ሕይወቱና ፡ ሀብቱ ፡ የሚጠበቅበትን ፡ ያገር ፡ አስተዳደርም ፡ ባዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ ተለውጦ ፡ ፍጹም ፡ የሚሆንበትን ፡ ይህን ፡ ለመሰለው ፡ ለምንደከምበት ፡ ሥራ ፡ አብሮ ፡ ደካሚ ፡ መሆን ፡ አለባችሁ ።

ይህን ፡ እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ የሠራልንን ፡ ሥራ ፡ መዠመሪያ ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ረዳታችን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ያደረገልንን ፡ ውለታ ፡ ለመመለስ ፡ እምፔሪያል ፡ ትሩፕ ፡ የተባሉት ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ተዛውረው ፡ የጋራ ፡ ጠላታችንን ፡ ለማጥቃት ፡ እንዲችሉ ፡ ማድረግና ፡ በጦር ፡ ሠራዊትም ፡ እንድናግዝ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በመርዳት ፡ ሁለተኛም ፡ በሀገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚያስከብርና ፡ የሚጠብቅ ፡ መንግሥት ፡ በማቋቋም ፡ የሕዝብና ፡ የኅሊና ፡ ነፃነት ፡ በመፍቀድ ፡ ለሕዝብና ፡ ለሀገር ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ብርቱ ፡ ምኞታችንና ፡ አሳባችን ፡ ነው ።

አሁን ፡ በመጨረሻ ፡ ለናንተ ፡ ለሕዝቤ ፡ የማስታውቃችሁ ፡ ዛሬ ፡ የሁላችን ፡ የደስታ ፡ ቀን ፡ መሆኑን ፡ ነው ፡ ዛሬ ፡ ጠላታችንን ፡ ድል ፡ የመታንበት ፡ ቀን ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በሙሉ ፡ ልባችን ፡ ሁላችን ፡ ደስ ፡ ይበለን ፡ ስንል ፡ ደስታችን ፡ በክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ አይሁን ። ለክፉ ፡ ክፉ ፡ አትመልሱ ፥ ጠላት ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ልማድ ፡ እስከዚህ ፡ መጨረሻ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ ያለ ፡ የጭካኔና ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ ። ለጠላታችን ፡ መውቀሻ ፡ በሚሆነው ፡ ነገር ፡ የኢትዮጵያን ፡ መልካም ፡ ስም ፡ እንዳታሳድፉ ፡ ተጠንቀቅ ። ጠላቶቻችን ፡ በእጃቸው ፡ ያለውን ፡ መሣሪያ ፡ እንዲያስረክቡና ፡ በመጡበቱ ፡ መንገድ ፡ ተመልሰው ፡ እንዲሄዱ ፡ እናደርጋለን ። ደራጐንን ፡ የገደለ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የኛም ፡ የባለቃል ፡ ኪዳን ፡ ረዳታችንም ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ባልደረባ ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ አዲስ ፡ የተነሣውን ፡ ሰውን ፡ ልጆች ፡ የሚያስጨንቀውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማያምን ፡ ጨካኝ ፡ ዘንዶ ፡ ለመቃወም ፡ እንድንችል ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖር ፡ ወዳጅነትና ፡ ዝምድና ፡ ከባለቃል ፡ ኪዳን ፡ ረዳታችን ፡ ጋራ ፡ እንተሳሰር ፡ እነሱንም ፡ እንደ ፡ ዘመድና ፡ ወዳጅ ፡ ተመልከታችሁ ፡ ደግነትና ፡ ቸርነት ፡ እንድታሳዩዋቸው ፡ አደራ ፡ እላችኋለሁ» ።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ተክለጻድቅ ፡ መኩሪያ ፡ ባ፲፱፻፯ ፡ ዓ.ም ፡ በተጉለትና ፡ ቡልጋ ፡ አውራጃ ፡ አሳግርት ፡ ልዩ ፡ ስሙ ፡ ሣር ፡ አምባ ፡ በተባለ ፡ ሥፍራ ፡ ተወለዱ። ዕድሜያቸው ፡ ለትምህርት ፡ ሲደርስ ፡ መዠመሪያ ፡ ካባታቸውና ፡ ቀጥሎም ፡ ባጥቢያቸው ፡ ባህላዊውን ፡ ትምህርት ፡ እስከ ፡ ቅኔ ፡ ያለውን ፡ ቀስመዋል።

ከዚያም ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ አሊያንስ ፡ ፍራንሴዝና ፡ ከተፈሪ ፡ መኮንን ፡ ት/ቤት ፡ ገብተው ፡ የጊዜውን ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ አጠናቀቅዋል።

ኢጣሊያ ፡ አገራችንን ፡ የወረረች ፡ ጊዜም ፡ በየካቲት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ.ም. ፡ ፍጅት ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ ሶማሊያ ፡ ደናኔ ፡ ተግዘው ፡ ለሦስት ፡ ዓመታት ፡ ታሥረዋል።

ከነጻነትም ፡ መልስ ፡ አገራቸውን ፡ በተለያዩ ፡ የኃላፊነት ፡ ደረጃዎች ፡ አገልግለዋል። መዠመሪያ ፡ ተቀጥረው ፡ ያገለገሉት ፡ በትምህርትና ፡ ሥነጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነበር። እዚያም ፡ እያሉ ፡ ባነራችን ፡ ሰው ፡ የተጻፈ ፡ የአገራችን ፡ ታሪክ ፡ አንድም ፡ ባለመኖሩ ፡ በቁጭትና ፡ በመቆርቆር ፡ ነበር ፡ 'መጻፍ ፡ አለብኝ' ፡ ብለው ፡ በደንብ ፡ ከሚታወቀው ፡ ከቅርቡ ፡ ጊዜ ፡ በቅጡ ፡ ወደማይታወቀው ፡ የሩቁ ፡ ዘመን ፡ መጣፍ ፡ የዠመሩት። ፡ የመዠመሪያውን ፡ መጽሐፍ ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ቀ.ኃ.ሥ." ፡ ባ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ.ም. ፡ አሳተሙ። ከጫፍ ፡ እስከጫፍ ፡ ጽፈው ፡ የመጨረሻውን ፡ መጣፍ ፡ የታሪካችን ፡ መዠመሪያ ፡ የሚኾነውን ፡ የኢትዮጵየ ፡ ታሪክ ፡ ኑብያ - አክሱም - ዛጉዬ ፡ እስከ ፡ ዐፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመነ - መንግሥት ፡ የሚለውን ፡ ባ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ.ም. ፡ አቅርበዋል። እንህኑ ፡ መጻሕፍት ፡ ትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ታሪክ ፡ ለማስተማሪያ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ተጠቅሞባቸዋል።

ተክለጻድቅ ፡ ከታሪክ ፡ ውጭ ፡ የጻፉዋቸው ፡ "የሰው ፡ ጠባይና ፡ ዐብሮ ፡ የመኖር ፡ ዘዴና ፡ በሚዮቶሎዢያ ፡ ላይ ፡ ያተኮረ ፡ ከጣዖት ፡ አምልኮ ፡ እስከ ፡ ክርስትና" ፡ የሚሉም ፡ መጣፎች ፡ አሏቸው።

ተክለተድቅ ፡ በምድር ፡ ባቡር ፡ በዋና ፡ ጸሐፊነት ፡ በቤተመጽሐፍት ፡ ወመዘክር ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅነት፤ እንዲሁም ፡ በፈረንሣይ፣ በእስራኤል፣ በዩጎዝላቪያ ፡ በዲፕሎማሲ ፡ ሥራ ፡ በመጨረሻም ፡ የትምህርትና ፡ የባህል ፡ ሚኒስትር ፡ ኾነው ፡ አግልግለዋል። በፈቃዳቸው ፡

ጡረታ ፡ ከወጡም ፡ በኋላ ፡ በምርምር ፡ የታገኑ ፡ ሦስት ፡ ታላላቅ ፡ የታሪክ ፡ ሥራዎችን ፡ አቅርበዋል።

ተክለጻድቅ ፡ ከረዥም ፡ ያገልግሎት ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በተወለዱ ፡ በ፹፯ ፡ ዓመታቸው ፡ ሐምሌ ፡ ፲፯ቀን ፡ ባ፲፱፻፺፪ ፡ ዓ.ም. ፡ ዐርፈዋል።

## የደራሲው ሥራዎች

1. የግራኝ አሕመድ ወረራ (**ታሪክ**)
2. ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት (**ታሪክ**)
3. ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት (**ታሪክ**)
4. ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት (**ታሪክ**)
5. የኢትዮጵያ ታሪክ - ኑቢያ [ሜርዌ - ናፓታ] (**ታሪክ**)
6. የኢትዮጵያ ታሪክ - ኑብያ-አክሱም ዛጕዬ እስከ ዐፄ ይኩኖ አምላክ (፩ኛ መጽሐፍ) (**ታሪክ**)
7. የኢትዮጵያ ታሪክ - ከዐፄ ይኵኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል (፪ተኛ መጽሐፍ) (**ታሪክ**)
8. የኢትዮጵያ ታሪክ - ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ (፫ተኛ መጽሐፍ) (**ታሪክ**)
9. የኢትዮጵያ ታሪክ - ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (፬ተኛ መጽሐፍ) (**ታሪክ**)
10. ጥንታዊት ኢትዮጵያና ግብፅ (**ታሪክ**)
11. ከጣኦት አምልኮ እስከ ክርስትና (**ታሪክ**)
12. የሕይወቴ ታሪክ (**ታሪክ**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY